# መርሐ ሕይወት

## ሦስተኛው መጽሐፍ

አዘጋጅቶ ያቀረበው

ዓሥራት ገብረ ማርያም

1993 ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

«ሰው የሚኖረው እግዚአብሔር በሚናገረው ቃል ሁሉ እንጂ
በእንጀራ ብቻ አይደለም።»
(ዘዳ. 8፥3)



ዓሥራት ገብረ ማርያም

«የምሥራቹን ቃል ማብሠር ግዴታዬ ስለሆነ የምመካበት ነገር አይደለም፤
እንዲያውም የምሥራቹን ቃል ሳላበሥር ብቀር ወዮልኝ።»
(1ኛ. ቆሮ. 9፥16)

# ዘጠነኛ ክፍል

ገጽ


ምዕራፍ 1:- ትምህርተ ሃይማኖት........ 10
የእግዚአብሔር ክብር........ 10
በጌታ ተአምራት........ 13
በሕማማቱና በሞቱ........ 13
በዳግም ምጽአቱ........ 13
በሰዎች ተግባር........ 13
አብ ወልድን፥ ወልድ ደግሞ አብን ያከብራል........ 13
እግዚአብሔር የክብር ጌታ ነው........ 13
ሁሉም ለእግዚአብሔር ክብር መስጠት አለበት........ 14
እግዚአብሔር ለክብሩ ቀናተኛ ነው........ 14
የእግዚአብሔር መጠሪያዎች........ 14
የመንፈሳውያን በዓላት አከባበርና የዘመን አቈጣጠር........ 15
የበዓላት አከባበር........ 15
የዘመን አቈጣጠር........ 16
ክፍለ ዓመት በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት........ 16
ቅዳሜ ስዑር........ 18
የንግሥ በዓል........ 20
አሥርቆት (ማሥረቅ)........ 22
የዘመን አቈጣጠር ስሌት........ 23
የግብጾች የአቈጣጠር ስሌት........ 26
ጥያቄዎች........ 29
ምዕራፍ 2:- መጽሐፍ ቅዱስ........ 30
ብሉይ ኪዳን........ 30
1ኛ. መጽሐፈ ሳሙኤል........ 30
2ኛ. መጽሐፈ ሳሙኤል........ 32
1ኛ. መጽሐፈ ነገሥት........ 33
2ኛ. መጽሐፈ ነገሥት........ 35
ሐዲስ ኪዳን........ 37
1ኛ. ተሰሎንቄ........ 37
2ኛ. ተሰሎንቄ........ 38
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት........ 38
ጥያቄዎች........ 40
ምዕራፍ 3:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ........ 42
የጌታችን ትምህርት........ 42
በታላቅ ክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ........ 42
በቤተ መቅደስ የሚገበያዩትን ማስወጣቱ........ 43
ጌታችንን ሽቶ የቀባች ሴት........ 43
የጌታችን ተአምራት........ 43
ያለ ፍሬ የተገኘች የበለስ ዛፍ........ 43
ርኩስ መንፈስ ያደረበት ሰው መፈወስ........ 43
የጌታችን ምሳሌዎች........ 43


www.ethiopianorthodox.org

ገጽ


43
የማታፈራ የበለስ ዛፍ........ 44
የአገልጋይ ግዳጅ........ 44
የደጉ ሳምራዊ ምሳሌ........ 44
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት........ 48
ጥያቄዎች........ 50
ምዕራፍ 4:- ቤተ ክርስቲያን........ 50
የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር........ 51
የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን........ 51
ቅዱስ ድሜጥሮስ........ 52
ቅዱስ ጎርጎርዮስ፥ ነባቤ መለኮት........ 53
ቅዱስ መርቆርዮስ፥ ባለ ሁለት ሰይፉ........ 54
ቅዱስ ያሬድ........ 55
ኢትዮጵያዊው ጻድቅ፥ አቡነ ተክለ ሃይማኖት........ 56
የቤተ ክርስቲያን ዜማ........ 57
ጥያቄዎች........ 59
ምዕራፍ 5:- መንፈሳዊነትና ግብረ ገብነት........ 59
የክርስቲያናዊ ሕይወት መመሪያ........ 59
ጥላቻ ወይም ፍትወት ሳይሆን ንጹሕ ፍቅር........ 59
ሰውን ማሳዘን ሳይሆን ሰውን ማጽናናት........ 60
ቍጣ ሳይሆን ፈገግታ........ 60
ጭካኔ ሳይሆን ርኅራኄ........ 61
ጥረት ካደረጉ በኋላ ለአምላክ መተው እንጂ አለመጨነቅ........ 61
ንቱግነት ሳይሆን ለጋስነት ወይም ቸርነት........ 62
የግዴለሽነት ንግግር ሳይሆን ለሰው ስሜት መጠንቀቅ........ 62
ራስ ወዳድነት ሳይሆን ለሌላም ሰው ማሰብ........ 63
ለጥያቄ መልስ ለመስጠት ካልሆነ በቀር ከክርክር መራቅ........ 63
ከሐሜት መራቅ........ 64
ግዴታን አክብሮ መወጣት........ 65
ጥያቄዎች........ 67
ዐሥረኛ ክፍል........ 67
ምዕራፍ 1:- ትምህርተ ሃማኖት........ 67
የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን........ 67
ከኖኅ ጋር የገባው ቃል ኪዳን........ 68
ከአብርሃም ጋር የገባው ቃል ኪዳን........ 68
ከይስሐቅ ጋር የገባው ቃል ኪዳን........ 68
ከያዕቆብ ጋር የገባው ቃል ኪዳን........ 68
ለፊንሐስ የገባው ቃል ኪዳን........ 68
ከዳዊት ጋር የገባው ቃል ኪዳን........ 68
የእግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ታማኝነት........ 69
ጸሎተ ፍትሐት........ 70
ጸሎተ ፍትሐት ለሟቾች የሚያስገኘው ጥቅም........ 71
ጸሎተ ፍትሐት የሚደረገው ለማን ነው?........ 72
ጥያቄዎች........ 73
ምዕራፍ 2:- መጽሐፍ ቅዱስ........


ገጽ


ብሉይ ኪዳን........ 73
አንደኛ ዜና መዋዕል........ 73
ሁለተኛ ዜና መዋዕል........ 74
ትንቢተ ኢሳይያስ........ 77
ትንቢተ ኤርምያስ........ 79
ሰቆቃወ ኤርምያስ........ 80
ጥበበ ሰሎሞን........ 81
ሐዲስ ኪዳን........ 81
መጀመሪያ ወደ ጢሞቴዎስ የተላከ መልእክት........ 81
ሁለተኛ ወደ ጢሞቴዎስ የተላከ መልእክት........ 82
የያዕቆብ መልእክት........ 83
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት........ 83
ጥያቄዎች........ 88
ምዕራፍ 3:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ........ 90
የጌታችን ትምህርት........ 90
የዘብዴዎስ ልጆች እናት ልመና........ 90
ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው ተስፋ........ 90
ሕፃናትን መባረኩ........ 90
የጌታችን ተአምራት........ 91
የአንድ ዕውር መፈወስ........ 91
የአንድ ድዳ መፈወስ........ 91
የአንድ ለምጻም መፈወስ........ 91
የቤተ መቅደስን ግብር መክፈል........ 91
የጌታችን ምሳሌዎች........ 91
የበለስ ዛፍ ምሳሌነት........ 91
የሠርጉ ግብዣ ምሳሌ........ 91
የሦስቱ አገልጋዮች ምሳሌ........ 92
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት........ 92
ጥያቄዎች........ 98
ምዕራፍ 4:- ቤተ ክርስቲያን........ 100
ቤተ ክርስቲያንና ሲኖዶሶችዋ........ 100
የኒቅያ ጉባኤ........ 100
የቍስጥንጥንያ ጉባኤ........ 104
የኤፌሶን ጉባኤ........ 106
የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን........ 108
ቅዱስ ቄርሎስ........ 108
ቅዱስ ዲዮስቆሮስ........ 109
ቅዱስ ኤፍሬም........ 109
የቤተ ክርስቲያን ዜማ........ 110
ጥያቄዎች........ 113
ምዕራፍ 5:- መንፈሳዊነትና ግብረ ገብነት........ 114
ነጻነትን በአግባቡ መጠቀም........ 114
መብትንና ግዴታን ጠንቅቆ ማወቅ........ 115
እውነትን መናገር እንጂ መማል አለማስፈለጉ........ 116


www.ethiopianorthodox.org

ገጽ


.......... 117
ጥያቄዎች .......... 118
ዐሥራ አንደኛ ክፍል .......... 118
ምዕራፍ 1– ትምህርተ ሃይማኖት .......... 118
የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት .......... 118
መግቢያ .......... 118
ሦስትነትን የተቃወሙ ክሕደቶች .......... 118
1. የአርዮስ ክሕደት በአጭሩ .......... 119
2. አቡሊናርዮስ .......... 119
3. ሰባልዮስ .......... 119
4. መቅዶንዮስ .......... 120
በብሉይ ኪዳን የአንድነት እምነትና የሦስትነት ምልክቶች .......... 120
አንድነትና ሦስትነት በሐዲስ ኪዳን .......... 121
ሦስትነት በአንድነትና አንድነት በሦስትነት .......... 121
አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ .......... 121
እግዚአብሔር አብ .......... 122
እግዚአብሔር ወልድ .......... 122
እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ .......... 123
የቅዱሳን አባቶች ምስክርነት .......... 124
የሕፃናት ጥምቀት .......... 126
ጥያቄዎች .......... 127
ምዕራፍ 2:- መጽሐፍ ቅዱስ .......... 127
ብሉይ ኪዳን .......... 127
ትንቢተ ሕዝቅኤል .......... 129
ትንቢተ ሆሴዕ .......... 131
ትንቢተ ኢዩኤል .......... 131
ትንቢተ አሞጽ .......... 132
ትንቢተ አብድዩ .......... 133
ትንቢተ ሚክያስ .......... 133
ተረፈ ዳንኤል – ቤልና ዘንዶው .......... 134
ሐዲስ ኪዳን .......... 134
የመጀመሪያው የጴጥሮስ መልእክት .......... 135
ሁለተኛው የጴጥሮስ መልእክት .......... 136
የመጀመሪያው የዮሐንስ መልእክት .......... 136
ሁለተኛው የዮሐንስ መልእክት .......... 136
ሦስተኛው የዮሐንስ መልእክት .......... 136
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት .......... 139
ጥያቄዎች .......... 141
ምዕራፍ 3:- ጌታችን፥ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ .......... 141
የጌታችን ትምህርት .......... 141
ስለሚደርስበት ሕማምና ሞት .......... 141
የደቀ መዛሙርቱን እግር ማጠቡ .......... 142
የምሥጢረ ቍርባን ምሥረታ .......... 142
ጌቴሴማኒ .......... 14
የጌታችን መያዝ ..........


ገጽ


ወደ ፍርድ ሸንጎ መቅረቡ .......... 142
ጴጥሮስ ጌታችንን መካዱ .......... 143
ወደ ጲላጦስ ፊት ቀርቦ መመርመሩ .......... 143
የሞት ፍርድ እንደተፈረደበት .......... 144
ስቅለቱ .......... 144
ከጌታችን ጋር የተሰቀሉ ወንጀለኞች .......... 144
የጌታችን ሞት .......... 145
የጌታችን ተአምራት .......... 145
የቤተ ሳይዳው ሽባ .......... 145
የወታደሮች ወደ ኋላ መውደቅ .......... 146
የማልኮስ ጆሮ መፈወስ .......... 146
የጌታችን ምሳሌዎች .......... 146
ድኻዋ መበለትና ዐመፀኛው ዳኛ .......... 146
የጌታችን መልካም እረኛነት .......... 146
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት .......... 147
ጥያቄዎች .......... 155
ምዕራፍ 4:- ቤተ ክርስቲያን .......... 156
ሰባቱ አብያተ ክርስቲያን .......... 156
1. የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን .......... 156
2. የሰርምኔስ ቤተ ክርስቲያን .......... 156
3. የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን .......... 157
4. የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን .......... 157
5. የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን .......... 157
6. የፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን .......... 157
7. የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን .......... 157
የአንዳንድ ወገኖች ማንነት .......... 157
ፈሪሳውያን .......... 157
ሰዱቃውያን .......... 158
ጸሐፍት .......... 158
ኢሴኒያውያን .......... 158
ሽማግሌዎች .......... 159
የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን .......... 160
መጥምቁ ዮሐንስ .......... 160
ቅዱስ ጎርጎርዮስ (ገባሬ ተአምር) .......... 161
ቅዱስ ጎርጎርዮስ (የቅዱስ ባስልዮስ ወንድም) .......... 161
ዘጠኙ ቅዱሳን .......... 162
የቤተ ክርስቲያን የዜማ ጸሎት .......... 165
ጥያቄዎች .......... 168
ምዕራፍ 5:- መንፈሳዊነትና ግብረ ገብነት .......... 169
ተገቢ በሆነ መንገድ በችሎታ መጠቀም .......... 169
ሰውን እንደ ሰውነቱ ማየት .......... 170
ፈተና ሲያጋጥም በእግዚአብሔር መታመን .......... 171
ጥያቄዎች .......... 172
ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል .......... 173


www.ethiopianorthodox.org

ገጽ


173
ምዕራፍ 1:- ትምህርተ ሃይማኖት.......................................173
የእግዚአብሔር ህልውና.......................................173
የፍጥረቱ ሥነ ሥርዓታዊ አሠራር.......................................175
የኅሊና ምስክርነት.......................................175
በተፈጥሮ ዝንባሌ የዓለም ሕዝብ ስምምነት.......................................175
የቅዱሳት መጻሕፍትና የታሪክ ማስረጃዎች.......................................177
የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ክብር.......................................177
መግቢያ.......................................177
ነቢያት ለክርስቶስ አምላክነት መስክረዋል.......................................178
ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ክርስቶስ አምላክነት.......................................178
ብሉይ ኪዳን.......................................178
ሐዲስ ኪዳን.......................................178
በሁሉም ነገር ላይ የክርስቶስ ፍጹም ሥልጣን.......................................
1. ዘለዓለማዊ ሕይወትን በሚሰጠን.......................................178
በእግዚአብሔር ልጅ ማመን.......................................
2. እርሱ ሁሉን ነገር የሚሰጥና ኃጢአትን.......................................178
የሚያስተሰርይ አምላክ ነው.......................................179
በምሥጢረ ሥላሴ ውስጥ የክርስቶስ መለኮታዊ ክብር.......................................179
የክርስቶስ መለኮታዊ መጠሪያዎች.......................................181
የመከራከሪያ ጥቅሶችና መልሶቻቸው.......................................199
ጥያቄዎች.......................................199
ምዕራፍ 2:- መጽሐፍ ቅዱስ.......................................199
ብሉይ ኪዳን.......................................199
ነቢዩ ኤልሳዕ.......................................201
ትንቢተ ናሆም.......................................202
ትንቢተ ዕንባቆም.......................................203
ትንቢተ ሰፎንያስ.......................................204
ትንቢተ ሐጌ.......................................204
ትንቢተ ዘካርያስ.......................................205
ትንቢተ ሚልክያስ.......................................206
መጽሐፈ መቃብያን.......................................209
ሐዲስ ኪዳን.......................................209
ራእየ ዮሐንስ.......................................212
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት.......................................215
ጥያቄዎች.......................................216
ምዕራፍ 3:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ.......................................216
የጌታችን ትምህርቶች.......................................216
የጌታችን መቃብር.......................................216
የጌታችን ከሞት መነሣት.......................................216
እንደ ወንጌላዊው ማቴዎስ አቀራረብ.......................................216
እንደ ወንጌላዊው ማርቆስ አቀራረብ.......................................217
እንደ ወንጌላዊው ሉቃስ አቀራረብ.......................................217
እንደ ወንጌላዊው ዮሐንስ አቀራረብ.......................................217
ጌታችን ለሁለት ደቀ መዛሙርት መገለጡ.......................................


ገጽ


218
ደቀ መዛሙርቱ በተሰበሰቡበት ቤት መገኘቱ.......................................219
ጌታችንና ሐዋርያው ቶማስ.......................................219
ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ መታየቱ.......................................220
ጌታችንና ሐዋርያው ጴጥሮስ.......................................220
ጌታችንና ሌላው ደቀ መዝሙር.......................................220
የጌታችን ዕርገት.......................................220
የጌታችን ተአምራት.......................................220
በተዘጋ ቤት ውስጥ የመግባቱ ተአምር.......................................221
የመሰወሩ ተአምር.......................................221
የጌታችን ምሳሌዎች.......................................221
የዮናስ ምሳሌነት.......................................221
የቤተ መቅደስ መፍረስና መሠራት.......................................221
የሙሴ የነሐስ እባብ.......................................221
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት.......................................222
ጥያቄዎች.......................................223
ምዕራፍ 4:- ቤተ ክርስቲያን.......................................223
የቤተ ክርስቲያን ማእከልነት.......................................224
የቅዱሳት መጻሕፍት አተረጓጐም ማእከልነት.......................................225
የመሠረተ እምነት ማእከልነት.......................................226
የአምልኮ ሥርዓት ማእከልነት.......................................227
ማጠቃለያ.......................................227
የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን.......................................227
ትልቁ ባስልዮስ.......................................228
የሆሣዕና በዓል ሥርዓት.......................................232
ጥያቄዎች.......................................233
ምዕራፍ 5:- መንፈሳዊነትና ግብረ ገብነት.......................................233
መከራከር አስፈላጊ አለመሆኑ.......................................234
ምንም ያኽል ደግነት ያለን ቢመስለን መኮራራት የለብንም.......................................235
ጥያቄዎች.......................................236
መክሥተ ርእስ.......................................249
የተነበቡ መጻሕፍት.......................................


www.ethiopianorthodox.org

ደጀ ሰላም ረታና ቤትስብ
ምግባ ቤተ መጻሕፍት

## ዘጠነኛ ክፍል

## ምዕራፍ 1

## ትምህርተ ሃይማኖት

### የእግዚአብሔር ክብር

የእግዚአብሔር ክብር ሲባል እርሱነቱ፣ ልዕልናው፣ ግርማው፣ ጌትነቱ፣ እንዲሁም እነዚህ ንና እነዚህን የመሳሰሉትን የእግዚአብሔርን ከፍተኛነትና ከሁሉም በላይነት የሚገልጥ ቃል ነው። እግዚአብሔርም ክብሩን የገለጠባቸውና የሚገልጥባቸው የተለያዩ ወቅቶችና ሁኔታዎች አሉ። ሆኖም እግዚአብሔር ክብሩን የሚያሳየን እርሱ በሚፈቅዳቸው መንገዶች ነው እንጂ እኛ በምንፈልገው ዐይነት አይደለም። ለምሳሌ ሙሴ ክብርህን አሳየኝ ብሎ እግዚአብሔርን መጠየቁ አንተነትህን አሳየኝ ማለቱ ነው (ዘጸ:ም:33 ቁ:17–21)።

ታዲያ የእግዚአብሔር መልስ ምን ነበር?

«ደግነቴን ሁሉ በፊትህ አሳልፋለሁ፣ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ስሜን በፊትህ ዐውጃለሁ፣ የምምረውን እምራለሁ፤ የምራራለትንም እራራለታለሁ፤ ፊቴን አይቶ ከቶ ለመኖር የሚችል ሰው ስለሌለ ፊቴን ለማየት አትችልም» (ዘጸ:ም:33 ቁ:19–20)።

ምንም እንኳ አሁን እኛ የምንነጋገረው ስለ እግዚአብሔር ክብር ቢሆን ዐልፎ ዐልፎ ስለ ሰው ክብርም የሚነገርበት ጊዜ አለ። ለምሳሌም የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት:-

«ክብሬን ከፊቴ ላይ ገፎ አዋረደኝ» (ኢዮ:ም:19 ቁ:9)።

«የወጣቶች መመኪያ ብርታታቸው ነው፤ የሽማግሌዎችንም መከበሪያ ሽበታቸው ነው» (ምሳ:ም:20 ቁ:29)።

«ሰሎሞንስ እንኳ በዚያ ሁሉ ክብሩ ከእነርሱ እንደ አንዱ አልለበሰም» (ማቴ:ም:6 ቁ:29)።

ሰው ግን በሞት፣ በሽረትና የነበረውን ሀብት በማጣት ክብሩን ሊያጣ ይች ላል። የሰው ልጅ ሀብቱ፣ ንብረቱ፣ ሹመቱና ዝነኛነቱ ጊዜያዊ እንደመሆኑ ክብሩም እንደዚያው ጊዜያዊ ነው። ሰው በሚሞትበት ጊዜ የክብር ስሙ ብቻ ሳይሆን መጠሪያ ስሙ እንኳ በአንድ ቀን ተለውጦ ሬሳ፣ በድን፣ ወይም አስከሬን የሚባል ስም ይሰጠዋል።

ስለዚህ ጊዜያዊ የሆነውን የሰው ክብር ከዘለዓለማዊው የእግዚአብሔር ክብር ጋር ለማወዳደር በፍጹም አይቻልም። ምን ዐይነት ሙከራ ነው? እስቲ በዚህ ጉዳይ ቅዱሳት መጻሕፍት ምን እንደሚሉ እንመልከት።

ሰው ሁሉ እንደ ሣር ነው፤ ክብሩም ሁሉ እንደ ሜዳ አበባ ነው... ሣሩ እንደሚደርቅና አበባውም እንደ ሚረግፍ ሰውም እንዲሁ ረጋፊ ነው፤ ... የአምላካችን ቃል ግን ለዘለዓለም ጸንቶ ይኖራል» (ኢሳ:ም:40 ቁ:6–8)።

«ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ ሐሳቤም ከሐሳባችሁ ከፍ ያለ ነው ይላል» (ኢሳ:ም:55 ቁ:9)።

እግዚአብሔር ክብሩን የገለጠባቸውንና የሚገልጥባቸውን አንዳንድ ሁኔታዎች ቀጥለን እንመልከት።

አብዛኛውን ጊዜ እግዚአብሔር ክብሩን የሚገልጠው እርሱን ባለማ ወቃቸው ምክንያት ኃጢአት እየሠሩ ራሳቸውን ለፍርድ ቅጣት ያዘጋጁ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ንስሐ ገብተው እንዲመለሱ ለማድረግና እነርሱንም ያዩ ሰዎች እን ዲማሩ ለማድረግ ነው።

ለምሳሌ የፈርዖንንና የግብጽን ሕዝብ ሁናቴ ብናስተውል ይህን አባባል የሚያመለክት ሆኖ እናገኘዋለን።

ምንም እንኳ ፈርዖን ለዘለቄታው ባይመለስ የእግዚአብሔር ቅጣት በበዛበት ጊዜ:- «አሁንስ በድዬአለሁ፤ እግዚአብሔር እውነተኛው ነው፤ እኔና ሕዝቤ ግን በደለኞች ነን» ብሎአል (ዘጸ:ም:9 ቁ:27)።

እንዲሁም እግዚአብሔር ስለ ፈርዖን የተናገረውን እንመልከት

ደጀ ሰላም ረታና ቤትስብ
ምግባ ቤተ መጻሕፍት

---

www.ethiopianorthodox.org

«እኔም ልቡን ስለማደነድነው ያሳድዳችኋል፤ ስለዚህም በንጉሡና በሠራዊቱ ላይ የምገኘው ጸፈው ድል ለእኔ ክብር ይሆናል፤ በዚያን ጊዜ ግብጻውያን እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ያውቃሉ» (ዘጸ:ም:14 ቁ:4)።

በዚህም አባባል መሠረት በግብጻውያን ላይ ከወረደው ዐሥር መቅሠፍት ሌላ የግብጽን ሠራዊት በቀይ ባሕር ውስጥ አስጥሞታል። ስለዚህ እግዚብሔር ክብሩን ከሚገልጥባቸው መንገዶች መካከል ኃጢአተኞችን የሚያስደ ነግጥበትና እነርሱን ለመቅጣት የሚያደርገው ድንቅ ሥራ ነው። ለዓለም በሙሉ ክብሩን ላመግለጥ የግብጽን ሕዝብ በዐሥር መቅሠፍቶችና፥ ሠራዊ ታቸውን ደግሞ በቀይ ባሕር ውስጥ አስጥሞ በመግደል ቀጥቶአቸዋል። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን በግብጾች መካከል ይኖሩ በነበሩ በእስራኤል ልጆች ላይ አንዳችም ጉዳት አልደረሰባቸውም። ይህም የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት ስለሚያመለክት ክብሩ ተገልጦበታል። ከዚህም ድንቅ ሥራ ጋር በተያያዘ እግዚአብሔር ቀይ ባሕርን ለሁለት የከፈለው የእስራኤልን ልጆች በደረቅ መሬት ላይ እየተራመዱ እንዲሻገሩ ለማድረግ ሲሆን፥ በታላቅ ኀይሉ ከግብጽ ባርነት ነጻ ያወጣ ቸውን እስራኤላውያንን እንደገና ወደ ባርነት ለመመለስ ይከታተላቸው በነበረው የግብጽ ሠራ ዊት ላይ ለሁለት ተከፍሎ የነበረው የባሕር ውሃ ተመልሶ እንዲያሰ ጥማቸው አድርጓል። ስለዚህ እግዚአብሔር እዚህ ላይ ክብሩን የገለጠው በሁ ለት መንገድ ነው። አንዱ መንገድ የእስራኤልን ልጆች ለማዳን ያደረገው ተአምር ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ ግብጾችን የቀጣበት ኀይሉ ነው (ዘጸ:ም:14 ቁ:15:31)።

በዚህም ምክንያት ሙሴና የእስራኤል ሕዝብ:- «ፈረሱንና ፈረሰኛውን ወደ ባሕር አሽቀን ጥሮ በመጣል ክብር የተሞላው ድል ስለተጐናጸፈ ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ» በማለት ምስጋናቸውን አቅርበዋል (ዘጸ:ም:15 ቁ:1)።

ጥፋተኞችን በመቅጣትና ለሌሎችም ትምህርት በመስጠት እግዚአብሔር ክብሩን ከገለጠባቸው ሁኔታዎች መካከል የቆሬ፥ የዳታንና የአቤሮን ቅጽበታዊ ቅጣት አንዱ ነው።

ከሌዊ ነገድ የነበረው ቆሬ፥ ከሮቤል ነገድ የነበሩት ዳታንና አቤሮን፥ ከሁለት መቶ ኀምሳ ተባባሪዎቻቸው ጋር ሆነው በሙሴና በአሮን ላይ ዐመፁ። ሙሴን በመሪነቱ፥ አሮንን በክህነቱ ቀኑባቸው። ሙሴንም ሆነ አሮንን የመረጣ ቸው እግዚአብሔር መሆኑን አላስተዋሉም። እነርሱን በሚቃወሙበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ውሳኔ እንደተቃወሙ ልብ አላደረጉም። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር፥ የእስራኤልን ማኅበረሰብ ሊደመስስ በነበረ ጊዜ በሙሴና በአ ሮን አማላጅነት ጥፋተኞቹን ብቻ ለመቅጣት ወሰነ።

ቆሬ ሙሴንና አሮንን ለመቃወም መላውን ማኅበረሰብ ሰብስቦ ሁሉም በሙ ሴና በአሮን ፊት በቆሙ ጊዜ ደመናው የማደሪያውን ድንኳን ሸፍኖት የእግዚአ ብሔር ክብር ተገልጦ አዩ። እግዚአብሔርም ሙሴን ሰዎች ሁሉ ከቆሬ፥ ከዳታንና ከአቤሮን ድንኳን እንዲርቁ ንገር አለው። ሙሴም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተናግሮ እንዳበቃ መሬት ተከፍቶ ዐመፀኞቹን ከቤተሰቦቻውና ካላቸው ንብረት ሁሉ ጋር ዋጣቸው። ዕጣን ያጥኑ የነበሩትም ሁለት መቶ ኀምሳ ሰዎች እሳት ወርዶ አቃጣላቸው።

ይህ በሆነ በማግስቱ መላው የእስራኤል ማኅበር የእግዚአብሔር ወገኖች የሆኑ ወገኖቻችንን ገድላችኋል ብሎ ሙሴንና አሮንን በመቃወም ተሰበሰበ። ነገር ግን ወደ የማደሪያው ድንኳን ዞር ብለው ሲመለከቱ ደመናው የማደሪያውን ድንኳን ሸፍኖት የእግዚአብሔር ክብር ተገለጠ። እግዚአብሔርም ሙሴን እነዚህን ሰዎች ስለምደመስስ ከእነርሱ ርቃችሁ ቁሙ አለው። አሮንና ሙሴም በግንባራቸው በመሬት ላይ ተደፉ። ሙሴም አሮንን በፍጥነት ለሕዝቡ እንዲያስ ተሰርይ ነገረው። አሮንም በፍጥነት በጥናው ውስጥ ፍምና ዕጣን አድርጎበት ለሕዝቡ አስተሰረየ። አሮን ከማስተሰረዩ በፊት መቅሠፍቱ ጀምሮ ስለነበረ በአሮን ማስተስረይ ከመቆሙ በፊት በመቅሠፍቱ ዐሥራ አራት ሺህ ሰባት መቶ ሰዎች ሞቱ።

ይህ በአሮን አማካይነት የተደረገው የማስተሰረይ ተግባር ለካህናት የተሰጠውን የክህነት ሥልጣን ያመለክታል። ሙሴ እንኳ አሮንን እንዲያስ ተሰርይ ነገረው እንጂ እርሱ ራሱ አልቶዳፈረም።

እግዚአብሔር ሰዎችን ለማዳንና ጥፋተኞችን ቀጥቶ ለሌሎች መቀጣጫ ለማድረግ ክብሩን የሚገልጥ ከመሆኑ ጋር ሰዎች እግዚአብሔርን በመፍራትና ትእዛዙን በመጠበቅ እንዲኖሩ ለማድረግም ክብሩን ይገልጣል።



እግዚአብሔር [illegible] በሙሴ
አማካይነት የሰጣቸው ከግብጽ በወጡ በሦስተኛው ወር ወደ ሲና ተራራ አጠገብ በደረሱ ጊዜ በተራራው ላይ ሆኖ ነው።

ከዚህ ቀጥሎ እግዚአብሔር ክብሩን በገለጠ ጊዜ ሕዝቡ ምን እንደ ተሰማውና ሙሴም ለሕዝቡ ምን ዐይነት መግለጫ እንደሰጠ እንመለከታለን።

«ከዚህ በኋላ ሙሴ ከተራራው ወርዶ፥ ሕዝቡ ልብሱን አጥቦ እንዲቀደስ አደረገ። ሙሴም ሰዎቹን ለተነገ ወዲያ ዕለት ተዘጋጁ፤ እስከዚያም ቀን ድረስ ወደ ሴት አትቅረቡ አላቸው። በሦስተኛው ቀን ማለዳ የነጐድጓድ ድምፅ አስተጋባ፤ መብረቅ ብልጭልጭታና ጥቅጥቅ ያለ ደመና በተራራው ላይ ታየ፤ እንዲሁም ከፍተኛ የመለከት ድምፅ ተሰማ:- ... እግዚአብሔር በእሳት ስለወረ ደበት መላው የሲና ተራራ በጢስ ተሞላ፤ ጢሱም ከእሳት ምድጃ እንደሚወጣ ዐይነት ሆኖ ወደ አየር ተትጐለጐለ፤ ሰዎቹም እጅግ ፈርተው ተንቀጠቀጡ፤ የመለከቱም ድምፅ እያከታተለ ማስተጋባት ጀመረ፤ ሙሴ ሲናገር እግዚአ ብሔር በነጐድጓድ ይመልስለት ነበር» (ዘጸ:ም:19 ቁ:14–19)።

«ሰዎቹም የነጐድጓዱንና የመለከቱን ድምፅ በሰሙ ጊዜ፤ እንዲሁም መብረቁ ሲብለጨ ለጭና ተራራው ሲጤስ ባዩ ጊዜ በፍርሃት በመንቀጥቀጥ ርቀው ቆሙ፤ እነርሱም ሙሴን አንተ ተናገረን፤ እናዳምጥሃለን፤ እግዚአ ብሔር ቢናገረን ግን እንሞታለን ብለን እንፈራለን አሉት። ሙሴም አይዞአችሁ አትፍሩ፤ እግዚአብሔር በዚህ ሁኔታ ወደ እናንተ የመጣው ሊፈትናችሁና እርሱን በመፍራት ኃጢአት ከመሥራት ርቃችሁ እንድትኖሩ ነው ሲል መለሰላቸው» (ዘጸ:ም:20 ቁ:18–20)።

እንዲሁም እግዚአብሔር እርሱ ራሱ የሚመለክበትን ቦታ ለማክበር ክብሩን ይገልጣል።

«ከዚህ በኋላ የማደሪያው ድንኳን በደመና ተሸፈነ፤ የእግዚአብሔርም ክብር ድንኳኑን ሞላው። ደመናው ስለረበበበትና የእግዚአብሔርም ክብር ድን ኳኑን ስለሞላው ሙሴ ወደ ድንኳኑ ሊገባ አልቻለም» (ዘጸ:ም:40 ቁ: 34–35)።

«ካህናቱ ከቤተ መቅደሱ እንደወጡ ቤተ መቅደሱ ድንገት በደመና ተሞላ፤ በደመናውም ውስጥ የነበረው የእግዚአብሔር ክብር ቤቱን ስለሞላ ካህናቱ ተመልሰው ለመግባትና አግልግ ሎታቸውን ለማከናወን አልቻሉም» (:1ኛ:ነገ: ም:8 ቁ:10–11)።

«የእግዚአብሔር ክብርም ከኪሩቤል ወጥቶ በቤተ መቅደሱ ደጃፍ ቆመ፤ ቤቱም በደመናው ተሞላ፤ አደባባዩም የእግዚአብሔርን ክብር በሚገልጠው ብርሃን ተንጸባረቀ» (ሕዝ:10፡4)።

«የእግዚአብሔርም ክብር ወደ ምሥራቅ በሚመለከት በር ወደ መቅደሱ ገባ። መንፈሱም አነሣኝ፤ ወደ ውስጠኛውም አደባባይ አገባኝ፤ እነሆም፤ የእግዚአብሔር ክብር መቅደሱን ሞልቶት ነበር (ሕዝ:43፡4–5)።

የእግዚአብሔር ክብር ከሦስቱ የመለኮት አካላት በአንዱ ማለት የሰውን ሥጋ በለበሰው በወልድ ተገልጾአል።

ይህንኑም በሚቀጥሉት ማስረጃዎች እንመልከት:-

«ቃል ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ ዐደረ፤ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን» (ዮሐ:ም:1 ቁ:14)።

«እግዚአብሔርን ያየው ከቶ ማንም የለም፤ ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ያለው አንድያ ልጁ ብቻ ገለጦታል» (ዮሐ:ም:1 ቁ:18)።

«አብ በወልድ ምክንያት እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርግላችኋለሁ» (ዮሐ:ም:14 ቁ:13))።

«እርሱ የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅ ነው፤ እርሱ በባሕርዩ ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም ትክክል ነው። በኀያል ቃሉ ዓለምን ሁሉ ደግፎ ይዞአል፤ ሰዎችንም ከኃጢአት ካነጻ በኋላ በሰ ማይ፥ በኀያሉ እግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦአል» (ዕብ:ም:1 ቁ:3)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአምላክነቱን ክብር በተለያዩ ሁኔታዎች ገልጾአል። ይህንንም በሚከተሉት ምሳሌዎች ይመለከቷል:-



www.ethiopianorthodox.org

## በተአምራቱ

«ኢየሱስም ይህን የተአምራት ሁሉ መጀመሪያ የሆነውን ተአምር በገሊላ ክፍል ሀገር በቃና ከተማ አደረገ፤ በዚህም ዐይነት ክብሩን ገለጠ፤ ደቀ መዛሙር ቱም በእርሱ አመኑ (ዮሐ:ም:11 ቍ:11)።

«ኢየሱስም ይህን በሰማ ጊዜ ይህ ሕመም ለሞት የሚያደርስ አይደለም። ነገር ግን ለእግዚአብሔር ክብር እንዲሆንና የእግዚአብሔር ልጅም በዚህ ምክንያት እንዲከበር ነው» (ዮሐ: ም:11 ቍ:4)።

«ኢየሱስም ‹ካመንሽ የእግዚአብሔርን ክብር ታያለሽ ብዬሽ አልነበ ረምን?› አላት» (ዮሐ:ም:11 ቍ:4)።

## በሕማማቱና በሞቱ

«ደቀ መዛሙርቱ ይህ ነገር በመጀመሪያ አልገባቸውም ነበር፤ ግን ኢየሱስ በክብር ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ ይህ ነገር ስለ እርሱ እንደተጻፈና ለእርሱም እንደተደረገለት አስታወሱ» (ዮሐ: ም:12 ቍ:16)።

«ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ እነሆ የሰው ልጅ የሚከበርበት ሰዓት ደርሶአል፤ እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ የስንዴ ቅንጣት በመሬት ላይ ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ከሞተች ግን ብዙ ታፈራለች» (ዮሐ:ም:12 ቍ:23–24)።

## በዳግም ምጽአቱ

«የሰው ልጅ በአባቱ ክብር ሆኖ ከመላእክቱ ጋር ይመጣል። በዚያን ጊዜም ለያንዳንዱ እንደየሥራው ዋጋውን ይከፍለዋል» (ማቴ: ም:16 ቍ:27)።

«ከዚህም በኋላ የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ላይ ይታያል፤... የሰው ልጅም በኀይልና በታላቅ ክብር በደመና ላይ ሆኖ ሲመጣ ያዩታል» (ማቴ: ም:24 ቍ:30)።

«በዚህ በከሐዲና በኃጢአተኛ ትውልድ ፊት በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ፤ የሰው ልጅ በአባቱ ክብር ከቅዱሳን መላእክት ጋር ሲመጣ በእርሱ ያፍርበታል» (ማር:ም:8ቍ:38)።

«ከዚህ በኋላ የሰው ልጅ በታላቅ ኀይልና ክብር በደመና ላይ ሆኖ ሲመጣ ይታያል» (ሉቃ: ም:21 ቍ:27)።

«በዚህ ዐይነት የተባረከውን ተስፋችንን እንጠብቃለን፤ ይህም የምን ጠባበቀው ተስፋ የታላቁ አምላካችን፤ አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ የክብር መገ ለጥ ነው» (ቲቶ:ም:2 ቍ:13)።

## በሰዎች ተግባር እግዚአብሔር ይከብራል፡-

«በእኔ ብትኖሩ፤ ቃሌም በእናንተ ቢኖር፤ የፈለጋችሁትን ስትጠይቁ ታገኛላችሁ። ብዙ ፍሬ ስታፈሩ አባቴ ይከብራል» (ዮሐ:ም:15 ቍ:7–8)።

«ይህንንም ያለው ጴጥሮስ በምን ዐይነት ሞት እግዚአብሔርን ማክበር እንዳለበት ሲያመለክት ነው» (ዮሐ:ም:21 ቍ:19)።

## አብ ወልድን ወልድ ደግሞ አብን ያከብራል

«ኢየሱስ ይህን ከተናገረ በኋላ ወደ ሰማይ ቀና ብሎ እንዲህ አለ፡- አባት ሆይ፤ እነሆ፤ ሰዓቱ ደርሶአል፤ ልጅህ እንዲያከብርህ ልጅህን አክብረው።» (ዮሐ:ም:17ቍ:1)።

## እግዚአብሔር የክብር ጌታ ወይም የክብር ንጉሥ ነው

«የክብር ንጉሥ ይገባ ዘንድ እናንተ ጥንታውያን በሮች ተከፈቱ፤ ይህ የክብር ንጉሥ ማነው? ይህ የክብር ንጉሥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው» (መዝ:24 ቍ:9–10)።

" ዐውቀውትስ ቢሆን የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር (1ኛ:ቆሮ:ም:2 ቍ:8)።

«ወንድሞቼ ሆይ፤ በክብር ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የምታምኑ ሆናችሁ አንዱ ከሌላው ይበልጣል በማለት በሰው መካከል አድልዎ አታድርጉ» (ያዕ:ም:2ቍ:1)።



## ሰው ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር መስጠት አለበት

የእግዚአብሔርን ክብርና ምስጋና ለራሱ የሚያደርግ ሰው፤ ወይም ለእግዚአብሔር መስጠት ያለበትን ክብር ሳይሰጥ የሚቀር ሰው እግዚአብሔር ምሕረት አያደርግለትም።

የእስራኤል ልጆች በበረሓወው ጉዞአቸው ወደ [illegible] ውሃ አጣንም፡ እግዚአብሔርም ሙሴን አለቱን መትቶ ውሃ እንዲያወጣ [illegible] ሙሴና አሮን ግን ይህ በእግዚአብሔር ትእዛዝ የተፈጸመውን ተአምር ለራሳቸው [illegible] ስላደረጉትና ለእግዚአብሔር ምንም ክብር ሳይሰጡ በመቅረታቸው ወደ ተስፋ [illegible] እንዳይገቡ እግዚአብሔር ፈረደባቸው (ዘኍ:ም:20 ቍ:7–13)።

የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ የመሞቻው ጊዜ መድረሱ [illegible] ያረዝምለት ዘንድ ምርር ባለ ለቅሶ ስለጸለየ በዕድሜው ላይ [illegible] ረለት። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ጸሎቱን ሰምቶ ዕድሜውን ስላረዘመለት ለእግዚአብሔር አክብሮቱንና ምስጋናውን ስላላ ቀረበ በይሁዳና በኢየሩሳሌም [illegible] ምሕረት የተደረገላቸው ንጉሡና ሕዝቡ ንስሓ ከገቡ በኋላ ብቻ ነው (2ኛ: ዜ:መ:ም:32 ቍ:24–26)።

«ሄሮድስ ለእግዚአብሔር ክብር ሳይሰጥ በመቅረቱ [illegible] የእግዚአብሔር መልአክ ቀሠፈውና ተልቶ ሞተ» (የሐ: ሥ: ም:12 ቍ:23)።

«እንግዲህ ስትበሉም ሆነ ስትጠጡ፤ ወይም ማናቸውንም ነገር ስታደርጉ፤ ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉ» (1ኛ: ቆሮ: ም:10 ቍ:31)።

## እግዚአብሔር ለክብሩ ቀናተኛ ነው።

«እኔ አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝ» (ዘጸ:ም:20ቍ:5)።

«አምላካችሁ እግዚአብሔር የሚባላ እሳት ቀናተኛ አምላክ ነው» (ዘዳ:ም:4 ቍ:24)።

«ስሜ እግዚአብሔር ነው፤ የእኔንም ክብር የሚጋራ ሌላ አምላክ የለም፤ ማንም ምስጋናዬን እንዲካፈሉ አልፈቅድም» (ኢሳ: ም:42 ቍ:8)።

ይህን ያደረግሁት ስለ ራሴ ነው፤ ክብር እንዲነሣኝ ወይም ክብሬን ከሌሎች አማልክት ጋር እንድካፈል አልፈቅድም» (ኢሳ:ም:48 ቍ:11)።

## የእግዚአብሔር መጠሪያዎች

እግዚአብሔር አምላካችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያዩ ስሞች ተጠርቶአል። ለጊዜው የቀረቡት የሚከተሉት ናቸው፡-

እግዚአብሔር ፡- «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» (ዘፍ:ም:1ቍ:1)

ልዑል እግዚአብሔር፡- «የልዑል እግዚአብሔር ካህን የነበረው የሳሌም ንጉሥ መልከጼዴቅ ለአብርሃም ኅብስትና የወይን ጠጅ አመጣለት (ዘፍ:ም:145 ቍ:18)።

ያህዌ፡- «ሁሉን የምችል አምላክ (ኤልሻዳይ) መሆኔን በመግለጼት ለአብርሃም፤ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ተገልጬላቸዋለሁ፤ እግዘአብሔር ያህዌ በተሰ [illegible] ቅዱስ ስሜ አማካይነት ግን አልተገለጥሁላቸውም» (ዘጸ:ም:65 ቍ:3)።

ልዑል፡- «የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰማው ሰው የትንቢት ቃል ወድቆ ሳለ ዐይኖቹ ተከፍተው ሁሉን የሚችል አምላክን (የልዑልን) ራእይ የሚያይ ሰው መልእክት ይህ ነው» (ዘኍ: ም:24 ቍ:16)፡

ሕያው እግዚአብሔር፡- «ሕያው እግዚአብሔር በእሳት ውስጥ ሆኖ ከተና ገረው በኋላ በሕይወት ከሰው ዘር መካከል አንድ ሰው እንኳ ይገኛልን? » (ዘዳ:ም:5ቍ:26።

የአማልክት አምላክ፥ የጌቶች ጌታ፡- አምላካችሁ እግዚአብሔር የአማል ክት አምላክ፤ የጌቶች ጌታ ነው» (ዘዳ:ም:10 ቍ:17)።

የእስራኤል ክብር ፡- «የእስራኤል ክብር (ኀይል) እግዚአብሔር አያብ ልም፤ አሳቡንም አይለውጥም» (1ኛ:ሳሙ:ም:15 ቍ:29)፡

www.ethiopianorthodox.org

የሠራዊት ጌታ:- «የሠራዊት ጌታ ከእርሱ ጋር በመሆኑ ዳዊት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበረታ ሄደ» (1ኛ:ዜ:መ:ም:11 ቁ:9)።

የሰማይና የምድር አምላክ:- «እኛ የሰማይና የምድር አምላክ ባሪያዎች ነን» (ዕዝ:ም:5 ቊ:11)

ቅዱስ:- «የቅዱሱን ቃል ምንጊዜም አልካድሁም» (ኢዮ: ም:65 ቊ:10)።

የሠራዊት አምላክ:- «የሠራዊት አምላክ አቤቱ፥ መልሰን፤ ፊትህንም አብራ፤ እኛም እንድናለን።» (መዝ: 80 ቊ:7)።

አምላክ:- «የምናመልከው አምላካችን» (ዳን:ም:3 ቊ:17)።

የጸባዖት ጌታ (የሠራዊት ጌታ):- «የጸባዖት ጌታስ ዘር ባያስቀርልን» (ሮሜ:ም:9 ቊ:29)።

የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ:- (1ኛ:ጢ:ሞ:ም:6 ቊ15)።

የብርሃን አባት:- «ይህም የሚመጣው ከብርሃን አባት ከእግዚአብሔር ነው» (ያዕ: ም:1ቊ:17)።

## የመንፈሳውያን በዓላት አከባበር፥ የዘመንና የአጽዋም አቈጣጠር

የበዓላት አከባበር:- ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያደረ ጋቸውን ቸርነቶች፥ የሰጠውንም ጸጋና በረከት በመንፈሳዊ ስሜት ለማስታ ወስና ምስጋና ለማቅረብ የተለያዩ በዓላት እንዲከበሩ የደነገገችው በመንፈስ ቅዱስ ተመርታ ነው።

ይህ የመንፈሳውያን በዓላት አከባበር የጀመረው ከቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ጀምሮ ብቻ ሳይሆን በዘመነ ኦሪትም እስራኤላውያን የተለያዩ በዓላትን እንዲያከብሩ በእግዚአብሔር ታዘው ነበር። ለምሳሌ በኦሪት ዘሌዋውያን ም:23 ቊ:1–3 ሰንበትን እንዲያከብሩ፥ በቊ:5–6 የፋሲካን በዓል እንዲያከብሩ፥ በቊ:15–22 የመከርን በዓል እንዲያከብሩ፥ በቊ:23–24 የዓመት መባቻን ቀን እንዲያከብሩ፥ በቊ:26–32 የኃጢአት ስርየትን ቀን እንዲያከብሩ፥ በቊ: 33–44 የዳስ በዓልን እንዲያከብሩ ታዝዘዋል።

የሐዋርያት ትምህርት በሆነው በመጽሐፈ. ዲድስቅልያ አንቀጽ 18 እና አንቀጽ 31 ላይ የተለያዩ በዓላት እንዲከበሩ ታዝዞአል። ከእነዚህም መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

«ወንድሞቻችን ሆይ፥ በዕብራውያን አቈጣጠር በዘጠነኛው ወር፥ በኻያ አምስተኛው ቀን፥ ይህም ማለት በግብጻውያን አቈጣጠር በአራተኛው ወር በኻያ ዘጠነኛው ቀን የጌታን ልደት አክብሩ» (አንቀጽ 18)።

«ጌታችን መለኮታዊ ክሩን መግለጥ የጀመረበትን የጥምቀቱን በዓል በዕብ ራውያን አቈጣጠር በዐሥረኛው ወር፥ በስድስተኛው ቀን፥ ይህም ማለት በግብ ጻውያን አቈጣጠር በአምስተኛው ወር በዐሥራ አንደኛው ቀን አክብሩ» (አንቀጽ 18)።

በአንቀጽ ሠላሳ አንድ ላይ የጌታችን የትንሣኤ በዓል ከአይሁድ የፋሲካ በዓል በሚቀጥለው እሑድ ቀን እንዲከበር ታዝዞአል።

በዓለ ቶማስ ከትንሣኤ በዓል አንድ ሳምንት በኋላ እንዲከበር ታዝዞአል (አንቀጽ 31)።

የጌታ ዕርገት በዓል ከትንሣኤ በዓል በአርባኛው ቀን እንዲከበር ታዝዞአል (አንቀጽ 31)።

ከዕርገት በዓል በኋላ በዐሥረኛው ቀን ደግሞ ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ የላከበት የጰራቅሊጦስ በዓል እንዲከበር ታዞአል። (አንቀጽ 31)።

በዚሁ በሠላሳ አንደኛው የዲድስቅልያ አንቀጽ የረቡዕና የዓርብ፥ እንዲ ሁም የአርባው ቀን ጾም ታዞአል።

በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ዐሥራ ዘጠኝ ላይ ከላይ በዲድስቅልያ የታዘዘው ትእዛዝ የተደገመ ከመሆኑም በላይ በቊጥር 10 ላይ ከጌታችን በዓላት የመጀመሪያው በዐለ ብሥራት ነው ይላል።

በዚሁ አንቀጽ በቊጥር 27 ላይ:- «እናንተ ክርስቶስን እንድታውቁ በማድ ረግ አስተምረው መንፈስ ቅዱስን ሉዋቀበል ብቁ በአደረጉአችሁ በሐዋርያት መታሰቢያ ቀን ምንም አትሥሩ ይላል።



እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠንን ጸጋና በረከት ለማስታወስና ምስጋና ለማቅረብ ከምናከብራ ቸው በዓላት በተጨማሪ የሰማዕታትንና የቅዱሳንን መታሰቢያ በዓላት እንድናከብር ቤተ ክርስቲያን ደንግጋለች።

የሰማዕታትንና የቅዱሳንን በዓላት በምናከብርበት ጊዜ ሰማዕታቱና ቅዱሳኑ ያደረጓቸውን የሃይማኖት ተጋድሎዎች፥ የፈጸሙአቸውን የትሩፋት ተግባ ሮች፥ ዓለማዊ ችግር ሳይገታቸው ያሳዩትን ድፍረት፥ መንፈሳዊ ቅናታቸውንና የትሕትና ታሪካቸውን በማስተዋልና የእነርሱን አርአያነት ለመከተል በመሞከር ከስንፍና ወደ ትጋት እንመለሳለን፤ እንማራለንም።

ቅዱስ ባስልዮስ ይህን ጉዳይ በተመለከተ:- «ለቅዱሳን የመታሰቢያ በዓል ብናከብርላቸውና ምስጋና ብናቀርብላቸው ለእነርሱ ምንም የሚያስፈልጋቸው ሆኖ አይደለም። ለእኛ ግን የእነርሱን ታሪክ ማወቅ የእነርሱን አርአያነት ለመከ ተል ስለሚረዳን በጣም ይጠቅመናል፤ ይህም የሚሆንበት ምክንያት ብርሃን ከብርሃን፥ መልካም ሽታ ከመልካም ሽቶ እንደሚገኙ ከቅዱሳን ተግባር መታ ሰቢያ ጸጥ ያለ ብርሃንና የንጹሕ በጎ ተግባረ ሽታ እናያለን» ብሏል። (ሚካኤል ሚና፥ ትምህርተ መለኮት፥ 3ኛ. መጽሐፍ፥ ገጽ. 444–445)

## የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች:-

«ጻድቅ ሰው ለዘለዓለም ይታሰባል» (መዝ:112 ቊ:6)።

«ይህ ወንጌል በዓለሙ ሁሉ በሚሰበክበት በማናቸውም ስፍራ እርስዋ ያደረገችው ለእርስዋ መታሰቢያ ሆኖ ይነገርላታል» (ማቴ:ም:6 ቊ:13)።

«እነሆ፥ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ነሽ ይሉኛል» (ሉ:ቃ:ም:1 ቊ:48)።

«ጳውሎስ በእስያ ጊዜ እንዳያባክን ብሎ ኤፌሶንን ዐልፎ ለመሄድ የፈለገው የአይሁድ ፋሲካ ባለፈ በኀምሳኛው ቀን በሚከበረው በጰንጠቆስጤ በዓል በተቻለ መጠን በኢየሩሳሌም ለመገኘት አስቦ ስለነበረ ነው (የሐ: ሥ:ም:20 ቊ:16)።

«የእግዚአብሔርን ቃል በመጀመሪያ የነገሩአችሁን መሪዎቻችሁን አትርሱ፤ አኗኗራቸውንና ሥራቸውን በማስታወስ እምነታቸውን ተከተሉ» (ዕብ: ም:13ቊ:7)።

እነዚህን መንፈሳውያን በዓላት የምናከብርባቸው ቀኖች የሚወሰኑት በሁ ለት መንገዶች ነው። አንዱ መንገድ የአይሁድ የፋሲካ በዓል ቀን ከሚያደርገው መለዋወጥ ጋር የሚለዋወጥ ሲሆን፥ ሁለተኛው መንገድ ደግሞ በየዓመቱ በእነዚያ በተወሰኑት ቀኖች የሚውሉ በዓላት ናቸው። ለምሳሌ የትንሣኤ በዓል በየዓመቱ በተለያዩ ቀኖች የሚከበር ሲሆን የጥምቀት በዓል ደግሞ ሁልጊዜ ጥር 11 ቀን ይውላል።

የዘመን አቈጠጠር:- የዘመን አቈጣጠር ለተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮች የሚ ጠቅም ቢሆንም እዚህ የቀረበው ግን ሃይማኖታዊ አሠራርን በተመለከተ ነው።

የዘመን አቈጣጠርን በተመለከተ የኢትዮጵያና የግብጽ አብያተ ክርስቲያን የድሜጥሮስን የባሕረ ሐሳብ አሠራር መሠረት የሚያደርጉ በመሆናቸው የሃይ ማኖት በዓሎቻቸው የሚውሉት በተመሳሳይ ቀን ነው። ይህም ማለት እኛና እነ ርሱ የሃይማኖት በዓላትን የምናከብረው በአንድ ቀን ይሁን እንጂ በዓላቱ መቼ እንደሚውሉ ለማወቅ የሚደረጉት የስሌት አሠራሮች ይለያያሉ። እነዚህን ሁለት የአሠራር መንገዶች ለመረዳት በ1937 ዓ.ም. ታትሞ የወጣውን የዘመን አቈጣጠር መጽሐፍ ይመለከቷል። በዚህም መጽሐፍ ውስጥ በሙሉ ቀርቦአል።

## ክፍለ ዓመት በቤተ ክርስቲያን ሥርዐት፥

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በየቀኑ የሚነበበው የቅዱሳት መጻሕፍት ንባብ፥ የሚዘመረው መዝሙር፥ የሚቀደሰው ቅዳሴና የሚሰጠው ትምህርት በዓመቱ ውስጥ ያሉትን ወቅቶች (ዘመናት) በዓላትንና አጽዋማትን የሚመለከት ነው።

እንደሚታወቀው በዓመቱ ውስጥ አራት ዐበይት የዘመን ክፍሎች ሲኖሩ በመካከላቸው ደግሞ ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምባቸው ሌሎች ንኡሳን ክፍ ሎች አሉ። እነዚህም ከላይ እንደተገለጠው ለእግዚአብሔር በየጊዜው የተለያየ ምስጋና ለማቅረብ የተመደቡ ናቸው። አራቱ ዐበይት የዓመት ክፍሎች የሚባሉ ትም መፀው፥ ሐጋይ (በጋ)፥ ጸደይ (በልግ) ፥ እና ክረምት ናቸው። እያንዳንዱ ክፍለ ዓመት 91 ቀናት አሉት። ዓመቱን በእኩል ይካፈሉታልና።



www.ethiopianorthodox.org

## 1ኛ. ክፍለ ዓመት መፀው፥

መፀው ማለት የአበባ ወራት የአበባ ዘመን ማለት ነው። ይኸውም ከመስ ከረም 26 ቀን እስከ ታሕሣሥ 25 ቀን ድረስ ያለው ወቅት ነው። በዚህም ወቅት ሦስት ንኡሳን ክፍላተ ዘመን ይገኛሉ።

ሀ. ዘመነ ጽጌ:- ይህም ከመስከረም 26 እስከ ኅዳር 5 ቀን ድረስ ያለው ጊዜ ነው። በዚህ በአንደኛው ክፍለ ዘመን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያ ምና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ግብጽ መሰደዳቸው ይታሰባል። እግዚ አብሔር ክረምቱን ስለማሳለፉ፥ የተዘሩትን አዘር ዕትና የተተከሉትን አትክ ልት፥ የምድረ በዳውን ዕፀዋትና ሐመልማል ሁሉ ለአበባና ለፍሬ ስለማብቃቱ ሰማይን በከዋክብት፥ ምድርን በአበቦች ስለማስጌጡ ይመሰገናል። እመቤታችንና ቤተ ክርስቲያን በሙሽሪትና መልካም መዓዛ ባለው ገነት፥ ጌታችን ደግሞ በሙሽራና በጎ መዓዛ ባለው የገነት አበባ መመሰላቸውን የሚያ መለክት መዝሙር ይዘመራል፥ ንባብ ይነበባል።

ለ. ዘመነ አስተምሕር

አስተምሕሮ ማለት ምህላ ወይም ልምና፥ ምልጃ ማለት ነው። ዘመነ አስተ ምሕር የሚባለው ከኅዳር 6 ቀን ጀምሮ እስከ ታሕሣሥ 6 ቀን ወይም 12 ቀን ድረስ ያለው ጊዜ ነው። በዚህም ወቅት:- እግዚአብሔር ቸርና ታጋሽ ይቅር ባይም በመሆኑ በየጊዜው የሰዎችን በደል ሳይመለከት የቸርነቱን ሥራ መሥ ራቱ፥ ለሰዎች የዕረፍት ቀን እንድትሆን ሰንበትን መቀደሱ፥ ጌታችን በምኩ ራብ ተገኝቶ ማስተማሩ፥ ባሕሩንና ነፋሱን መገሠፁ፥ የተለያየ ደዌ ያለባቸውን ሰዎች መፈወሱ ይታሰባል።

ሐ. ዘመነ ስብከት

ከታኅሣ ሥ 7 ወይም 13 ቀን ጀምሮ እስከ ታኅሣ ሥ 28 ቀን ያለው ጊዜ ዘመነ ስብከት ይባላል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሦስት እሑዶች የሚገኙ ሲሆን እያንዳንዱ እሑድ የተለየ ስያሜ አለው።

1ኛ እሑድ ስብከት ይባላል:- ክርስቶስ ሰው ለመሆን እንደሚመጣ በሙሴ ሕግና በነቢያት፣ በሌሎችም መጻሕፍት አስቀድሞ መሰበኩ ሳምንቱን በሙሉ ይታሰባል።

2ኛው እሑድ ብርሃን ይባላል:- ክርስቶስ ብርሃን ሆኖ፥ ወደ ጨለማው ዓለም እንደሚመጣ፥ በጨለማ የሚኖረው ሕዝብ ብርሃን ክርስቶስን እንደ ሚያይ የተነገረው ትንቢት ሁሉ በዚህ ሳምንት ይነገራል።

3ኛው እሑድ ኖላዊ ነው:- ክርስቶስ ስለ መንጋዎቹ ሲል ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ ቸር እረና ሆኖ እንደሚመጣ በነቢያት የተነገረው ትንቢት የሚታሰብበት ሳምንት ነው።

ዘመነ ስብከት የሚጀመርበትን ወይም ስብከት የሚውልበትን እሑድ ማግኘት የሚቻለው በሚከተለው የአቈጣጠር መንገድ ነው።

ታሕ.1 ቀን ማክሰኞ ቢውል ስብከት ታሕ. 13 ቀን ይሆናል።
ታሕ.1 ቀን ረቡዕ ቢውል ስብከት ታሕ. 12 ቀን ይሆናል።
ታሕ.1 ቀን ሐሙስ ቢውል ስብከት ታሕ. 11 ቀን ይሆናል።
ታሕ. 1 ቀን ዐርብ ቢውል ስብከት ታሕ. 10 ቀን ይሆናል።
ታሕ. 1 ቀን ቅዳሜ ቢውል ስብከት ታሕ. 9 ቀን ይሆናል።
ታሕ. 1 ቀን እሑድ ቢውል ስብከት ታሕ 8 ቀን ይሆናል።
ታሕ 1 ቀን ሰኞ ቢውል ስብከት ታሕ. 7 ቀን ይሆናል።

## 2ኛ ክፍለ ዓመት ሐጋይ (በጋ)

ሐጋይ ማለት ድርቅ የድርቅ ወራት ማለት ነው። ይህ ክፍለ ዓመት ከታሕሣሥ 26 እስከ መጋቢት 25 ቀን ድረስ ያለው ወቅት ሲሆን በውስጡም ሦስት ንኡሳን ክፍለ ዘመኖች ይገኙበታል።

ሀ. ዘመነ ልደት

ከታሕሣሥ 29 እስከ ጥር 10 ቀን ያለው ጊዜ ዘመነ ልደት ይባላል። በዚህ ክፍለ ዘመን ውስጥ ክርስቶስ በቤተ ልሔም መወለዱ፥ በተወለደ ጊዜም ሰብአ ሰገል እጅ መንሻ ይዘው መምጣታቸው፥ ሄሮድስ ያስገደላቸው የቤት ልሔም ሕፃናት፥ ግዝረቱ፥ ወደ ናዝሬት መግባቱና



በናዝሬት ማደጉ ይታሰባሉ። በዚህ ወቅት በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸመው የንባብ፣ የዜማና የቅዳሴ ሥነ ሥርዓት ሁሉ ይህን የሚመለከት ይሆናል።

ለ. ዘመነ አስተርእዮ

አስተርእዮ ማለት መገለጥ መታየት ማለት ነው። ዘመነ አስተርእዮ የሚባለው ከጥር 11 ቀን ጀምሮ እስከ ጾመ ነነዌ ያለው ጊዜ ነው፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ:- አምላክ ሰው ሆኖ በሥጋ መገለጡ፥ በዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ የአንድ ነትና የሦስትነት ምሥጢር መታወቁ፥ በቃና ዘገሊላ በተደረገው ሠርግ ላይ የመጀመሪያውን ተአምር በማድረግ አምላካዊ ኃይሉ መገለጡ እየታሰበ ምስጋና ይቀርባል።

ሐ. ዘመነ መርዓዊ

ይህ ክፍለ ዘመን ከጾመ ነነዌ እስከ ዐቢይ ጾም ያለው ጊዜ ነው። ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን እንደ ሙሽራ መሆኑ የሚነገርበትና ቀዳማዊ ምጽአቱ የሚታ ሰብበት ጊዜ ነው።

## 3ኛ. ክፍለ ዓመት ጸደይ (በልግ)

የዚህ ክፍለ ዓመት ምድብ ከመጋቢት 26 ቀን ጀምሮ እስከ ሰኔ 25 ቀን ድረስ ያለው ጊዜ ነው፤ በውስጡም የተለያዩ ንኡሳን ክፍለ ዘመኖች አሉ።

ሀ. ዘመነ ዐቢይ ጾም

ይህ ክፍለ ዘመን ጾሙ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ቅዳሜ ስዑር ያለው ጊዜ ነው። የጾሙ መግቢያ ወደ ታች ሲወርድ ከየካቲት አንድ በታች ወደ ጥር አይወርድም። ወደ ላይ ሲወጣም ከመጋቢት አምስት በላይ አይወጣም። በዐ ቢይ ጾም ስምንት ሳምንቶች አሉ። እነዚህም ሳምንቶች በተለያየ ስም ይጠራሉ።

1ኛው ሳምንት ዘወረደ ይባላል፤ የክርስቶስ ከሰማይ መውረድ፥
2ኛው ሳምንት ቅድስት ይባላል፤ የሰንበት ቅድስና፥
3ኛው ሳምንት ምኩራብ ይባላል፤ ክርስቶስ በምኩራብ ማስተማሩ፥
4ኛው ሳምንት መፃጕዕ ይባላል፤ ክርስቶስ በሽተኞችን መፈወሱ፥
5ኛው ሳምንት ደብረ ዘይት ይባላል፤ ደብረ ዘይት በተባለው ተራራ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት መነገሩ፥
6ኛው ገብርኄር ይባላል፤ ለደግ አገልጋይ ዋጋ ያለው መሆኑ፥
7ኛው ሳምንት ኒቆዲሞስ ይባላል፤ ጌታችን ከኒቆዲሞስ ጋር መነጋገሩ፥
8ኛው ሳምንት ሆሣዕና ይባላል፤ ጌታችን ሆሣዕና በመባል እየተመሰገነ ወደ ቤተ መቅደስ መግባቱና ስለ እኛ ሕማማትን መቀበሉ ይታሰብበታል።

ቅዳሜ ስዑር (ቀዳም ስዑር)

ከትንሣኤ በፊት ከስቅለት ማግሥት ያለው ቅዳሜ «ቅዳሜ ስዑር» ይባ ላል። ስዑር ማለትም የተሻረ ማለት ነው። በዓመት አንድ ጊዜ ስለሚጾም «ቅዳሜ ስዑር» ተብሏል። በአማርኛ ቅዳሜ ሹር ይባላል። ቅዳሜ ሥዑር ተብሎ በንጉሡ ከተጻፈ ግን ለምለም ቅዳሜ ማለት ይሆናል። በዚሁ ዕለት ከሚታደለው ለምለም ቄጤማ ጋር የተያያዘ ስያሜ ነው።

እንደገናም ይህ ዕለት ታላቁ ቅዳሜ በመባል ይጠራል። የፊተኛው ቅዳሜ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ፈጥሮ ያረፈበት እንደሆነ በዚህኛውም ቅዳሜ የማዳን ሥራውን በዕለተ ዐርብ በመስቀል ላይ ፈጽሞ በመቃብር ዐርፎ ውሎበታልና።

በቅዳሜ ስዑር ዕለት ግብረ ሕማማት በተባለው መጽሐፍ እንደ ታዘዘው ካህናትና ምእመናን ጧት በቤተ ክርስቲያን ይሰባሰባሉ። የጧቱ ጸሎት ከተፈጸመ በኋላ:-

«ወለመልእክ ሕይወትሰ ሰቀልዎ፥ ለዘተንሥአ እሙታን ገብረ ሰላመ በመስቀሉ ትንሣኤሁ አግሀደ። ከሙታን ተለይቶ የተነሣውን የሕይወት ጌታ ሰቀሉት፤ በመስቀሉ ሰላምን አደረገ፤ ትንሣኤውን ገለጠ።» የተባለው የሰላም መዝሙር ይዘመራል።

በዚህ ጊዜ ቄጠማ በሊቀ ጳጳሱ፣ ጳጳስ በሌለበትም በቁሱ ገባርኮ በቤተ ክርስቲያን ለተሰበሰቡት ምእመናን ሁሉ ይታደላል። ምእመናኑም ቄጠማውን እየሰነጠቁ በመስቀል ምልክት ሠርተው በራሳቸው ያስሩታል።

ወደ ቤተ ክርስቲያን ላልመጡትም ልብሰ ታክህኖ የለበሱ ካህናት መስቀልና ቃጭል ይዘው በእየመንደሩ በመዞር «ገብረ ሰላም በመስቀሉ...» «የም ሥራች» እያሉ ቄጠማውን

www.ethiopianorthodox.org

ይሰጡአቸዋል። ምእመናንም ቁጠማው፣ ለሚሰጡአቸው ካህናት ግንዘብ ይሰጣሉ። ወይም ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውል ስጦታ ይሰጣሉ። አንዳንዶችም ከትንሣኤ በኋላ ካህናቱን ጠርተው ግብር ያገባሉ (ይጋብዛሉ)። ይህም የ«ገብረ ሰላመ» ግብዣ ይባላል።

በዚህ ዕለት የሚታደለው ቁጠማ የምሥራች ምልክት መሆኑ ከቅዱስ መጽሐፍዊ ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው። በጥፋት ውሃ ጊዜ ኖኅ በመርከብ ውስጥ ሆኖ የውሃውን መጒደል ለማወቅ ቁራ የተባለውን አሞራ ላከ። ነገር ግን ቁራው ሳይመለስ በመቅረቱ ርግብን ላከች ርግብዋም የለመለመ የወይራ ቅጠል በአፍዋ ይዛ ወደ ኖኅ ተመለሰች። ኖኅም በዚህ ለምለም የወይራ ቅጠል የውሃ ውን መጒደል ተረድቶ ደስ አለው። መርከቡንም ለማሳረፍ ተዘጋጀ። በዚህ መሠረት የወይራው ቅጠል ለጥፋት ውሃ መጒደል ምልክት እንደሆነ በቅዳሜ ስዑር የሚታደለው ለምለም ቁጠማም ኃጢአትና የነፍስ ሞት በክርስቶስ ሞት ከሰው ልጆች ላይ ለመደምሰሳቸው የምሥራች ምልክት ነው (ዘፍ:8፥6–12። ኤፌ. 2፥ 14–17)።

ለ. <u>ዘመነ ትንሣኤ</u>

ትንሣኤ ከዋለበት እሑድ ጀምሮ እስከ ጰንጠቆስጤ ያለው ጊዜ ዘመነ ትን ሣኤ ይባላል። በዚህ ክፍለ ዘመን:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ በሥልጣኑ መነሣቱ፥ ነፍሳትን ከሲኦል ማውጣቱ፥ ቅዱሳት አንስት (ሴቶች) ወደ መቃብሩ ሄደው የተነሣው ክርስቶስን ማየታቸው፥ ክርስቶስ ከተ ነሣ በኋላ በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች ለደቀ መዛሙርቱ መገለጡ ይነገራል።

ከአርባኛው ቀን ጀምሮ እስከ ጰራቅሊጦስ ያለው ጊዜ በክፍለ ዘመን ባይመ ደብም ዘመነ ዕርገት በመባል ይታወቃል። ዕርገቱን በተመለከተም ምስጋና ማቅረብ የሚጀመረው ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ነው።

ከትንሣኤ በኋላ አምሳኛው ቀን እሑድ መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት መው ረዱ ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ መውረድ መመሥረትዋ ይታሰባል። ሳምንቱም የጰንጠቆስጤ ወይም የበዐለ ኀምሳ ሳምንት በመባል ይጠራል።

ሐ. <u>ዘመነ ጰራቅሊጦስ</u>

ከጰራቅሊጦስ እሑድ በኋላ ካለው እሑድ ጀምሮ እስከ ሰኔ 16 ቀን ድረስ ያለው ጊዜ ዘመነ ጰራቅሊጦስ ነው። በዚህ ወቅት የክርስቶስን ወደ ሰማይ መውጣትና የመንፈስ ቅዱስን መውረድ የሚመለከት ንባብ ይነበባል፥ መዝሙር ይዘመራል፤ ምስጋናም ይቀርባል።

መ. <u>ዘመነ አስተምሕሮ</u>

ከሰኔ 17 ቀን ጀምሮ እስከ ሰኔ 25 ቀን ያለው ጊዜ ዘመነ አስተምሕሮ ይባላል። የምህላ ወቅት ማለት ነው። ይህ ክፍለ ዘመን አንዳንዴ በጊዜ መሳሳብ ምክንያት ይቀራል። በዚህ ወቅት የሚፈጸመው ሥርዐት ባለፈው ዘመነ አስተምህሮ የተጠቀሰው ነው።

## <u>4ኛ. ክፍለ ዓመት ክረምት</u>

ከሰኔ 26 ቀን ጀምሮ እስከ መስከረም 25 ቀን ድረስ ያለው የዓመቱ ክፍል ዘመነ ክረምት ነው።

በውስጡም ሰባት ያኽል ንኡሳን ክፍለ ዘመኖች ይገኙበታል።

ሀ. <u>ከሰኔ 26 እስከ ሐምሌ 18</u> ያለው ጊዜ የዝናብ፥ የደመና፥ የዘርና የቡቃያ ዘመን ተብሎ ይጠራል። እግዚአብሔር:- በዚህ ወቅት ዝናቡን በሚፈል ግበት ቦታ ስለማዝነቡ፥ የተዘራውን ስለማብቀሉ፥ ምድርን በዝናብ ስለማር ካቱና አራሹን ደስ ስለማሰኘቱ ይመሰገናል።

ለ. <u>ከሐምሌ 19 እስከ ነሐሴ 9 ቀን ድረስ ያለው ጊዜ የመብረቅ የነጐድጓድ የባሕርና የወንዞች ወቅት ነው።</u> በዚህ ጊዜ ስለ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ለእግ ዚአብሔር ምስጋና ይቀርባል የሚዘመረው መዝሙርና ንባብ ሁሉ እነዚህን የተመለከተ ይሆናል።

ሐ. <u>ከነሐሴ 10 ቀን ጀምሮ እስከ ነሐሴ 27 ባለው</u> ክፍለ ዘመን እግዚአብሔር የቍራ ጫጩቶችን መመገቡ፥ የፍጥረቱ ሁሉ ዐይን እርሱን ተስፋ ማድረጉ የሚታሰብበትና ምስጋና ያሚቀርብበት ነው።

መ. <u>ከነሐሴ 28 እስከ ጳጒሜን 5(6) ያለው ጊዜ ጎህ (ውጋጋን)</u> ጽባሕ (ጥዋት) ፥ ብርሃን ይባላል፤ የክረምቱ ጊዜ ለማለቅ መቃረቡን ያመለክታል፥ ከዚህም ጋር አምስቱ የጳጒሜን ቀኖች የክርስቶስ ዳግም ምጽአት መታሰቢያ ናቸው።

ሠ. <u>ከመስከረም 1 ቀን እስከ መስከረም 8 ቀን ዘመነ ዮሐንስ ይባላል።</u>



መጥምቁ ዮሐንስ ከርሱ በኋላ የሚመጣውን ክርስቶስን ለመቀበል ሰዎች እንዲዘጋጁና የንስሐ ፍሬ እንዲያደርጉ ማስተማሩ የሚታሰብበት ጊዜ ነው።

ረ. <u>ዘመነ ፍሬ</u>:- ይህ ክፍለ ዘመን ከመስከረም 9 ቀን እስከ መስከረም 16 ቀን ድረስ ያለው ጊዜ ነው። እግዚአብሔር የተዘራውን ዘር ለፍሬ ስለማብቃቱና ለሰዎች ስለሚሰጠው ጸጋና ስለ ልዩ ልዩ በረከቱ ሁሉ ምስጋና የሚቀርብበት ወቅት ነው።

ሰ. <u>ዘመነ መስቀል</u>

ከመስከረም 17 እስከ መስከረም 25 ቀን ያለው ጊዜ ዘመነ መስቀል ይባ ላል። የጌታችን መስቀል አይሁድ ቀብረውት ለብዙ ዓመታት ከቆየ በኋላ በቅድ ስት ዕሌኒ እማካይነት መገኘቱ፥ በመስቀሉ አስደናቂ ተአምር መደረጉ፤ በቅ ዱስ መስቀሉ ስም የተሠራው ቤተ ክርስቲያን መመረቁ የሚታሰብበት ጊዜ ነው።

## <u>የንግሥ በዓል</u>

በዓመት አንድ ጊዜ በደመቀ መንፈሳዊ ሥርዓት የሚከበር የቤተ ክርስቲያን በዓል የንግሥ በዓል ወይም ክብረ በዓልና ዓመት በዓል በመባል ይጠራል።

የንግሥ በዓል መባሉ፥ አንድ ንጉሥ ዘውድ ተቀዳጅቶ የነገሠበትን ቀን በየዓመቱ በመኳንንት፥ በብዙ ሕዝብና በብዙ ሠራዊት ታጅቦ እንደሚያከብር ነቢያትና ሐዋርያት፥ ጻድቃንና ሰማዕታት፥ ቅዱሳን መላእክት እግዚአብሔርን በማገልገላቸው ክብር ያገኙበት ቀን ብሩህ ልብሰ ተክህኖ በለበሱ ካህናትና ነጭ ልብስ በለበሱ ምእመናን ደምቆ መከበሩን ያሳያል። ክብረ በዓል ሲባልም የበዓሉን አከባበር ሁኔታ ለመግለጥ ነው። የዓመት በዓል መባሉም በዓመት አንድ ጊዜ መሆኑን ያመለክታል።

የንግሥ በዓል የሚባለው:-

- የቅድስት ሥላሴ በዓል፥
- ከሦስቱ አካላት የአንዱ አካል የእግዚአብሔር ወልድ በዓል፥
- የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም በዓል፥
- የቅዱሳን መላእክት በዓል፥
- የቅዱሳን ነቢያትና የሐዋርያት በዓል፥
- የጻድቃንና የሰማዕታት በዓል ነው።

<u>ስለ ጌታችን በዓላት</u>:- «በዐቢይትና ንኡሳን በዓላትን» ይመለከቷል።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስለእመቤታችን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደችበት ዕለት (ልደታ) ወደ ቤተ መቅደስ በገባችበት ዕለት (በአታ) ባረፈችበት ዕለት (አስተርእዮ)፥ ተነሥታ ባረገችበት ዕለት (ፍልሰታ) የንግሥ በዓል አድርጋ ታከብራለች። እነዚህም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በኦርቶዶክስ ዓለም ሁሉ የታወቁና በከፍተኛ ክብር የሚከበሩ በዓላት ናቸው።

<u>ስለ ቅዱሳን መላእክትም</u>:- ቃል ኪዳን በተቀበሉበትና ከእግዚአብሔር ተልከው ለሰው ልጆች ታላቅና ድንቅ ሥራ በሠሩበት ቀን የንግሥ በዓል ይደረ ግላቸዋል። እንደዚሁም :- ቤተ ክርስቲያን:- የእግዚአብሔር ቃል በራእይ ወይም በመልእክ የተገለጠላቸውና ስለ እግዚአብሔር ወልድ ሰው መሆን በትንቢትና በምሳሌ የተናገሩ ነቢያትን፥ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሦስት ዓመት የኖሩ፥ ከእርሱም የተማሩ፥ ተአምራቱን፥ ሞቱንና ትንሣኤውን ዕርገቱንም ያዩ፥ ወንጌልን በዓለም ዞረው ያስተማሩ ሐዋርያትን፥ በከሐድያን ፊት ቆመው ስለ ክርስቶስ ያለ ፍርሀት የመሰከሩ ሰማዕታትን፥ እንደዚሁም ዓለሙንና በዓለሙ ያለውን ተድላ ደስታ ንቀው በዋሻና በፍርክታ ተወስነው መከራውን ታግሠው በጾምና በጸሎት የኖሩ ጻድቃንን ባረፉበት ወይም በተወለዱበት ቀን የንግሥ በዓል አድርጋ ታከብራቸዋለች።

ሐዋርያት፥ ጻድቃን ሰማዕታትን ስለማክበር ዲድስቅልያ በተባለው መጽሐፋቸው በአንቀጽ 25 ላይ የሚከተለውን አስተምረዋል። «ሊቀ ዲያቆናት ቀዳሚ ሰማዕት እስጢፋኖስ በእኛ ዘንድ የከበሩ እንደሆኑ ሰማዕታትን ከፍ ከፍ አድርጓቸው፤ አክብሯቸውም። ሰማዕታት:- በእግዚ አብሔር ዘንድ የተመረ ጡና የተቀደሱ ኃጢአትም የነጹ ናቸው። ቂም የላቸውም። ነገር ግን ሰላምን የሚያደርጉ ናቸው። ዘወትርም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸምና ትእዛዙን ለማድረግ የሚደክሙ ናቸው። እንደ እነዚህም ስለሉት ዳዊት «የጻድቃት ሞቱ በእግዚአብሔር

www.ethiopianorthodox.org

ዘንድ የከበረ ነው» ይላል (መዝ:115፥6) ሰሎምንም «የጻድቅ መታሰቢያው ለበረከት ነው» ይላል (ምሳሌ 10፥7)

ቤተ ክርስቲያን ለጻድቃንና ለሰማዕታት የተለየ የበዓል ቀን ወስና በዓመት አንድ ጊዜ የምታከብረው ይህን የሐዋርያትን ትእዛዝ መሠረት በማድረግ ነው።

የንግሥ በዓል የሚከበረው በተከበረው ቅዱስ ስም በታነጸውና በስሙ የተቀ ረፀው ጽላት (ታቦት) ባለበት ቤተ ክርስቲያን ነው፤ በመሆኑም በዓለ ንግሡን የሚያከብሩት የሰበካው ምእመናን ናቸው።

ከዚህ ቀጥሎ በዓመቱ ከሚውሉት የንግሥ በዓላት መካከል በሁሉ ዘንድ የታወቁት ጥቂቶቹ እንደሚከተለው ለምሳሌ ተመልክተዋል።

መስከረም 1፥ ቅዱስ ራጉኤል
መስከረም 2፥ ቅዱስ ዮሐንስ፥ ምትረተ ርእሱ
ጥቅምት 14፥ ቅዱስ አባ አረጋዊ
ጥቅምት 17፥ ቅዱስ እስጢፋኖስ በሰማያትነት ያረፈበት
ኅዳር 11፥ ቅድስት ሐና ዕረፍታ
ኅዳር 12፥ ቅዱስ ሚካኤል እስራኤልን ከግብጽ ሲወጡ የረዳበት
ኅዳር 21፥ ጽዮን፥ ታቦተ ጽዮን ዳጎን የተባለውን ጣዖት የቀጠቀጠችበት
ኅዳር 25፥ ቅዱስ መርቆርዮስ በሰማዕትነት ያረፈበት
ታኅሣሥ 3፥ እመቤታችን በ3ዓመትዋ ወደቤተ መቅደስ የገባችበት
ታኅሣሥ 19፥ ቅዱስ ገብርኤል፥ ሠለስቱ ጸቂቅን ከእሳት ማውጣቱ
ታኅሣሥ 24፥ ቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት፥ ልደታቸው
ጥር 4፥ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ፥ዕረፍቱ
ጥር 7፥ ቅድስት ሥላሴ፥ ለአብርሃም መገለጣቸው፥ እግዚአብሔር ወልድ ሰው መሆኑ የሚታሰብበት
ጥር 12፥ ቅዱስ ሚካኤል፥ ያዕቆብን ከዔሳው ማዳኑ፥ ቃና ዘገሊላ
ጥር 15፥ ቅዱስ ቂርቆስ፥ ዕረፍቱ
ጥር 21፥ እመቤታችን፥ ዕረፍታ፥ (አስተርእዮ)፥
የካቲት 16፥ እመቤታችን፥ የምሕረት ቃል ኪዳን የተቀበለችበት
መጋቢት 5፥ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፥ ዕረፍታቸው
መጋቢት 27፥ መድኃኔዓለም፥ ስለዓለም ቤዛ የተሰቀለበት
ሚያዝያ 23፥ ቅዱስ ጊዮርጊስ፥ በሰማዕትነት ያረፈበት
ሚያዝያ 30፥ ቅዱስ ማርቆስ፥ ዕረፍቱ
ግንቦት 1፥ እመቤታችን ፥ ልደታ፥ የተወለደችበት
ግንቦት 11፥ ቅዱስ ያሬድ፥ ዕረፍቱ
ሰኔ 12፥ ቅዱስ ሚካኤል ባሕራንን ያዳነበት
ሐምሌ 5፥ ቅዱሳን ጴጥሮስና ጳውሎስ፥ ቅዱስ ጴጥሮስ በመስቀል ቅ/ጳውሎስ በሰይፍ ሰማዕት የሆኑበት
ሐምሌ 19፥ ቅዱስ ቂርቆስና ኢየሉጣ ቅዱስ ገብርኤል ከእሳት አዳናቸው
ሐምሌ 22፥ ቅዱስ ኡራኤል፥ ከእግዚአብሔር ቃልኪዳን የተቀበለበት
ነሐሴ 16፥ እመቤታችን፥ ፍልሰታ፥ ተነሥታ ወደ ሰማይ ያረገችበት
ነሐሴ24፥ አቡነ ተክለሃይማኖት፥ ዕረፍታቸው
ጳጉሜን 3፥ ቅዱስ ሩፋኤል፥ ጦቢትንና ልጁን ጦብያን መርዳቱ፥ ሊቀመ ላእክት መሆኑ የሚታሰብበት

የንግሥ በዓላት ወይም የዓመት በዓላት የሚከበሩት በዑደት ነው። ለበዓሉ የተዘጋጀው መዝሙር እየተዘመረ ካህኑ ታቦቱን ከመንበሩ አንሥቶ በመሸከም ሦስት ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ከተዞረ በኋላ ሠርሖተ ሕዝብ ይሆናል (ሕዝቡ ይሰናበታል)። እንደዚህ የሚሆነው ጧት በሚቀደ ስበት ዕለት ነው። ነገር ግን ዕለቱ የጾም ጊዜ ቢሆን ቅዳሴው ውሎ ስለሚሆን ዑደቱ ከቅዳሴው



በፊት ይደረጋል፥ ታቦቱ ከዑደት እንደተመለሰ ጸሎተ ቅዳሴው ይጀመራል የቅዳሴው ጸሎት እንዳበቃም ሕዝቡ ይሰናበታል ወይም ሠርሖተ ሕዝብ ይሆናል።

## አሥርቆት (ማሥረቅ)

አሥርቆት ማለት ማውጣት ማለት ነው። እርሱም ሌሊትና ጨረቃን ለማግኘት መጠቀሚያ ቃል ነው። በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በግል ጸሎት ጊዜ፥ ጸሎት ከመጀመሩ በፊት አሥርቆት ይደረጋል። በቅዳሴ ጊዜ ግን በሥርዐተ ቅዳሴው መካከል ይደረጋል።

አሥርቆት ለማድረግ ወይም ሌሊቱንና ጨረቃን ለማግኘት የሚያገለግሉ ቀዋምያን የሆኑ መመሪያዎች የሚከተሉት ናቸው።

አንደኛ/ ለሠርቀ ሌሊት (ለሌሊቱ አወጣጥ)
ሀ. ዕለት (ቀን) መስከረም 1፥2፥3–30
ለ. የአውራኅ (የወሮች) ሕፀፅ 6
የመስከረምና የጥቅምት 1
የኅዳርና የታኅሣሥ 2
የጥርና የየካቲት 3
የመጋቢትና የሚያዝያ 4
የግንቦትና የሰኔ 5
የሐምሌና የነሐሴ 6
ሐ. የዘመኑ አበቅቴ
ሁለተኛ/ ለሠርቀ ወርኅ (ለጨረቃ አወጣጥ)
ሀ. ያደረው ሌሊት
ለ. የጨረቃው ተውሳክ 4
ከአበቅቴው በቀር ሌሎቹ መመሪያዎች ቀዋምያን ናቸው።

የጸሎቱ መሪ ሌሊቱንና ጨረቃውን ከማሥረቁ በፊት ዓመተ ዓለሙንና ዓመተ ምሕረቱን ይናገራል። ለመሳሌ መስከረም 1 ቀን 1990 ዓ.ም. አሥር ቆቱን እንደሚከተለው ይጀምራል።

«በተባረከው ወንጌላዊ በቅዱስ ማርቆስ ዘመን ሳለን የጌታችንና የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ የሕጉንና የትእዛዙን ቊጥር (ሐሳብ) በምናሰብ ገንዘብ:- የምሥራች ነጋሪ እስከ ሆነው እስከ ሉቃስ ዘመን ያድርሰን። ዓመተ ዓለም 5500 ሆነ። ዓመተ ምሕረት 1990 ሆነ። የተባረከው የመስከረም ወር ባተልን (ገባልን) እግዚአብሔር እስከ ጥቅምት ወር በሰላም ያድርሰን አሜን» ካለ በኋላ:-

«ዛሬ ቀኑ (ዕለቱ) 1
ሌሊቱ 5
ጨረቃው 9 ነው ይላል።

ከዚህ ላይ ሌሊቱና ጨረቃው ሊገኙ የቻሉት ከላይ በተገለጡት መመሪ ያዎች መሠረት ለመሆኑ የሚከተለውን ያስተውሏል:-

| | | |
|---|---|---|
| ዕለቱ መስከረም | 1 | |
| የመስከረም ሕፀፅ | 1 | |
| የ1990 ዓ.ም. አበቅቴ | 3 | |
| ድምር | 5 | ሌሊት ይባላል። |
| የጨረቃ ተውሳክ | 4 | |
| ድምር | 9 | ጨረቃ ይባላል። |

በዚህ መንገድ መመሪያዎቹን በመጠበቅ የዓመቱን ማውጣት ይቻላል።

አበቅቴ የሚገኝበትን መንገድ ለማወቅ በ1987 ዓ.ም. የታተመውን የዘ መን አቈጣጠር የተባለውን መጽሐፍ ይመለከቷል።

ሌሊቱም ሆነ ጨረቃው ከሠላሳ በላይ ሲሆን ሠላሳው ተቀንሶ ቀሪው ብቻ ይያዛል።

www.ethiopianorthodox.org

# <u>የዘመን አቈጣጠር ስሌት</u>

የኢትዮጵያና የግብጽ አብያተ ክርስቲያን ለዘመን አቈጣራቸው በዲድስቅልያና በኒቅያ ጉባኤ ውሳኔ የተደነገጉትን እንዲሁም የድሜጥሮስን የዘመን አቈጣጠር ደንብ መሠረት ያደርጋሉ። በዚህም መሠረት የሁለቱ አብያተ ክርስቲያን የበዓላትና አጽዋማት ዘመኖች አይለያዩም። ይሁን እንጂ የበዓላቱንና የአጽዋማቱን ቀኖች ለማወቅ በሚደረገው የስሌት መንገድ ይለያያሉ። የስሌት ዘዴአቸው ቢለያይም ሄደው ሄደው የሚደርሱበት የበዓል ቀን ግን ያው ነው። ሌላው ልዩነት ደግሞ ኢትዮጵያ አቈጣጠርዋን የምትጀ ምረው ከዓመተ ምሕረት ሲሆን ግብጽ ግን የምትጀ ምረው ከዓመተ ሰማዕታት ነው። ከዚህ ቀጥሎ የኢትዮጵያን አቈጣጠር ስሌትና የግብጾችን ስሌት ደግሞ ከጥቂት ለውጥ ጋር በዓመተ ምሕረት ተጀምሮ ሲሠራበት ምን እንደሚመስል ለማሳየት ቀርቦአል። በምሳሌነት የቀረበው 1990 ዓ.ም. ነው።

<u>ዓመተ ወንጌላውያን:-</u> እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር ዓመቶች በመፈ ራረቅ በአራቱ ወንጌላውያን ይሰየማሉ። አንድን ዘመን በማንኛው ወንጌላዊ ስም እንደተሰየመ ለማወቅ ዓመተ ምሕረቱን ለአራት ማካፈል ያስፈልጋል። ለአራት ሲካፈል አንድ ቢተርፍ ማቴዎስ፥ ሁለት ቢተርፍ ማርቆስ፥ ሦስት ቢተርፍ ሉቃስ፥ ምንም ሳይተርፍ ቢቀር ዮሐንስ ይሆናል። ይህም የቊጥር ቅደም ተከተል እንደ ወንጌሎቹ ቅደም ተከተል መሆኑ ነው።

1. ማቴዎስ
2. ማርቆስ
3. ሉቃስ
4. ወይም 0–ዮሐንስ

ስለዚህ 1990 ዓ.ም ለ4 ሲካፈል

1990፥ 4፥ = 497 ደርሶ 2 ስለሚተርፍ ዘመኑ ዘመነ ማርቆስ መሆኑ ነው።

<u>የዘመን መለወጫ የሚውልበት ቀን:-</u> የዘመን መለወጫ ማለት መስከረም 1 ቀን ከሳምንቱ ቀኖች በማንኛው ቀን እንደሚውል ለማወቅ የምንከተለውን የስሌት መንገድ ቀጥለን እንመልከት:-

በዘመን አቈጣጠር ስሌት ውስጥ ለአቈጣጠር መነሻ ወይም ተጨማሪ የሚሆን ቊጥር ተውሳክ ይባላል። በዚህም መሠረት የዕለታት ተውሳክ የሚከ ተሉት ናቸው:-

| | |
|---|---|
| ቅዳሜ | 8 |
| እሑድ | 7 |
| ሰኞ | 6 |
| ማግሰኞ | 5 |
| ረቡዕ | 4 |
| ሐሙስ | 3 |
| ዓርብ | 2 |

ከዚያም በላይ ደግሞ ማግሰኞ ዕለተ ቀመር ይባላል። እርሱም ለአንዳንድ ስሌቶች የመነሻ ቀን ነው።

ሌላው ዓመተ ወንጌላውያንን የማግኛ ዘዴ ደግሞ የሚከተለው ስሌት ነው።

| | |
|---|---|
| ዓመተ ዓለም | 5500 |
| ዓመተ ምሕረት | 1990 |
| ድምር | 7490 |

7490፥ 4 = 1872 ደርሶ 2 ስለሚተርፍ ዘመነ ማርቆስ መሆኑ ታውቆአል። ለአራት ተካፍሎ የደረሰው ድርሻ ተራፊው ሳይታሰብ ማለት 1872 መጠነ ራብዒት ይባላል። ይህን መጠነ ራብዒት ከዓመተ ዓለምና ከዓመተ ምሕረት ጋር በማዳመር የሚገኘውን ውጤት ለሰባት ከአካፈሉት በኋላ የሚገኘውን ትርፍ ከዕለተ ቀመር ማለት ከማግሰኞ ተነሥቶ በመቊጠር መስከረም 1ቀን መቼ እንደሚውል ለማወቅ ይቻላል።

| | |
|---|---|
| ምሳሌ:- ዓመተ ዓለም | 5500 |
| ዓመተ ምሕረት | 1990 |
| መጠነ ራብዒት | 1872 |
| ድምር | 9362 |



9362፥7 = 1337 ደርሶ 3 ይተርፋል። በዚህም መሠረት ከማግሰኞ ጀምረን 3 ቀኖችን የቈጠርን እንደሆነ ሐሙስ ላይ ስለሚያርፍ የ1990 ዓ.ም መስከረም 1 ቀን የሚውለው በሐሙስ ቀን ነው ማለት ነው።

<u>መደብና ወንበር</u>:- መደብን ለማግኘት ዓመተ ዓለሙንና ዓመተ ምሕረቱን አዳምሮ ለ19 ማካፈል ነው። ከተካፈለ በኋላ የሚገኘው ትርፍ መደብ ሲሆን ከመደብ ላይ 1 ሲቀነስ ደግሞ ወንበር ይባላል።

<u>ለምሳሌ</u>:- 1990 + 5500 = 7490፥ 19 = 394 ደርሶ 4 ይተርፋል። ይህም መደብ ይባላል። ከዚህ ላይ 1 ሲቀነሽለት የሚተርፈው 3 ወንበር ይባላል።

<u>አበቅቴ</u> :- የዘመኑን ወንበር በ11 አባዝቶ ውጤቱ ከ30 ከበለጠ ለ30 ይከፈልና ተራፊው የዘመኑ አበቅቴ ይሆናል።

<u>ለምሳሌ</u>:- 3 x 11 = 33 ይሆናል። ከዚያ 30 ሲቀነስለት ወይም ለ30 ሲካፈል 3 ይተርፋል። ይህም የዘመኑ አበቅቴ መሆኑ ነው።

<u>መጥቅዕ:-</u> መጥቅዕ የሚገኘው የዘመኑ ወንበር በ19 ተባዝቶ በሚገኘው ውጤት ሲሆን ውጤቱ ከ30 ከበለጠ ለ30 አካፍሎ የሚተርፈው ትርፍ የዘመኑ መጥቅዕ ይሆናል።

ምሳሌ:- 3x19 = 57፥30 ደርሶ 27 ስለሚተርፍ የ1990 ዓ.ም መጥቅዕ 27 ነው ማለት ነው።

<u>በዓለ መጥቅዕ</u>:- በዓለ መጥቅዑ የሚውልበትን ቀን ለማወቅ ከመስከረም 1 ቀን ሐሙስ ተነሥቶ 27 ቀኖች ሲቈጠር የ1990 ዓ.ም በዓለ መጥቅዕ የሚውለው ማክሰኞ መስከረም 27 ቀን ይሆናል ማለት ነው።

ከ2 እስከ 13 ለሆነ መጥቅዕ በዓለ መጥቅዑ በጥቅምት ወር ይውላል ከ15 በላይ ለሆነ መጥቅዕ በዓለ መጥቅዑ በመስከረም ወር ይውላል። ይህንኑም በሚቀ ጥለው የመስከረም ወር የቀኖች ሠንጠረዥ ይመለከቷል:-

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሐሙስ | 1 | 8 | 15 | 22 | 29 |
| ዓርብ | 2 | 9 | 16 | 23 | 30 |
| ቅዳሜ | 3 | 10 | 17 | 24 | |
| እሑድ | 4 | 11 | 18 | 25 | |
| ሰኞ | 5 | 12 | 19 | 26 | |
| ማግሰኞ | 6 | 13 | 20 | 27 | |
| ረቡዕ | 7 | 14 | 21 | 28 | |

ቀለል ባለ መንገድ አጽዋማትና በዓላት የሚውሉበትን ቀን ለማግኘት የሚ ቻለው በዓለ መጥቅዑ ከሚውልበት ቀን ተነሥቶ የነነዌ ጾም መግቢያን ካገኙ በኋላ ከነነዌ ጾም መግቢያ ተነሥቶ በመቊጠር ነው። አሠራሩም እንደሚ ከተለው ቀርቧል:-

<u>ጾመ ነነዌ</u>:- በዓለ መጥቅዕ በቅዳሜ ቀን ቢውል ከበዓለ መጥቅዕ እስከ ጾመ ነነዌ ድረስ 128 ቀኖች ናቸው።

በዓለ መጥቅዑ በእሑድ ቀን ቢውል እስከ ነነዌ ጾም ድረስ 127 ቀኖች ናቸው።
በዓለ መጥቅዑ በሰኞ ቀን ቢውል እስከ ጾመ ነነዌ ድረስ 126 ቀኖች ናቸው።
በዓለ መጥቅዑ በማግሰኞ ቀን ቢውል እስከ ጾመ ነነዌ ድረስ 125 ቀኖች ናቸው።
በዓለ መጥቅዑ በረቡዕ ቀን ቢውል እስከ ጾመ ነነዌ ድረስ 124 ቀኖች ናቸው።
በዓለ መጥቅዑ በሐሙስ ቀን ቢውል እስከ ጾመ ነነዌ ድረስ 123 ቀኖች ናቸው።
በዓለ መጥቅዑ በዓርብ ቀን ቡውል እስከ ጾመ ነነዌ ድረስ 122 ቀኖች ናቸው።

www.ethiopianorthodox.org

ዐቢይ ጾም:- ከነነዌ ጾም መግቢያ ማግስት እስከ ዓቢይ ጾም መግቢያ ድረስ 14 ቀኖች ናቸው።

ደብረ ዘይት:- ከነነዌ ጾም መግቢያ ማግስት እስከ ደብረ ዘይት በዓል ድረስ 41 ቀኖች ናቸው።

ሆሣዕና:- ከነነዌ ጾም መግቢያ ማግስት እስከ ሆሣዕና በዓል ድረስ 62 ቀኖች ናቸው።

ስቅለት:- ከነነዌ ጾም መግቢያ ማግስት እስከ ስቅለት ድረስ 67 ቀኖች ናቸው።

ትንሣኤ:- ከነነዌ ጾም መግቢያ ማግስት እስከ በዓለ ትንሣኤ ድረስ 69 ቀኖች ናቸው።

ርክበ ካህናት:- ከነነዌ ጾም መግቢያ ማግስት እስከ እስከ ርክበ ካህናት 93 ቀኖች ናቸው።

ዕርገት:- ከነነዌ ጾም መግቢያ ማግስት እስከ ዕርገት 108 ቀኖች ናቸው።

በዓለ ኀምሳ:- ከነነዌ ጾም መግቢያ ማግስት እስከ በዓለ ኀምሳ ድረስ 118 ቀኖች ናቸው።

ጾመ ሐዋርያት:- ከነነዌ ጾም መግቢያ ማግስት እስከ ጾመ ሐዋርያት ድረስ 19 ቀኖች ናቸው።

ጾመ ድኅነት:- ከነነዌ ጾም መግቢያ ማግስት እስከ ጾመ ድኅነት ድረስ 121 ቀኖች ናቸው።

## ያለ ተውሳክ የሚገኙ አጽዋማትና በዐላት

ጾመ ነቢያት (የልደት ጾም):- ኅዳር 16 ቀን ይጀምርና ከልደት በዐል አንድ ቀን በፊት ያልቃል።

በዐለ ልደት ከዘመነ ማቴዎስ እስከ ዘመነ ሉቃስ ባሉት ሦስት ተከታታይ ዓመቶች ታኅሣ ሥ 29 ቀን ይከበራል። በአራተኛው ዓመት ማለት በዘመነ ዮሐንስ ግን ታኅሣ ሥ 28 ቀን ይከበራል።

የጥምቀት በዐል:- ሁልጊዜ ጥር 11 ቀን ይከበራል። በማግስቱ ጥር 12 ቀን ደግሞ የቃና ዘገሊላ በዐል ነው።

ጾመ ፍልሰታ:- በየዓመቱ ነሐሴ 1 ቀን ይጀምርና ነሐሴ 15 ቀን ያልቃል።

የገሀድ ጾም:- በጥምቀት በዐል ዋዜማ የሚጾም የአንድ ቀን ጾምና እንዲሁም ጾመ ነቢያትን ለማይጾሙ ሰዎች በልደት በዐል ዋዜማ የሚጾም የአንድ ቀን ጾም ናቸው።

በዐለ ብሥራት:- በሉቃስ ወንጌል ም:1 ቍ.31 እንደተገለጸው መልአኩ ገብርኤል ለድንግል ማርያም «እነሆ፥ ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅም ትወልጂአለሽ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ» ብሎ ባበሠራት ጊዜ በዚሁ ምዕራፍ ቍ. 38 መሠረት «እነሆኝ እኔ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነኝ፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ» ብላ እምነትዋን በእግዚአብሔር ላይ በማሳረፍዋ በዚያኑ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ጌታችንን እንደፀነሰችና ይህም የሆነው መጋቢት 29 ቀን መሆኑን ቤተ ክርስቲያን የምታምነውና የምታስተምረው ትምህርት ነው።

በዐለ ስምዖን:- በሉቃስ ወንጌል ም 2ቍ. 25–32 መሠረት ሕፃን ጌታችን ኢየሱስ እንደ አይሁድ ሥርዐት ወደቤተ መቅደስ የተወሰደበት ቀን በየካቲት 8 ቀን እንደሚታሰብ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ነው።

ግዝረት:- ጥር 6 ቀን የሚውለው የጌታችን ግዝረት መታሰቢያ የሚሆነው በሉቃስ ወንጌል ም.2 ቍ21 መግለጫ መሠረት ነው።

ደብረ ታቦር:- በማቴዎስ ወንጌል ም.17 ቍ.1–8 መሠረት ጌታችን ለሦስት ደቀ መዛሙርቱ መለኮታዊ ክብሩን የገለጸበት መታሰቢያ በዐል ነሐሴ 13 ቀን ይከበራል።

ጸሎተ ሐሙስ:- በማቴዎስ ወንጌል ም. 26 ቍ. 26–36 እና በዮሐንስ ወንጌል መ. 13 መሠረት የምሥጢረ ቍርባን ምሥረታና የኀፅበተ እግር መታሰቢያዎች የሚከበሩት በበዐለ ስቅለት ዋዜማ በፅለተ ሐሙስ ነው።

በዐለ ቶማስ:- በዮሐንስ ወንጌል ም. 20 ቍ. 24–29 መሠረት ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያው ቶማስ በተገኘበት የተገለጸበት መታሰቢያ ቀን ከትንሣኤ በሚቀጥለው እሑድ ይውላል።

ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው የግብጾት በዓላትና አጽዋማት ከእኛ ቤተ ክርስቲያን በዓላትና አጽዋማት ልዩነት የላቸውም። ይሁን እንጂ የእነርሱ የስ ሌት መንገድና መነሾ የሚያደርጉት



ዘመን ከእኛ የተለየ ነው። የእኛ ዘመን አቈጣጠር የሚጀምረው ከክርስቶስ ልደት ሲሆን የእነርሱ አቈጣጠር የሚጀ ምረው ግን ከዘመነ ሰማዕታት ነው።

የግብጾች የስሌት መንገድ ጥቂት ለውጦችን ብቻ በማድረግ የተዘጋጀው አቈጣጠር ቀጥሎ ቀርቦአል።

በስሌታቸው ውስጥ የሚጠቀሙባቸው ቃላት በእኛ አቈጣጠር ከምንጠቀምባቸው ቃላት የተለዩ ናቸው።

ይህ የግብጾች የአቈጣጠር ስሌት የቀረበው የእኛን አቈጣጠር በእነርሱ አቈጣጠር ለመተካት ሳይሆን እነርሱ የሚሠሩበትንም ዘዴ ለመመልከት ያኽል ብቻ ነው።

## የግብጾችን የስሌት መንገድ በመከተል የዘመን አቈጣጠር

አስፈላጊ ሠንጠረዦች

| ተረፈ ፀሐይ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የሳምንቱ ቀኖች | ረቡዕ | ሐሙስ | ዓርብ | ቅዳሜ | እሑድ | ሰኞ | ማግሰቅ |

የመስከም ወር 1990 ዓ.ም. ቀኖች

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሐሙስ | 1 | 8 | 15 | 22 | 29 |
| ዓርብ | 2 | 9 | 16 | 23 | 30 |
| ቅዳሜ | 3 | 10 | 17 | 24 | |
| እሑድ | 4 | 11 | 18 | 25 | |
| ሰኞ | 5 | 12 | 19 | 26 | |
| ማግሰኞ | 6 | 13 | 20 | 27 | |
| ረቡዕ | 7 | 14 | 21 | 28 | |

### በተመሳሳይ ቀኖች የሚጀምሩና የሚጨርሱ ወሮች

መስከረምና ሚያዝያ – ታኅሣሥና ሐምሌ
ጥቅምትና ግንቦት – ጥርና ነሐሴ
ኅዳርና ሰኔ – የካቲትና ጳጉሜ
መጋቢት ግን አጣማጅ ወር ስለሌለው ለብቻው ይያዛል።

### መስከረም 1 ቀን ከሳምንቱ ቀኖች የሚውልበትን ቀን ለማወቅ

ከላይ እንደተመለከተው የተረፈ ፀሐይንና የሳምንቱን ቀኖች በሚመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት የ1990 ዓ.ም መስከረም 1 ቀን የሚውልበት ቀንን ለማቅ ዐውደ ፀሐይንና ተረፈ ፀሐይን ማስላት ያስፈልጋል።

ዐውደ ፀሐይ የሚባለው ዓመተ ምሕረቱን ለ28 ከአካፈሉ በኋላ የሚተርፈው ትርፍ ነው። ትርፉ ከአራት ያነሰ ከሆነ ግን 28 ይደመርበታል።

ምሳሌ:- 1990 ÷ ለ28 ሲካፈል 71 ደርሶ 2 ይተርፋል። ሁለት ግን ከ4 ያነሰ ስለሆነ 28 ተደምሮበት 30 ይሆናል ማለት ነው።

ተረፈ ፀሐይ የሚገኘው ዐውደ ፀሐዩንና የዐውደ ፀሐዩን ሩብ በማዳመርና (ተራፊው ሳይታሰብ) ድምሩን ለ7 አካፍሎ የሚገኘው ትርፍ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ምሳሌ:- 30 + 7 = 37

37 ለ 7 ሲካፈል 5 ደርሶ 2 ስለሚተርፍ ተረፈ ዐሐይ 2 መሆኑ ነው።

በሠንጠረዡ መሠረት 2 ማለት ሐሙስ ስለሆነ በ1990 ዓ.ም መስከረም 1 ቀን የሚውለው ሐሙስ ቀን ነው ማለት ነው።

<u>የአይሁድ የፋሲካ በዓልና የክርስቲያን ትንሣኤ በዓል</u>

የአይሁድን የፋሲካ በዓል ለማወቅ ዐውደ ጨረቃንና ተረፈ ጨረቃን አስልቶ ማግኘት ያስፈልጋል።

<u>ዐውደ ጨረቃ</u>:- በተፈለገው ዓመተ ምሕረት ላይ 8 ከተደመረበት በኋላ ለ19 አካፍሎ የሚገኘው ትርፍ ዐውደ ጨረቃ ይባላል።

<u>የዐውደ ጨረቃ ምሳሌ:</u>- በዓ.ም ላይ 8 ይደመራል።

1990 + 8 = 1998 ፥ 19 = 105 ደርሶ 3 ይተርፋል። ይህም ዐውደ ጨረቃ ይባላል።

<u>ተረፈ ጨረቃ</u>

ተረፈ ጨረቃውን ለማግኘት ዐውደ ጨረቃውን በ11 አባዝቶ ውጤቱን ለ30 ማካፈል ነው። ከማካፈል በኋላ የሚገኘው ትርፍ ተረፈ ጨረቃ ይባላል።

ምሳሌ:- 3x11 = 33-30 = 3

የአይሁድን የፋሲካ በዓል ቀን ለማወቅ ተረፈ ጨረቃውን ከ40 ላይ መቀነስ ቋሚ ደንብ ነው። የመቀነሱ ውጤት ከ1 እስከ 23 ቢሆን የፋሲካው በዓል የሚውለው በሚያዝያ ወር ውስጥ ይሆናል። ከ25 እስከ 30 ቢሆን ግን የአይሁድ የፋሲካ በዓል የሚውለው በመጋቢት ወር ውስጥ ይሆናል። የክርስቲያኑ የትንሣኤ በዓል ሁልጊዜ ከአይሁድ የፋሲካ በዓል በኋላ መሆን አለበት። ከዚያም በኋላ በዓላትና አጽዋማት ሁሉ የሚገኙት በትንሣኤ በዓል አማካይነት ነው። በዚህም መሠረት ከ40 ላይ 3 እና 30 ወይም 33 ሲቀነስ 7 ይተርፋል። ይህም የሚያመለክተው በ1990 ዓ.ም የአይሁድ የፋሲካ በዓል የሚውለው ሚያዝያ 7 ቀን መሆኑን ነው። መስከረምና ሚያዝያ የሚጀምሩና የሚጨርሱት በተመሳሳይ ቀኖች ስለሆነና ሚያዝያ 7 ቀን ደግሞ ረቡዕ በመሆኑ ከዚያ ቀጥሎ ያለው እሑድ ሚያዝያ 11 ቀን የትንሣኤ በዓል ይሆናል ማለት ነው። አጽዋማትና በዓላት የሚታወቁት በትንሣኤ በዓል አማካይነት መሆኑ ቀደም ተብሎ ተገልጦአል።

በዚህም መሠረት:-

<u>የነነዌ ጾም</u>:- የትንሣኤ በዓል በመጋቢት ወር ቢውል በበዓሉ ቀን ላይ 21 ተደምሮበት 30 ከተቀነሰ በኋላ የሚገኘው ውጤት የሚያመለክተው የነነዌ ጾም በጥር ወር ውስጥ የሚጀምርበትን ቀን ነው።

የትንሣኤው በዓል በሚያዝያ ወር ውስጥ ቢውል በበዓሉ ቀን ላይ 21 ይደመርበትና ከውጤቱ 30 ከተቀነሰ በኋላ ተራፊው ቍጥር የሚያመለክተው የነነዌ ጾም በየካቲት ወር ውስጥ የሚጀምርበትን ቀን ነው።

ምሳሌ:- 1990 ዓ.ም

| | |
|---|---|
| የ1990 ዓ.ም የትንሣኤ በዓል ሚያዝያ | 11 ቀን |
| የሚደመር | 21 |
| ድምር | 32 ከዚህ ላይ 30 ሲቀነስለት የነነዌ ጾም |

የካቲት 2 ቀን ይጀምራል ማለት ነው።

<u>ዐቢይ ጾም</u>:- የትንሣኤ በዓል በመጋቢት ወር ውስጥ ቢውል በበዓሉ ቀን ላይ 5 ተደምሮበታል 30 ከተቀነሰለት በኋላ ተራፊው የሚያመለክተው ዐቢይ ጾም በየካቲት ወር ውስጥ ሚጀምርበትን ቀን ነው።

የትንሣኤው በዓል በሚያዝያ ወር ቢውል በበዓሉ ቀን ላይ 5 ተደምሮበት ውጤቱ ከ30 ካልበለጠ ዐቢይ ጾም የሚጀምረው በየካቲት ወር ውስጥ ይሆናል። ከ30 ቢበልጥ ግን ከውጤቱ 30 ተቀንሶለት በተራፊው ቍጥር ዐቢይ ጾም በመጋቢት ወር ውስጥ ይጀምራል።

| | | |
|---|---|---|
| ምሳሌ:- | የትንሣኤ በዓል | 11 |
| | የሚደመር | 5 |
| የዐቢይ ጾም መግቢያ | – የካቲት | 16 ቀን |



<u>ደብረ ዘይት</u>:- የትንሣኤ በዓል በመጋቢት ወር ውስጥ ቢውል 2 ተደምሮበት ውጤቱ ከ30 ካልበለጠ የደብረ ዘይት በዓል በየካቲት ወር ውስጥ ይውላል። የድምሩ ውጤት ግን ከ30 ቢበልጥ 30 ከተቀነሰለት በኋላ የሚገኘው ትርፍ የሚያመለክተው በመጋቢት ወር ውስጥ የደብረ ዘይት በዓል የሚከበርበትን ቀን ነው።

የትንሣኤው በዓል በሚያዝያ ወር ቢውል 2 ተደምሮበት የሚገኘው ውጤት የሚያመለክተው የደብረ ዘይቱ በዓል በመጋቢት ወር ውስጥ የሚከበርበትን ቀን ነው።

| | |
|---|---|
| ምሳሌ:- የትንሣኤ በዓል | 11 |
| የሚደመር | 2 |
| የደብረ ዘይት በዓል መጋቢት | 13 ቀን |

<u>ሆሣዕና</u>:- የሆሣዕና በዓል የሚከበረው ከትንሣኤ በዓል አንድ ሳምንት በፊት ባለው እሑድ ነው።

<u>ጸሎተ ሐሙስ</u>:- የጸሎተ ሐሙስ በዓል የሚከበረው ከትንሣኤ በዓል በፊት ባለው ሐሙስ ነው።

<u>ስቅለት</u>:- የጌታችን ስቅለት መታሰቢያ በዓል የሚከበረው ከትንሣኤ በዓል በፊት ባለው ዓርብ ነው።

<u>ርክበ ካህናት</u>:- የትንሣኤ በዓል በመጋቢት ወር ውስጥ ቢውል በዕለቱ ቍጥር ላይ 24 ተደምሮበት 30 ከተቀነሰለት በኋላ የሚገኘው ትርፍ የሚያመለክተው ርክበ ካህናት በሚያዝያ ወር የሚውልበትን ቀን ነው።

የትንሣኤው በዓል በሚያዝያ ወር ውስጥ ቢውልና በቀኑ ቍጥር ላይ 24 ተደምሮበት ውጤቱ ከ30 ባይበልጥ ርክበ ካህናት በሚያዝያ ወር ውስጥ ይው ላል። ውጤቱ ግን ከ30 ቢበልጥ 30 ተቀንሶለት ተራፊው ቍጥር የሚያመ ለክተው ርክበ ካህናት በግንቦት ወር ውስጥ የሚውልበትን ቀን ነው።

| | |
|---|---|
| ምሳሌ:- የትንሣኤ በዓል | 11 |
| የሚደመር | 24 |
| ድምር | 35 – 30 = 5 |

የ1990 ዓ.ም ርክበ ካህናት ግንቦት 5 ቀን ይውላል።

<u>ዕርገት</u>:- የትንሣኤ በዓል በመጋቢት ወር ውስጥ ቢውል 9 ተደምሮበት 30 ከተቀነሰለት በኋላ የዕርገት መታሰቢያ በዓል በግንቦት ወር ውስጥ ይውላል።

የትንሣኤው በዓል በሚያዝያ ወር ውስጥ ቢውል 9 ተደምሮበት ውጤቱ ከ30 ያልበለጠ ከሆነ የዕርገት በዓል በግንቦት ወር ይውላል። ከ30 ቢበልጥ ግን 30 ተቀንሶለት የሚተርፈው የሚያመለክተው የዕርገት መታሰቢያ በዓል በሰኔ ወር ውስጥ የሚከበርበትን ቀን ነው።

| | |
|---|---|
| ምሳሌ:- የትንሣኤ በዓል | 11 |
| የሚደመር | 9 |
| ድምር ግንቦት | 20 ቀን የዕርገት በዓል ነው። |

<u>በዓለ ኀምሳ</u>:- የትንሣኤ በዓል በመጋቢት ወር ውስጥ ቢውል በበዓሉ ቀን ቍጥር ላይ 19 ተደምሮበት 30 ከተቀነሰ በኋላ የሚገኘው ውጤት የሚያመለክተው በዓለ ኀምሳ በግንቦት ወር ውስጥ የሚውልበትን ቀን ነው።

የትንሣኤው በዓል በሚያዝያ ወር ቢውል በትንሣኤው በዓል ቀን ላይ 19 ተደምሮበት ከ30 ካልበለጠ በዓለ ኀምሳ በግንቦት ወር ውስጥ ይውላል። ከ30 ቢበልጥ ግን በዓለ ኀምሳ በሰኔ ወር ውስጥ ይውላል።

| | | |
|---|---|---|
| ምሳሌ:- | የትንሣኤ በዓል | 11 |
| | የሚደመረው | 19 |
| | ድምር ግንቦት | 30 ቀን በዓለ ኀምሳ |

<u>ጾመ ሐዋርያት</u>:- የትንሣኤ በዓል በመጋቢት ውስጥ ቢሆን በትንሣኤው በዓል ቍጥር ላየ 20 ተደምሮበት ከሚገኘው ውጤት ላይ 30 ተቀንሶለት የሚተርፈው ቍጥር የሚያመለክተው በግንቦት ወር ውስፕ ጾመ ሐዋርያት የሚጀምርበትን ቀን ነው።

www.ethiopianorthodox.org

የትንሣኤው በዓል በሚያዝያ ወር ውስጥ ቢውል በበዓሉ ቀን ላይ 20 ተደምሮበት የድምሩ ውጤት ከ30 ባይበልጥ ጾመ ሐዋርያት በግንቦት ወር ውስጥ ይጀምራል። ድምሩ ግን ከ30 ቢበልጥ 30 ከተቀነሰለት በኋላ የሚገኘው ትርፍ የሚያመለክተው ጾመ ሐዋርያት በሰኔ ወር ውስጥ ሚውልበትን ቀን ነው።

ምሳሌ:- የ1990 የትንሣኤ በዓል ሚያዝያ 11 ቀን
የሚደመረው 20
ድምር 31 –30 = 1

ስለዚህ ጾመ ሐዋርያት የሚጀምረው ሰኔ 1 ቀን ነው ማለት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የሐዋርያትን ጾም የቀኖች ብዛት ለማወቅ የሚከተለውን ስሌት ይመለከቷል።

የትንሣኤ በዓል በመጋቢት ወር ቢውል የወሩ ቀሪ ተወስዶ 45 ሲደመርበት በድምሩ ውጤት የሐዋርያትን ጾም የቀኖች ብዛት ለማወቅ ይቻላል። የትንሣኤ በዓል በሚያዝያ ወር ቢውል በወሩ ቀሪ ላይ 15 ተደምሮበት የድምሩ ውጤት የሐዋርያትን ጾም የቀኖች ብዛት ያመለክታል።

ምሳሌ :- 30–11 = 19+15 = 34 ቀኖች

## ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር ክብር ሲባል ምን ማለት ነው?
2. እግዚአብሔር ክብሩን የሚያሳየን እኛ በምንፈልገው መንገድ ነውን?
3. ሙሴ እግዚአብሔርን ክብርህን አሳየኝ በሚልበት ጊዜ ምን ማለቱ ነው?
4. በእግዚአብሔር ክብርና በሰው ክብር መካከል ያለው ልዩነት እንዴት ነው?
5. እግዚአብሔር አብዛኛውን ጊዜ ክብሩን የሚገልጠው በምን ምክንያት ነው?
6. ፈርዖን የእግዚአብሔር ቅጣት ሲበዛበት ምን አለ?
7. ቆሬ፣ ዳታንና አቤሮን ያመፁት በምን ምክንያት ነው?
8. እግዚአብሔር ዐመፀኞቹን የቀጣቸው በምን መንገድ ነው?
9. በማግስቱስ ያመፁት እነማን ነበሩ? ምክንያቱስ ምን ነበር?
10. በዚህስ ምክንያት ስንት ሰው ሞተ?
11. መቅሠፍቱስ እንዴት ሊቆም ቻለ?
12. እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ክብር ባስደነገጣቸው ጊዜ ሙሴን ምን አሉት?
13. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአምላክነቱን ክብር ከገለጠባቸው መንገዶች መካከል ምን ምን ይገኙባቸዋል?
14. ሰው ለእግዚአብሔር ክብር መስጠት የሚገባው ለመሆኑ ሁለት ምሳሌዎችን አቅርብ?
15. መንፈሳዊ በዓላት መከበር የተጀመረው መቼ ነው?
16. ከመጽሐፍ ቅዱስ ሌላ ስለ መንፈሳዊ በዓላት መከበር የሚናገሩ ሁለት መጻሕፍት ምንና ምን ናቸው?
17. መንፈሳውያን በዓላትን በማክበር ምን ጥቅም እናገኛለን?
18. በዓላቱን የምናከብርባቸው ቀኖች እንዴት ይወሰናሉ?
19. መንፈሳዊ በዓላቸውን እኛ በምናከብርበት ቀን የሚያከብሩ እነማን ናቸው?
20. በዓመቱ ውስጥ ያሉት አራት ዐበይት የዘመን ክፍሎች እነማን ናቸው?
21. ዘመነ ጽጌ ከመቼ እስከ መቼ ነው? እርሱስ የሚያመለክተው ምንን ነው?
23. ዘመነ አስተምሕሮ ምንን ያመለክታል? እርሱስ ከመቼ እስከመቼ ነው?
24. በዘመነ ስብከት ውስጥ ስንት እሑዶች አሉ?
25. መፀው ከመቼ እስከ መቼ ነው?
26. እርሱስ ስንት ንኡሳን ክፍሎች አሉት?
27. ዘመነ ልደት ማለት ከመቼ እስከ መቼ ነው?
28. መታሰቢያነቱስ ለምን ለምን ነው?
29. ዘመነ አስተርእዮ ከመቼ እስከ መቼ ነው?



30. መታሰቢያነቱስ ለምን ለምን ነው?
31. ዘመነ መርዓዊ ከመቼ እስከ መቼ ነው?
32. ጊዜው የምን መታሰቢያ ነው?
33. ሐጋይ ወይም በጋ ከመቼ እስከ መቼ ነው?
34. እርሱስ በስንት ንኡሳን ክፍሎች ይከፈላል?
35. ዘመነ ዐቢይ ጾም ከመቼ እስከ መቼ ነው?
36. ዘመነ ትንሣኤ ከመቼ እስከ መቼ ነው?
37. ዘመነ ጰራቅሊጦስ ከመቼ እስከ መቼ ነው?
38. ጸደይ ወይም በልግ ማለት ከመቼ እስከ መቼ ነው?
39. ጸደይ ስንት ንኡሳን ክፍሎች አሉት?
40. ክረምት ከመቼ እስከ መቼ ነው?
41. ክረምት ስንት ንኡሳን ክፍሎች አሉት?
42. ዘመነ ዮሐንስ የሚባለው ከመቼ እስከ መቼ ነው?
43. ዘመነ ፍሬ የሚባለው ከመቼ እስከ መቼ ነው?
44. ዘመነ መስቀል የሚባለው ከመቼ እስከ መቼ ነው?
45. ከሰኔ 26 እስከ ሐምሌ 18 ቀን ያለው ጊዜ የምን ጊዜ ተብሎ ይጠራል?
46. ከሐምሌ 19 እስከ ነሐሴ 9 ቀን ያለው ጊዜ የምን ወቅት ነው?
47. ከነሐሴ 10 ቀን ጀምሮ እስከ ነሐሴ 27 ያለው ጊዜ ምን የሚደረግበት ጊዜ ነው?
48. ከነሐሴ 28 እስከ ጳጉሜን 5/6/ ምን ይባላል?
49. አሥርቆት ማለት ምን ማለት ነው?
50. ለሠርቀ ሌሊት አወጣጥ የሚያገለግሉ ምን ምን ናቸው?
51. ለጨረቃ አወጣጥ የሚያገለግሉ ምን ምን ናቸው?
52. የንግሥ በዓል ማለት ምን ለማለት ነው?
53. የንግሥ በዓል የሚከበርባቸው ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?
54. የኢትዮጵያና የግብጽ አብያተ ክርስቲያን የዘመን አቈጣጠራቸው በምን፣ በምን ላይ የተመሠረተ ነው?

# ምዕራፍ 2

# መጽሐፍ ቅዱስ

## ብሉይ ኪዳን

<u>አንደኛ መጽሐፈ ሳሙኤል</u>:- ይህ መጽሐፍ ከሰባው ሊቃውንት ትርጓሜ በፊት ከሁለተኛው መጽሐፈ ሳሙኤል ጋር አንድ መጽሐፍ ነበር። ሰባው ሊቃውንት ግን ለሁለት ከፍለውታል። መጽሐፉ በሳሙኤል ስም የተጠራበት ምክንያት አንደኛ መጽሐፉ በሳሙኤል የሕይወት ታሪክ ስለሚጀምርና ሁለተኛ ደግሞ በአብዛኞች ምሁራን እንደታመነበት የመጽሐፉ ጸሐፊ ነቢዩ ሳሙኤል ስለሆነ ነው። በዚሁ በአንደኛው መጽሐፍ ም.25 ላይ ሳሙኤል መሞቱ ስለተገለጠ ከዚያ በኋላ ያለውን ክፍል ሳሙኤል ጽፎታል ለማለት አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ መጽሐፉን የጻፈው ሳሙኤል ብቻው አለመሆኑን ለመገንዘብ በመጀመሪያው ዜና መዋዕል ም:29 ቍጥር 29 ይመለከቷል። «የንጉሡም የዳዊት የፊተኛውና የኋለኛው ነገር እነሆ፣ በባለ ራእዩ በሳሙኤል ታሪክ፣ በነቢዩ በናታን ታሪክ፣ በባለ ራእዩም በጋድ ታሪክ ተጽፎአል።» ይህም ማለት 2ኛውን የመጽሐፈ ሳሙኤል መጽሐፍ የጻፉት ሦስቱ ነቢያት ናቸው ማለት ነው።

እንዲያውም በሰባው ሊቃውንት መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ መጨረሻ ላይ «የመጀመሪያውን መጽሐፈ ሳሙኤል፣ ሳሙኤል ጀመረው ናታንና ጋድም ፈጸሙት ይላል። በሁለተኛው መጽሐፈ ሳሙኤል መጨረሻ ላይ «ሁለተኛው መጽሐፈ ሳሙኤል ናታንና ጋድ ፈጸሙት ይላል።

ይህ መጽሐፍ ሠላሳ አንድ ምዕራፎች ያሉት ሆኖ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

www.ethiopianorthodox.org

መጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ አራት ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የአንድ ኤፍሬማዊ ቤተ ሰብ አጭር ታሪክ ተነግሮአል። ይህም ቤተሰብ በየዓመቱ የእግዚአብሔር የምስክሩ ድንኳን ወደሚገኝበት ወደ ሴሎ እየሄደ መሥዋዕት በመሠዋት የሃይማኖት በዓል ያከብር ነበር። ይህ ሕልቃና የተባለው ኤፍሬማዊ ሁለት ሚስቶች ነበሩት። የአንደኛዋ ስም ሐና ሲሆን የሁለተኛዋ ስም ፍናና ይባል ነበር። ፍናና ልጆች ነበሩአት። ሐና ግን መኻን ስለነበረች ልጅ አልወለደችም ነበር። ሐና መኻን በመሆንዋ በጣም ታዝን ነበር። እንደልማዳቸው ወደ ሴሎ ሄደው በነበረበት በአንዱ ጊዜ ሐና ወደ እግዚአብሔር ቤት ሄዳ በመጸለይ ስለት ተሳለች። ስለቱም፥ እግዚአብሔር ወንድ ልጅ የሰጣት እንደሆነ ሕይወቱን በሙሉ ለእግዚአብሔር የተለየ አገልጋይ ሆኖ እንዲኖር የምትሰጠው መሆንዋን የሚገልጥ ቃል ኪዳን ነው። በመጀመሪያ ሲያያት የሰከረች የመሰለው ካህኑ ዔሊ፥ ሁናቴዋን ከገለጸችለት በኋላ «በደኅና ሂጂ፤ የእስራኤል አምላክ የለመንሽውን ልመና ይስጥሽ» በማለት በጸሎትዋ ረዳት። ከዚያ በኋላ ጸሎትዋ ተቀባይነትን አግኝቶ ወንድ ልጅ ወለደች። እርሱም ነቢዩ ሳሙኤል ነው። ከዚያም ከፍተኛ ትርጉም ባለው መዝሙር እግዚአብሔርን አመሰገነች። በዚሁ ክፍል ውስጥ ሳሙኤል ጡት መጥባት ባቆመበት ጊዜ እናቱ ለእግዚአብሔር አገልግሎት አሳልፋ የሰጠችው መሆኑ ይገኝበታል። ይህንንም ያደረገችው አስቀድማ ለእግዚአብሔር ቃል ገብታ ስለነበረ ሳሙኤል በሕይወት ዘመኑ ሁሉ የእግዚአብሔር አገልጋይ ይሆን ዘንድ የስለት ቃልዋን ለመፈጸም ነው።

እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ ለሳሙኤል ገና በልጅነቱ የተገለጠለት በዔሊና በቤተ ሰቡ ላይ የሚደርሰውን ቅጣተ በመግለጥ ነው። ይህም ለሳሙኤል የተገለጠለት ትንቢታዊ ራእይ በአፋጣኝ የደረሰው በእስራኤላውያንና በፍልስጥኤማውያን መካከል በተደረገው ጦርነት ነው። በጦርነቱ ላይ እስራኤላውያን ተሸነፉ፤ የካህኑ የዔሊ ሁለት ልጆች ተገደሉ፤ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦትም ተማረከች። ይህም የሆነው ሁለቱ የዔሊ ልጆች ሖፍኒና ፊንሐስ በእግዚአብሔር ቤት ካህናት ሆነው በሚያገለግሉበት ጊዜ ብዙ አሳፋሪና አሳዛኝ ተግባሮችን በመፈጸም እግዚአብሔርን በድለው ስለነበረ ነው። ዔሊም የጦርነቱ ውጤት በተነገረውና የቃል ኪዳኑ ታቦት መማረክ በሰማ ጊዜ ከተቀመጠበት ወንበር ተገልብጦ ወደ ኋላው ወደቀ፤ ዐንገቱም ተሰብሮ ሞተ። ነፍሰ ጡር የነበረችው የፊንሐስ ሚስትም የባልዋና የዐማትዋን መሞትና የቃል ኪዳኑም ታቦት መማረክ በሰማች ጊዜ እግዚአብሔር ከእስራኤል ተለየ በማለት በወሊድ ላይ እያለች ሞተች።

ሁለተኛው ክፍል ከምዕራፍ አምስት እስከ ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የእግዚአብሔርን ታቦት ማርከው በወሰዱት ወገኖች ላይ የደረሰው መቅሠፍትና እነርሱም ታቦቱን ከስጦታ ጋር በክብር ወደ እስራኤል ልጆች ድንበር የላኩ የመሆናቸው ታሪክ ይገኝበታል። እግዚአብሔርም ሳሙኤልን ለእስራኤል ሕዝብ መሪና ነቢይ አድርጎ ሾሞታል። ሳሙኤልም ሕዝቡ የጣዖት አምልኮን ትተው እግዚአብሔርን በማምለክ እንዲጸኑ ብዙ ጥረት አድርጓል። እርሱ በሸመገለ ጊዜ ኢዩኤልና አብያ የተባ ሉትን ሁለቱን ልጆቹን በእስራኤል ላይ ፈራጆች እንዲሆኑ ሾሞአቸው ነበር። ይሁን እንጂ እነርሱ የአባታቸውን አርአያነት አልተከተሉም። የገንዘብ ጥቅም ፈላጊዎች ሆነው ጉቦ በመቀበል ፍርድን ያጣምሙ ጀመር። በዚህም ምክንያት የእስራኤል ልጆች ወደ ሳሙኤል ቀርበው በአካባቢአቸው እንዳሉ ሕዝቦች ንጉሥ እንዲያነግሥላቸው ጠየቁት። ሳሙኤል የሕዝቡን ጥያቄ ለመቀበል አመንትቶ ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሳሙኤልን የሕዝቡን አሳብ ተቀብሎ ንጉሥ እንዲያነግሥላቸው አዘዘው። ይሁን እንጂ የሚገዙአቸው ነገሥታት ወደፊት በእነርሱ ላይ ምን እንደሚፈጽሙባቸው በመግለጥ በብርቱ እንዲ ያስጠነቅቃቸው ነገረው። ከዚያ በኋላ ከብንያም ነገድ የነበረውን ሳኦልን ቀብቶ አነገሠላቸው። ሳኦልንም ካነገሠላቸው በኋላ የእስራኤልን ልጆች ሰብስቦ መሰነባበቻ መሰል ንግግር አደረገላቸው።

ሦስተኛው ክፍል ከምዕራፍ 13 እስከ ምዕራፍ 31 ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ በእስራኤል ላይ አርባ ዓመት የነገሠው የአል ታሪክ ይገኝበታል። እንዲሁም ያደረጋቸው ጦር ቶች፥ የታዘዛቸውን የእግዚአብሔር ትእዛዞች አለ መክበሩ፥ በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር እንደናቀውና በእርሱ ቦታ ንጉሥ ዳዊት የመቀባቱ ታሪክ የሚገኘው በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ነው። ዳዊት ከነገደ ይሁዳ የቤተልሔሙ የእሴይ ልጅ ነበር። በሰውነቱ ግዙፍ የነበረውን ጎልያድን ዳዊት በወንጭፍ ገድሎት ዝነኛ በሆነ ጊዜ ሳኦል ቀናበት። ከዕለታት አንድ ቀን በእ ቦታ ተተክቶ ይነግሣል ብሎ በማሰብ ቀናበት። በዚህም ምክንያት ሊገድለው ፈለገ። ሳኦል እግዚአብሔር በተለየው ጊዜ በዐይንዶር ወደም ትገኘው መናፍስት ጠሪ ዘንድ ሄዶ ምክ



ጠይቆአል። ሳሙኤል ከሞተ በኋላ ለሳኦል ተገልጦለት ገሥጾት እርሱና ልጆቹ እንደሚሞቱ ነገሮታል። ሳኦልም ሳሙኤል በነረገው መሠረት እርሱ ከነልጆቹ በጦርነት ላይ ተገድለዋል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሁለት የተለያዩ ታሪኮች አሉ። አንዱ የከፉዎች ሰዎች ታሪክ ሲሆን፥ ሁለተኛው የደጋግ ሰዎች ታሪክ ነው።

ክፉዎች ሰዎች ሲባል እንደ ዔሊ ልጆች ያሉ፥ እንደ ሳሙኤል ልጆች ያሉና፥ እንደ ሳኦል ያሉ፥ ስማቸው፥ በክፉ ተግባራቸው ምክንያት የተበላሸ ለማለት ነው። ለምሳሌ ሳኦል ሹመቱ ልቡንና ኀይናውን ማረከውና ትዕቢትንና ኀይናቢስነትን፥ አሳድሮበት በእግዚአብሔር ትእዛዛት ላይ ዐመፀ፤ እጆቹንም በንጹሑ በዳዊት ደም ሊቀባቸው ፈለገ። እግዚአብሔር ግን በግፈኞች ላይ ስለሚፈርድ ዙፋኑን ከእርሱ ወስዶ ለዳዊት ሰጠው።

ሁለተኛው ደግሞ የደጋግ ሰዎች ማለት የጻድቃን ታሪክ ሲሆን ከእነርሱም መካከል ሳሙኤልና ዳዊት ይገኙባቸዋል። እነርሱም በትሩፋት ሥራቸው፥ በንጹሕነታቸው፥ በቀጥተኛነታቸውና በጨዋነታቸው፥ በወጣትነት፥ በጐልማሳነት፥ በሙሉ ሰውነትና በሽምግልና ዕድሜ ላሉ ሰዎች ሁሉ የበጎ ተግባር መመሪያ የሆኑ ናቸው። እነርሱንም የሰው ልጆች ሁሉ በምሳሌነት የሚያ ነሡአቸው ናቸው።

## <u>ሁለተኛ መጽሐፈ ሳሙኤል:-</u>

ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው መጀመሪያውና ሁለተኛው መጻሕፍት በአንድ መጽሐፍ የተጠቃለሉ እንጂ ሁለት ስላልነበሩ ለሁለት ከተከፈሉ በኋላ ይህ ሁለተኛውም መጽሐፍ በሳሙኤል እንደተሰየመ ቀርቶአል። ሳሙኤል ከዚህ ከሁለተኛው መጽሐፍ ታሪክ በፊት መሞቱ የተገለጠ ስለሆነ ይኸኛውን መጽሐፍ እርሱ ጽፎታል ለማለት አይቻልም። በሳሙኤል ስም መሰየሙም እርሱ ቀብቶ ያነገሣቸውን የነገሥታት ታሪክ ስለያዘ ነው። በመጀመሪያው የዜና መዋዕል መጽሐፍ ምዕራፍ 29 ቍጥር 29 ላይ እንደተገለጠው ከመጀ መሪያው መጽሐፍ የተወሰነውን ክፍልና ሁለተኛውን መጽሐፍ የጻፉት ጋድና ናታን የተባሉት ነቢያት ናቸው።

መጽሐፉ 24 ምዕራፎች ያሉት ሆኖ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ሊከፈል ይቻላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ ዐሥር ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ዳዊት መናገሻ ከተማውን በኬብሮን በማድረግ በይሁዳ ነገድ ላይ ሰባት ዓመት መንገሡ ተገልጾአል። የቀሩት የእስራኤል ነገዶች ሁሉ በተገዙለት ጊዜ ዋና ከተማውን ወደ ኢየሩሳሌም በማዛወር ለሠላሳ ሦስት ዓመት ነግሦአል። ይህንንም ያደረገው ኢያቡሳውያንን ከጽዮን ተራራ ካስወገደ በኋላ ነው።

የቀሩት የእስራኤል ነገዶች በዳዊት አገዛዝ ሥር የገቡበት ሁናቴ እንደሚ ከተለው ነው:- የኔር ልጅ አበኔር የሳኦል ሠራዊት አለቃ ነበር። ሳኦል ከሞተ በኋላ አበኔር የሳኦልን ልጅ ኢያቡስቴን በመህናይም አነገሠው። ከዳዊት ሠራ ዊትም ጋር እብዙ ጊዜ ተዋጋ። በጦርነቱም መጀመሪያ ላይ የዳዊት የእኅት ልጆችና የሠራዊቱ አዛገሮች የነበሩት የኢዮአብና የአቢሳ ወንድም የነበረው ዐሣሄል ተገደለ። ኢዮአብና አቢሳም የወንድማቸውን ደም ለመበቀል ዐቀዱ።

ከዚህ በኋላ በአበኔርና በኢያቡስቴ መካከል አለመግባባት ተከሠተ። ይህም የሆነው አበኔር በምሥጢር የሳኦል ቁባት ከነበረችው ከሪድፋ ጋር ተኝቶ ስለ ነበረ ነው። ኢያቡስቴ ጉዳዩን ሰለሰማ ስለምን ከአባቴ ቁባት ጋር ተኛህ ብሎ ወቀሰው። አበኔር በጣም ስለተናደደ ከሁዳ መንግሥት ጋር ዕርቅ ለመመሥረትና የእስራኤልን ሕዝብ ሁሉ በዳዊት ሥር ለማድረግ ዐቀደ። ከጥቂቶች ሰዎች ጋር ሆኖም ወደ ኬብሮን በመሄድ ሌሎቹን የእስራኤል ነገዶች ሁሉ በእርሱ መንግሥት ሥር እንዲያደርጉለት ከዳዊት ጋር ስምምነት አደረገ። አበኔር ይህን ለማድረግ ወደ ኬብሮን መጥቶ በሚመለስበት ጊዜ ወንድማማቾቹ ኢዮአብና አቢሳ የወንድማቸውን የዐሣሄልን ደም ለመበቀል ገደሉት። ለአበኔርም በጣም ተለቀሰለት። በተለየም ንጉሥ ዳዊት የዚህ የታላቅ ጦር መሪ መገደል እንደ ወንጀልና እንደ ከሐዲነት ቈጥሮት በጣም አለቀሰለት። ከዚህ በኋላ ሁለት የኢያቡስቴ ወታደሮች ወደ መኝታ ቤቱ ገብተው በመግደል ራሱን ቈርጠው በኬብሬን ወደሚገኘው ወደንጉሥ ዳዊት ይዘውለት ስለመጡ የሚ ሾሙ የሚሸለሙ መሰላቸው። እርሱ ግን እነዚያ ሰዎች በሰላም በአልጋው ላይ የነበረውን ንጉሥ በመግደላቸው የሞት ፍርድ ፈረደባቸውና አስገደላቸው። ከኢያቡስቴም ሞት በኋላ የእስራኤል ነገዶች በሙሉ በዳዊት ግዛት ሥር ተጠቃለሉ። የቃል ኪዳኑንም ታቦት በታላቅ ክብር ለማረፊያ ቦታ ወደ አዘጋ ጀለት ወደ ኢየሩሳሌወም አመጣ። በአካባቢው የነበሩትን ሕዝቦች ሁሉ ድል በመንሣት ግዛቱ ተስፋፍቶ በሁለቱ ወንዞች መካከል ወደ አለው አካባቢ ደረሰ። እርሱም እጅግ ገናና ሆነ።

www.ethiopianorthodox.org

ሁለተኛው ክፍል ከምዕራፍ ዐሥራ አንድ እስከ መዕራፍ ዐሥራ ዘጠኝ ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የዳዊት በኃጢአት ከፍተኛ አወዳደቅ፥ የኦር ዮን ሚስት ከደፈረ በኋላ ለራሱ ሚስት ሊያደርጋት ፈልጎ ባልዋን ኦርዮን በተንኰል በማስገደል እግዚአብሔርን ማሳዘኑ፥ ከዚያ ነቢዩ ናታን በበደሉ ከወ ቀሰው በኋላ የሚደርስበትን ቅጣት የመንገሩ ታሪክ ይገኝበታል። እግዚአ ብሔርም በነቢዩ ናታን አማካይነት ለዳዊት ከነገረው ትንቢት መካከል የሚከተ ለው ይገኝበ ታል:- «አንተ ለእኔ ስላልታዘዝክና የኦርዮን ሚስት ስለ ወሰድህ እነሆ፥ ከቤትህ በሰይፍ የሚገደል አይጠፋም፤ ከቤተሰብህ አንዱ ተነሥቶ ችግር እንዲያደርስብህ የማደርግ መሆኔን በመሐላ አረጋግጥልሃለሁ፤ ሚስቶችህን ወስጄ ለሌላ ሰው በምስጥበት ጊዜ ይህ ነገር እንደሚፈጸም ትገነዘባለህ፤ እርሱም ከሚስቶችህ ጋር በቀን ብርሃን ይገናኛል። አንተ ይህን ኃጢአት በሰውር ሠርተሃል፤ እኔ ግን እስራኤላውያን ሁሉ ይመለከቱ ዘንድ ይህን ነገር የቀን ብርሃን ባለበት በግልጥ አደርጋለሁ» (2ኛ: ሳሙ: ም:12 ቍ: 10–12)።

በዚህም ትንቢት መሠረት በዳዊት ቤት ውስጥ ችግሮች ተፈራርቀው ደረሱ። የበኵር ልጁ አምኖን እኅቱን ትዕማርን አስገድዶ ክብረ ንጽሕናዋን ደፈረ፤ ልጁ አቤሴሎም የእኅቱን የትዕማርን በግዴታ መደፈር ለመበቀል ወንድሙን አምኖንን ገደለው። አቤሴሎምም ከአባቱ ቅጣት ለማምለጥ ወደ ሌላ አገር ሸሸ። ከዚያም በኢዮአብ ዘዴ ከአባቱ ጋር ታረቀ። አቤሴሎም በዚህ ብቻ አላበቃም። ዐመፅ አስነሥቶ በአባቱ ላይ ዘመተ። አባቱንም አባርሮ በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ። ይህም አልበቃው ብሎ ከአባቱ ቁባቶች ጋር ተኛ። አቤሴሎም ብዙ ክፉ ነገሮችን የሚያደርገው በአኪጦፌል ምክር ነበር፤ የዳዊት ወዳጅ የነበረው ሑሻይ ግን ተቃራኒ ምክር በመስጠት ያዘናጋው ነበር። በዚህም መሠረት የዳዊት ሠራዊት በአቤሴሎም ሠራዊት ላይ ድልን ተቀዳጅቶ፥ አቤሴ ምም ሞቶ ዳዊት ወደ ቀደመ ክብሩ ተመለሰ። ይህም የሆነው በንስሓ ራሱን አዋርዶ የእግዚአብሔርን ምሕረት ስለ ተማጸነ ነው።

ሦስትኛው ክፍል ከምዕራፍ ኻያ እስከ ምዕራፍ ኻያ አራት ድረስ ነው። በዚህም ክፍል የቢክሪ ልጅ ሺባዕ በዳዊት ላይ ዐመፅ ማስነሣቱና እርሱም በአቤልቤትማዕካ ከተማ በአንዲት ብልኀተኛ ሴት አማካይነት መገደሉ፥ ኢያሱና የእስራኤል ልጆች ከገባዖን ሰዎች ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን ሳኦል በማፍረሱ በእስራኤል ላይ ለሦስት ዓመት ጽኑ ረሀብ የመምጣቱ ታሪክ ይገኝበታል።

ዳዊት ስለ ራቡ ጉዳይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በጠየቀ ጊዜ ሳኦል ቃል ኪዳንን አፍርሶ የገባዖንን ሰዎች በመፍጀቱ ምክንያት መሆኑ ተነገረው። ከዚያ በኋላ ዳዊት የገባዖንን ሰዎች ጠርቶ የእስራኤልን ሕዝብ ትመርቁ ዘንድ በተፈጸመባችሁ በደል ምን ካሣ ልክፈላችሁ ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም ብርና ወርቅ አንፈልግም፤ ከእስራኤልም ወገን ማንንም መግደል አንፈል ግም፤ ነገር ግን ሊያጠፋን ተነሥቶ በነበረው በሳኦል ምክንያት ከእርሱ ተወላጆች ሰባት ወንዶች ይሰጡንና እንስቀላቸው ብለው ጠየቁ። ዳዊትም በገባዖን ሰዎች ጥያቄ መሠረት ሰባት ከሳኦል የተወለዱ ወንዶችን ሰጥቶአቸው ከሰቀሉአቸው በኋላ የራቡ ቅጣት ተነሣላቸው። እንዲሁም ዳዊት የሕዝብ ቈጠራ በማድረጉ እግዚአብሔር ስለተቈጣበት በቸነፈር ሰባ ሺህ ሰዎች አለቁ።

<u>አንደኛ መጽሐፈ ነገሥት:-</u> የአንደኛና የሁለተኛ መጽሐፈ ነገሥት ጸሐፊ ማን እንደሆነ በእርግጠኛነት አይታወቅም። ከሰባው ሊቃውንት ትርጉም በፊት አንደኛና ሁለተኛ መጽሐፈ ነገሥት አንድ እንጂ ሁለት መጻሕፍት አልነበሩም። በተልሙድ ሰዎች እምነት ጸሐፊው ነቢዩ ኤርምያስ ነው። አንዳ ንድ ሰዎች እንደሚያስቡት ደግሞ ሰሎሞንና ሕዝቅያስ የዘመነ መንግሥታ ቸውን ታሪክ ጽፈዋል፤ ኢሳይያስ፥ ዒዶና ኤርምያስ የዘመናቸውን ታሪክ ጽፈዋል (2ኛ:ዜ:መ: ም:9 ቍ:29፥ ም:12 ቍ:15፥ ም13 ቍ:22)። በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት ዋነኞች ጉዳዮች ስለ ንጉሥ ሰሎሞን፥ የይሁዳ ነገሥታት ዜና መዋዕልና የእስራኤል ነገሥታት ዜና መዋዕል ናቸው። በእነዚህ በሁለቱ የነገሥት መጻሕፍትና በሁለቱ የዜና መዋዕል መጻሕፍት መካከል ያለው ልዩነት በግልጽ መታወቅ ይኖርበታል። ሁለቱን የዜና መዋዕል መጻ ሕፍት የጻፈው ከባቢ ሎን ምርኮ በኋላ ዕዝራ ነው። መጽሐፈ ነገሥት ከሌሎቹ መጻሕፍት ሁሉ ጋር አብሮ ጠፍቶ ነበር።

አንደኛው መጽሐፈ ነገሥት ኻያ ሁሉት ምዕራፎች ያሉት ሆኖ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ ዐሥር ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ዳዊት በተናዘዘው መሠረት ሰሎሞን የአባቱን ዙፋን የመውረሱ ታሪክ ይገኝበታል።



ሰሎሞንም እንደነገሠ በአባቱ ጠላቶች ላይ የበ ቀል እርምጃ ወስዶአል። በተለየ የተበቀላቸውም ያለዳዊት ትእዛዝና ፍላጎት የጦር መሪዎች የነበሩትን የኔርን ልጅ አበኔርንና የዩቴርን ልጅ ዐማሳን የገደላ ቸውን የዳዊት የጦር አዛዥ የነበረውን ኢዮአብን፥ በአቤሴሎም ዐመፅ ጊዜ እየተከታተለ ዳዊትን የሰደበውን ብንያማዊውን የጌራን ልጅ ሺምዒን፥ የአባቱን ሚስት ሱናማይቱን አቢሻግን ሊያገባ የፈለገውን አዶንያስን በሞት በመቅጣት ሲሆን ካህኑን አብያታርን ደግሞ አዶንያስን ለማንገሥ ከነ ኢዮአብ ጋር ተባብሮ ስለነበረ ከክህነቱና ከመኖሪያው በማባረር ቀጥቶታል። የሰሎሞንም ጥበበኛነት ለሁለቱ የሕፃናት እናቶች በሰጠው የፍርድ ብይን ገልጽ ሆኖ ታይቶአል። በጥበቡም ያልሞተው ልጅ እናት የትኛዋ እንደሆነች ለማወቅ ችሎአል።

ከዚያም የሰሎሞን ገናናነት፥ ክብሩ፥ የሠራዊቱ፥ የፈረሶቹ፥ የሠረገላዎቹ ብዛት፥ የቤቱ ምግብ፥ ለቤተ መቅደስ ሥራ የነበረው ትጋት፥ ከቤተ መቅደ ሱም ሥራ ጋር በተያያዘ ጌጡ፥ ቅርጾቹ ያንንም ለመሥራት የተሰለፉት ሰዎች ብዛት፥ ከዚያም ሰሎሞን ለመጀመሪያ ጊዜ በመሠዊያው ላይ ያቀረበው ቍር ባን፥ በምረቃው ቀን ያቀረበው አስደናቂ ጸሎት፥ ያዘጋጀው የአምልኮ ሥር ዓት፥ የንግሥተ ሰባ ጕብኝትና ታላቅነቱን፥ ብልጽግናውን፥ ጥበበኛነቱን የመገንዘብዋ ታሪክ ይገኝበታል። በዘመኑ የነበሩት ነቢያት ናታን፥ አኪያና ዒዶ ናቸው።

ሁለተኛው ክፍል ምዕራፍ ዐሥራ አንድ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የሰሎሞን ከፍተኛ አወዳደቅና ጣዖታትን የማምለኩ ታሪክ ይገኝበታል። ከዚህ በኋላ በእርሱ ላይ ዐመፀኞች ተነሡበት። በተለየም እግዚአብሔር ከኤፍሬም ነገድ የነበረውን ኢዮርብዓምን በሰሎሞን ላይ አስነሣበት። ይህም ከተቀጣባቸው ቅጣቶች አንዱና የመጀመሪያው ክፍል ነው። በእስራኤል ላይ የነገሠበት ዘመን አርባ ዓመት ነው። ከአወዳደቁ በኋላ ስላለው የእርሱ ሁኔታ የተለያዩ አስተ ያቶች አሉ። አንድ አስተያየት፥ ሰሎሞን እስከሞተበት ቀን ድረስ በኃጢአቱ ቀጠለ የሚለው ሲሆን፥ ሌላው አስተያየት ደግሞ ንስሓ ገብቶ ወደ አምላኩ በመመለስ ከመሞቱ በፊት ራሱንና እንደርሱ ያሉ ሰዎችን የሚገሥጽበትንና የሚወቅስበትን መጽሐፈ መክብብን ጽፎአል ይላሉ። ይህን መጽሐፍ ያጠናቀቀውም ልክ ከመሞቱ በፊት ነው ይላሉ።

ሦስተኛው ክፍል ከምዕራፍ ዐሥራ አንድ እስከ ምዕራፍ ኻያ ሁለት ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የሰሎሞን ልጅ ሮብዓም መንገሡና ከአስተሳሰብና ከአነጋገር ደካማነቱ የተነሣ መንግሥቱ ለሁለት የመከፈሉ ታሪክ ይገኝበታል። ለእርሱም የቀሩለት የይሁዳና የብንያም ነገዶች ብቻ ናቸው። የቀሩት ነገዶች ግን በአባቱ ላይ ዐመፅ ላስነሣው ለኢዮርብዓም ሆኑ። ኢየሩሳሌም የይሁዳ መንግሥት መናገሻ ስትሆን የእስራኤል መንግሥት ዋና ከተማ በመጀመሪያ ቤቴል፥ ከዚያ ቲርጻ፥ በመጨረሻም ሰማርያ ሆነች። በዚህም ክፍል ውስጥ ስለ አራት የይሁዳ ነገሥታት ተነግሮአል። ከእነርሱም የመጀመሪያው የሰሎሞን ልጅ ሮብዓም ነው። የአያቱን መንገድ ከመከተል ይልቅ እርሱና ሕዝቡ ጣዖትን ስላመለኩ እግዚአብሔር ቀጣቸው። እግዚአብ ሔርም በእነርሱ ላይ የግብጹን ንጉሥ ሺሻቅን አስነሣባቸው። ይህም ሺሻቅ ኢየሩሳሌምን በወታደሩ ብዛት ልክ እንደ አንበጣ ወርሮ ከተማይቱንና ቤተ መቅደሱን ዘረፈ። በዘመኑ የነበረውም ነቢይ ሸማዕያ ነበር። ሮብዓምም የነገሠበት ዘመን ዐሥራ ሰባት ዓመት ነው። ከእርሱ ቀጥሎ የነገሠው ልጁ አቢያ ነው። የእርሱም ጠባይና ተግባር ልክ እንደ አባቱ ነበር። ሦስተኛ የነገሠው አሳ ነው። እርሱም አርባ አንድ ዓመት የነገሠ፡ ደግና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጻሚ ነበር። አራተኛው ኢዮሣፍጥ ነበር። እርሱም የአባቱን የአሳን አርኣያነት የሚከተል ደግ ንጉሥ ነበር። በእርሱ ዘመን የነበረው ነቢይ የሐናኒ ልጅ ኢዩ ነበር። እርሱም የነገሠው ለኻያ አምስት ዓመት ነው።

በዚህ ክፍል ውስጥ የስምንት የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ይገኝበታል። ከእነርሱም መጀመሪያው የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ነው። ይህ ኢዮርብዓም በሁዳ መንግሥት ላይ በማመፅ ቤቴልን መናገሻ ከተማው አድርጎ በዐሥሩ የእስራኤል ነገድ ላይ የነገሠው ነው። የእስራኤል ልጆች ለአምልኮ ሥርዓት ወደ ኢየሩሳሌም የሄዱ እንደሆነ ስሜታቸው ተለውጦ ያምፁብኛል ብሎ ስለሰጋ ሁለት የወርቅ ጣዖቶችን በማሠራትና በተለያዩ ቦታዎች በመትከል ሕዝቡ እንዲሰግድላቸው አዘዘ። ከሌዊ ወገን ያልሆኑትን ሰዎች ካህናት አድርጎ በመሾም ጣዖቶቹን እንዲያገለግሉ ፈቀደ። ይህንንም ያደረገው አስቀድሞ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ ችላ በማለት ነው። ይህንኑ ያሠራውን ጣዖት ለማስመረቅ በዓል ባደረገበት ጊዜ አንድ የእግዚአ ብሔር ሰው ከይሁዳ ተልኮ እንዲገሥጸውና ኃጢአተኛነቱን እንዲገልጽለት ሄዶ ነበር። ያም የእግዚአብሔር ሰው ተግሣጹንና ትንቢቱን በኢዮርብዓምና በሕዝቡ ፊት በተናገረ ጊዜ ኢዮርብዓም እጁን ዘርግቶ ያዙት አለ። እጁ እንደተዘረጋ ደርቆ በመቅረቱ ወደ እግዚአብሔር



www.ethiopianorthodox.org

እንዲጸልይለት ነቢዩን ለመነውና ከጸለየለት በኋላ ተመለሰለት። ለነቢዩ ንግግር እውነተኛነት ማስረጃ ይሆን ዘንድ ኢዮርብዓም ያሠራው መሠዊያ ተሰባብሮ ወደቀ፤ ዐመዱም ተበተነ። ኢዮርብዓም እነዚህን ሁሉ ሁናቴዎች ከተመለከተ በኋላ ቢጋብዘው ያ ነቢያ እህል እንዳይበላ የታዘዘ መሆኑን ገልጾለት በመጣበት ሳይሆን በሌላ መንገድ ተመልሶ ወደ አገሩ ሄደ። ነገር ግን በቤቴል የነበረ ሌላ ሽመግሌ ነቢይ አታልሎት ከእርሱ ጋር ምግብ በመብላትና ውሃ በመጠጣት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስላፈረሰ በመንገዱ ላይ ጠብቆ አንበሳ እንዲገድለው ተደረገ። እግዚአብሔር ኢዮርብዓምን በሕይወት ዘመኑ ከቀጣበት መንገድ አንዱ እርሱ በሕይወት እያለ አንድ ልጁ እንዲሞትበት መደረጉ ነው። እርሱም በእስራኤል ላይ ኻያ ሁለት ዓመት ከነገሠ በኋላ ሞተ። በእርሱም ምትክ ልጁ ናዳብ ለሁለት ዓመት ከነገሠ በኋላ ባዕሻ ገድሎት በቦታው ተተካ። እርሱም የናዳብን ቤተሰብ ሁሉ ገደለ። ባዕሻም በክፉ ተግባሩ ከእርሱ በፊት ከነበሩት የእስራኤል ነገሥታት አይለይም ነበር። በእርሱም ዘመን ኢዩ የተባለው ነቢይ ነበር። የባዕሻም የንግሥ ዘመን ኻያ አራት ዓመት ነው። ባዕሻ ከሞተ በኋላ ልጁ ኤላ ተተካ። ሁለት ዓመት ከነገሠ በኋላ ዚምሪ የተባለው የጦር መኰንን ገደለው። ዚምሪም የባዕሻን ቤተሰብ በሙሉ ገደለ። ዚምሪ ሰባት ቀን ከነገሠ በኋላ ራሱን ገደለ። ከእርሱ ቀጥሎም ዖምሪ ነገሠ። እርሱም ዋና ከተማውን በሰማርያ አድርጎ ለዐሥራ ሁለት ዓመት ነገሠ። ሰባተኛ የዖምሪ ልጅ አክዓብ ነገሠ። እርሱም የሲዶንን ንጉሥ ሴት ልጅ አረማዊትዋን ኤልዛቤልን አግብቶ ነበር። በዚህም ምክንያት የባዓልና የአሽታሮት ጣዖቶችን አምልኮት አስፋፋ፤ ለጣዖቶቹም የአምልኮ ቦታ ሠራላቸው። አክአብ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ነገሥታት ሁሉ አስበልጦ ኃጢአት ሠራ። ለጣዖታቱም አራት መቶ ኀምሳ ካህናትን ሾመላቸው። እነርሱን ሁሉ ግን ነቢዩ ኤልያስ አስገደላቸው። የነገሠውም ኻያ ሁለት ዓመት ነው። በእርሱ ዘመን የነበሩት ነቢያት ኤልያስ፥ ኤልሳዕና የይምላ ልጅ ሚክያስ ናቸው። እርሱ ከሞተ በኋላ የነገሠው አካዝያስ ነው። እርሱም የአባቱን የአክዓብንና የእናቱን የኤልዛቤልን መጥፎ አርአያነት እየተከተለ ለሁለት ዓመት ነገሠ።

ሁለተኛው መጽሐፈ ነገሥት:- ይህ መጽሐፍ ኻያ አምስት ምዕራፎች ያሉት ሆኖ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ነው።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ ዐሥራ ሰባት ድረስ ነው። ይህ ክፍል እስራኤላውያን በአሦራውያን እስከ ተማረኩበት ባለው ጊዜ ስለ ይሁዳና ስለ እስራኤል መንግሥታት የሚናገር ነው።

ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከምዕራፍ ዐሥራ ስምንት እስከ ምዕራፍ ኻያ አምስት ድረስ ነው። ይህ ክፍል ናቡከደነፆር ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን አጥፍቶ ሕዝቡን በምርኮ ወደ ባቢሎን እስከወሰደበት ጊዜ ድረስ የነበረውን ሁናቴ የሚገልጥ ነው። የይሁዳ ነገሥታትም ዐሥራ ስድስት ናቸው። ከእነርሱም የመጀመሪያው ኢዮራም ነው። እርሱም የኢዮሳፍጥ ልጅ ነው። የእስራኤልን ንጉሥ የአክዓብን ልጅ አግብቶ ነበር። ወንድሞቹን ሁሉ ገደላቸው። ኤልያስ በእሳት ሠረገላ ወደ ሰማይ ከተወሰደ በኋላ ለኢዮራም ወቀሳና የተግሣጽ ደብዳቤ ልኮለታል። (2ኛ:ዜ:መ:ም:21ቍ:12) ኢዮራም ከሞተ በኋላ ልጁ አካዝያስ በእርሱ ተተክቶ ነገሠ። አካዝያስም እንደ አክዓብ ቤተሰብ ኃጢአት በመሥራት እግዚአብሔርን አሳዘነ። እርሱም አንድ ዓመት ብቻ ከነገሠ በኋላ ከኢዮራም ቀጥሎ የነገሠው ኢዩ ገደለው። ከአካዝያስ ቀጥሎ እናቱ ዐታልያ ለስድስት ዓመት ነገሠች። እርስዋም የነገሥታትን ዘሮች ሁሉ ገደለች። ከነገሥታቱ ልጆች ኢዮአስ ብቻ አክስቱ ስለሸሸገችው ከመገደል ተረፈ። በካህኑ ዮዳሄ እርዳታ በዐታልያ ላይ ኢዮአስ እንዲነግሥ ተደርጎ ዐታልያ ተገድላለች። ኢዮአስ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሰባት ዓመት ነበር። ኢዮአስን ሸሽጋ ከሞት ያዳነችው አክስቱ የካህኑ የዮዳሄ ሚስት ነበረች። ኢዮአስ ግን የካህኑን የዮዳሄን ውለታና መንፈሳዊ ትምህርት በፍጥነት ዘንጋና ጣዖት አምላኪ ሆነ። ካህኑ ዮዳሄ ከሞተ በኋላ ኢዮአስ በሌሎች ሰዎች አስተሳሰብና ምክር ባዕድ አምልኮን በተከተለ ጊዜ የዮዳሄ ልጅ ዘካርያስ በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርቶ ንጉሥ ኢዮአስንና ሕዝቡን ወቀሰ። ኢዮአስም የዘካርያስ አባት ካህኑ ዮዳሄ የዋለለትን ውለታና ቅን አገልግሎት በመዘንጋት ፀዘካርያስ ላይ በተደረገው ሤራ ተባባሪ ሆኖ ዘካርያስ በድንጋይ ተወግሮ እንዲገደል አደረገ። በዚህም ባደረገው ክፉ ተግባር ምክንያት በሕመም አልጋ ላይ ሳለ የራሱ አገልጋዮች ገድለውት የዘካርያስን ደም ተበቀሉለት። የነገሠውም ለአርባ ዓመት ነው። ከእርሱ በኋላ ልጁ አሜስያስ ኻያ ዘጠኝ ዓመት ነገሠ። በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን መንገድ ይከተል ነበር፤ በዚህም ምክንያት ኤዶምን ድል ለማድረግ ችሏል። ነገር ግን ከዚያ በኋላ ጣዖትን ስላመለከ በእስራኤል ንጉሥ በዮአስ ተሸነፈ፤ እንዲሁም አባቱን እንደገደሉ፥ አገልጋዮቹ እርሱንም ገደሉት። ከእርሱ



በኋላ ልጁ ዖዝያ ለኀምሳ ሁለት ዓመት ነገሠ እርሱም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጻሚ ነበር። ይሁን እንጂ የካህናትን የአገልግሎት ተግባር በመዳፈሩ ለምጻም ሆነ። በእርሱ ዘመን የነበሩት ነቢያት ኢሳይያስ፥ አሞጽና ሆሴዕ ነበሩ። ከእርሱ በኋላ ልጁ ኢዮአታም ለዐሥራ ስድስት ዓመት ነገሠ። እርሱም ጻድቅና ደግ ሰው ነበረ። በእርሱ ዘመን የነበሩት ነቢያት ኢሳይያስና ሚክያስ ነበሩ። ከእርሱ ቀጥሎ ልጁ አካዝ ለዐሥራ ስድስት ዓመት ነገሠ። እርሱ በጣም ክፉ ነበር። የጣዖት አምልኮን አስፋፋ፤ ወንዶች ልጆቹን ለአምልኮ ጣዖት የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ። በደማስቆ ያየውን ዐይነት የአረማውያን መሥዋዕት መሠዊያ አሠራ። ብዙ ኃጢአትም ስለሠራ በሶርያ ፥ እንዲሁም በእስራኤል ንጉሥ እንዲሸነፍ ተደረገ፤ ከይሁዳም ብዙ ሰዎች ተገደሉ፤ ብዙዎችም ተማረኩ። በእርሱ ዘመን የነበረው ነቢዩ ኢሳይያስ ነው። ከእርሱ ቀጥሎ ልጁ ሕዝቅያስ ለኻያ ዘጠኝ ዓመት ነገሠ። እርሱ በጣም ጻድቅ የሆነ የይሁዳ ንጉሥ ነበር። እርሱ ሊሞት በነበረ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጸልዮ በዕድሜው ላይ ዐሥራ አምስት ዓመት የተጨመረለት ሰው ነው። የአሦር ንጉሥ ሰናክሬብ ኢየሩሳሌምን ለመውረር አስቦ እግዚአብሔር በአንድ ሌሊት አንድ መቶ ሰማንያ ሺህ ወታደሮች የገደለበት በንጉሥ ሕዝቅያስ ዘመን ነው። የእስራኤል መንግሥት የወደቀውና ሕዝቡ በአሦር ንጉሥ በሰልምናሶር ተማርኮ ወደ አሦር የተወሰደው በንጉሥ ሕዝቅያስ ዘመን ነው። ከሕዝቅያስም ቀጥሎ ልጁ ምናሴ ኀምሳ አምስት ዓመት ነገሠ። እርሱ ለአባቱ ደግነት ተቃራኒ በሆነ መንገድ ክፉ ነገርን ሁሉ አደረገ። አባቱ አጥፍቶአቸው የነበሩትን ጣዖቶች ሁሉ መልሶ አመጣ፤ ሰገደላቸው፤ ልጁንም ለሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ አቀረበው። እግዚአብሔርም የአሦርን ንጉሥ አስነሥቶበት ወደ ባቢሎን ተማርኮ እንዲወሰድ አደረገው። ንጉሠ ምናሴም ሥቃዩ ሲበዛበት ንስሐ በመግባት ከልቡ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። እግዚአብሔርም ወደ መንግሥቱ መለሰው (2ኛ:ዜ:መ:ም:33 ቍ:11–13)። ከምናሴ በኋላ ልጁ አሞን ለሁለት ዓመት ነገሠ። እርሱ ክፉ ስለነበረ አገልጋዮቹ ገደሉት። ከእርሱ በኋላ ልጁ ኢዮስያስ ነገሠ። እርሱም በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ስምንት ዓመት ነበር። ለሠላሳ አንድ ዓመት ነግሦአል። በዕድሜው ዘመን ሁሉ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ተግባር ፈጽሞአል። ኢዮስያስ ባዕዳን አማልክትን ሁሉ ከአገሩ አስወግዶአል። እርሱም ከእርሱ በፊት ከነበሩ ነገሥታት ሁሉ በላይ ጻድቅ ነበር። ከግብጹ ንጉሥ ኒኮ ጋር ባደረገው ጦርነት ላይ ተገደለና ልጁ ኢዮአሐዝ ነገሠ። በእርሱም ዘመን የነበሩት ነቢያት ነቢይት ሑልዳ፥ ኤርምያስና ሰፎንያስ ነበሩ። ኢዮአሐዝ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ኻያ ሦስት ዓመት ነበር። የእርሱም ተግባር ከአባቱ ተቃራኒ ነበር። ኤርምያስ ሻሉም ይለዋል (ኤር:ም:22 ቍ11)። ሦስት ዓመት ከነገሠ በኋላ የግብጹ ንጉሥ ፈርዖን ኒኮ ማርኮ ወደ ግብጽ ወስዶት የሞተውም እዚያው ነው። ከእርሱ ቀጥሎ የኢዮስያስ ልጅ ኢዮአቄም ለዐሥራ አንድ ዓመት ነገሠ። እርሱም ኃጢአት በመሥራት እግዚአብሔርን አሳዘነ። ለባቢሎን ንጉሥ ሲገብር ከቈየ በኋላ በማመፁ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር አገሩን ወረረ፤ ሕዝቡን በከፊል በምርኮ አጋዘ። ኢዮአቄም ከሞተ በኋላ ልጁ ኢኮንያን ለሦስት ወር ነገሠ። በእርሱ ዘመን የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ወረረ፤ ቤተ መቅደሱን ዘረፈ፤ ንጉሡንና ቤተሰቡን በምርኮ ወደ ባቢሎን ወሰደ። ከዚያ በኋላ የኢዮስያስ ልጅ ሴዴቅያስ ለዐሥራ አንድ ዓመት ነገሠ። በእርሱ ዘመን ናቡከደነፆር ኢሩሳሌምን ለሦስተኛ ጊዜ ወረራት። የሴዴቅያስንም ዐይን አውጥቶ ወደ ባቢሎን ወሰደው። ንጉሥ ሴዴቅያስ በክፉ ሥራው ልክ እንደ ኢኮንያን እግዚአብሔርን ቅር አሰኘ። እግዚአብሔርም በይሁዳ ሕዝብ ላይ ተቈጥቶ ከፊቱ ያስወገዳቸው በዚሁ ምክንያት ነው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት የእስራኤል ነገሥታት ዐሥራ አንድ ናቸው። ከእነርሱም የመጀመሪያው የአክዓብ ልጅ ኢዮራም ነበር። እርሱም ክፉ ነበር። ከይሁዳ ንጉሥ ከኢዮሣፍጥ ጋር ቃል ኪዳን ገብቶአል። ሞአብን በጦርነት ድል አድርጎአል። የሶርያ ንጉሥ እርሱን ሊደመስሰው ሞክሮ ነበር። ነገር ግን ነቢዩ ኤልሳዕ ተንኰሉን እንደሚያውቅበትና የእስራኤልን ንጉሥ እንደሚያስጠነቅቀው በተገነዘበ ጊዜ ኤልሳዕን ይዞ ሊያስረው ዐቀደ። ነገር ግን እግዚአብሔር ወታደሮቹን ስላሳወራቸው የፈለገውን ለማድረግ አልቻለም። ነቢዩም ወታደሮቹን እየመራ ወደ ከተማ ወሰዳቸው። የሶርያ ወታደሮች በሰማርያ ላይ ከበባ ባደረጉ ጊዜ ሀገሪቱ በጣም ከመራብዋ የተነሣ ሰዎች የአህያ ሥጋና የርግብ ኩስ እስከመብላት ተገድደዋል፤ እንዲሁም ሴቶች የልጆቻቸውን ሥጋ ቀቅሎ እስከመብላት ደርሰዋል። ነገር ግን እግዚአብሔር የሶርያን ሠራዊት ድል ባስመታ ጊዜ እስራኤላውያንን በምርኮ እንዲበለጽጉ አድርጎአል። የሠራዊት አለቃ የነበረው የኒምሺ ልጅ ኢዩ ለንጉሥነት በተቀባ ጊዜ በነቢዩ በኤልያስ ትንቢት መሠረት ኢዮራምንና የአባቱን ዘር በሙሉ ገደለ። ከዚያም በኋላ ኢዩ ለኻያ ስምንት ዓመት

www.ethiopianorthodox.org

ነገሠ። የባዓልን ካህናት በዘዴ ፈጃቸው፤ ይሁን እንጂ የእስራኤልን መንግሥት የመሠረተው ኢዮርብዓም በቤቴልና በዳን ላቆማቸው ጣዖቶች መስገዱን አልተወም። ከእርሱ ቀጥሎ ልጁ ኢዮአካዝ ለዐሥራ ሰባት ዓመት ነገሠ። እርሱም እንደ አባቶቹ ኃጢአት በመሥራት እግዚአብሔርን አሳዘነ። እግዚአብሔር በሶርያ ሠራዊት ድል እንዲመቱ አደረጋቸው። ከእርሱ ቀጥሎ ልጁ ዮአስ ለዐሥራ ስድስት ዓመት ነገሠ። እርሱም እንደ አባቶቹ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረገ። በሶርያ ሠራዊት ድል ተመትቶ በእነርሱ ቀንበር ሥር ወደቀ። ንስሓ በመግባት እግዚአብሔርን በተማጠነ ጊዜ እግዚአብሔር እርሱንና ሕዝቡን ነጻ አወጣቸው። ከእርሱ ቀጥሎ ልጁ ዳግማዊ ኢዮርብዓም ለአርባ አንድ ዓመት ነገሠ። በእግዚአብሔርም ፊት ክፉ አደረገ። ይሁን እንጂ በሶርያ ነገሥታት ተወስዶ የነበረውን ምርኮና አገር አስመለሰ። በእርሱ ዘመን የነበሩ ነቢያት ዮናስ፥ ሆሴዕና አሞጽ ናቸው። ከእርሱ ቀጥሎ ልጁ ዘካርያስ ለስድስት ወር ነገሠ። እርሱም በክፉ መንገድ ሄደ የያቤሽ ልጅ ሻሉም ዘካርያስን ገድሎ አንድ ወር ነገሠ። ሻሉምንም የጋዲ ልጅ ምናሔም ገድሎት ለዐሥር ዓመት ነገሠ። ከእርሱም በኋላ ልጁ ፈቃሕያ ለሁለት ዓመት ነገሠ። ፈቃሕያንም የረማልያ ልጅ ፋቁሔ ገድሎት ለኻያ ዓመት ነገሠ። የአሦር ንጉሥ ተግላት ፐሌሴር ዒዮን፥ አቤልቤትማዕካን፥ ያኖሐን፥ ቁዴሽና ሐጾር ተብለው የሚጠሩትን ከተሞች፥ እንዲሁም የገለዓድን፥ የገሊላንና የንፍታሌምን ግዛቶች በመውረር ሕዝቡን ወደ አሦር ማርኮ የወሰደው ፋቁሔ በነገሠበት ዘመን ነው። የኢላ ልጅ ሆሴዕ ፋቁሔን ገድሎ በእስራኤል ላይ ነገሠ።

# ሐዲስ ኪዳን

ወደ ተሰሎንቄ የተላከ የመጀመሪያ መልእክት:- እንደ አንዳንድ ምሁራን እምነት ሁለቱ የተሰሎንቄ መልእክቶች ከሌሎቹ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክቶች ሁሉ ቀደምትነት ያላቸው ናቸው። እንዲያውም በአንዳንዶች ምሁራን አስተሳሰብ የመጀመሪያው የተሰሎንቄ መልእክት በቀደምትነት ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘ ነው ይባላል። ይህ የመጀመሪያው መልእክት የተጻፈው ብዙ ክርስቲያኖች የጌታችንን ዳግመኛ መምጣት ሳያዩ እንደማይሞቱ፥ ማለት ጌታችን የሚመጣው በእነርሱ የሕይወት ዘመን ይመስላቸው በነበረበት ጊዜ ነው። ከዚያም በላይ የተሰሎንቄ ሰዎች ጌታችን የሚመጣው እነርሱ ባሉበት ዘመን ከሆነ ያ የእግዚአብሔር ጸጋና በረከት ቀድመው የሞቱት ሰዎችስ አያገኙትምን? በማለት የሚያስቡ መሆናቸውን ጢሞቴዎስ ስለገለጠለት ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ ለእነዚህ ለሁለት ጥያቄዎች መልስ ሰጥቶአል። አንደኛ ጌታችን የሚመጣው በድንገት ሳይታሰብ መሆኑንና ሁላቸውም በትጋት እንዲጠባበቁ ያስተምራል (ም:5 ቊ:1–11)።

ጌታችን በሚመጣበት ጊዜ ቀደም ብለው የሞቱት ሰዎችስ እንዴት ይሆናሉ ለሚለው ጥያቄ ደግሞ የሞቱት አስቀድመው እንደሚነሡ ገልጦአል (ም:4 ቊ:13–18)።

ተሰሎንቄ ቀደም ብላ ከታላቁ እስክንድር ግዛቶች አንድ ክፍል ነበረች። በሮማውያን ግዛት መቄዶንያ ለሚባለው ክፍል ዋና ከተማ ነበረች። እስላሞችም ገዝተዋታል፤ በኋላ ግን በግሪኮች እጅ ገብታለች።

በሐዋርያት ዘመን ብዙ የአይሁድ ወገኖች ይኖሩባት ነበር። እዚያ ከነበሩት አይሁድ ብዙዎቹን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ክርስትና መልሶአቸዋል። በዚህም ምክንያት በአይሁድነታቸው ጸንተው የቈዩት ቅዱስ ጳውሎስን አሳደ ዱት፥ ዕርምጃውንም በሌሎች ቦታዎች አደናቀፉበት። እርሱም ከዚያ ተነሥቶ ከሄደ በኋላ ሁናቴአቸውን ለማወቅ ፈልጎ ጢሞቴዎስን ላከ። ጢሞቴዎስም እነርሱ በምን ሁናቴ ላይ እንዳሉ ገለጠለት። እርሱም የመጀመሪያ መልእክቱን የጻፈው እነርሱን ለማጽናትና ለማበረታታት ነው። ይህን ካደረገ በኋላ ነው ስለ ትንሣኤ ሙታን መልስ የሰጣቸው። ከመቸገራቸውና ከመሳደዳቸውም ጋር በእምነታቸው በመጽና ታቸው ያመሰግናቸዋል።

አንዳንድ ምሁራን የተሰሎንቄን መልእክት የጻፈው ቅዱስ ጳውሎስ ብቻውን ሳይሆን ከጢሞቴዎስና ከሲላስ ጋር ነው ይላሉ። ለዚህም ማስረጃ አድርገው የሚያቀርቡት እኔ በማለት ፈንታ እኛ ስለሚል ነው። ይህንኑም በሐዋርያት ሥራ:ም:16፡11–40 እና በዚሁ በአንደኛ ተሰሎንቄ ም:2ቊ.2ላይ ይመለከቷል።

ይህ መልእክት የተጻፈው ከ50 እስከ 52 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ሆኖ አምስት ምዕራፎች አሉት። እነርሱም በአጠቃላይ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ።



የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ ሦስት ድረስ ነው። በዚህም ክፍል ውስጥ ሐዋርያው በጽናታቸው አመስግኖአቸው ይህን በእምነት የመጽናቱን ጸጋና ትዕግሥት ለሰጣቸው አምላክ ምስጋናውን አቅርቦአል። እንዲሁም ከፈታኙ ተቃውሞ መበርታት ጋር በእምነትና በበጎ ተግባር ጸንተው እንዲያድጉ ያበረታታቸዋል።

ሁለተኛው ክፍል ምዕራፍ አራትና አምስት ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ያለው ጉዳይ የትንሣኤ ሙታንና የጌታችን ለፍርድ ወደዚህ ዓለም መምጣት እምነት ነው። በመጨረሻም በንጽሕና በወንድማዊ ፍቅር እንዲኖሩና የወንጌል አገልጋዮችን እንዲያከብሩ በመምከር፥ በጸሎት ያጠናቀቃል።

ወደ ተሰሎንቄ የተላከ ሁለተኛ መልእክት:- በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያለው አብዛኛው ጉዳይ በአንደኛው መጽሐፍ ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ስለትንሣኤ ሙታን በመጀመሪያው መጽሐፍ የተጀመረው ትምህርት በመቀጠል፥ በዚህ በሁለተኛው መጽሐፍ የቀረበውን ሐሳብ በመመልከት የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን የጻፉ የተለያዩ ሰዎች ናቸው ወደ ማለት ውሳኔ የደረሱ ሰዎች አሉ። ጌታችን የሚመጣበት ቀን ደርሶአል ብለው ለተጨነቁት ሰዎች በመጀ መሪያው መጽሐፍ የተሰጠው መልስ እርሱ የሚመጣው ማንም በማያውቀው ጊዜ በድንገት ነው ተብሎ ነበር። በዚህ በሁለተኛው መጽሐፍ ግን ጌታችን የሚመጣበት ጊዜ በምልክት ተገልጾአል። ይኸውም የጥፋት ሰው (ሐሳዌ መሲሕ) አስቀድሞ ይመጣል በማለት ነው።

በዚህ መልእክት የጌታችን መምጫ ጊዜ ከነምልክቱ የተገለጠው አንዳንድ ሰዎች የጌታችን መምጫ ጊዜ ስለደረሰ ሥራም መሥራት አያስፈልግም ብለው እጃቸውን አጣጥፈው መቀመጥ ስለጀመሩ ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ በሁለተኛው መልእክቱ ም:3 ቊ:6–15 ድረስ የመሥራትን ግዴታ ጠንከር ባለ ቋንቋ ሲገልጠው ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብሏል።

ይህም መልእክት ሦስት ምዕራፎች የአሉት ሆኖ አጠቃላይ ትኩረቱ የክርስቶስን መምጫ ጊዜ የተመለከተ ነው። እንዲሁም ምክርና ምስጋና ታክሎበታል።

## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

በአንደኛና በሁለተኛ መጽሐፈ ሳሙኤል ውስጥ ያለው ዋነኛው ጉዳይ የሳኦልና የዳዊት መንገሥና የዘመነ ንግሣቸው ታሪክ ነው። እግዚአብሔር በየጊዜው ለእስራኤላውያን መሪዎችን ያስነሣላቸው ነበር እንጂ ከዘር በሚወረስ የነገሥታት አገዛዝ ወይም ከሕዝብ በተመረጠ መሪ ተገዝተው አያውቁም ነበር። እነዚያም መሪዎች ዓለማዊ አስተዳደርን ያካሄዱ የነበሩ ከመሆና ቸውም ጋር ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ሕግጋት መጠበቁን ለመቈጣጠር የእግዚአብሔር መሣሪያ ዎች ነበሩ።

እስራኤላውያን ግን እግዚአብሔር ለእነርሱ ይጠቅማል ብሎ ከሚሾምላቸው ሰው ይልቅ ንጉሥ እንዲያነግሥላቸው ጠየቁ። እግዚአብሔር ይህ ጥያቄአቸው ደስ ያላሰኘው ቢሆንም እንኳ የሰውን ልጅ በፈጠረው ጊዜ የፈቃድ ነጻነትን ስለሰጠውና እስራኤላውያንም ንጉሥ በመፈለጋቸው ፈቀደላቸው። ይሁን እንጂ አሁን መፍትሔ ያስፈለገው ጉዳይ ለእስራኤላውያን ንጉሥ እንዲያነግሡ ይፈቀድላቸው ወይም አይፈቀድላቸው ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን በማስፈጸም ረገድ ነገሥታቱ የመሣሪያነት ወይም የውክልና ሥራቸውን እንዴት ይቀጥሉ የሚለው ጥያቄ ነው። በተለይም አሁን ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ገዥነት ይልቅ የሰውን ንጉሥነት ስለመረጡ ጉዳዩን የተወሳሰበ ያደርገዋል። እዚህ ላይ ነው እንግዲህ የሳሙኤል ከፍተኛ ግምት ያለው ሥራ የሚከሠተው። የእግዚአብሔር ሕጎች በእስራኤላውያን መካከል ተግባራዊ ይሆኑ የነበረው እርሱ በመረጣቸው የሕዝብ መሪዎች አማካይነት ነበር። አገዛዙ ወደ ንጉሥ አገዛዝ ሲለወጥ ደግሞ ምን መደረግ እንዳለበት ደንቡንና ሥርዓቱን ማዘጋጀት የነቢዩ ሳሙኤል ኀላፊነት ነበር። በዚህ የታሪክ ወቅት የሳሙኤል ተግባር፥ ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ወደነበረው ግንኙነት ዐይነት ያቀርበዋል (መዝ:99፥ 6፥ ኤር:15፥ 1)። የእግዚአብሔር ሕግ በሙሴ አማካይነት ለሕዝቡ እንደተሰጠ፥ ይህ ሕግ፥ ትእዛዝ፥ ወይም ቃል ኪዳን ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ሳሙኤል ወደ ንጉሣዊ አገዛዝ የመሸጋገሪያውን መንገድ ማመቻቸት ነበረበት። ሳሙኤልም ይህን ያደረገው የሳኦል የንግሥ በዓል በተከበረበት ጊዜ ነበር። እርሱም በዚያን ቀን እስራኤላውያንን ጠርቶ ንስሓ እንዲገቡና ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ቃል ኪዳን እንዲያድሱ ነገራቸው። የንጉሥ አገዛዝን ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ቃል ኪዳን እንደማደስ አድርጎ አቀረበላቸው። የንጉሥም አገዛዝ በአካባቢ ካሉ ሕዝቦች በተለየ ሁኔታ የቀረበ ነበር። የሌሎች

www.ethiopianorthodox.org

ሕዝቦች ነገሥታት ማንም የበላይ ተቈጣጣሪ ሳይኖርባቸው አምባገነኖች ሲሆኑ የእስራኤል ነገሥታት ግን እግዚአብሔር ከበላያቸው ሆኖ መተዳደሪያ ወይም መመሪያ ሕጋቸው ሕገ እግዚአብሔር ነበር።

ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው በመጽሐፈ ሳሙኤል ውስጥ የተተኰረበት ዋነኛው ጉዳይ የሳኦልና የዳዊት መንግሥና የዘመነ ንግሣቸው ታሪክ ነው። ታዲያ መጽሐፉ ባጠቃላይ የእነርሱን ጉዳይ የሚያወሳ ሆኖ ሳለ የእነርሱ የልጅነትና የአስተዳደግ ታሪክ ሳይነገር ከእነርሱ በፊት የነበረውና ቀብቶ ያነገሣቸው የሳሙኤል የልጅነት ታሪክ ብቻ መነገሩ በወቅቱ ሁናቴ ከእነርሱ ይልቅ ለሳሙኤል የበለጠ ግምት ስለተሰጠው ነው። እንዲያውም በተዘዋዋሪ አነጋገር ሥጋና ደም ከመንፈስና ከቃል በታች መሆናቸውን የሚያመለክት ነው።

እስራኤላውያን በጐረቤቶቻቸው እንዳሉ ሕዝቦች ንጉሥ እንዲኖራቸው በጠየቁ ጊዜ እግዚአብሔር ደስ አለመሰኘቱ ያለምክንያት አልነበረም። የመጀመሪያው ንጉሥ ሳኦል እንኳ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከመፈጸም ይልቅ በራሱ ሐሳብ መመራት ለመጀመር ብዙ ጊዜ አልፈጀበትም። ከእርሱም በኋላ የነገሡት በተለይ የእስራኤል ነገሥታት እነርሱ በድለው ሕዝቡንም ወደ ከፋ ኃጢአት መርተውታል።

ወደ ሳሙኤል ልደት ታሪክ መለስ ያልን እንደሆነ ሰዎች ከልባቸው የጸለዩ እንደሆነ እግዚአብሔር እንዴት አትረፍርፎ እንደሚሰጣቸው እንረዳለን። የሕልቃና ሚስት ሐና፥ እግዚአብሔር አንድ ልጅ ይሰጣት ዘንድ ጸለየች። እግዚአብሔር ግን በስእለት ወልዳው ለቤተ መቅደስ አገልግሎት ባስረከበችው በሳሙኤል ምትክ ሦስት ወንዶችና ሁለት ሴቶች ልጆችን ሰጣት (1ሳሙ:ም:2 ቍ:21)።

መጽሐፈ ነገሥት፥ በነገሥታት ዘመን የነበረውን የእስራኤልን ሕዝብ ታሪክ የሚያቀርብ ከመሆኑም ጋር ሁለት የብሉይ ኪዳን ትኵረቶችን ያመለክታል። አንዱ ትኵረት በእግዚአብሔርና በተመረጠው ሕዝቡ መካከል ያለውን የቃል ኪዳን ግንኙት ሲሆን ሁለተኛው ትኵረት ደግሞ በታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር ሥራ ነው (1ኛ:ነገ:ም:8 ቍ:53)።

ለቃል ኪዳኑ ታማኝ መሆንና አለመሆን የሚለካው በሕጉ ጸንቶ በመኖርና ጸንቶ ባለመኖር ነው። ይህንንም አባባል በሚከተለው የቃለ እግዚአብሔር ምስክርነት ይመለከቷል።

ዳዊት ከመሞቱ በፊት ለልጁ ለሰሎሞን የሚከተለውን መመሪያ ሰጥቶታል:-

«አምላክህ እግዚአብሔር እንድታደርግ የሚያዝህን ሁሉ አድርግ፤ በምትሄድበት ስፍራ ሁሉ የምታደርገው ማናቸውም ነገር እንዲከናወንልህ በኦሪት ሕግ የተጻፉትን የእግዚአብሔርን ሕግና ትእዛዝ፥ ፍርድና ሥርዓት ሁሉ ጠብቅ፤ በዚህ ሁሉ ነገር ታዛዥ ብትሆን፥ ልጆችህ በጥንቃቄ ተጠብቀው ቢኖሩ፥ በፍጹም ልባቸውና በፍጹም ነፍሳቸው በፊቴ በቅንነት ቢመላለሱ፥ በእስራኤል ዙፋን ላይ ነግሦ የሚገዛ ዘር አላሳጣህም› ብሎ የነገረኝን የተስፋ ቃል ይፈጽማል።» (1ኛ:ነገ:ም:2 ቍ:3–4)።

ሰሎሞን ግን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳንና የአባቱን መመሪያ በመጣሱ እግዚአብሔር እንዲህ አለው:-

«ከእኔ ጋር የገባኸውን ቃል ኪዳን ሆን ብለህ ስላፈረስክና ትእዛዜን ስላልፈጸምክ መንግሥትህን ከአንተ ወስጄ ከአገልጋዮችህ ለአንዱ ልሰጠው ወስኛለሁ» (1ኛ: ነገ:ም:11 ቍ:11)።

ቀደም ብሎ እግዚአብሔር ለሰሎሞን መንግሥት ሰላም ሰጥቶት ነበር። አሁን ግን ኃጢአት በምሠራቱ ጠላቶችን አስነሣበት (ቍ:14)።

ኃጢአትም የሠሩት ነገሥታቱ ብቻ ሳይሆኑ ሕዝቡም ጭምር በመሆኑ የተላለፈው ፍርድ በሕዝቡ ሁሉ ላይ ነው። ስለዚህ ሙሴ ቀደም ብሎ ሕዝቡን ቃል ኪዳን ባስገባ ጊዜ በገሪዛንና ሸዔባል ተራራ ላይ የበረከትና የመርገም ተግባ ሮችን ዘርዝሮ አቅርቦላቸው ነበር (ዘዳ:ም:27 ቍ:11 እስከ ምዕራፍ:28)።

ለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች ይመለከቷል:-

«እግዚአብሔር እስራኤልንና ይሁዳን የሚያስጠነቅቁ መልእክተኞችንና ነቢያትን በመላክ «ከክፉ መንገዳችሁ ሁሉ ተመለሱ፤ አገልጋዮቼ በሆኑት ነቢያትና ባለ ራእዮች አማካይነት ለቀድሞ አባቶቻችሁና ለእናንተም በሰጠሁት ሕግ የተጻፈውን ትእዛዜን ጠብቁ» ብሎ ነግሮአቸው ነበር፤ እነርሱ ግን መታዘዝ አልፈለጉም፤ በአምላካቸው በእግዚአብሔር እንዳልታመኑት እንደ ቀድሞ አባቶቻቸው እልኸኞች ሆኑ። የሰጣቸውንም መመሪያዎች ለማክበር ፈቃደኞች አልሆኑም፤ ከቀድሞ አባቶቻቸው ጋር የገባውንም ቃል ኪዳን አልጠበቁም፥ የሰጣቸውንም ማስጠንቀቂያዎች ሁሉ ቸል አሉ» (2ኛ: ነገ: ም:17 ቍ:13–15)።

«እግዚአብሔርም በእስራኤል ላይ ተቈጥቶ የይሁዳን መንግሥት ብቻ በመተው እስራኤላውያንን ከፊቱ አስወገደ» (ቍ:18)።

«ለሙሴ ሕግ በመታዘዝ በፍጹም ልቡ፥ በፍጹም ነፍሱና በፍጹም ኀይሉ እግዚአብሔርን ያመለከ እንደ ኢዮስያስ ያለ ንጉሥ ከእርሱም በፊት ሆነ ከእርሱ ወዲህ ከቶ አልነበረም። ነገር ግን ይህም ሁሉ ሆኖ ንጉሥ ምናሴ ባደረገው ክፉ ነገር ምክንያት በይሁዳ ላይ የነደደው አስፈሪ የእግዚአብሔር ቍጣ እስከ አሁን ድረስ ገና አልበረደም ነበር። ስለዚህም እግዚአብሔር እንዲህ አለ:- በእስራኤል ላይ ያደረግሁትን ነገር ሁሉ በይሁዳም ላይ አደርጋለሁ፤ ይኸውም የይሁዳን ሕዝብ ከፊቴ አስወግዳለሁ፤ የመረጥኋትን ከተማ ኢየሩሳሌምንና ስሜ በዚያ ይሆናል ብዬ የነበረውንም ቤተ መቅደስ እተዋለሁ» (2ኛ: ነገ:ም:23 ቍ:25–27)።

እነዚህም እግዚአብሔር የተናገራቸው ትንቢታዊ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን በዚህ በሁለተኛው መጽሐፈ ነገሥት ምዕራፍ 17 እና ምዕራፍ 25 ይመለከቷል።

በታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር ሥራዎች ግልጥ ሆነው የሚታዩት ደግሞ የእግዚአብሔር ነቢያት የተናገሩት ትንቢት ወቅቱ ደርሶ በሚፈጸምበት ጊዜ ነው። ለምሳሌ እግዚአብሔር በነቢዩ አኪያ አማካይነት ኢዮርብዓም በዐሥሩ የእስራኤል ነገድ ላይ እንደሚነግሥ የነገረው መሆኑን በአንደኛ ነገሥት ምዕራፍ 11 ከቍጥር 29 እስከ 40 ይመለከቷል። ይህም ትንቢት እንዴት ተግባራዊ እንደሆነ በምዕራፍ 12 ከቍጥር 1 እስከ 20 ይመለከቷል። በዚሁም ዐይነት ብዙ ተመሳሳይ ትንቢቶች ተነግረው ጊዜያቸው ሲደርስ ተግባራዊ ሆነዋል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በጢሮአዳ ሳለ በሌሊት አንድ የመቄዶንያ ሰው ቆሞ እባክህ ወደ መቄዶንያ መጥተህ እርዳን ብሎ ሲለምነው በራእይ አየ። በዚህም እርሱና ጓደኞቹ ወደ መቄዶንያ ሄደው ወንጌልን ለማስተማር እንደተጠሩ አመኑና ወደ እዚያ ሄዱ። በዚያን ጊዜ መቄዶንያ ከሮማ ግዛቶች አንድዋ ነበረች። ዋና ከተማዋም ተሰሎንቄ ነበረች። ተሰሎንቄ የአረማውያን ከተማ ብትሆንም ብዙ የአይሁድ ወገኖችና ወደ አይሁድ ሃይማኖት የተመለሱ አረማውያን ወገኖች ነበሩባት። ቅዱስ ጳውሎስም ወደ ተሰሎንቄ እንደደረሰ ወደ አይሁድ ምኵራቦች እየሄደ ማስተማሩን ቀጥሎ ብዙዎች የአይሁድ ሃይማኖት ተከታዮችን ወደ ክርስትና ለመመለስ ችሎአል። በዚህም ምክንያት አይሁድ በእርሱ ላይ በተነሡበት ጊዜ ከዚያ ተነሥቶ ወደ ቤርያ ሄዶ ማስተማሩን ቀጠለ፤ ከዚያም ወደ ቆሮንቶስ ሄደ። ከተቃውሞው ብርታት የተነሣ ወደ ተሰሎንቄ ሊመለስ ባለመቻሉ ከአረመኔነትና ከአሁድነት ተመላሾች የሆኑት አዲሶቹ አማኞች በምን ሁናቴ ላይ እንዳሉ አጣርቶ መልስ እንዲያመጣለት ጢሞቴዎስን ላከው (1ኛ: ተሰ:ም:3 ቍ:6–10)። ጢሞቴዎስም በገለጠለት መሠረት አዲሶቹ አማኞች ብዙ መሳደድና መዋከብ ቢደርስባቸውም በእምነታቸው የጸኑ ጠንካሮች መሆናቸውንና ነገር ግን ስለትንሣኤ ሙታን ዘመንና ሁናቴ መረዳት ችግር እንዳለባቸው ለማወቅ ችሎአል። በዚህም መሠረት ስለ ሃይማኖታቸው ጥንካሬ ካመሰገናቸው በኋላ ስለ ተንሣኤ ሙታን መላልሶ ገለጻ አድርጎላቸዋል። በእነርሱ ላይ ችግር የሚያደርሱባቸውም ወገኖች እግዚአብሔር የክፋት ዋጋቸውን እንደሚመልስላቸው ገልጾላቸዋል። እንዲሁም የትንሣኤ ሙታንና የጌታችን ዳግም መምጫ ጊዜ ሳይታሰብ ድንገት እንደሚሆንና ያውም ከሐሳዊ መሲህ መምጣት በኋላ ነው ብሎአቸዋል። ጌታችን በቅርቡ ስለሚመጣ መሥራት አያስፈልገንም ብለው ሥራ ለፈቱት ሰዎች ያልሠራ አይብላ በማለት ቍርጥ ያለ ሐሳቡን ገልጦላቸዋል።

## ጥያቄዎች

1. መጽሐፈ ሳሙኤል በነቢዩ ሳሙኤል ስም የተጠራበት ምክንያት ምንድነው?
2. ሁለቱን የሳሙኤል መጻሕፍት እርሱ ብቻውን ያልጻፋቸው ለመሆኑ የሚቀርበው ማስረጃ ምን የሚለው ነው?
3. የመጀመሪያው ሳሙኤል ስንት ምዕራፎች አሉት?
4. በስንት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል?
5. የሕልቃና ሁለት ሚስቶች ማንና ምን ይባሉ ነበር?

www.ethiopianorthodox.org

6. የሳሙኤል እናት ስምዋ ማን ይባል ነበር?
7. የሕልቃና ቤተ ሰብ በየዓመቱ ወዴት ይሄድ ነበር?
8. የሳሙኤል እናት ምን ፈልጋ ጸለየች?
9. በጸሎትዋ የረዳት ማነው?
10. ይህ በጸሎትዋ የረዳት ሰው እርስዋ ስትጸልይ ምን መስሎት ነበር?
11. ለእግዚአብሔርስ የተሳለችው ምን ብላ ነው?
12. ስለትዋን ተግባራዊ ያደረገችው መቼ ነው?
13. ሁለቱ የዔሊ ልጆች ማንና ማን ይባሉ ነበር?
14. ዔሊ ምን በሰማ ጊዜ ነው የሞተው?
15. አሟሟቱስ እንዴት ነበር?
16. በወሊድ ላይ እያለች የሞተችው ማነች? ምክንያቱስ ምንድነው?
17. የእግዚአብሔርን ታቦት ማርከው የወሰዱት ሰዎች ምን ደረሰባቸው?
18. እግዚአብሔር ለሳሙኤል ምን አደረገለት?
19. ኢዩኤልና አብያ የተባሉት የሳሙኤል ልጆች ምን አደረጉ?
20. በእነርሱ ምክንያት ሕዝቡ ምን ጠየቀ?
21. ሳሙኤል የሕዝቡን ጥያቄ ወዲያው ተቀበለን?
22. ስለ ሕዝቡስ ጥያቄ እግዚአብሔር ሳሙኤልን ምን አለው?
23. ሳኦል ከየትኛው ነገድ ነበር?
24. ሳሙኤል ለሳኦል ምን አደረገለት?
25. ሳኦል ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙት የሻከረው በምን ምክንያት ነው?
26. በሳኦል ላይ ዳዊት ለምን ተመረጠ?
27. ዳዊት ከመጀመሪያው ዝነኛ የሆነው በምን ነበር?
28. ዳዊት ከማን ነገድ ነበር?
29. ሳኦል በዳዊት ላይ የቀናው በምን ምክንያት ነበር?
30. ሳሙኤል ከሞተ በኋላ እንዴት ከሳኦል ጋር ሊገናኝ ቻለ?
31. እርሱስ ለሳኦል ምን ብሎ ነገረው?
32. በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት ሁለት የተለያዩ ታሪኮች ምንና ምን ናቸው?
33. ዳዊት የኬብሮንን ከተማ መናገሻ ባደረገ ጊዜ በማን ላይና ለስንተ ዓመት ነገሠ?
34. አበኔር ማነው?
35. ኢያቡስቴስ ማነው?
36. አበኔርና ኢያቡስቴ ለምን የማይግባቡ ሆኑ?
37. በዚህስ ምክንያት አበኔር ምን አደረገ?
38. ኢዮአብና አቢሳ ለምን አበኔርን ገደሉት?
39. ሁለት የኢያቡስቴ ወታደሮች ምን አደረጉ?
40. ንጉሥ ዳዊት ለእነርሱ ምን አደረገላቸው?
41. መላው የእስራኤል ነገድ በዳዊት አገዛዝ ሥር የሆነው መቼ ነው?
42. ዳዊት የፈጸመው ትልቅ ኃጢአት ምንድነው?
43. ዳዊትን የወቀሰው ነቢይ ማን ይባላል?
44. የእኅቱን ክብረ ንጽሕና የደፈረ የዳዊት ልጅ ማን ይባላል? እርስዋስ ማን ነች?
45. አቤሴሎም የፈጸማቸው ክፉ ሥራዎች ምን ምን ናቸው?
46. የአቤሴሎም ክፉ አማካሪ ማን ይባል ነበር?
47. እርሱንስ ያዘናጋው የነበረው ማን ይባል ነበር?
48. ከእስራኤል ሕዝብ ሰባ ሺህ የሞተው በምን ምክንያት ነው?
49. ዳዊት ለገባዖን ሰዎች ሰባት የሳኦል ልጆችን በስቅላት እንዲቀጡአቸው የሰጣቸው በምን ምክንያት ነው?
50. በአንዳንድ ሰዎች አስተሳሰብ መጽሐፈ ነገሥትን [illegible] ሰዎች እነማን ናቸው?



51. የዜና መዋዕልን መጻሕፍት የጻፈው ማነው? መቼ?
52. ሰሎሞን የበቀል እርምጃ የወሰደባቸው ሰዎች እነማን ናቸው?
53. የሰሎሞን ጥበበኛነት የተገለጠበት የፍርድ ብይን የትኛው ነው?
54. ሰሎሞን በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ስለነበረበት ሁኔታ የተነገሩት ሁለት አስተያየቶች ምንና ምን ናቸው?
55. የእስራኤል ሕዝብ ለምን ለሁለት ተከፈለ?
56. በሮብዓም ዘመን ኢየሩሳሌምን የወረረና የዘረፈ ማነው?
57. የእስራኤል ንጉሥ የኢዮርብዓም ዋናው ኃጢአት ምንድነው?
58. ከይሁዳ ወደ ቤቴል የተላከው ነቢይ ለምን አንበሳ እንዲገድለው ተደረገ?
59. ስለተሰሎንቄ መልእክቶች በተለየም ስለ አንደኛው መልእክት ሰዎች ምን አስተያየት አላቸው?
60. በተሰሎንቆ መልእክቶች ስለ ጌታችን ዳግመኛ መምጣትና ስለ ሙታን ትንሣኤ ምን ዐይነት ትምህርቶች ተሰጡ?
61. በተሰሎንቄ ያሉት አይሁድ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን የተቃወሙት ለምን ነበር?
62. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ወደ ተሰሎንቄ የላከው ለምንድነው?
63. እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝብ የንጉሥ ጥያቄ ያላስደሰተው ሲሆን ለምን ታዲያ ንጉሥ ፈቀደላቸው?
64. የእስራኤል ነገሥታትና የሌሎች ሕዝቦች ነገሥታት ልዩነታቸው ምንድነው?
65. መጽሐፈ ነገሥት የሚያቀርባቸው ሁለት ትኩረቶች ምንና ምን ናቸው?
66. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ተሰሎንቄ ለመሄድ ምክንያት የሆነው ምንድነው?
67. ከተሰሎንቄ ወጥቶ ከሄደ በኋላ፥ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደገና ሊመለስ ያልቻለው በምን ምክንያት ነው?
68. ታዲያ እርሱ በተሰሎንቄ ሳለ ስላስተማራቸው ሰዎች ሁኔታ ለማወቅ ምን አደረገ?

# ምዕራፍ 3

# ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ

## የጌታችን ትምህርቶች

ጌታችን በታላቅ ክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ላይ ሳለ በደብረ ዘይት ተራራ አጠገብ ወደሚገኙት ወደቤተፋጌና ወደ ቢታንያ በቀረበ ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን እንዲህ ብሎ ላካቸው:- «በፊታችሁ ወደምት ገኘው መንደር ሂዱ፤ እዚያም በደረሳችሁ ጊዜ ገና ማንም ሰው ያልተቀመጠበትን የአህያ ውርንጫ ታስሮ ታገኛላችሁ፤ ያን ውርንጫ ፈትታችሁ ወደዚህ አምጡት። ለምን ትፈቱታ ላችሁ ብሎ ማንም ሰው ቢጠይቃችሁ፥ ጌታ ስለሚፈልገው ነው ብላችሁ መልስ ስጡት።» እነዚያ የተላኩትም ደቀ መዛሙርት ወደ ተላኩበት ቦታ በሄዱ ጊዜ ልክ ጌታችን እንደነገራቸው ሆኖ አገኙት። ውርንጭላውንም ፈትተው በሚያመጡበት ጊዜ ባለቤቶቹ ለምን ትፈቱታላችሁ ብለው ቢጠይቁአቸው ጌታ ይፈልገዋል ብለው መልሰ ሰጡአቸው። ይህንንም ብለው ውርንጫውን ወደ ጌታችን ይዘውት መጡ። ከዚያም ልብሳቸውን በውርንጫው ጀርባ ላይ አንጥፈው ጌታችን እንዲቀመጥበት አደረጉ። በውርንጫዋም ላይ ተቀምጦ ሲሄድ ሳለ ሰዎች ሸማቸውን በመንገዱ ላይ አነጠፉለት። ወደ ኢየሩሳሌም ሊደርስ በተቃረበ ጊዜ የደብረ ዘይትን ተራራ ሲወርድ ሳለ ይከተሉት የነበሩት ሰዎች ሁሉ በእርሱ እጅ ይደረጉ ስለ ነበሩት ተአምራት በደስታ ተሞልተው ስለነበረ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እግዚአብሔርን አመሰገኑ። «በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ንጉሥ የተባረከ ነው፤ ሰላም በሰማይ፥ ክብርም ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን» እያሉ ያመሰግኑ ነበር።

በሕዝቡ መካከል የነበሩት ፈሪሳውያን ጌታችን ደቀ መካሙርቱን ዝም እንዲያሰኝ ነገሩት። [illegible] ኻሉ አላቸው (ሉቃ:ም:19 ቁ:29–40)።

www.ethiopianorthodox.org

<u>ጌታችን በቤተ መቅደስ የሚገበያዩትን ማስወጣቱ</u>:- የአይሁድ የፋሲካ በዓል ቀርቦ ስለነበር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ሳለ በዚያ በሬዎችንና በጎችን፥ ርግቦችንም የሚሸጡትን ሰዎች፥ እንዲሁም ገንዘብ ለዋጮችን ገንዘብ በመለወጥ ላይ እንዳሉ አገኘ። በዚህ ጊዜ የገመድ ጅራፍ አበጅና ሰዎችን ሁሉ፥ በጎችንና በሬዎችን ከቤተ መቅደስ አስወጣቸው፤ የገንዘብ ለዋጮችንም ገንዘብ በተነ፤ ጠረጴዛዎቻቸውን ገለበጠ። ርግብ የሚሸ ጡትንም ሰዎች:- «ይህን ሁሉ ወዲያ ውሰዱ፥ የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት» አላቸው።

ከዚህ በኋላ የአይሁድ ባለሥልጣኖች ጌታችንን «አንተ ይህን ለማድረግ መብት እንዳለህ ምን ተአምር ታሳየናለህ?» አሉት። ጌታችንም «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱትና እኔ በሦስት ቀን እሠራዋለሁ» አላቸው። እነርሱም ያን ቤተ መቅደስ ለመሥራት አርባ ስድስት ዓመት ፈጅቶ ሳለ እንዴት በሦስት ቀን ውስጥ ሊሠራው እንደሚችል በመገረም ጠየቁት። እርሱ ግን የተናገረው ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ነበር። ደቀ መዛሙርቱም ይህን ያስተዋሉት ጌታችን ከሞት ከተነሣ በኋላ ነው። በዚህም ምክንያት በመጽሐፍ የተጻፈውን ቃልና ጌታችን የተናገረውን ቃል አመኑ (ዮሐ:ም:2ቊ13–22)።

<u>ጌታችንን ሽቶ የቀባች ሴት</u>:- የአይሁድ የፋሲካ በዓል ሊከበር ስድስት ቀኖች ሲቀሩት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቢታንያ ሄደ። ቢታንያም ጌታችን ከሞት ያስነሣው አልዓዛር የሚኖርባት መንደር ነች። እዚያም ራት አዘጋጅተውለት፥ ማርታ ስታገለግል፥ አልዓዛር ከጌታችን ጋር በማእድ ከቀረቡት ሰዎች አንዱ ነበር። በዚያን ጊዜ ማርያም ዋጋው እጅግ የከበረ ከንጹሕ ናርዶስ የተሠራ ግማሽ ሊትር የሚሆን አንድ ብልቃጥ ሽቶ ወስዳ የጌታችንን እግር ቀባች። በጠጉርዋም አበሰቻቸውና ቤቱ ሁሉ በሽቶው መዓዛ ተሞላ። ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፥ ኢየሱስን አሳልፎ የሚሰጠው አስቆሮታዊው ይሁዳ ይህ ሽቶ በሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ገንዘቡ ለድኾች ለምን አልተሰጠም? አለ። እርሱ ይህን የተናገረው ለድኾች አዝኖ ሳይሆን ሌባ ስለነበረ ነው። የገንዘብ ከረጢት የሚይዝ እርሱ በመሆኑ በከረጢቱ የሚከተተውን ገንዘብ መውሰድ ለምዶ ነበር። ጌታችን ግን ለምቀበርበት ቀን ያደረገችው ዝግጅት ስለሆነ ተው አታስቸግሩአት፤ ድኾች ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ናቸው፤ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልሆንም» አላቸው (ዮሐ:ም:12 ቊ:1–8)።

## <u>የጌታችን ተአምራት</u>

<u>ያለፍሬ የተገኘች የበለስ ዛፍ</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጧት በማለዳ ወደከተማ ሲሄድ ራበው። አንዲት የበለስ ዛፍ በመንገድ ዳር አየና ወደእርስዋ ሄደ። ነገር ግን ከቅጠል በቀር ምንም አላገኘባትም። ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ከቶ ፍሬ አይገኝብሽ አላት። ዛፊቱም ወዲያውኑ ደረቀች። ደቀ መዛሙርቱ ይህን ባዩ ጊዜ ያቺ ዛፍ እንደዚያ ቶሎ በመድረቅዋ ተደነቁ። ጌታችንም ለደቀ መዛሙርቱ ሲያረጋግጥላቸው እነርሱ እምነት ቢኖራቸው ተራራውን እንኳ ወደ ባሕር እንዲወረወር ቢያዝዙት እንደሚታዘዝላቸው ነገራቸው። ስለዚህ አምነው በጸሎት የሚለምኑትን ነገር ሁሉ እንደሚያገኙ ነገራቸው (ማቴ:ም:21 ቊ:18–22)።

<u>ርኩስ መንፈስ ያደረበት ሰው መፈወስ</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ የሰንበት ቀን ወደ አይሁድ ጸሎት ቤት ገብቶ ማስተማር ጀመረ። እርሱ ግን የሕግ መምህራን እንደሚያስ ተምሩት ሳይሆን እንደባለሥልጣን ያስተምራቸው ነበር: ስለዚህ የሰሙት ሁሉ በትምህርቱ ተደነቁ። በጸሎት ቤታቸውም ርኩስ መንፈስ ያደረበት ሰው ስለነበረ «የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፥ እኛ ከአንተ ጋር ምን አለን? ልታጠፋን መጣህን? አንተ ማን እንደሆንህ እኔ ዐውቃለሁ። አንተ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነህ» ብሎ ጮኸ። ጌታችን ርኩሱን መንፈስ ዝም ብሎ ከዚያ እንዲወጣ ገሠጸው። በጌታችንም ትእዛዝ መሠረት ርኩሱ መንፈስ ሰውዬውን ጥሎ ካንፈራገጠው በኋላ በታላቅ ድምፅ እየጮኸ ከእርሱ ወጣ። ሰዎቹም በመደነቅ እንዲህ በማለት እርስ በርሳቸው ተጠያየቁ:- «ይህ ነገር ምንድነው? ርኩሳን መናፍስትን በሥልጣኑ ያዝዛል፤ እነርሱም ይታዘዙለታል። ይህ አዲስ ትምህርት አደለምን?» የጌታችንም ዝና በገሊላ ሁሉ ተሰማ (ማር:ም:1 ቊ 21–28)።

## <u>የጌታችን ምሳሌዎች</u>

<u>የማታፈራ የበለስ ዛፍ ምሳሌ</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለማያፈራው የበለስ ዛፍ ምሳሌ ሲናገር እንዲህ ብሏል:- «አንድ ሰው በአትክልቱ ውስጥ የተተከለች የበለስ ዛፍ ነበረችው።



ከዚያም የበለስ ዛፍ ፍሬ አገኛለሁ ብሎ ቢሄድ ምንም ሳያገኝ ቀረ። ስለዚህ አትክልተኛውን:- «እነሆ፥ ከዚህች የበለስ ዛፍ ፍሬ ለማግኘት ሦስት ዓመት ሙሉ ተመላለስሁ፤ ግን ምንም ፍሬ አላገኘሁባትም፤ አሁንስ ቊረጣት፤ ስለምን የአትክልቱን ቦታ በከንቱ ይዛ መሬት ታበላሻለች?» አለው። አትክልተኛው ግን:- ‹ጌታ ሆይ፥ እስቲ ለዚህ ዓመት ደግሞ ተዋት፤ ዙሪያዋን ኰትኵቼ ማዳበሪያ አደርግላታለሁ፤ ለመጪው ዓመት ፍሬ ብትሰጥ መልካም ነው፤ አለበለዚያ ግን ትቈረጣለች» ሲል መለሰለት (ሉቃ: ም:13 ቊ:6–9)።

<u>የአገልጋይ ግዳጅ</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ አገልጋይ ግዴታ በምሳሌ ሲናገር እንዲህ ብሏል

«ከእናንተ አንዱ በእርሻ ሥራ የተሰማራ ወይም በጎችን የሚጠብቅ አገልጋይ ቢኖረው አገልጋዩ ከሥራው በተመለሰ ጊዜ ወዲያውኑ ና ተቀመጥና ራትህን ብላ› ይለዋልን? ይልቅስ በል ራቴን አዘጋጅልኝ፤ እስክበላና እስክጠጣ አደግድገህ አገልግለኝ፤ ከዚህ በኋላ አንተ ደግሞ ትመገባለህ» ይለው የለምን? ታዲያ አገልጋዩ የታዘዘውን ስለፈጸመ ጌታው የሚያመሰግነው ይመስላችኋልን? እናንተም እንዲሁ የታዘዛችሁትን ሁሉ ከፈጸማችሁ በኋላ የማንጠቅም አገልጋዮች ነን በሉ» (ሉቃ: ም:17 ቊ:7–10)።

<u>የደጉ ሳምራዊ ምሳሌ</u>:- አንድ ጊዜ አንድ የሙሴ ሕግ መምህር ጌታችንን ሊፈትነው ፈልጎ:- «መምህር ሆይ፥ የዘለዓለምን ሕይወት ለማግኘት ምን ማድረግ ይገባኛል?» ብሎ ጠየቀው። ጌታችንም «በሙሴ ሕግ ምን ተብሎ ተጽፎአል? አንብበህስ እንዴት ትረዳዋለህ?» ብሎ ጠየቀው። ሰውዬውም «ሕጉማ እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ፥ በፍጹም ነፍስህ፥ በፍጹም ኀይልህ፥ በፍጹም ሐሳብህ ውደድ፤ እንዲሁም ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ ይላል» አለው። ጌታችንም በትክክል መልሰሃል፤ አንተም ይህን ብታ ደርግ የዘለዓለምን ሕይወት ታገኛለህ» አለው።

የሕግ መምህሩ ግን ራሱን ጻድቅ ለማድረግ ፈልጎ:- «ለመሆኑ ባልንጀራዬ ማነው?» ብሎ ጠየቀው።

በዚህ ጊዜ ጌታችን የሚከተለውን ምሳሌ ነገረው:- «አንድ ሰው ከኢየሩ ሳሌም ወደ ኢያሪኮ ሲወርድ ወንበዴዎች አደጋ ጣሉበት። ወንበዴዎቹም ልብሱን ገፍፈው ከደበደቡት በኋላ ሊሞት ሲያጣጥር ጥለውት ሄዱ። በዚህ ጊዜ አንድ ካህን ሰውዬውን ወድቆ አይቶት ምንም ሳያደርግለት በሌላ በኩል ዐልፎ ሄደ። እንዲሁም አንድ ሌዋዊ በዚያ በኩል ሲያልፍ አደጋ የተጣለበትን ሰው አይቶት ምንም ሳያደርግለት ሄደ። አንድ ሳምራዊ ግን በዚያ በኩል ሲያልፍ አደጋ የተጣለበትን ሰው አይቶ አዘነለት። በቊስሉም ላይ ዘይትና የወይን ጠጅ አፈሰሰለት። ከዚያም በገዛ አህያው ጭኖት ወደ እንግዳ ማረፊያ ቤት ወሰደው። ለእንግዳ ማረፊያ ቤቱ ኀላፊ ገንዘብ ከፍሎ ከመንገዱ እስኪ መለስ ድረስ እንዲጠነቀቅለት ዐደራ አለው። በሚመለስበትም ጊዜ ተጨማሪ ገንዘብ እንደሚከፍል ቃል ገብቶ ሄደ። መሆኑን ከእነዚህ ከሦስት ሰዎች መካከል ለዚያ አደጋ ለደረሰበት ሰው ጓደኛ የሆነለት የትኛው ነው?» ሲል የሕግ መምህሩን ጠየቀው። የሕግ መምህሩም:- «በጎ ሥራ የሠራለት ነው ብሎ መለሰ።» ጌታችንም «እንግዲያውስ ሂድ አንተም እንደዚሁ አድርግ» አለው (ሉቃ:ም: 10ቊ:25–37)።

## <u>ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት</u>

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በታላቅ ክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱና ባህያ ላይ መቀመጡን በተመለከተ በትንቢት የተነገረው እንዲህ ተብሎ ነው:-

«አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ፥ እጅግ ደስ ይበልሽ፤ አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ፥ እልል በዪ፤ እነሆ፥ ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው፤ ትሑትም ሆኖ፥ በአ ህያ፥ በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል። (ዘካ: ም:9ቊ:9)።

የጽዮን ልጅ ሲባል አንድም ለእግዚአብሔር የተለዩ የነበሩት እስራኤላውያን ናቸው፤ ወይም ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ነች፤ ንጉሥዋም ክርስቶስ ነው (መዝ:2ቊ:6)። ጽዮንም የተባለችው ኢየሩሳሌም ነች (2ኛ:ሳሙ:ም:5ቊ:7)።

በአይሁድ ሕዝብ ዘንድ ይጠበቅ ስለነበረውና ወደፊት ይነግሣል ስለተባለው ንጉሥ ነቢያት ምን እንዳሉ እንመልከት:-

www.ethiopianorthodox.org

«እነሆ ሕፃን ተወልዶልናል፤ ...

ድንቅ፥ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘለዓለም አባት፥ የሰላም አለቃ ይባላል፤ ለንጉሥዊ ሥልጣኑ ወሰን የለውም፤ መንግሥቱም ዘለዓለም ሰላም የሰፈነበት ይሆናል፤ ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘለዓለም እውነትና ፍትሕ የሰፈነበት መንግሥት በዳዊት ዙፋን ላይ ተመሥርቶ እንዲጸና ያደርገዋል፤ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይህን ለማድረግ ወስኖአል» (ኢሳ:ም:9 ቍ:6-7)።

«እርሱ በሚነግሥበት ጊዜ የይሁዳ ሕዝብ ደኅንነትን ያገኛል፤ የእስራኤል ሕዝብ በሰላም ይኖራል፤ እርሱም እግዚአብሔር ጽድቃችን ተብሎ ይጠራል» (ኤር:ም:23 ቍ:6)።

«በዚህ ፈንታ ለእኔ ለአምላካቸው ይሰግዱልኛል፤ እኔ በዙፋን ላይ ለማስቀ ምጥላቸው የዳዊት ዘር ለሆነው ንጉሣቸው ይገዛሉ» (ኤር:ም:30 ቍ:9)።

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- አንቺ በኤፍራታ ምድር የምትገኚ ቤተልሔም ሆይ፥ ምንም እንኳ አንቺ ከይሁዳ ከተሞች ያነሰሽ ብትሆኚ አወ ጣጡ ከጥንት ዘመናት በፊት የሆነ የእስራኤል መሪ የሚሆን መስፍን ከአንቺ ይወጣልኛል» (ሚክ:ም:5 ቍ:2)።

የእስራኤል ልጆች ይጠብቁት የነበረው መሲሕ ከሮም አገዛዝ ነጻ አውጥቶ ጠላቶቻቸውን ሁሉ ድል ካደረገ በኋላ የዳዊትን መንግሥታዊ ክብር የሚያመጣላቸውን ንጉሥ ነበር። ከዚያም በላይ በዓለም ባሉት ነገሥታት ሁሉ ላይ ድልን ተጐናጽፎ ሁሉንም በሥልጣኑ ሥር እንደሚያ ደርግ ተስፋ ያደርጉ ነበር። ይህም ማለት የእስራኤል ልጆች የትንቢቱ መንፈስ አልገባቸውም ነበር ማለት ነው። የክርስቶስ ንጉሥነት ምድራዊ ሳይሆን ሰማያዊ መሆኑን አልተገነዘቡትም ነበር። ምንም እንኳ የሚጠበቀው ክርስቶስ ንጉሥ ሆኖ በድል አድራጊነት ወደ ኢየሩሳሌም ቢገባ፥ ይህ፥ የእርሱ ነጉሥነት ግን ዓለማዊ ግርማን፥ የጀብደኝነት ምልክትን፥ ዓለማዊ ሥልጣ ንን እያሳየ በወርቅማ መንኰራኵር ላይ ተሳፍሮ መንኰራኵሩም በከበረ የሐር ልብስና በዕንቍ አጊጦ፥ ምርጥ በሆነ ፈረስ እየተጐተተ የሚሄድና፥ በሺህ የሚቈጠሩ እስረኞች በሰንሰለት ታስረው እየተከተሉት የሚመጣ አይደለም። ነገር ግን እውነተኛው ንጉሥ፥ ማለት የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ክርስቶስ፥ ብዙዎች ሊሳፈሩበት በሚቻለው ዝቅ ያለ ደረጃ ባለው በአህያ ተሳፍሮ በትሕትና ይመጣል። በዚህም የእርሱ መንግሥት ከዚህ ዓለም አለመሆኑን ያረጋግጣል (ዮሐ:18፥ 36)። እንዲሁም በዚህ ዓለም ክብር የተካበበ አለመሆኑን፥ የእርሱ መንግሥት ግን ሰማያዊ መሆኑን በሚያመለክትበት ጊዜ የእነርሱ አስተሳሰብ ለሚጠፋውና ለሚያልፈው ለዚህ ዓለም መሆኑ ቀርቶ ወደ ሰማይ እንዲሆን ለማድረግ፥ ምኞትና ፍላጎታቸው ለምድራዊ ጥቅምና ትርፍ መሆኑ ቀርቶ ወደ ሰማያዊ በረከት እንዲሆን ለማድረግ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምስጋና፥ በሆታና በእልልታ ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ ከአምስት ቀናት በኋላ ጠላቶቹ እንደሚገድሉት ያውቅ ነበር። ይህም ሁሉ ሆኖ ተደብቆ ሳይሆን በግልጥ፥ በፍርሃት፥ በድንጋጤና በሐዘን ሳይሆን በደስታ፥ በሆታና በእልልታ መግባቱ እርሱ የሚሞተው በፈቃዱ እንጂ በጠላቶቹ ፍላጎት አለመሆኑን ለማረጋገጥ ነው።

ስለ ክርስቶስ ማንነት የተሳሳተውም ሕዝቡ ብቻ ሳይሆን ደቀ መዛሙርቱም ጭምር ናቸው። ደቀ መዛሙርቱ የመምህራቸውን ማንነት ሊገነዘቡ የቻሉት ሕማማትን ተቀብሎ ሞቶ ከተነሣና ካረገ በኋላ ብቻ ነው። ጌታችን በአህያው ላይ ሆኖ ወደ ኢየሩሳሌም በሚገባበት ጊዜ ሰዎች ልብሳቸውን ማንጠፋቸው ይህ ድርጊት ለነገሥታት ክብር የሚደረግ ልማድ የነበረ መሆኑን የምንርዳው ኢዩ በእስራኤል ላይ እንዲነግሥ በተቀባ ጊዜ ሁሉም ፈጥነው ልብሳቸውን ያነጠፉለት መሆኑን በመመልከት ነው (2ኛ:ነገ:ም:9ቍ:13)።

አይሁድ የቤተ መቅደሱን ቅዱስነትና የእግዚአብሔር መገኛ መሆኑን ባለማስታወስ ክብር ነሥተውት የመሸጫና የመግዣ ገበያ አደረጉት። ቅጥር ግቢውንም በሬዎችን፥ በጎችንና ርግቦችን የሚሸጡ ነጋዴዎች አጣበቡት። የከብቶቹም እበትና የርግቦቹ ኩስ የቤተ መቅደሱን ቅጥር ግቢ ስላጐደፈው የከብቶች በረት መሰለ። ገንዘብ ለዋጮች ገንዘቡን ማንኳኳት ብቻ ሳይሆን ድምፃ ቸውንም እያሰሙ ይጮኹ ነበር። በዚህም የካህናቱና የሌዋውያኑ የጸሎ ትና የምስጋና መዝሙር ከእንስሳቱ ጩኸት ጋር ይቀላቀል ነበር። ካህናቱ ነጋዴዎቹን ቀረጥ በማስከፈልና ትርፉንም በመካፈል በንግዱ ሥራ ላይ ከነጋዴዎቹ ጋር ይተባበሩ ነበር። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚ አብሔር ቤት ላይ ያየው አክብሮት አልባ ድርጊት አሳዘነው። እርሱም ቤተ መቅደሱን የበሬዎች፥ የበጎችና የርግቦች መሸጫ ተደርጎ አገኘው። ገንዘብ ለዋጮችንም በጠረጴዛቸው አጠገብ ተቀምጠው አየ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ትሑት፥ በሰማያዊ ርቀት ረቂቅ፥ በአባትነት ርኅራኄ ርኅሩኅ፥ ለበጎቹ እንደሚሳሳ የበጎች ጠባቂ የሚሳሳ፥ ኀይለኛና ጨካኝ ያይደለ፥ በማንም



ባይ ...

ሲናገር ቀስ ብሎ፥ በለስላሳ አነጋገር፥ በሰላማዊ መንገድ፥ በይቀር ባይነት፥ በጥበብ፥ በትዕግ ሥትና በመቻል ነው። እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ጠባዮች የእርሱ ገንዘቦች ቢሆኑም እርሱ ምንጊዜም ቢሆን የማይቈጣ ነበር ማለት አይደለም። ወይም ደግሞ ኀይለኛነትና ወሳኝነት አስፈላጊዎች በነበሩበት ጊዜ ሁሉ ኀይለኛና ወሳኝ አልነበረም ማለት አይደለም። ራሱን ዝቅ ማድረጉና ትሕትናው ባሕርያዊ ጠባዩ ነው እንጂ የደካማነት ምልክት አይደለም።

ሁናቴው አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ጊዜ ሁሉ ኀይለኛነትንና ቍጡነትን ተግባራዊ አድርጎአ ቸዋል። እነዚህንም ተግባራዊ የሚያደርጋቸው ለተቀደሰ ቍጣ ነበር። ይኸውም ክፉን ድርጊት እንዳያደርጉ በመከልከልና በመጠበቅ የማስተካከልና የማስተማር መንገድ ነው። በዚህም መሠረት አይሁድ፥ ንጹሑን፥ የተቀደሰውንና ለአምልኮተ እግዚአብሔር የተለየውን ቦታ ለንግድ ሥራ ማዋላቸውን ጌታችን ባየ ጊዜ በጣም ቈጣ።

ጌታችን እንደ ንጉሥ ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ እንደ ምድር ነገሥታት ወደ ቤተ መንግሥት አልገባም። የእርሱ ንግሥ መንፈሳዊና ሰማያዊ በመሆኑ እርሱ የገባው ወደ ቤተ እግዚአብሔር ነው። በዚህ በተቀደሰው ቤትም ሥልጣን ያለው በመሆኑ ነው በመነገድ ላይ የነበ ሩትን ሁሉ ያስወጣቸው። በዚህ ዓለም ሥጋ ለብሶ በኖረባቸው ዘመኖች ሁሉ ንጉሣዊ ሥልጣ ኑንና ኀይሉን በሰዎች ዘንድ የተጠቀመባቸው በዚህ ጊዜ ብቻ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቤተ መቅደስ በገባ ጊዜ ወደ ቤቱ መግባቱ እንደመሆኑ አንድ የቤት ባለቤት ወደቤቱ ሲገባ የማይሆን ነገር በሚያይበት ጊዜ እንደሚያስተካክለው ሁሉ ጌታችንም የማይሆን ነገር ስላየ አስወገደው።

ማንኛውም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ማለትም በእርሱ ላይ ካለው ከልብ ከመነጨ እምነት የሚደረግ ነገር ሁሉ ብዙ ነው ወይም ብክነት ነው ሊባል አይገባውም። ከልብ ፍቅርና አክብሮት የተነሣ እስከ ሆነ ድረስ ብዙ ለወደደ ብዙ ይሰረይለታል (ሉቃ:ም:7 ቍ:47) ። ደቀ መዛሙርቱ፥ ወይም እዚያ የነበሩ ሰዎች፥ ወይም ይሁዳ ያን ውድ የሆነ ሽቶ አባክነች ብለው ተስፋ ሊያስቈርጡአት ቃጣቸው። ጌታችን ግን ለእርስዋ ተከላከለላት ተሸጦ ለድኾች ምጽዋት ሊሰጥ በቻለ ነበር ለሚለው ወቀሳ ድኾችን ለመርዳት የሚፈልግ ሰው ችግር የለበትም፤ ምክንያቱም ድኾች ሁልጊዜ አሉ ካለ በኋላ እኔ ግን በስድስት ቀኖች ውስጥ በሥጋ መሞቴ ስለሆነ ይህች ሴት ለመቃብሬ የሚፈጸመውን ሥርዓት አስቀድማ ፈጽማዋለችና አታስቸግሩአት አላቸው። ጌታችንም የእርስዋን ሥራ በበለጠ ባመሰገነበት ንግግሩ እንዲያውም ይህች ሴት የሠራ ችው በጎ ሥራ ይህ ወንጌል በሚሰበክበት ቦታ ሁሉ ይነገርላታል» ብሎአል። በሃማኖታዊ ተግባር ከእኛ ይበልጥ ብዙ ነገር የሚያደርጉ ሰዎች ከሚገባ በላይ አደረጉ ብሎ መውቀስ ሳይሆን እኛም የእነርሱን ያኽል ለማድረግ መጣጣር ይኖርብናል።

ይህን በውድ ዋጋ የተገዛ ሽቶ በጌታችን እግር ላይ አፍስሳ እግሩን በጠጕርዋ ያበሰችለት ማርያም አንድም በጌታችን ከማመንዋና ከአክብሮት ፍቅርዋ ታላቅነት የተነሣ ዐቅምዋ የሚፈቅድላትን ያኽል ለጌታችን ለማድረግ አስባ ነው፤ ወይም ጌታችን ሊሞት የተቃረበ መሆኑን ዐውቃ ለቀብር ሥነ ሥርዓት መደረግ ያለበትን ነገር አስቀድማ ማድረግዋ ነው። በዚህም ሆነ በዚያ የእርስዋ ድርጊት ተመስግኖላታል።

ጌታችን በለምጻሙ ስምዖን ቤት ለማእድ ተጋብዞ የነበረው አይሁድ ሊገድሉት በዶለቱበት ሰሞን ስለነበረ በቅርብ ጊዜ እንደሚገደል በሕዝቡ ዘንድ ጥርጣሬ ወይም እምነት ነበር። ጌታችን በእርሱ ቤት ውስጥ የተጋበዘበት ስምዖን ምናልባት ጌታ ከለምጽ በሽታ ካነጻቸው ሰዎች አንዱ ሳይሆን አይቀርም የሚል አስተሳሰብ አለ። ይህም አስተሳሰብ ያለምክንያት የቀረበ ሳይሆን በዚያን ጊዜ አንድ ለምጻም ሰው እንዲሁ በቀላሉ ከኅብረተሰቡ ጋር መቀላቀል ይችል ስላል ነበረ ነው፤ ይህም ማለት እርሱ ከለምጽ የዳነ ባይሆን ሰዎች በቤቱ ባልተገኙም ነበር።

በማለዳ ተነሥቶ ሲሄድ ተራበና በመንገድ ዳር አንድ የበለስ ዛፍ አይቶ ወደዚያ ሄደ። ያልተጠፋፉ የመለኮትና የሰውነት ባሕርይ ያለው በመሆኑ በሰው ነቱ ተራበ። ክርስቶስም እዚህ ላይ የተራበው ተአምራቱን አድርጎ የእውነት ፍርድ ፈራጅነቱንና የኀያልነቱን ምሳሌ ሊያቀር ብልን ፈቅዶ ነው። ፍርዱን በተመለከተ እርሱ ወደዛፉ ፍሬ ለማግኘት ሄዶ ፍሬ ባጣበት ጊዜ ዳግመኛ ፍሬ እንዳያፈራ ረገመው። ይህም ሕይወት በሌለው ነገር በዛፍ ላይ የቀረበው ታሪክ ለምሳሌነት የቀረበ ነው። ለምለም ቅጠል የነበረው በመሆኑ ፍሬ እንደሚያፈራ ጠብቆ ወደዚያ የበለስ ዛፍ ቢሄድ ፍሬ የሌለው ሆኖ ስላገኘው ከእንግዲህ ወዲያ ፍሬ እንዳያፈራ ፈረደበት።



www.ethiopianorthodox.org

ይህም የበለስ ዛፉ እርግማን በአጠቃላይ በግብዞች ሰዎች የሚመሰል የሚከተሉትን ትምህርቶች ይሰጠናል:-

አንደኛ/ የበለስ ፍሬ ቅጠል ካለው የበለስ ዛፍ የሚገኝ መሆኑ ሲሆን ሃይማኖተኞች ነን ብለው ከሚናገሩ ሰዎች ደግሞ ክርስቶስ የሃይማኖትን ኀይል ለማየት ይጠብቃል።

ሁለተኛ/ ሃይማኖተኛነታቸውን በብዛት የሚናገሩ ሰዎች በክርስቶስ በኩል የሚጠበቅባቸውን ተግባር በተመለከተ የሚታየው ውጤት የሚያሳዝንና ተስፋ የሚያስቈርጥ ነው። ብዙዎቹ በመኖር ስም ይኖራሉ እንጂ ሕያዋን አይደሉም።

ሦስተኛ/ ፍሬቢስ የመሆን ኃጢአት በእርግማንና በመካንነት መቅሠፍት መቀጣቱ ትክክለኛ ፍርድ ነው። ከበረከቶች አንዱ ዋነኛው በረከት፥ እንዲያ ውም የመጀመሪያው በረከት:- «ብዙ፤ ተባዙ፤ ምድርንም ሙሉአት የሚለው ነው። ስለዚህም በጣም አሳዛኙም እርግማን:- «ከእንግዲህ ወዲያ ለመቼውም ፍሬ አይገኝብሽ» የሚለው ነው።

አራተኛ/ ሐሰተኛና ግብዝ የሆነ ሃይማኖታዊ ምስክርነት በዚሁ ዓለም ሚሸሽ ይጠፋል። ያ ፍሬ አልባ የሆነው የበለስ ዛፍ ቅጠሉቹም ወዲያውኑ ደረቁ። ግብዞች ለተወሰነ ጊዜ ታማኞችና እውነተኞች ይመስሉ ይሆናል። አስመሳይነታቸው ግን ዋጋቢስ ይሆናል። ስጦታዎቻቸው ይጠፋሉ፥ ተራ ጸጋዎ ቻቸው ይዝጋሉ፤ የአስመሳዮቹ ውሸት ለሰው ሁሉ ግልጥ ይሆናል። ይህም ሁናቴ በተለየ የአይሁድን ሕዝብ የሚመለከት ነው። እነርሱ በክርስቶስ መንገድ ላይ የተተከሉ የበለስ ዛፍ ናቸው፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስንም አሳዝነ ውታል። ወደ እነርሱ የመጣው አንዳች ለእርሱ ደስ የሚያሰኝ ፍሬ ለማግኘት ነው። እርሱ የጠበቀው ነገር ሳይሆን ቅጠል ብቻ አገኘ። እነርሱ ተስፋ የተሰጣቸውን ክርስቶስን የሚጠብቁ መሰሉ። ሲመጣ ግን በሚገባ አልተቀበሉትም። ስለዚህ ባልተቀበሉት ላይ ፍሬ ጽድቅ እንዳያፈሩ ፈረደባቸው። ከእነርሱም አንዳንድ በእርሱ ያመኑት ሰዎች በቀር ምንም ደግ ነገር አልተገኘም። ክርስ ቶስን መቀበል እምቢ ካሉበት ጊዜ ጀምሮ ሁናቴአቸው እየተበላሸ ሄደ። ይህም የሆነው «ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን» ብለው በራሳቸው ላይ ከፈረዱ በኋላ ነው (ማቴ:ም:27: ቍ:25)።

5ኛ/ እንዲሁም የበለስ እርግማን በክርስቶስ የኀጢአት መደምሰስን ያመለክታል።

አንድ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅፍርናሆም ከሚገኙት ምኵራቦች (የአይሁድ ጸሎት ቤቶች) በአንዱ ውስጥ ሳለ ከሕዝቡ መካከል አንዱ በርኩስ መንፈስ የተያዘ ማለት ርኩስ መንፈስ ያደረበት ሰው ነበር። ርኩሳን መናፍስትም በእግዚአብሔር ላይ ስላመፁ የእግዚአብሔር ብርሃን ወደሌለበት ጨለማ የተጣሉ ናቸው። ንጽሕናቸውንም ያጡ ስለሆነ ፍጹም ቅዱስ ወደ ሆነው እግዚአብሔር ለመቅረብ አይደፍሩም። በፍርድ ቀን የሚጠብቃቸውን ፍርድ በመጠባበቅም በፍርሃትና በመርበድበድ ይኖራሉ። በሁናቴአቸውም ቅናት፥ ምቀኝነት፥ ብስጭትና ቍጣ ሞላባቸው። ቍጭታቸውን የሚወጡትም የእነርሱ ሰለባዎች በሆኑት በሰው ልጆች ላይ ነው። የሰዎችም ዕድል ፈንታ እንደ እነርሱ ይሆን ዘንድ ወደ ኃጢአት ሥራ ይገፋፉአቸዋል። ሰውም ለእነርሱ ተስማሚ ሆኖ በሚያገኙት ጊዜ በመላ ሰውነቱ ላይ ይሰፍሩበታል:- በሰውነቱም ላይ ሲሰፍሩ የሰፈሩበትን ሰውነት ያሠቃዩታል። ሰይጣንም ሰውን በሚያሠቃይበት ጊዜ ያ ክፉ ሥራው ያስደስተዋል። እነርሱ ለሚሠቃዩበት የቅጣት ሥቃይ በቀል የሚበቀሉት የእነርሱ ሰለባ በሆነው የሰው ልጅ ላይ ነው። ምንም እንኳ ያ በምኵራቡ ውስጥ በነበረው ሰውዬ ላይ የሰፈረው ርኩስ መንፈስ ጌታችንን ቢፈራና ቢርበደበድ ክፋት ከሰይጣን አይጠፋምና በንግግሩ ላይ የናዝሬቱ ኢየሱስ አለ። ይህንንም ያለው በሕዝቡ ዘንድ መልካም ነገር ከናዝሬት እንደማ ይወጣ እምነት ስለነበረ ነው (ዮሐ:ም:1ቍ:46)። ጊዜው ሳይደርስ ልታጠፋን መጣህን? ማለቱ የፍርድ ቀን ከመምጣቱ በፊት ማለቱ ነው። የጌቶች ጌታ ፈጣሪ አምላክ በመሆኑ ሰይጣን ለጌታችን ከመታዘዝ በቀር ሌላ ምርጫ አልነበረውም። ካደረበት ሰውም ላይ ወጥቶ ሄደ።

በማታፈራው የበለስ ዛፍ ምሳሌ አማካይነት የተነገረው በሕይወቱ መልካም ሥራ ሠርቶ የማያውቅ ሰው ምሳሌ ነው። እንደዚህም ያለው ሰው ደግ ሥራን አለመሥራቱ ብቻ ሳይሆን ለኅብረተሰቡ መጥፎ ምሳሌ በመሆን የማኅበራዊ መልካም ኑሮን ያቃውሳል። በዚህም ምክንያት መጥፋት አለበት። ከዚህም ሁሉ ጋር እንደዚህ ላለው ሰው በንስሓ የመመለስ ዕድል ተሰጥቶታል። በዕድሉ ተጠቅሞ ከክፋት ወደ በጎ ተግባር ቢመለስ ይበጀዋል። በዚያች በፍርድ ቀን እግዚአብሔር ሌላ ምንም ምክንያት አይቀበልም። በፈጸመው ክፉ ተግባሩ ይፈርድበታል እንጂ በእግዚአብሔር ፊት እሰጥ፥ አገባ አይኖርም። ለእርሱ የሚበጀው በመጨረሻ ደቂቃ እንኳ ቢሆን ከክፋቱና ከበደሉ በንስሓ ቢመለስ ነው። ከዚያ በኋላ ለዘለዓለማዊ ሕይወት የበቃ ይሆናል።



በእልኸኛነቱ ቢጸናና አትክልተኛው በመኰትኰትና ፍግ በማስታቀፍ እንዳደረገላት የበለስ ዛፍ ንስሓ ባይገባና በጎ ተግባር ባያደርግ ዕድል ፈንታው እንደዚያች የበለስ ፍሬ ይሆናል። ይህም የሚሆንበት ምክንያት ያቺን ዛፍ ለማንደድ ካልሆነ በስተቀር ለሌላ ለምንም ስለማትጠቅም እርሱም እንደዚያው በገሀነመ እሳት ስለሚቃጠል ነው። ይህ ምሳሌ ሌላም ትርጕም አለው። እግዚአብሔር ሕጉን የሰጠው ለአይሁድ ሕዝብ ነበር። ሕጉም መልካም ፍሬ ያፈራ ዘንድ ጠበቀው። ነገር ግን ምንም ፍሬ ሳያገኝበት ለብዙ ዘመን ጠበቀው። ከክፋት በስተቀር ምንም አላገኘም። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትም ሕዝቡ መልካም ፍሬ እንዲያፈራ የመጨረሻ መልካም ዕድል ነበር። የሰጠው ታላቅ ትምህርትና ጸጋም ለዚህ አመቺ ነበሩ። ነገር ግን ሕዝቡ ለጌታችን ትምህርት ጆሮውን ዘጋ፤ ለጸጋው ዐይኑን ጨፈነ፤ በእልኸኛነቱም ቀጠለ፤ በጥፋት ተግባሩም ጸና፤ ፍሬ እንደማታፈራው የበለስ ዐይነት መሆኑንም ቀጠለ፤ ዕድል ፈንታውም እንደዚያ ፍሬ እንደማያፈራው ዛፍ ጥፋት ሆነ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ለእግዚአብሔር ስለሚያቀርቡት አገልግሎት ሲነጋገር እናንተ ለእግዚአብሔር በምታቀርቡት አገልግሎት ግዴታችሁን እንደፈ ጸማችሁ እንጂ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር ባለውለታዎች አድርጋችሁ መቍጠር የለባችሁም ብሉአቸዋል። እነርሱ ሊከፍሉት የማይችሉት ብዙ የእግዚአብሔር በረከትና ጸጋ የተሰጣቸው መሆኑንና እነርሱ እስከ ዘለዓለም የእግዚአብሔር ባለ ዕዳ እንደሆኑ አስረዳ ቸው። ለዚህም ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ የአገልጋይን ግዳጅ ምሳሌ ነግሮአ ቸዋል። ምሳሌውንም ከነገራቸው በኋላ «እንዲሁም እናንተ የታዘዛችሁትን ሁሉ ከፈጸማችሁ በኋላ:- የማንጠቅም አገልጋዮች ነን፤ ልንፈጽም ግዴታችን የሆነውን እንጂ ምንም የሚያስመሰግነን ሥራ አልሠራንም በሉ ብሉአቸ ዋል። ስለዚህ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ማድረግ የሚገባውን ግዴታ ስለሰጠው ያን በማድረጉ ወዲያው ሽልማት የሚገኝ አይመስለው። ሆኖም እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ የሚፈጽም ሰው የእግዚአብሔር መንፈሳዊ በረከት በሚገኝበት አምላካዊውን ማእድ እንደሚታደል ይጠብቅ፤ በፈጸመው የእግዚአብሔር ትእዛዝ ግን የእግዚአብሔርን ምስጋና በመጠበቅ ራሱን ከፍ ከፍ አያድርግ፤ አይታበይ። እግዚአብሔር ጌታው ስለሆነ ከእግዚአብሔር ምስጋና አይጠብቅ። ምንም ያኽል አገልግሎት ቢፈጽም እግዚአብሔር ከዋለለት ውለታ ጋር ሊመጣጠን ስለማይችል አገልግሎቱን ከግምት አያግባው። እግዚአብሔርም በማእዱ እንዲቀመጥ ሲፈቅድለት ከቸርነቱ፥ ከፍቅሩና ከደግነቱ የተነሣ ነው እንጂ ለእርሱ ባለውለታ ሆኖ አይደለም።

ከሕግ ዐዋቂዎች አንዱ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት በግልጽ የማያውቅ ከመሆኑ የተነሣ በሰው ፊት መልስ አሳጥቶ የሚያሳፍረው መስሎት:- «መምህር ሆይ፥ የዘለዓለምን ሕይወት እወርስ ዘንድ ምን ላድርግ» ብሎ ጠየቀው። የሕግ ምሁራን፥ ፈሪሳውያን፥ ሰዱቃውያንና የሃይማኖት ወገኖች ሁሉ በጌታችን ላይ በጠላትነት ተነሥተውበት የነበረው በእርሱ ላይ በመቅናት፥ በምቀኝነትና በጥላቻ ነበር። እርሱ ክፋታቸውን ይገልጥባቸው፥ በአይሁድ ማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ የነበራቸውን ከፍተኛ ቦታ ይወስንባቸው የነበረ ከመሆ ኑም በላይ ሕዝቡ በጌታችን ትምህርት ተስቦ እርሱን ማካበቡ እነዚህን የሃይማኖት ወገኖች አስቈጣ፤ አበሳጨም። የበለጠ ቅናትና ጥላቻም አሳደረባቸው። በዚህም ምክንያት እርሱን ከስሶ ለማጥፋት ምክንያቶችን ይፈልጉበት ነበር። የጥያቄዎቹም ዓላማ ከእርሱ አንደበት በሞት የሚያስቀጣ መልስ ለማግኘትና እርሱን ከስሶ ለማስቀጣት ነበር። እነርሱ መስሉአቸው ሙከራ ያደርጉ ነበር እንጂ ጌታችን ግን ተንኰላቸውን ያውቀው ነበር። ይሰጥ የነበረውም መልስ ከሕጋቸው ያልወጣ ነበር። የጥያቄውም መልስ ሌላ ጥያቄ አስከትሎ ጓደኛዬስ ማነው ባለው ጊዜ የደጉን ሳምራዊ ምሳሌ ተረከለት። ከሦስቱ ሰዎች ማናቸው ይበልጥ ጓደኛ እንደሆነለት ቢጠይቀው በጎ ሥራ የሠራለት መሆኑን ስለገለጠለት በል አንተም ሂድና እንደዚያ አድርግ አለው። በዚህም ዐይነት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያን ተንኰለኛ የሕግ መምህር ከካህኑና ከሌዋዊው ይበልጥ ለዚያ አደጋ ለደረሰበት ሰው ውለታ የዋለለት መሆኑን በአንደበቱ እንዲመሰክር አደረገው። አይሁድ፥ በተለየም የሃይማኖቱ መምህራን ሳምራውያንን በጣም ይጠሉአቸው ነበር። ምንም እንኳ ከእነርሱ ጋር አንድ ዘር ቢሆኑ የሰማርያን ሰዎች ይጸየፉአቸው ነበር።

## ጥያቄዎች

1. ጌታችን ሁለት ደቀ መዛሙርቱን ወደ ፊት በላካቸው ጊዜ ምን ብሎ አዘዛቸው?
2. ደቀ መዛሙርቱ ወደ ተላኩበት ቦታ በሄዱ ጊዜ ምን አገኙ?

www.ethiopianorthodox.org

በሐዋርያት ሥራ፥ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቲቶና ለጢሞቴዎስ በላካ ቸው መልእክ ቶቹ፥ እንዲሁም በመጽሐፈ ዲድስቅልያ በተለያዩ የኀላፊነት ሥራዎች የሚመደቡና የተመደቡ ኤጲስ ቆጶሳት፥ ካህናትና ዲያቆናት መሾማ ቸውና እንዲሾሙ መታዘዛቸው ተገልጦአል። ኤጲስ ቆጶሳቱ በበላይነት፥ ካህናቱ በአስተማሪነት፥ ዲያቆናቱ ደግሞ በረዳትነት የሚመደቡ ናቸው (የሐ: ሥ:14፥ 23፥ ቲቶ:1፥ 5–6፥1ኛ: ጢ.ሞ:ም:3፥ ዲድስቅልያ አንቀጽ 3)።

እነዚህ ሦስቱ የክህነት ደረጃዎች ቀደም ብለው የተመሠረቱ ናቸው። ይሁን እንጂ ዘመናት ዐልፈው ዘመናት ሲተኩ በአገልግሎቱ መስፋፋት ምክንያት የተለያዩ የሥልጣን እርከኖችን መጨመር ስላስፈለገ አሁን ያለው የአብያተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር በብዛቱም ሆነ በዐይነቱ ከቀድሞው የተለየ ነው።

ስለዚህ ከመሠረታዊው የሃይማኖት ሥርዓት ሳትርቅ ቤተ ክርስቲያን የሠራተኛና የገንዘብ አስተዳደርን መንገድ በመከተል በሥርዓት ተሠራለች።

## የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን

ቅዱስ ድሜጥሮስ:– የሥጋ ፍትወትን ታግሎ የተፈጥሮን ዝንባሌ ድል ለማ ድረግ የቻለው፥ ድሜጥሮስ የተባለው ቅዱስ፥ ዐሥራ ሁለተኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ነው። እርሱም ማንበብና መጻፍ የማይችል መሀይምን ነበር። ሚስ ትም አግብቶ ነበር። ለፓትርያርክነት እስከተመረጠበት ጊዜ ድረስ ከሚስቱ ጋር አርባ ሁለት ዓመት ኖሮአል። በእነዚያ ሁሉ ዓመቶች በባልና በሚስትነት ግንኙት አልተዋወቁም። ሁለቱም ድንግልናቸውንና ንጽሕናቸውን ጠብቀው ይኖሩ ነበር። ከሕዝቡም መካከል ይህን ጉዳይ የሚያውቅ አልነበረም።

ፓትርያርክ ዩልያኖስ፥ ከዚህ ዓለም በሞት መለያው ጊዜ ሲቃረብ የእግዚ አብሔር መልአክ በራእይ ተገልጦ በእርሱ ምትክ የፓትርያርክነቱን ሥልጣን የሚረከበው ድሜጥሮስ መሆኑን ገለጠለት። ይህ ድሜጥሮስም ማን እንደሆነ ሲገልጥለት ነገ አንድ የወይን ዘለላ ይዞልህ የሚመጣ ሰው ስላለ እርሱን አቆየ ውና ጸልይለት አለው። ከእንቅልፉም በነቃ ጊዜ በእርሱ ዘንድ ለተገኙ ጳጳሳትና ካህናት ስላየው ራእይ ነገራቸው።

በማግስቱ ድሜጥሮስ ከጊዜው በፊት ያፈራ አንድ የወይን ዘለላ አገኘ። ከፓትርያርክ ዩልያኖስ በረከት ለመቀበል ብሎ ያገኘውን የወይን ዘለላ ይዞ ወደ ፓትርያርኩ ሄደ። ፓትርያርኩም ባገኘው ጊዜ እጁን ይዞ እዚያ ለተገኙት ሰዎች ከእኔ በኋላ ፓትርያርካችሁ ይሄ ነው አላቸውና ለእርሱ ጸለየለት። ዩልያ ኖስም እስከሚያርፍበት ጊዜ ድረስ በዚያው አቆዩት። ዩልያኖስ ካረፈ በኋላ ሥርዓተ ሢመቱ ተፈጽሞለት በሰማያዊ ጸጋ ተመላ። እግዚአብሔር ኅሊናውን አብርቶለት መጻፍና ማንበብ ተማረ። መጻሕፍትንና ትርጓሜአቸውንም ተማረ። በሚሰብክበት ጊዜ ከአንደበቱ የሚወጣው ጸጋን የተመላ ትምህርት ነበር።

ቋሚ ደንብን ተከትሎ የአጽዋማትን ጊዜ ለማወቅ የሚያስችለውን የአብ ቀጢን ሒሳብ (አበቅቴ) ያዘጋጀ ድሜጥሮስ ነው። ከዚያ በፊት ክርስቲያኖች ዐቢይ ጾምን የሚጾሙት ከጥምቀት በዓል ቀጥለው ወዲያው በመጀመር ነበር። ለዚህም የሚሰጡት ምክንያት ጌታችን አርባ ቀኖችን የጾመው ከተጠመቀ በኋላ ነው የሚል ነው። ጾመ ሕማማትን የሚጾሙት ደግሞ የክርስቶስን ትንሣኤ ከአይ ሁድ የፋሲካ በዓል በኋላ ለማክበር ሲባል ከዐቢይ ጾም ተለይቶ ነበር። ከክርስ ቲያኖችም መካከል የትንሣኤን በዓል በኒሳን ዐሥራ አራት ቀን ሚያከብሩም ነበሩ። ይህም ማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት የተነሣበትን ከአይሁድ የፋሲካ በዓል ጋር አብረው ያከብሩት ነበር ማለት ነው። በዚህም ምክንያት ቅዱስ ድሜጥሮስ ስለ በዓላትና ስለ አጽዋማት አወጣጥ ቋሚ ደንብን በሚያ ዘጋጅበት ጊዜ በቂ ጥንቃቄ አድርጎአል። ጾመ አርባንም ከሕማማት ጾም ጋር አጠቃለለው። ስለአሠራሩም አጋፕያኖስ ለተባለው የኢየሩሳሌም ጳጳስ፥ መክ ሲሞስ ለተባለው የአንጾኪያ ፓትርያርክና ለሌሎችም ጻፈላቸው። እነርሱም በሐሳቡ ተስማሙበት። የሮማ ቤት ክርስቲያን ግን ከዐሥራ ስድስተኛው መቶ ዘመን ጀምራ በጎርጎሮሳዊው የዘመን አቈጣጠር ስልት ተጠቅማለች። ከዚያ በፊት የእስክንድርያው ቤተ ክርስቲያን መሪ በየዓመቱ የትንሣኤ በዓል የሚከ በርበትን ቀን ለየቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያስተላልፍ ነበር። ይህም ይደረግ የነበረው በዓለም በመላ የሚገኙ ክርስቲያኖች ሁሉ የጌታችን ትንሣኤ በአንድ ቀንና በአንድ ላይ እንዲያከብሩት ለማድረግ ተብሎ ነው።

ንጹሕ ሰው ስለነበረ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ከፓትርያርክ ድሜጥሮስ ጋር ነበር። ቅዳሴውን ጨርሶ ለማቍረብ በሚዘጋጅበት ጊዜ ሁሉ ለሥጋውና ለደሙ ብቁ የሆነውን ሰው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደቍርባኑ ሲያቀርበው የማየ ትንና ብቁ ያልሆነውን ሰው ደግሞ ኃጢአቱን



በዝርዝር የማየትን ስጦታ ዐደለው። እግዚአብሔርም በሚያሳየው የኃጢአት ዝርዝር መሠረት አንተ ገና ንስሓህን አልጨረስክምና ከመቍረብህ በፊት ንስሓህን አጠናቅ ብሎ ይከለክል ነበር። በዚህም ምክንያት በእርሱ ዘመን ምእመናን ተስተካክለው ይራመዱ ነበር።

ኃጢአተኞችን ከመገሠጹና ወደ ንስሓ ከመምራቱ ብዛት የተነሣ አንዳንድ ሰዎች እርሱ ሚስት ያገባ ሰው መሆኑ አንሶ እንደገና በእኛ ላይ ይህን የመሰለ ተግሣጽ መሰንዘሩ እንደ ምን ነው ብለው ያጕረመርሙ ጀመር። እግዚአብሔርም የድሜጥሮስን ማንነት ለመግለጥ ስለፈቀደ የጌታ መልአክ በሌሊት መጥቶ አንተ ራስህን ለማዳን ፈልገህ ሌላው ሰው በጥርጣሬ እንዲጠፋ አታድርግ! በአንተና በሚስትህ መካከል ያለውን ምሥጢር ለሕዝቡ ግልጥ አድርግላቸውና ጥርጣሬ ከኅሊናቸው እንዲጠፋ አድርግ አለው። ድሜጥሮስም በማግስቱ ጧት ከቅዳሴ ውጪ ሕዝቡ ከቤተ ክርስቲያን እንዳይወጣ አዘዘ። ከዚያም ሚስቱን ጠርቶ የእሳት ፍም በልብሷ አስታቀፋት! እርሱም በልብሱ ታቀፈና ቤተ ክርስቲያኑን ይዞሩ ጀመሩ። ይህንንም ሲያደርጉ ልብሳቸው ምንም የቃጠሎ ጉዳት አልደረሰበትም። ሕዝቡ በጣም መገረሙን ባየ ጊዜ የፍትወትን እሳት ድል የሚነሣ ሰው ይህ የተፈጥሮ እሳት ሊያይልበት አይችልም አላቸው። ንግግሩንም በመቀጠል ይህች ሚስቴ የአጎቴ ልጅ ነች። አባትዋ ገና ከልጅነትዋ ስለሞተ አብረን አድገናል። አባቴም እንድንጋባ አደረገን። ነገር ግን በወንድምና በእኅት ስምምነት እስከካዛሬ ድረስ በድንግልና ኖርን ብሎ በገለጠላቸው ጊዜ ያጕረመርሙ የነበሩት ሰዎች ይቅርታ ጠየቁ።

ይህ ፓትርያርክ በመንበሩ ላይ አርባ ሦስት ዓመት ከቈየ በኋላ በአንድ መቶ አምስት ዓመት ዕድሜው ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

የጥቅምት ዐሥራ ሁለት ቀን ስንክሳርን ይመለከቷል።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት:- ይህ ቅዱስ የተወለደው በትንሽዋ እስያ አርያንዝ በተባለ መንደር ነው። ወላጆቹ የፍልስጥኤም ቂሳርያ በሆነው ትምህርት ቤት እንዲማር አድርገውታል። ወደ አቴና በመርከብ ላይ ሆኖ በሚጓ ዝበት ጊዜ ከባሕሩ መናወጥ የተነሣ የተሳፈረበት መርከብ ሊሰጥም ተቃርቦ ነበር። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ከዚያ ችግር ቢያድነው ሕይወቱን ሙሉ ለእግ ዚአብሔር እንደሚያውለው ተሳለ። ጸሎቱም ተቀባይነትን አግኝቶ ጕዞውን በሰላም ፈጸመ። አቴና በደረሰ ጊዜ ከጓደኛው ከባስልዮስ ጋር ተገናኘ። ጓደኛሞቹም እየተረዳዱ ትምህርታ ቸውን ቀጠሉ። ወደ ሀገሩም በተመለሰ ጊዜ በእንዚናዝ አባቱን በሃይማኖት አገልግሎት ይረዳው ጀመር። ከዚያም በኋላ ከጓደኛው ጋር በቀጰዶቅያ ተራራ ላይ አብረው መኖር ጀመሩ።

ባስልዮስ የቀጰዶቅያ ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ በተሾመ ጊዜ ለጓደኛው ለጎርጎርዮስ ሳዚሚ ለምትባል አዲስ ሀገረ ስብከት ኤጲስ ቆጶስነት እንዲሾም ሐሳብ አቀረበለት። ጎርጎርዮስ ግን እነዚህን ሹመቶች ይጠላቸው ስለነበረ እምቢ አለ። ይህም እምቢታ በሁለቱ ጓደኛሞች መካከል የነበረ ውን የጓደኛነት ፍቅር ወደ ማቀዝቀዝ አቃርቦት ነበር። ነገር ግን የጎርጎርዮስ አባት በጉዳዩ ገብቶ ሹመቱን እንዲቀበል አስገደደው። የኤጲስ ቆጶስነቱን ማዕረግ ከተሾመ በኋላ ወደ ሀገረ ስብከቱ በሚሄድበት ጊዜ ከኤጲስ ቆጶሳቱ አንዱ ተገናኘውና ሀገረ ስብከቱ የእኔ ነው በማለት እንዳይገባ ከለከለው። እርሱም ትቶለት ወደ ሀገሩ ተመለሰ። የቍስንጥንያ መንበር በመናፈቃን ተይዞ ስለነ በረ ኤጲስ ቆጶሳት ሁሉና ትልቁ ቴዎዶስይስ ጎርጎርዮስን በ380 ዓ.ም. የቍስጥንጥያ ኤጲስ ቆጶስ ለማድረግ በአንድ ድምፅ ተስማሙ። ለቦታው ባለመብት ሊገኝ ቦታውን እለቃለሁ በሚል ግዴታ ቦታውን ተረከበ።

መክሲሚያኖስ የኤጲስ ቆጶስነቱን ቦታ ለመውሰድ ብዙ ሙከራ አደረገ። የጎርጎርዮስንም ስም ማጥፋት ጀመረ። አንዳንድ ሰዎችም መክሲሚያኖስን እንዲሾምላቸው የእስክንድርያውን ፓትርያርክ አባ ጴጥሮስን ለመኑት። አባ ጴጥሮስም በጥያቄአቸው መሠረት ሾመላቸው። በዚያን ጊዜ ጎርጎርዮስ ታምሞ የነበረ ቢሆንም እንኳ ሹመቱን በሰማ ጊዜ ከከተማዋ ወጣ። ሕዝቡ ግን አዲሱን ኤጲስ ቆጶስ አንቀበልም በማለት ጎርጎርዮስን አስገድደው መለሱት።

የቍስጥንጥንያ ጉባኤ በተሰበሰበ ጊዜ ጳጳሳቱ ኒክታርዮስን ለቍስጥንጥንያ መንበር ኤጲስ ቆጶስነት መረጡት። እርሱም የጎርጎርዮስ ወዳጅ ስለነበረ ጎርጎርዮስ በጉዳዩ ተደስቶ በምሥጢር ወደ ሀገሩ ተመልሶ ራሱን ለአምልኮተ እግዚአብሔር ብቻ ለየ።

የብሕትውናውንም ሁናቴ ሲገልጥ እንዲህ ብሏል:- «የምኖረው በቋጥኞ ችና በአውሬዎች መካከል ነው፤ መኖሪያዬ ዋሻ ነው፤ ከአንድ ልብስ በቀር የለኝም፤ ጫማ አላደርግም፤ እሳት አላነድም፤ የምተኛው በዐፈር ላይ ነው፤ ስተኛም የምለብሰው ከአትክልት የተሠራ ጆንያ ነው፤ ትራሴም የተናቀ ዐይነት ነው፤ ሁልጊዜም እንባዬ እንዳረጠበው ነው።»

www.ethiopianorthodox.org

ነበቤ መለኮት የተባለውም በትምህርተ መለኮት ላይ ያለውን ጠለቅ ያለ ዕውቀት ለማመል
ከት ነው።

በስሙም የቅዳሴ ጸሎት አዘጋጅቶአል።

(አጭር የቤተ ክርስቲያን ታሪክን ይመለከቷል። ዮስጦስ ኤልድዌይሪ፥ ካይሮ እ.ኤ.አ
1949 ዓ.ም. ገጽ 234 – 235)።

<u>ባለ ሁለት ሰይፉ ቅዱስ መርቆርዮስ</u>:- ይህ ሰማዕት፥ በሮም ከተማ ከክርስቲያን ቤተሰብ
የተወለደ ነው። ወላጆቹ ስሙን ፊልዮፓቴር ብለው በመሰየም በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር
አሳድገውታል። ለጐልማሳነት ዕድሜ በደረሰ ጊዜ ኢአማኒ በነበረው በዳክዮስ ዘመነ መንግሥት
በውትድርና ተቀጠረ። እግዚአብሔር ኀይልና ድፍረትን ሰጥቶት በአለቆቹ ዘንድ ተወዳ ጅነትን
በማትረፍ መርቆርዮስ ብለው ስም ሰጥተውታል። በንጉሡ ዘንድም ቅርብነት ካላቸው ሰዎች
አንዱ እርሱ ለመሆን በቅቶአል።

በርበሮች በሮማውያን ላይ ባመፁ ጊዜ ከእነርሱ ጋር ለመዋጋት ዳክዮስ ወጥቶ ብዛታቸውን
ሲያይ ደነገጠ። እግዚአብሔር ጠላቶቻችንን አጥፍቶ እኛን አሸናፊዎች የሚያደርገን ስለሆ
አይዞህ አትፍራ ብሎ ቅዱስ መርቆርዮስ ዳክዮስን አበረታታው። ቅዱስ መርቆርዮስ ከንጉሡ
ተለይቶ ሲወጣ ነጭ ልብስ ለብሶና ሰው መስሎ አንድ መልአክ ተገናኝቶት ጠላቶችህን ድል
ብትነሣ ጌታ አምላክህን አስታውስ ብሎ አንድ ሰይፍ ሰጠው። (ባለሁለት ሰይፍም የተባለው
በዚሁ ምክንያት ነው፤ ይህም ማለት የውትድርናና የእግዚአብሔር ኀይል ሰይፍ ነው።)
በተመለሰ ጊዜ መልአክ

ዳክዮስ ጠላቶቹን ድል አድርጎ፥ መርቆርዮስም በአሸናፊነት በተመለሰ ጊዜ መልአክ
ተገልጦለት የቀድሞውን አባባል ማለት ጌታ እግዚአብሔርን እንዲያስታውስ ነገረው።

ዳክዮስ ከወታደሮቹ ጋር ሆኖ ለአማልክቱ ለማጠን በፈለገ ጊዜ ቅዱስ መርቆርዮስ ከእነርሱ
ተለየ። ጉዳዩን ለዳክዮስ ነገሩት። በዚህ ጊዜ አስጠርቶ የሚታለል መስሎት ስለ እርሱ ያለውን
አድናቆትና አክብሮት ነገረው። የጦር ሜዳ ጀግንነቱንና ድል አድራጊነቱን እያነሣሣ አሞገሰው
በመጨረሻም ለጣዖቱ እንዲሰግድና ዕጣን እንዲያጥን ጠየቀው። ቅዱስ መርቆርዮስ ግን ይህ
የንጉሡን አሳብ ሊቀበል ባለመፍቀዱ ንጉሡ ተቈጣ። በዚህ ጊዜ ቅዱስ መርቆ ርዮ
የመኰንንነት ትጥቁንና ልብሱን አውልቆ በንጉሡ ፊት ጣለና «ንጉሥ ሆይ የፈለግኸውን
ማድረግ ትችላለህ። እኔ ቸሩ ፈጣሪዬን አልተወውም፤ የእኔ ፈጣሪ ሰማይንና ምድርን የፈጠረ
ወልደ እግዚአብሔር ነው እንጂ እንደዚህ ጣዖት አይደለም። እኔ የክርስቶስ ነኝ» በማለት በታላቅ
ድፍረት ተናገረ፤ ስለ ክርስቶስ አምላክነት ያለ ፍርሀት መሰከረ፤ የንጉሡንም ጣዖት አዋረደ
የሮም ሕዝብ የሚንቀጠቀጥለትን ቄሣር ከምንም አልቈጠረውም። ይህም የሆነው የእግዚአብ
ሔር ኃይል ከእርሱ ጋር ስለነበረ ነው።

ንጉሡ ይህን ሲሰማ ተቈጣ፤ እጅግም ተናደደ። በዙሪያው የቆሙት ወታደ ሮቹ እንደ
ተራቡ አንበሶች ቅዱስ መርቆርዮስን እንዲበጫጭቁት ወደደ፥ ግን የከተማው ሕዝብ
ከሠራዊቱ አብዛኛው ቅዱስ መርቆርዮስን ስለሚከተሉት፥ በጀግንነቱም ስለሚወዱት ከፍተኛ
ዐመፅን እንደሚቀሰቀስ ፈርቶ በጅራፍ ካስገረፈው በኋላ በሰንሰለት አስሮ ወደቂሣርያ ሰደደው
በብረት አልጋ ላይ አጋድመው

ከዚህም በኋላ በተለያየ ሥቃይ እንዲሠቃይ ተደርጓል። በብረት አልጋ ላይ አጋድመው
ከሥር እሳት አነደዱበት፤ ይሁን እንጂ፥ ደሙ እየተንጠፈጠፈ ወርዶ እሳቱን አጥፍቶታል
ለልማዱ ደም እንደ ሰም እሳት ያቀጣጥላል እንጂ አያጠፋም። የቅዱስ መርቆርዮስ ደም ግን
በአምላካዊ ተአምር እሳቱን አጥፍቶታል።

ቅዱስ መርቆርዮስ፥ ዳኬዎስ ቄሣር ክርስቲያኖችን በፈጀባቸው በሦስቱ ዓመታት (349-
351) ወንጌልን በማስተማር፥ ስለ ክርስቶስ በመመስከር፥ ምእመናንን በማጽናናትና በመምከር
ቄሣር ዳኬዎስንና መኳንንቶቹን ስለ እውነት በመገሠጽ፥ አምልኮ ጣዖትን በማጥፋት አምልኮተ
እግዚአብሔርን በማስፋፋት መልካም ተጋድሎ ተጋድሎአል፥ በመጨረሻም ኅዳር 25 ቀን
351 ዓ.ም. አንገቱን በሰይፍ ተቆርጦ የተቀደሰ ተጋድሎውን ፈጽሞአል።

ቅዱስ መርቆርዮስ በዚህ ዐይነት ተጋድሎውን ከፈጸመ በኋላ ሦስት አክሊ ላትን ተቀዳጅቶ
ሦስት ዓመት የተጋደለላትንና በተስፋ ደጅ የጠናትን የእግዚ አብሔርን መንግሥት ወርሶአል
ለሰማዕቱ የተሰጡት ሦስቱ አክሊላት፥ አንዱ ሰለ ድንግልናው፥ 2ኛው ይህን ኃላፊ ዓለም
ስለመናቁ፥ 3ኛው ክርስቶስን በማመን ጸንቶ በሰማዕትነት ስለመሞቱ ነው። ይህም ሰማዕቱ
ከፈተኛ ክብርና በእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን ባለሟልነት ያገልጣል።



ቅዱስ መርቆርዮስ ከሞተ ከ12 ዓመት በኋላ በ363 ዓ.ም. ያደረገው አስደናቂ ተአምር
ሁልጊዜ ሲወሳ ይኖራል። ዩልያኖስ የተባለው አረማዊ ቄሣር፥ ክርስቲያኖችን ሲያሳድድ፥
አብያተ ክርስቲያንን ሲያነድ፥ ቅዱስ ባስልዮስና (330–79 ቅዱስ ገርጎርዮስ ( 330–395)
በሰማዕቱ በቅዱስ መርቆርዮስ ሥዕል ፊት ቆመው እግዚአብሔር የመከራውን ዘመን አሳልፎ
ሰላምና የዕረፍት ዘመን እንዲተካ ቅዱስ መርቆርዮስ ይማልድ ዘንድ ጸለዩ። እየጸለዩ ሳሉም
ሥዕሉ እሺ እንደሚል ሰው አንገቱን ዘንበል አድርጓል፤ ቅዱሳን ባስልዮስና ጎርጎርዮስም ይህን
ምልክት ከሥዕሉ ባዩ ጊዜ ደስ አላቸው። የክርስቲያኖች አሳዳጅ ዮልያኖስም ካልታወቀ አቅጣጫ
በተወረወረ ፍላጻ ተወግቶ ሞቷል። ባስልዮስና ጎርጎርዮስም እንደገና ከሥዕሉ ፊት ቆመው
«ቀተልኮኑ ለኡልያኖስ:- ቅዱስ መርቆርዮስ ሆይ ዐመፀኛውንና ከሃዲውን ዩልያኖስን ገደልከ
ውን? አያሉ ለጊዜው ለክርስቲያኖች ስለተገኘው ዕረፍት ደስ ብሏቸዋል።

ቅዱሳን በአጸደ ሥጋም በአጸደ ነፍስም ሆነው እንደሚያማልዱ፥ ለደጋጉ መልካም እንዲደረ
ግላቸው በክፉዎች ደግሞ የከፋታቸው ብድራት እንዲመለስባቸው የሚጸልዩ መሆናቸውን ከዚህ
ታሪክ መረዳት ይቻላል። በዮሐንስ ራእይ 6፥ 10 ላይ የተጻፈውም ከዚህ ጋር ፍጹም ተመሳሳ
ይነት አለው።

ቅዱስ መርቆርዮስ በሃይማኖታችን ምክንያት መከራና ችግር ቢደርስብን እንኳን መከራውን
እንድንታገሥ ስለ እኛ ይጸልያል፤ ቅዱሳን ባስልዮስንና ጎርጎርዮስን እንደ ረዳቸው እኛንም
ይረዳናል።

ቅዱስ መርቆርዮስ በወጣትነት ዕድሜው በ24 ዓመቱ በእምነት ተጋደለ፤ ጠላትን ድል
ነሣ፤ ጽድቅን አደረገ፤ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አገኘ፤ እንደ አንበሳ የተነሡበትን የጣላቶችን
አፍ ዘጋ፤ እሳቱን በደሙ አጠፋ፤ የሰይፉን ስለትና የጅራፉን ግርፋት ታገሠ፤ በዚህም ሁሉ
መንፈሳዊ ኃይሉ፥ ትዕግሥቱና ቈራጥነቱ ለወጣት ክርስቲያኖች ሁሉ መመኪያና ጠባቂ ሰማዕት
ነው።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ይህን ቅዱስ ሰማዕት በዓመት ሦስት ጊዜ በመንፈሳዊ ክብር
ታከብራዋለች፤

1ኛ. ኅዳር 25 ቀን ዕረፍቱን፥ 2ኛ. ጥር 25 ቀን ከእግዚአብሔር መልአክ ሰማያዊ ሰይፍ
የተቀበለበትንና 3ኛ ሐምሌ 25 ቀን በስሙ የታነጸው ቤተ ክርስቲያን የተባረከበትን (ቅዳሴ
ቤቱን) ታከብራለች።

ምእመናን በጸሎቱና በአማላጅነቱ በረከትንና ረድኤትን እንደሚያገኙ ታስተምራለች። እኔ
የክርስቶስ ነኝ፥.. አምላኬን ኢየሱስ ክርስቶስን አልተ ውም...» በማለት በዐላውያን ፊት
የተናገረውን ምስክርነት አንብባ በመተ ርጐም ምእመናንን ታበረታታለች፥ ታጽናናበታለች፥

የኅዳር 25 ቀን ስንክሳር

<u>ቅዱስ ያሬድ</u>:- ቅዱስ ያሬድ በ505 ዓ.ም. በትግራይ ክፍለ ሀገር በአክሱም ተወለደ። አባቱ
ይስሐቅ እናቱም ታውክልያ ይባሉ ነበር። በተወለደ በሰባት ዓመቱ አባቱ ስለሞተ እናቱ የአክ
ሱም ገበዝ ለነበረው ለአጎቱ ለጌዴዎን እንዲያሳድገውና እንዲያስተምረው በዐደራ ሰጠችው።

ያሬድ በመጀመሪያ በትምህርቱ ደካማ ነበር፤ ይህም በመሆኑ የፊደል ጥናት ብዙ ጊዜ
ወሰደበት። መምህሩም ብዙ ጊዜ ስለገረፈው ከትምህርት ቤቱ ጠፍቶ ሄደ። እግረ መንገዱን
በአንድ ዛፍ ሥር ዐርፎ ሳለ አንዲት ትል በዛፉ ላይ ለመውጣት ስትፍጨረጨር አየ። ጥቂት
እንደወጣች ስትወድቅ አያት። እንደገ ናም ለመውጣት ሞከረችና ተመልሳ ወደቀች። እንደዚህ
እየወደቀችና እየተነሣች ስድስት ጊዜ ያኽል ከሞከረች በኋላ በመጨረሻ ተሳክቶላት ወጣች።

ያሬድ የትልዋን ከፍተኛ ጥረት ተመልክቶ ከትልዋ እንደማያንስ ገመተ። የትልዋ ትጋት፥
ትዕግሥትና አለመሰልቸት ለያሬድ ትምህርትና ምሳሌ ሆነው። ወዲያውኑ ወደ አስተማሪው
ተመለሰና ይቅርታ ጠይቆ ትምህርቱን ቀጠለ።

ከዚያ በኋላ መንፈስ ቅዱስ አእምሮውን አበራለትና በአጭር ጊዜ ብሉይንና ሐዲስን አጠና።
ዛሬ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትገለገልበትን ዜማ ሁሉ ያዘጋጀ ያሬድ ሲሆን የዜማውን
ስልት ከሦስት ወፎች እንደቀሰመው በገድሉ ውስጥ ተጽፎ ይገኛል።

የያሬድ የዜማ ስልቶች ሦስት ናቸው። እነርሱም:- ግእዝ፥ አራራይ፥ ዕዝል ናቸው። እንዲ
ሁም በርካታ የዜማ መጻሕፊትን የደረሰ ሲሆን እነርሱም:- ጾመ ድጓ፥ ድጓ፥ ምዕራፍና ዝማሬ
መዋሥዕት ናቸው።

www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ያሬድ የደረሳቸው መዝሙሮች ከብሉይ፥ ከሐዲስና ከሐዋርያት መጻሕፍት የተው ጣጡ በመሆናቸው ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ምሥጢር አላቸው። ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን ሳታቋርጥ ትጠቀምባቸዋለች።

ቅዱስ ያሬድ ግንቦት 11 ቀን 571 ዓ.ም ዐርፎ በስሙ በሚጠራው በሰሜን ተራራ ገዳም ተቀብሮአል።

(የግንቦት 11 ቀን ስንክሳርና ገድለ ያሬድን ይመለከቷል)

ኢትዮጵያዊው ጻድቅ አቡነ ተክለ ሃይማኖት:- ኢትዮጵያ የብዙዎች ቅዱሳን ሀገር ናት። ከታወቁት ብዙዎች ቅዱሳን አንዱ ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ናቸው። የጻድቁ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት አባት ጸጋ ዘአብ ይባላል። እርሱም በሸዋ ክፍለ ሀገር በቡልጋ አውራጃ እቲሳ በሚባለው ቦታ ይኖር ነበር።

ጸጋ ዘአብ ካህን ነበር። እግዚእ ኀረያ የተባለች እግዚአብሔርን የምትፈራ ደግ ሴት አግብቶ ሲኖር ሞተለሚ የተባለው የወላሞ ንጉሥ ወደ ቡልጋ ዘምቶ ወረራ ባደረገ ጊዜ የጸጋ ዘአብን ሚስት እግዚእ ኀረያን ማርኮ ወደ ወላሞ ወሰዳት።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን በእግዚብሔር ኀይል ወደ አገርዋ ወደ እቲሳ ተመልሳ ገባች። ጸጋ ዘአብም በሚስቱ መማረክ እያዘነ ቀንና ሌሊት ወደ እግዚአብሔር ይጸልይ ነበርና እግዚአብሔር ጸሎቱን ሰምቶ ሚስቱን ስለመለሰለት እግዚአብሔርን በደስታ አመሰገነ።

ከዚህም በኋላ በ1152 ዓ.ም ታሕሣሥ 24 ቀን ወንድ ልጅ ወለደችለት። ስሙንም ፍሥሐ ጽዮን ብሎ ጠራው። ፍሥሓ ጽዮን ማንኛውንም የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ከአባቱ ከካህኑ ጸጋ ዘአብ እየተማረ ዐደገ። ካደገም በኋላ ፈረስ መጋለብና አውሬ ማደን ተማረና ይህን ሥራ አጠንክሮ ሲኖር እግዚአብሔር ፍሥሐ ጽዮንን ከዚህ ሥራው መለሰው። ፍሥሐ ጽዮን ያን ጊዜ የኢትዮጵያ ጳጳስ ከነበረው ከ1ኛ ጌርሎስ (ቄርሎስ) ዲቁናና ቅስናን ተቀበሉ። በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ቦታዎች እየተዘዋወሩ ወንጌልን አስተማሩ፤ ብዙ ሰዎችን ከጨለማ ወደ ብርሃን መለሱ። በወንጌል ትምህርታቸውም እንደ ቅዱስ ጳውሎስ አዲስ ሐዋርያ ዘኢትዮጵያ ተባሉ። ፍሥሐ ጽዮን የተባለው ስማቸውም ተለውጦ ተክለ ሃይማኖት ተባለ። ተክለ ሃይማኖት ብሎም የሰየማቸው ከእግዚአብሔር የተላከው ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ነው።

ተክለ ሃይማኖት በወንጌል ማስተማር ተግባር ብዙ ጊዜ ከቈዩ በኋላ ወደ አማራ ሳይንት አባ በጸሎተ ሚካኤል የተባሉ ኢትዮጵያዊ ጻድቅ ወደነበሩበት ግሽቅ ወደ ተባለ ገዳም ሄዱ። በዚህም ገዳም መነኲሳትን እያገለገሉና የትሩፋት ሥራን እየሠሩ በገዳማዊ ሕየወት ኖሩ።

በአባ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም ዐሥር ዓመት ከቆዩ በኋላ ወደ አባ ኢየሱስ ሞአ ገዳም ወደ ሐይቅ ሄዱ። በዚያም ከአባ ኢየሱስ ሞአ የምንኵስና ልብስ ለበሱ። በሐይቅ ገዳምም ለዐሥር ዓመት ያኽል ቈይተው በትግራይ ውስጥ ወደሚገኘው ወደ ደብረ ዳሞ ገዳም ሄደው አባ ዮሐኒ ከተባሉት አባት ቆብና አስኬማ ተቀበሉ( ለበሱ) በደብረ ዳሞ ዐሥራ ሁለት ዓመት ቆይተው ከተመለሱ በኋላ የቀደመ የወንጌል ማስተማር ሥራቸውን ቀጠሉ። በኢትዮጵያ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የስብከታቸው ብርሃን ያልደረሰበት አገር የለም። በዚህም ምክንያት ተክለ ሃይማኖት ፀሐይ ተብለዋል። ብዙ የተለያዩ ተአምራትና ድንቅ ሥራዎች በእጃቸው ተደርገዋል። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ብዙ ድውያንን ፈውሰዋል፥ ሙታንን አንሥተዋል፥ ርኩሳን መናፍስትንም አውጥተዋል።

ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት ዲቁናና ቅስና የሰጣቸው ጳጳስ ጌርሎስ ከሞተ በኋላ በምድረ ግብጽ በየብስና በባሕር ጦርነት ስለ ሆነ መንገዱ ተዘጋ። በዚህም ምክንያት ከእስክንድርያ ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ ለማስመጣት ባለመቻሉ ኢትዮጵያ ያለ ጳጳስ ብዙ ዓመቶች ቈየች።

በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ከየገዳማቱና አድባራቱ ተሰብስበው ጉባኤ አደረጉ። የምድረ ግብጽ መንገዱ እስኪከፈትና ጳጳስ ከእስክንድርያ እስኪመጣ ድረስ ኢትዮጵያ ያለ ጳጳስ መኖር አይገባትምና ከሀገራችን ሃይማኖቱ የጸና ምግባሩ የቀና አንድ ሰው መርጠን ጳጳስ አድርገን እንሹም ብለው ወሰኑ።

በዚያ ወራት በኢትዮጵያ አውራጃዎች እየተዘዋወሩ በማስተማርና በመስበክ፥ ተአምራትም በማድረግ የታወቁና የተወደዱ ሐዲስ ሐዋርያ ብርሃን ዘኢትዮጵያ እየተባሉ የሚጠሩ አቡነ ተክለ ሃማኖት ስለነበሩ፥ ከእርሳቸውም የሚበልጥ ሌላ ሰው ባለመገኘቱ በእግዚአብሔር ፈቃድ፥ በቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነት ሊቃውንቱ እርሳቸውን መርጠው ጵጵስና ሾሙአቸው።



ቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጳጳስ ከሆኑም በኋላ በይበልጥ በኢትዮጵያ አውራጃዎች እየተዘዋወሩ ታቦታትን እየባረኩ፥ ዲቁናና ቅስና እየሾሙ፥ አረማውያንን በማስተማር እያሳመኑና እያጠመቁ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል የወንጌልን ብርሃን አበሩ።

አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወንጌልን እያስተማሩ፥ ዲቁናና ቅስና እየሾሙ፥ ታቦታትንና አብያተ ክርስቲያንን እየባረኩ ከኖሩ በኋላ ሲሸመግሉ ደብረ ሊባኖስ በሚባለው ገዳም የብሕትውና ሥራ ጀመሩ።

ከዚህ በኋላ አቡነ ዮሐንስ 5ኛ የተባለው ጳጳስ ተሹሞ ከእስክንድርያ ወደ ኢትዮጵያ በመጣ ጊዜ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን በአንድነት ለመሥራት ጠየቃቸው። ይልቁንም «አንተ በኢትዮጵያ እኩሌታ ኤጲስ ቆጶስ ሁን፤ እኔም በእኩሌታዋ ጳጳስ እሆናለሁ» ቢላቸው «ለእኔ ለመጻተኛው ይህ ሥራ አይገባኝም ይህን የምወደው ከሆነ ቀድሞም ከእግዚአብሔር ዘንድ ተፈቅዶልኝ ነበር። እነርሱም እነሆ ክህነት የምሾምበት መጽሐፍና ቅብዐ–ሜሮን በመልአኩ እጅ ልኮልኝ ነበር፤ እነዚህ ናቸው ብለው አሳዩትና ለጳጳሱ አስረከቡት። ከዚህ በኋላ ወደ ገዳማቸው ወደ ደብረ ሊባኖስ ተመልሰው የጀመሩትን የብሕትውና ሥራ ቀጠሉ። በዚያም ብዙ ወንዶችና ሴቶች መነኰሳትን አሰባስበው እስከ ዛሬ በስማቸው የሚጠራውን ገዳማዊ አንድነትን ካቋቋሙ በኋላ በነሐሴ 24 ቀን 1266 ዓ.ም. ዐርፈው አሁን ደብረ ሊባኖስ በሚባለው በደብረ ዐስቦ ተቀበሩ።

አቡነ ተክለ ሃይማኖት በዓመት ሦስት ጊዜ የመታሰቢያ በዐል አላቸው። 1ኛ ታሕሣሥ 24 ቀን የተወለዱበት፥ 2ኛ ነሐሴ 24 ቀን ያረፉበት ሲሆን 3ኛ ግንቦት 12 ቀን ዐፅማቸው የፈለሰበት ነው።

ገድለ ተክለ ሃይማኖት
ቀዜማ ከብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ
1921 ዓ.ም ኀሐ–ጽባሕ ማ/ቤት
አዲስ አበባ

## የቤተ ክርስቲያን ዜማ

### በግዕዝ

ይካ:- ሀበነ ንኅበር በዘኢአከ:መንፈስ ቅዱስ፤ ወፈውሰነ በዝንቱ ጽርሰፎሬ። ከመ ብከ ንሕየው ዘለኵሉ ዓለም ወለዓለመ ዓለም።

ይ:ሕ:- ከማሁ

ይ:ካ:- ቡሩክ ስሙ ለእግዚአብሔር ወቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር፤ ወይትባረክ ስመ ስብሐቲሁ። ለይኩን ለይኩን ቡሩክ ለይኩን።

ይ:ሕ:- ከማሁ

ይ:ካ:- ፈኑ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ላዕሌነ

ይ:ሕ:- ከማሁ

ይ:ዱ:- ተንሥኡ ለጸሎት

ይ:ሕ:- እግዚኦ ተሣሃለነ።

ይ:ካ:- ሰላም ለኵልክሙ

ይ:ሕ:- ምስለ መንፈስከ

ይ:ዲ:- ጸልዩ

ይ:ሕ:- አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ፤ ትምጻእ መንግሥትከ፤ ወይኩን ፈቃድከ በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር። ሲሳየነ ዘለለ ዕለትነ ሀበነ ዮም። ኅድግ ለነ አባሳነ ወጌጋየነ። ከመንሕነኒ ንኅድግ ለዘአበሰ ለነ። ኢታብእነ እግዚኦ ውስተ መንሱት። አላ አድኅነነ ወባልሐነ እምኵሉ እኩይ። እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት፤ ኀይል ወስብሐት ለዓለመ ዓለም። በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አበሳነ (3ተ ጊዜ) ሠራዊተ መላእክቲሁ ለመድኅኔ ዓለም ዮ: ዮ :ዮ: ይቀውሙ ቅድሜሁ ለመድኅኔ ዓለም። ወይኬልዎ ለመድኅኔ ዓለም ዮ፡ ዮ፡ ዮ፡ ሥጋሁ ወደሙ ለመድኅኔ ዓለም ወንብጻሕ ቅድመ ገጹ ለመድኅኔ ዓለም ዮ: ዮ ዮ በአሚነ ዚአሁ ለክርስቶስ ንገኒ። (ሐዋርያት ተለዉ ዓሠሮ)

www.ethiopianorthodox.org

## በአማርኛ

ይካ:- ያንተ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስ አንድ አድርገን፤ በዚህ በሥጋው በደሙ አድነን፤ በአንተ ለዓለም ሁሉ የሚሆን ሕይወትን ለዘለዓለም እንኖር ዘንድ

ይ:ሕ:- እንደርሱ ይበሉ።

ይ:ካ:- የእግዚአብሔር ስሙ ምስጉን ነው።

በእግዚአብሔር ስም የሚመጣውም ምስጉን ነው። የጌትነት ስሙ ይመስገን ይሁን፤ ይሁን፤ ስሙ የተመሰገነ ይሁን።

ይ:ሕ:- እንደርሱ – የካህኑን አባባል ይድገሙ

ይ:ካ:- የመንፈስ ቅዱስን ሀብት አሳድርብን።

ይ:ሕ:- እንደርሱ ይበሉ

ይ:ዲ:- ለጸሎት ተነሡ።

ይ:ሕ:- አቤቱ ይቅር በለን።

ይ:ካ:- ሰላም ለሁላችሁ ይሁን

ይ:ሕ:- ከመንፈስህ ጋር

ይ:ዲ:- ጸልዩ

ይ:ሕ:- በሰማይ ያለህ አባታችን፥ ስምህ ይመስገን፤ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነ እንዲሁ በምድር ይሁን፤ የዕለት ምግባችንን ዛሬ ስጠን። ኃጢአታችንንና በደላችንን ይቅር በለን። እኛም የበደሉንን ይቅር እንድንል። አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን፤ ከክፉ ነገር ሁሉ አድነን እንጂ። መንግሥት ያንተ ናትና፤ ኀይል ምስጋናም ለዘለዓለሙ (ሦስት ጊዜ) አምላካችን እንደ ቸርነትህ እንጂ እንደ በደላችን አይሁን። ሁሉም በመፈራረቅ ይህን ይበሉ (3 ጊዜ) የመድ ኀኔዓለም አገልጋዮች ሠራዊት ዮ፥ ዮ፥ ዮ በመድኀኔዓለም ዓለም ፊት ይቆማሉ፤ መድኀ ዓለምን ያመሰግኑታል ዮ፥ ዮ፥ ዮ የመድኀኔ ዓለም ሥጋውና ደሙ ይህ ነው።

ወደ መድኀኔ ዓለም ፊት እንቅረብ፤ ዮ፥ ዮ፥ ዮ እርሱን በማመን ለክርስቶስ እንገዛለን (ሐዋርያት እርሱን አምነው ተከተሉ)

## ጥያቄዎች

1. አስተዳደር ማለት ምን ማለት ነው?
2. ሥራው የሚካሄደው በማን ነው?
3. ቍጥጥር የሚደረገው በማን ላይ ነው
4. በአስተዳደር ተግባር ውስጥ ምን ምን ይገኛሉ?
5. አንድ የሥራ ተቋም ሲጀመር ምን ይዘጋጃል?
6. ምን ሲሆን ነው ለበላይ ባለ ሥልጣን ቀርቦ ውሳኔ የሚሰጥበት?
7. ቍጥጥር የሚደረገው በምን መሠረት ነው?
8. በአስተዳደር ሥራ ውስጥ ሥራው የተሳካ እንዲሆን ምን ይደረጋል?
9. የአስተዳደር ሥነ ሥርዓትን በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ያቀረበው ማሳሰቢያ ምን የሚል ነው?
10. ቤተ ክርስቲያን ምን ዐይነት መመሪያዎች አሉአት?
11. የኢየሩሳሌም ጉባኤ የተሰበሰበው በምን ምክንያት ነው?
12. ዲያቆናት የተሾሙት በምን ምክንያት ነው?
13. ዓለም ዐቀፍ የአብያተ ክርስቲያን ጉባኤዎች ለምን ይሰበሰቡ ነበር?
14. ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ ሥርዓት አስፈላጊነት የቀረቡት ሦስት ምሳሌዎች ምን ምን ናቸው?
15. በቀድሞ ጊዜ ይሰበሰቡ የነበሩት ዓለም ዐቀፍ ጉባኤዎች ከምን ጋር ይመሳሰላሉ?
16. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስንና ቲቶን ያዘዛቸው አስተዳደራዊ ተግባር ምን ነበር?



17. አንዳንድ ሰዎች ካልተገረዛችሁ አትድኑም ብለው ያስተማሩት የት አገር ነው?
18. ሦስቱ የክህነት ደረጃዎች ምን ምን ናቸው?
19. ድሜጥሮስ የተባለው ቅዱስ ማነው?
20. ከመሾሙ በፊት ምን ያኽል ትምህርት ነበረው?
21. ፓትርያርክ ዩልያኖስ ድሜጥሮስን እንዴት ዐወቀው?
22. የእግዚአብሔር መልአክ ለፓትርያርክ ዩልያኖስ የነገረው ምንድነው?
23. ድሜጥሮስ በመጣ ጊዜ ዩልያኖስ ምን አደረገ?
24. ከዚያስ ድሜጥሮስን ምን አደረጉት?
25. ዩልያኖስ ከሞተ በኋላ ለድሜጥሮስ ምን ዐይነት ዕውቀት ተገለጠለት?
26. የአብቀጢን (አበቅቴ) ሥርዓት የመሠረተ ማነው?
27. ከዚያ ሥርዓት በፊት ዓቢይ ጾመ የሚጾመው በምን ጊዜ ነበር?
28. ለድርጊቱስ የሚሰጠው ምክንያት ምን ነበር?
29. የሕማማት ጾም ከዐቢይ ጾም ተለይቶ ይጾም የነበረው በምን ምክንያት ነው?
30. ከክርስቲያኖች መካከል የትንሣኤን በዓል ያከብሩበት የነበረው አንድ የተወሰነ ቀን መቼ ነበር?
31. ዐቢይ ጾምን ከሕማማት ጾም ጋር ያጠቃለለው ማነው?
32. ጎርጎርዮሳዊው የዘመን አቈጣጠር ሥርዓት ከመጀመሩ በፊት በየዓመቱ የትንሣኤ በዓል የሚከበርበትን ቀን ለየአብያተ ክርስቲያኑ የሚያስተላልፍ ማን ነበር?
33. ይህስ የሚደረገው በምን ምክንያት ነበር?
34. እግዚአብሔር ሁልጊዜ ከፓትርያርክ ድሜጥሮስ ጋር የነበረው በምን ምክንያት ነው?
35. ቅዳሴውን ከፈጸመ በኋላ ለማቍረብ ሲዘጋጅ ጌታችን ምንን ይገልጽለት ነበር?
36. በዚህስ መገለጥ ምክንያት ምን ያደርግ ነበር?
37. ኃጢአተኞችን ከመገሠጹና ወደ ንስሓ ከመምራቱ ብዛት የተነሣ አንዳንድ ሰዎች ምን ብለው አጕረመረሙ?
38. እግዚአብሔር የድሜጥሮስን ማንነት ለመግለጥ ስለፈቀደ ምን አደረገ?
39. ድሜጥሮስስ በእርሱና በሚስቱ መካከል ስለነበረው ግንኙነት ለመግለጥ ምን አደረገ?
40. በዚህ ድርጊቱስ ምን ተአምር ታየ?
41. የሕዝቡን መገረም ሲያይ ለሕዝቡ ምን አለ?
42. ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት የተወለደው የት ነው?
43. በመርከብ ወደ አቴና ሲሄድ በምን ምክንያት ስለት ተሳለ? የተሳለውስ ምን ብሎ ነው?
44. አቴና በደረሰ ጊዜ ማን የሚባል ጓደኛውን አገኘ?
45. የጎርጎርዮስና የጓደኛው ወዳጅነት ሊቀዝቅዝ የተቃረበው በምን ምክንያት ነው?
46. በዚህ ጉዳይ የጎርጎርዮስ አባት ምን አደረገ?
47. የቍስጥንጥንያ መንበር ባዶ በሆነበት ጊዜ ጎርጎርዮስ በታውን ለመረከብ የተስማማው በምን ግዴታ ነው?
48. ጎርጎርዮስ በተሾመ ጊዜ መክሲሚያኖስ ምን አደረገ?
49. የእስክንድርያው አባ ጴጥሮስ ምን አደረገ?
50. ጎርጎርዮስ ምን አደረገ? ሕዝቡስ ምን አደረገ?
51. የቍስጥንጥንያ ጉባኤ በተሰበሰበ ጊዜ ለቍስጥንጥያ መንበር ማን ተመረጠ?
52. ጎርጎርዮስ፥ ነባቤ መለኮት የተባለው ለምንድነው?
53. መርቆርዮስ የተወለደው የት ነው?
54. ውትድርና የተቀጠረው በማን ዘመን ነው?
55. ወላጆቹ ያወጡለት ስም ማን ይባል ነበር?
56. ታዲያ መርቆርዮስ ያለው ማነው?
57. ዳክዮስ በፈራ ጊዜ መርቆርዮስ ምን አለው?
58. ባለሁለት ሰይፍ የተባለው በምን ምክንያት ነው?

www.ethiopianorthodox.org

59. ከዳክዮስ ጋር ለምን ሳይግባባ ቀረ?
60. ዳክዮስ ሕዝብ ያምፅብኛል ብሎ የፈራው በምን ምክንያት ነው? ታዲያ ምን አደረገ?
61. በመጨረሻ መርቆርዮስ ምን ሆነ?
62. ቅዱስ ያሬድ የተወለደው የት ነው?
63. በስንት ዓመት ዕድሜው አባቱ ሞተ?
64. እናቱስ ምን አደረገች?
65. ቅዱስ ያሬድ ከመጀመሪያ ጀምሮ በትምህርቱ ጐበዝ ነበርን?
66. ከአስተማሪው ሸሽቶ የሄደው በምን ምክንያት ነው?
67. ቅዱስ ያሬድ ትጋትን፥ አለመሰልቸትንና ትዕግሥትን ከምንና እንዴት ተማረ?
68. ከዚያስ ምን አደረገ?
69. በአጭር ጊዜ ውስጥ ያጠናው ምንን ነው?
70. የቅዱስ ያሬድ የዜማ ስልቶች ስንት ናቸው? እነርሱስ ምን ምን ናቸው?
71. ቅዱስ ያሬድ የደረሳቸው የዜማ መጻሕፍት ምን ምን ናቸው?
72. የአቡነ ተክለ ሃማኖት አባትና እናት ማንና ማን ይባላሉ?
73. የአቡነ ተክለ ሃማኖት የቀድሞ ስም ማን ይባል ነበር?
74. አስኬማ የለበሱት የት ነው?
75. ተክለ ሃይማኖት ፀሐይ የተባሉት በምን ምክንያት ነው?
76. አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጵጵስና የተሾሙት በማን ተራዳኢነት ነው?
77. አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሲሸመግሉ ወዴት ሄዱ?
78. አቡነ ተክለ ሃይማኖት ያረፉት መቼ ነው?

## ምዕራፍ 5

## መንፈሳዊነትና ግብረ ገብነት

### የክርስቲያናዊ ሕይወት መመሪያ

ጥላቻ ወይም ፍትወት ሳይሆን ንጹሕ ፍቅር:- ክርስቲያናዊ ሕይወትን ለመኖር የወሰነ ሰው ሰውን ሁሉ ሊወድ ይገባል። ፍቅርም ሲባል ፍትወታዊ የጾታ ፍቅር ሳይሆን ማንንም ከማንም ሳይለዩ ከልብ መውደድ ነው። ይህንኑ ዐይነት ፍቅር ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብ ሔርን ከመውደድና ከማምለክ ቀጥሎ ከሕግጋት ሁሉ ያስበለጠው (ማቴ:ም:23 ቍ:1–12)።

እንዲሁም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው የመጀመሪያ መልእክቱ ምንም ያኽል ሃይማኖት አለን ብንልና ምንም ያኽል በጎ ተግባር ብንፈጽም ፍቅር ከሌለን ከንቱ መሆኑን ይገልጣል (1ኛ: ቆሮ:ም:13)።

እውነተኛ ፍቅር ያለው ሰው ጥላቻ አይኖረውም። ጥላቻም የሰይጣን ስሜት ነው። መጥላት ያለብን ኃጢአትን እንጂ ኃጢአተኛውን አይደለም። በፍቅራችን ኃጢአተኛውን ከኃጢአቱ እንመልሰዋለን።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ኃጢአተኞችን ሁሉ ስለወደደ ቤዛ በመሆን ኃጢአታቸውን ሊያስወግድላቸው ወደዚህ ዓለም መጣ። ይህም አባ ሕርያቆስ:- «ኀያል ወልድን ፍቅር ከዙፋኑ ሳበው፤ እስከ ሞትም አደረሰው» እንዳለው ነው (ቅዳሴ ማርያም ቍ:127)።

እንዲሁም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቀ:- «ፍቅር የአምላክን ልጅ ከዙፋኑ ሳበው፤ እስከ ሞትም አደረሰው፤ በደል የሌለበትን እንደ በደለኛ ሰቀሉት፤ ሕይወትን የሠራውን ከበደለኞች ጋር ቈጠሩት» እንዳለው ነው» (የዮሐንስ አፈወርቅ ቅዳሴ፥ ቍ:53)።

ሰውን ማሳዘን ሳይሆን ሰውን ማጽናናት:- በማንኛውም ጊዜ ያዘነ ሰው ሲታይ ማጽናናት ክርስቲያናዊ ተግባር ነው። ሰዎች ብዙ ጊዜ በተለያዩ ምክንያቶች ያዝናሉ። ከእነርሱ ጋር የሐዘናቸው ተካፋይ ከመሆንም በላይ በተቻለ መጠን እንዲጽናኑ መርዳት ይገባል እንጂ ማንም ሰው ሐዘን እንዲደርስበት ምክንያት መሆን አይገባም። ሁልጊዜ በንግግር፥ በተግባር፥ ወይም



በአስተያየት ሌላውን ሰው ቅር ማሰኘት ወይም ማሳዘን ተገቢ አይደለም። እያንዳንዱ ሰው ሌላ ሰው እንዲያሳዝነው አይፈቅድም፤ በሌላ በኩል ደግሞ ማንም ሰው በሐዘኑና በችግሩ ጊዜ አይዞህ ብሎ የሚያጽናናው ሰው ቢኖር ደስ ይለዋል።

ይህም በመሆኑ ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ:- «ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን ሁሉ እናንተም እንዲሁ አድርጉላቸው» ያለው (ማቴ:ም:7 ቍ:12 : ሉቃ:ም:6 ቍ:31)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዚህ ምሳሌ ሊሆንልን ብሎ ነው ከአልዓዛር እኅቶች ጋር በማልቀስ የሐዘናቸው ተካፋይ ከሆነ በኋላ ወንድማቸውን አልዓዛርን ከሞት ያስነሣው (ዮሐ:ም:11)።

እንዲሁም በናይን ከተማ ለመበለቲቱ አዝኖላት የሞተውን ልጅዋን አስነሥቶላታል (ሉቃ:ም:7 ቍ:11–17)።

በሌላ ጊዜ ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ፥ ጌታቸውና መምህራቸው ከእነርሱ ተለይቶ እንደሚሄድ ሲገልጥላቸው የሐዘን ስሜት ስለተሰማቸው የእርሱ መሄድ ለእነርሱ እንደሚጠቅማቸው በመግለጥና እርሱም ከሄደ በኋላ አጽናኝ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው ተስፋ በመስጠት አጽናንቶአቸዋል (ዮሐ:ም:14፥ ቍ:16)።

ጌታችን ባደረጋቸው ድርጊቶች ሁሉ እንደ እርሱ እንድናደርግ ሲ.መራን እኔን ምሰሉ ብሎአል (ማቴ:ም:11 ቍ:29፥ ዮሐ:ም:13 ቍ:34–35)።

ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰጠን ምሳሌነት መሠረት ለሰው ማዘንና ሰውን ማጽናናት ይገባናል።

ቍጣ ሳይሆን ፈገግታ:- ማንም ሰው በፈገግታ ሲቀበሉት ወይም በፈገግታ ሲያነጋግሩት ሰውነቱ ይዝናናል፤ ከፍርሀት ይላቀቃል፤ የደስታ ስሜትም ፡ ይሰማዋል። ሥራዎች፥ ወይም ንግግሮች ከመንፈሳዊ ፈገግታ ጋር ሲደረጉ አብዛኛውን ጊዜ የተሳኩ ይሆናሉ። ፊቱን የሚያኰሳትር ወይም የሚቈጣ ሰው፥ ሰውን ያሸሻል፤ ፈግግ የሚል ፊት ግን ሰውን ይጋብዛል። ከፍትፍቱ ፊቱ የሚለው አባባል ያለምክንያት የተነገረ አይደለም።

ቍጣ ግን ሰውን ያስደነግጣል፤ ያስፈራል። ሰውን በቍጣ ሲቀበሉት ነገሮች ሁሉ ይደናገሩበታል፤ አብዛኛውን ጊዜ ሁናቴዎች አይሳኩለትም። በቍንተትና በድንጋጤ የሚሠሩ ሥራዎችና የሚነገሩ ንግግሮች ስኬታማ አይሆኑም። ስለዚህ ነው እግዚአብሔር ለቍጣ የዘገየ ነው ሚባለው (መዝ:103 ቍ: 8፥ ኢሳ:ም:48 ቍ:9)።

በኢያሱ ወልደ ሲራክ መጽሐፍ ምዕራፍ 35 ቍ: 9 ላይ ለስጦታዎችህ ሁሉ የፈገግታ ፊት አክልባቸው፤ የዐሥራት ግዴታህንም ደስ ብሎህ ክፈል በሚልበት ጊዜ ለፈገግታ ምን ያኽል ታላቅ ግምት እንደተሰጠው ያመለክተናል።

ስለዚህ የግድ ሐዘን የሚያስፈልገው ሁናቴ ካልሆነ በቀር ከሰው ጋር ስንነጋገር፡ ሰውን ስንቀበልና እንዲሁም በአጋጣሚ ሁሉ ፈገግ ማለት ይኖርብናል እንጂ ፊታችንን ማኰሳተር ወይም መቈጣት የለብንም።

ጭካኔ ሳይሆን ርኅራኄ:- ከዋነኞቹ ክርስቲያናዊ የሕይወት መመሪያዎች አንዱ ርኅራኄ ነው።

ርኅራኄ ማለት የሌላን ሰው ችግር ወይም ጭንቀት ከተመለከቱ በኋላ ከልብ የሚሰማ የሐዘን ስሜት ነው። እውነተኛ ክርስቲያን ሁልጊዜ ለችግረኛ ይራራል። ለተቸገረ ሰው መራራት የሰው ልጅ ሰብአዊ ስሜት ቢሆንም እንኳ በተለየ በክርስቲያናዊ ሕይወት ከሚራመድ ሰው ላይ የሚጠበቅ ነው። አምላካችን ለእኛ እንደሚራራልን እኛም እንደ እርሱ ርኅሩኆች እንድንሆን ይፈቅዳል (መዝ:103፥13፤ 145፡8)።

ለምሳሌ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተናገራቸው ምሳሌዎች አንዱ አገልጋዮቹን ሊቈጣጠር የጀመረው ሰው ነው። አገልጋዮቹን ሊቈጣጠር በጀመረ ጊዜ አንድ በብዙ ሺህ ለሚቈጠር ብር ባለዕዳ የሆነው አገልጋይ ይቅርታ ስለለመነ ጌታው ይቅርታ ያደረገለት ሲሆን አገልጋዩ ግን የመቶ ብር ባለዕዳውን ወደዳኛ ዘንድ ወስዶ በማሳሰሩ ጌታው ተቈጥቶ አንተ በጣም ትንሽ ዕዳ ላለበት ጓደኛህ ርኅርኄ ከሌለህ እኔም አልራራልህም ብሎ እንዳሳሰረው ገልጦአል (ማቴ:18፡ 32–35)። ይህ የሚያመለክተን እግዚአብሔር ከፍተኛ ውን ኃጢአታችንን በርኅራኄው ይቅር ካለልን እኛም ለፍጡራን ጓደኞቻችን ርኅራኄ ማድረግ እንደሚገባን ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ርኅራኄ ምን ይላሉ?

www.ethiopianorthodox.org

«ለድኾች የሚሰጥ ለእግዚአብሔር እንዳበደረ ይቈጠራል» (ምሳ:ም: 19ቍ: 17)።
«በአራጣ በማበደርና ሰዎችን በመበዝበዝ ብትከብር ሀብትህ ሁሉ ለድኾች ልግሥና
ለሚያደርግ ሰው ይተላለፋል» (ምሳ:ም:28ቍ:8)።
«ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ በመስማማት ኑሩ፤ የሌላውን ሰው ችግር እንደ ራሳችሁ ችግር
አድርጋችሁ አስቡ፤ በወንድማማችነት ፍቅር ተዋደዱ፤ ደጎችና ትሑቶች ሁኑ» (1ኛ: ጴጥ:
ም:3 ቍ:8)።
«ሰው በዚህ ዓለም ሀብት እያለው ችግረኛውን አይቶ ባይራራለት እንዴት እግዚአብሔርን
እወዳለሁ ማለት ይችላል» (1ኛ: ዮሐ:ም:3 ቍ:17)።
ከላይ በተዘረዘሩት ጥቅሶች ግልጥ ሆኖ እንደ ታየው ርኅራኄ ማለት ስለተቸገረ ሰው ከልብ
አዝኖ ከንፈርን መምጠጥ ብቻ አይደለም። የሚቻለውን ያኽል የችግረኛውን ችግር ማቃለል
ደግሞ የርኅራኄን ትርጒም የተሟላ ያደር ገዋል። እሺ ካለ በኋላ የአባቱን ፈቃድ ሳይፈጽም
ከቀረው ልጅ እምቢ ካለ በኋላ የአባቱን ትእዛዝ የፈጸመው ልጅ የተመሰገነ መሆኑን እናስተውል
(ማቴ: ም:21 ቍ: 28–32።

<u>የራስን ጥረት ካደረጉ በኋላ ለእግዚአብሔር መተው እንጂ አለመጨነቅ</u>

አንዳንድ ሰዎች አለመጨነቅ የሚለውን ሐሳብ በተሳሳተ መንገድ በመተርጐም ወደ ሥራ
ፈትነት ይቃጣቸዋል። ጌታችን አትጨነቁ ባለ ጊዜ ለሥራችን ውጤት ለማለት ነው እንጂ
እጃችሁን አጣጥፋችሁ ተቀመጡ ማለቱ አይደለም። ይህማ ቢሆን ኖሮ ባለ አንድ መክሊቱ
ተወቅሶ ባለ ሁለትና ባለ አምስት መክሊቶቹ ባልተመሰገኑም ነበር (ማቴ:25፥ 14–30)።
ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፥ እያንዳንዱ ሰው መሥራት እንደሚገባው ሲያመለክት ሊሠራ
የማይወድድ ሰው አይብላ ብሏል (2ኛ: ተሰ:ም:3 ቍ:10)።
እግዚአብሔርም አዳምን «ወደ መጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ
እንጀራን ትበላለህ» አለው እንጂ እጅህን አጣጥፈህ በመቀመጥ ትበላለህ አላለውም (ዘፍ:ም:3
ቍ:19)።
አትጨነቁ የሚለው አስተሳሰብ በምን ዐይነት እንደቀረበ የቅዱሳት መጻሕፈትን ማስረጃዎች
እንመልከት
«አካሄድህን ለእግዚአብሔር ዐደራ ስጥ፤ በእርሱ ታመን፤ እርሱም ይረዳሃል።» (መዝ:37
ቍ:5)።
«ችግርህን ሁሉ ለእግዚአብሔር አቅርብ፤ እርሱም በእንክብካቤ ይጠብቅሃል» (መዝ:55
ቍ:22)።
«ልመናችሁን ሁሉ በጸሎትና በምስጋና አቅርቡ እንጂ ስለምንም ነገር አትጨነቁ»
(ፊል:ም:4ቍ:6)።
«እግዚአብሔር ስለ እናንተ ስለሚያስብ የሚያስጨንቃችሁን ሐሳብ ሁሉ ለእርሱ አስረክቡ»
(1ኛ: ጴጥ: ም:5 ቍ:7)።
ከላይ በቀረቡት ጥቅሶች በግልጥ እንደተመለከተው አትጨነቁ አለ እንጂ አትሥሩ አላለም።
ከላይ በቀረቡት ጥቅሶች በግልጥ እንደተገለጠው የቅዱስ ጳውሎስ ሥራ ድንኳን
በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 18 ቍጥር 3 ላይ እንደተገለጠው የቅዱስ ጳውሎስ ሥራ ድንኳን
መስፋት ነው ተብሎአል። እርሱም የሚኖረው በማስተማሩ ሥራው ገንዘብ የሚሰጠው ሰው
ኖሮ ሳይሆን ይህንኑ የድንኳን መስፋት ሥራውን እየሠራ የነበረ መሆኑን ለተሰሎንቄ ሰዎች
ሲገልጥላቸው:- «የማንንም እንጀራ በብላሽ አልበላንም፤ ይልቅስ ከእናንተ በማንም ላይ ሸክም
እንዳንሆንበት በማለት ሌሊትና ቀን በመድከምና በመጣር እንሠራ ነበር» በማለት የእርሱን
ምሳሌነት እንዲከተሉ ነግሮአቸዋል (2ኛ:ተሰ: ም:3 ቍ:7–8)።

<u>ንፉግነት ሳይሆን ለጋስነት ወይም ቸርነት</u>:- ለጋስነት ወይም ቸርነት ማለት ሳይሳሱ ወይም
ሳይቈጥቡ መስጠት ማለት ነው። ንፉግነት ግን ሥሥታምነት፥ ለመስጠት አለመፈለግ ማለት
ነው:
ከእኛም የሚጠበቀው ክርስቲያናዊ ሕይወት፥ ለጋስነት እንጂ ንፉግነት አይደለም። ቅዱሳት
መጻሕፍትም ለጋሶች እንድንሆን እንጂ ንፉጎች እንዳንሆን ያስጠነቅቁናል።



«ኃጢአተኛ ሰው ቀኑን ሙሉ ምኞትን ይመኛል፤ ጻድቅ ሰው ግን ሳይሠሥት ይሰጣል»
(ምሳ:ም:21 ቍ:26)።
«ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው» (የሐ:ሥ:ም:20 ቍ:35)።
በቆላስይስ መልእክት ም:3ቍ:5 ንፉግነት ጣዖትን እንደ ማምለክ ነው ተብሏል።
«የገንዘብ ፍቅር የክፋት ሁሉ ምንጭ ነው፤ አንዳንድ ሰዎች ገንዘብ ለማግኘት በመመኘት
ከእምነት ርቀዋል ልባቸውንም በጭንቀት ጣር ወግተ ዋል። ስለዚህ ሀብታሞች ለመሆን
የሚፈልጉ በፈተና ይወድቃሉ፤ ሰዎችን በሚያበላሽና በሚያጠፋ ከንቱና አደገኛ በሆነ በብዙ
ምኞት ወጥመድም ይያዛሉ» (1ኛ:ጢሞ:ም:6 ቍ:9–10)።
በምንሰጥበት ጊዜ እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርግልን የሚያመለክ ተውን መግለጫ
ቀጥለን እንመለከት:-
«ስጦታዎችህን ሁሉ በፈገግታ ስጥ... አስቀድሞ ለሰጠህ ለልዑል እግዚአብሔር ዐቅምህ
በሚችለው መጠን በልግስና ስጥ፤ ጌታም መልካም ውለታ ከፋይ ስለሆነ ሰባት ጊዜ አስበልጦ
ይከፍልሃል።» (ሢራ:ም:35 ቍ:9–11)
ለእነዚህ ለትናንሾች ያደረጋችሁት ለእኔ እንዳደረጋችሁት፥ ለእነርሱ ያላደረጋችሁት ደግሞ
ለእኔ እንዳላደረጋችሁት ነው ብሎ ጌታችን በፍርድ ቀን ምስጋናና ወቀሳውን ከተናገረ በኋላ
ፍርድን እንደሚሰጥ ገልጦአል (ማቴ:ም:25 ቍ:40 እና 45)።

<u>የግዴለሽነት ንግግር ሳይሆን ለሰው ስሜት መጠንቀቅ</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚፈጽ
ማቸውን ተአምራት ሰዎች ሁሉ ስላዩአቸውና ሊያስተባብሉአቸው ባለመቻላቸው ፈሪሳውያን
በማመን ወይም ዝም በማለት ፈንታ እርሱ ተአምራትን የሚያደርገው ከሰይጣን አለቃ ጋር
በመስማማት ነው በማለት ክፉ ንግግራቸውን ቀጠሉ። ጌታችን ግን እነርሱ እንዳሉት አለመሆኑን
በተለያዩ ምሳሌዎች ከማስረዳቱም በላይ እንዲህ ሲል ገለጠላቸው:-
«ሰው በአፉ የሚናገረው በልቡ ሞልቶ የተረፈውን ነው፤ መልካም ሰው ከመልካም መዝገቡ
መልካም ነገርን ያወጣል፤ ክፉ ሰውም ከክፉ መዝገቡ ክፉ ነገርን ያወጣል፤ በእውነት እላችኋ
ለሁ፤ ሰዎች በግዴለሽነት በሚናገሩት በያንዳንዱ ቃል በፍርድ ቀን ይጠየቁበታል። ከቃልህ
የተነሣ ይፈረድልሃል፤ ከቃልህም የተነሣ ይፈረድብሃል» (ማቴ:ም:12 ቍ:34–37)።
ሰው፥ ክፉ ንግግር ሲሰማ ወይም ሲሰደብ ልቡ ይሰበራል፤ ያዝናል። ስለዚህ ቀደም ተብሎ
እንደተገለጠው ሰውን በመልካም ቃላት ማረጋጋት፥ ወይም ማጽናናት እንጂ ምንም ሳያስቡ
በግዴለሽነት ከአፍ በሚወጣ ቃል ማሳዘን ወይም ስሜትን ማሻከር ተገቢ አይደለም። ሰውን
መምከር ተገቢ ቢሆ ንም እንኳ ተቀባይነት ባላቸው አነጋገሮች ስሜትን የሚጎዱ ቃላትን በግዴለ
ሽነት መወርወር ግን የሰሚውን ስሜት መጒዳት ብቻ ሳይሆን በራስም በኩል ተቀባይነትን
ያሳጣል።
«እንደበት ከሚያንሸራትት ይልቅ በመሬት ላይ ተንሸራትቶ መውደቅ ይሻላል፤ የክፉ
ሰዎች አወዳደቅም እንደዚያው ፈጣን ነው፤ ባለጌ ሰው፥ ዕውቀት በሌላቸው ሰዎች አንደበት
ወትር እንደሚነገር የብልግና ታሪክ ነው» (ሢራክ ም:20 ቍ:18–19)።

<u>ራስ ወዳድነት ሳይሆን ለሌላም ሰው ማሰብ</u>:- ራስ ወዳድነት ሲባል ስለ ራስ ምቾትና ጥቅም
ብቻ በጣም ከማሰብ የተነሣ ስለ ሌሎች ሰዎች ወይም ስለ ማኅበረሰቡ ግዴለሽ መሆንና
እንዲያውም ስለ ግል ጥቅም ሲባል የሌላውን ሰው መብት መጋፋት ማለት ነው። ስለሌላ ሰው
ማሰብ ሲባል ደግሞ ሰው ለራሱ እንዲሆንለት ወይም እንዲደረግለት የሚፈልገውን ጉዳይ
ሌላም ሰው እንዲደ ረግለት መመኘት ወይም ለማድረግ ፈቃደኛ መሆን ማለት ነው። እንዲ
ሁም በራስ ሊደርስ የማይፈለግ ድርጊት በሌላ ሰው ላይ እንዲደርስ አለመመኘት ወይም
ለማድረግ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ይህም የድርጊት ሥነ ሥርዓት የእምነት አባት አብርሃም በተግባር ላይ አውሎታል። ምንም እንኳ አብርሃም በታላቅነቱ ቅድሚያና መከበር የሚገባው ቢሆን እርሱ ግን ምርጫን ለሎጥ ትቶለት ከራስ ወዳድነት ሸሸ። ሎጥ ራስ ወዳድ ሆኖ የተሻለ መስሎ የታየውን አቅጣጫ መረጠ። ከዚያ በኋላ ሎጥ የመረ ጠው አገር ሰዶምና ገሞራ እንዲጠፋ በተወሰነበት ጊዜ ከዚያች አገር ተሰድዶ ተንከራተተ። አብርሃምን ግን እግዚአብሔር ባለበት ቦታ ባረከው (ዘፍም:13፥ 8፥ 13፥ ም:19)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ጉዳይ ላይ የተናገራቸውን አባባሎች ይመለከቷል:-

«ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተም ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው።» «በማንም ላይ አትፍረዱ፤ በእናንተም ላይ አይፈረድ ባችሁም፤ ሌሎችን አትንቀፉ፤ እናንተም አትነቀፉም፤ ይቅር በሉ እናንተም ይቅርታ ታገኛላችሁ፤ ስጡ ለእናንተም ይሰጣችኋል» (ሉቃ:ም:6 ቍ:31፥ 37፥ 38)።

ብዙዎች እውነተኛ መንፈሳውያን ሰዎችም ከራሳቸው ክብርና ጥቅም ይልቅ የሌላውን ሰው ክብርና ጥቅም ያስቀድማሉ።

በዚህም መሠረት እርግማን ከሆነው ራስ ወዳድነት ይልቅ ጸጋና በረከት የሚገኝበትን ለሌላ ሰው የማሰብን ጠባይ እንከተል።

<u>ለጥያቄ መልስ ለመስጠት ካልሆነ በቀር ከክርክር መራቅ</u>:- መከራከር ሲባል አንድን ሐሳብ በመደገፍ ወይም በመቃወም ከሌላ ያን ሐሳብ ከሚቃወም ወይም ከሚደግፍ ሰው ጋር መጫቃጨቅ ነው። ክርክር በሚደረግበት ጊዜም ሁለቱ ተቃራኒ ወገኖች እያንዳንዱ የራሱን ሐሳብ በሌላ ሰው ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ ጥረት ያደርጋል። ክርክሩም የአንድን ሐሳብ ትክክለኛነትና እውነተኛነት ለማረጋገጥ፥ ወይም አንድ ሐሳብ እውነተኛ ወይም ትክክለኛ አለመ ሆኑን ለማስረዳት ሊሆን ይችላል። በክርክሮች መካከል አብዛኛውን ጊዜ ለምን የእኔ ሐሳብ ድጋፍ አላገኘም? ወይም ከእኔ ሐሳብ የተለየ ለምን ሌላ ሐሳብ ቀረበ ብለው ጠብ የሚያነሡ ሰዎች ስለሚኖሩ ክርክሮች አብዛኛውን ጊዜ በሰላም የሚያልቁ አይደሉም። ስለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀ መዝሙሩ ለጢሞቴዎስ በላከው መልእክቱ ከክርክር እንዲርቅ ያስጠነቀቀው።

«ጢሞቴዎስ ሆይ፥ በዐደራ የተሰጠህን ጠብቅ፤ ዕውቀት ሳይሆን፥ ዕው ቀት ስለሚመስለው ነገር ከከንቱ ልፍለፋና ክርክር ራቅ» (1ኛ: ጢሞ:ም:6 ቍ:20)።

እንዲርቅ የተነገረው ጥቅም ከሌለው ከከንቱ ልፍለፋና ክርክር ነው እንጂ ከማስተማርና ተገቢ ጥያቄን ከመመለስ አይደለም። ስለዚህም «ስለጌታ ለመመስከር አትፈር፤ ስለእርሱ በታሰርሁት በእኔም አትፈር፤ ነገር ግን እግዚአ ብሔር በሚሰጥህ ኀይል መጠን ስለ ወንጌል ከእኔ ጋር የመከራ ተካፋይ ሁን» ብሎታል (2ኛ: ጢሞ:1፥ 8)። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም እንዲህ ብሏል።

«ጌታ ክርስቶስን በልባችሁ አክብሩት፤ በእናንተ ስላለው ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቃችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠተ ዝግጁዎች ሁኑ» (1ኛ:ጴጥ:ም:3 ቍ:15)።

ስለዚህ ለመከራከር ሳይሆን ስለ እምነታችን በምንጠየቅበት ጊዜ ለማስረዳት መጣር አለብ ማለት ነው። አለበለዚያ ግን ክርክር አስፈላጊ አይደለም።

<u>ከሐሜት መራቅ</u>:- ሐሜት ማለት ስለአንድ ሰው እርሱ በሌለበት የነቀፋ ወይም የስ ማጥፋት ወሬ መናገር ነው። ሐሜት በእውነት ወይም በሐሰት ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይችላል። በእውነት ላይ የተመሠረተ በሚሆንበት ጊዜ የሚታማው ሰው የፈጸመውን ድርጊት በክ በመተርጐም በነቀፋ መልክ መናገር ነው። በሐሰት ላይ የተመሠረተ በሚሆንበት ጊዜ ደግ ሆን ብሎ የዚያን የሚታማውን ሰው ስም ለማጥፋት የሚወራ ወሬ ነው።

የእውነተኛ ክርስቲያናዊ ሕይወትን መመሪያ የሚከተል ሰው ከሐሜት ይርቃል እንጂ ሰው አያማም። ሌሎች ሰዎች ሌሎችን ሰዎች በሚያሙበት ጊዜ እንዳልሰማ ሰው ዝም ይላል እን



ምንም ዐይነት ትችት አይሰጥም። በዚህ ሁናቴ ሐሜተኛው ያፍ...ል፤ ኅሊናውም ይወቅሰው ይጀምራል። ይህም ማለት መልስ ሳይሰጥ ወይም ክፉና ደግ ሳይናገር በዝምታ ብቻ ሐሜተኛውን አስተማረው ማለት ነው።

ሐሜትም በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ለመሆኑ የሚከተሉትን የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች ይመለከቷል:-

«እግዚአብሔር ሆይ፥ ወደ መኖሪያህ መግባት የሚችል ማነው? ... የሌሎች ሰዎችን ስም የማያጠፋ፥... ጐረቤቶቹን የማያማ:.... እነዚህን ነገሮች የሚያደርግ ሰው ከማናቸውም ክፉ ነገር ተጠብቆ ይኖራል እንጂ ከቶ አይናወጥም» (መዝ: 15)።

ሰውን በሹክሹክታ የሚያማውን ሰው እኔ ዝም አሰኘዋለሁ» (መዝ:101 ቁ:5)።

«ሐሜትን የሚያሠራጭ ሰው ሞኝ ነው» (ምሳ:ም:10 ቍ:18)።

«የሰሜን ነፋስ ዝናብን እንደሚያመጣ ሐሜትም ቍጣን ማስከተሉ የተረጋገጠ ነው» (ምሳ:ም:25 ቍ:23)።

«ሰዎች እግዚአብሔርን ለማወቅ ስላልፈለጉ አስነዋሪ ነገር እንዲያደርጉ እግዚአብሔር ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው። ... ሐሜተኞች፥ የሰውን ስም የሚያጠፉ፥... ፍቅር የሌላቸው ጨባኞች ናቸው» (ሮሜ:ም:1 ቍ:28–31)።

«እንግዲህ ክፋትን ሁሉ፥ ማታለልን ሁሉ፥ ግብዝነትን፥ ቅንዓትን፥ ማናቸውንም ዐይነት ሐሜት አስወግዱ» (1ኛ: ጴጥ: ም:2 ቍ1)።

<u>ግዴታን አክብሮ መወጣት</u>:- ግዴታን በሦስት አጠቃላይ ክፍሎች ለመክፈል ይቻላል:-

አንደኛ/ አንዳንድ ድርጊቶችን የመፈጸም ግዴታ ሲኖር ሌሎች ድርጊቶችን ከማድረግ የመቈጠብ ግዴታ አለ። እነዚህን ግዴታዎች መፈጸም ወይም አለመፈጸም ምድራዊ፥ ወይም ሰማያዊ፥ ወይም ሁለቱንም ቅጣቶች ያስከትላሉ። በዓለማዊው ሕግ ለመንግሥት መከፈል ያለበትን ግብር አለመክፈል ያስቀጣል። በተለያየ መንገድ የሌላውን ግለሰብ ወይም ማኅበረሰብ መብት ተጋፍቶ የተከለከለውን ድርጊት ማድረግ ያስቀጣል።

በእግዚአብሔር በኩል ደግሞ የተራበን ማብላት፤ የተጠማን ማጠጣት፥ እንግዳን መቀበል፥ የታረዘን ማልበስ፥ የታመመን መጠየቅና የታሰረን መጐብኘት ይጠበቅብናል። ይህም ግዴታችን በመሆኑ ይህን ግዴታ ያልተወጣን እንደሆነ ዕድል ፈንታችን በፍርድ ቀን «ከእኔ ወዲያ ራቁ ለሰይጣንና ለተከታዮቹ ወደ ተዘጋጀው ወደ ዘለዓለም እሳት ሂዱ» መባል ነው (ማቴ: ም:25ቍ:41–46)።

ነፍሰ ገዳይነትን የመሰለ ወንጀል ደግሞ በነፍስም በሥጋም ያስቀጣል። አትግደል የሚለው አምላካዊ ትእዛዝ ከዐሥሩ ትእዛዞች አንዱ ነው (ዘጸ:ም:20)።

ሁለተኛው ዐይነት ግዴታ ደግሞ በባህሉ መሠረት ማኅበረሰቡ ከእኛ የሚጠብቀው አንዳንድ ነገሮችን ማድረግና ሌሎች ነገሮችን ደግሞ ከማድረግ መቈጠብን ነው። ለምሳሌ አባትንና እናትን፥ እንዲሁም ሽማግሌዎችን ማክበርና ለእነርሱም መታዘዝ፤ የሌላውን ሰው አስተሳሰብ ምንም ያህል የማይስ ማሙበት ቢሆን በጥሞና ማዳመጥ እንጂ ሐሳቡን ያቀረበውን ሰው የሚያሳዝንና ዝቅ የሚያደርግ አስተሳሰብ አለመሰንዘር፤ መልስም ቢሰጥ ሐሳቡን ለማብራራት እንጂ ሐሳብ አቅራቢውን የሚያንቋሽሽ እንዳይሆን ያስፈልጋል። ሰውን ሁሉ እንደ ሰውነቱ እንጂ እንደ ኑሮ ደረጃው አለመመልከት፤ በስብሰባም ሆነ በሌላ ጊዜ በሰዎች መካከል የሐሳብ መለዋወጥ በሚደረግበት ጊዜ ተራን ጠብቆ መናገር እንጂ በሰው ንግግር መካከል ጣልቃ አለመ ግባት፥ ከሰዎች ጋር በሚደረጉ ስምምነቶች በቃል ኪዳን መጽናት እንጂ ቃል ኪዳንን አለማፍረስ፥ በአንድ ማኅበራዊም ሆነ የሥራ ተቋም ውስጥ የተሰጠውን ኀላፊነት በትጋት መፈጸም እንጂ ችላ በማለትና ሥራውን በመበደል ተጠቃሚውን ወገን አለማጉላላት፥ አንዳንድ በተፈጥሮአቸው ጉድለት ያለባቸው ሰዎችን መርዳት እንጂ በእነርሱ አለመሳለቅና አለማላገጥ፥

www.ethiopianorthodox.org

ሰው እያየ በይፋ፣ ኅብረተሰቡ አ[illegible]ዎች ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ድርጊቶች አለማድረግ፥ እነዚህንና የመሳሰሉትን ባህላዊ ሥርዓቶች አክብሮ ከኅብረተሰቡ ጋር አብሮ መራመድ እንጂ ኅብረተሰቡን አንቅሮ መትፋት ወይም በኅብረተሰቡ አንቅሮ መተፋት አስፈላጊም፥ ጠቃሚም አይደለም።

ሦስተኛው ዐይነት ግዴታ ደግሞ ለተፈጸመልን ውለታ አጸፋውን ለመመለስ የሚሰማን ግዴታ ነው። የዚህ ዐይነቱ ግዴታ በእኛና በኅሊናችን መካከል ያለ ስሜት እንጂ ሌላ ሦስተኛ ወገን የሚያሳትፍ አይደለም። አንድ ሰው አንድ ችግር ሲደርስበት ለረዳው ሰው ውለታ የመመለስ ግዴታ ይሰማዋል።

የክርስቲያናዊ ሕይወት መመሪያም ከላይ የተዘረዘሩት ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም አሉ። ከእነዚህም መካከል ለምሳሌ አንድ ሰው ከክፉ ነገር ወይም ከክፉ ሁናቴ ገለል ማለት እንጂ ክፉን በመጋፈጥ ራስን ለሰይጣን ፈተና አሳልፎ መስጠት ተገቢ አይደለም። ይህማ ባይሆን ኖሮ ወደ ፈተና አታግባን ብለን በየቀኑ መጸለይ ባላስፈለገንም ነበር። እንዲሁም ሌላ ሰው የሚያደርስብንን በደል ለመበቀል መነሣት ተገቢ አይደለም። በቀልን ለእግዚአብሔር መተው እንጂ ለበቀል መሯሯጥ ተገቢ አይደለም። አንዳንድ ጊዜ በተለያዩ ምክንያቶች ሰውን መናቅ ወይም መጸየፍ ይከሠት ይሆናል። የእግዚአብሔር ፍጡር የሆነውን ሰው ሁሉ በእኩልነት ማየት እንጂ በሰዎች መካከል ልዩነት ማድረግ ተገቢ አይደለም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማንንም ከማን ሳይለይ ያስተምር፥ ይፈውስና ያድን እንደነበረ እናስታውስ።

እነዚህ ከላይ የቀረቡት ዝርዝር ጉዳዮች ለዐይነት ያኽል የቀረቡ እንጂ ለክርስቲያናዊ ሕይወት መመሪያ የሚሆኑት የትምህርት አርእስት እነርሱ ብቻ አይደሉም።

## ጥያቄዎች

1. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሕግጋት ሁሉ ይበልጣሉ ያላቸው ሁለት ሕጎች ምንና ምን ናቸው?
2. የሰይጣን ስሜት የተባለው ምንድነው?
3. ኃጢአተኛውን ከኃጢአቱ ልንመልስ የምንችልበት አንዱ መንገድ ምንድነው?
4. ኅያል ወልድን ከዙፋኑ ስቦ እስከሞት ያደረሰው ምንድነው?
5. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አልዓዛርን ከሞት ሲያስነሣ ለእኛ ምሳሌነትን ያሳየን ምን በማድረግ ነው?
6. የጌታችን ከእነርሱ መለየት ደቀ መዛሙርቱን ባሳዘናቸው ጊዜ ምን ብሎ አጽናናቸው?
7. ለሰዎች ማድረግ የሚገባንን ድርጊት ሲያዝዘን ጌታ ምን አለ?
8. ሰውን በፈገግታ ሲቀበሉት ምን ይሰማዋል?
9. ሥራዎች፥ ወይም ንግግሮች ከመንፈሳዊ ፈገግታ ጋር ሲደረጉ ምን ውጤት ይኖራቸዋል?
10. ቍጣ ምን ያደርጋል?
11. ሰውን በቍጣ ሲቀበሉት ምን ይሆናል?
12. እግዚአብሔር ለቍጣ የዘገየ ነው የተባለው በምን ምክንያት ነው?
13. ርኅራኄ ማለት ምን ማለት ነው?
14. አምላክ ለእኛ የሚራራልን መቼ ነው?
15. አንዳንድ ሰዎች አለመጨነቅ ለሚለው አስተሳሰብ ምን ዐይነት ስሕተት ይሳሳታሉ?
16. ይህን ስሕተት የባለ መክሊቶቹ ምሳሌ እንዴት ያርመዋል?
17. የአትጨነቁ ሐሳብ ከሥራ ጋር ያለው ግንኙት ምንድነው?
18. በዚህ ጉዳይ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ ምሳሌነትን ዘርዝር።
19. ለጋስነት ማለት ምን ማለት ነው?
20. ንፉግነት ማለትስ ምን ማለት ነው?
21. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚያደርጋቸው ተአምራት ፈሪሳውያን ምን አሉ?
22. ሰው ከሌላ ሰው ክፉ ንግግርን ሲሰማ ምን ይሆናል?



23. በግዴለሽነት የሚናገር ሰው ምን ይደርስበታል?
24. ራስ ወዳድነት ማለት ምን ማለት ነው?
25. ስለ ሌላ ሰው ማሰብ ማለት ምን ማለት ነው?
26. አብርሃም ራስ ወዳድ ባለመሆኑና ሎጥ ግን ራስ ወዳድ በመሆኑ የየራሳቸው ተግባር ውጤት ምን ዐይነት ሆነ?
27. መከራከር ማለት ምን ማለት ነው?
28. ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ጥረት የሚያደርጉት በምን ላይ ነው?
29. ክርክሮች በሰላም የማያልቁት ምን ሲሆን ነው?
30. ሐሜት ማለት ምን ማለት ነው?
31. በእውነት ላይ የተመሠረተ ሐሜት ምን ዐይነት ነው?
32. በሐሰት ላይ የተመሠረተ ሐሜትስ እንዴት ያለ ነው?
33. የክርስቲያናዊ ሕይወትን መመሪያ የሚያደርግ ሰው ከሐሜት ጋር ያለው ግንኙት እንዴት ነው?
34. ግዴታ በስንት አጠቃላይ ክፍሎች ይከፈላል?
35. እነርሱስ ምን ምን ናቸው?

www.ethiopianorthodox.org

# ዐሥረኛ ክፍል

## ምዕራፍ 1

## ትምህርተ ሃይማኖት

### የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን

ቃል ኪዳን ማለት በሁለት ሰዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው። በስምምነቱም ውስጥ ሁለቱ ወገኖች እያንዳንዳቸው የሚገቡት ግዴታ አለ። እንደዚህ ላለው ስምምነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለያዩ ምሳሌዎችን እናገኛለን። ለምሳሌ በያዕቆብና በላባን መካከል (ዘፍ: ም:31 ቍ:44–54)፥ በዳዊትና በዮናታን መካከል (1ኛ: ሳሙ: ም:18 ቍ:3፡ ም:23 ቍ:18)፡ በአብርሃምና በጌራሩ ንጉሥ በአቢሜሌክ መካከል (ዘፍ:21 ቍ:22–32)፡ በአበኔርና በዳዊት መካከል (2ኛ: ነገ: ም:5 ቍ:12)። (1ኛ :ሰሙ: ም: 3ቍ: 12–13፡ 21)፡ በሰሎምንና በኪራም መካከል

ሌላው ዐይነት ቃል ኪዳን ደግሞ ኀይለኛ ወገን በደካማ ላይ የሚያደርገው ተጽዕኖ ነው። ኀይለኛው ወገን ከደካማው ወገን ታማኝነትን ሲጠይቅ በራሱ በኩል ደግሞ ደካማውን ወገን ለመጠበቅ ቃል ይገባል። ለምሳሌ በእስራኤልና በገባዖን ሰዎች መካከል (ኢ.ያ:ም:9)፡ የያቤሽ ገለዓድ ሰዎች ለአሞን ንጉሥ ያቀረቡት ልመና (1ኛ: ሳሙ: ም:11 ቍ:1–2)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሰው ቃል ኪዳን እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን ነው።

በአራት ዘጸአት ከምዕራፍ ዐሥራ ዘጠኝ እስከ ምዕራፍ ኻያ አራት ድረስ የሲና ተራራ ቃል ኪዳን ታሪክ ተዘርዝሮአል። በም:19ቍ:4–6 እና በም:20 ቍ:2 ላይ እግዚአብሔርንና አዳኝነቱን የሚያስተዋውቅ ክፍል ነው። የቃል ኪዳኑን ዝርዝር ከምዕራፍ 20ቍ:3 እስከ ምዕራፍ 23ቍጥር 33 ባለው ክፍል ይመለከቷል። የቃል ኪዳኑም ጽሑፍ በታቦቱ ውስጥ እንዲቀመጥ የተደረገ መሆኑን (በዘጸ: ም:25 ቍ: 16፥ ም: 40 ቍ: 21፥ ዘዳ: ም:10 ቍ: 1–5፥ ም:31 ቍ: 25–29) መመልከት ይቻላል። ለቃል ኪዳኑ ምስክር መሆናቸው የተጠቀሰው ሰማይና ምድር ናቸው (ዘዳ: ም:4 ቍ:26፡ ም:30 ቍ:19፥ ም:31 ቍ:28)። በሰዎች በኩል በዚህ ቃል ኪዳን መጽናት የሚያስገኘው በረከትና ቃል ኪዳኑን በማፍረስ የሚመጣው እርግማን በዘዳ: ም:27 ቍ:11 እስከ ም:28 ቍ:68 ድረስ ይመለከቷል። በዚህም ቃል ኪዳን ምክንያት እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ልጆች ተብለዋል። (ዘዳ: ም4 ቍ:22፡ ም:19 ቍ:4፥ ዘዳ: ም:32 ቍ:9–12)።

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የገባው ቃል ኪዳንም ለእስራኤል ሕዝብ የመንፈሳዊና ሥጋዊ መተዳደሪያ ሕግ ሆኗል።

እግዚአብሔር፥ ቃል ኪዳን የሰጠው ለእስራኤል ሕዝብ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው ለተለያዩ ግለሰቦችም መሆኑን ቀጥለን እናመልከት:-

<u>ከኖኅ ጋር የገባው ቃል ኪዳን</u>:- በዘመኑ ከነበሩት ሰዎች ሁሉ ኖኅ የተሻለ ሰው ሆኖ በመገኘቱ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን በሚከተሉት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች እንመልከት:-

«ከአንተ ጋር ቃል ኪዳን እገባለሁ፤ አንተና ሚስትህ፡ ልጆችህና የልጆችህ ሚስቶች ወደ መርከቡ ግቡ፤... እነሆ፡ ከእናንተና ከዘራችሁ ጋር ቃል ኪዳኔን አመሠርታለሁ፤ .. በዚሁ በገባሁላችሁ ቃል ኪዳን መሠረት ከእንግዲህ ወዲህ ሕያዋን ፍጥረቶች ሁሉ በጥፋት ውሃ ከቶ አይደመሰሱም፤ ምድርም ዳግመኛ በጥፋት ውሃ አትጠፋም፤ ከእናንተና ከሕያዋን ፍጥረቶች ሁሉ ጋር ለምገባው ለዚህ ለዘለዓለማዊ ቃል ኪዳን ቀስቴን በደመናዎች ላይ አደርጋለሁ፤ ይህም ቀስት ከምድር ጋር ለገባሁት ቃል ኪዳን ምልክት ሆኖ ይኖራል» (ዘፍ: ም:6 ቍ:18፡ ም:9 ቍ:9፥ ም:9 ቍ:11–13)።



www.ethiopianorthodox.org

<u>ከአብርሃም ጋር የገባው ቃል ኪዳን</u>:- አብርሃም ለእግዚአብሔር ፍጹም ታማኝ በመሆኑ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ቀጥለን እንመልከት:-

«በዚያን ዕለት እግዚአብሔር ለአብራም እንዲህ በማለት ቃል ኪዳን ገባለት፡ ከግብጽ ወንዝ ጀምሮ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ያለውን ምድር ሁሉ ለዘርህ እሰጣለሁ» (ዘፍ: ም:15 ቍ:18)።

እግዚአብሔርም ከአብርሃም ጋር በገባው ቃል ኪዳን የብዙ ሕዝቦች አባት እንደሚያደርገውና የከነዓንንም ምድር ለዘሩ እንደሚሰጥ ቃል ገባለት። እንዲሁም ለቃል ኪዳኑ ምልክት ይሆን ዘንድ ወንዶች ልጆቹ ሁሉ እንዲገረዙ አዘዘው (ዘፍ: ም:17)።

<u>ከይስሐቅ ጋር የገባው ቃል ኪዳን</u>:- ይስሐቅ ገና ከመወለዱ በፊት እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን እንደሚገባ ለአብርሃም ነግሮታል።

«ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፤ ስሙንም ይስሐቅ ትለዋ ለህ፤ ቃል ኪዳኔን ከእርሱና ከዘሩ ጋር ለዘለዓለም አጸናለሁ» (ዘፍ:ም:17 ቍ:19)።

«እዚሁ ኑር፤ እኔም ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ እባርክሃለሁም፤ ይህን ምድር ለአንተና ለዘሮችህ እሰጣለሁ፤ በዚህ ዐይነት ለአባትህ ለአብርሃም የገባሁትን ቃል ኪዳን እፈጽማለሁ» (ዘፍ: ም:26 ቍ: 3)።

<u>ከያዕቆብ ጋር የገባው ቃል ኪዳን</u>:- እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ቃል ኪዳን ከልጁ ከይስሐቅና ከልጅ ልጁ ከያዕቆብ ጋርም አጽንቶታል።

«እግዚአብሔርም በአጠገቡ ቆሞ እንዲህ አለው፡ እኔ የአባትህ የአብርሃምና የይስሐቅ አምላክ እግዚአብሔር ነኝ፤ ለአንተና ለዘርህ እንዲሆን ይህን የተኛህበትን ምድር እሰጥሃለሁ፤ ዘርህን እንደ ምድር አሸዋ አበዛዋለሁ፤ እነርሱ በሁሉም አቅጣጫ ይዞታቸውን ያስፋፋሉ፤ በአንተና በዘርህ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ይባረካሉ፤ አይዞህ እኔ ከአንተ ጋር ነኝ በምትሄድበትም ስፍራ ሁሉ እጠብቅሃለሁ፤ ወደዚህም ምድር በደኅና እመልስሃለሁ፤ የገባሁልህን ቃል ኪዳን ሁሉ እፈጽምልሃለሁ፤ ከቶም አልተውህም» (ዘፍ:ም:28 ቍ:13–15)።

<u>ለፊንሐስ የገባው ቃል ኪዳን</u>:- የአሮን የልጅ ልጅ የአልዓዛር ልጅ ፊንሐስ ለእግዚአብሔር ቀናተኛ በመሆኑ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገባለት:-

«እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው:- ‘የካህኑ የአሮን የልጅ ልጅ የአልዓዛር ልጅ ፊንሐስ ባደረገው ነገር ምክንያት በእስራኤል ሕዝብ ላይ ያለኝ ቍጣ በርዶአል፤ ፊንሐስ ከእኔ በቀር ለሌላ አምላክ የሚሰግዱትን መታገሥ አልፈለገም፤ በቍጣዩ እስራኤልን ያላጠፋሁትም እርሱ ስለ እኔ ባሳየው ቅንአት ነው። ስለዚህ እኔ ከእርሱ ጋር ለዘለዓለም ጸንቶ የሚኖር የሰላም ቃል ኪዳን የምሰጠው መሆኔን ንገረው። እርሱ ለእኔ ለአምላኩ ቀናተኛ በመሆኑና የሕዝቡን ኃጢአት በማስተሰረዩ እርሱና የእርሱ ልጆች በሙሉ ለዘለዓለም ካህናት ይሆናሉ»’ (ዘኍ:ም:25 ቍ:10–13)።

<u>ከዳዊት ጋር የገባው ቃለ ኪዳን</u>:- ዳዊት እምነቱን ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ያሳረፈ ቅን ታዛዥ በመሆኑ እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ቃል ኪዳን ገብቶአል።

«በሁሉም ነገር የተመቻቸና አስተማማኝ ዘለዓለማዊ ቃል ኪዳን ከኔ ጋር ስለገባ በውኑ ቤቴ ከእኔ ጋር አይደለምን? እርዳታዬና ፍላጎቴስ ሁሉ እንዲሟላ አያደርግምን?» (2ኛ:ሳሙ:ም:23ቍ:5)።

«አንተ አስቀድመህ ‹ከመረጥሁት ሰው ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ፤ ለአገልጋዩ ለዳዊት የተስፋ ቃል ሰጠሁት› ብለህ ነበር፤ የሰጠኸውም ቃል ኪዳን:- ‹ዘርህ ለዘለዓለም ይነግሣል፤ ትውልድህንም ለዘለዓለም አጸናለሁ› የሚል ነው» (መዝ:89 ቍ:3–4)።

<u>የእግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ታማኝነት</u>:- ሰዎች በእግዚአብሔር ቃል ጸንተው እስከኖሩ ድረስ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ነው። የቃል ኪዳኑም ተፈጻሚነት ከሰዎች ሁኔታ ጋር የተያያዘ ነው። ሰዎች በቃል ኪዳኑ ግዴታዎች ጸንው በኖሩ ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር የገባላቸውን ቃል ሁሉ ይፈጽምላቸዋል። ሳይፈጽሙ ሲቀሩ ግን ይቀጡባታል። ለምሳሌ እስራኤላውያን በሲና ተራራ ላይ የተሰጣቸውን ቃል ኪዳን ባለመፈጸማቸው አገራቸውና ቤተ መቅደሳቸው ፈራረሱ፤ እነርሱም ተማርከው ወደ ሌሎች አገሮች ተወሰዱ። የእግዚአብሔርን

በቃል ኪዳኑ መጽናት በተመለከተ የሚከተሉትን የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች ይመለከቷል:-

«እግዚአብሔር አምላካችሁ በፍጹም የታመነ አምላክ መሆኑን አስታውሱ፤ እርሱ ቃል ኪዳኑን ይጠብቃል፤ ለሚወዱትና ትእዛዛቱንም ለሚፈጽሙ ሁሉ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ዘለዓለማዊ ፍቅሩን ያሳያል፤ ነገር ግን የሚጠሉትን ወገኖች በማጥፋት ይበቀላል፤ እነርሱንም ከመበቀል ፈጽሞ አይዘገይም። እኔም ዛሬ የሰጠኋችሁን ትእዛዛትና ሕግጋት በጥንቃቄ ጠብቁ» (ዘዳ:ም:7 ቍ:9–11)።

«የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፥ ለአገልጋዮቹ ቃል ኪዳኑን የሚጠብቅና ከልባቸው ታማኞች እስከሆኑ ድረስ ፍቅሩን የሚያጸና፥ በላይ በሰማይ፥ በታችም በምድር እንደ አንተ ያለ አምላክ የለም» (1ኛ: ነገ:ም:8 ቍ:23)።

«እግዚአብሔር አምላካችን ነው፤ ፍርዱም በዓለም ሁሉ ነው። ቃል ኪዳኑን ወይም የሰጠውን ተስፋ እስከ ሺህ ትውልድም ሆነ ለዘለዓለም አይረሳም» (መዝ: 105 ቍ:7–8)።

«እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ ነው፤ በአስደናቂ ሥራው የገነነ ነው፤ ለሚፈሩት ሁሉ ምግባቸውን ያዘጋጅላቸዋል፤ ቃል ኪዳኑንም ከቶ አይረሳም» (መዝ: 111 ቍ:4–5):

«ልጆችህ ቃል ኪዳኔንና የምሰጣቸውን ትእዛዞች ከጠበቁ፥ ልጆቻቸው ከአንተ በኋላ ለዘለዓለም ይነግሣሉ» (መዝ:132 ቍ:12)።

## ጸሎተ ፍትሐት

ፍትሐት ማለት ከኃጢአት እስራት መፍታት ወይም መፈታት ማለት ነው። ስለዚህም ለሞቱ ሰዎች የሚደረገው ጸሎት፥ ጸሎተ ፍትሐት ይባላል።

ቅዱሳት መጻሕፍትንና የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት መሠረት በማድረግ የሙታን ነፍሳት ከሥጋ እንደተለዩ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ በማረፊያ ቦታ ይቈያሉ እንጂ በቀጥታ ወደ መንግሥተ ሰማይ ወይም ወደገሃነመ እሳት እንደማይላኩ ቤተ ክርስቲያን የምታምነውና የምታስተምረው ትምህርት ነው። እስከ ፍርድ ቀን ድረስ የሚቈዩበትም ቦታ ለጻድቃን ገነት ሲሆን ለኃጢአተኞች ደግሞ ሲኦል ነው። የጻድቃን ማረፊያ ቦታቸው ገነት መሆኑን ለማመልከት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በነበረ ጊዜ ንስሓ ለገባው ወንበዴ:- «በእውነት እልሃለሁ፤ ዛሬውኑ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ» ብሎታል (ሉቃ:ም:23 ቍ:43) ። የኃጢአተኞች መቈያ ደግሞ ሲኦል መሆኑን ለማመ ልከት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሀብታሙ ሰውና በድኻው አልዓዛር ምሳሌ ትምህርቱ፥ ሀብታሙ ሰው በሲኦል ውስጥ እንደነበረ ገልጾአል (ሉቃ:ም:16 ቍ:23)።

የጻድቃንም ሆኑ የኃጢአተኞች ነፍሳት ወዲያው ከሥጋ እንደተለዩ የመጨረሻ ዘለዓለማዊ መኖሪያቸው ወደ ሆነው መንግሥተ ሰማያት ወይም ወደ ገሃነመ እሳት የማይወሰዱበት ምክንያት ነፍስና ሥጋ በአንድነት ሆነው ለፈጸሙት በጎም ሆነ ክፉ ተግባር ዋጋቸውንም አብረው ሆነው ማግኘት ስላለባቸው ነው። ስለዚህ በሙታን ትንሣኤ ጊዜ የምንነሣው በውርደት፥ ወይም ክብር በሌለው ሁናቴ በመሬት ውስጥ እንደተቀበርነው ሳይሆን፥ ሐዋር ያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው በክብር፥ በኀይልና በመንፈሳዊነት ነው (1ኛ:ቆሮ:ም:15 ቍ:42–44)። ከዚያም በኋላ ወደ ክርስቶሰ ፍርድ ወንበር ፊት እንቀርባለን (2ኛ: ቆሮ:ም:5 ቍ:10)።

በራእየ ዮሐንስ ም:6 ቍ:9–11 የተነገረውን እንመልከት:-

«አምስተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ሰጡትም ምስክርነት የተገደሉትን ሰዎች ነፍሶች ከመሠዊያው በታች አየሁ እነርሱም በታላቅ ድምፅ ቅዱሱና እውነተኛው፥ በሁሉም ላይ የበላይነት ያለህ ጌታ ሆይ፥ በምድር ባሉት ሰዎች ላይ የማትፈርደውና ስለደማችንም የማትበ ቀለው እስከ መቼ ነው? እያሉ ጮኹ። ለያንዳንዳቸውም ነጭ ልብስ ተሰጣ ቸው፤ እንደ እነርሱ የሚገደሉ፥ እንደ እነርሱ አገልጋዮች የሆኑ የጓደኞቻቸውና የወንድሞቻቸው ቍጥር እስኪሞላ ጥቂት ጊዜ ዐርፈው እንዲቆዩ ተነገራቸው።»

እንዲሁም ደግሞ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ ብሏል:-

«ኃጢአት በሠሩ ጊዜ እግዚአብሔር መላእክትን እንኳ ሳይቀር የፍርድን ቀን እንዲጠባበቁ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ጥሎ ያሰራቸው ከሆነ» (2ኛ: ጴጥ:ም:2 ቍ:4)።



እነዚህ ከላይ የቀረቡት ጥቅሶች የሚያመለክቱት የጻድቃንና የኃጢአተኞች ነፍሶች እስከፍርድ ቀን ድረስ እንደየተግባራቸው ለመቈያነት በተወሰነላቸው ቦታ የሚቈዩ መሆናቸውን ነው።

ጻድቃን ዋጋቸውንና ኃጢአተኞች ቅጣታቸውን የሚቀበሉት በፍርድ ቀን መሆኑን በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 25 ከቍጥር 31 እስከ 46 ባለው ክፍል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘርዝሮ አስረድቶአል።

**ጸሎተ ፍትሐት ለሟቾቹ ምን ጠቀሜታ አለው?**

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ:- «በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም፥ በደሉ ይቅር አባልለትም» ማለቱ በዚህ ዓለምና በሚመጣው ዓለም ይቅር ሊባል የሚችልና ይቅር ሊባል የማይችል ሁለት የኃጢአት ዐይነቶች መኖራቸውን ያመለክታል (ማቴ:ም:12 ቍ:32)።

በዚህም አባባል መሠረት በሚመጣው ዓለም ኃጢአት ይቅር የሚባል ከሆነ ጸሎተ ፍትሐት ጠቃሚ ይሆናል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያመለከተውን የወዲያኛውን ዓለም የኃጢአት ስርየት መሠረት በማድረግ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶ ለነበረው ለኦኔሲፎር «በመጨረሻው ቀን ጌታ ምሕረትን ይስጠው» ብሎ ጸልዮለታል (2ኛ: ጢሞ: ም:1 ቍ:18)። ኦኔሲፎርም በሕይወት ያልነበረ መሆኑ የሚታወቀው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሌሎቹ ሰላምታ ሲያቀርብ ለእርሱ የጸለየለት በመሆኑ ነው። እንዲያውም ለእርሱ ሳይሆን ለቤተሰቡ ሰላምታ አቅርቦአል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን በሚያኽል ታላቅ የሃይማኖት መሪ ከሃይማኖት ሕግና ትእዛዝ ውጪ የሆነ ድርጊት አይደረግም። ለሞቱ ሰዎች መጸለይ የማያስፈልግና ጥቅም የሌለው ቢሆን ኖሮ ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ለሞተ ሰው ባልጸለየም ነበር።

ለሞቱ ሰዎች መጸለይ ደግሞ በጥንት በዘመነ ብሉይም የነበረ እንጂ በክርስትና ሃይማኖት የተጀመረ አይደለም። ጀግናው ይሁዳ መቃብዮስ በጦርነት ለሞቱ ወታደሮቹ የኃጢአት መሥዋዕት ይደረግላቸው ዘንድ ሁለት ሺህ የብር ድራህም አሰባስቦ ወደ ኢየሩሳሌም የላከ መሆኑን በሁለተኛው መጽሐፈ መቃብያን ምዕራፍ 12 ቍ43–45 ላይ ይመለከቷል።

የቤተ ክርስቲያን ትውፊት ማስረጃዎችም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካረገበት ጊዜ ጀምሮ ጸሎተ ፍትሐት ይሠራበት እንደነበረ ይመሰክራሉ። ለምሳሌ የሐዋርያት ትምህርት የሆነው ዲድስቅልያ ምን እንደሚል እንመልከት:-

«በጌታ አማኞች የነበሩ ወንድሞቻችሁ ሰማዕታትም ሆኑ ሌሎች ክርስቲያኖች በሚያርፉበት ጊዜ ያለ መሰልቸት በቤተ ክርስቲያን ተሰብስባችሁ ዘምሩላቸው። በየአብያተ ክርስቲያናችሁ የቅዳሴ ጸሎት አድርጉ። ሟቾቹ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ ከሆነ ወደፊት በመሪመድ አሸኛኘት አድርጉ። በመጽሐፈ መዝሙር:- 'የቅዱሳን ሞት በእግዚአብሔር ዘንድ የከበረ ነው» ተብሏል (መዝ:116ቍ:15)። በሌላ ጊዜ ደግሞ «ጻድቅ ሰው ለዘለዓለም ይታሰባል' ተብሏል (3ዝ:112ቍ:6)።

«በእግዚአብሔር አምነው ላረፉት ጻድቃን ትንሣኤ ሙታን መኖሩንና እነርሱም ሟቾች አለመሆናቸውን ሲያመለክት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሏል:- ‹ደግሞም ስለ ሙታን መነሣት እግዚአብሔር የነገራችሁን አላነበባችሁምን? እርሱም እኔ የአብርሃም፡ አምላክ፡ የይስሐቅ አምላክ፡ የያዕቆብ አምላክ ነኝ ነው ያለው። ስለዚህ እግዚአብሔር የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም»› (ማቴ:ም:22 ቍ:31–32)።

«ደግሞም በእግዚአብሔር ሕያዋን የሆኑ ሰዎች ዐፅም የተጣለ ወይም የረከሰ አይደለም። ለዚህም የሚከተለውን ማስረጃ እንመልከት:- «ኤልሳዕም ሞተ፡ ተቀበረም። ከሞአብ የሚመጡ አደጋ ጣዮች በየዓመቱ የእስራኤልን ምድር ይወርሩ ነበር፡ አንድ ጊዜ ሥርዓተ ቀብር በሚፈጸምበት ሰዓት ከእነዚያ አደጋ ጣዮች መካከል አንድ ቡድን ሲመጣ ስለታየ የሚቀበረውን ሬሳ ወደ ኤልሳዕ መቃብር ውስጥ በመወርወር ጥለውት ሸሹ፡ ያም ሬሳ ከኤልሳዕ አስከሬን ጋር በተገናኘበት ቅጽበት ወዲያውኑ ከሞት ተነሥቶ ቆመ (2ኛ: ነገ:ም13 ቍ:20–21)።

ይህም የሚያመለክተው የኤልሳዕ ዐፅም ቅዱስ የነበረ መሆኑን ነው። ሙሴና ኢያሱም የዮሴፍን ዐፅም ይዘው ሲሄዱ እንደ ርኩሰት አልተቈጠረ ባቸውም። (ዘጸ:ም:13 ቍ:19) ኤጲስ ቆጶሳትና ሌሎችም ሁሉ፡ አሁንም እኛ ያረፉትን ሰዎች አስከሬን ራሳችንን ሳንቈጥብ እንንካ፤

www.ethiopianorthodox.org

አንረክስም፤ የእነር ሱንም ዐፅም አንጸየፍ፡ ይህንንም ከሞተ ሰው የመራቅን ልምድ ከእኛ እናስ ወግድ። እንደዚህ ያለው ልምድ እንደ ሕጸጽና እንደ ፈሪነት ይቈጠርብናል። የሕይወት ተሳታፊዎች ትሆኑ ዘንድ በንጽሕና በጥበባዊ ልብ ተዘጋጁ። የእግዚ አብሔርም መንግሥት ተካፋዮች ሁኑ። ሰዎችንም ተቀባዮች ሆናችሁ ለዘለዓለም ዕረፉ። ሁሉን ቻይ አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአበሔርን ቃል ለመስማት ጆሮአችሁን ይከፈትላችሁ» (ዲድስቅልያ አንቀጽ 33)።

በየአብያተ ክርስቲያኑ በየዕለቱ ከሚደረገው የቅዳሴ ጸሎት መካከል ለሙታን የሚጸለይ መሆኑ ይህ ለሙታን የመጸለይ ሥርዓት ከጥንት ጀምሮ ሲሠራበት የኖረ መሆኑን ያመለክታል።

በሁለተኛው መቶ ዓመተ ምሕረት አካባቢ የነበረው ተርቱልያኖስ:- «ስለ ሞቱ ሰዎች ቍርባን እናቀርባለን፤ ይህን አሠራር ከወዴት አመጣችሁት ተብለን ብንጠየቅ የቀድሞ አባቶች የደነገጉትና የተለመደውን አሠራር ሳናቋርጥ በታማኝነት ስለቀጠልን ነው ብለን መልስ እንሰጣለን፤ ደም አልባ የሆነውም መሥዋዕት ስለ ሕያዋንና ስለ ሙታን ይቀርባል» ብሏል።

በአራተኛው መቶ ዓመተ ምሕረት መጀመሪያ አካባቢ የነበረው አውግስ ጢኖስ የመጽሐፈ መቃብያንን ጥቅስ በማመልከት «ስለሙታን ለምናቀርበው ጸሎት በቂ መስረጃ ነው ብሎአል።»

ቅዱስ ዲዮናስዮስም «ከሰው ልጅ ደካማነት የተነሣ ሰው ለሚፈጽማቸው አንዳንድ በደሎች በካህኑ ጸሎት አማካይነት ለሞተው ሰው ይቅርታ ተደርጎለት ወደ ብርሃንና ወደ ሕይወት ቦታ፥ ማለት ወደ አብርሃም፥ ወደ ይስሐቅና ወደ ያዕቆብ ጉያ ይወሰዳል» ብሏል።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቀ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ላይ ባደረገው አርባ አንደኛ ሰብከት፡ እንዲህ ብሏል:- «አንድ ሰው ኃጢአተኛ እንደሆነ ቢሞት የምንችለውን ያኽል ልንረዳው ይገባል። የምንረዳውም በለቅሶና በሐዘን ሳይሆን፥ በጸሎት፥ በምጽዋትና በቍርባን ነው። የዓለምን ኃጢአት ወደ ተሸከመው የእግዚአብሔር በግ ስለ ሙታን የምንጸልየው እነርሱ መጽናናትንና ዕረፍትን እንዲያገኙ ብለን ነው እንጂ በከንቱ አይደለም። ጻድቁ ኢዮብ ስለልጆቹ ያቀርብ የነበረው ቍርባን ጠቀሜታ ከነበረው ስለ ሙታን የምናቀርበው ቍርባን ምንኛ የበለጠ ጠቀሜታ ይኖረው?»

የቆሞስ ሚና የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ መለኮት 3ኛ መጽሐፍ (ገጽ:508–509)

<u>ከሞቱ በኋላ ጸሎት የሚደረግላቸው ለእንዴት ያሉ ሰዎች ነው</u>? የጸሎተ ፍትሐት ሥርዓት የሚደረግላቸው ለኃጢአተኞችና ለማይታዘዙ ሳይሆን መንገዳቸውን ደግና የተቀደሰ ላደረጉ ሰዎች ነው። ይሁን እንጂ ከምድር የተፈጠሩ ናቸውና አንዳንድ ኃጢአቶችን መሥራታቸው ስለማይቀር እግዚአብሔር ዋጋቸውን እንዳያጐድልባቸው ለእነርሱ እንጸልያለን። ባለመዝሙሩ እንዳለው ኃጢአት እንዳይሠለጥንብኝ ዐውቆ ከመበደል ጠብቀኝ፤ ይህም ከሆነ ታላቅ በደል ከመሥራት ንጹሕ እሆናለሁ» (መዝ:19 ቍ:13)።

እግዚአብሔር የሚችን ኃጢአት ያስተሰርይ ዘንድ የሚለመነው ሳይታወቁ ለተፈጸሙ ኃጢአቶች፥ በድብቅ ለተፈጸሙ ኃጢአቶች፡ እንዲሁም ለተረሱ ኃጢአቶችና ኃጢአት ሠሪው ኃጢአት መሥራቱ ሳይሰማው ለሚሠራቸው ኃጢአቶች ናቸው። ምንም እንኳ እንደዚህ ያሉት ኃጢአቶች ከሰው ተፈጥሮ ደካማነት የተነሣ የተፈጸሙ መሆናቸው ቢታመንበት በእግዚአብሔር ፍርድ በኩል ግን እንዲህ አይደለም። እግዚአብሔር ለሙሴ የነገረው:- «አንድ ሰው ባለማወቅ ከእግዚአብሔር ትእዛዛት አንዱን ቢተላለፍ በደለኛ ነው» ብሎ ነው (ዘሌ:ም:5 ቍ:17)። በዚህም መሠረት አንድ ሰው የሠራውን ኃጢአት ቢረሳ እንኳ በእግዚአብሔር ዘንድ ስለማይረሳ ኃጢአት ሠሪው ይፈረድበታል፤ ይቀጣበታልም። ያን የሠራውን ኃጢአት መርሳት ላለመቀጣት ምክንያት ሆኖ ሊቀርብ አይችልም።

ሰውም ዐፈር የሆነውን ሥጋ የለበሰ እንደመሆኑ መጠን ቢሆን ሙሉ ለሙሉ ከኃጢአት የነጻ ሊሆን አይችልም። ለዚህ አባባል የሚቀርበው የመጽ ሐፍ ቅዱስ ማስረጃ:- «ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናታልላለን፡ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም» የሚለው ነው (1ኛ:ዮሐ:ም:1 ቍ:8)።

ነፍስ ከሥጋ እንደተለየች የመጨረሻ ዋጋዋን የምትቀበለው ወዲያው ሳይሆን በመጨረሻው ፍርድ ቀን መሆኑ የሚታመን በመሆኑና ጻድቃን ምንም ኃጢአት አልሠሩም ማለት ስላይደለ፤



ይህም ማለት ድብቅ ወይም ሳይታወቅ የቀረ፡ ወይም የተረሳ ኃጢአት ስለሚኖርባቸውና የተሰፋ በራቸው ክፍት ስለሆነ የፍትሐቱ ጸሎት እንደሚጠቅማቸው የታመነ ነው።

ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው ጸሎተ ፍትሐት ለእምቢተኞችና ለኃጢአተኞች ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለሚፈጽሙ ነው ከተባለ ለምን ታዲያ ለሚሞት ክርስቲያን ሁሉ ይጸለያል ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል።

እግዚአብሔር በንስሓ የሚመለሰውን ሰው በማንኛውም ጊዜ ቢሆን ይቀበለዋል። ለምሳሌ በሞት አፋፍ ላይ የነበረውና ከጌታችን ጋር ተሰቅሎ የነበረው ወንበዴ ንስሓው ተቀባይነት ያገኘው በመጨረሻው ደቂቃ ነው። ስለዚህ ንስሓ የገባ ሰውና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያገኘው ማን እንደሆነ ስለማናውቅ ለሁሉም እንጸልያለን።

## <u>ጥያቄዎች</u>

1. ቃል ኪዳን ማለት ምን ማለት ነው?
2. በቃል ኪዳን ውስጥ ምን አለ?
3. በሁለት ሰዎች መካከል ስለ ተደረገ ቃል ኪዳን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምሳሌዎችን አቅርብ።
4. ሁለተኛው ዐይነት ቃል ኪዳንስ እንዴት ያለ ነው?
5. ስለ ሁለተኛው ዐይነት ቃል ኪዳን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምሳሌ አቅርብ።
6. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የተነገረው ዋነኛው ክፍል የትኛው ነው?
7. የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ዝርዝር የሚቀመጠው የት ነበር?
8. ቃል ኪዳኑ የተጻፈው በምን ላይ ነበር?
9. የቃል ኪዳኑ ምስክሮች ምንና ምን ነበሩ?
10. የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ማክበር ምንን ያመጣል? አለማክበርስ ምንን ያስከትላል?
11. በቃል ኪዳኑ ምክንያት የእስራኤል ሕዝብ ምን የሚል ስም ወጣለት?
12. እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጠው ቃል ኪዳን ምን ሆነላቸው?
13. እግዚአብሔር ከግለሰቦች ጋር ስለገባው ቃል ኪዳን ምሳሌዎችን ስጥ።
14. እግዚአብሔር ለፊንሐስ ምን ብሎ ቃል ኪዳን ገባለት?
15. የእግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ታማኝነት ከምን ጋር የተያያዘ ነው?
16. ፍትሐት ማለት ምን ማለት ነው?
17. ጻድቃን እስከ ፍርድ ቀን ድረስ የሚቈዩበት ቦታ ምን ይባላል?
18. ኃጢአተኞችስ የሚቈዩበት ቦታ ምን ይባላል?
19. እነዚህ ቦታዎችስ መቈያ ለመሆናቸው ምን ማስረጃ አለ?
20. ጻድቃንም ሆኑ ኃጢአተኞች እስከ ፍርድ ቀን መቈየት ያለባቸው በምን ምክንያት ነው?
21. በሙታን ትንሣኤ ጊዜ ሙታን የሚነሡት በምን ዐይነት ነው?
22. «በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም አይሰረይለትም» የሚለው ጥቅስ ምንን ያመለክታል?
23. የጸሎተ ፍትሐትን ተገቢነት ከሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የተማርነው እንዴት ነው?
24. ጸሎተ ፍትሐት ከክርስትና ዘመን ጀምሮ ብቻ አለመሆኑን የምንረዳው እንዴት ነው?
25. ከመጽሐፍ ቅዱስ ሌላ ለጸሎተ ፍትሐት ማስረጃነት የሚቀርበው ምንድነው?
26. በመጽሐፈ ዲድስቅልያ የቀረበው የሰው ዐፅም ርኩስ አለመሆን ማስረጃ ምንድነው?
27. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በየዕለቱ ለሙታን ጸሎት የሚደረገው በየትኛው ጸሎት ዐይነት ነው?
28. ጸሎተ ፍትሐት የሚደረግላቸው ለእንዴት ያሉ ሰዎች ነው?
29. የኃጢአቶቹስ ዐይነቶች የትኞቹ ናቸው?

www.ethiopianorthodox.org

30. ሳያውቅ ኃጢአት የሠራ ሰው ኃጢአተኛ ለመሆኑ ምን ማስረጃ ይገኛል?
31. ከኃጢአት በፍጹም ንጹሕ የሆነ ሰው እንደማይገኝ ምን ማስረጃ አለ?
32. በዓለም ላይ ጻድቃንና ኃጢአተኞች የሚኖሩ መሆናቸውን እያወቅን ለምን ለሞተ ሰው ሁሉ የፍትሐት ጸሎት እንጸልያለን?

## ምዕራፍ 2

## መጽሐፍ ቅዱስ

### ብሉይ ኪዳን

<u>አንደኛ ዜና መዋዕል</u>:- ከባቢሎን ምርኮ መልስ በኋላ የዜና መዋዕልን መጽሐፍ የጻፈው ካህኑ ዕዝራ ነው። የዜና መዋዕልን መጽሐፍ ለሁለት የከፈሉት ሰባዎቹ ተርጓሚዎች ናቸው። ከዚያ በፊት ግን አንድ መጽሐፍ ነበር እንጂ ሁለት መጻሕፍት አልነበሩም።

ሁለቱ የዜና መዋዕል መጻሕፍት ከመጽሐፈ ሳሙኤልና ከመጽሐፈ ነገሥት ጋር ተመሳሳ ይነት ቢኖራቸውም እንኳ ልዩነቶችም አሉአቸው። አንዳቸው ዘንድ ያለው ጉዳይ ሌላው ዘንድ የለም፤ ወይም አንዳቸው ዘንድ የሌለው ጉዳይ ደግሞ ሌላው ዘንድ አለ።

የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ለጽሑፉ መነሻ ወይም መሠረት ያደረገው የዐይን ምስክረነትን ሳይሆን የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ለጽሑፉ መነሻ ... የሳሙኤልንና የነገሥትን መጻሕፍት ነው። መንግሥታዊ ወይም ታሪካዊ መዝገብን፡ እንዲሁም የሳሙኤልንና የነገሥትን መጻሕፍት ነው። ከሳሙኤልና ከነገሥት መጻሕፍት በማብዛት ወይም በመቀነስ የሚለየውም በዚሁ ምክንያት ነው። የአንድ መንግ ሥት ታሪክ መዝጋቢና የአንድ የሃይማኖት ጽሑፍ አዘጋጅ ዓላማ የተለያየ ነው። በዚህም ምክንያት አንዱ የሚያተኩርበትን ሌላው ችላ ብሎ ይተወዋል፤ ወይም በአጭሩ እግረ መንገዱን ነካ አድርጎት ያልፋል። የዜና መዋዕል መጽሐፍ አዘጋጅ ከጠቀሳቸው መጻሕፍት መካከል የባለ ራእዮቹ የሳሙኤል፥ የናታንና የጋድ የታሪክ መጻሕፍት ይገኙባቸዋል (1ኛ:ዜ:መ: ም:29 ቊ:29)። እንዲሁም ደራሲያቻቸው ያልተገለጡ የእስራኤልና የይሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጻሕፍት ተጠቅሰዋል (2ኛ:ዜ:መ:ም:35 ቊ:27)።

በዜና መዋዕል መጻሕፍት ውስጥ የተጠቀሱት መጻሕፍት አሁን የት እንደሚገኙ አይታወቅም።

ስለ ሴሎናዊው የአኪያ ትንቢት፥ ስለ ነቢዩ ናታን ታሪክ፥ ስለ ዒዶ ራእይ፥ ስለ ነቢዩ ሸማዕያ ትንቢት ምን እንላለን? የትስ ይገኛሉ? (2ኛ: ዘ:መ:ም:9 ቊ:29፥ ም:12 ቊ:15፥ ም:13 ቊ:22)። የአናኒ የኢዩ ታሪክ የትኛው ነው? (2ኛ: ዜና:መ:ም:20 ቊ:34)። የነቢዩ ኢሳይያስ ጽሑፍ ያለው የት ነው? (2ኛ: ዜ:መ:ም:26 ቊ:22፥ ም:32 ቊ:32)።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት መጻሕፍት አንዳንድ ጉዳዮችን በመጨመር ወይም በመቀነስ የሚያቀርቡ ቢሆኑ ነው የዜና መዋዕል መጽሐፍ ከሳሙኤልና ከነገሥት መጻሕፍት የተለየው።

በአንደኛ ሳሙኤል የቀረበው ታሪክ አብዛኛው የቀረበ ቢሆንም ለምሳሌ የሳኦል መንግሥት መነሣትና መውደቅ በአጭሩ ወይም በአጠቃላይ አነጋገር ከመታለፉ በቀር ምንም የታሪክ ዘገባ በዜና መዋዕል ውስጥ አልቀረበም። ስለ ዳዊት መንግሥት ግን በሰፊው ቀርቦአል። ይሁን እንጂ ዳዊት ከሳኦል ጋር የነበረውን ግንኙት ማለት ከሳኦል ሸሽቶ በጋት ንጉሥ ዘንድ ከለላ ማግኘቱ፥ እርሱና ተከታዮቹ የሚኖሩበት አንድ ከተማ ከጋት ንጉሥ የተሰጠው መሆኑ፥ በፈጸመው በደል በነቢዩ በናታን መወቀሱ፥ በደሉን አምኖ ንስሐ መግባቱ፥ ልጁ አምኖን በእኅቱ በትዕማር ላይ በደል መፈጸሙ፥ ሌላው ልጁ አቤሴሎም ለእኅቱ ለትዕማር በመበቀል ወንድሙን አምኖንን መግደሉ፥ ይኸው አቤሴሎም በአባቱ ላይ በማመፅ አባቱን ከመንግሥቱና ከከተማው ማባረሩ፥ አቤሴሎም ድል ሆኖ ከሞተ በኋላ ዳዊት እንደገና ወደ መንግሥቱ መመለሱ፥ እነዚህ ሁሉ ጉዳዮች በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ሳይቀርቡ ታልፈዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ በሳሙኤልና በነገሥት መጻሕፍት የሌሉና በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ውስጥ የተነገሩ ጉዳዮች አሉ። ለምሳሌ በመጀመሪያው ዜና መዋዕል የመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ ምዕራፎች የእስራኤል ሕዝብ የቀድሞ አባቶች ትውልድ ከአዳም እስከ አብርሃም፡ ከይስሐቅና ከያዕቆብ እስከ ዳዊትም፡ ከዳዊት እስከ ዘሩባቤል ተዘርዝሮአል። የትውልዱ ሐረግ በአሪት



ዘፍጥረትና በኦሪት ዘኍልቍ የቀረበ ቢሆንም እንኳ የዜና መዋዕሉ ዝርዝር በእስራኤል ሕዝብ ዘንድ በጠንቃቄ የተጠበቀ ነበር። ይሁን እንጂ በመጀመሪያው ዜና መዋዕል የቀረቡት የስም ዝርዝሮች በኦሪት ዘፍጥረትና በኦሪት ዘኍልቍ ከቀረቡት ስሞች ልዩነት ይታይባቸዋል። ልዩነትም ሊታይ የቻለው ሰዎች በመጠሪያ ስም ወይም በቤተሰብ ስም ስለሚጠሩ ነው። እንዲሁም በመጽሐፈ ዜና መዋዕል በሳሙኤልና በነገሥት መጻሕፍት ውስጥ የማይገኝ የካህናት አገልግሎትና የመዘምራን ሥርዓት ተመዝግበው ይገኛሉ።

የመጀሪያው ዜና መዋዕል ኻያ ዘጠኝ ምዕራፎች ያሉት ሆኖ በሁለት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ ዘጠኝ ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኘው ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው የዘር ሐረግ ዘርዝር ነው።

ሁለተኛው ክፍል ከምዕራፍ ዐሥር እስከ ምዕራፍ ኻያ ዘጠኝ ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የሳኦል መንግሥት ወድቆ የዳዊት መንግሥት መተካት፡ የጦር ሠራዊቱ ብዙ ጦርነቶችን ማሸነፉ፥ በአካባቢ ያሉትን ነገሥታት ሁሉ ማስጨነቃቸው፡ በእነርሱም ላይ ግብር መጫኑ፡ ዳዊት በከተማዋ ውስጥ ብዙ ቤቶችን መሥራቱ፡ ከቤቶቹም አንዱን ለቃል ኪዳኑ ታቦት ማረፊያ እንዲሆን ማድረጉ፥ የተወሰኑ ሌዋውያንንም ለአገልግሎት፡ መሥዋዕት ለማቅረብና መንፈሳዊ ዜማንም እንዲያዚሙ ለማድረግ መቅጠሩና ለቤተ መቅደሱ ሥራ የሚያገለግሉ ዕቃዎችን ካዘጋጀ በኋላ መንግሥቱን ለልጁ ለሰሎሞን ማስረከቡ ይገኙበታል።

<u>ሁለተኛው መጽሐፈ ዜና መዋዕል</u>:- ይህ መጽሐፍ ሠላሳ ስድስት ምዕራፎች ያሉት ሆኖ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ ዘጠኝ ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የንጉሥ ሰሎሞን ሀብታምነትና ዝነኛነት፡ በቤተ መቅደስ ሥራ መጠመዱ፡ ለዚሁ ለቤተ መቅደሱ ሥራ ያወጣው ወጪ ብዛት፡ ቤተ መቅደሱም በተለይ እግዚአብሔር ከተገለጠበት በኋላ፥ ከሰማይ በታች የትም ቦታ እርሱን የመሰለ አለመኖሩ በዝርዝር ተገልጦበታል።

ሁለተኛው ክፍል ከምዕራፍ ዐሥር እስከ ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ሰሎሞን ከሞተ በኋላ ልጁ ሮብዓም የአባቱን መንግሥት መውረሱ ታሪክ ይገኝበታል። በእስራኤል ሕዝብ ላይም ስለታበየ መንግሥቱ ለሁለት ተከፈለ። ብዛት ያላቸው ዐሥሩ ነገዶች ከናባጥ ልጅ ከኢዮርብዓም ጋር ሲሄዱ ለእርሱ የቀሩለት የይሁዳና የብንያም ነገዶች ብቻ ናቸው። ዐምፀው የሄዱትን ነገዶች አስገድዶ ለመመለስ ወታደሮችን ባሰባሰበ ጊዜ እግዚአብሔር በነቢዩ ሸማዕና አማካይነት በእስራኤል ላይ እንዳይዘምት አስጠነቀቀው። ሮብዓም ከሞተ በኋላ አቢያ የአባቱን መንግሥት ሲወርስ የእስራኤሉ ንጉሥ ኢዮርብዓም በይሁዳ መንግሥት ላይ አደጋ ለመጣል ተነሣ። ኢዮርብዓም ያሰለፈው የእስራኤል መንግሥት ጦር ሠራዊት ብዛት ስምንት መቶ ሺህ ወታደር ነበር። ይሁን እንጂ የይሁዳ መንግሥት አራት መቶ ሺህ ሰዎች ብቻ ባሉት ጦር ሠራዊት በእግዚአብሔር ርዳታ የኢዮርብዓምን ሠራዊት ድል አደረገ።

የይሁዳ ንጉሥ አሳ፥ እግዚአብሔር ታላቅ ድልን ያጐናጸፈው መሆኑን ቢያይም እንኳ የእስራኤልን ንጉሥ ባዕሻን ከድንበሩ ለማባረር በእግዚአብሔር ላይ በመተማመን ፈንታ የሶርያን ንጉሥ እርዳታ በመጠየቅ እግዚአብሔርን አስቈጣ።

ሦስተኛው ክፍል ከምዕራፍ ዐሥራ ሰባት እስከ ምዕራፍ ኻያ አንድ ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ኢዮሣፍጥ ሃይኖትንና ሕግን ያጠናከረ መሆኑ ተገልጾአል። ሕግ ነክ ክርክርን በሚመለከት ጉዳይ ሁሉ ይዳኙ ዘንድ ሌዋውያንን፡ ካህናትንና የታወቁ ያገር ሽማግሌዎችን በየቦታው ሾመ። አንድ የፈጸመው ከባድ ጥፋት ግን የአክዓብና የኤልዛቤል ልጅ የነበረችውን ዐታልያን ለልጁ ለኢዮራም ማጋባቱ ነው። ዐታልያም የነገሥታቱን ተወላጆች ሁሉ የፈጀች ነች። ኢዮሣፍጥ ከአክዓብ ጋር በጋብቻ ስለተሳሰረ በራሞት ገለዓድ ላይ ለመዝመት ከአክዓብ ጋር ተስማማ። በዚያም ጦርነት አክዓብ ቈሰለና በኋላም ሞተ። ኢዮሣፍጥ ግን በሰላም ወደ ሀገሩ ተመለሰ። ቀጥሎም የሞአብና የዐሞን ሠራዊት፡ እንዲሁም የሚዒር ተራራ ነዋሪዎች ተባብረው ይሁዳን ለመውረር ዘመቱ። እግዚአብሔር ግን በወራሪዎቹ ሠራዊት ላይ ሽብር ፈጠረባቸውና እርስ በርሳቸው ተፋጁ። የይሁዳም ሰዎች ብዙ ምርኮ ሰበሰቡ።

በአንድ ወቅት ኢዮሣፍጥ ብዙ ክፉ ነገር ከፈጸመ ከእስራኤል ንጉሥ ከአካዝያስ ጋር የስምምነት ውል አድርጎ ነበር። ሁለቱ በመተባበር ዔጽዮንጋብር ተብሎ በሚጠራ ወደብ ላይ ውቅያኖስን አቋርጠው ሊጓዙ የሚችሉ መርከቦችን ሠርተው ነበር፡ ነገር ግን የማሬሻ ተወላጅ



www.ethiopianorthodox.org

የሆነው የዶዶዋ ልጅ ኤልዔዘር ኢዮሣፍጥን፡- «ከአካዝያስ ጋር የስምምነት ውል ስላደረግህ እግዚአብሔር የሠራኸውን ሁሉ ያጠፋል» ሲል አስጠንቅቆት ስለነበር መርከቦቹ በሙሉ ተሰባበሩ፤ ከቶም በባሕር ላይ አልተጓዙም።

ኢዮሣፍጥ ከሞተ በኋላ ልጁ ኢዮራም ነገሠ። የኢዮራምም አካሄድ በጣም የተበላሸ ነበር። የንጉሥ አክዓብን ልጅ በማግባቱ አካሄዱን ሁሉ እንደ አክዓብና እንደሌሎቹ የእስራኤል ነገሥታት አደረገ። ከበደሉም ብዛት የተነሣ በእርሱና በቤቱ ላይ ችግር እንደሚደርስበት በመግለጥ ነቢዩ ኤልያስ የወቀሳ ደብዳቤ ልኮለታል። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር በኢዮራም ላይ ሊድን የማይችል ከባድ የአንጀት በሽታ አመጣበት። እርሱም በበሽታው ለሁለት ዓመቶች ከተሠቃየ በኋላ አንጀቱ ወጥቶ በብርቱ ሥቃይ ሞተ።

አራተኛው ክፍል ከምዕራፍ ኻያ ሁለት እስከ ምዕራፍ ሠላሳ ስድስት ድረስ ነው። በዚህም ክፍል በዳዊት ሥርወ መንግሥት ሥር ስለተነሡት ነገሥ ታት ታሪክ፥ ናቡከደነፆር ዋና ከተማዋን ኢየሩሳሌምን አፍርሶና አብዛኛዎቹን የይሁዳ ሕዝብ ማርኮ እስከ ወሰደበት ጊዜ ድረስ የሚዘረዝር ነው።

የመጀመሪያው የዜና መዋዕል መጽሐፍ ከሳሙኤልና ከነገሥት መጻሕፍት ጋር በመጨመር ወይም በመቀነስ፥ ወይም በአጠቃላይ በማቅረብ እንደሚለያይ ሁሉ ሁለተኛው መጽሐፍም በዚያው አካሄድ የቀጠለ ነው። ይህ መጽሐፍ ቀደም ብለው በቀረቡት መጻሕፍት ውስጥ የሌሉ ታሪኮችን የሚያቀርብ ሲሆን ቀደም ብለው ከቀረቡት ታሪኮችም አንዳንዶቹን በአጠቃላይና በጣም በማሳጠር አቅርቦአቸዋል፤ ሌሎችን ታሪኮች ደግሞ በፍጹም ትቶአቸዋል።

ቀደም ብለው ከቀረቡት ታሪኮች በዜና መዋዕል መጽሐፍ በተጨማሪ የቀረቡት ጉዳዮች ለምሳሌ ኢዮሣፍጥ ሃይማኖትንና የአምልኮ ስርዓትን ማጠና ከሩና እንዲስፋፋ ማድረጉ፥ ቀደም ብለው ያልተነገሩ ጦርነቶች፥ ከእነዚህም መካከል አቢያ ከኢዮርብዓም ጋር ጦርነት መግጠሙ፥ ሌላው ደግሞ ኤልያስ ለኢዮራም የጻፈው ደብዳቤ፥ የካህኑ የዮዳሄ ልጅ ዘካርያስ ንጉሡን በጥፋቱ ስለወቀሰው የአባቱን የዮዳሄን ውለታ ከግምት ውስጥ ባለማስገባት ንጉሥ ኢዮአስ ዘካርያስን በድንጋይ ተወግሮ እንዲገደል ማስደረጉ፥ ንጉሥ ዖዝያ ለካህናት በቀር ለእርሱ ያልተፈቀደለትን ዕጣን ማጠን ስለ ተዳፈረ ለምጽ የወጣበት መሆኑ፥ የንጉሥ ምናሴ ንስሐ መግባትና እግዚአብሔርም ንስሓውን መቀበሉ፥ እንዲሁም በነገሥት መጽሐፍ ውስጥ ስማቸው ያልተጠራ ነቢያት ዒዶ፥ ያሄድ፥ ኤልዓዘር መጠቀሳቸው ናቸው (2ኛ:ዜና:መ:ም:13 ዝቁ:22፥ ም:15ቍ: 8፥ ም:20 ቍ:37፥ ም:28 ዝቁ:9)።

ቀደም ተብለው በመጽሐፈ ነገሥት የቀረቡ ታሪኮች ደግሞ በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ሳይቀርቡ ቀርተዋል። ለምሳሌ መጽሐፈ ዜና መዋዕል የሚያቀርበው ስለ ይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ብቻ ነው። ከይሁዳ ነገሥታት ጋር ባላቸው ግንኙነት ካልሆነ በቀር ስለ እስራኤል ነገሥታት ታሪክ በፍጹም አልተ ተረከም። በዚህም ምክንያት የእስራኤልን መንግሥት መውደቅና የሕዝቡ ወደ አሦር መማረክ ጉዳይ የሰሎሞን ከእግዚአብሔር መንገድ መራቅንና ጣዖት ማምለኩን ምንም ሳያነሣው ዐልፎታል። ወንድሙ አዶንያስ የአባቱን ዙፋን ለመውረስ ሙከራ በማድረጉና የአባቱ ሚስት የነበረችውን አቢሻግን ለማግባት በመጠየቁ ሰሎሞን ያስገደለው መሆኑ፥ የኔርን ልጅ አብኔርንና አማሳን በመግ ደሉ ኢዮአብን ማስገደሉ፥ ካህኑን አብያታርን ማባረሩ፥ አባቱን ዳዊትን በመስ ደቡ ሺምኢን ማስገደሉ እነዚህ ሁሉ ታሪኮች በዜና መዋዕል መጽሐፍ ውስጥ የማይገኙ ናቸው።

የአንዳንድ ነቢያትም ታሪክ ሳይጠቀስ ታልፎአል። ለምሳሌ ኢዮርብዓም ያሠራውን ጣዖት የማስመረቂያ በዓል ያከብር በነበረበት ጊዜ ጥፋቱን ነግሮ ሊገሥጸው ከይሁዳ ወደ ቤቴል የመጣው የእግዚአብሔር ሰው ታሪክ አልቀረ በም። እንዲሁም ጦርነቱ ምን ውጤት እንደሚኖረው ለአክዓብና ለኢዮሣፍጥ በመንገር ከአራት መቶዎቹ የሐሰት ነቢያት የተለየው የነቢዩ ሚክያስ ታሪክ አልቀረበም።

በነቢዩ ኤልሳዕ ታሪክ ውስጥ የዮርዳኖስን ወንዝ በሚሻገርበት ጊዜ የኢያሪኮ ሰዎች ውሃቸው መራራ መሆኑን ሲገልጡለት ጨው ጨምሮበት እንዲጣፍጥ ማድረጉ፥ በቤቴል የነበሩ ልጆች ባላገጡበት ጊዜ ድቦች ወጥተው አርባ ሁለቱን ልጆች መግደላቸው፥ የሞአብ ንጉሥ ሜሻ በየዓመቱ ለእስራ ኤል ንጉሥ የአንድ መቶ ሺህ ጠቦቶችና የአንድ መቶ ሺህ በግ ጠጕር ይገብር ነበር። ነገር ግን የእስራኤል ንጉሥ አክዓብ በሞተ ጊዜ አልገብርም ብሎ ዐመፀ፥ የእስራኤል ንጉሥ ኢዮራም ከይሁዳ ንጉሥ ከኢዮሣፍጥ ጋር ለጦርነት ወጣ፥ ነገር ግን ውሃ ስላለቀባቸው



ወደ ነቢዩ ኤልሳዕ ሄዱ። የጦር ጓደኞቹም የይሁዳ፥ የእስራኤልና የኤዶም ነገሥታት ነበሩ። እግዚአብሔር በኤልሳዕ ዐድሮ ከሸለቆው ውሃ እንደሚወጣላቸው ነገራቸው። የሞአብ ሰዎች የተጥለቀለቀውን ውሃ ሲያዩ ከፀሐዩ ነጸብራቅ ጋር ደም መሰላቸው። ስለዚህም፡- ይህ የሰው ደም ነው፤ ሦስቱ ጠላቶቻችን እርስ በርሳቸው ተፋጅተዋል ብለው በማመን አደጋ ለመጣል ወጡ። በዚህ ጊዜ የጦር ተባባሪዎቹ ደመሰሱአቸው፥ ምርኮም ሰበሰቡ። የሞአብም ንጉሥ ጦርነቱ በበረታበት ጊዜ ልጁን በግንብ አጥሩ ላይ አውጥቶ የሚቃጠል መሥዋዕት በማድረግ ሲያቀርበው በማየታቸው ድርጊቱ ስለ ዘገነናቸው ሦስቱ የጦር ኪዳን ጓዶች ጦርነቱን አቁመው ወደየአገራቸው ተመለሱ።

የነቢያት ጉባኤ አባል የነበረ አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ባለ ዕዳ መጥቶ በአባታቸው ዕዳ ምክንያት ልጆቹን ባሪያ ሊያደርጋቸው መፈለጉን የሟች ሚስት በተገነዘበች ጊዜ ወደ ነቢዩ ኤልሳዕ ሄዳ ችግርዋን አዋየችው። እርሱም ጥቂት የወይራ ዘይት ያለበትን ማሰሮ ወደ ብዙ ማድጋዎች እንድትገለብጥ ካዘዛትና እርስዋም በብዙ ማድጋዎች ከሞላች በኋላ ዘይቱን ሸጣ ዕዳውን እንድትከፍልና የተረፈውን ገንዘብ ለእርስዋና ለልጆችዋ መተዳደሪያ እንድታደርገው ነገራት።

ነቢዩ ኤልሳዕ ሹኔም በምትባለ ከተማ በኩል ሲያልፍ አንዲት ሀብታም ሴት ወደ ቤትዋ ገብቶ ምግብ እንዲበላ ጋበዘችው። ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ወደ ሹኔም በመጣ ጊዜ ሁሉ ወደ ቤትዋ እየገባ ይመገብ ነበር። በሚመጣበት ጊዜ ማረፊያ እንዲሆነውም በሰገነቱ ላይ አንዲት ትንሽ ክፍል እንዲሠራላት ባልዋን ጠየቀችው። ቤቱም ተሠርቶ አንድ አልጋ፥ አንድ ጠረጴዛ፥ አንድ ወንበርና አንድ የፋኖስ መብራት ተቀመጠለት። ወደ ሹኔምም በሚመጣበት ጊዜ ሁሉ የሚያርፈው እዚያ ነበር። የውለታዋንም አጸፋ ለመክፈል ብሎ ሴትዮዋ ልጅ ያልወለደች መሆንዋን ስላወቀ ልጅ እንድትወልድ ከጸለየላት በኋላ አንድ ወንድ ልጅ ወለደች። ልጁ ካደገ በኋላ ድንገት ታሞ ሞተ። እናትዮዋ የሞተውን ልጅ በነቢዩ አልጋ ላይ አኑራው ነቢዩ ወደሚገኝበት ቦታ በፍጥነት ሄደች። ከነቢዩም ጋር ወደ ቤትዋ ተመልሰው የኤልሳዕ መምህር የነበረው ኤልያስ የሰራጵታዋን መበለት ልጅ ያስነሣበትን መንገድ በመከተል ልጅዋን ከሞት አስነሣላት።

በመላ ሀገሪቱ ላይ ራብ በነበረበት ጊዜ ነቢዩ ኤልሳዕ የነቢያትን ጉባኤ በማስተማር ላይ እያለ አገልጋዩን ወጥ እንዲያዘጋጅ አዘዘው። ከነቢያት አንዱ ወደ ሜዳ ወጥቶ ጕመን መሰል መራራ ቅጠል ለቅሞ አመጣ። ያን ቅጠል ቈራርጦ ከቀቀለው በኋላ እየጨለፈ አወጣላቸውና መብላት ሲጀምሩ «በዚህ ወጥ ውስጥ የሚገድል መርዝ አለበት» ብለው ወደ ነቢዩ ኤልሳዕ ጮኹ። ነቢዩ ኤልሳዕም ዱቄት እንዲያመጡለት በማድረግ በወጡ ውስጥ ከጨመረበት በኋላ ጣፍጦአቸው ሊመገቡት ችለዋል።

አንድ ሰው በዓልሻሊሻ ተብሎ ከሚጠራ ስፍራ በመከር ጊዜ መጀመሪያ ከተወቃው ገብስ የተጋገሩ ኻያ ሙልሙሎችና አዲስ የተቈረጠ እሸት ለነቢዩ ኤልሳዕ ይዞለት መጣ። ነቢዩም አገልጋዩን ያን የመጣውን ምግብ አንድ መቶ ለሚሆኑ የነቢያት ጉባኤ አባላት እንዲያቀርብ አዞት ሁሉም ከበሉ በኋላ ተርፎ ለማንሣት ተችሎአል።

የሶርያ ጦር አዛዥ የነበረው ንዕማን የለምጽ በሽታ ነበረበት። አንድ ጊዜ የሶርያ ጦር ሠራዊት ከእስራኤል ጦር ሠራዊት ጋር ባደረገው ጦርነት አንዲት እስራኤላዊት ሴት ልጅ ተማርካ ለንዕማን ሚስት አገልጋይ ሆና ስለነበረ ለእመቤትዋ ለንዕማን ሚስት፡- «ጌታዬ ንዕማን ወደ እስራኤል አገር ቢሄድ ነቢዩ ኤልሳዕ ከለምጹ ሊያድነው ይችል ነበር» ብላ ነገረቻት። በእርስዋም አባባል መሠረት ወደ እስራኤል ጉዞውን ቀጠለ። የሶርያውም ንጉሥ ወደ እስራኤሉ ንጉሥ የዐደራ ደብዳቤ ጽፎ በንዕማን እጅ ልኮት ነበር። የእስራኤሉ ንጉሥ የሶርያውን ንጉሥ ደብዳቤ በተመለከተ ጊዜ የተንኰል ደብዳቤ መስሎት ግራ ተጋብቶ ነበር። ነቢዩ ኤልሳዕ ግን አይዞህ ወደ እኔ ላከው ብሎ አረጋጋው። ከዚያም ነቢዩ ኤልሳዕ ንዕማንን ሄደህ በዮርዳኖስ ወንዝ ሰባት ጊዜ ተነከር ብሎ አዘዘውና እንደታዘዘው ባደረገ ጊዜ ከለምጹ በሽታ ዳነ።

በነቢዩ ኤልሳዕ ኀላፊነት ሥር የነበሩት ነቢያት ጉባኤ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ በመሄድ ዛፍ እንዲቈርጡና የሚኖሩበትን ቤት ለመሥራት እንዲችሉ ይፈቅድላቸው ዘንድ ጠየቁት። ከፈቀደላቸውም በኋላ ከእነርሱ ጋር እንዲሄድ ለመኑትና ከእነርሱ ጋር ሄደ። እዚያም ዛፍ በመቍረጥ ላይ እያሉ አንዱ መጥረቢያው ወልቆ በውሃው ውስጥ ወደቀ። ያ መጥረቢያው የወደቀበት ሰው መጥረቢያው የተውሶ ስለሆነ ምን ይሻለኛል ብሎ ጮኸ። ኤልሳዕም መጥረቢያው የወደቀበትን አቅጣጫ ከጠየቀ በኋላ አንድ እንጨት ቈርጦ በውሃው ላይ ስለጣለው መጥረቢያው ተንሳፈፈ። ከዚያም አውጥቶ እንዲወስደው ነገረውና አውጥቶ ወሰደው።

www.ethiopianorthodox.org

የሶርያ ሠራዊት ሰማርያን በመክበቡ በሰማርያ ታላቅ ራብ ሆኖ በነበረበትና ሕዝቡ ተጨንቆ በነበረበት ጊዜ እህል በሁለት ቀን ውስጥ በጣም እንደሚረክስ ተናግሮ ነበረ። እርሱም በተናገረው ትንቢት መሠረት በሚያስገርም ሁኔታ የተናገረው ትንቢት ደርሶአል።

ኤልሳዕ ከሞተ በኋላ፣ አንድ ጊዜ ሰዎች የሞተ ሰው ለመቅበር ተሸክመው ሲሄዱ የሞአብ ወራሪዎች ከሩቅ ሲመጡ ስላዩ ደንግጠው አስከሬኑን ወደ ኤልሳዕ መቃበር ወርውረው ሸሹ። ሬሳው የኤልሳዕን ዐፅም በነካ ጊዜ የሞተው ሰው ተነሥቶ በእግሩ ቆመ።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ጉዳዮች ሁሉ በዜና መዋዕል መጽሐፍ ውስጥ ሳይነገሩ የታለፉ ናቸው።

<u>ትንቢተ ኢሳይያስ:-</u> ይህ የትንቢት መጽሐፍ ከትንቢት መጻሕፍት የመጀመሪያው ነው። እንዲያውም እንደ ተልሙድ ነቢዩ ኢሳይያስም ከነገሥታት ዘር ወገን እንደሆነ ይነገር ለታል። እንዲያውም እንደ ተልሙድ ነቢዩ ኢሳይያስም ከነገሥታት ዘር ወገን እንደሆነ ይነገር ለታል። የኢሳይያስ አጻጻፍ አባባል የይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ የኢሳ ይያስ አባት የአሞጽ ወንድም ነው። የኢሳይያስ አጻጻፍ ከሌሎች ነቢያት ሁሉ የላቀ ነበር። ከዚህ በቀር አገልግሎቱን ከመጀመሩ በፊት ስለ ኢሳይያስ የቀድሞ ሕይወት ታሪክ እጅግም አይታወቅም። ሥራውን ማለት አገልግሎቱን የጀመረው በዖዝያ መንግሥት መጨረሻ ከክርስቶስ ልደት በፊት ወደ 759 ዓመት አካባቢ ነው። በሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት በዐሥራ አራተኛው ዓመት የነበረ መሆኑን በሁለተኛው ነገሥት ምዕራፍ ዐሥራ ስምንት ከቊ:13 እስከ ምዕራፍ 19 ይመለከቷል። ሁለተኛውን መጽሐፈ ነገሥት ከምዕራፍ 15 እስከ ምዕራፍ 20 ድረስ በመመልከት የኢሳይያስ የአገልግሎት ዘመን ወደ 47 ዓመት አካባቢ እንደሚሆን ይገመታል። የኖረውም እስከ ንጉሥ ምናሴ፥ ዘመን ድረስ ሲሆን፥ ንጉሥ ምናሴ ገና በንስሓ ወደ አምላኩ ከመመለሱ በፊት ኢሳያያስን በመጋዝ አስቈርጦ እንዳስገደለው ይነገራል (ዕብ:ም:11 ቊ37)። በዚህም መሠረት ከስድሳ ዘመን ዕድሜ በላይ እንደኖረ ይገመታል።

ትንቢተ ኢሳይያስ ስድሳ ስድስት ምዕራፎች ያሉት ሲሆን በስድሰት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ አምስት ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የተናገራቸው ጉዳዮችና ትንቢቶች የሚከተሉት ናቸው:- በዖዝያ ዘመነ መንግሥት የይሁዳ ሕዝብ የሰዶምንና የገሞራን ሕዝብ ዐይነት ርኵሰት እያራመደ በመሆኑ በንስሓ ካልተመለሰ በቀር እግዚአብሔር ከባድ ቅጣት የሚያመጣበት መሆኑን በመግለጥ አስጠንቅቆአል። ሕዝቡ ግን ከኃጢአቱ በንስሓ ቢመለስ እግዚአብሔር ይቅርታ እንደሚያደርግለት ገልጦለ ታል። ይህንንም የገለጠላቸው እንዲህ በማለት ነው:- «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- ‹ኑ! እንወ ቃቀስ! በኃጢአት እንደ አለላ ብትሆኑ እንደ በረዶ ትነጻላ ችሁ! እንደ ደምም ብትቀሉ እንደ ባዘቶ ትነጣላችሁ! እሺ ብላችሁ ብትታ ዘዙኝ ምድር የምታስገኘውን በረከት ትበላላችሁ! እምቢ ብላችሁ ብታምፁ ግን ሰይፍ ይበላችኋል፤ ይህን የተናገርሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝ (ኢሳ:ም:1 ቊ:18–20)። የሕዝብ መሪዎችም ከሌላው ሕዝብ ይበልጥ ኀላፊነት እንዳለ ባቸው በመግለጥ ወቅሶአቸዋል (ም:1 ቊ:10–17)። ማድረግ የሚገባቸውንም እንዲያደርጉ መክሮአ ቸዋል። መሪዎች ሕዝቡን እንደሚያስቱ ማለት መንገዳቸውን እንደሚያጣምሙባቸው ይናገራል። የኃጢአቶቹንም ዐይነቶች በመዘርዘር ከባድ ቅጣት እንደሚደርስባቸው ማስጠንቀቂያ የሰጠባቸው ሥሥታምነት፥ ስግብግብነት፥ በድኾች ላይ መጨከን፥ መጠጥን በብዛት ማዘውተር፥ ሰውነትን ለማስደሰት የሚደረጉ ድርጊቶች፥ የተፈቀዱና ያልተፈቀዱ ነገሮችን የመለየት ችሎታ አለመኖር እንዲሁም በክፉና በደጉ፥ በመራራና በጣፋጩ መካከል፥ በብርሃንና በጨለማ መካከል ለመለየት አለመቻል፤ በጉቦ ምክንያት ፍርድ ማጣመም ናቸው።

ሁለተኛው ክፍል ከምዕራፍ ስድስት እስከ ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ስለ ኢዮአታምና ስለ አካዝ ትንቢት መናገሩ፥ ጌታ በቤተ መቅደስ ውስጥ በከፍተኛ ዙፋን ላይ በልዕልና ተቀምጦ፥ መጐናጸፊ ያውም ቤተ መቅደሱን ሞልቶ፥ ሱራፌል የተባሉት መላእክትም እያንዳ ንዳቸው ስድስት ክንፎች ያላቸው፥ በሁለቱ ክንፎቻቸው ፊታቸውን የሚሸፍኑ፥ በሁለቱ ክንፎቻቸው እግሮቻቸው የሚሸፍኑ፥ በሁለቱ ክንፎቻቸው የሚበርሩ በጌታ ዙሪያ ቆመው በመቀባበል ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ቅዱስ ነው» ይሉ ነበር። ከመላእክቱም አንዱ በጉጠት እሳት ፍም ይዞ በመምጣት የነቢዩን ከንፈር በማስነካት በደልህ ተወገዶልህ! ኃጢአትህም ይቅር ተብሎልሃል አለው። ይህም ድርጊት የሚያመለክተው እግዚአ ብሔር በቅዳሴው ጸሎት ላይ ተገኝቶ ሥጋውንና ደሙን ለምእመናን በመስጠት

የኃጢአት ስርየት የሚያደርግላቸው መሆኑን ነው። ሌላው በዚህ ክፍል ውስጥ ያለው ትንቢት ደግሞ የክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለድ ነው። «እግዚአብሔር ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል! እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች» (ም:7 ቊ:14)። እንዲሁም:- «እነሆ ሕፃን ተወልዶልናል፤ ወንድ ልጅም ተሰጥ ቶናል! እርሱም መሪ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ፤ መካር፤ ኀያል አምላክ፤ የዘለዓለም አባት፥ የሰላም አለቃ ይባላል» (ም:9 ቊ:6) ። እንዲሁም በዚሁ ክፍል ያለው ሌላው ትንቢት ደግሞ:- «ከእሴይ ግንድ በትር ይወጣል፤ ከሥ ሩም ቊጥቋጦ ያፈራል፤ የእግዚአብሔር መንፈስ፥ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፤ የምክርና የኀይል መንፈስ፤ የዕውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል» ብሎአል (ኢሳ:ም:1 ቊ:1–2)።

ስለ ክርስቶስም መምጫ ጊዜ በዛብሎንና በንፍታሌም ነገዶች ምድር የክርስቶስ ብርሃን እንደሚገለጥ ትንቢት ተነግሮአል (ም:9 ቊ:1)። በዚሁ ክፍል ውስጥ ስለ እስራኤልና ሶርያ መፍረስና ስለ ሕዝቦቻቸውም መማረክ ትንቢት ተነግሮአል። ይህም የሆነው የእስራኤል ንጉሥ ፋቁሔና የሶርያው ንጉሥ ረጺን ይሁዳን ለማጥቃት አሢረው በለነበረ ነው (ም:7 ቊ:1–9)።

ሦስተኛው ክፍል ከምዕራፍ ዐሥራ ሦስት እስከ ምዕራፍ ኻያ ሦስት ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ስለ ባቢሎን፥ ስለ አሦር፤ ስለ ሞአብ፥ ስለ ሶርያ፤ ስለ እስራኤል፥ ስለ ግብጽና ስለ ጢሮስ መውደም የተለያዩ ትንቢቶች ተነግረውበታል።

አራተኛው ክፍል ከምዕራፍ ኻያ አራት እስከ ሠላሳ አምስት ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ እምቢተኛነትና ዐመፀኛነት ማስጠንቀቂያ የተሰጠበት ሲሆን፥ ከሕዝቡም መካከል የእነርሱን ችግር የሚመኙ ወገኖችን አጥፍቶ ለመንገሥ ወደፊት በሚመጣው መሲሕ ጥበቃ ለመኖር የሚጠባበቁ አሉ።

አምስተኛው ክፍል ከምዕራፍ ሠላሳ ስድስት እስከ ምዕራፍ ሠላሳ ዘጠኝ ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ንጉሥ ሰናክሬም ይሁዳን መውረሩ፤ በንጉሥ ሕዝቅያስ ጸሎት አማካይነት በእግዚአብሔር እርዳታ ከንጉሥ ሰናክሬም ወታደሮች አንድ መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ በተአምር መሞታቸው፥ እንዲ ሁም ሕዝቅያስ ከሕመሙ መፈወሱ፥ የፀሐይ ጥላ ዐሥር እርምጃ ወደ ኋላ መመለሱ ይገኙበታል።

ስድስተኛው ክፍል ከምዕራፍ አርባ እስከ ምዕራፍ ስድሳ ስድስት ድረስ ነው። አንዳንድ ሰዎች የኢሳይያስን ትንቢት ከወንጌል እንደ አንዱ ክፍል አድርገው ይቈጥሩታል። ነቢዩ ኢሳይያስንም ወንጌላዊው ነቢይ ይሉታል። ይህንንም ያሉት ስለ ክርስቶስ መምጣትና ስለ ሥራው፥ እንዲሁም ስለ አዳኝ ነቱ ግልጥ የሆኑ ትንቢቶችን የተናገረ በመሆኑ ነው። ነቢዩም ወንጌላዊው ነቢይ የተባለበት ሌላው ምክንያት ብዙዎችን ጉዳዮች ግልጥ አድርጎ ያመለከተው ከትንቢትነት ይልቅ ታሪክ ተራኪ ስላስመሰለው ነው። ለምሳሌ የዮሐንስ መጥምቁን መምጣት ሲናገር «የዐዋጅ ነጋሪ ቃል:- የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ ጥረጉ፤ ለአምላካችንም ጐዳና በበረሓ አስተካክሉ» ብሎአል (ኢሳ:ም:40 ቊ:3)።

የክርስቶስን አመጣጥና ትሕትናውን ሲገልጥ እንዲህ ብሎአል:-

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- ‹እኔ የምደግፈው፥ የመረጥሁትና በእርሱ ደስ የሚለኝ አገልጋዩ ይህ ነው፤ መንፈሴ በእርሱ እንዲያድርበት አደርጋለሁ፤ እርሱ ለሕዝቦች ሁሉ ትክክለኛ ፍርድን ያስገኛል»› (42፥ 1)።

ክርስቶስ ሕዝቦች ሁሉ ይታዘዙለት ዘንድ ያቀረበውን ጥሪ እንዲህ ሲል ገልጦታል:-

እንዲሁም:-

«ላልጠየቁኝ ተገለጥሁ፤ ላልፈለጉኝም ተገኘሁ፤ ስሜንም ለማይጠሩ ሕዝቦች እነሆ፤ አለሁ አልኋቸው» (ም:65 ቊ:1)።

«እርሱ በኀይለኛ ነፋስ እንደሚመጣ ጐርፍ አደጋ ይጥላል፤ በምሥራቅና በምዕራብ ያሉ ሕዝቦች አስደናቂ ስሙን እያስከበሩ ያመሰግናሉ» (ም:59 ቊ:19)።

«የኢየሩሳሌም ሕዝብ ግን፥
እግዚአብሔር ትቶናል፤ ረስቶናልም አሉ።
እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል ይመልሳል:-
እናት የራስዋን ልጅ መርሳት፥


www.ethiopianorthodox.org

የወለደችውንስ መጥላት ትችላለችን?
ምንአልባት እናት ልጅዋን ልትረሳ ትችል ይሆናል፤
እኔ ግን እናንተን ከቶ አልረሳችሁም።
ከዚህ በኋላ አንቺም በልብሽ እንዲህ ትዪአለሽ፥
‹‹እነዚህን ሁሉ ልጆች ማን ወለደልኝ?
ብዙ ልጆቼን አጥቼ ነበር፤
ሌሎችንም እወልዳለሁ የሚል ተስፋ አልነበረኝም፤
በመባረር ተሰድጀ ነበር።
ታዲያ እነዚህን ሁሉ ልጆች ያሳደገልኝ ማን ነው?
እኔ ብቻዬን ቀርቼ ነበር፤
እንግዲህ እነዚህ ሁሉ ልጆች ከወዴት መጡ?››»
ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- ለሕዝቦች ምልክት እሰጣለሁ፤ ለወገኖችም ዐርማ
እሰቅላለሁ፤ እነርሱም ወንዶች ልጆችሽን በክንዳቸው፥
ሴቶች ልጆችሽንም በትከሻቸው ተሸክመው ያመጣሉ።
እጄን በማንሣት ለሕዝቦች ሁሉ ምልክት እሰጣለሁ፤
ወንዶችና ሴቶች ልጆችሽን ታቅፈው ያመጡልሻል፤
ነገሥታት አሳዳጊ አባቶችሽ ይሆናሉ፤
እቴጌዎቻቸውም ሞግዚቶችሽ ይሆናሉ፤
ግንባራቸውንም ወደ ምድር ዝቅ አድርገው ይሰግዱልሻል።
የእግርሽንም ትቢያ ይልሳሉ፤
ከዚህም የተነሣ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቂያለሽ፤
የእኔን እርዳታ ለማግኘት የሚጠባበቁ ከቶ አያፍሩም» (ኢሳ:ም:49 ቍ:14–15፥ 21–23)።
«ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር የተቀላቀለ መጻተኛ ከሕዝቡ ጋር እንዳመልከው እግዚአብሔር
አይፈቅድልኝም ብሎ ማሰብ ለበትም።
ጃንደረባ የሆነ ሰው ልጅ ባለመውለዱ:- የእግዚአብሔር ሕዝብ ወገን ለመሆን አልበቃም
ብሎ አያስብ (ኢሳ:ም:56 ቍ:3)።
ክርስቶስ ስለ ዓለም ኃጢአት ሕማማትን መቀበሉን፥ መሞቱን ፥ መቀበሩንና ድል
መንሣቱን ነቢዩ በምዕራፍ ኀምሳ ሦስት ላይ ገለጸ አድርጓል።
ስለ መንፈስ ቅዱስ መውረድም እንዲህ ሲል ትንቢት ተናግሮአል:-
«ለተጠማው ምድር ውሃን እሰጣለሁ፥
በደረቀውም ምድር ምንጮች እንዲፈሱ አደርጋለሁ፤
መንፈሴን ለልጆችህ በመስጠት
እባርካቸዋለሁ» (ኢሳ:ም:44 ቍ:3)።
የወንጌልን በረከት ይሳተፉ ዘንድ የዓለምን ሕዝቦች እንዲህ ሲል ጋብዞአል:-
«የተጠማችሁ ሁሉ ወደ ውሃ ኑ፤ የምትገዙበት የሌላችሁ ኑ፤ ያለ ገንዘብና ያለ ዋጋ
ገዝታችሁ ብሉ፤ ያለ ገንዘብና ያለ ዋጋም የወይን ጠጅና ወተት ግዙ» (ም:55ቍ:1)።
<u>ትንቢተ ኤርምያስ:-</u> ነቢዩ ኤርምያስ ከሌዊ ነገድ የካህኑ የኪልቅያ ልጅ ነበር። አባቱ ኪልቅያ በኢዮስያስ ዘመን የሕጉን መጽሐፍ ያገኘው ነው ይባላል። በመጽሐፉ እንደተገለጠው የአባቱ መኖሪያ የብንያም ነገድ ክፍል የሆነው አናቶት የሚባል መንደር ነው። ያም መንደር ንጉሥ ሰሎሞን ካህኑን አብያታርን ከኢየሩሳሌም አባርሮ በዚያ እንዲኖር ያደረገበት ቦታ ነው (1ኛ:ነገ:ም:2 ቍ:26)። እግዚአብሔር ኤርምያስን ለአገልግሎት የለየው ገና በእናቱ ማሕፀን ሳለ ነው (ም:1 ቍ:5)። በተመሳሳይ ሁኔታ መጥምቁ ዮሐንስና፥ (ሉቃ:1፥ 15) ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም (ገላ:1፥15) ተመርጠውበታል።
ገና በልጅነቱ የተጠራው በየመንገዳቸው ወጥቶ ሕዝቦችን፥ ጕሣዎችን፥ የተለያዩ ነገሥታትን እንዲያስተምር ነው። ሥራውንም የጀመረው የይሁዳ ንጉሥ ኢዮስያስ በነገሠ በዐሥራ



www.ethiopianorthodox.org

ሦስተኛው ዓመት ነው። እርሱም ... ቀጥሎአል። በጥሪው መሠረት የማስተማሩን ትኩረት በወገኖቹ ዘንድ ብቻ ያስቀረው አልነበረም። ነገር ግን የተለያዩ አገሮችንም ያካትት ነበር። በዘመኑ የእስራኤል ጐረቤቶች በነበሩ አገሮች ሁሉ ላይ አተኵሮ ነበር። ለምሳሌ የባቢሎን ንጉሥ ግብጽን እንዲወርር (ም:46 እና 49)፥ የባቢሎን አወዳደቅ፥ ክብርዋ ሁሉ የሚጠፋ ስለመሆኑ (ም:51 እና 52) ተናግሮአል። ስለ አይሁድ ግን የተናገራቸው ስለ አራት ጉዳዮች ነው:- (1ኛ) እግዚአብሔርን መክዳታቸው፥ ባለመታዘዝ ዓመፀኞች መሆናቸው፥ ስሙንና ትእዛዙን በመናቃቸው፥ (2ኛ) ያጠፉትን ጥፋትና የበደሉትን በደል ለማረም በንስሓና በጸጸት እንዲመለሱ ጥሪ አድርጎ ላቸዋል። (3ኛ) ይህን ምክር ተቀብለው በንስሓ ባይመለሱ ግን ሀገራቸውና ቤተ መቅደሳቸው መፈራረስና መውደም እነርሱም ለሰባ ዓመቶች ወደ ባቢሎን መማረክ የሚደርስባቸው መሆኑን አስጠነቀቃቸው (ም:25 እና 29)። (4) ከዚያም በኋላ ወደ ግብጽ በመሸሽ ፈንታ ለባቢሎን ንጉሥ መገዛት ያለባቸው መሆኑንና ይህን ማድረግ ደግሞ የባቢሎኑ ንጉሥ ከተማዋንና ቤተ መቅደስዋን እንዳያፈርስ ርኅራኄ ያድርበታል ብሎ ምክር ሰጥቶአቸዋል።

በእነዚህም ጉዳዮች ላይ እየተመላለሰ ነቢዩ ኤርምያስ ማስተማሩን ቀጠለ። ሰዎችም ተመላልሶ ስለተነገራቸው የትንቢቱን ተፈጻሚነት ይጠባበቁ ነበር። የሚጠባበቁትም ከምርኮ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው አገራቸውንና ቤተ መቅደሳቸውን እንደገና የሚገነቡበትን ጊዜ ነበር። በዚህም ትንቢት አማካይነት መንፈስ ቅዱስ በሕዝቡ ኀሊና የክርስቶስን መምጣት ወደ ወንጌልና ወደ ክርስትና ሃይማኖት መጠራት፥ የክርስትናንም እምነት በመከተል የሚመጣውን በረከት፥ የአገልጋዮቹን ክብርና የክብሩም ዘለዓለማዊነትን ያመለክታል። ይህንንም በሚከተለው ጥቅስ ይመለከቷል:-

«በዚያን ጊዜ የዳዊት ዘር ቅርንጫፍ የሆነ አንድ ጻድቅ ንጉሥ እመርጣለሁ፤ ያም ንጉሥ በሀገሪቱ ላይ የሆነውን ነገር ያደርጋል፤ ትክክለኛ ፍርድንም ይሰጣል» (ኤር:ም:3ቍ:15)።

በኦሪት ሕግ ቦታ ሐዲስ ኪዳንና የወንጌል ሕግ የሚመጣ መሆኑን ሲያመለክት እንዲህ ብሎአል:-

«እነሆ፥ ከእስራኤል ሕዝብና ከይሁዳ ሕዝብ ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ጊዜ ይመጣል ይላል እግዚአብሔር» (ም:31ቍ:31)። እንዲሁም:-

«በዚያችም ምድር ቍጥራችሁ በሚበዛበት ጊዜ ስለ ኪዳኑ ታቦት የሚናገሩ ሰዎች አይኖሩም፤ ከዚያ በኋላ ስለ እርሱ አያስቡም፤ ሊያስታውሱትም አይችሉም፤ አስፈላጊነቱ ስለማይታያቸው እንደገና ሌላ ለመሥራት አይሞክሩም» (3፥ 16)።

መጽሐፉ ኀምሳ ሁለት ምዕራፎች አሉት። አቀማመጡም የድርጊቶችን ቅደም ተከተል ያልጠበቀ ነው። ጽሑፉ ታሪካዊ ድርጊቶችን፥ የባቢሎን ንጉሥ ኢየሩሳሌምን መውረሩ፥ አገሪቱን ማጥፋቱና፥ ሕዝቡን በምርኮ መውሰዱ፥ ነቢዩም አገልግሎቱን እየፈጸመ ሳለ የደረሰበትን አሳዛኝ ሁናቴ ይገልጣል። እነዚህንም አንዳንዶቹን ሁናቴዎች ገለጸ በሚያደርግበት ጊዜ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንደበት የሚናገር ይመስላል።

«ወደ ዕርድ እንደሚሄድ በግ ጠቦት ሆኜ ነበር እነርሱ:- ‹ስሙ ዳግመኛ እንዳይታወስ ዛፉን ከነፍሬው እናጥፋ ከሕያዋን ዓለም እናስወግደው› ብለው በእኔ ላይ ማድማቸውን አላወቅሁም ነበር» (ኤር:ም:11 ቍ:19)።

ከደረሱበት ብዙ ችግሮች የተነሣ ይህ ነቢይ የለቅሶ ነቢይ እስከ መባል ደርሶአል። ይኸውም ሕይወቱን በመላ እየተሠቃየና እያለቀሰ የኖረ በመሆኑ ነው። ኢየሩሳሌም በተወረረችና በተደመሰሰች ጊዜ ወደግብጽ ከተሰደዱት አይሁድ ጋር አብሮ ሄዶ ነበር። ወገኖቹን አይሁድን በጣም ይወቅሳቸው ስለ ነበረ በድንጋይ ወግረው እንደገደሉት ይነገራል።

<u>ሰቆቃወ ኤርምያስ:-</u> ስሙ በግልጽ እንደሚያመለክተው መጽሐፉ ስለ ኢየሩሳሌም መፍረስ የነቢዩ ኤርምያስ የሐዘን እንጕርጕሮ ነው። ምዕራፍ አንድና አምስት በኢየሩሳሌም መፍረስ ጊዜ ምን ያኽል አገሪቱ ባድማ መሆንዋን የሚገልጥ የሐዘን እንጕርጕሮ ነው። ምዕራፍ ሁለትና አራት ደግሞ ሁናቴውን ግልጽ በሆነ መንገድ ያቀርበዋል።

ነቢዩ ኤርምያስም ሰቆቃውን ማለት ሙሾውን ወይም የሐዘን እንጕርጕሮውን ያዘጋጀው ኢየሩሳሌም በጠላት እጅ አወዳደቅዋን፥ የአጥሮችዋና የቤተ መቅደስዋ መፍረስን፥ የንብረትዋና የሕዝብዋ መማረክን መሠረታዊ መነሻ በማድረግ ነው። ስለ ባድማዋ ኢየሩሳሌም የነቢዩ

የእንጉርጉሮ ግጥም ራስዋ ኢየሩሳሌም እንደምትናገር ተደርጎ የሁለቱ የሐዘን እንጉርጉሮዎች እየተፈራረቁ ቀርበዋል። በዚህም ዐይነት ስለ ባድማይቱ ኢየሩሳሌም፥ ስለ እግዚአብሔር ቍጣና ቅጣት፥ ለሕዝቡ አሁንም ቢሆን ተስፋ ያለ መሆኑን በማመን ስለ ይቅርታ ጸሎት በሙሾና በእንጉርጉሮ ቀርቦአል።

<u>ጥበበ ሰሎሞን</u>:- ይህን መጽሐፍ በተመለከተ የአባቶች አስተሳሰብ የተለያየ ነው። አንዳንዶቹ እንደሚሉት የአጻጻፉ ዘይቤ፥ የአስተሳሰቡ ርቱዕነት፥ የሥነ ጽሑፉ ረቂቅነት የሚያመለክተው መጽሐፉ የተጻፈው የግሪክን ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ በሚያውቅ ምሁር ነው። ሌሎች ደግሞ ይህን መጽሐፍ የጻፈው ሰሎሞን ለመሆኑ የሚከተለውን ጥቅስ በማስረጃነት ያቀርባሉ:-

«የሕዝብህ ንጉሥ እሆንና በወንዶችና በሴቶች ልጆችህ ላይ እፈርድ ዘንድ መርጠኸኛል! ከመጀመሪያው ባዘጋጀኸው፥ በተቀደሰው ድንኳን አምሳል፥ በተቀደሰው ተራራህ ላይ ቤተ መቅደስንና መኖሪያህ በሆነው ከተማ መሠዊያን እንድሠራ አዘኸኛል! የአንተን ሥራ የምታውቀው ጥበብ ከአንተ ጋር ነች! ዓለምንም በፈጠርክ ጊዜ ከአንተ ጋር ነበረች! አንተን ምን እንደሚያስደስትህ ታውቃለች። በትእዛዛትህም መሠረት ትክክለኛው ነገር የትኛው እንደሆነ ታውቃለች። ከእኔ ጐን ሆና እንድትሠራና አንተን ደስ የሚያሰኝህን ነገር እንዳውቅ ከተቀደሰው ሰማይና ከክብር ዙፋንህ ወደ እኔ ላካት። ከዚያ በኋላ ሥራዬ ተቀባይነት ይኖረዋል! ለሕዝብህም ትክክለኛ ፍርድን በመፍረድ ለአባቴ ዙፋን የተገባሁ እሆናለሁ» (ም:9 ቊ:7–10፥ 12)።

እንደሚታወቀው ይህ አባባል የዳዊት ልጅ ለነበረው ለሰሎሞን በስተቀር ለሌላ የሚስማማ አይደለም። ይህን መጽሐፍ የጻፈው ሰሎሞን ከሆነ ለምን ታዲያ ጸሐፊው ዕዝራ ቅዱሳት መጻሕፍትን ባሰባሰበ ጊዜ ይህንንም አብሮ ሳያሰባስበው ቀረ? በእውነት እንደዚህ ያለውን መጽሐፍ ዋጋ እንደሌለው ቈጥሮት ይሆን? ወይስ ደግሞ መጻሕፍቱን ባሰባሰበ ጊዜ ሳያገኛቸው ከቀሩት መጻሕፍት አንዱ እርሱ ይሆን? ምናልባት እንደተባለውም መጽሐፉን ሳያገኘው ቀርቶ ባለማሰባሰቡ ይሆናል እንጂ ንጉሥ ሰሎሞንስ ሦስት ሺህ ምሳሌ ዎችን መናገሩና መኃልዩም አንድ ሺህ አምስት መሆኑ ተገልጦአል (1ኛ:ነገ: ም:4 ቊ:32)። ጥበበ ሰሎሞን ዐሥራ ዘጠኝ ምዕራፎች ያሉት ሆኖ፥ ምሁራን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፍሉታል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ ዘጠኝ ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የጽድቅ ሥራ ጠቃሚነት ተዘርዝሮአል! የኃጢአተኞች ተግባር ተወግዞበታል! የጻድቃን ዕድል ፈንታ ምን እንደሚመስልና ኃጢአተ ኞችስ ምን ይጠብቃቸወል የሚሉት ሐሳቦች መግለጫ ተሰጥቶባቸዋል። እንዲ ሁም ስለ ጻድቃን ድልና ስለ መጨረሻው ፍርድ፥ የጻድቃን ዋጋቸው ምን እንደሆነ ተዘረዝሮአል። የጥበበ ምንነት ተዘርዝሮ ነገሥታት ጥበብን እንዲሹ ምክር ተሰጥቶአቸዋል። ሰሎሞንም፥ እግዚአብሔር ጥበብን ይሰጠው ዘንድ ይጸልያል።

ሁለተኛው ክፍል ከምዕራፍ ዐሥር እስከ ምዕራፍ ዐሥራ ዘጠኝ ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ከአዳም እስከ ሙሴ በነበረው ዘመን የጥበብ ሥራ፥ ጥበብ እስራኤላውያንን እየመራ ከግብጽ ማውጣቱ፥ በበረሓው ጉዞ እስራኤላውያንን የመራ መሆኑ፥ የክፉዎች ቅጣት፥ የእግዚአብሔር ኀያልነትና መሐሪነት፥ የከነዓናውያን ኃጢአት፥ የእግዚአብሔር ልዕልና፥ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጠው ትምህርት፥ ተፈጥሮን የማምለክ ሞኝነት፥ የጣዖት አምልኮ ክፋትና መሠረቱ፥ እውነተኛውን አምላክ የማምለክ ጥቅም፥ በግብጾች ላይ በሌሊት የመጣ ድንጋጤ፥ ለእስራኤላውያን የበራ ብርሃን፥ የግብጻውያን በኲር መሞት፥ በምድረ በዳ የማለቅ ፍርሀት፥ ቀይ ባሕር፥ እግዚአብሔር የራሱን ሕዝብ መምራቱና መጠበቁ፥ የግብጾች መቀጣት እነዚህ አጠቃላይ ርእሶች በመጽሐፉ በመጨረሻዎቹ ዐሥር ምዕራፎች በዝርዝር ተገልጠዋል።

## ሐዲስ ኪዳን

<u>ወደ ጢሞቴዎስ የተላከ የመጀመሪያ መልእክት</u>:- ጢሞቴዎስ ከልስጥራ የአንድ አረማዊ አባትና ያአንዲት አይሁዳዊት እናት ልጅ ነበር። እናቱ ኤውኒቄ አያቱ ሉዊስ ይባሉ ነበር። አያቱና እናቱም በጣም ሃይማኖተኞች ስለነበሩ ጢሞቴዎስን ሃይማኖተኛ አድርገው አሳድገውታል። እነርሱም መጽሐፍ ቅዱስን ጠንቅቆ እንዲማር በማድረግ ረድተውታል። በወጣትነቱም በቅዱስ ጳውሎስ የእምነት ትምህርት ተመርቶ ደቀ መዝሙሩና የሥራ ተባባሪው ሆነ። አይሁድ ከእርሱ እንዳይሸሹና በእነርሱ መካከል የሚያደርገው ድካም ስኬታማ እንዲሆን ተገረዘ። ጢሞቴዎስ ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ወደ ተለያዩ ቦታዎች አብሮት ከሄደ በኋላ ወደ ተለያዩ



ቦታዎች የቅዱስ ጳውሎስ መልእክትና በመሆን እርሱን [illegible] ጥቅሶች እንመልከት:-

«ጢሞቴዎስ በሚመጣበት ጊዜ በእናንተ ዘንድ ያለ ፍርሀት እንዲኖር እርዱት፥ እርሱም እንደ እኔው የጌታን ሥራ ይሠራል» (1ኛ:ቆሮ:16፥10)።

«እኔ ስለ እናንተ ሁኔታ በመስማት እንድጽናና ጢሞቴዎስን በፍጥነት ወደ እናንተ ለመላክ እንደሚያስችለኝ በጌታ ኢየሱስ ተስፋ አደርጋለሁ» (ፊል:ም:2 ቊ:19)።

«ወንድማችንንና የክርስቶስን ወንጌል በማብሠር ከእኛ ጋር ተባባሪ የሆነውን ጢሞቴዎስን ልከንላችኋል! እርሱንም የላክነው ያጽናናችሁና በእምነት እንድትበረቱ ይመክራችሁ ዘንድ ነው» (1ኛተሰ:ም:3 ቊ:2)።

በኤፌሶን ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ያሲይዝ ዘንድ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን የኤፌሶን ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ ሾመው። ከዚህ በኋላ በተለያየ ደረጃ ለሚገኙት ክርስቲያኖች በተለየም ለወንጌል አገልጋዮች፥ እንዲሁም ለራሱ ለጢሞቴዎስ መመሪያ የሆኑትን ሁለቱን መልእክቶቹን በተከታታይ ልኮለታል። ይህን የመጀመሪያውን መልእክት የጻፈው በ64 ዓ.ም ወደ መቄዶንያ በሚሄድበት ጊዜ ለመሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን እምነታቸውን ገልጠዋል።

የመጀመሪያው መልእክት ስድስት ምዕራፎች ያሉት ሆኖ በአራት ክፍሎች ይከፈላል:-

የመጀመሪያው ክፍል ምዕራፍ አንድና ምዕራፍ አራት ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ለጢሞቴዎስ ምክርና መመሪያዎች ተሰጥተውበታል።

ሁለተኛው ክፍል ምዕራፍ ሁለት ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ስለ ሁሉም ሰው በተለየም ስለ ነገሥታትና በከፍተኛ ሥልጣን ላይ ላሉ ሁሉ መጸለይ እንደሚገባ ተገልጦአል። የክርስቲያን ሴቶችም ጠጕርን በመሠራት፥ ወይም በወርቅ፥ ወይም በዕንቊ፥ ወይም ውድ በሆነ ልብስ ማጌጥ ሳይሆን በማፈርና በትሕትና ተገቢ የሆነ ልብስ እንዲለብሱ ታዘዋል።

ሦስተኛው ክፍል ስለ ኤጲስ ቆጶሳት፥ ስለ ቀሳውስትና ስለ ዲያቆናት ግዴታ ነው። አንዳንዶች እንደሚሉት ቀሳውስት ማለት ኤጲስ ቆጶሳት ማለት አይደለም። ሽማግሌዎች ሲል ግን ቀሳውስት ማለቱ ነው። የኤጲስ ቆጶሳት፥ የቀሳውስትና የዲያቆናትን ደረጃና ልዩነታቸውን መጽሐፈ ዲድስቅልያ ግልጥ አድርጎ ያቀረበው ከመሆኑም በላይ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቀርጤስ ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ የሾመውን ቲቶን ቀሳውስትንና ዲያቆናትን በየከተማው እንዲሾም አዞታል። (ዲድስቅያ አንቀጽ ሦስትንና ቲቶ ምዕራፍ አንድን ይመለከቷል።)

አራተኛው ክፍል ምዕራፍ አምስትና ስድስት ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ለክርስቲያን ወገኖች በተለየም ለባሪያዎችና ለመበለቶች ሕጎችና ትምህርቶች ተሰጥተውበታል፤ ከሐሰተኞች መምህራን ጥንቃቄ እንዲደረግ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአል፤ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለተወዳጅ ደቀ መዝሙሩ ምክር፥ ዐደራና መመሪያ አጥብቆ ሰጥቶበታል።

<u>ወደ ጢሞቴዎስ የተላከ ሁለተኛ መልእክት</u>:- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው ለሁለተኛ ጊዜ በኔሮን ትእዛዝ ታስሮ ሳለ ነው። እርሱም ከዚያ በኋላ እንደማይፈታና በሞት አፋፍ ላይ እንደነበረ በማመን ተስፋ ቈርጦ ነበር። መልእክቱ አራት ምዕራፎች አሉት።

በምዕራፍ አንድ ላይ ተወዳጅና ተመስጋኝ ደቀ መዝሙሩን መገናኘት ናፍቆት እንዳደረበት ይገልጣል። በመግለጫውም የእርሱ ማለት የጢሞቴዎስ የእምነት ጥንካሬ ከእናቱና ከአያቱ ተያይዞ የመጣ መሆኑን ገልጦለታል። በዚህ ምዕራፍ በፍቅራቸው ስላልጸኑ ስለ አንዳንድ ሰዎች ነቀፋ ሰንዝሮአል። ነገር ግን ኦኔሲፎርን አመስግኖ በመጨረሻው ቀን እግዚአብሔር ምሕረትን ይሰጠው ዘንድ ጸልዮለታል።

በሁለተኛው ምዕራፍ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደቀመዝሙሩን ጢሞቴ ዎስን በእምነት ይጸና ዘንድ፥ ሊደርስበት የሚችለውን ጭንቀትና መከራ ይችል ዘንድ፥ ታማኝ እረኛ ለበጎቹ ጥበቃ እንደሚያደርግና ፍላጎታቸውንም እንደሚ ያሙአላ እርሱም ግዴታውን እንዲወጣ ዐደራ ብሎታል።

በሦስተኛው ምዕራፍ በመጨረሻው ዘመን ሰዎች ከእውነት ርቀው የሐሰተኛ ጽድቅ ልብስን ለብሰው፥ ሃይማኖተኞች ሳይሆኑ የሃይማኖትን ካባ ለብሰው ስለሚመጡ ሌሎችን እንዲያስጠነቅቅና ራሱም በእውነተኛው ጽድቅ ይጸና ዘንድ ያስጠነቅቀዋል። ይህንንም ሲያደርግ ስደት

www.ethiopianorthodox.org

[illegible]
መጽሐፍ ቅዱስን የተማረ ሰው እንደሚጸና እምነቱን ይገልጥለታል:

በአራተኛው ምዕራፍ ሰዎች ከእውነት መንገድ ርቀው ጠማማውን መንገድ መከተላቸውን፥ ንጹሑን ቃል ከመስማት ይልቅ ተረት መስማት የሚመርጡበት ጊዜ የሚመጣ ስለሆነ ቢመችም ባይምችም ተግቶ እንዲያስ ተምር ዐደራ ብሎታል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መሥዋዕት ለመሆን መቃረ ቡንና፥ ከዚህ ዓለም ተለይቶ የሚሄድበት ጊዜ መድረሱን ለደቀ መዝሙሩ ለጢሞቴዎስ ገለጠለት። በደረሰበት መከራ ምክንያት መጨረሻው መንግሥተ ሰማይ እንደሆነ ያምናል። ከዚያም ይህን ዓለም ከመውደዳቸው የተነሣ አንዳንዶች እርሱን ትተውት እንደሄዱ በመግለጥ ወቀሳ አቅርቦአል።

<u>የሐዋርያው የያዕቆብ መልእክት</u>:- ይህን መልእክት ያዘጋጀው ከዐሥራ ሁለቱ ሐርያት አንዱ የእልፍዮስ ልጅ፥ ወይም የቀለዮጳ ልጅ ነው። እርሱም የድንግል ማርያም እኅት የሆነችው የማርያም ልጅ ነው። ወንድሞቹም ዮሴፍ፣ ስምዖንና ይሁዳ ይባሉ ነበር። እነርሱም የጌታችን የአክስቱ ልጆች መሆናቸው ነው። (ማቴ:ም:13 ቍ:55፥ ም:27 ቍ:56፥ ዮሐ: ም:19 ቍ:25)። ጽሑፉን ሲጀምር ሐዋርያ ብሎ ራሱን ከማስተዋወቅ ይልቅ የእግዚአብሔርና የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ብሎ ነው። ከሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክቶች መካከል ለምሳሌ ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች የተላከው መልእክት፥ ወደ ፊልሞና የተላከው መልእክት በመነሻቸው ላይ የቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያነት አልተገለ ጠባውም። ይህም ከትሕትናና ራስን ከመካድ የተነሣ ሳይሆን አይቀርም። ይህን መልእክት የጻፈው በጵጵስና መንበሩ በኢየሩሳሌም ሆኖ በ61 ዓ.ም. ነው።

ይህ መልእክት አምስት ምዕራፎች አሉት።

የመጀሪያው ምዕራፍ በመከራ ከታገሡ ለመንፈሳዊ ሕይወት ታላቅ ዋጋ የሚያስገኝ መሆኑ፥ የወንጌልን ሕግ መፈጸም እንጂ መስማት ብቻ ለድኅነት ጠቃሚነት የሌለው መሆኑ ተገልጾበታል።

ሁለተኛው ምዕራፍ ክርስቲያናዊ እምነት ያለ ተግባር፣ ወይም ያለ ሕግ ፈጻሚነት ዋጋ የሌለው መሆኑ ተገልጦበታል።

በሦስተኛው ምዕራፍ አንደበትን መቈጣጠር እንደሚገባ፣ ምድራዊ ሳይሆን ሰማያዊ ጥበብ ሊኖር እንደሚገባ ተገልጾአል።

በአራተኛው ምዕራፍ የክፋት ምክንያቶች፥ ክፉዎች ከክፉ ሥራቸው በንስሓ ባይመለሱና ለእግዚአብሔር ባይገዙ በመጨረሻ ጊዜ የተዘጋጀላቸውን ፍርድ የሚቀበሉ መሆናቸው ተገልጦአል።

በአምስተኛው ምዕራፍ ሥሥታሞች ለሆኑ ሀብታሞች ማስጠንቀቂያ ተሰጥ ቶአቸዋል። ታጋሾች የሆኑ ድኾች ደግሞ ተስፋ እንደሚኖራቸው ተነግሮአ ቸዋል። እነርሱም አንደበታቸውን ከክፉ ንግግር ጠብቀው፥ ሐሰትን ሳይሆን እውነትን ተከትለው፥ በጸሎትና ኃጢአትን በመናዘዝ በትዕግሥት እንዲኖሩ መክሮአቸዋል።

## <u>ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት</u>

የሳሙኤልና የነገሥት መጻሕፍት የተዘጋጁት በምርኮ ላይ ለነበሩ እስራኤላውያን የነበረ መሆኑ ሲገመት፥ የዜና መዋዕል መጽሐፍ ከምርኮ ለተመለሱ አይሁድ የእስራኤልን ሕዝብ ታሪክ ዐውቀው ማንነታቸውን እንዲገነዘቡ ነው። በዚህ በዜና መዋዕል መጽሐፍ ውስጥ የቀረበው አተራረክ በተቻለ መጠን ደስ የሚያሰኙትን የታሪክ ክፍሎች በመምረጥና ደስ የማያሰኙትን የታሪክ ክፍሎች በመተው ነበር።

መጽሐፉም የተጻፈው ከምርኮ መልስ በኋላ እንደመሆኑ ጸሐፊው ከምርኮ ለተመለሱት አይሁድ ምን ዐይነት አስደናቂ ታሪክ ያላቸው መሆናቸውን ለማሳየት ከመጀመሪያው የሰው ልጆች አባት ከአዳም ጀምሮ የእስራኤልን ልጆች የዘር ሐረግ መዘርዘር አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል።

የመጽሐፉም ዋና ዓላማ የእስራኤል ሕዝብ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙት ምን ያኽል ተከታታይነት ያለው መሆኑን ለማሳየት ነው።

እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ያለው ግንኙት አሁንም ያው ነውን? ቃል ኪዳኖቹስ አሁንም በሥራ ላይ ናቸውን? አሁን በዳዊት ሥርወ መንግሥት ሥር ሳይሆኑ በፋርስ መንግሥት



ሥር ባሉበት ጊዜ እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር የገባው ቃል ኪዳን ትርጉም አለውን? የዳዊት መንግሥት፥ ኢሩሳሌምና ቤተ መቅደስዋ ከፈረሱ በኋላና ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ከቀድሞው የእስራኤል መንግሥት ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት ምን ዐይነት ነው? የዜና መዋዕሉ አዘጋጅ ለእነዚህ ጥያቄዎች ሁሉ የሚሰጠው መልስ አለ።

የታሪኩ ሂደት ካለፈው ጋር ቀጣይነት ወይም ተከታታይነት ይኖረዋል ወይ? ለሚለው ጥያቄ እግዚአብሔር የፋርስን ነገሥታት አነሣሥቶ ቤተ መቅደሱ እንዲሠራ ማድረጋቸው ትልቁ ምልክት ነው (2ኛ: ዜ:መ:ም:36 ቍ:22–23)። በንጉሥ ዳዊት ተዘጋጅቶ የነበረው የአምልኮ ሥርዓት ቤተ መቅደሱ እንደገና ከተሠራ በኋላ በሥራ ላይ መዋሉ የታሪኩን ተከታታይነት የሚያመለክት ነው። የሌዊ ልጆች ለቤተ መቅደሱ አገልግሎት መመረጣቸው፣ ዳዊት በእስራኤላውያን ላይ እንዲነግሥ መደረጉ፥ የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ንጉሥ ቤተ መቅደሱን ማሠራቱ፣ ኢየሩሳሌም በእግዚአብሔር የተመረጠች ከተማ መሆንዋና ቤተ መቅደሱም እግዚአብሔር የሚመለክበት ቦታ ሆኖ መመረጡ ተከታታይነት ያለው የታሪክ ሂደት ሲሆን እነዚህ ሁኔቴዎች እንዳሉ መቀጠ ላቸው ከምርኮ መልስም ቢሆን አዲስ መጀመር ሳይሆን በዚያው ሁኔቴ ስለቀ ጠሉ የታሪኩ ተከታታይነትና ከእግዚአብሔርም ጋር ያለው ግንኙነት ያልተለወጠ ነው።

በተጨማሪም፥ እስራኤላውያን ሁልጊዜ ሕግና ነቢያት ስለ ነበሩአቸው በዳዊት ትውልድ መሪነት የቃል ኪዳኑ ቀጣይነት አስተማማኝ ነበር። ይሁን እንጂ ነገሥታቱም ሆኑ ቤተ መቅደሱ ለእስራኤል ሕዝብ ደኅንነትና በረከት አስተማማኞች አልነበሩም። ሁሉም ነገር የእስራኤል ነገሥታት ለሕጉ ታማኞች በመሆናቸው ግዴታ ላይ የተመሠረተ ነበር።

የዜና መዋዕሉ መጽሐፍ አዘጋጅ ለሕግና ለነቢያት ታዛዥ መሆን ፈጣን ውጤትን እንደሚያመጣ ገልጦአል። በመጽሐፉ ተመላልሶ እንደተገለጠው ኃጢአት በሽታንና በጦርነት ድል የመሆንን ችግር ያመጣል። በሌላ በኩል ደግሞ ንስሓ መግባት፣ ታዛዥነትና በእግዚአብሔር መታመን ሰላምን፥ ድልንና ብልጽግናን ያመጣል።

እንዲሁም እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር የገባው ቃል ኪዳን ተመላልሶ ተገልጦአል (1ኛ:ዜ:መ:ም:17: 2ኛ:ዜ:መ:ም:13 ቍ:5፥ ም:21ቍ:7፥ ም:23ቍ:3)።

የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ሌላው ያተኰረበት ጉዳይ ስለ መላው የእስራኤል ሕዝብ ነበር። በየጊዜው ለአምልኮ ወደ ኢየሩሳሌም የሚመጡትን ሰዎች ደጋግ ሰዎች ይላቸዋል።

በታሪኩ ትረካ ጊዜ የንጉሥ ሳኦልን ጠቅላላ ታሪክ ከማቅረብ ይልቅ የዳዊትን በእርሱ ቦታ መተካት ብቻ ነካ በማድረግ ዐልፎአል። የዳዊትንም ታሪክ በሚተርክበት ጊዜ ዳዊት በእግዚአብሔር የተመረጠና ምንም ጥፋት የሌለበት ቅን ሰው መሆኑን ለማሳየት በደሎቹና ጥፋቶቹ፣ የተወቀሰባቸውና የተቀጣባቸው ስሕተቶች ሁሉ ሳይጠቀሱ ታልፈዋል። ይህም የሆነበት ምክንያት የእስራኤልን ሕዝብና የንጉሣቸውን የዳዊትን ታሪክ ምንም እንከን የሌለበት አድርጎ ለማቅረብ ስለተፈለገ ነው። ከይሁዳ ነገሥታት ጋር ባላቸው ግንኙት ካልሆነ በቀር የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ አለመቅረቡ አብዛኞቹ የእስራኤል ነገሥታት ከእግዚአብሔር የራቁና ታሪካቸው የማያምር በመሆኑ ነው። ብዙዎቹ የይሁዳ ነገሥታት ግን የእግዚአብሔርን መንገድ የተከተሉ ነበሩ። ከዚያም በላይ በዚያን ጊዜ ከስደት የተመለሱት አብዛኞቹ የይሁዳና የብንያም ነገዶች ነበሩ። በዳዊትና በልጅ ልጆቹ መንግሥት ማለት በይሁዳ መንግሥት ሥር የነበሩት ነገዶች እንደ እውነተኞች እስራኤላውያን ሲቈጠሩ በሰሜን በኩል የነበሩት ማለት በእስራኤል መንግሥት ሥር የነበሩት ነገዶችም ከእውነተኞቹ እስራኤላውያን ጋር እንዲዳበሉ በየጊዜው ጥረት ይደረግ ነበር። ይሁን እንጂ በዚያ በኩል የሚገኘው መልስ የሚያረካ አልነበረም። የእውነተኛ እስራኤላዊነት ስኬት ወይም አለመሳካት የሚለካው ለእግዚአብሔር ታማኝ በመሆንና ለሕጉም ታዛዥ በመሆን ነበር። ጦርነቶች ታማኝ ካለመሆን የሚመጡ የእግዚአብሔር ፍርዶች ናቸው። ድል የሚገኘው በእምነት ነው። ድል አድራ ጊውም እግዚአብሔር ነው። ድሉም የሚመጣው ታማኞች በሚያቀርቡት ልመና መልስ ነው። ባለመታዘዝና ታማኝ ባለመሆን፥ የነቢያትንም ማስጠን ቀቂያ ችላ በማለት የሚመጣው የፍርድ ውጤት በባቢሎናውያን ድል ሆኖ መማረክና አገሪቱን ባድማ ማድረግን የመሰለ መከራ ነው።

ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢት መጽሐፉ የተደራጀ ነገረ መለኮትን ያቀርባል። በተለየም ስለ ክርስቶስ ያቀረባቸው ትንቢቶች በጣም ግልጽ ከመሆናቸው የተነሣ ወንጌላዊው ነቢይ የመባል ስም ተሰጥቶታል። ከግልጽ ትንቢቶቹም መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

www.ethiopianorthodox.org

«ስለዚህ እግዚአብሔር ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ብላ ተጠራ ዋለች» (ም:7 ቊ:14)።

«እነሆ ሕፃን ተወልዶልናል፥
ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል፥
እርሱም መሪ ይሆናል፤
ስሙም ‹ድንቅ፥ መካር፥ ኃያል አምላክ፥
የዘለዓለም አባት፥ የሰላም አለቃ ይባላል።
ለንጉሣዊ ሥልጣኑ ወሰን የለውም፤
መንግሥቱም ዘለዓለማዊ ሰላም የሰፈነበት ይሆናል፤
ከአሁን ጀምሮ እስከ ዘለዓለም፥
እውነትና ፍትሕ የሰፈነበት መንግሥት
በዳዊት ዙፋን ላይ ተመሥርቶ እንዲጸና ያደርገዋል፤
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ቅናት ይህን ለማድረግ ወስኖአል» (ኢሳ:ም:9 ቊ:6–7)።

«ፈሪ ልብ ላላቸው እንዲህ በሉአቸው:-
በርቱ፤ አትፍሩ፤ አምላካችሁ እግዚአብሔር ጠላቶቻችሁን
ለመበቀልና በመለኮታዊ ፍትሕ ሊያድናችሁ ይመጣል።
በዚያን ጊዜ ዕውሮች ያያሉ፤
ደንቆሮዎችም ይሰማሉ፤
አንካሳዎች እንደ ሚዳቋ ይዘላሉ፤
መናገር የማይችሉ ድዳዎች ይዘምራሉ፤
በበረሓ ውስጥ የጅረት ውሃ ይፈስሳል።» (ኢሳ:ም:35 ቊ:4–6)።

ይህም ነቢይ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕማማትና ሞት የተናገረው አስደናቂ ትንቢት ምዕራፍ ኀምሳ ሦስትን አጠቃልሎ የያዘ ነው።

ነቢዩ ኢሳይያስ እግዚአብሔርን የእስራኤል ቅዱስ ይለዋል። ቅዱስም ማለት የተለየ ማለት እንደመሆኑ በልዕልናው ከሰው ይለያል ለማለት ነው።

ስለ ክርስቶስ ከሚናገራቸው ትንቢቶች መካከል በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ ምሳሌነት የተነገረው ይገኝበታል። የእግዚአብሔር ምርጥ ግን ከዳዊት ዘር የሚ መጣ መሆኑን ይገልጣል። (ም:7 ቊ:10–17) እርሱም የሰላምና የጽድቅ መንግሥት ያቋቊማል። (ም:11 ቊ:1–9)

ይመጣል ተብሎ በኢሳይያስ የተነገረለት ንጉሥ ቂሮስ ወይም ዘሩባቤል ሳይሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ ግልጥ ነው። ሕማማት ይደርሱበታል ተብሎ በብሉይ ኪዳን የተነገረው በብሉይ ኪዳን ሰዎች ይጠበቅ የነበረው ዐይነት ምድራዊ ንጉሥ ሳይሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን እኛ የሐዲስ ኪዳን ሰዎች ትንቢቱ ከተፈጸመ በኋላ ልንረዳው ችለናል። ስለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የክርስቶስን አመጣጥ ተሰውሮ የነበረ ምሥጢር ሲል የገለጠው (1ኛ:ቆሮ:2፥ 7)።

ኢሳይያስ የተናገራቸው ትንቢቶች ብዙዎቹ ጊዜያቸው ደርሶ ተፈጽ መዋል። ስለ እስራኤልና ስለ ሌሎችም ሕዝቦች የተናገራቸው ትንቢቶች ተፈጽመዋል።

ሌላው የኢሳይያስ እምህርት ደግሞ እግዚአብሔር የሰማይና የምድር፥ እንዲሁም የፍጥረቱ ሁሉ ጌታ ነው የሚለው ነው። በተቃራኒው ሰዎች አማልክት ብለው የሚሰግዱላቸው እግዚአብ ሔር የፈጠራቸው ነገሮች ናቸው። እንዲያውም አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች የሚሰግዱት ራሳቸው ቀርጸው ለሠሩአቸው ምስሎች ነው። ይህ አባባል የሚያመለክተው እስራኤላውያን ከመጀመ ሪያው ጀምረው የተቀበሉት አምልኮ የአንድ አምላክ አምልኮ መሆኑን ነው። ይህም አምላክ ሁሉንም የፈጠረና በራሱ ዕቅድ መሠረት የሚመራ ነው። እንዲሁም ይኸው አንዱ አምላክ በመለኮታዊ ሥልጣኑ በጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ እየገባ የታሪክን አቅጣጫ መርቶአል። በተለየም ሰዎችን ከጠላቶቻቸው በመታደግ ሕዝቦችን አድኖአል።

የአይሁድን ሕዝብ ከባቢሎን ምርኮ ወደ ሀገሩ እንዲመለስ ለማድረግ የፋርሱ ንጉሥ ቂሮስ የእግዚአብሔር መሣሪያ ነበር። ክርስቶስ ግን ከኃጢአት ባርነት ነጻ ያወጣው የሰውን ዘር ሁሉ ነው (ም:52 ቊ:7–10፥ ም:53 ቊ:12)።



ነቢዩ ኤርምያስ ከመጀመሪያ ጀምሮ ለነቢይነት በእግዚአብሔር የተጠራ መሆኑን ያውቅ ነበር።

«በሆድ ሳልሠራህ ዐውቄሃለሁ፤ ከማሕፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ፥ ለሕዝቦች ሁሉ ነቢይ አድርጌሃለሁ» ተብሎአል (ም:1ቊ:5)።

በዚህም መሠረት እንደሚፈጸሙ እርግጠኛ የሆነባቸውን የእግዚአብሔርን ውሳኔዎች ማወጅ ጀመረ።

«እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ:- ‹ሄደህ የሸክላ ሠሪውን ገንቦ ግዛ፤ ከሕዝቡና ከካህናቱ መካከል ታላላቆቹን መርጠህ ከአንተ ጋር አብረው እንዲሄዱ አድርግ፤ በሸክላ ሰባሪ በር በኩል አድርገህ ወደ ሂኖም ሸለቆ ሂድ፤ በእዚያም እኔ የምነግርህን እንዲህ ብለህ ዐውጅ:- «የይሁዳ ነገሥታትና የኢየሩ ሳሌም ሕዝብ ሁሉ እኔ የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የምነግራችሁን አድምጡ፤ እነሆ፥ ያን ነገር በጆሮው ለሚሰማው ሰው ሁሉ የሚዘገንን መቅሠፍት አመጣለሁ» (ኤር:ም:19 ቊ:1–3)።

«ስለ ሰላም የተናገረ ነቢይ፥ የነቢዩ ቃል በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር በእውነት የላከው ነቢይ እንደሆነ ይታወቃል» (ም:28 ቊ:9)።

የነቢዩ ኤርምያስ ብዙዎቹ ትንቢቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ ተፈጽመዋል፤ ሌሎችም ቈየት ብለው ተፈጽመዋል (ም:16 ቊ:15፥ ም:ም20 ቊ:4፥ ም:25 ቊ:11–14፥ ም:27 ቊ:19–22)፤ ም:29 ቊ:10፥ ም:34 ቊ:4–5፥ ም:43 ቊ:10–11፥ ም44 ቊ:30፥ ም:46 ቊ:13–14)። እነዚህ ጥቅሶች በአጭር ጊዜ ስለተፈጸሙት ትንቢቶች ሲሆኑ ረዘም ያለ ጊዜ ያስፈለጋቸው ትንቢቶች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው:- (ም:23 ቊ:5–6፡ ም:30 ቊ:8–9፡ ም:31 ቊ:31–34፥ ም:33 ቊ:15–16)።

የነቢዩ ኤርምያስ ዋና ሐሳብ በእግዚአብሔርና በሰው ልጆች መካከል ስላለው ግንኙነት ነው። መጽሐፉ በተለይ ያተኰረው በእግዚአብሔርና በራሱ ሕዝብ፥ እንዲሁም በእግዚአብ ሔርና በራሱ በኤርምያስ መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡን በዘለዓለማዊ ፍቅር ወዶአቸዋል። በዚህም ፍቅሩ መሠረት ከጠላቶቻቸው ታድጓቸዋል፤ ወይም የታሪክን አቅጣጫ ለውጦአል። ይሁዳ ግን ቃል ኪዳኑን በመጣስ በእግዚአብሔር ላይ ዐምፆአል። እግዚአብሔርም ይሁዳን ለመቅጣት በጠላቶቻቸው እንዲሸነፉና እንዲያጠፉአቸው አድርጓል (ም:27 ቊ:6–9)።

ምንም እንኳ ኢየሩሳሌም በጠላት እጅ ብትወድቅና ሕዝብዋም በምርኮ ቢወሰድ ሐዘንተኛው ኤርምያስ ግን አሁንም ተስፋ ነበረው። ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው ከአጐቱ ልጅ ከአናምኤል በአናቶት የሚገኘውን መሬት መግዛቱ ነው። ይህም የሚያመለክተው ነቢዩ ኤርምያስ የይሁዳን ሕዝብ እግዚአብሔር ከምርኮ እንደሚመልሰው ያምን እንደነበረ ነው (ም:32)፤ ይህንኑም እምነቱን በም:31 ቊ: 31–34 ገልጦታል።

በሕዝቡ ኃጢአት ምክንያት ስለሚመጣው የእግዚአብሔር ቍጣ በግልጽ ይናገር ስለነበረ ከመጀመሪያው ጀምሮ ተቃውሞ በዝቶበታል። ወገኖቹ ተማርከው በሚኖሩበት አገር ታዛዦች ሆነው እንዲኖሩ እንጂ ምንም ተቃውሞ እንዳያደርጉ የሰጠው ምክር በብዙዎቹ ዘንድ አገሩን የከዳ አስኙቶታል። ይሁን እንጂ ከዐመፅ እንዲገቱ መምከሩ ሕዝቡ ሲያልቅ ዝም ብሎ ላለማየት ስለሆነ ይህ ለወገኖቹ ያለው ፍቅር አገር ወዳድ አስኙቶታል። ኤርምያስ አዘውትሮ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይገልጥላቸው ነበር።

በረጅሙ የምናሴ ዘመነ መንግሥት የይሁዳ ሕዝብ በተከተለው የኃጢአት መንገድ ምክንያት በሕዝቡ ላይ እንደሚደርስበት የተወሰነውን ጥፋት መግለጥ የኤርምያስ ግዴታ ነበር።

በሕዝቡ ላይ የሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድ ግን የመጨረሻው ታሪክ አልነበረም። ምሕረትና ለቃል ኪዳኑ ታማኝነት አሸናፊዎች ናቸው። ከፍርድ ባሻገር ከስደት መመለስና ተሐድሶ ይመጣል። እስራኤላውያን ከስደት ይመለሳሉ፤ ቀደም ብለው እነርሱን ያጕሳቈሉአቸው ሕዝቦች ይደመሰሳሉ፤ እግዚአብሔርም ከእነርሱ ጋር አዲስ ቃል ኪዳን ይገባል። ይህንንም ሕግ በልባቸው ውስጥ ይጽፈዋል። እነርሱንም ለአገልግሎቱ የተለዩ ያደርጋቸዋል (ም:31 ቊ:31–34)።

www.ethiopianorthodox.org

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ለቅሶና ሐዘን (ሰቆቃው) የተጻፈው በኤርምያስ አማካይነት ብቻ አይደለም። ይሁን እንጂ ሙሉውን መጽሐፍ ስለ ሐዘንና ለቅሶ የጻፈ ነቢዩ ኤርምያስ ነው። ቀጥተኞች አይሁድ ማለት የአይ ሁድን ሃይማኖት ነጥብ በነጥብ ሚከተሉ ይህን መጽሐፈ ሰቆቃው በአቢብ (ነሐሴ) ዘጠኝ ቀን ድምፃቸውን እያሰሙ ያነቡታል። ይህንንም የሚያደርጉት ከክርስቶስ ልደት በፊት የሰሎሞን ቤተ መቅደስ በ586 ዓመት የፈረሰበትንና ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ70 ዓ.ም. ደግሞ የሄሮድስ ቤተ መቅደስ የፈረሰበትን ቀን ለማስታወስ ነው።

ስለጠቅላላ ውድመትና ስለ ነገሥታት መገደል በም.2 ቊ:6 እና 9፥ በም:4ቊ:20 ይመለከቷል።

ስለ ልውላን በም:1 ቊ:6፥ በም:2 ቊ:2 እና 9፥ በም:4 ቊ:7–9፥ በም:5ቊ:12 ይመለከቷል።

ስለ ሽማግሌዎች በም:1 ቊ:19፥ በም:2 ቊ10፥ በም:4 ቊ: 16፥ በም:5 ቊ:12 ይመለከቷል።

ስለ ካህናት በም:1 ቊ:4 እና 19፥ ም:2 ቊ:6 እና 20፥ በም: 4ቊ: 16 ይመለከቷል።

ስለ ነቢያት በም: 2 ቊ: 9 እና 20 ይመለከቷል።

ስለ ሌሎች ሰዎች:- በም:2 ቊ:10–12፥በም:3 ቊ:48፥ በም:4 ቊ:6 ይመለከቷል።

እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ላመጣው ቅጣት ባቢሎናውያን ሰብአዊ መሣሪያዎች ብቻ እንደነበሩ የመጽሐፉ ጸሐፊ በግልጥ ያውቃል። ከተማውንና ቤተ መቅደሱን ያፈረሰ ራሱ እግዚአብሔር ነው (ም:1 ቊ:12–15፥ ም:2 ቊ:1–8፥ 17፥ 22፥ ም:4 ቊ:11)። የእግዚአብ ሔርም ቅጣት ያለ ምክንያት የመጣ አይደለም። ደፋሮች መሆን፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የማፍረስ ኃጢአት፥ ቃል ኪዳንን የማፍረስ ዐመፀኛነት የሕዝቡ የወዮታ ምክንያቶች ናቸው (ም:1 ቊ:5፥ 8–9፥ ም:4 ቊ:13፥ ም:5 ቊ:7፥16)።

በም:1ቊ:1–2 በለቅሶ የጀመረው መጽሐፍ በም:5 ቊ:21–22 በንስሓ ይፈጽማል።

የመጽሐፈ ጥበብ ዋና ዓላማ በጊዜው ከነበረው የፍልስፍና እንቅስቃሴ የአይሁድ ሃይማኖት ምን ያኽል ከፍተኛ መሆኑን ለማመልከትና አይሁድንም በሃይማኖት ለማበረታታት ነው። እንዲሁም የአይሁድ ጠላቶች የነበሩትን ወገኖች ዝም የሚያሰኝ ነው። በዚህም ሆነ በዚያ የአይሁድን ሃይማኖት በጥበባዊ መንገድ ያቀርባል። እንዲሁም ተዳክሞ የነበረውን የአይሁድን ስሜት ያነቃ ቃል። ግብረ ገብነት ላልነበረው ለአረማውያኑም ዓለም ተቃውሞ መልስ ይሰጣል።

ወደ ጢሞቴዎስ የተላኩት ሁለቱ መልእክቶችና ወደ ቲቶ የተላከው አንድ መልእክት የቤተ ክርስቲያን መሪ ማለት ኤጲስ ቆጶስ፥ እንዲሁም አስተ ማሪዎች የሆኑት ካህናትና ረዳቶች የሆኑት ዲያቆናት ምን መሆን እንዳለባቸው፥ ኀላፊነታቸውንና ግዴታቸውን ዘርዝረው ስለሚያስረዱ የእረኞች ወይም የጠባቂዎች፥ ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መመሪያ መልእክቶች ይባላሉ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የመጀመሪያውን መልእክት የጻፈባቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሉት።

1ኛ/ ጢሞቴዎስን ቀደም ብሎ አዞት የነበረውን ትእዛዝ ለማጠናከር:-

«እዚያ ያሉ አንዳንድ ሰዎች ሐሰተኛ ትምህርት እንዳያስተምሩ ወደ መቄ ዶንያ ስሄድ ሳለሁ ዐደራ እንዳልኩህ በኤፌሶን ተቀመጥ» (ም:1 ቊ:3–4)።

«ልጄ ጢሞቴዎስ ሆይ፥ ከዚህ ቀደም ስለ አንተ በትንቢት በተነገረው መሠረት ይህን ትእዛዝ በዐደራ እሰጥሃለሁ» (ቊ:18)።

2ኛ/ ሐሰተኛ ትምህርትን ለመቃወም:- (ም:1 ቊ:3–7፥ ም:4ቊ:1–8፥ ም:6 ቊ:3–5፥ 20–21)

3ኛ/ በማደግ ላይ በነበረችው የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ላይ ክትትል ለማድረግ:- (ም:2 ቊ:1–15)

4ኛ/ ብቃት ያላቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን መምረጥ:- (ም:3 ቊ:1–13፥ ም:5 ቊ:17–25)።



የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ዋነኞቹ ችግሮች የክሓዲዎች መነሣት ነበር። በዚያን ጊዜ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን የነበሩት ክሓዲያዎች ግኖስቲኮች፥ የአይሁድን ሃይማኖት በትክክል ሳያውቁ የሚናገሩ ሰዎች፥ እንዲሁም የሐሰት መንፈሳዊነት ነበሩ (ም:1ቊ:3:7፥ ም:4ቊ:1–5)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሁለተኛ ጊዜ የጻፈባቸው ሦስት ዋና ዋና ምክንያ ቶች አሉ:-

1ኛ/ በእስያ ያሉት ሁሉ በተለየም በስም የጠራቸው ፊጌሉስና ሄርሞጌኔስ የከዱት በመሆኑና ዴማስም ይህን ዓለም ወድዶ የተለየው በመሆኑ ብቸኝነት ስለተሰማው ነው (2ኛ: ጢሞ: ም:1 ቊ:15፥ ም:4 ቊ:10) ። ስለዚህም ጢሞቴዎስ በቶሎ እንዲመጣለት ጠየቀው።

2ኛ/ በኔሮ ማሳደድ ምክንያት ስለቤተ ክርስቲያን በጣም አስቦ ስለነበረ ጢሞቴዎስ ወንጌልን እንዲጠብቅ፥ በእርሱም እንዲጸና፥ ማስተማሩን እንዲ ቀጥል፥ አስፈላጊም ከሆነ ስለ ወንጌል መከራን እንዲቀበል መከረው (ም:1 ቊ:14:14፥ ም:3 ቊ:14፥ ም:4 ቊ:2፥ ም:1 ቊ:8፥ ም:2 ቊ:3)።

3ኛ/ በጢሞቴዎስም አማካይነት ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ለመጻፍ ፈለገ።

በያዕቆብ መልእክት ውስጥ ብዙ የትምህርት አርእስት ተደጋግመው ስለመጡ በዕቅድ እንጂ እንዲሁ ያለ ዕቅድ ከዚህም ከዚያም የተሰባሰቡ ምክሮች ወይም ተራ ስብከቶች አለመሆናቸውን ያመለክታል። በመጀመሪያው ምዕራፍ ውስጥ የተነሡት የፈተና፥ የጥበብ፥ የሀብት፥ የለጋሥነት፥ ትምህርቶች በቀጣዮቹም ምዕራፎች ተዘርዝረዋል እንጂ ዝም ተብለው የታለፉ አይደሉም። የተለ ያዩትን ምዕራፎች የሚያስተባብረው የተግባርን አስፈላጊነት ለማጠናከር ነው። እነዚህም ተግባሮች አንድ ግለሰብ ለኅብረተሰቡ ያለበት ግዴታ፥ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር፥ ሕግ በመፈጸም እንደሚገለጥ ተመልክቶአል (ም:4 ቊ:11)። ክርስቲያኖች የሚጠብቁት ሕግ የፍቅርን ትእዛዝ መፈጸም ነው። ጐረቤትህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ የሚለው ትእዛዝ ነው (ም:2 ቊ:8) ሕግ ፈጻሚነትም ፍጹም ሕግ የተባለው ነው (ም:1ቊ:25)። ወይም መንግሥታዊ ሕግ የተባለው ነው (ም:2 ቊ:8)። ክርስቲያናዊም ፍቅር አድልዎ የሌለበት ፍቅር ነው። (ም:2 ቊ:1–13) ለድኻ መራራት (2፥14–26) ፥ በሰው ላይ አለመፍረድ፥ ወይም የሰውን ስም አለማጥፋት ከክርስቲያናዊ ተግባሮች መካከል መሆናቸውን መረዳት ይገባል (ም:4 ቊ:11–12)። ንጹሕ ሃይማኖት ለችግረኞች ማሰብን ያካትታል (ም:1 ቊ:27)። ክርስቲያናዊም ሥነ ምባር በግል ፍላጎት ላይ የተመሠረተ አይደለም (4፥13–5:6)፥ ወይም ዓለማዊነት አይደለም (4፥ 1–6)፥ ነገር ግን ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ይገለጣል ( 4፥ 7–10፥ ም5፥7–11)።

## ጥያቄዎች

1. የዜና መዋዕልን መጽሐፍ ያዘጋጀ ማነው?
2. ያዘጋጀውስ መቼ ነው?
3. የዜና መዋዕልን መጽሐፍ ለሁለት የከፈሉት እነማን ናቸው?
4. የዜና መዋዕል መጽሐፍ ተመሳሳይነት ያለው ከየትኞቹ መጻሕፍት ጋር ነው?
5. የተለያዩትስ እንዴት ነው?
6. የዜና መዋዕል መጽሐፍ ሳያቀርብ የቀረው ምን ዐይነቶቹን ጉዳዮች ነው?
7. በዜና መዋዕል መጽሐፍ የቀረቡት አንዳንድ ስሞች በኦሪት ዘፍጥረትና በኦሪት ዘኊልቊ ከቀረቡት ስሞች ለምን ተለዩ?
8. አንደኛ ዜና መዋዕል ስንት ምዕራፎች አሉት?
9. ሁለተኛ ዜና መዋዕል ስንት ምዕራፎች አሉት?
10. የእስራኤል መንግሥት ለሁለት የተከፈለው መቼ ነው?
11. መንግሥቱ ለሁለት በተከፈለ ጊዜ የይሁዳ ንጉሥ ማን ነበር? የእስራኤልስ ንጉሥ ማን ሆነ?
12. በይሁዳ መንግሥት ሥር ስንት ነገዶች ቀሩ?
13. [illegible] ስንት ነገዶች ነበሩ?
14. [illegible]

www.ethiopianorthodox.org

15. በኢዮርብዓም ዘመን እግዚአብሔር ለይሁዳ መንግሥት በእስራኤል መንግሥት ላይ ድልን ያጐናጸፈው በምን ዐይነት ነው።
16. የይሁዳ ንጉሥ አሳ እግዚአብሔርን ያስቈጣው ምን በማድረጉ ነው?
17. ኢዮሣፍጥ ሃይማኖትንና ሕግን ያጠናከረው እንዴት ነው?
18. ኢዮሣፍጥ የፈጸመው ከባድ ጥፋት ምንድነው?
19. ዐታልያ ማን ነች?
20. ኢዮሣፍጥ በራሞት ገለዓድ ምን አደረገ?
21. በኢዮሣፍጥ ዘመን ይሁዳን ለመውጋት የተስማሙ ሦስት አገሮች ማን ማን ናቸው?
22. የእነርሱስ ውጤት ምን ሆነ?
23. ኢዮሣፍጥ ከእስራኤል ንጉሥ ከአካዝያስ ጋር ምን አደረገ?
24. የድርጊቱስ ውጤት ምን ሆነ?
25. የዶዳዋ ልጅ ኤልዓዛር ኢዮሣፍጥን ምን አለው?
26. የኢዮራም አካሄድ የተበላሸበት ዋናው ምክንያት ምንድነው?
27. ለኢዮራም የወቀሳ ደብዳቤ የላከለት ማን ነው?
28. የዮዳሄን ልጅ ዘካርያስን በድንጋይ ተወግሮ እንዲሞት ያስደረገ ማነው? ምክንያቱስ ምንድነው?
29. ንጉሥ ዖዝያ ለምጽ የወጣበት በምን ምክንያት ነው?
30. እግዚአብሔርን ቅር አሰኝቶ የነበረው ንጉሥ ምናሴ እንዴት ንስሐ ገባ? እግዚአብሔር ንስሓውን ተቀበለውን?
31.በኢዮሣፍጥና በአክዓብ ፊት ከአራት መቶዎቹ ነቢያት የተለየ ትንቢት የተናገረው ነቢይ ማን ይባል ነበር?
32. የሞአብ ንጉሥ ሜሻዕ በእስራኤል ላይ ያመፀው እንዴት ነው?
33. እርሱና የጦር ጓደኞቹ እንዴት ተሸነፉ?
34. የሞአቡ ንጉሥ ምን ሲያደርግ ስላዩት ነው የጦር ጓዶቹ ዘማቾአቸው ወደየአገራቸው የተመለሱት?
35. ባለ ዕዳ የነበረ የአንድ ሟች ነቢይ ሚስት ወደ ነቢዩ ኤልሳዕ መጥታ ምን አደረገላት?
36. ነቢዩ ኤልሳዕ ንዕማንን እንዴት ከለምፅ በሽታ አዳነው?
37. ኤልሳዕ ከሞተ በኋላ በአስከሬኑ አማካይነት ምን ተአምር ተደረገ?
38. ንጉሥ ምናሴ ኢሳይያስን ያስገደለው በምን ዐይነት ነው?
39. ነቢዩ ኢሳይያስ ወንጌላዊው ነቢይ የተባለው በምን ምክንያት ነው?
40. ነቢዩ ኤርምያስ ከየትኛው የእስራኤል ነገድ ነበር?
41. የአባቱ መኖሪያ ማን የሚባልና ከየትኛውስ የነገድ ክፍል ነበር?
42. ነቢዩ ኤርምያስ ለትንቢት አገልግሎት የተመረጠው መቼ ነው?
43. ነቢዩ ኤርምያስ ወገኖቹን አይሁድን ከናቡከደነፆር ጋር በላቸው ግንኙነት ምን ብሎ መከራቸው?
44. የኤርምያስ ትንሹ መጽሐፍ ሰቆቃው የሚል ስም የተሰጠው ለምንድነው?
45. ስለ ጥበበ ሰሎሞን ጸሐፊ የተሰጠው ሁለት ዐይነት አስተያት ምንና ምን ነው?
46. የጢሞቴዎስ ትውልድ እንዴት ነበር?
47. የጢሞቴዎስ እናትና አያት ማንና ማን ይባሉ ነበር?
48. ጢሞቴዎስን እንዴት አድርገው አሳድገውት ነበር?
49. ጢሞቴዎስ የተገረዘው ለምን ነበር?
50. የያዕቆብን መልእክት ያዘጋጀው ያዕቆብ ከድንግል ማርያም ጋር ያለው ዝምድና እንዴት ነው?
51. የሳሙኤልና የነገሥት መጻሕፍት አጻጻፍ ከዜና መዋዕል አጻጻፍ የሚለየው እንዴት ነው?
52. በዜና መዋዕል መጽሐፍ ውስጥ ከአዳም ጀምሮ ዘር ቈጠራ የተደረገው በምን ምክንያት ነው?



53. ነገሥታቱና ቤተ መቅደሱ ለእስራኤል ሕዝብ ደኅንነትና በረከት አስተማማኞች ነበሩን?
54. እንደ እውነተኞች እስራኤላውያን የሚቈጠሩት የትኞቹ ነበሩ?
55. እውነተኛ እስራኤል መሆን ወይም አለመሆን መለኪያ የሚለካው በምን ነበር?
56. ጦርነቶች ምን ዐይነት የእግዚአብሔር ፍርዶች ናቸው?
57. ድልስ የሚገኘው ከምንድነው?
58. ይመጣል ተብሎ በኢሳይያስ የተነገረለት ንጉሥ ማነው?
59. በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ ኀምሳ ሦስት ውስጥ የተነገረው ስለምን ጉዳይ ነው?
60. ነቢዩ ኤርምያስ ከመጀመሪያው ጀምሮ ያውቅ የነበረው ምኑን ነው?
61. ኤርምያስ ከመጀመሪያ ጀምሮ ተቃውሞ የበዛበት በምን ምክንያት ነው?
62. አይሁድ በአቢብ (ነሐሴ) ዘጠኝ ቀን ድምፃቸውን እያሰሙ ሰቆቃወ ኤርምያስን የሚያነብቡት በምን ምክንያት ነው?

## ምዕራፍ 3

# ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ

## የጌታችን ትምህርቶች

<u>የዘብዴዎስ ልጆች እናት ልመና</u>:- የዘብዴዎስ ልጆች እናት ከልጆችዋ ጋር ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመቅረብ እጅ ነሣች፤ አንድ ነገር እንዲያደርግላትም ለመነችው። ጌታችንም ምን እንደምትፈልግ በጠየቃት ጊዜ «አንተ በምትነግሥበት ጊዜ ሁለቱንም ልጆቼን፣ አንዳቸውን በቀኝህ ሌላውን በግራህ የመቀመጥ ሥልጣን እንዲኖራቸው አድርግልኝ» አለችው። ጌታችን ግን የምትለምኑትን አታውቁም እኔ የምጠጣውን የመከራ ጽዋ መጠጣት ትችላላችሁን? አላቸው እነርሱም አዎን እንችላለን አሉት።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም:- «በርግጥ እኔ የምጠጣውን የመከራ ጽዋ ትጠጣላችሁ፤ ነገር ግን በቀኜና በግራዬ እንድትቀመጡ የማደርገው እኔ አይደለሁም፡ ይህ ቦታ የሚሰጠው አባቴ ላዘጋጃላቸው ሰዎች ነው» አላቸው።

ከዚህ በኋላ ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን ሁሉ ወደ እርሱ ጠርቶ «ከናንተ መካከል አለቃ መሆን የሚፈልግ ከናንተ በታች ሆኖ ያገልግል፤ እንዲሁም ከናንተ የበላይ መሆን የሚፈልግ የናንተ አገልጋይ ይሁን። የሰው ልጅም ብዙዎቹን ለማገልገልና ለማዳን ሕይወቱን አሳልፎ ለመስጠት መጣ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም አላቸው» (ማቴ. ም:20 ቊ:-20–28)።

<u>መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክ ጌታችን የሰጠው ተስፋ</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ተስፋ ሲሰጣቸው እንዲህ ብሎአቸዋል። «ከወደዳችሁኝ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ። አብን ጠይቄ ለዘለዓለም ከናንተ ጋር የሚሆን ረዳት (አጽናኝ) ይላክላችኋል። እርሱም የእውነት መንፈስ ነው። ስለ አላየውና ስለማያውቀው ዓለም እርሱን አይቀበለውም። እናንተ ግን በእናንተ ውስጥ ስላለና ከእናንተም ጋር ስለሚኖር ታውቁታላችሁ። ወላጆቻቸው እንደሞቱባቸው ልጆች አልተዋችሁም። ወደ እናንተ እምጣለሁ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዓለም አያየኝም፤ እኔ ስለምኖርና እናንተም ስለምትኖሩ ግን ታዩኛላችሁ። በዚያን ቀን እኔ በአባቴ፣ እናንተ በእኔና እኔም በእናንተ መሆኔን ታውቃላችሁ። የሚወድደኝ ትእዛዜን ተቀብሎ የሚፈጽመው ነው። እኔን የሚወድ አባቴ ይወድደዋል። እኔም ወድጄው ራሴን እገልጥለታለሁ። .... ገና ከእናንተ ጋር ሳለሁ ይህን ሁሉ ነግሬአችኋለሁ። አባቴ በእኔ ስም የሚልከው ረዳት (አጽናኝ) መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል፤ የነገርኳችሁንም ነገር ሁሉ ያስታውሳችኋል (ዮሐ ም:14 ቊ:15–26ስ) ። «እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ ረዳት አጽናኝ ከአብ የሚሠርጸው የእውነት መንፈስ በሚመጣበት ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል» (ዮሐ:ም:15 ቊ:26)።

<u>ጌታችን ሕፃናትን መባረኩ</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲዳስሳቸው ብለው ሰዎች ሕፃናትን ወደ እርሱ አቀረቡለት። ደቀ መዛሙርቱ ሰዎቹን ገሠጹ አቸው። ጌታም ይህን ባየ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው:- «መንግሥተ ሰማይ እንደነዚህ ላሉት ስለሆነ ሕፃናት

www.ethiopianorthodox.org

ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸው፤ ተዉአቸው። በእውነት እላችኋሁ፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን ሆኖ የማይቀበላት አይገባባትም።» ሕፃናቱንም ዐቅፎ ባረካቸው (ማር:ም:10 ቍ:13–16)።

## የጌታችን ተአምራት

የአንድ ዐይነ ስውር መፈወስ:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሆኖ ወደ ቤተ ሳይዳ በደረሰ ጊዜ ሰዎች አንድ ዐይነ ስውር ወደ እርሱ አምጥተው እንዲዳስሰው ለመኑት። ጌታችንም የዐይነ ስውሩን እጅ ይዞ እየመራ ከመንደር ወደ ውጪ አወጣው። በሰውዬውም ዐይኖች ላይ ምራቁን እንትፍ ብሎ እጁን ጫነበትና አንዳች ነገር ታያለህን? ሲል ጠየቀው። ዐይነ ስውሩም ቀና ብሎ «አዎ ሰዎች ይታዩኛል፤ ግን እንደሚራመዱ ዛፎች ይመስላሉ» አለ።

እንደገናም ጌታ በሰውዬው ዐይኖች ላይ እጁን ጫነ፤ በዚህ ጊዜ ሰውዬው ትኩር ብሎ አየ፤ ድኖም ሁሉን ነገር አጥርቶ ማየት ጀመረ። ከዚያም በኋላ ጌታችን ወደ መንደሩ አትግባ ብሎ ወደ ቤቱ እንዲሄድ አሰናበተው (ማር:ም:8 ቍ:22–26)።

የአንድ ድዳ መፈወስ ተአምር:- ዐይኖቻቸው የተከፈቱላቸው ሰዎች ሄደው ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዝና በደረሱበት ቦታ ሁሉ አውርተው ስለነበረ ሰዎች ጋኔን ያደረበት አንድ ድዳ ሰው ይዘው ወደ ጌታችን መጡ። ያም ሰው ጋኔኑ ከወጣለት በኋላ ተናገረ። ሕዝቡም:- «እንዲህ ያለ ነገር በእስ ራኤል ከቶ ታይቶ አይታወቅም» አሉ። ፈሪሳውያን ግን:- «እርሱ አጋንንትን የሚያስወጣው በአጋንንት አለቃ አማካይነት ነው» አሉ (ማቴ:ም:9 ቍ:32–33)።

የአንድ ለምጻም ሰው መፈወስ:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ ከተማ ውስጥ በነበረ ጊዜ ሰውነቱ በመላ በለምጽ የተሸፈነ ሰው ወደ እርሱ መጣ። ጌታችንም ባየው ጊዜ በምድር ላይ ተደፍቶ እንዲህ ሲል ለመነው:- «ጌታ ሆይ፤ ብትፈቅድስ ልታነጻኝ ትችላለህ።» ጌታችንም እጁን ዘረግቶ ዳሰሰውና:- «ፈቅጄአለሁ፤ ንጻ» አለው። ወዲያውኑ ለምጹ ለቀቀው።

ከዚያ በኋላ ጌታችን እንዲህ ብሎ አዘዘው:- «ለማንም አትናገር፤ ነገር ግን ለእነርሱ ምስክር ይሆን ዘንድ ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ፤ ስለመንጻትህም ሙሴ ያዘዘውን መሥዋዕት አቅርብ» (ሉቃ:ም:5 ቍ:12–114)።

የቤተ መቅደስን ግብር መክፈል:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ደቀ መዛሙርቱ ወደ ቅፍርናሆም በደረሱ ጊዜ የቤተ መቅደስ ግብር ሰብሳቢዎች ወደ ቅዱስ ጴጥሮስ መጥተው:- «መምህራችሁ የቤተ መቅደስን ግብር አይከፍልምን» ብለው ጠየቁት።

ቅዱስ ጴጥሮስም:- «አዎ፤ ይከፍላል» ብሎ መለሰላቸው። ቅዱስ ጴጥሮስ ወደ ቤት በገባ ጊዜ መጀመሪያ የተናገረው ጌታችን ነው፤ እርሱም ቅዱስ ጴጥሮስን:- «ስምዖን ሆይ፤ ምን ይመስልሃል? የምድር ነገሥታት ቀረጥንና ግብርን የሚቀበሉት ከማን ነው? ከልጆቻቸው ነው? ወይስ ከሌሎች ነው? ብሎ ጠየቀ።

ቅዱስ ጴጥሮስም ከሌሎች ነው ብሎ መለሰ። ጌታችንም እንግዲያውስ ልጆቻቸው ግብር ከመክፈል ነጻ ናቸው ማለት ነው አለ። ነገር ግን መሰናክል እንዳንሆንባቸው ወደ ባሕር ሂድና መንጠቆህን ጣል፤ በመጀመሪያ የምትይዘውን ዓሣ ወስደህ አፉን ክፈትና ለእኔና ለአንተ የሚሆን ገንዘብ ሰለምታገኝ ወስደህ ክፈል ብሎ አዘዘው (ማቴ:ም:17 ቍ:24–27)።

## የጌታችን ምሳሌዎች

የበለስ ዛፍ ምሳሌነት:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ምሳሌ ሲናገር እንዲህ ብሏል:- «በለስንና ሌሎች ዛፎችን ተመልከቱ፤ ቅጠሎቻቸው በሚያቈጠቍጡበት ጊዜ በጋ እንደተቃረበ ትክ ብላችሁ አስተውሉ። እንዲ ሁም እነዚህ ነገሮች ሁሉ ሲፈጸሙ ባያችሁ ጊዜ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደተቃረበ ዕወቁ። በእውነት እላችኋለሁ እነዚህ ሁሉ ነገሮች እስኪፈጸሙ ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም። ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን ከቶ አያልፍም» (ሉቃ:ም:21 ቍ:29–33)።

የሠርግ ግብዣ ምሳሌ:- እንደገናም ጌታችን በሌላ ጊዜ ይህን ምሳሌ ተናገረ:- «መንግሥተ ሰማይ ለልጁ የሠርግ ግብዣ ያዘጋጀን ሰው ትመስላለች። እርሱም የተጋበዙትን ሰዎች ወደ ሠርጉ ግብዣ እንዲጠሩ አገልጋዮቹን ላካቸው። እነርሱ ግን ለመምጣት ፈቃደኞች አልሆኑም።

«ከዚያም በኋላ ሌሎች አገልጋዮችን ልኮ ለተጋባዮቹ እንዲህ ብለው እንዲነግሩአቸው አዘዛቸው:- ድግሱ ተዘጋጅቶአል፤ ሰንጋዎቼና የሰቡ ፍሪዳዎቼ ታርደዋል፤ ሁሉም ነገር ተዘጋጅቶአል፤ ስለዚህ ወደ ሠርጉ ግብዣ ኑ። እነርሱ ግን ነገሩን ችላ ብለው አንዱ ወደ እርሻው፤ ሌላው ወደ ንግዱ ሄዱ። የቀሩት ደግሞ አገልጋዮቹን ይዘው በማዋረድ ደበደቡና ገደሉአቸው። በዚህ ጊዜ ንጉሡ ተቈጣና ወታደሮቹን ልኮ እነዚያን ገዳዮች አስገደለ፤ ከተማቸውንም በእሳት እንዲያቃጥሉ አደረገ። ከዚያም በኋላ አገልጋዮቹን እንዲህ አላቸው፤ እነሆ፥ የሠርጉ ድግስ ተዘጋጅቶአል። የተጠሩት ግን ለግብዣው የተገቡ አልሆኑም። ስለዚህ በየአደባባዩ ሂዱና ያገኛችሁትን ሰው ሁሉ ወደ ሠርጉ ግብዣ ጥሩ። አገልጋዮቹም በየመንገዱ ሄደው ያገኙትን ሰው ሁሉ ክፉዎችንም ደጎችንም ሰበሰቡ። የሠርጉንም አዳራሽ በተጋባዦች ሞሉት»።

«ነገር ግን ንጉሡ ተጋባዦቹን ለማየት ወደ አዳራሹ በገባ ጊዜ የሠርግ ልብስ ያልለበሰ አንድ ሰው በዚያ አየ። እርሱም:- የሠርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ? አለው። ሰውየው ግን ዝም አለ። ንጉሡም አገልጋዮቹን እጅና እግሩን እሰሩና አውጥታችሁ በውጪ ወዳለው ጨለማ ጣሉት፤ በዚያም ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል አለ። ጌታችንም:- ስለዚህ የተጠሩት ብዙዎች ናቸው፤ የተመረጡት ግን ጥቂቶች ናቸው አለ» (ማቴ:ም:22ቍ:1–14)።

የሦስቱ አገልጋዮች ምሳሌ:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሌላ ጊዜ የተና ገረው ምሳሌ የሚከተለው ነው:- «በዚያን ጊዜ ወደ መንግሥተ ሰማይ የመግባት ሁናቴ እንዲህ ይሆናል:- ወደ ሌላ አገር የሚሄድ አንድ ሰው አገልጋዮቹን ጠርቶ ንብረቱን አስረከባቸው። ለያንዳንዱ እንደ ችሎታው በማካፈል፥ ለአንዱ አምስት መክሊት፥ ለአንዱ ሁለት መክሊት፥ ለአንዱ ደግሞ አንድ መክሊት ሰጠና ወደ ሌላ አገር ሄደ። አምስት መክሊት የተቀበለው ወዲያውኑ ሄዶ ነገደበትና ሌላ አምስት መክሊት አተረፈ። ሁለቱ መክሊት የተቀበለውም እንዲሁ ነግዶ ሌላ ሁለት መክሊት አተረፈ። አንድ መክሊት የተቀበለው ግን ሄደና መሬት ቈፍሮ የጌታውን ገንዘብ ቀበረ።

ከብዙ ጊዜ በኋላ የነዚያ አገልጋዮች ጌታ መጣና ከአገልጋዮቹ ጋር መተሳሰብ ጀመረ። አምስት መክሊት የተቀበለው አገልጋይ ወደ ጌታው መጣና ሌላም አምስት መክሊት አቅርቦ ‹ጌታ ሆይ፥ አምስት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር፤ እነሆ፤ ሌላ አምስት መክሊት አትርፌአለሁ› አለ። ጌታውም ‹መልካም አደረግህ፤ አንተ ታማኝና ደግ አግልጋይ፤ በጥቂት ነገር ታማኝ ሆነህ ስለተገኘህ በብዙ ነገር ላይ እሾምሃለሁ፤ ና፤ የጌታህን ደስታ ለመካፈል ግባ።› አለው። ሁለት መክሊት የተቀበለውም ቀርቦ ‹ጌታ ሆይ፥ ሁለት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበረ፤ እነሆ፥ ሌላ ሁለት መክሊት አትርፌአለሁ› አለ። ጌታውም ‹መልካም ነው፤ አንተ ታማኝና ደግ አገልጋይ፥ በጥቂት ነገር ታማኝ ሆነህ ስለተገኘህ በብዙ ነገር ላይ እሾምሃለሁ፤ ና፤ የጌታህን ደስታ ለመካፈል ግባ› አለው። አንድ መክሊት የተቀበለውም ቀርቦ ‹ጌታ ሆይ፤ ካልዘራህበት የምታጭድ ካልበተንህበት የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን ዐውቃለሁ፤ ስለዚህ ፈራሁና ሄጄ ገንዘብህን በመሬት ውስጥ ቀበርሁት፤ ይኸውልህ ገንዘብህ› አለው። ጌታው ግን እንዲህ አለው:- ‹አንተ ክፉና ሰነፍ አገልጋይ፥ ካልዘራ ሁበት እንደማጭድ፥ ካልበተንሁበት እንደምሰበስብ የምታውቅ ከሆነ ገንዘቤን በባንክ ማስቀመጥ ነበረብህ፤ እኔም በመጣሁ ጊዜ ገንዘቤን ከነወለዱ እወስድ ነበር። በሉ ገንዘቤን ተቀበሉና ዐሥር መክሊት ላለው ስጡት። ላለው ይሰጠዋል፤ ይጨመርለታል፤ ይበዛለታልም፤ ከሌለው ሰው ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል፤ ይህን የማይረባ አገልጋይ ግን በውጪ ወዳለው ጨለማ አውጥታችሁ ጣሉት፤ በዚያም ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል»› (ማቴ:ም:25 ቍ:14–30)።

## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

በደቀ መካሙርቱ አስተሳሰብ የጌታችን የኢየሱስ ክስርስቶስ እንግሥ ማለት የመንግሥቱ መነሣት ምድራዊ መንግሥትን ለማቋቋም ማለት እንደሆነ መሰላቸው። ስለዚህም ያዕቆብና ዮሐንስ ከእናታቸው ጋር ሆነው ያ እነርሱ ይቋቋም የመሰላቸው መንግሥት በሚቋቋምበት ጊዜ አንዳቸው በቀኙ አንዳ ቸው ደግሞ በግራው የመቀመጥ ከፍተኛ ሥልጣን እንዲሰጣቸው ጠየቁት። ይህም የሚያመለክተው በደቀ መዛሙርቱ ዘንድ እንኳ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይታመን የነበረው ምድራዊ መንግሥት ያቋቍማል ተብሎ የነበረ መሆኑ ነው። በዚህም ምክንያት እናትና ልጆቿ የእርሱ ንግሥ ምን ዐይነት መሆኑንና የሚጠይቁትን ባለማወቃቸው ገሦጻ ቸው። እርሱ የገለጻላቸው ምን ዐይነት ክብር እንደሚያገኙ ሳይሆን ምን ዐይነት ሕማማት እንደሚጠብቃቸው ነው። የሚጠብቃቸውም የመከራ ጽዋና የመከራ ጥምቀት መሆኑን ገለጠላ

www.ethiopianorthodox.org

ቸው። በቀኝና በግራ ስለመቀመጥ ጉዳይ ግን ከአብ ዘንድ ለተዘጋጀላቸው የሚሰጥ መሆኑን ገልጦ እርሱ ለሁላቸውም በሰማይ ቦታ እንዳዘጋጀላቸው አስቀድሞ ተስፋ የሰጣቸው በመሆኑ ያ በቂ መልስ ነው ብሎ ዐልፎታል። የእግዚአብሔር ዕቅዶች ሁሉ አስቀድመው የተዘጋጁ እንደመሆናቸው የሰማያዊ ክብር ደረጃም በዚሁ ዐይነት አስቀድሞ በዘለዓለማዊ ዕቅዶቹ ውስጥ ያሉ ናቸው እንጂ እንደምድራዊ ክብር በዝምድናና በወዳጅነት ወይም በአድ ልዎ የሚሰጡ አይደሉም። ስለ ሰማያዊ ክብር ደግሞ እነርሱ ተነሥተው ከሌሎቹ ጓደኞቻችን የበለጠ ክብር ስጠን ብለው መጠየቅ አልነበረባቸውም። ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ያዕቆብና ዮሐንስ በእኛ ላይ አለቃ እንሁን አሉ ብለው በሁለቱ ወንድማማች ላይ ተቈጡ። ይህም የሁለቱ ወንድማማች ጥያቄ በደቀ መዛሙርቱ መካከል ቅናትና ለክብር የደረጃ ፉክክርን አስከተለ። የአረማውያን አለቆች እንደሚያደርጉት እንዳያደርጉ በመካልከል መምህራቸው ወቀሳቸው። የአረማውያን አለቆች በሕዝቦቻቸው ላይ አምባገነኖች ሆነው እንደሚገ ዙአቸው ታውቃላችሁ። በእናንተ መካከል ግን እንዲህ መሆን የለበትም። የመንግሥተ ሰማይ አሠራር ከምድራዊ መንግሥት የተለየ ነው። በሰማያዊው አሠራር ጌታ ለመሆን የሚፈልግ ለሁሉም እንደ ባሪያ መሆን አለበት፤ ትልቅ ነት የሚገኝበት መንገድ ትሕትናና አገልጋይነት ነው። ደቀ መዛሙርቱም ሊገለ ገል ሳይሆን ሊያገለግልና ለሕዝቦችም ቤዛ ለመሆን የመጣውን መምህራቸውን መምሰል አለባቸው። የክብር ጌትነቱ እየታወቀ የባሪያውን መልክ በመልበሱ እርሱ ከፍተኛ የትሕትና ምሳሌ ሆኖአል። በአገልግሎትም እርሱ ከፍተኛ ምሳሌ የሆነው ትምህርቶቹና ሥራዎቹ ያተኰሩት በአገልግሎት ላይ ስለነበረና እንዲያውም የሰውን ዘር ከጥፋት ለማዳን በቤዛነት ነፍሱን እስከመስጠት መድረሱ ነው።

ለዘለዓለም ከእናንተ ጋር ይሆን ዘንድ አጽናኙን እንዲሰጣችሁ አባቴን እጠይቀዋለሁ ማለቱ ከሰማያዊ አባቱ ጋር ፍጹም አንድነት ያለው የእግዚአ ብሔር አንድያ ልጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመለኮት ከአባቱ ጋር አንድ የሆነ፡ በፈቃድ፡ በዝግጅትና በጥበቃ አንድ እንደመሆናቸው ሊለያዩ አይች ሉም። ስለዚህም እንዲልክላቸው ተስፋ በሰጣቸው መሠረት ወልድም ከአብ ጋር በአንድነት ሆኖ ይልክላቸዋል እንጂ አብ ብቻ የሚልክ አይደለም። ምንም እንኳ መንፈስ ቅዱስ የሚሠርጸው ከአብ ቢሆን ስጦታ የሚደረገው በአብ፡ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ነው። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ የሚላከው በአብና በወልድ ለመሆኑ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ከአባቴ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ ሲመጣ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል» ብሎአል (ዮሐ:ም:15 ቍ:26)።

አጽናኝ የተባለው ቃል በግሪኩ ጰራቅሊጦስ (ፓራክሌት) ሲሆን ትርጕሙም አጽናኝ፤ ወይም ጠበቃ፥ ወይም ረዳት ወይም አማላጅ፡ እርሱም ከደካማ ጐን ቆሞ ደካማውን የሚረዳና የሚደግፍ ማለት ነው። በዚህም መሠረት መንፈስ ቅዱስ የሚረዳውን ሰው መተማመንና እምነት ያበረታታዋል። ጌታችንና አዳኝ ቃሉን እንዲሰማው ያደርገዋል፤ ይረዳዋል፤ ያጽናናዋል፤ አይዞህ ብሎ ከአብ ዘንድ እንደሚልክላቸው ቃል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ጠበቃ፡ ረዳት ወይም አጽናኝ ስጦታዎች ነው። መንፈስ ቅዱስ ከአብና ገባላቸው። የሚልከውም የመንፈስ ቅዱስን ጸጋና ስጦታዎች ነው። መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር ፍጹም አንድነት ያለው ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእውነት መንፈስ ይለዋል። እርሱም የእውነት መንፈስ የተባለው የእግዚአብሔር መንፈስ በመሆኑና እግዚአብሔርም እውነት በመሆኑ ነው። እርሱም የእውነት መንገድ፡ ወደ እውነት የሚመራ ነው። በሌላም ቦታ ጌታችን እንዲህ ብሎአል:- «የእውነት መንፈስ የሚናገረው የሰማውን እንጂ የራሱን ስላልሆነ እርሱ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል። እርሱ ወደፊት የሚሆኑትን ነገሮች ይነግራችኋል። የእኔ ከሆነው ወስዶ ስለሚነግራችሁ እኔን ያከብረኛል። የአብ የሆነ ሁሉ የእኔ ነው፤ የእኔ ከሆነው ወስዶ ይነግራችኋል ያልኋችሁ ስለዚህ ነው» (ዮሐ:ም:16 ቍ:13–15)። የሚናገርበት መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር በባሕርይ፡ በመለኮት፡ በሥልጣን አንድ ነው። የሚናገርበት ነው፤ እውነት ከእርሱ ብቻ የተገኘ አይደለም። ይህ እውነት ግን የተገኘው ከሥሉስ ቅዱስ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በመጀመሪያ መልእክቱ ስለ እውነት መንፈስ ሲያብራራ እንዲህ ብሎአል:- «እኛ የእግዚአብሔር ነን፤ እግዚአብሔርን የሚያውቅ ሁሉ ይሰማናል፤ የእግዚአብሔር ያልሆነ ግን አይሰማንም፤ እውነተኛን መንፈስና ሐሰተኛን መንፈስ ለይ ተን የምናውቀው በዚህ ነው:» (1ኛ:ዮሐ:ም:4 ቍ:6) ። እንዲሁም የሚከተ ሉትን ሁለት ጥቅሶች እንመልከት፡



«ጥምቀቱን በሚያመለክት ውሃና ሞቱን በሚያመለክት ደም የመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ የመጣው በውሃ ብቻ ሳይሆን በውሃና በደም ነው፤ እውነት ስለሆነ ይህ ነገር እውነት መሆኑን መንፈስ ቅዱስ ይመሰክራል» (1ኛ:ዮሐ:ም:5ቍ:6)።

«እኛ የእግዚአብሔር መሆናችንን እናውቃለን፤ ዓለም ግን በሞላው የሰይጣን ተገዢ ሆኖአል። የእግዚአብሔር ልጅ እንደመጣና እውነተኛውን አምላክ እንድናውቅ አስተዋይ ልቡና እንደሰጠን እናውቃለን፤ በልጁም በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእርሱ ከእውነተኛው አምላክ ጋር ኅብረት አለን፤ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛው አምላክና የዘለዓለም ሕይወት ነው» (1ኛ:ዮሐ:ም:5 ቍ:19–20)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ሊልክላቸው ቃል የገባላቸው አጽናኝ «የእውነት መንፈስ ነው፤ ዓለም ስለማያየውና ሰለማያውቀው ሊቀበ ለው አይችልም፤ እናንተ ግን፥ እርሱ ከእናንተ ጋር ስለሆነና በውስጣችሁ ስላለ ታውቁታላችሁ» በሎአቸዋል (ዮሐ:ም:14 ቍ:17)። ይህም የሆነበት ምክንያት የሰው ዘር በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ዓለም ለሰይጣን ተገዢ ሆኖ ይኖር ስለነበረ ነው። ከሰይጣንም ጋር የነበረው ግንኙነት በባሪያና በባሪያ አሳደሪ መካከል ያለውን ግንኙት ይመስል ነበር። ይህም ማለት ሰይጣን የፈለገውን ድርጊት በሰው ዘር ላይ ያደርግ ነበር ማለት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለም ላይ ሰይጣን የነበረውን ሥልጣን ሲያመለክት የዚህ ዓለም ገዢ ብሎታል (ዮሐ:ም:12 ቍ:31፡ ም:14 ቍ:30፡ ም:16 ቍ:11)። ቅዱስ ጳውሎስም የዚህ ዓለም አምላክ ብሎታል።

«እነርሱ የማያምኑበት ምክንያት የዚህ ዓለም ገዢ የሆነው ሰይጣን ልቡናቸውን ስላሳወረው ነው፤ በእግዚአብሔር መልክ ስለተገለጠው ስለ ክርስቶስ ክብር ከተነገረው ወንጌል የሚመጣላቸውን ብርሃን እንዳያዩ ያደረጋ ቸው እርሱ ነው» (2ኛ:ቆሮ:ም:4 ቍ:4)።

እንዲሁም:-

«የእኛ ውጊያ ከሰዎች ጋር ሳይሆን በዚህ በጨለማ ዘመን ከሚሠሩት ገዢዎች፥ ከባለ ሥልጣኖችና ከዓለም ኀይሎች፥ ይህም ማለት ከሰማይ ካሉት የርኩሳን መናፍስት ሠራዊት ጋር ነው» (ኤፌ:ም:6 ቁ:12)።

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም በመጀመሪያ መልእክቱ እንዲህ ብሎአል:- «እኛ የእግዚአብሔር መሆናችንን እናውቃለን፤ ዓለም ግን በመላው የሰይጣን ተገዢ ሆኖአል» (1ኛ:ዮሐ:ም:5 ቍ:19)።

ዓለምን ሁሉ ወደ ክፋት ለሚጐትተው ሐሰተኛና የሐሰት መሥራች ለሆነው ሰይጣን ፍጹም ተገዢ እስከሆነ ድረስ ደግ የሆነውንና ወደ ደግነት የሚመራውን መንፈስ ቅዱስን ሊቀበል አይችልም። ይህም የሆነበት ምክንያት በክፋትና በሐሰት የተመላ በመሆኑ ነው። መንፈስ ቅዱስም እውነትና እውነትን የሚያስተምር ነው። ሰይጣንም ሰዎችን በቁሳዊና በሥጋዊ ነገሮች ላይ እንዲ ያተኵሩ አስተምሮአቸዋል። ሰማያዊና መንፈሳዊ ነገሮችንም እንዳያዩ ዐይና ቸውን አሳውሮታል።

መንፈስ ቅዱስ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ ዓለም ሊያየው አልቻ ለም። ሊያየውም ስለማይችል አይቀበለውም፤ አያውቀውምም። ሰይጣንም በእርሱ ተሞልቶ ስላየለበት ቁሳዊና ሥጋዊ ነገርን በቀር ሊያይ አይችልም፤ ሊያውቅም አይችልም። በዚህም ምክንያት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሎአል:-

«ያስተማርነው የወንጌል ቃል ምናልባት የተሰወረ ቢሆንም፥ የተሰወረው ለሚጠፉት ነው። እነርሱ የማያምኑበት ምክንያት የዚህ ዓለም ገዢ የሆነው ሰይጣን ልቡናቸውን ስላሳወረው ነው፤ በእግዚአብሔር መልክ ስለተገለጠው ስለ ክርስቶስ ክብር ከተነገረው ወንጌል የሚመጣላቸውን ብርሃን እንዲያዩ ያደረጋቸው እርሱ ነው» (2ኛቆሮ:ም:4 ቍ:3–4)።

ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልእክቱም እንዲህ ይላል:- «እናንተ በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ምክንያት የሞታችሁ ነበራችሁ፤ በዚያን ጊዜ የዚህን ዓለም ክፉ ነገር እየተከተላችሁ በበደልና በኃጢአት ትኖሩ ነበር፤ እንዲሁም በአየር ያሉትን የመናፍስት ኀይሎች የሚገዛውን ትከተሉ ነበር፤ እርሱ በማይታዘዙ ሰዎች ላይ የሚሠራ ርኩስ መንፈስ ነው። እኛም ሁላችን ከዚህ በፊት በእነርሱ መካከል የሥጋችንን ፈቃድና የአእምሮአችንን ሐሳብ እየተከተልን በሥጋችን ምኞት እንኖር ነበር፤ እንደ ሌሎችም በተፈጥሮአችን በእግዚአብሔር ቍጣ ሥር

www.ethiopianorthodox.org

ነበርን። ነገር ግን የእግዚአብሔር ምሕረት ብዙ ከመሆኑና ለእኛም ያለው ፍቅር ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ ምንም እንኳ በበደላችን የሞትን ብንሆን እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ሕወትን ሰጥቶናል፤ እናንተም የዳናችሁት በጸጋው ነው» (ኤፌ:ም:2 ቍ:1–5)።

ክፉው ዓለም ወይም በዓለም ላይ ያሉት ክፉዎች ሰዎች ሰይጣን በእነርሱ ላይ ሠልጥኖ ቁሳውያንና ሥጋውያን በመሆናቸው በቁሳዊ አካላቸውና በምድራዊ አስተሳሰባቸው መንፈስ ቅዱስን ለማየት የማይችሉ ሲሆኑ የጌታችን ደቀ መዛሙርት ግን መምህራቸው ለዘለዓለም ከእነርሱ ጋር ስለሚኖርና እርሱም ካረገ በኋላ መንፈሱ በእነርሱ ላይ ስለሚወርድ ያውቁታል። እርሱም እንዲህ ሲል ተስፋ ሰጥቶአቸዋል:- ... ተመልሼ ወደ እናንተ

«እናትና አባት እንደሌላቸው ልጆች ብቻችሁን አልተዋችሁም፤ ተመልሼ ወደ እናንተ እመጣለሁ» (ዮሐ:ም:14 ቍ:18)።

ይህንንም የነገራቸው እርሱ በሥጋ ከእነርሱ በመለየቱ ወላጆች እንደሌላቸው ልጆችና ደጋፊ እንደሌላቸው ሰዎች የተስፋ መቍረጥ ስሜት እንዳይሰማቸው ለማድረግ ነው። እርሱ በሥጋው ሳይሆን በመንፈሱ ለዘለዓለም ከእነርሱ እንደማይለይና ሁልጊዜ የኀያልነት ድጋፉ ከእነርሱ ጋር እንደሚኖር ተስፋ ሰጣቸው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ እንደሚልክላቸው ተስፋ የሰጠው አጽናኝ የሚያመለክተው በበዓለ ኀምሳ ቀን በደቀ መዛሙርቱ ላይ የወረደው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው። በዚያን ቀን በመንፈስ፥ በፍቅር፥ በደስታ፥ በሰላም፥ በመጽናናትና በድፍረት፥ እንዲሁም የራሳቸው ባልሆነ ቋንቋ በመናገር ችሎታ ተሞሉ (የሐ:ሥ:ም:2 ቍ:1–11)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊልክ ያቀደው የመንፈስ ቅዱስን ስጦታዎች ነው። ከቤተ ክርስቲያን ጋር ለዘለዓለም አብሮ የሚኖረው ማነው? ዓለም ሊቀበለው የማይችል የሕይወት መንፈስ የተባለው ማነው? ነቢይ በሆነ ከሌሎቹ ከቀድሞዎቹ ነቢያት የሚለየው በምንድነው? አንድ ነቢይ ከሆነ እንደማንኛውም ሰው እርሱ አንድ ሰው ነው። ይህ አጽናኝ የተባለው የታወቀ ሰው ከሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማንም ሰው አያየውም፤ አያውቀውምም ብሎ እንዴት ስለዚያ ሰው ይናገራል? ጌታችን ደግሞ እርሱ ከእናንተ ጋር ስለሚኖር እናንተ ታውቁታላችሁ ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ነግሮአቸዋል። ታዲያ፤ ከእነርሱ ጋር የሚኖርና እነርሱ የሚያውቁት ማነው? በበዓለ ኀምሳ በጌታችን ደቀ መዛሙርት ላይ የወረደው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ካልሆነ በቀር ሌላ ሊሆን አይችልም።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ መሆኑንና እርሱ የነካው ሰው ሁሉ ጸጋና በረከትን ሊያገኝ እንደሚችል ሰዎች ያምኑ ስለነበረ ልጆቻቸውን ይዳስስላቸው ዘንድ ወደ እርሱ ይዘው መጡ። ይህንንም የጌታችን ደቀ መዛሙርት ግን ሕፃናቱን ይዘው የመጡትን ሰዎች ተቈጡአቸው። ይህንንም የጌታችን ደቀ መዛሙርት ግን ሕፃናቱን ይዘው የመጡትን ሰዎች ሁሉ ሕፃናትን በንቀት፥ ግምት ያደረጉት፥ ደቀ መዛሙርቱም በዚያን ጊዜ እንደነበሩት ሰዎች ሁሉ ሕፃናትን በንቀት፥ ግምት ባለመስጠትና በማቃለል ዐይን ያዩአቸው ስለነበረ ነው። በጊዜው ከነበረው አስተሳሰብ ጋር በማስተያየት ሕፃናቱን እንዲዳስሳቸው ወደ ጌታችን ማቅረብ እርሱን እንደ ማስቸገር፥ ሥራ እንደማስፈታትና የእርሱን ክብር እንደመዳፈር የቈጠሩት ይመስላል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ደቀ መዛሙርቱ ያን ያደረጉትን ድርጊት እንዳያደርጉ ከለከላቸው። ሕፃናቱንም እንዲህ ሲል ጠራቸው:- የእግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ነውና «ሕፃናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸው»።

ሕፃናት በትሕትናቸው፥ በቅን ልቦናቸው፥ በንጽሕናቸው ገና በዚህ ዓለም ክፋት ያልተ... ትዕቢት፥ ግብዝነት፥ ከሐዲነት አስመሳይነት፥ ከሉ፥ አታላይነትና ተንኰል የሌለባቸው፥ በመሆናቸው የሰማይ መላእክት በሚገለጡበት ጠባዮች ሥሥታምነት፥ ልበ ደንዳናነት የሌላቸው በመሆናቸው የሰማይ መላእክት በሚገለጡበት ጠባዮች ይገለጣሉ። ስለዚህ የነዚህን ሕፃናት ጠባይ በመያዝ የጥንቱ የተወረሰው ኃጢአት ከተወገደለ... በኋላ ነው ማንም ሰው መንግሥተ ሰማይን ለመውረስ የሚችለው ማለት ነው።

ወደ ቤተ ሳይዳ በመጡ ጊዜ ሰዎች አንድ ዓይነ ስውር አምጥተውለት ይዳስሰው ዘንድ ለመኑት። ይህንንም ያደረጉት እሱ ከዳሰሰው ሊድን እንደሚችል አምነው ነው። የዕውሩንም ... ተቈጥቶባ... እጅ ይዞ ከቤተ ሳይዳ ውጪ ያወጣው ብዙ ተአምር እንኳ ቢያደርግባት ባለማመንዋ ተቈጥቶባት ስለነበረ ነው። ስለዚህም በቤተ ሳይዳ ሆኖ ተአምራት ሊደረግባት ተገቢ ሆና ስላላገኛት በተአም... ወደ ውጪ ... ዐይኑን ሊያበራለት የፈቀደውን ሰው ከቤተ ሳይዳ ውጪ ይዞት ወጥቶአል። ወደ ውጪ ... የሚራመ... አውጥቶ በዐይኑ ላይ እንትፍ ብሎበት በእጁ ዐይኑን ዳሰሰ። ያይ እንደሆን ቢጠይቀው የሚራመ... ዛፎች የሚመስሉ ሰዎችን እንደሚ ያይ ነገረው። ዳግመኛ በእጅ ከዳሰሰው በኋላ አጥር...



እንዲያይ በማድረግ ፈወሰው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃሉ ወይም በእጅ መዳሱን ዕውሩን በአንድ ጊዜ ሊፈውሰው በቻለ ነበር። በቀስ ቀስ ወይም በየደረጃ የፈወሰው የሰውየው እምነት ትንሽ የነበረ መሆኑን በማወቁ ነው። ይህንንም ያደረገው ጥቂት በጥቂት ወደ እምነት ሊመራው ፈቅዶ ነው። በዚህም የተሟላ እምነት እንዲኖረው ሲደረግ የመንፈስና የሥጋ ፈውስ የተሟላ ይሆናል። ስለዚህ የጌታችን ዓላማ ያ ሰው የተሟላ እንዲሆን ለማድረግ ነበር። ጌታችንም ወደ መንደር አትግባ፤ ለማንም አትናገር ማለቱ በዚያች መንደር ላይ ተቈጥቶ ስለነበረ ነው።

የድዳው ሰው መፈወስ ተአምር እንደሚያመለክተው ለመናገር ያልቻለው በሰይጣን ምክንያት መሆኑ ግልጥ ነው። ጌታችን ርኩስ መንፈሱን ባስወጣለት ጊዜ ድዳው ሰው ለመናገር ችሎአል። ሌላው አተረጓጐም ደግሞ ሰውን የያዘው ድዳ ሰይጣን ስለነበረ ድዳ ሰይጣን ሲይዝ የያዘውንም ሰው ድዳ ስለሚያደ ርገው ይህ የተጠቀሰው ሰው ድዳ የሆነው በዚህ ምክንያት ነው የሚሉ ምሁራን አሉ። ሌሎች እንደሚሉት ደግሞ ሰይጣን በሰው ላይ ሲሰፍር ያን የሰፈረበትን ሰው ከጸሎትና ከምስጋና ድዳ ያደርገዋል። ጌታም ችግሩን ከሥሩ ለማጥፋት የችግሩ ምክንያት የነበረውን ሰይጣንን ከሰውየው አስወጥቶ አባሮለታል። ከዚያ በኋላም ከድዳነቱ ተፈውሶ መናገር እንዲችል ሆኖአል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቅፍርናሆም ከተማ በገባ ጊዜ ሰውነቱን በሙላ ለምጽ የወረሰው ሰው አግኝቶት በግንባሩ በመደፋት ብትፈቅድስ ከለምጼ ልታነጻኝ ትችላለህ ብሎ ለመነው። ምንም እንኳ እርሱ የነበረበት የለምጽ በሽታ ተስፋ የሚያስቈርጥ ቢሆን ጌታችን የመፈወስ ኀይል የነበረው መሆኑንና እርሱ ከፈቀደ ምንም የሚሳነው ነገር እንደሌለ ያምን ስለነበረ ጌታችን የሰውየውን ጥልቅ እምነት፥ ያቀረበውን ጸሎት፥ በመስገድም ያሳየውን ትሕትና በተመለከተ ጊዜ እጁን በለምጻሙ ላይ በመጫን ፈቅጀአለሁ ንጻ ብሎ መልስ ሰጠው። እርሱም ወዲያው ከለምጽ በሽታው ነጻ። ጌታችንም በዚህ አድራጎቱ እርሱ በፈቀደ በማንኛውም ጊዜ ተአምራትን እንደሚያደርግ አስመሰከረ። ይህም ፈቃዱ ለሰዎች የማይቻል መስለው የሚታዩትን ነገሮች ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። የሙሴ ሕግም ለምጽ የያዘው ሰው ሁሉ ርኩስ እንደሚሆን ለምጻምን የሚነካ ሰው እንደሚረክስ ያስተምር ነበር። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ፍጹም ንጹሕ በመሆኑ ለምጻሙን ሰው ነካው። ርኵሰትም በእርሱ ላይ ምንም ሊያደርግ አይችልም። ነገር ግን ከሰዎች ላይ ርኵሰትን በፍጹም ለመደምሰስ የሚችል እርሱ ብቻ ነው። ምንም እንኳ የተደረገው ተአምር ከፍተኛ ቢሆን ጌታችን በትሕትና ራሱን ዝቅ ለማድረግ እንጂ ራሱን ከፍ ለማድረግ አልፈለገም። በመሆኑም ይህ ጉዳይ እንዲታወቅ አልፈለገም። ስለዚህም ከለምጽ የዳነውን ሰው ለማንም እንዳይናገር አዘዘው። ይሁን እንጂ እርሱ የኦሪትን ሕግ ፈጻሚ ነበር። የኦሪት ሕግ አንድ ሰው ከለምጽ በሽታ ቢድን ስለ መዳኑ የሚፈጸመውን ሥርዓት በመፈጸም በመጀመሪያ ራሱን ለካህን ማሳየት እንደሚገባው ያዛል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር ባደረገው ጥያቄና መልስ የምድር ነገሥታት ግብር የሚቀበሉት ከውጪ ሰዎች እንጂ ከልጆቻቸው አለመሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ግብር አስከፋዮቹ እንዳይሰናከሉ ወደ ባሕር ሄዶ ዓሣ በማጥመድ ከዓሣ ሆድ ውስጥ ገንዘብ አውጥቶ ስለ እርሱና ስለ ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲከፈል አዘዘ። ጌታችን የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ የአባቱ የሆነው ሁሉ የእርሱም መሆኑን ያረጋገጠ፥ ቤተ መቅደሱ የአባቱና የእርሱ መሆኑን ያረጋገጠ እንደመሆኑ ስለ ቤተ መቅደሱ አገልግሎት ግብር ለመክፈል ግዴታ ባልነበረበትም ነበር። ነገር ግን ሞቶ ከመነሣቱ በፊት ጌታችን የእግዚአብሔር ልጅ ነው ብሎ ሌሎችን ማሳመን ባለመቻሉ መሰናከል ከመሆን ይልቅ እንዲከፈል አዘዘ። አከፋፈሉም ስለ ራሱና ስለ ቅዱስ ጴጥሮስ ብቻ መደረጉ ቅዱስ ጴጥሮስ ስለ ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ሁሉ ሆኖ ማለት ነው። ይህም ድርጊት የሚያመለክተው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ በፈቃዱ ስለ ደኸየ ለግብር የሚከፈለውን ያኽል ያ ትንሽ ገንዘብ እንኳ ስላልነበረው ከዓሣ ሆድ ውስጥ በተአምር ገንዘብ እንዲወጣ ማድረጉን ነው። ሌላው ትልቅ ትምህርት ደግሞ ምንም ያኽል ድኾች ብንሆን አቅማችን የሚችለውን ያኽል ለእግዚአብሔር አገልግሎት ከመክፈል ወደ ኋላ እንዳንል ነው። በዚህም ድርጊት የእርሱን ሁሉን ቻይነትና ምንም የሚሳነው ነገር የሌለ መሆኑን ያመለክታል። እርሱም በቤት ውስጥ ሆኖ ሳለ ግብር አስከፋዮች ውጪ ሆነው ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር የተነጋገሩትን ንግግር ማወቁ ከእርሱ ምንም ሊሰወር የሚችል ምሥጢር አለመኖሩንና ሁሉን ነገር ዐዋቂነቱን ማለት መለኮታዊ ዕውቀቱን ያመለክታል።

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ስለ አይሁድ ሕዝብ መጥፋት ስለ ቤተ መቅደስና ስለ ኢየሩሳሌም መፍረስ፥ ከዚሁም ጋር አያይዞ ስለ ደግማዊ ምጽአቱና ስለ

www.ethiopianorthodox.org

መጨረሻው ፍርድ ቀን ልዩ ልዩ ምልክ ቶችን ተናግሮአል። የጊዜውንም መቃረብ እንዴት ማወቅ እንደሚቻል በምሳሌ ሲያመለክት የበለስን ዛፍ ምሳሌ ተናግሮአል። የበለስ ዛፍና ሌሎችም ዛፎች ቅጠሎቻቸው ሲያቈጠቍጡ ባያችሁ ጊዜ በጋ እንደተቃረበ እንደምታውቁ ሁሉ የነገርኋችሁ ምልክቶች በሚደርሱበት ጊዜ የፍርድ ቀን እንደተቃረበ ዕወቁ ብሎአቸዋል። ዛፎች ቅጠሎቻቸው ሲያቈጠቍጡ ስታዩ በጋ መድረሱን ታውቃላችሁ ማለቱ በብዙዎች አገሮች ዛፎች የሚያቈጠቍጡት በበጋ ስለሆነ ነው።

ጌታችን የተናገራቸው ምልክቶች በሁለት የሚከፈሉ ናቸው። አንዱና የመጀመሪያው ስለ ኢየሩሳሌምና ስለ ቤተ መቅደስዋ መፍረስ፥ ስለ አይሁድ ሕዝብ ፍጅትና መበታተን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ስለ ዳግማዊ ምጽአቱና ስለ መጨረሻው የፍርድ ቀን ነበር። ይህ ሁናቴ ከመፈጸሙ በፊት ይህ ትውልድ አያልፍም ያለው በሰባ ዓ.ም ስለተፈጸመው ስለ ኢየሩሳሌምና ስለ ቤተ መቅደሱ መፍረስ፥ ስለ አይሁድ ሕዝብ ፍጅትና ከእነርሱ የተረፉት ጥቂቶቹ መበታተን ስለ ቤተ መቅደሱ መፍረስ፥ ስለ አይሁድ ሕዝብ ፍጅትና ከእነርሱ የተረፉት ጥቂቶቹ መበታተን ጉዳይ ነው። ታዲያ፥ የሁለቱን ትንቢታዊ ትምህርቶች ልዩነት ለይቶ ካለማወቅ የተነሣ የጌታችን ዳግመኛ መምጣትና የፍርድ ቀን በዚያን ዘመን በእነርሱ ዕድሜ የሚፈጸም ይመስላቸው የነበሩ ጥቂቶች አልነበሩም። ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም ብሎ የሰጠው ማረጋገጫ በኢየሩሳሌምና በቤተ መቅደስዋ መፍረስ፥ እንዲሁም በአይሁድ ሕዝብ ፍጅት ጊዜ ተግባራዊ ስለ ሆነ የዳግማዊ ምጽአቱና የመጨረሻው ፍርድ ቀንም እኛ ባላወቅነው ቀን በትክክል እንደሚ ፈጸም እርግጠኞች እንሁን። እርግጠኞችም የምንሆነው የእርሱ ቃል በትክክል የሚፈጸም መሆኑን ስለምናውቅ ነው።

ጌታችን የተናገረው ሌላ ምሳሌ ደግሞ የታላቁ ሠርግ ድግስ ምሳሌ ነው። ንጉሡ አገልጋዮቹን ወደ ተጋባዦች መላኩ እግዚአብሔር የብሉይ ኪዳንን ነቢያት የእግዚአብሔር ሕዝቦች ወደተባሉት ወደ አይሁድ መላኩን ያመለክ ታል፤ ግብዣውም ለቤተ ክርስቲያን አባልነት ነበር። እርሱም የወንጌል ተስፋ፥ የመንፈስ ቅዱስ ማጽናናት፥ የኀሊና ሰላም፥ የኃጢአት ስርየት፥ የእግዚአ ብሔር ጸጋና ፍቅሩ፥ የተረጋገጠ የዘለዓለማዊ ሕይወት ተስፋ የመሳሰሉት በረከቶች ናቸው። ነቢዩ ኢሳይያስ ቀደም ብሎ ስለ ወንጌል በረከት ሲናገር እግዚአብሔር ለዓለም ሕዘብ ታላቅ ግብዣ እንደሚያዘጋጅ ተናግሮአል (ኢሳ:ምዕ:25 ቍ:6)። አይሁድ ግን ይህን ግብዣ ከመቀበል እምቢ አሉ። እግዚአብሔርም ሌሎች መልእክተኞችን ወደ እነርሱ ላከ፤ እነርሱም የሐዲስ ኪዳን ሐዋርያት ናቸው። አይሁድ ግን ጥሪውን ተቀብለው ወደ ተዘጋጀው ግብዣ ከመምጣት ይልቅ ገበሬው ወደ ግብርናው፥ ነጋዴው ወደ ንግዱ ሄዱ። የካህናት አለቆች፥ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ግን ገበሬዎች ወይም ነጋዴዎች ባለመሆናቸው ሐዋርያትን ይዘው አዋረዱአቸው፤ ገደሉአቸው። ንጉሡ በአገል ጋዮቹ ላይ ምን እንደደረሰባቸው በሰማ ጊዜ በጣም ተቈጣና ወታደሮቹን ልኮ ገዳዮቹን አስገደለ፤ ከተማቸውንም አቃጠለ። እግዚአብሔርም በአይሁድና በከተማቸው በኢየሩሳሌም ላይ ያደረገው ይኸው ነው። የሮማ ወታደሮችን ወደ እነርሱ ልኮ እነርሱን እንዲፈጁአቸውና ከተማቸውን ኢየሩሳሌምን እንዲያቃጥሉ አደረገ። ከዚያ በኋላ ንጉሡ አገልጋዮቹን እንዲህ አላቸው:- እነሆ፥ የሠርጉ ድግስ ተዘጋጅቶአል፤ የተጠሩት ግን ለግብዣው የተገቡ አልሆኑም፤ ስለዚህ በየአደባባዩ ሂዱና ያገኛችሁትን ሰው ሁሉ ወደ ሠርጉ ግብዣ ጥሩ። አገልጋዮቹም በየመንገዱ ሄደው ያገኙትን ሰው ሁሉ ክፉዎችንም ደጎችንም ሰበሰቡ። የሠርጉም አዳራሽ በተጋባዦች ሞሉት። ይህም ማለት እግዚአብሔር አይሁድን ተገቢ ሆነው ስላላገኛቸው በእነርሱ ቦታ ሌሎች ወገኖችን ወደ ክርስትናው ጋበዘ ማለት ነው። ሐዋርያቱን ልኮ አረማውያንንና ማንንም ሳይለዩ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይጋብዙ ዘንድ አዘዛቸው። አረማውያንም ጥሪውን ስለተቀበሉ ቤተ ክርስቲያንን ሞሉአት። ነገር ግን ንጉሡ ተጋባዦቹን ለማየት ወደ አዳራሽ በገባ ጊዜ የሠርግ ልብስ ያልለበሰ አንድ ሰው በዚያ አየ። እርሱም የሠርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ አለው። ሰውየው ግን ዝም አለ። ንጉሡም አገልጋዮቹን እጅና እግሩን እሰሩና አውጥታችሁ በውጪ ወደለው ጨለማ ጣሉት፤ በዚያ ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል አለ። ይህ የሠርግ ልብስ ያልለበሰው የክርስትናን ጥምቀት ባልተጠመቀ ሰው ይመሰላል፤ ወይም እውነተኛውን የቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነት በተግባር በማያሳየው ግብዝ ሰው ይመሰላል። እንደዚህ ያሉ ሰዎች ሌሎችን አታልለው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚገቡ ናቸው። እግዚአብሔር ግን በፍርድ ቀን ማንነታቸውን ገልጦ ስለ ግብዝነታቸው ይገሥጻቸዋል። መላእክቱንም ወደ ገሀነመ እሳት እንዲጥሉአቸው ያዝዛል። እዚያም የጥፋት ጨለማ ያጠላባቸዋል። እዚያም ያሉት በቁጭትና በጸጸት ጥርሳቸውን እያፋጩ የሚኖሩ ናቸው። ይህም ማለት የሚሆነው የተጠሩት ብዙዎችና የተመረጡት ግን ጥቂቶች በመሆናቸው ነው። ይህም ማለት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚጠሩት ብዙዎች ሆነው ሳለ ለጥሪው ተገቢ መልስ የሚሰጡ ጥቂቶች በመሆናቸው፥ ወይም ጥሪውን የተቀበሉ ያስመሰሉና በልባቸው ግን ያልተቀበሉት፥ ወይም የጥሪውን ግዴታ ያልፈጸሙ ናቸው። በእምነትና በቅን ልቦና የተቀበሉት ግን እግዚአብሔር እነርሱን ለመንግሥተ ሰማይ መርጦአቸዋል፤ እነርሱም ጥቂቶች ናቸው።

በሦስቱ አገልጋዮች ምሳሌ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ሊነግራቸው የፈለገው እውነተኛ ክርስቲያን ሁልጊዜ ያለማቋረጥ በጎ ተግባርን ይፈጽማል እንጂ ዝም ብሎ የጌታችንን ዳግመኛ መምጫ ጊዜ አይጠባበቅም ለማለት ነው። የጌታው ከሄደበት አገር መመለስና ከአገልጋዮቹ ጋር መተሳሰብ የሚካሄደው ከብዙ ጊዜ በኋላ ነው። ይህም ጊዜ የሚደርሰው በመለኮታዊው ፈቃድ ሲወሰን ነው። ያም ጊዜ ሲደርስ ሁሉ ሰው ለፈጸመው ተግባር ክፉም ሆነ ደግ እንደየሥራው ዋጋውን ይቀበላል። እውነተኞቹ ክርስቲያኖች፥ የተሰጣቸውን ስጦታና ጸጋ የጠበቁ፥ ያንንም ስጦታ በእጥፍ ያሳደጉ እማኞች ክርስቶስ አገልግሎታቸውን ተቀብሎ ያመሰግናቸዋል፤ ወደ ደስታው ገብተው እንዲሳተፉ በማድረግ ዋጋውን ይከፍላቸዋል፤ ይህም ማለት ቅዱሳኑ በሰማይ ሆነው ከጌታቸው ጋር በሚደሰቱበት ደስታና ሐሴት ተሳታፊዎች ያደርጋቸዋል ማለት ነው። እውነተኞችና ታማኞች ያልሆኑት ክርስቲያኖች ግን ያን አንድ መክሊት ተሰጥቶት የደበቀውን ሰው ይመስላሉ። እነርሱ ወደ ሃይማኖቱ የሚገቡት በግዴለሽነትና ምንም ዐይነት ሃይማኖታዊ ጥረት ሳያደርጉ ለመኖር ነው። ልባቸውን በሚሞላው ክፋት ብቻ የሚኖሩ ሳይሆኑ እግዚአብሔርን እንደ ግፈኛና እንደ ጨካኝ አድርገው እየቈጠሩት የሚኖሩ ናቸው። በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር እነርሱ ሰነፍና ክፉ አገልጋይ በማለት በከፍተኛ ወቀሳ ይወቅሳቸዋል። እነርሱ በስንፍናቸው ምክንያት ክፉዎች የሆኑና በክፋታቸውም ምክንያት ሰነፎች የሆኑ ናቸው። ይህም የሚሆነው ስንፍና ወደ ክፉ ሥራ፥ ክፉ ሥራ ደግሞ ወደ ስንፍና የሚወስዱ በመሆናቸው ነው። ይህም ራሳቸውን በራሳቸው እንዲቃረኑ ያደርጋቸዋል። እነርሱም የእርሱን ጨካኝነት ስለፈሩ በጎ ነገርን አልፈጸምንም ይላሉ። እርሱን ደስ ለማሰኘት በጎውን ሥራ አይፈጽሙም ነበርን? ባይወዱት እንኳ የሚፈሩት ከሆነ የእርሱን ፈቃድ መፈጸም ነበረባቸው። እርሱ ስጦታውን የሰጣቸው እንዲጠብቁትና እንዲያዳብሩት ነበር። ይህም እርሱን ደስ ባሰኘው ነበር። ስለዚህ በተሰጣቸው ጸጋ የማይሠሩበት ሲሆን ይህ እርሱን ያስቈጣዋል። በዚህም ምክንያት ለእነርሱ የተሰጠው ስጦታ ተወስዶ ለሌሎች እርሱን የሚያስደስት ሥራ ለሠሩት ይጨመርላቸዋል። ስለዚህ ነው ጌታችን ላለው ይሰጠዋል፤ ይጨመርለታልም፤ ከሌለው ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል ያለው። ትጉሆች የሆኑት ቅዱሳን፥ ማለት በእጃቸው ያለውን ዕድል የሚጠቀሙበት እግዚአብሔር ያበዛ ላቸዋል። በተሰጣቸው ዕድል መጠቀምን ችላ የሚሉ ያ ዕድል ከእጃቸው ያመ ልጣል፤ ለዘለዓለምም ያጡታል። በተሰጣቸው መንፈሳዊ ስጦታ ተጠቅመው አገልግሎታቸውን እየጨመሩ የሚሄዱ ሁሉ የአገልግሎት ችሎታቸው እየበዛ ይሄዳል፤ የተሰጣቸውም መንፈሳዊ ስጦታ እያደገ ይሄዳል። በተሰጣቸው ስጦታ የማይሠሩበት ግን ያ ስጦታ እየቀነሰ ሄዶ በመጨረሻም ይጠፋል።

## ጥያቄዎች

1. የዘብዴዎስ ልጆችና እናታቸው ልመና ምን ነበር?
2. ጌታችን ምን መልስ ሰጣቸው?
3. በዚህ ጊዜ ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ምን አላቸው?
4. ጌታችን ከዐረገ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ ሊልክላቸው ቃል የገባላቸው ምንድነው?
5. የእውነትን መንፈስ ዓለም የማይቀበለው በምን ምክንያት ነው?
6. ደቀ መዛሙርቱስ የሚያውቁት በምን ምክንያት ነው?
7. ጌታችን፥ የሚወደው ሰው ምን ያደርጋል አለ?
8. ጌታችንን የሚወድ ሰው ማን ይወድደዋል?
9. ጌታችን ስለ እኔ ይመሰክራል ያለው ማንን ነው?
10. ሰዎች ሕፃናትን ወደ ጌታችን ያቀረቡአቸው ለምን ነበር?
11. በዚህ ምክንያት ደቀ መዛሙርቱ ምን አደረጉ?
12. ጌታችንስ ለደቀ መዛሙርቱ ምን አላቸው?
13. ጌታችን ዕውሩን እንዴት አድርጎ ፈወሰው?
14. የተፈወሰውን ዕውር ጌታችን ምን አዘዘው?

www.ethiopianorthodox.org

15. ጌታችን ድዳውን በፈወሰ ጊዜ ሰዎች ምን አሉ?
16. ፈሪሳውያንስ ምን አሉ?
17. ለምጻሙ ሰው ጌታችንን ምን ብሎ ለመነው?
18. ጌታችንስ ምን መልስ ሰጠው?
19. ከፈወሰውስ በኋላ ምን ብሎ አዘዘው?
20. የቤተ መቅደስ ግብር ሰብሳቢዎች ቅዱስ ጴጥሮስን ምን ብለው ጠየቁት?
21. ቅዱስ ጴጥሮስስ ምን መልስ ሰጠ?
22. ጌታችንስ ቅዱስ ጴጥሮስን ምን ብሎ ጠየቀው?
23. ከዚያስ ጌታችን ቅዱስ ጴጥሮስን ምን ብሎ አዘዘው?
24. ስለ በለሱ ዛፍ ምሳሌ ተናገር።
25. በሠርጉ ግብዣ ምሳሌ የተጋበዙት ሰዎች ግብዣውን አክብረው መጡን?
26. የሠርጉን ግብዣ ያዘጋጀው ሰው ለሦስተኛ ጊዜ አገልጋዮቹን የላካቸው ወዴት ነው?
27. ንጉሡ ተጋባዦቹን ለማየት ወደ አዳራሽ በገባ ጊዜ ምን አየ?
28. ከዚያስ ምን ጥያቄ ጠየቀ? አገልጋዮቹንስ ምን ብሎ አዘዛቸው?
29. ወደ ሌላ አገር ለመሄድ የተነሣው ሰው ለሦስት አገልጋዮቹ ስንት ስንት መክሊት ሰጣቸው?
30. እነዚያስ ሦስቱ አገልጋዮች በመክሊቶቹ ምን አደረጉባቸው?
31. ጌታቸው ከውጪ ሲመጣ አገልጋዮቹ ለጌታቸው ምን አሉት? እርሱስ ምን መልስ ሰጣቸው?
32. ደቀ መዛሙርቱ ስለጌታችን ምን ይመስላቸው ነበር?
33. በዚህስ ምክንያት የዘብዴዎስ ልጆች ምን አደረጉ?
34. ጌታችንስ ለዘብዴዎስ ልጆች ምን እንደሚጠብቃቸው ነገራቸው?
35. የሰማያዊ ክብር ደረጃዎች የተዘጋጁት እንዴት ነው?
36. የሁለቱ ወንድማማች ጥያቄ በደቀ መዛሙርቱ ዘንድ ምንን አስከተለ?
37. በዚህ ጉዳይ ላይ ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ምን ዐይነት ትምህርት ሰጣቸው?
38. በመንግሥተ ሰማይ ትልቅ ለመሆን የሚቻልበት መንገድ የትኛው ነው?
39. ጰራቅሊጦስ የተባለው ቃል በምን በምን ቃላት ይተረጐማል?
40. የእውነት መንፈስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያከብረው በምን ዐይነት ነው?
41. የሰው ዘር በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ሰይጣን ምን ዐይነት ሥልጣን አገኘ?
42. ዓለም የእውነትን መንፈስ መቀበል የማይችለው በምን ምክንያት ነው?
43. ደቀ መዛሙርቱ በበዓለ ኀምሳ ቀን በምን ተሞሉ?
44. ሕፃናት ይዘው ወደ ጌታችን የመጡትን ሰዎች፥ ደቀ መዛሙርቱ የተቃወሙአቸው በምን ምክንያት ነው?
45. ሕፃናት እንደ ሰማይ መላእክት ናቸው የሚባለው በምን ምክንያት ነው?
46. ጌታችን ዕውሩን ሰው ለመፈወስ ከቤተ ሳይዳ ውጪ ይዞት የሄደው በምን ምክንያት ነው?
47. ጌታችን ዕውሩን ሰው በአንድ ጊዜ ሊፈውሰው ሲችል በየደረጃው ቀስ በቀስ የፈወሰው ለምንድነው?
48. መፈወሱንም እንዳይናገር ያዘዘው በምን ምክንያት ነው?
49. በኦሪት ሕግ ለምጻም ሰውን መንካት ክልክል ሲሆን ጌታችን ለምጻሙን ሰው እንዴት ነካው?
50. ከፈወሰው በኋላ ምን ብሎ አዘዘው?
51. ስለ ቤተ መቅደስ ግብር በመክፈል ታሪክ ውስጥ ሁለት የምናገኛቸው ትምህርቶች ምንና ምን ናቸው?
52. ጌታችን የተለያዩ ምልክቶችን ከተናገረ በኋላ ይህ ከመሆኑ በፊት ይህ ትውልድ አያልፍም ያለው ስለምን ጉዳይ ነው?



53. ሰዎች የጌታችን ዳግመኛ መምጫ ጊዜ በቅርብ ቀን ይመስላቸው የነበረው በምን ምክንያት ነው?
54. በሠርጉ ድግስ ምሳሌ ንጉሡ አገልጋዮቹን መላኩ በምን ይመሰላል?
55. ሌሎች መልእክተኞች መላካቸውስ በምን ይመሰላል?
56. ንጉሡ ወደየአደባባዩ ሄደው ያገኙትን ሰው ሁሉ ወደ ግብዣው እንዲጠሩ ማድረጉ በምን ይመሰላል?
57. ንጉሡ ወደ አዳራሹ ገብቶ ያየው የሠርግ ልብስ ያልለበሰ ሰው በምን ይመሰላል?
58. ጌታው ወደ ሩቅ አገር መሄዱ በምን ይመሰላል?
59. የጌታውስ ከጊዜ በኋላ መመለስ በምን ይመሰላል?

# ምዕራፍ 4

# ቤተ ክርስቲያን

## ቤተ ክርስቲያንና ሲኖዶሶችዋ

ሲኖዶስ ማለት ቃሉ ግሪክ ሲሆን ስብሰባ ወይም ጉባኤ ማለት ነው። በተለየም የዓለም አብያተ ክርስቲያን ለተለያዩ ጉዳዮች ተሰብስበው ውሳኔ ያሳለፉባቸው ስብሰባዎች ሲኖዶሶች ይባላሉ። እንደነዚህ ያሉትም የቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች የተጀመሩት በጊዜአቸው ትላልቅ መንግሥታት የነበሩት አገሮች ክርስትናን ብሔራዊ ሃይማኖት ባደረጉበት ጊዜ ነው። ክርስቲያኖች ሁሉ በእምነትና በአምልኮ ሳይለያዩ አንድ በነበሩበት ዘመን የሃይማኖት ችግር በሚያጋጥምበት ጊዜ ሁሉ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚገኙ የሃይማኖት መሪዎች በአንድነትና በአንድ በተወሰነ ቦታ እየተሰበሰቡ ለተከሠተው ችግር የመፍትሔ ውሳኔ ያሳልፉ ነበር። በኬልቄዶን ጉባኤ ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ወገን ከመከፈልዋ በፊት አብያተ ክርስቲያን ሁሉ መንፈሳዊነታቸውን አምነው በይፋ የሚቀበሉአቸው ሦስት ሲኖዶሶች ወይም ጉባኤዎች የኒቅያ፥ የቍስጥንጥንያና የኤፌሶን ጉባኤዎች ናቸው። በ451 ዓ.ም. በኬልቄዶን የተሰበሰበው ጉባኤ ግን በወገናዊነት፥ በአድልዎና በተንኰል የተሞላና ዓላማውም ዲዮስቆሮስን ለመበቀል የተሰበሰበ፥ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ያለያየ መንፈሳዊነት የጐደለው ጉባኤ ስለነበረ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያን አይቀበሉትም።

<u>የኒቅያ ጉባኤ</u>:- የኒቅያ ጉባኤ የተሰበሰበው በ325 ዓ.ም. በንጉሥ ቈስጠንጢኖስ ዘመን ነው። የስብሰባውም ዋና ዐላማ በአርዮስ የክሕደት ትምህርት ላይ ለመነጋገር ነበር። የአርዮስም የክሕደት ትመህርት ወልድ ፍጡር ነው የሚል ነበር። በእርሱ አባባል እግዚአብሔር አብ፡ ወልድን ፈጥሮ የአምላክነትን ሥልጣን ሰጠው። ሁሉንም ነገር ለመፍጠር የቻለው እግዚአብሔር በሰጠው ሥልጣን ነው ብሏል። በጉባኤው ላይ የተገኙት ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት ኤጲስ ቆጶሳት ነበሩ። በስብሰባው ከተገኙት ሰዎች መካከል የግብጹ ቤተ ክርስቲያን መሪ እለስክንድሮስና የእርሱ ረዳት የነበረው ሊቀ ዲያቆን አትናቴዎስ ይገኙበታል። ይህም አትናቴዎስ ለኒቅያ ጉባኤ መሳካት ትልቅ አስተዋፅኦ ያደረገና ከእለስክንድሮስ በኋላ ፓትርያርክነቱን የተረከበ ነው። ስለ ቤተ ክርስቲያንም ከአርዮሳውያን ጋር ታላቅ ተጋድሎ ያደረገ ነው።

አርዮርስ በእስክንድርያ የክሕደት ትምህርቱን ማሠራጨት የጀመረው የግብጽ ቤተ ክርስቲያን መሪ በነበረው በተፍጻሜተ ሰማዕት ጴጥሮስ ጊዜ ነው። አርዮስ ከክሕደቱ እንዲመለስ ፓትርያርኩ ብዙ ምክር ቢሰጠውም እርሱ ግን በክሕደቱ ስለጸና ከአንዴም ሁለቴ በጳጳሳት ጉባኤ እንዲወገዝ አድርጓአል። ፓትርያርኩ ለሰማዕትነት የተቃረበ መሆኑን በተገነዘበ ጊዜ ግዝቱ ሳይፈታው እንዳይሞት ስለሰጋ ከግዝቱ እንዲፈታው በመለመን አርዮስ ወደ ፓትርያርኩ አማላጅ ልኮ ነበር። ፓትርያርኩ ግን የበለጠ ከመገዘቱም በላይ ለደቀ መዛሙርቱ ለአርኬላኦስና እለስክንድሮስ እንዳይቀበሉት አዘዛቸው። ፓትርያርኩ ጴጥሮስ በሰማዕትነት ከሞተ በኋላ አርኬላኦስ መንበሩን ሲረከብ አርዮስን ተቀብሎ የአንድ ቤተ ክርስቲያን ካህን በማድረግ ሾመው። ይሁን እንጂ አርኬላኦስ ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ መንበሩን እለስክንድሮስ ተረክቦ የአርዮስን አባረረው። በዚህ ጊዜ አርዮስ ደጋፊዎች የነበሩ ጳጳሳት አርዮስ እንደተበደለ በማስመሰል ለንጉሥ ቈስጠንጢኖስ አቀረቡለት። ንጉሥ

www.ethiopianorthodox.org

ቈስጠንጢኖስም ጉዳዩን የሚያጠና መልእክተኛ ወደ እስክንድርያ ልኮ ካጣራ በኋላ በኒቅያ ከተማ ጉባኤ እንዲደረግ ጥሪ አስተላለፈ።

ጉባኤ ተሰብስቦ አርዮስ እምነቱን እንዲያብራራ በተጠየቀ ጊዜ በወልድ ላይ ያለውን ክሕደት ግልጥ አደረገ። የእርሱ ትምህርት ስሕተት መሆኑን በመዘ ርዘር ብዙ ማስረጃዎች ቢቀርቡለትም ከክሕደቱ ፈቀቅ የማይል ሆኖ ባገኙት ጊዜ አውግዘውታል። እርሱንም ካወገዙ በኋላ ጸሎተ ሃይማኖት የተሰኘውን የሚከተለውን የእምነት ቀኖና ደንግገዋል።

«ሁሉን በያዘ፡ ሰማይንና ምድርን፡ የሚታይና የማይታየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን። ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ በተወለደ የአብ አንድያ ልጅ በሚሆን በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን። ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፡ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ፡ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ፡ በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል፣ ሁሉ በእርሱ የሆነ፣ ስለ እኛ ስለ ሰዎች እኛን ለማዳን ከሰማይ ወረደ፡ በመንፈስ ቅዱስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆነ፤ ሰው ሆኖም በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ ተሰቀለ፤ ታመመ፤ ሞተ፤ ተቀበረ፤ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ፥ በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ፤ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ፤ ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ በጌትነት ይመጣል፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ ለውም።»

ጉባኤውም አርዮስን ካወገዘ በኋላ ስለ መናፍቃን ጥምቀት፡ ስለ ትንሣኤ በዓል አከባበር፤ ስለ ድንግልና ኑሮ፡ መላትዮስ ስለተባለው ኤጲስ ቆጶስ ጉዳዮች ቀርበውለት ውሳኔ አሳልፎባቸዋል።

<u>ስለ መናፍቃን ጥምቀት</u>:- መናፍቃን የተጠመቁት በመናፍቅነታቸው እንዳሉ ከሆነና ከዚያ በኋላ ወደ ትክክለኛው የክርስትና እምነት ለመመለስ ከፈለጉ በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንደገና መጠመቅ ይኖርባ ቸዋል፤ ነገር ግን ቀደም ብለው በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠም ቀው የነበሩና ከዚያ በኋላ ወደ መናፍቃን ጐራ የገቡ ከሆነ ወደ እውነተኛው እምነት በሚመለሱበት ጊዜ ሌላ ጥምቀት አያስፈልጋቸውም ብሎ ጉባኤው ወሰነ።

<u>ስለ ትንሣኤ በዓል አከባበር</u>:– ስለ ትንሣኤ በዓል አከባበር በዘመን አቈጣጠር መጽሐፍ ውስጥ የተመዘገበውን አባባል ቀጥለን እንመልከት:-

«ሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የትንሣኤ በዓልን በተመለከተ ክርስቲያ ኖችን ለሁለት ከፍሎ ሲያከራክር የኖረ ዘመን ነው። (1) በትንሽዋ እስያ፡ በኪልቅያ፡ በሁለቱ ወንዞች መካከ ልና በሶርያ የነበሩ ክርስቲያኖች የስቅለትን በዓል የሚያከብሩት ኒሳን በተባለው የዕብራውያ ወር በ14ኛው ቀን ነበር። በዓለ ትንሣኤውን ደግሞ በኒሳን 16 ቀን ያከብሩት ነበር። እነዚህም በዓላት ከሳምንቱ ቀኖች በማናቸውም ቀኖች ቢውሉ ግድ አልነበራቸውም። ጾማቸውንም የሚፈስኩት የስቅለትን በዓል በሚያከብሩበት ቀን ነበር። ለዚህም ድርጊታቸው የሚሰጡት ምክንያት ይህ ቀን የሰው ልጆች ከኃጢአት ባርነት ነጻ የወጡበት ቀን ስለሆነ ነው የሚል ነው። እነርሱም የስቅለትን በዓል በሐዘን ካሳለፉ በኋላ ወዲያው ከትንንሣኤ በፊት ይፈስኩ ነበር። (2) በግሪክ፡ በግብጽ፡ በፍልስጥኤምና በዐረብ አገሮች የነበሩ ክርስቲያኖች ግን ኒሳን ዐሥራ አራትንና ኒሳን ዐሥራ ስድስትን ለስቅለትና ለትንሣኤ መታሰቢያ የበዓል ቀኖች አድርገው አላከበሩአቸውም። ይህንንም ያደረጉት ጌታችን የተሰቀለውና የሞተው በዓርብ ቀን ሲሆን የተነሣው ደግሞ በእሑድ ቀን በመሆኑ ነው። በዚህ መሠረት እነዚህኞዎቹ ወገኖች ስቅለትን የሚያከብሩት በዓርብ ቀን ሲሆን ትንሣኤን የሚያከብሩት ደግሞ በእሑድ ቀን ነበር።

«የኒቅያ ጉባኤ የትንሣኤ በዓል ከአይሁድ የፋሲካ በዓል በኋላ በሚመጣው እሑድ እንዲከበር በመወሰን በአብያተ ክርስቲያን መካል የነበረውን ክርክር አስወገደ። በዓሉ የሚውልበትን ቀን የእስክንድርያው ቤተ ክርስቲያን መሪ በየዓመቱ እንዲያሳውቅ ወሰነ።»

<u>ስለ ድንግልና ኑሮ</u>:- የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሁሉ በድንግልና መኖር አለባቸው ተብሎ የቀረበው ሐሳብ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ካህናት ሚስት ያገቡ እንዲሆኑና ጳጳሳት ብቻ በድንግልና እንዲኖሩ ተወሰነ፤ እንዲሁም ሚስቶ ቻቸው የሞቱባቸው ካህናት እንደገና እንዲ ያገቡ ተብሎ ተወሰነ።

<u>መላትዮስ፡ የአስዩት ኤጲስ ቆጶስ</u>:- የአስዩት ኤጲስ ቆጶስ የነበረው መላትዮስ በዲዮ ቅልጥያኖስ ክርስቲያኖችን ማሳደድ ምክንያት ታስሮ ነበር። በእስር ቤት ሳለ ኤጲስ ቆጶሳት ጓደኞቹ አይዞህ እያሉ ቢመክሩትና ቢያበረታ ቱትም እንኳ ምክራቸውን ሳይቀበል ቀርቶ ለምድራዊ ሕይወቱ በመፍራት ለጣዖት አጠነ። ከእስር ቤት ከወጣ በኋላ ንስሐ የገባ ይሁ



እንጂ የፓትርያርክን ተግባር በመሻማት ሥርዓት አልባ ሆነ፤ እርሱም ኤጲስ ቆጶሳትን ራሱ ይሾም ጀመር። በዚህም ሥራው ፓትርያርኩ ተፍጻሜተ ሰማዕት ጴጥሮስ የጳጳሳትን ጉባኤ ሰብስቦ አውግዞታል። የኒቅያ ጉባኤም መላትዮስን ከማንኛውም የክህነት ሥልጣን ሽሮ ተራ ሰው እንዲሆን ወስኖበታል።

<u>ጳውሎስ ሰምሳጢ</u>

ጳውሎስ ሳምሳጢ በሦስተኛወ ምእት ዓመት በታናሽ እስያ በሶርያ ውስጥ በሳምሳታ ከሀብታም ወገን የተወለደ መናፍቅ ጳጳስ ነበር። ሳምሳጢ እየተባለ መጠራቱ በትውልድ ሀገሩ በሳሞሳታ ነው። በአንጾኪያ ትምህርት ቤት ተምሮአል፤ ነገር ግን የቀጥተኞቹን የአንጾኪያ ትምህርት ቤት ሊቃውንት ፈለግ አልተከተለም።

ጳውሎስ ሳምሳጢ የኑፋቄ ትምህርቱ ከመከሠቱ በፊት በ260 ዓ.ም. የአንጾኪያ ጳጳስ ሆኖ ተሾሞአል። በጵጵስናውም ዘመን ቀድሞ ደብቆት የኖረ ውን በምሥጢረ ሥላሴና በምሥጢረ ሥጋዌ ላይ የነበረውን ክሕደቱን አውጥቶ ማስተማር ጀመረ።

1ኛ. በመሥጢረ ሥላሴ ላይ የነበረ ክሕደቱ:- ቃል ከሥጋዌ በፊት በአካላዊነት አልነበረም፤ ግን እንደ ሰው ድምፅ ወይም ቃል በአብ አካል ውስጥ ያለ ዝርው ቃል፡ ዝርው ኃይል ነበረ። በዚህም አስተሳሰቡ:- ጳውሎስ ሳምሳጢ እግዚአብሔር አንድ አካል፡ አንድ ገጽ እንደ ሆነ ያምን ነበር ማለት ነው። ይህም ትምህርቱ በምንም ይዘቱ ከሰባልዮስ ትምህርት ያልተለየ ነው።

2ኛ. ስለ ምሥጢረ ሥጋዌም ሲያስተምር እንዲህ ይል ነበር:- ድንግል ማርያም የወለደችው ኢየሱስ ዕሩቅ ብእሲ ማለት አምላክነት የሌለው ሰው ነው። ይኸው የድንግል ማርያም ልጅ በዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ በአብ አካል ውስጥ የነበረው ዝርው ቃል መጥቶ አደረበት፡ ከዚያም በኋላ ኢየሱስ በተጋድሎውና በትሩፋቱ የእግዚአብሔር የጸጋ ልጅ ሆነ። የእግዚአብሔር ቃል በዮርዳኖስ በማርያም ልጅ ላይ ባደረ ጊዜ በጸጋ አምላክ አደረገው በማለት ምሥጢረ ሥጋዌን ኀድረትና ጸጋ አድርጎ ለተከታዮቹ መርዙን ይነዛ ነበር።

ከዚህም ጋር ቃል በኢየሱስ ላይ ማደሩ እስከ መስቀል ድረስ ነው፡ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ ግን ቃል ተለይቶት ሄደ ይል ነበር።

ባጠቃላይ ጳውሎስ ሳምሳጢ የቃልን ቅድምና በመካዱ ምሥጢረ ሥላሴን አፋልሶአል፤ የክርስቶስን አምላክነትና የድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክነት ክዶአል። በዚህም ምክንያት በ268 ዓ.ም. በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ ተወግዞ ሲለይ ትምህርቱም ተቀባይነት እንዳይኖረው ተወግዞአል።

በጳውሎስ ሳምሳጢ ትምህርት አምነው የተጠመቁ ቢኖሩ ጥምቀታቸው በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ስላልተፈጸመ እንዳልተጠመቁ ተቈጥሮ ዳግመኛ እንዲጠመቁ በኒቅያው ጉባኤ ቀኖና ላይ «ከጳውሎስ ሳምሳጢ የተጠመቀ ቢኖር ዳግመኛ ያጥምቁት» ሲል ውሳኔ አስተላልፎአል።

<u>የኒቅያ ጉባኤ ቀኖናዎች:</u>

ጉባኤው ከመፈጸሙ በፊት የተሰበሰቡት አባቶች የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር በሚመለከት ኻያ ቀኖናዎችን ደንግገዋል።

1. በሕመም ምክንያት ሐኪሞች ጃንደረባ ያደረጉት፡ ጠላት በማጥቃት ጃንደረባ ያደረገው፤ ወይም አለቃው ለቤቱ ጠባቂነት ሲል ጃንደረባ ያደረገው ሰው ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ብቁ ሆኖ ከተገኘና ወደ ክህነት አገልግሎት ለመግባት ቢፈልግ ሕጉ ይፈቅድለታል። ራሱን በፍላጎቱ ጃንደርባ ያደረገ ሰው ማዕረገ ክህነት አይፈቀድለትም። በክህነት አገልግሎት ላይ እያለ ራሱን ጃንደረባ ያደረገ ሰው ከክህነት ሥልጣን መሻር ይኖርበታል።

2. በጣም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ወይም በግዴታ ሊሆን ቢችልም የቤተ ክርስቲያንን ቀኖና የሚቃረኑ ብዙ ሁናቴዎች ተፈጽመዋል። ከአረመኔነት ገና አዲስ የመጡ ሰዎች ጥቂት ጊዜ ብቻ ትምህርት ከተሰጣቸው በኋላ በቶሎ ተቀባይነት አግኝተው ወዲያው እንደተጠመቁ ለኤጲስ ቆጶስነት ወይም ለክህነት ይመደባሉ። ከእንግዲህ ወዲህ ግን እንደዚህ ያለው ጉዳይ መከልከል አለበት። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም አዲስ አማኝ ከጥምቀት በኋላ በቂ የልም ምድ ጊዜ ሊኖረው እንደሚገባ ሲያስረዳ «በትዕቢት ተነፍቶ ዲያብሎስ እንደተፈረደበት እንዳይፈ ረድበት አዲስ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያን መሪ አይሁን» ብሏል (1ኛ ጢሞ.ም3 ቍ.6)።



www.ethiopianorthodox.org

3. ከእናቱ ከእኅቱ ከአክስቱ ወይም በእንደዚህ ያለ ሁናቴ ከማትታሰብ ሴት ጋር ካልሆነ በቀር አንድ ኤጲስ ቆጶስ፥ አንድ ካህን፥ አንድ ዲያቆን፥ ወይም ሌላ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ከማንኛዋም የውጪ ሴት ጋር አብሮ እንዳይኖር ታላቁ ጉባኤ በጥብቅ ከልክሏል።

4. ኤጲስ ቆጶስ የሚሰየመው ቢቻል በሀገረ ስብከቱ በሚገኙት ኤጲስ ቆጶሳት እጅ ሆኖ አለበለዚያ ግን ቢያንስ በሦስት ኤጲስ ቆጶሳት እጅ መሆን ይኖርበታል። ለዚሁም ቀሪዎቹ በምርጫው የተስማሙ መሆናቸውን በጽሑፍ ሊያረጋግጡ ይገባል። ሆኖም አንብሮት እዱ በርእስ ኤጲፋስ ቆጳሳቱ አማካይነት ካልሆነ አይጸናም።

5. በየሀገረ ስብከቶች ኤጲስ ቆጳሳት ከኅብረት ስለከለከሉአቸው ካህናት ወይም ምእመናን ወገኖች በሌሎች ዘንድ ተቀባይነት እንዳያገኙ የሚወሰነው አስተያየት በሕጉ መሠረት ይጠበቅ። የተከለከሉበት ምክንያት ምንአልባት ከመንፈስ ደካማነት የተነሣ፥ ወይም በመጣላት፥ ወይም ደግሞ የኤጲስ ቆጶሱ የግል ጥላቻ እንዳይሆን ምርመራ ያድርጉ። ተመሳሳይ ሁናቴዎችን ለመመርመር የየሀገረ ስብከቱ ኤጲስ ቆጳሳት በአጠቃላይ በዓመት ሁለት ጊዜ መሰብሰብ ይኖርባቸዋል። ሁለቱ ስብሰባዎች መካሄድ ያለባቸው አንዱ ከዐቢይ ጾም በፊት ለእግዚአብሔር ንጹሕ ስጦታ ለማቅረብና ሁለተኛው ደግሞ በመጸው ነው። በኤጲስ ቆጶሱ ላይ በደለኞች ሆነው የተገኙ ሰዎች የኤጲስ ቆጳሳቱ ጉባኤ ይቅርታ እስኪያደርግላቸው ድረስ ከኅብረት የተከለከሉ ይሆናሉ።

6. በግብጽ፥ በሊብያና በአምስቱ ከተሞች ከቀድሞ ጀምሮ የነበረው ልማድ እንደተጠበቀ ይኖራል። ይህም ልማድ የእስክንድርያው ኤጲስ ቆጶስ ሥልጣን በሦስቱ ሁሉ ላይ እንደሆነ የሮማው ኤጲስ ቆጶስም የዚሁ ዐይነት ልማድ አለው። የአንጾኪያ መንበርና ሌሎችም ሀገረ ስብከቶች ይህንኑ ልማድ ይከተሉ። በአጠቃላይ አንድ ኤጲስ ቆጶስ ያለ ርእስ ኤጲስቆጶሳቱ (ሜትሮፖሊቱ) ፈቃድ መሾም የማይገባው መሆኑን ታላቁ ጉባኤ ወስኖአል። የሁለቱ ወይም የሦስቱ አስተያየት ከሌሎቹ ኤጲስ ቆጳሳት የተለየ ቢሆን በቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠረት በድምፅ ብልጫ ይወሰን።

7. ከቀድሞ ጀምሮ ተያይዞ በመጣው ልማድና ባህል (ትውፊት) እንደተመለከተው የኢየሩሳሌሙ ኤጲስ ቆጶስ የተለየ ክብር አለው። ድርጊቱ ዋናይቱ ከተማ ቂሣርያ ያላትን ክብር የማይጐዳ ሆኖ ለኢየሩሳሌሙ ኤጲስ ቆጶስ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል።

8. ንጹሓን ነን የሚሉ ሰዎች ራሳቸውን ዓለም ዐቀፋዊትና ሐዋርያዊት ወደሆነችው ቤተ ክርስቲያን ሲያቀርቡ አንብሮተ እድ ተደርጎላቸው በዚሁ ሁናቴ ወደ ክህነት አገልግሎት ሊገቡ እንደሚችሉ ታላቁ ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ አሳለፈ። ከዚያ ሁሉ በፊት ግን የቤተ ክርስቲያንን አንድነት እንደሚፈልጉ ሥርዓትዋንም እንደሚያከብሩ በጽሑፍ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

9. ሁናቴአቸው ሳይመረመር ካህናት የሆኑ ሰዎች ወይም ሁናቴአቸው ሲመረመር ስለኃጢአታቸው ከተናዘዙ በኋላ በሕገወጥ መንገድ ቢሾሙ እንደዚህ ያሉትን ቀኖናው የማይቀበላቸው ቤተ ክርስቲያን የምትፈልገው ነቀፋ የሌለበትን መሪ በመሆኑ ነው (1ኛ ጢሞ.ም.3ቍ.2)።

10. ማንኛውም ኃጢአተኛ ሰው ማንነቱ ባለመታወቁ ወይም በሿሚው ዘንድ እየታወቀ አንድ የክህነት ደረጃ ቢሾም ሕግ የሚያዝዘው ይፈጸምበታል። ይህም ማለተ ከሹመቱ መሻር ማለት ነው።

11. ሳይገደዱ፥ ምንም ንብረት ሳይወሰድባቸው፥ ያለ ምንም አደጋ ማለት በአምባ ገነኑ በሊኪኒዩስ ዘመን እንደተደረገው ያለ ችግር ሳይደርስባቸው ለወደቁ ሰዎች ሁሉ ርኅርኄ ማድረግ ለጉባኤው አስፈላጊ ሆኖ ታይቶታል። እውነተኛ ጸጸትን የተጸጸቱ ሰዎች ሦስት ዓመት ከሰሚዎች ጋር ማሳለፍ ይኖርባቸዋል፤ ሰባት ዓመት ይስገዱ። ቅዱስ ቍርባንን ሳይቈርቡ ለሁለት ዓመት ከሕዝቡ ጋር በጸሎት ይሳተፉ።

12. በጸጋ የተጠሩና የመጀመሪያውንም እርምጃ ያሳዩ፥ ከዚያ በኋላ ግን ያንን ትተው እንደ ውሾች ወደ ትውከታቸው ከተመለሱት ጥቂቶች ወደ ውትድርናው ለመመለስ ፈልገው ብርና ስጦታ የሰጡት ሰዎች ሁናቴአቸው የሚወሰነው ከሰሚዎች ጋር ሦስት ዓመት ከፈጸሙ በኋላ ዐሥር ዓመት እንዲሰግዱ ነው። ከዚህ ሁሉ ጋር ዝንባሌአቸውና የንስሓቸው ሁናቴ ሊመረ መር ይገባል። አመላለሳቸው በፍርሀት፥ በእንባ፥ በትዕሥትና በበጎ ተግባር እንጂ በማስመሰል ብቻ አለመሆኑ ከታየ የመስሚያውን ጊዜ ከፈጸሙ በኋላ በጸሎት ሊሳተፉ ይገባል። ከዚያም በኋላ ኤጲስ ቆጶሱ ሁናቴአቸውን በበለጠ ርኅርኄ ሊመለከትላቸው ይችላል። ወደ ቤተ ክርቲያን



www.ethiopianorthodox.org

መመለሳቸውን ብቻ በቂ ነው ብለው የሚያስቡና ግድ የሌላቸው ሰዎች ግን የተወሰነውን ዘመን ይፈጽሙ።

13. የጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን ደንብ እንደሚያመለክተው አንድ ለሞት የተቃረበ ተነሳሒ ቅዱስ ቍርባንን ለመቀበል የሚፈቀድለት ሲሆን ከዚያ በኋላ ከሕመሙ ቢፈወስ ግን ብቁ መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር በሞት አፋፍ ላይ በነበረ ጊዜ በመቍረቡ ብቻ ከዳነም በኋላ ለመቍረብ ብቁ ሆነ ማለት ባለመሆኑ ብቁ እስኪሆን ድረስ ክፍሉ ለመቍረብ ገና ከሆኑ ጸሎተኞች ጋር ኅብረት እንዲኖረው ነው።

14. የሃይማኖት ደቀ መዛሙርት በኃጢአት ቢወድቁ ሦስት ዓመት ከሰሚዎች ጋር ካሳለፉ በኋላ ከሃይማኖት ደቀ መዛሙርት ጋር እንዲጸልዩ ይፈቀድላቸው ዘንድ ታላቁ ቅዱስ ሲኖዶስ ወሰነ።

15. በብዙ ሁከትና ጠብ ምክንያት በአንዳንድ ቦታዎች ያለው ልማድ በፍጹም እንዲቀር አስፈለገ። የአንድ ኤጲስ ቆጶስ፥ የአንድ ካህን፥ ወይም የአንድ ዲያቆን ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ መዘዋወር ሐዋርያዊውን ሕግ የሚቃረን አሠራር ነው።

16. ፈሪሀ እግዚአብሔር ሳይኖራቸውና የቤተ ክርስቲያንን ቀኖና ሳያውቁ ቤተ ክርስቲያናቸውን ትተው ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱ ቀሳውስት፥ ዲያቆናትና ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በሌላ ቤተ ክርስቲያን ተቀባ ይነት ሊኖራቸው አይገባም። ወደ ነበሩበት ቤተ ክርስቲያን መመለስ ይኖርባ ቸዋል። እንቢ ብለው ቢሄዱ ግን ኅብረት እንዳይፈ ቀድላቸው መደረግ አለበት። አንድን ቤተ ክርስቲያን ትቶ ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን የሄደን ሰው ከመጣባት ቤተ ክርስቲያን ፈቃድ ሳያገኝ አንድ ኤጲስ ቆጶስ በድፍረት ክህነትን ሰጥቶ ቢቀበለው ያ ሹመቱ ዋጋ የሌለው ይሆናል።

17. «ገንዘቡን በአራጣ የማያበድር ... ለዘላለም አይታወክም» የሚለውን ቃለ እግዚአብሔር ረስተው አስከፊ የሆነውን ሥሥትና ወራዳ የሆነውን አራጣ በመፈለግ ብዙዎች ሰዎች ገንዘባቸውን በአራጣ ያበድራሉ (መዝ.15 ቍ:5)።

ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ለመኖሪያው እንኳ ቢሆን ይህ ቀኖና ከተደነገገበት ጊዜ ጀምሮ በአራጣ ገንዘብ አበድሮ ቢገኝ ከሢመተ ክህነት ተሽሮ ተራ ሰው እንዲሆን ጉባኤው ወስኖአል።

18. በአንዳንድ ከተማዎችና በአንዳንድ ቦታዎች ዲያቆናት ለቀሳውስት ሥጋ ወደሙ የሚያቀብሉ መሆናቸውን ይህ ታላቁ ሲኖዶስ ለማወቅ ችሏል። ይህ ድርጊት በሕጉም በኩል ሆነ በትውፊቱ ቍርባኑን ለማቅረብ ሥልጣን ያላቸው ወገኖች ከሚያቀርቡላቸው መገኖች የጌታን ሥጋ መቀበል ከመሠረቱ ያልተረከብነው ነው። እንዲሁም አንዳንድ ዲያቆናት ከኤጲስ ቆጳሳት በፊት እንደሚቈርቡ ታውቋል። ይህ ሁሉ ድርጊት ቀርቶ ዲያቆናት ከወሰናቸው አይለፉ። የኤጲስ ቆጳሳት አገልጋዮች መሆናቸውንና ደረጃቸውም ከቀሳውስት ዝቅ ያለ መሆኑን ተገንዝበው ማንነታቸውን ይወቁ። የሚቈርቡት ከቀሳውስት በኋላ ሆኖ የሚያቈርባቸውም ኤጲስ ቆጶሱ ወይም ቄሱ ነው። እንዲያውም ዲያቆናት በቀሳውስት መካከል መቀመጥ የለባቸውም፤ ምክንያቱም ይህ ድርጊት ሕግንና የደረጃ ቅደም ተከተልን ይቃረናልና። ከዚህ ውሳኔ በኋላ ራሱን ዝቅ ለማድረግ የማይፈልግ ዲያቆን ካለ ከዲቁና አገልግሎት መታገድ ይኖርበታል።

19. የጳውሎስ ሳምሳጢ ተከታዮች የነበሩ ወደ ዓለም ዐቀፋዊቱ ቤተ ክርስቲያን በሚመ ለሱበት ጊዜ የግድ እንደገና በሥላሴ ስም መጠመቅ ይኖርባቸዋል። ቀድሞ ካህናት የነበሩና ነቀፋ የሌለባቸው ከሆኑ ከተጠመቁ በኋላ የዓለም ዐቀፋዊት ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ ሊሾማቸው ይገባል። ከምርመራ በኋላ ግን ነቀፋ ከተገኘባቸው ይሻራሉ።

20. አንዳንድ ሰዎች በዕለተ እሑድና በበዓለ ኀምሳ በጉልበታቸው ተንበርክከው ይጸልያሉ። በነዚያ ቀኖች ግን ሰዎች ሁሉ ቆመው እንዲጸልዩ ለሁሉም በያለበት ሕግ ይሆን ዘንድ ቅዱሱ ሲኖዶስ ወሰኗል።

<u>የቍስጥንጥንያ ጉባኤ:</u>- የቍስጥንጥንያ ጉባኤ የተሰበሰበው በ381 ዓ.ም. በትልቁ ቴዎዶስ ዮስ ዘመን ነው። ጉባኤው የተሰበሰበባቸው ምክንያቶች የመቅዶንዮስ፥ የአቡሊናርዮስና የአውሳብዮስ ክሕደቶች ናቸው።

<u>መቅዶንዮስ</u>:- መቅዶንዮስ የቍስጥንጥንያ ፓትርያርክ ነበር። እርሱም ከአርዮሳውያን ወገን ስለ ነበረ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ያነሰ መሆኑን በመግለጥ እንደ አርዮሳውያን ሁሉ በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት ላይ የክሕደት ትምህርቱን አሠራጨ። በዚያን ጊዜ በንጉሥ

ቴዎዶስዮስ ጋባዥነት [illegible] ኤጲስ ቆጶሳት የተገኙበት ጉባኤ በቍስጥንጥንያ ከተማ ተካሄደ። ጉባኤውም መቅዶንዮስን ስለ እምነቱ በጠየቀው ጊዜ ወልድ ሁሉንም ነገር የፈጠረ በመሆኑና እርሱ ያልፈጠረው ነገር ስለሌለ መንፈስ ቅዱስም በወልድ የተፈጠረ ነው ሲል መልስ ሰጠ። ጉባኤው ስለአብ፥ ስለ ወልድና ስለ መንፈስ ቅዱስ አለመበላለጥና እኩልነት የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎችን አቅርቦለታል። ከቀረቡትም ማስረጃዎች መካከል በትንቢተ ኢሳይያስ ም:6ቍ:3ላይ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ቅዱስ ነው የሚለውና ጌታችን በማቴዎስ ወንጌል፥ ም:28ቍ19 ላይ ከዕርገቱ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱና በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁአቸው የሚለው ይገኙባቸዋል። ይሁን እንጂ መቅዶንዮስ ስሕተቱን ተረድቶ የማይመለስ ስለሆነ በጉባኤው ተወግዞአል።

<u>አቡሊናርዮስ</u>:- አቡሊናርዮስ በታናሽቱ እስያ የሎዶቅያ ኤጲስ ቆጶስ ነበር። እርሱም ስለትምህርቱ በጉባኤው በተጠየቀ ጊዜ:- በዮሐንስ ወንጌል ም:1 ቍ:14 ላይ ቃል ሥጋ ሆነ የሚለውን ጥቅስ መሠረት በማድረግ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ማለት እግዚአብሔር ወልድ ወይም ቃለ እግዚአብሔር ሰው የሆነው፥ ነፍስ የሌለውን ሥጋ በመልበስ ነው፤ እንደእርሱ አባባል ነፍስ ከመለኮት ተከፍላ የመጣች ነች፤ ነፍስና መለኮት ሊዋሐዱ ስለማይችሉ ከሥጋ ጋር የተዋሐደው መለኮት በነፍስ ቦታ ሆኖ ነው ብሎአል።

ጉባኤው ለአቡሊናርዮስ ክሕደት ከሰጣቸው መልሶች መካከል የሚከተሉት አባባሎች ይገኙባቸዋል:-

«እግዚአብሔር ወልድ ከጠባያችን ጋር የተዋሐደው ሊያድነን ብሎ ሲሆን፥ እንስሳዊ ሥጋን ብቻ የተዋሐደ ከሆነ እንስሳትን እንጂ ሰውን አያድንም ማለት ነው። ሰው በትንሣኤ ሙታን ጊዜ የሚነሣው በነፍስና በሥጋ ሆኖ የጽድቅ ወይም የሀኔ ፍርድን የሚቀበል ነው እንጂ በሥጋ ብቻ ያን ፍርድ የሚቀበል አይደለም። ሥጋንና ነፍስን ባይዋሐድ ኖሮ ራሱን የሰው ልጅ ብሎ ባልጠራም ነበር» (የ1983 ዓ.ም. ትምህርተ መለኮት፥ ገጽ 75)።

አቡሊናርዮስም ከክሕደቱ እንዲመለስ የተሰጠውን ምክር የማይቀበል ሆኖ ስለተገኘ ጉባኤው አውግዞታል።

<u>አውሳብዮስ</u>:- የሰባልዮስን ክሕደት በማንጸባረቅ እግዚአብሔር ሦስት አካል የለውም፤ በዘመነ ኦሪት እንደ አብ፥ በዘመነ ሐዲስ እንደወልድ፥ በሐዋርያት ላይ ደግሞ እንደ መንፈስ ቅዱስ ተገልጦአል በማለት የምሥጢረ ሥላሴን ትምህርት ክዶአል። ጉባኤውም ለአውሳብዮስ ምክር ሰጥቶት የማይመለስ በመሆኑ አውግዞ ለይቶታል።

ጉባኤው ከላይ የተዘረዘሩትን ሦስቱን ክሕደቶች ካወገዘ በኋላ በኒቅያ ጉባኤ የተጀመረውን የሃይማኖት ጸሎት ከፍጻሜ አድርሶአል:-

«ሕይወትን በሚሰጥ ጌታ፥ ከአብ በሠረጸ፥ ከአብና ከወልድ፥ ጋር በሚሰገድለት፥ በነቢያት ዐድሮ በተናገረ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን። ዓለም ዐቀፋዊትና ሐዋርያዊት ባሆነች በአንዲት ቅድስት ቤት ክርስቲያን እናምናለን። ኃጢአትን ለማስተስረይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን። የሙታንን መነሣትና የሚመጣውን ሕይወት ተስፋ እናደርጋለን፤ ለዘለዓለሙ አሜን»።

ከዚህ በኋላ ጉባኤው ሰባት ቀኖናዎችን ደንግጎ ሥራውን ፈጽሞአል።

1. በኒቅያ የተሰበሰቡት የ318 አባቶች ውሳኔ ማንም የሚቃወመው ሰው መኖር የለበትም ብለው በቍስጥንጥንያ የተሰበሰቡት አባቶች ወሰኑ።

2. ኤጲስ ቆጶሳት ሁሉ ከአስተዳደራቸው ውጪ በሆነ ሀገረ ስብከት ጉዳይ ውስጥ መግባት አይኖርባቸውም። ማንኛውም ኤጲስ ቆጶስ ተጋብዞ ካልሆነ በቀር በሌላ ሀገረ ስብከት ለመሾም ወይም ሌላ ያስተዳደር ሥራ ለማከናወን መብት የለውም። በአረማውያን ሀገሮች ለሚገኙ የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያን ግን በአባቶች ልማድ መሠረት ይፈጸም።

3. ቍስጥንጥንያ አዲስዋ ሮማ እንደመሆንዋ የኤጲስ ቆጶስዋም ክብር ከሮማው ኤጲስ ቆጶስ ቀጥሎ የአንደኛነት ማዕረግ ይኖረዋል።

4. በእርሱ ምክንያት በቍስጥንጥንያ ስለደረሰው መተራመስ ኪኒቃዊው መክሲምስ ኤጲስ ቆጶስ እንደሆነ መታሰብ አይገባውም። ምንም የክህነት ማዕረግ የለውም። በእርሱ አማካይነት ማዕረገ ክህነት የተቀበሉ ሁሉ ተቀባይነት የሌላቸው ናቸው።

5. በምዕራብ የተፈጸመውን በሚመለከት በአንጾኪያም ያሉትን በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ አንድ መለኮት የሚያምኑትን እንቀበላለን።



6. ብዙ ሰዎች ሥልጣነ ክህነትን ለማራከስና የሕዝብን ሰላም ለማደፍረስ ፈልገው ቤተ ክርስቲያንን በሚያስተዳድሩ ኦርቶዶክሳውያን ኤጲስ ቆጶሳት ላይ ከንቱ የስም ማጥፋት ክስ የሚመሠረቱት የቤተ ክርስቲያንን ሥርዐት የሚያቃውሱ ስለሚመስላቸው በመሆኑ በዚህ አጋጣሚ ቅዱስ ሲኖዶስ ማለት በቍስጥንጥንያ የተሰበሰበው የኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ የሚቀርበውን ክስ ሳይመ ረምር ምስክርነት አይሰማም። ተቀባይነት የሚኖረውም ከሁሉም አቅጣጫ የሚቀርብ ክስ አይደለም። ኤጲስ ቆጶስ የግል በደል እንዳደረሰ ተደርጎ የሚቀርብ ክስ ግን የከሳሹን ማንነትና እምነት መመልከት የለበትም። የኤጲስ ቆጶሱ ኀሊና ከሁሉም ነገር ነጻ መሆን ይኖርበታል። የተበደለውም ሰው ምንም ዐይነት አምነት ቢኖረው መብቱ መከበር አለበት። በኤጲስ ቆጶሱ ላይ የቀረበው ክስ ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከት ከሆነ ተከሳሾቹን መመርመር ያስፈልጋል። በክሕደታቸው ተወግዘው የተለዩ የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ በሚመለከት በኦርቶዶክሳውያን ኤጲስ ቆጶሳት ላይ ክስ ማቅረብ አይገባቸውም። ከሳሾቹ ግን በውግዘት ያልተለዩ ወገኖች ከሆኑ ክሳቸውን ለሀገረ ስብከቱ ኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ እንዲያቀርቡ ቅዱሱ ሲኖዶስ ያዛቸዋል። የኤጲስ ቆጶሳቱም ጉባኤ ክሱን በጥብቅ መመርመር ይኖርበታል። የሀገረ ስብከቱ የኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ መፍ ትሔ ለመስጠት የማይችል ከሆነ ከዚህ ከፍ ወዳለ ጉባኤ ይምራው። ከፍተኛ ውም ጉባኤ ከሳሾቹን አስጠርቶ ተከሳሹ ከተከሰሰበት ክስ ነጻ ሆኖ ቢገኝ ክሳቸው ሊያስቀጣ የሚችለውን ቅጣት ለመቀበል ፈቃደኞች መሆናቸውን በጽሑፍ ከማረጋገጣቸው በፊት ጉባኤው ክሱን መመርመር አይጀምርም።

የሀገረ ስብከቱን የኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ በማቃለል የተሰጠውን መግለጫ በንቀት ተላልፎ ለንጉሥ ወይም ለዓለማዊ ፍርድ ቤት፥ ወይም ለዓለም ዐቀፋዊ ሲኖዶስ ማሰማት ቀኖናዎችንና የቤተ ክርስቲያንን ሥርዐት ማዋረድ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም።

7. ከክሕደታቸው ተመልሰው ወደ ኦርቶዶክሳዊት እምነትና ወደዱኑት ወገኖች ኅብረት የሚመጡትን በቀኖናው መሠረት እንቀበላቸዋለን። የምንቀበላቸውም የቤተ ክርስቲያንን ቀጥተኛ የእምነት ቀኖና መቀበላቸውን ካረጋገጡና ከቤተ ክርስቲያን እምነት ውጪ የሆኑትን ኑፋቄዎች ካወገዙ በኋላ ነው።

<u>የኤፌሶን ጉባኤ</u>:- የኤፌሶን ጉባኤ የተሰበሰበው በ431 ዓ.ም. በትንሹ ቴዎዶስዮስ ዘመን ነው። የስብሰባው ዋና ምክንያት የንስጥሮስ ክሕደት ይሁን እንጂ ስለ ቢላግዮስም ክሕደት ክርክር ተደርጎ ውሳኔ ተሰጥቶበታል። በጉባኤውም ላይ የተገኙት ሁለት መቶ ጳጳሳት ነበሩ። የጉባኤውም ሰብሳቢ ዐምደ ሃይማኖት የሚል ስም የተሰጠው የግብጹ ቅዱስ ቄርሎስ ነበር።

<u>ንስጥሮስ</u>:- የንስጥሮስ የክሕደት ትምህርት እንዲህ የሚል ነበር:- «የእግዚአብሔር ቃል ከሁሉ በፊት የነበረ መሆኑን አምናለሁ፤ ማርያም የአም ላክ እናት ነች የሚለውን አባባል ግን አላምንም። የክርስቶስ እናት መሆንዋን አልክድም፤ እናትነትዋ ግን ለትስብእት ነው እንጂ ለመለኮት አይደለም። ከሥጋ የሚወለድ ሥጋ፥ ከመንፈስ የሚወለድ ደግሞ መንፈስ በመሆኑ ማርያም እግዚአብሔርን አልወለደችም። ፍጡር ሆና የወለደችው የእግዚአብሔር ማደሪያ የሚሆነውን ሰውን እንጂ አምላክን አይደለም። በዚህም መሠረት ጌታ ሁለት ጠባይ፥ ሁለት አካልና ሁለት ፈቃድ አለው። ሰብአ ሰገል ለሕፃን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስገዳቸው ስሕተት ነው፤ (በእርሱ እምነት) ሕፃን ጌታ ኢየሱስ መለኮት ያልተወሐደው ሰው ነውና» ብሎአል (የ1983 ዓ.ም. ትምህርተ መለኮት፥ ገጽ: 78–79)።

የንስጥሮስንም ክሕደት ጉባኤው አውግዞአል።

<u>ቢላግዮስ</u>:- የቢላግዮስ ክሕደት እንዲህ የሚል ነው:- «አንድ ሰው በሚወለድበት ጊዜ አዳም በኃጢአት ከመውደቁ በፊት እንደነበረው ሆኖ ይወለዳል እንጂ የአዳምን ኃጢአት አይወርስም። ሰውም ወደ ከፍተኛ የቅድስና ደረጃ ሊደርስ የሚችለው በተፈጥሮ ጠባዩና በፍላጎቱ ነው እንጂ በእግዚአብሔር እርዳታ አይደለም።» ይህ አባባል ግን የሚከተሉትን የቅዱሳት መጻሕፍት አባባሎች የሚቃረን ነው:-

«ከተፀነስሁበት ጊዜ ጀምሮ ኃጢአተኛ ነኝ፤ ከተወለድሁበት ጊዜ ጀምሮ በደለኛ ነኝ» (መዝ:51 ቍ:5)።

«በአንድ ሰው ምክንያት ኃጢአት ወደ ዓለም ገባ፤ በኃጢአትም ሞት መጣ፤ ይኸውም ሰው ሁሉ ኃጢአት ስለ ሠራ ሞት በሰው ሁሉ ላይ መጣ» (ሮሜ:ም:5 ቍ:12)።

www.ethiopianorthodox.org

«በአዳም ምክንያት ሰው ሁሉ እንደሚሞት እንዲሁም በክርስቶስ ምክን ያት ሰው ሁሉ ሕወትን ያገኛል»

በእነዚህና በሌሎችም ማስረጃዎች መሠረት ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ መሆኑን ጉባኤው ያቀረበለት ቢሆንም እርሱ ግን በሐሳቡ ስለጸና በውግዘት እንዲለይ ተደርጎአል።

ይህ ጉባኤ ስምንት ቀኖናዎችን ደንግጓል።

1. በቤተ ክርስቲያናዊም ሆነ በሥጋዊ ምክንያት ከቅዱስ ሲኖዶስ ልዩነት ያላቸው ሰዎች የጉባኤውን ድንጋጌ ችላ ማለት የለባቸውም (ውሳኔውን ማክበር ኖርባቸዋል)። በዚህም ለቅዱስነትዎና ለተወዳጅነትዎ የምናሳውቀው የአንድ ሀገረ ስብከት ርእስ ኤጲስ ቆጶሳት ለዓለም ዐቀፋዊው ሲኖዶስ ውሳኔ የማይ ታዘዝ ሆኖ የእምቢተኛነት ጉባኤ ቢሰበስብና ተቃራኒ ውሳኔ ቢያሳልፍ ወይም ከሌሎች ተቃራኒዎች ከሆኑ ውሳኔዎች ጋር ቢስማማ ከአሁን ጀምሮ በጉባኤው ውሳኔ ከቤተ ክርስቲያን አንድነት ተባሮ የተለየ በመሆኑ በሀገረ ስብከቱ ኤጲስ ቆጶሳት ላይ ምንም ውሳኔ ሊያስተላልፍ አይችልም። ቀጥተኛ አስተያየት ያላቸው የሀገረ ስብከቱ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ከክህነት ደረጃው ያባርሩት ዘንድ ጉባኤው ወክሎአቸዋል።

2. የአንዳንድ ሀገረ ስብከቶች ኤጲስ ቆጶሳት ከቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ዘግይተው ወደ እምቢተኛነት ካዘነበሉ፥ ወይም ንስጥሮስ ተወግዞ ከተለየ በኋላ ከመናፍቃን ጋር አንድ ግንባር ለመፍጠር የተስማሙ ከሆነ እንደዚህ ያሉ ሰዎች ከክህነት ማዕረጋቸው መሻር አለባቸው ብሎ ጉባኤው ወስኖአል።

3. ከአስተሳሰባቸው ቀናነት የተነሣ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በንስጥሮስ ወይም በተከታዮቹ አማካይነት ከክህነታቸው የተሻሩ ከሆኑ ጉባኤው በክህነት ደረጃቸው እንዲቀጥሉ ፈርዶላቸዋል። ዓለም ዐቀፋዊና ኦርቶዶክሳዊ በሆነው በቅዱስ ሲኖዶስ የእምነት ቀኖና ጸንተው ለሚገኙ ካህናት ሁሉ የምናስ ተላልፈው ትእዛዝ በውገዘት ለተለዩት ኤጲስ ቆጶሳት እንዳይታዘዙ ነው።

4. ከካህናት መካከል እምቢተኞች ሆነው የንስጥሮስንና የካላስትዮስን የክሕደት ትምህርት በመቀበል ሕዝብም ያንን የክሕደት ትምህርት እንዲቀበል የሚያደርግ ቢኖሩ ትክክለኛ በሆነው የቅዱስ ሲኖዶስ ፍርድ እንደተለዩ ይቈጠራሉ።

5. የክህነት ተግባሮችን እንዳያከናወኑ በቅዱስ ሲኖዶስ ወይም በኤጲስ ቆጶሳት ለተከለከሉ ሰዎች ንስጥሮስና ተከታዮቹ በግዴለሽነት ወደ ክህነት ደረጃ ኀብረት እንዲገቡ ቢያደርጉአቸው እነዚህ ሰዎች በውግዘት እንዲኖሩ ፈርደንባቸዋል።

6. በኤፌሶን የተሰበሰበው ቅዱስ ሲኖዶስ ከመዘገበው ውሳኔ ተቃራኒ የሆነ ድርጊትን ለማድረግ የሚፈልጉ ቢኖሩ ኤጲስ ቆጶሳት ወይም ቀሳውስት ከሆኑ ከክህነት ማዕረጋቸው ይሻሩ፤ ተራ ምእመን ቢሆን ግን ይለይ።

7. የሃይማኖትን ቀኖና በሚመለከት፥ ማንም ቢሆን በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ በኒቅያ የተሰበሰቡት ቅዱሳን አባቶች ከወሰኑት እምነት የተለየ ትምህርት መከታተል፥ መጻፍና መድረስ አይገባውም። ወደ አረማዊነት፥ ወደ አይሁዳዊነት፥ ወይም ወደ ሌላ የመናፍቃን ትምህርት ለመመለስ ለሚፈልጉ ሰዎች የእነዚያን እምነት ለማሳወቅ በድፍረት ድርሰት የሚያዘጋጁ ካሉ ኤጲስ ቆጶሳት ቢሆኑ ከኤጲስ ቆጶስነት ማዕረጋቸው፥ ካህናት ቢሆኑ ከክህነት ማዕረጋቸው ይሻሩ፤ ምእመናን ቢሆኑ ከኅብረቱ ይለዩ፤ ኤጲስ ቆጶሳት፥ ካህናት ወይም ሌሎች ምእመናን ስለ እግዚአብሔር ወልድ ሥጋ መልበስ የንስጥሮስን ትምህርት በመመርኰዝ ቄስ ካሪሲዩስ ያዘጋጀውን የክሕደት ትምህርት የተቀበሉ ወይም ያስተማሩ በዚህ ዓለም ዐቀፋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ ፍርድ ኤጲስ ቆጶስ ቢሆን ከሹመቱ ተሽሮ በውግዘት፤ ካህን ቢሆን ከክህነት ደረጃው ይሻር፤ ተራ ምእመን ቢሆን ከኅብረቱ ይለይ።

8. በኤጲስ ቆጶስነት ተባባሪአችንና የእግዚአብሔር ወዳጅ የቆጵሮሱ ኤጲስ ቆጶስ አርጌኖስ፥ እንዲሁም አብረውት የመጡት የእግዚአብሔር ወዳጆች ዘይኑንና ኢዩዋግሩስ ከቤተ ክርስቲያን ደንብና ከቅዱሳን ሐዋርያት ቀኖና የተለየ ድርጊት መፈጸሙን ነግረውናል። የአጠቃላዩ ችግር የበለጠ ጉዳት እንዳያመጣ ከፍተኛ እንክብካቤ የሚያስፈልገው ሲሆን ከቆጵሮስ የመጡት ሁላቸውም በቃልና በጽሑፍ እንደገለጹት የአንጾኪያው ኤጲስ ቆጶስ ከአሁን በፊት በቆጵሮስ ጉዳይ ገብቶ የማያውቅ ከሆነ በንጹሓን አባቶች ቀኖና እና ቀድሞ በነበረው ትውፊት መሠረት በቅድስት የቆጵሮስ ቤተ ክርስቲያንና በኀላፊዎችዋ ላይ ምንም ግራ መጋባትና ቅሚያ እንዳይደረግ። እነርሱም ኤጲስ ቆጶሳትንና መሪዎቻቸውን ሁሉ በራሳቸው ይሠይሙ። ይህም



ጉዳይ በሌሎች ሀገረ ስብከቶች ሁሉ ይጠበቅ። ማንኛውም የእግዚአብሔር ወዳጅ የሆነ ኤጲስ የእርሱ ተከታይ ባልነበረ ወይም እርሱ በተካው ኤጲስ ቆጶስ ሥር ያልነበ ረውን ሀገረ ስብከት በሥሩ ለማድረግ መሞከር የለበትም። የሌላውን ሀገረ ስብከት በድፍረት በቅሚያ መልክ በሥልጣኑ ሥር ያደረገ ካለ ያባቶችን ቀኖና ላለመቃወም ይመልስ።

ማንኛውም ሀገረ ስብከት የተቀማውና ከቀድሞ ጀምሮ የነበረው መብቱ ይመለስለት ዘንድ ዓለም ዐቀፋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ወስኗል።

## የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን

ቅዱስ ቄርሎስ:- ቅዱስ ቄርሎስ የፓትርያርክ ቴዎፍሎስ እኅት ልጅ ነበር። ከልጅነቱ ጀምሮ ያሳደገው ይኸው አጐቱ ነው። ወደ መንፈሳዊ ኮሌጅ አስገብቶት ታላቅ ዕውቀት ቀስሞአል። በተለየም የፍልስፍና ትምህርቱ ጥልቅ ነበር። ትምህርቱን ባጠናቀቀ ጊዜ የብሕትውናንና የምንኵስናን መሠረታዊ ዐላማዎች ተግባራዊ እንዲያደርግ ፓትርያርኩ፥ ቄርሎስን ወደ አስቄጥስ ገዳም ላከው። እዚያም የቅዱስ ሰራቢዮን ደቀ መዝሙር ሆኖ ወደ አምስት ዓመት ኖረ። ጸሎት በሚጸልይበት ጊዜ በራሱ ላይ ይፈጽም የነበረው የምንኵስና ድርጊት እንዲህ ነበር:- ያንቀላፋው እንደሆነ ያነቃው ዘንድ ባለብረት ሰይፍን ከጐኑ መሰካት ነበር። ከዚያ በኋላ አጐቱ ጠርቶ የዲቁና ማዕረግ ሰጠው። እስክንድርያ ለሚገኘው ካቴድራልም በሰባኪነት ቀጠረው። ትምህርትና ጥበብ ይገኝበት የነበረውን ስብከቱን ለመስማት ሕዝቡ በብዛት ይሰበሰብ ነበር። አጐቱ ፓትር ያርክ ቴዎፍሎስ ካረፈ በኋላም የፓትርያርክነቱን ሥልጣን የተረከበ እርሱ ነው።

ለፓትርያርክነት እንደተሾመ የአይሁድና የክርስቲያኖች ሁከት አጋጠመው። ይህም የሆነው ክርስቲያኖቹ በቍጥር እየበዙ መሄዳቸውን ባዩ ጊዜ አይሁድ በክርስቲያኖች ላይ ከእነርሱ ጋር እንዲተባበር ለአገረ ገገርው ጉቦ ሰጥተውት ስለነበረ ነው።

በአንድ ሌሊት የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ተቃጠለ ብለው አይሁድ ወሬ በማሠራጫታቸው ያን የተባለውን ቃጠሎ ለማጥፋት ብለው ክርስቲያኖች ከየቦታው በተሰባሰቡ ጊዜ አይሁድ ሰይፋቸውን ይዘው በመውጣት ብዙ ክርስያኖችን ገደሉ። በአይሁድ በኩል በተፈጸመው ተንኰል በጣም ተናድደው ወደ ፓትርያርካቸው ወደ ቅዱስ ቄርሎስ በመሄድ ለመበቀል እንዲችሉ ይፈቅድላቸው ዘንድ ጠየቁት። እርሱም ምንም ሳትጐዱአቸው ከእስክ ንድርያ ከተማ እንድታስወጡአቸው ብቻ ፈቅጄላችኋለሁ ስላላቸው አይሁድን ከዚያ አስወጥ ተው መስገጃዎቻቸውን ወረሩ። ይህም ሁከት ለአገረ ገገርው ምክንያት ሆነ። ክርስቲያኖቹ በአይሁድ ወገኖች ላይ ያደረጉት ድርጊት አይሁድ ካደረጉባቸው ድርጊት ጋር ሲነጻጸር በጣም ጥቂት መሆኑን በማብራራት ቅዱስ ቄርሎስ የአገረ ገዢውን ቍጣ አቀዝቅዞ የመጽሐፍ ቅዱስ ስጦታ ሰጠው።

ቅዱስ ቄርሎስ መናፍቃንን በመቃወም ብዙ መጻሕፍትን ጽፎአል።

1. የክርስትናን ሃይማኖት የአዳከሙ መስሎአቸው ኢአማንያን በጣም ኰርተውበት የነበረውን የክርስትናን ሃይማኖት በመቃወም ንጉሥ ዩልያኖስ በጻፋቸው ዐሥር መጻሕፍት ውስጥ የነበረውን አስተሳሰብ ቅዱስ ቄርሎስ በሰጠው መልስ ዋጋ አሳጥቶታል። በመጻሕፍቱም ውስጥ የቀረበው ትችት ብልሹ መሆኑን ቅዱስ ቄርሎስ ስለ አጋለጠው ንጉሡ ነገሥቱ ቴዎዶስዮስ መጻሕፍቱ እንዲቃጠሉ አዘዘ።

2. እግዚአብሔር የታጋዮችን ንስሓ አይቀበልም የሚለውን የሮማዊው የኑፋትያኖስ ተከታዮችን አስተሳሰብ ተቃውሞአል። ለእነርሱም መልስ ሲሰጥ ይህ አባባላቸው እግዚአብ ሔርን ምሕረት የሌለው አምላክ እንደሚያደርገው አብራራላቸው። ጳጳሳቸውም አገር ጥሎ እስኪሸሽ ድረስ አባረራቸው።

3. ለክርስቶስ ሁለት ባሕርያት፥ ሁለት አካልና ሁለት ፈቃድ እንዳሉትና እመቤታችንም የአመላክ እናት መባል የማይገባት መሆንዋን የተናገረውን የቍስጥንጥንያውን ፓትርያርክ የንስጥሮስን ክሕደት ተቃውሞአል። በ429 ዓ.ም. ለንስጥሮስ በጻፈለት መልእክት ድንግል ማርያምን የአምላክ እናት ለማለት የሚያስቸግርበት ምክንያት ከቶ የሚያስገርም ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑን ካመንን እንዴት የእርሱ እናት የአምላክ እናት አትባልም እንላለን። እኛስ ከሐዋርያትም ሆነ ከአባቶች የተቀበልነው ትምህርት ድንግል ማርያም የአምላክ እናት መሆንዋን ነው ብሎአል። ትክክለኛ ነው በሚለውና የተበላሸ የንስጥሮስ አስተሳሰብ ነው በሚለው መካከል ዐሥራ ሁለት ነጥቦችን ከዐሥራ ሁለት ውግዘት ጋር አቅርቦአል። በንስጥሮስ ምክንያት ለተሰበሰበው የኤፌሶን ጉባኤ ሰብሳቢ ቅዱስ ቄርሎስ ነበር።

www.ethiopianorthodox.org

በ444 ዓ.ም. ትግሉን ፈጽሞ እስካረፈበት ጊዜ ድረስ የንስጥሮስን ክሕደት እንደ ተቃወመ ኖሮአል።

እርሱ ካዘጋጃቸው ዝንኞች ጽሑፎች መካከል አምስቱ ብሔረ አሪት፣ የነቢያትና የሉቃስ ንጌል ትርጓሜዎች፣ ዩልያኖስን ለመቃወም የጻፈው ጽሑፍ፡ ስለ ምሥጢረ ሥላሴና ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ መልእክቶችና በስሙ የሚጠራው የቅዳሴ ጸሎት ይገኙባቸዋል።: (የሐምሌ 3ቀን ስንክሳር ይመለከቷል)።

<u>ቅዱስ ዲዮስቆሮስ</u>:- ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ኻያ አምስተኛው የግብጽ ፓትርያርክ ነበር። በንጉሥ መርቅያን ትእዛዝ ወደ ኬልቄዶን ጉባኤ በተጠራ ጊዜ ወደ ስድስት መቶ ሠላሳ የሚሆኑ ጳጳሳትን በማየቱ ይህን ያኸል ብዙ አባላት ያሉት ጉባኤ መሰብሰቡ ምን ያኸል አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ ቢገኝ ነው? ብሎ ጠየቀ። ይህ ጉባኤ የተሰበሰበው በንጉሡ ትእዛዝ ነው አሉት። እርሱም ጉባኤው የተሰበሰበው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ ቢሆን እኔም በጉባኤው ላይ እገኛለሁ፤ ጌታችን በእኔ አንደበት ሆኖ የሚናገረውንም እናገራለሁ። ስብሰባው በንጉሡ ትእዛዝ ከሆነ ንጉሡ በሚፈልገው ዐይነት ጉባኤውን ያዘጋጅ አለ። የሮማው ቤተ ክርስቲያን ሠሪ ልዮን ከተዋሕዶ በኋላ ክርስቶስ ሁለት ጠባይና ሁለት ፈቃድ አለው የሚል መሆኑን ዐወቀ። ይህን አዲስ እምነት በመቃወም እንዲህ አለ:- «ክርስቶስ አንድ ነው፤ እንደ ሰው ወደ ሠርግ ቤት የተጠራ እርሱ ነው፤ መለኮት ከትስብእት አልተለየም። ቅዱስ ቄርሎስን በማስረጃነት በማቅረብ የእግዚአብሔር ቃል ከሰውነት ጋር ያደረገው ተዋሕዶ ነፍስ ከሥጋ ጋር የሚያደርገው ተዋሕዶ ዐይነት ነው፤ የእሳትና የብረት ተዋሕዶ ዐይነት ነው። ሁለት የተለያዩ ጠባዮች ቢሆኑም በመዋሐዳቸው አንድ ሆነዋል። በዚህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ክርስቶስ ነው፤ አንድ ጌታ ነው፤ አንድ ባሕርይና አንድ ፈቃድ ነው።» ከተሰብሳቢዎቹ መካከል አንድም ሰው የተቃውሞ ሐሳብ ለማቅረብ አልደፈረም።

ከጉባኤውም መካከል ንስጥሮስ በተወገዘ ጊዜ በኤፌሶኑ ጉባኤ የተገኙ ነበሩ። እነርሱም ትእዛዛችሁን የማይቀበል የእስክንድርያው ፓትርያርክ ዲዮስቆሮስ ብቻ ነው ብለው ለንጉሡ ለመርቅያንና ለንግሥቲቱ ለብርክልያ ነገሩአቸው። እነርሱም ዲዮስቆሮስንና በስብሰባው ውስጥ ከነበሩት ከዋነኞቹ ጳጳሳት አንዱን አስጠርተው እንዲከራከሩ አደረጉአቸው። እስኪመሽ ድረስ ሲከራከሩ ቈይተው ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ከእምነቱ ዝንፍ የማይል መሆኑን ባዩ ጊዜ ንጉሡና ንግሥቲቱ ተበሳጩ። ንግሥቲቱ አፉ ላይ እንዲመቱትና ጢሙን እንዲላጭ አዘዘች። የንግሥቲቱም ትእዛዝ ተግባራዊ ስለሆነ የተነጨ ጢሙንና የተነቀለ ጥርሱን አንሥቶ ይህ የእምነት ፍሬ ነው በማለት ወደ እስክንድርያ ላከው። ሌሎቹ ጳጳሳት በዲዮስቆሮስ ላይ የደረሰውን ችግር ባዩ ጊዜ እኛም ችግር ይደርስብናል ብለው በመፍራት ለክርስቶስ ሁለት የተለያዩ ባሕርያት አሉት በሚለው ውሳኔ ላይ በመፈረም ከንጉሡ ጋር ተስማሙ። ዲዮስቆሮስ ሁናቴውን በተረዳ ጊዜ የሚፈርም በማስመሰል ውሳኔው እንዲመጣለት ጠየቀ። ካነበበው በኋላ እነርሱንና ከቀጥተኛው እምነት የሚወጣውን ሰው ሁሉ አውግዞ ጻፈ። ንጉሡም በጣም ተቈጥቶ ወደ ጋግራ ደሴት እንዲጋዝ አዘዘ። ከእርሱም ጋር የአድኮ ጳጳስ የነበረው ቅዱስ መቃርዮስና ሌሎች ሁለት አብረው ወደ ግዞት ተልከዋል።

ቅዱስ ዲዮስቆሮስን ወደ ጋግራ ደሴት ባመጡት ጊዜ ንስጥሮሳዊ የነበረው ጳጳስ ተቀበለው። እግዚአብሔርም በቅዱስ ዲዮስቆሮስ አማካይነት ተአምራትን ስለሠራ ሁላቸውም ታዘዙት፤ አከበሩትም። እግዚአብሔር የእርሱን ተመራጮች በሁሉም ቦታ ስለሚያከብር የእነርሱም አክብሮት እያደገ ሄደ። ቅዱስ ዲዮስቆሮስም ከእርሱ ጋር የተያዘውን ቅዱስ መቃርዮስን አንተ በእስክንድርያ የሰማዕትነት አክሊል ይጠብቅሃል ብሎት ከአንድ አማኝ ነጋዴ ጋር ላከውና የሰማዕትነትን አክሊል ተቀዳጅቶአል።

ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ግን መልካም ትግሉን ፈጽሞ ከዚህች ከከንቱ ዓለም በመሸጋገር ዘለዓለማዊውን ሕይወት አክሊል በጋግራ ደሴት ተቀዳጀ። ሥጋውም እዚያው እንዲያርፍ ተደረገ። (የመስከረም 7 ቀን ስንክሳር)

<u>ሶርያዊው ቅዱስ ኤፍሬም</u>:- ቅዱስ ኤፍሬም በንጉሡ በቈስጠንጢኖስ ዘመን ንጽቢን በምትባል ከተማ ከአረማውያን አባትና እናት ተወለደ። የንጽቢን ኤጲስ ቆጶስ የነበረውን ቅዱስ ያዕቆብን እንደ አጋጣሚ በተገናኘው ጊዜ ስለ ክርስቲያን ሃይማኖት አስተምሮ በማሳመን አጥምቆታል። ከዚያም በኋላ ከእርሱ ጋር አብሮ ኖሮአል። ቅዱስ ኤፍሬምም በአምልኮተ እግዚአብሔር በዘመኑ ከነበሩ ሰዎች ሁሉ የበለጠ ሆነ። በተሰጠውም ጸጋ ከአሕዛብ ጋር እየተከራከረ ያሸንፋቸው ነበር። የኒቅያ ጉባኤ በተደረገ ጊዜ መምህሩ ቅዱስ ያዕቆብ አስከትሎት ሄዶአል።

አንድ ቀን ቅዱስ ኤፍሬም በጸሎት ላይ እያለ የብርሃን ዐምድ ከመሬት እስከ ሰማይ መዘርጋቱን በራእይ አየ። በአየው ራእይ እየተደነቀ ሳለ ይህ ያየኸው የቂሣርያ ጳጳስ ቅዱስ ባስልዮስ ነው የሚል ድምፅ ሰማ። ወደ ቂሣርያ ሄዶ ይህን ጉዳይ ለማየት ወሰነና ሄዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመግባት ወደ ጥግ ቆመ። እዚያም ቆሞ ሳለ ቅዱስ ባስልዮስን በወርቅ ያንጸባረቀ ልብሰ ተክህኖ ለብሶ አየው። ይህንንም በማየቱ ቅዱስ ኤፍሬም በቅዱስ ባስልዮስ ቅድስና ተጠራጠረ። እግዚአብሔር ግን ነጭ ርግብ ወርዳ በቅዱስ ባስልዮስ ራስ ላይ ስታርፍበት ለቅዱስ ኤፍሬም አሳው። እንዲሁም ቅዱስ ኤፍሬም እዚያ ያለ መሆኑን እግዚአብሔር ለቅዱስ ባስልዮስ ገለጠለት። ከዚያም ቅዱስ ባስልዮስ ቅዱስ ኤፍሬምን በስሙ ጠራው። እርሱም እንዴት ስሜን ለማወቅ ቻለ ብሎ ተገረመ። ተገናኙተውም ሰላምታ ተሰጣጡ። ከዚያም በኋላ ቅዱስ ባስልዮስ ለቅዱስ ኤፍሬም የዲቁና ማዕረግ ሰጠው። የቅዱስ ኤፍሬምም መንፈሳዊነት በበለጠ እያደገ ሄደ። ብዙ በጎ ተግባሮችን ፈጸመ። አንድ ጊዜ አንዲት ሴት የሠራችውን ኃጢአት ከጧት ጀምራ እስከ ማታ ድረስ በወረቀት ላይ ዘርዝራ ስትጽፍ ከዋለች በኋላ ወደ ቅዱስ በስልዮስ በመሄድ በዚህ ወረቀት ውስጥ የተዘረዘሩትን በደሎች ይቅር ይለኝ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸልይልኝ አለችው። ወረቀቱን ተቀብሎ ከጸለየላት በኋላ ከፍተኛ ኃጢአት ከነበረው ከአንዱ በቀር ሁሉም ተደምስሶላት አየች። ሴትዮዋም በጣም እያለቀሰች የቀረውንም ኃጢአት እግዚአብሔር ይቅር እንዲልልኝ ጸልይልኝ አለችው። በበረሓ ወዳለው ወደ ቅዱስ ኤፍሬም ሂጂና እርሱ ይጸልይልሻል አላት። እርስ ዋም ወደ ቅዱስ ኤፍሬም ሄዳ ጉዳዩን አስረዳችው። እርሱ ደግሞ እኔ ለዚህ ደረጃ ብቁ አይደለሁም፤ ይልቅስ የካህናት አለቃ ወደሆነው ወደ ቅዱስ ባስል ዮስ ተመለሺ፤ ከዚህ ዓለም በሞት ሳይለይ በቶሎ ድረሺበት አላት። ሴትዮዋ ተመልሳ ብትሄድ ዐርፎ አገኘችው። ካህናትም አስከሬኑን ተሸክመውት አየች። አልቅሳም ወረቀቱን በሬሳ ሳጥኑ ላይ ወረወረችውና በቅዱስ ባስልዮስ አማላጅነትም ጸለየች። ከዚያ በኋላ ወረቀቱን ወስዳ ብታየው ኃጢአትዋ ተሰርዞላት አገኘችው።

ቅዱስ ኤፍሬም ብዙ ጹሑፎችን ጽፎአል፤ ከጽሑፎቹም አንዱ ውዳሴ ማርያም ነው። ብዙ ተአምራትንም አድርጓል።

ትግሉንም በፈጸመ ጊዜ ሐምሌ 15 ቀን 379 ዓ.ም. ዐረፈ። (የሐምሌ 15 ቀን ስንክሳርን ይመለከቷል)

## <u>የቤተ ክርስቲያን ዜማ</u>

<u>የሕዝብ ተሰጥዎ</u>:- <u>በግዕዝ</u>

ይ:ዲ: በሰማይ የሀሉ ልብክሙ።

ይ:ሕ:- እወ የሀሉ በሰማይ ልብነ በእንተ ስምከ አጽንዐነ ወረስየነ ድልዋነ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚእነ ወአምላክነ

ይ:ዲ:- ወለእመቦ ዘተሐየሰ ምስለ ቢጹ ይኅድግ ሎቱ።

ይ:ሕ:- በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አበሳነ። በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አበሳነ፤ በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አበሳነ።

ይ:ዲ:- እመቦ ዘሐለየ በልቡ ኑፋቄ ይትጋነይ።

ይ:ሕ:- በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አበሳነ።

ይ:ዲ:- እመቦ ነውረ ሕሊና ዘቦ ኢይቅረብ።

ይ:ሕ:- በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አበሳነ።

ይ:ዲ:- እመቦ ዘወድቀ በኃጢአት ኢይርሳዕ እስመ ዘኢይትረሳዕ

ይ:ሕ:- በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አበሳነ።

ይ:ዲ:- እመቦ ድውየ ሕሊና ዘቦ ኢይቅረብ።

ይ:ሕ:- በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አበሳነ።

ይ:ዲ:- እመቦ ስውብ ወዘኢኮነ ንጹሐ ይትገኃሥ።

ይ:ሕ:- በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አበሳነ።


www.ethiopianorthodox.org

ይ:ዲ:- እመቦ ነኪር እምትእዛዙ ለኢየሱስ ይትከላዕ።

ይ:ሕ:- በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አበሳነ።

ይ:ዲ:- እመቦ ዘያስተሐቅር ነቢያተ ያግኅሥ ርእሶ እመዓተ ዋሕድ ወያድኅን ነፍሶ። መስቀለ ኢይግፋዕ ወይጕየይ እመዓተ እግዚአብሔር እስመ ዘይሬእየነ ብነ አብ ብርሃን ምስለ ወልዱ ወመላእክቲሁ ቅዱሳን እለ ይሔውጹ ቤተ ክርስቲያን። ነጽሩ ነፍስክሙ ወአንጽሑ ነፍስተክሙ፤ ወለቢጽክሙሂ ኢትዝክሩ ኢየሀሉ በመዓት ምስለ ካልኡ። እግዚአብሔር ይሬኢ አልዕሉ አልባቢክሙ፤ ንቅረብ ለመድኃኒተ ሕይወት፤ ወቅድሳተ በጥበበ እግዚአብሔር ንንሣእ ዘተውህበ ለነ ጸጋ።

ይ:ካ:- እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ

ይ:ሕ:- ምስለ መንፈስከ

ይ:ካ:- አእኵትዎ ለአምላክነ።

ይ:ሕ:- ርቱዕ ይደሉ።

ይ:ካ:- አልዐሉ አልባቢክሙ።

ይ:ሕ:- ብነ ኀበ እግዚአብሔር አምላክነ

ይ:ካ:- ቅዱስ በቅዱሳን (3 ጊዜ)

ይ:ሕ:- ወትረ በሰማይ ወበምድር (3 ጊዜ)

ይ:ካ:- ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ እግዚአብሔር

ይ:ሕ:- ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ እግዚአብሔር አምላክ አማልክት ዘሀሎ ወይሄሉ ወትረ በሰማይ ወበምድር።

ይ:ሕ:- ኪያከ እግዚኦ ነአኵት ወንሴብሐከ

## ዘጎርጎርዮስ

ሆሣዕና በአርያም /9 ጊዜ/

ዘዮሐንስ አፈወርቅ

ይ:-ካ:- ዩ ዩ ዩ አማኑኤል አምላክነ ዩ፥ዩ፥ዩ፥ ኢየሱስ መድኃኒነ ዩ፥ዩ፥ዩ፥ ክርስቶስ ንጉሥነ

ይ:ካ:- ዩ፥ዩ፥ዩ፥ አውረድዎ እምዕፅ እደው ጻድቃን

## ዘያዕቆብ

ሠራዊተ መላእክቲሁ ለመድኃኔ ዓለም ይቀውሙ ቅድሜሁ ለመድኃኔ ዓለም። ወይኬልልዎ መላእክት ዘእሳት መንጦላዕቱ ለመድኃኔ ዓለም።

በእንተ ሥጋሁ ቅዱስ ወበእንተ ደሙ ክቡር። ወንብጻሕ ቅድመ ገጹ ከመ ንባእ ውስተ ጽርሐ ቅድሳቱ ለመድኃኔ ዓለም።አሚነነ ኪያሁ ተወኪለነ ቦቱ ነሐዩ

ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ ሥሉስ፥ ዘኢይትነገር፥ ሀበኒ ከመ እንሣእ ለሕይወት ዘንተ ሥጋ ወደመ ዘእንበለ ኵነኔ። ሀበኒ እግበር ፍሬ ዘያሰምረከ። ከመ አስተርኢ በስብሐቲከ። ወእሕየው ለከ እንዘ እገብር ዘዚአከ ፈቃደ በተአምኖ እጼውዐከ አብ ወእጼውእ መንግሥተከ ይትቀደስ እግዚኦ ስምከ በላዕሌነ እስመ ኃያል አንተ እኩት ወስቡሕ ወለከ ስብሐት ለዓለመ ዓለም። አቡነ ዘበሰማያት ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት።

ይ:ዲ:- አድንኑ አርእስቲክሙ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክነ በእደ ገብሩ ካህን ከመ ይባርከነ። (ይባርከሙ)

ይ:ሕ:- አሜን እግዚአብሔር ይባርከነ ወይሣሃለነ

ይ:ካ:- እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ

ይ:ሕ:- ምስለ መንፈስከ: አሜን እግዚአብሔር ይባርከነ ለአግብርቲሁ በሰላም። ሥርየተ ይኩነነ ዘተመጠነ ሥጋከ ወደምከ። እብሐነ በመንፈስ ንኪድ ኵሎ ኃይሎ ለጸላኢ.

በረከተ እዴከ ቅድስት እንተ ምልአተ ምሕረት ኪያሃ ንሴፎ ኵልነ እምኵሉ ምግባረ እኩይ እግኅሠነ። ወውስተ ኵሉ ምግባረ ሠናይ ደምረነ። ቡሩክ ዘወሀበነ ሥጋሁ ቅዱስ ወደሞ ክቡረ



ጸጋ ነሣእነ ወሕይወተ ረከብነ በኃይለ መስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ። ኪያከ እግዚኦ ነአኵት ንሤእነ ጸጋ ዘእመንፈስ ቅዱስ።

ይ:ሕዲ: እትው በሰላም

በአማርኛ

ይ:ዲ:- ልባችሁ በሰማይ ይኑር።

ይ:ሕ:- አዎ ልባችን በሰማይ ይኑር ጌታችን አምላካችን ኢ.ሱስ ክርስቶስ ሆይ፥ ስለ ስምህ አድነን፤ የተገባንም አድርገን።

ይ:ሕ:- ከወንድሙ ጋር የተጣላ ቢኖር ይተውለት

ይ:ሕ:- አምላካችን ሆይ፥ እንደ ቸርነትህ ነው እንጂ እንደ በደላችን አሁን። (ሦስት ጊዜ በል)

ይ:ዲ–:- በልቡ መጠራጠርን ያሰበ ቢኖር ይመን።

ይ:ሕ:- አምላካችን ሆይ፥ እንደ ቸርነትህ ነው እንጂ እንደ በደላችን አይሁን።

ይ:ዲ:- የሐሳብ ነውር ያለበት ሰው ቢኖር አይቅረብ።

ይ:ሕ:- አምላካችን ሆይ፥ እንደ ቸርነትህ ነው እንጂ እንደ ኃጢአታችን አይሁን።

ይ:ዲ:- በኃጢአት የወደቀ ሰው ቢኖር አይርሳ፤ የማይረሳ ነውና።

ይ:ሕ:- አምላካችን ሆይ፥ እንደ ቸርነትህ ነው እንጂ እንደ በደላችን አይሁን።

ይ:ዲ:- ሐሳቡ ድውይ የሆነ ቢኖር አይቅረብ።

ይ:ሕ:- አምላካችን ሆይ፥ እንደ ቸርነትህ ነው እንጂ እንደ በደላችን አይሁን።

ይ:ዲ:- ኃጢአትን የሚሠራ፥ ንጹሕም ያልሆነ ቢኖር ይወገድ።

ይ:ሕ:- አምላካችን ሆይ፥ እንደቸርነትህ ነው እንጂ እንደ በደላችን አይሁን።

ይ:ዲ:- ከኢየሱስ ትእዛዝ ልዩ የሆነ ቢኖር ይከልከል።

ይ:ሕ:- አምላካችን ሆይ፥ እንደ ቸርነትህ ነው እንጂ እንደ በደላችን አይሁን።

ይ:ዲ:- ነቢያትን የሚያቃልል ቢኖር ከአንድ እግዚአብሔር ቊጣ ራሱን ያርቅ፤ ነፍሱንም ያድን መስቀልን አይግፋ። ከእግዚአብሔር ቊጣ ይራቅ፤ የሚያየን ብርሃን አብ ከልጁ ጋራ ቤተ ክርስቲያንን ከሚጐበኙ ከቅዱሳን መላእክት ጋራ አለና። ነፍሳችሁን ተመልከቱ፤ ሰውነታችሁንም ንጹሕ አድርጉ፤ የባልንጀሮቻችሁንም በደል አታስቡ። ማንም ከወንድሙ ጋር በቊጣ እንዳይኖር አስተውሉ። እግዚአብሔር ያያል፤ ልቡናችሁን ከፍ ከፍ አድርጉ ወደ ሕይወት መድኃኒት እንቅረብ፤ በእግዚአብሔር ጥበብ ጸጋ ሆኖ የተሰጠንንም ሥጋውንና ደሙን እንቀበል።

ይ:ካ:- እግዚአብሔር ከሁላችሁም ጋር ይሁን

ይ:ሕ:- ከመንፈስህ ጋራ።

ይ:ካ:- አምላካችንን አመስግኑት

ይ:ሕ:- እውነት ነው ይገባል።

ይ:ካ:- ልቡናችሁን ከፍ ከፍ አድርጉ።

ይ:ሕ– በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ አለን።

ይ:ካ:- በቅዱሳን ዘንድ የተመሰገነ (3ጊዜ)

ይ:ሕ:- ዘወትር በሰማይና በምድር (3ጊዜ)

ይ:ካ:- ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ እግዚአብሔር

ይ:ሕ:- ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ እግዚአብሔር የአማልክት አምላክ፥ ዘወትር በሰማይና በምድር ያለ፥ የሚኖርም።

ይ:ሕ:- አቤቱ አንተን እናምናለን፤ እናመሰግንሃለን።

የጎርጎርዮስ

ሆሣዕና በአርያም (9 ጊዜ)

www.ethiopianorthodox.org

**የዮሐንስ አፈወርቅ**

ይ:ካ:- ዮ፥ዮ፥ዮ አማኑኤል አምላካችን ዮ፥ዮ፥ዮ ኢየሱስ መድኃኒታችን ዮ፥ዮ፥ዮ ክርስቶስ ንጉሣችን

ይ:ካ:- ዮ፥ዮ፥ዮ ደጋግ ሰዎች ከመስቀል አወረዱት

**የያዕቆብ**

የመድኃኔ ዓለም አገልጋዮች የመላእክት ሠራዊት በመድኃኔ ዓለም ፊት ይቆማሉ።
መላእክት ያመሰግኑታል፤ የመድኃኔ ዓለም መጋረጃው የእሳት።
ስለ ቅዱስ ሥጋው ስለ ክቡር ደሙ።
መድኃኔ ዓለም ወደሚመሰገንበት ወደ አዳራሹ እንገባ ዘንድ
እርሱን አምነን በእርሱ ታምነን እንድናለን።

ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ ሥሉስ የማይመረመር ከፍዳ አንጽተህ ሕይወት ሊሆነኝ ይህን ሥጋና ደም እንድቀበል አድርገኝ።

ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ ሥሉስ የማይመረመር ከፍዳ አንጽተህ ሕይወት ሊሆነኝ ይህን ሥጋና ደም እንድቀበል አድርገኝ። ደስ የሚያሰኝህን ሥራ እንድሠራ አድርገኝ። በክብርህ እገለጽ ዘንድ አንተ የምትወደውን እየሠራሁ አንተን በማገልገል እኖር ዘንድ አባት ሆይ፥ እጠራሀለሁ። መንግሥትህንም እለምናለሁ። አቤቱ ስምህ በእኛ ላይ ይመስገን ኃያል ክቡር ምስጉን ነህና ምስጋናም ለአንተ ይሁን ለዘለዓለሙ። በሰማይ ያለህ አባታችን አቤቱ ወደ መከራ አታግባን።

ይ:ዲ:- በአምላካችን በእግዚአብሔር ፊት እራሳችሁን ዝቅ አድርጉ በአገልጋዩ በካህኑ እጅ ይባርከን ዘንድ።

ይ:ሕ:- አሜን እግዚአብሔር ይባርከን፤ ይቅር ይበለን።

ይ:ዲ:- እግዚአብሔር ከሁላችሁም ጋር ይሁን።

ይ:ዲ:- እግዚአብሔር እኛን አገልጋዮቹን በፍቅር ይባርከን።

ይ:ሕ:- እንደ ቃልህ ይሁንልን። አሜን እግዚአብሔር እኛን አገልጋዮቹን በፍቅር ይባርከን። በመንፈስ ቅዱስም የጠላትን ኃይል የተቀበልነው ሥጋህ ደምህ የኃጢአት ማስተስረያ ይሁነን። በመንፈስ ቅዱስም የጠላትን ኃይል ሁሉ እንድናሸንፍ አድርገን። ቸርነትን የተመላች፥ የከበረች የእጅህን በረከት፥ እስዋን ሁላችን ሁሉ እንድናሸንፍ አድርገን። ቸርነትን የተመላች፥ የከበረች የእጅህን በረከት፥ እስዋን ሁላችን ተስፋ እናደርጋታለን። ከክፉ ሥራ ሁሉ አርቀን። በበጎውም ሥራ ሁሉ አንድ አድርገን ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን የሰጠን ቡሩክ የባሕርይ አምላክ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ኃይል ጸጋን ተቀበልን አቤቱ አንተን እናመሰግናለን።

ይ:ዲ:- በሰላም ግቡ።

## ጥያቄዎች

1. ሲኖዶስ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የቤተ ክርስቲያን ሲኖዶሶች የተጀመሩት መቼ ነው?
3. የተለያዩ አብያተ ክርስቲያን በአንድነት ተሰብስበው ስለ ጋራ ችግር የሚወያዩት መቼ ነበር?
4. ቤተ ክርስቲያን ለሁለት የተከፈለችው የትና መቼ ነው?
5. ሁሉም የሚያምንባቸው ሲኖዶሶች ስንት ናቸው? እነርሱስ ማን ማን ናቸው?
6. በ325 ዓ.ም. የተሰበሰበሰው ጉባኤ ማን ይባላል? የተሰበሰበውስ በማን ዘመን ነበር?
7. ያስ ጉባኤ የተሰበሰበበት ዋናው ምክንያት ምንድነው?
8. በዚህ ጉባኤ ውሳኔ የተሰጠባቸው ሌሎች ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?
9. የኒቅያ ጉባኤ ቀኖናዎች ስንት ናቸው?
10. በ381 ዓ.ም. የተሰበሰበው ጉባኤ ማን ይባላል?
11. የስብሰባው ምክንያት ምን ነበር?
12. ስብሰባውንስ የጠራው ንጉሥ ማን ይባላል?
13. ጉባኤውስ ስንት ቀኖናዎችን ደነገገ?
14. በ431 ዓ.ም. የተሰበሰበው ጉባኤ ማን ይባላል?
15. ስብሰባው በማን ዘመን ተደረገ? ሰብሳቢውስ ማን ነበር?
16. ስብሰባው በምን በምን ላይ አተኮረ?



www.ethiopianorthodox.org

17. ስንት ቀኖናዎችን ደነገገ?
18. የቅዱስ ቄርሎስ አጐት ማን ይባል ነበር?
19. ቅዱስ ቄርሎስ በራሱ ላይ የሚያደርገው የጭካኔ ሥራ ምን ነበር?
20. በቅዱስ ቄርሎስ ዘመን አይሁድ በክርስቲያኖች ላይ ምን አደረጉ?
21. ክርስቲያኖችስ በፓትርያርካቸው ፈቃድ ምን ዐይነት የበቀል ርምጃ ወሰዱ?
22. ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ስንተኛው የግብጽ ፓትርያርክ ነበር።
23. የኬልቄዶን ጉባኤ የተጠራው በማን ነው?
24. ቅዱስ ዲዮስቆሮስ የጉባኤውን አስፈላጊነት በጠየቀ ጊዜ ምን መልስ ተሰጠው?
25. ስለተሰጠውስ መልስ ምን አለ?
26. የዲዮስቆሮስና የሮማው ልዮን እምነት ልዩነት ምን ነበር?
27. ዲዮስቆሮስ ከቅዱስ ቄርሎስ የጠቀሰው ሐሳብ ምን ነበር?
28. ንስጥሮስ በተወገዘ ጊዜ የነበሩ ጳጳሳት በኬልቄዶን ጉባኤ ለንጉሡና ለንግሥቲቱ ምን ነገሩአቸው?
29. ንጉሥ መርቅያንና ንግሥት ብርክልያ ለምን ተበሳጩ?
30. ንግሥቲቱ በዲዮስቆሮስ ላይ ያስተላለፈችው ትእዛዝ ምን እንዲሆን ነው?
31. ዲዮስቆሮስስ ምን አደረገ?
32. ዲዮስቆሮስ ወደ ግዞት የተላከው ምን ስላደረገ ነው?
33. ቅዱስ ኤፍሬም የተወለደው የት ነው?
34. ወደ ኒቅያ ጉባኤ የሄደው ከማን ጋር ነው?
35. ቅዱስ ኤፍሬም ስለ ቅዱስ ባስልዮስ ያየው ምን ዐይነት ራእይ ነው?
36. ቅዱስ ኤፍሬም በቅዱስ ባስልዮስ ቅድስና የተጠራጠረው በምን ምክንያት ነው?
37. በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ምን አደረገ?
38. ወደ ቅዱስ ባስልዮስ የኃጢአትዋን ዝርዝር ያቀረበችው ሴት ሳይደመሰስ የቀረው ኃጢአትዋ እንዴት ተደመሰሰላት?
39. ስለዚያች ሴት ኃጢአት ጉዳይ ቅዱስ ባስልዮስ ምን ብሎአት ነበር? ቅዱስ ኤፍሬምስ ምን አላት?
40. ያ ኃጢአት እንዲደመሰስላት እርስዋ በመጨረሻ ያደረገችው ምን ነበር?

# ምዕራፍ 5

# መንፈሳዊነትና ግብረገብነት

## ነጻነትን በአግባቡ መጠቀም

የሰው ልጅ ሁሉንም ነገር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ የፈቃድና የፍላጎት ነጻነት ያለው መሆኑ በሁለተኛው ክፍል መጽሐፍ ምዕራፍ አንድ ላይ ተዘርዝሮ ተገልጦአል። አንድ ሰው ሁሉንም ነገር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ ሙሉ የፈቃድ ወይም የፍላጎት ነጻነት ያለው መሆኑ ደግሞ የሚያደርጋቸው ድርጊ ቶች በሰማያዊውም ሆነ በምድራዊው ሥርዓት ተቀባይነት ያላቸው ናቸው ማለት አይደለም። ሰማያዊና ምድራዊ ሕጎች የተደነገጉትም የሰው ዘር የፈቃድና የፍላጎት ነጻነት ስላለውና የሰው ፍላጎትም ገደብ የሌለው ስለሆነ ነው። ለሰው ልጅም የተፈጥሮ ዳኛ የሆነው ኅሊና የተፈጠረለት ይህን የፍላጎት ነጻነት በአግባቡ ይጠቀምበት ዘንድ እንዲረዳው ለማድረግ ነው።

ነጻነትን በአግባቡ መጠቀም ማለት ምን ማለት ነው? የፍላጎትንና የፈቃድን ነጻነት ከመብትና ከግዴታ ጋር አገናዝቦ ተግባራዊ ማድረግ ነጻነትን በአግባቡ መጠቀም ነው። ሰው የሚፈቅዳቸው ወይም የሚፈልጋቸው ማለት የሚመኛ ቸው ድርጊቶች ሁሉ ለራሱም ሆኑ ለኅብረተሰቡ ጠቃሚዎች ናቸው ማለት አይቻልም። ይሁን እንጂ እነዚህ ፍላጎቶችና ምኞቶች ጠቃሚዎች ላይሆኑ የሚችሉት ሥጋዊውን ፍላጎቶች በተመለከተ ነው እንጂ መንፈሳዊውን ፍላጎቶች በተመለከተ አይደለም።

ምነው እኔ እንደ ነቢያትና እንደ ጻድቃን ለእግዚአብሔር ቅርብ በሆንኩ፤ ምነው እኔ ከኃጢአት ርቄ ሁልጊዜ የጽድቅ ሥራዎችን ለመፈጸም በቻልኩ፤ ምነው እኔ ከሐሜት፥ የሰውን ስም ከማጥፋት፥ ከስድብ፥ ሰውን ከማሳዘን፥ ከዝሙት፥ ከክፋት፥ ከትዕቢት፥ ከምቀኝነት፥ ከክፉ ቅናት፥ ከክፉ ምኞት፥ ከጥላቻና እነዚህን ከመሳሰሉ ኃጢአቶች ለመራቅ በቻልኩ የሚሉት ምኞቶች እግዚአብሔር የሚፈቅዳቸው ምኞቶች በመሆናቸው አግባብነት ያላቸው ናቸው። ይህም ማለት እግዚአብሔር የሚፈቅዳቸው መንፈሳዊ ምኞቶችና ፍላጎ ቶች ሁሉ አግባብነት ያላቸው ናቸው ለማለት ነው። ነገር ግን የሰውን መብት የሚጋፉ፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚ ቃረኑ፥ ከእግዚአብሔርና ከምድራዊ መንግሥታት ሕጎች ተቃራኒ የሆኑ ፍላጎቶችና ምኞቶች አግባብነት የሌላቸው ናቸው። ሰውን መጥላት፥ ሕይወቱን ለማጥፋት ማሰብና መመኘት፥ የሌላ ሰው እንጂ የራስ ያልሆነውን ሀብትና ንብረት ለምሳሌ የሌላውን ሰው ገንዘብ፥ ቤቱን ሚስቱንና ሌላውንም ሁሉ ለራስ ለማድረግ መፈለግ፥ መመኘት፥ መውሰድ፥ መቀማት፥ መስረቅ፥ በሰው ላይ የኀይል እርምጃ መውሰድ፥ ማታ ለል፥ መዋሸት ማጭበርበር፥ ሰውን መሳደብ፥ ማዋረድ፥ ማማት፥ መታበይ፥ ሰውን መናቅ፥ ሰውን ማስጨነቅ፥ እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ድርጊቶች ሁሉ አግባብነት የሌላቸው ድርጊቶችና ምኞቶች ናቸው።

እግዚአብሔር ሰውን ከክፉ ዝንባሌው ለመጠበቅ የተፈጥሮ ዳኛ የሆነውን ኅሊናን ፈጠረለት። ነገር ግን ኅሊናው ገደብ የሌለውን ምድራዊና ሥጋዊ ፍላጎቱን ሊያስገድድ ስላልቻለ እግዚአብሔር ሰማያዊ ሕግን ደነገገለት። ይህም ገደብ የሌለው የሰው ልጅ ፍላጎትና ምኞት የሌላውን ሰው መብት እየተጋፋ ባስቸገረና ሰላም ባሳጣ ጊዜ ምድራውያን መንግሥታት የተለያዩ ሕጎችን ደነገጉ። ሆኖም ሰው ሃይማኖታዊ ስሜቱ ካላስገደደውና ኅሊናው ካልወቀሰው ማንም ሰው ሳያውቅበት የሚሠራቸው ወንጀሎች ሊኖሩ ይችላሉ። በእርግጥ ከእግዚአብሔር ምንም ነገር ሊሰወር የማይችል በመሆኑ እግዚአብሔር እንደሚ ፈርድበት የታመነ ነው። ይሁን እንጂ የታጋሹን አምላክ ፍርድ እስኪቀበል ድረስ በዚህ ዓለም ባሉ የተፈጥሮ ጓደኞቹ ላይ ብዙ ችግርን ሊያመጣ ይችላል። ታዲያ፥ ጊዜያዊ የሆነውን የዚህን ዓለም ፍላጎትና ምኞት ለማሙአላት ሲል ዘለዓለማዊ ሕይወቱን በአደጋ ላይ እንዳይጥል ማድረግ የሃይማኖት መምህራን ፈንታ ነው። ዋ፥ ይህች ዓለም ምንኛ አታላይ ነች? ሀብት፥ ብልጽግና፥ ዓለማዊ ደስታ፥ ዐዋቂነት፥ ዝነኛነት፥ ታዋቂነት፥ ዓለማዊ ክብርና እነዚህን የመሳሰሉ የዚህ ዓለም ጠቀሜታዎች የኛ እንዳልነበሩና ከእኛ ማንም እንደማወስድብን እንዳልተማመንንባቸው ሁሉ በአንድ ቅጽበት አጥተናቸውና ጥለናቸው ከንቱ በመሆን ከሁለት ሜትር ርዝመትና ከግማሽ ሜትር ባልበለጠ የመሬት ስፋት ውስጥ እንወሰናለን። ልብሳችን ዐፈር ሆኖ ሥጋችንም የትል ቀለብ ይሆናል። የትንሣኤ ሙታን ተስፋ ባይኖረንማ ሕይወታችን ምንኛ ተስፋ የሚያስቈርጥ በሆነ ነበር?

ስለዚህ እግዚአብሔር የሰጠንን የፈቃድና የፍላጎት ነጻነት በአግባቡ ባለመጠቀማችን ለዚህች በቅጽበት ለምናጣት ምድራዊ ደስታ ስንል ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት ሳይሆን ወደ ዘለዓለማዊ ሥቃይ እንዳንወሰድ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል።

### መብትንና ግዴታን ጠንቅቆ ማወቅ

የኅብረተሰብን ወይም የሌላን ሰው ጥቅምና ስሜት ከሚጐዳ ድርጊት ራስን መጠበቅ ሕጋዊ ወይም ማኅበራዊ ግዴታ ነው። በሃይማኖት ወይም በዓለማዊ ሕግ ያልተከለከለ፥ የኅብረተሰቡን ጥቅምና ስሜት የማይጐዳ እስከሆነ ድረስ አንድን ድርጊት ማድረግ የሰው ልጅ መብት ነው።

አንድ ሰው ስለጐረቤቶቹ ግድ የሌለው ሆኖ ሌሊት በመኝታ ሰዓት እንቅልፍ ሊነሣ በሚችል ከፍተኛ ድምፅ ሬዲዮውን ወይም ቴሌቪዥኑን ማሰማት መብት አይደለም። ያን አለማድረግ ግን ግዴታ ነው። አንድ ሰው ተቀጥሮ የሚሠራበትን መሥሪያ ቤት ጥቅም የሚጐዳ ድርጊት አለማድረግ ግዴታው ነው። ሠራተኛ የሠራበትን ደመወዝ መቀበል መብቱ ነው። አሠሪውም ያሠራበትን ዋጋ መክፈል ግዴታው ነው።

ሰዎች ሁሉ የሌላውን ሰው መብት ማክበር አለባቸው። ሰው ሁሉ ሰብአዊ ክብሩ እንዲጠበቅለት መብቱ ስለሆነ ያን ማክበር የሌላው ሰው ግዴታ ነው። ማንም ሰው ሌላውን ሰው የመሳደብ፥ የማዋረድ፥ የመደባደብ፥ ንብረቱን የመዝረፍ፥ መናጠቅና እነዚህን የመሳሰሉ ድርጊቶችን የማድረግ መብት የለ ውም። ሁሉም ሰው ከእንደነዚህ ያሉ ድርጊቶች መቆጠብ ግዴታ አለበት። እነዚህም ድርጊቶች ሰማያዊና ምድራዊ ቅጣትን የሚያስከትሉ ናቸው። አገር ሰላም የሚሆነው ሰው ሁሉ መብቱንና ግዴታውን ለይቶ በማወቅ ተግባራዊ ሲያደርግ ነው።



በጦር ሜዳ ካልሆነ በቀር ማንም ሰው ሌላውን ሰው የመግደል መብት የለውም። ማንም ሰው በሠራው ወንጀል በፍርድ ቤት ተፈርዶበት ካልሆነ በቀር በመገደል እንዳይሞት በሕይወት የመኖር መብቱ የተከበረ መሆን አለበት።

የእግዚአብሔርን ሕግጋት በተመለከተ ግን ሁናቴው ለየት ያለ ነው። ትእዛዛቱንና ሕጋቱን መፈጸም የማያወላውል ግዴታችን ሲሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ የእርሱን ፈቃድ፥ ምሕረትና አዳኝነት እናገኝ ዘንድ እንጸልያለን እንጂ እንደ መብት የምንጠብቀው ነገር አይኖርም። ስለዚህ ነው ጌታችን «እናንተም የታዘዛችሁትን ሁሉ ከፈጸማችሁ በኋላ የማንጠቅም አገልጋዮች ነን፤ የፈጸምነውም ግዳጃችንን ብቻ ነው በሉ» ያለው (ሉቃ:ም:17ቊ:10)።

ኀይለኛ ሆኖ ሌላውን ደካማ ማጥቃት የሚቻል ከሆነ፥ በኀይለኛውም ላይ ከእርሱ በላይ የሆነ ሌላ ኀይለኛ ሊነሣና እርሱ በሌሎች ላይ ባደረገው ዐይነት ሊያደርግበት ስለሚችል በዚህ ዐይነት የሰው ልጅ ኑሮ አስተማማኝነት ከማጣቱ የተነሣ ከእንስሳት ወይም ከአራዊት ኑሮ ያልተ ሻለ ይሆናል ማለት ነው። ስለዚህ ነው ቃለ እግዚአብሔር :- «ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትፈል ጉትን ሁሉ እናን ተም እንዲሁ አድርጉላቸው» በማለት እኛ በሰላም ለመኖር የምንፈልግ ከሆነ የሌላውን የፍጡር ጓደኞችንን ሰላም መጠበቅ ያለብን መሆኑን የገለጠልን (ማቴ:ም:7ቊ:12)። ይህም ማለት በሰላም የመኖር መብታችን እንዲጠበቅልን ከፈለግን እኛም የሌላውን ሰው በሰላም የመኖር መብት ማክበር ግዴታችን ነው ማለት ነው። ስለዚህ አንድ ሰው በማን አለብኝነት ሌላ ውን ሰው ቢበድል ጊዜው ይራቅ ወይም ይቅረብ እንጂ እርሱም እንዲሁ የሚበደልበት ወቅት እንደሚመጣ መገንዘብ አለበት። ከዚያም ሁሉ በላይ ሁሉን የፈጠረ፥ ከእርሱ ምንም ነገር የማይሰወር፥ ሁሉን ነገር የሚችል፥ ማንም በደለኛ ከእርሱ ቅጣት የማያመልጥ፥ በትክክለኛ ዳኝነቱም በክፉዎች ላይ በቀልን የሚበቀል አምላክ መኖሩን ማስታወስ ይገባል። ስለዚህም ሰዎች የራሳቸውን ደኅንነትና ሰላማዊ ኑሮ እንደሚመኙ ሁሉ የሌላውን ሰው የደኅንነትና በሰላም የመኖር መብት ማክበር አለባቸው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ጉዳይ በተመለከተ እንዲህ ይላል:-

«ሁሉ ነገር ተፈቅዶአል፤ ነገር ግን ሁሉ ነገር ጠቃሚ አይደለም፤ ሁሉ ነገር ተፈቅዶአል፤ ነገር ግን ሁሉ ነገር የሚያንጽ አይደለም፤ እያንዳንዱ ሰው የሌሎቹን ጥቅም ያስብ እንጂ የራሱን ጥቅም ብቻ አይፈልግ» (1ኛ:ቆሮ:ም:10 ቊ:23–24)።

### እውነትን መናገር እንጂ መማል አለማስፈለጉ

በኦሪቱ ሥርዓት ሰው በሐሰት ወይም አስፈላጊ ባልሆነ ሁናቴ እንዳይምል ተከልክሎ ነበር። ትእዛዙም የሚለው:-

«የአምላክህን የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አታንሣ፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ ሚያነሣውን ሰው ሁሉ ሳይቀጣው አያልፍም» (ዘጸ:ም:20 ቊ:7)።

«በስሜ በሐሰት አትማል፤ የአምላክህንም ስም አታርክስ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝ» (ዘሌ:ም:19 ቊ:12)።

ታዲያ አንዳንድ ሰዎች ንግግራቸውን ለማሳመን ወይም ለማረጋገጥ ብለው በየጊዜው ይምላሉ። አንድ ሰው የሚናገረው ንግግር ትክክል መሆኑን ኅሊናው እስካወቀ ድረስ ለምን መማል ያስፈልገዋል? ለሚናገረው ንግግር እውነተኛነት ጥርጣሬ ካደረበት ግን ከመናገር ይቈጠብ። እርሱ ተሳስቶ ሌላውንም ሰው አያሳ ስት። ሆን ብሎ ሐሰት የሚናገር ሰው ግን የእግዚ አብሔር ቅጣት አይቀርለትም። ለዚህም ምሳሌ ሐናንያና ሰጲራ የተባሉ ባልና ሚስት እውነትን ደብቀው ሐሰት ስለተናገሩ እግዚአብሔር በቅዱስ ጴጥሮስ አማካይነት በሞት የቀጣቸው መሆ ኑን በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 5 ቊ:1–11 ይመለከቷል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሐላን ሲከለክል በፍጹም አትማሉ ካለ በኋላ:-

«ስለዚህ ንግግራችሁ አዎ፥ አዎ፥ ወይም አይደለም፥ አይደም ይሁን። ከዚህ የተረፈ ቃል ግን ከሰይጣን ነው» ብሎአል (ማቴ:ም:5 ቊ:37)።

በዚህም መሠረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አብዛኛውን ጊዜ በንግግሮቹ መነሻ ላይ እውነት እላችኋለሁ፤ ወይም እውነት እውነት እላችኋለሁ ይል የነበረው መሓላ እንዳንምል እኛን ለማስተማር ብሎ ነው።

ሐዋርያው ያዕቆብም የጌታችንን አባባል ሲደግመው እንዲህ ብሎአል:-



www.ethiopianorthodox.org

«ወንድሞቼ ሆይ፥ ከሁሉ በፊት በሰማይ ወይም በምድር፥ ወይም በሌላ በምንም ነገር አትማሉ፤ ንግግራችሁ አዎ ከሆነ በእውነት አዎ ይሁን፤ አይደለም ከሆነም በእውነት አይደለም ይሁን፤ እንዲህ ካልሆነ ግን ይፈረድባችኋል» (ያዕ:ም:5 ቍ:12)።

በክርስትና ሕይወት ውስጥ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ሁልጊዜ እውነትን እንደሚናገር እንጂ እንደሚዋሽ ስለማይጠበቅ በሐዲስ ኪዳን መሐላ በፍጹም የተከለከለ ነው።

## ጥያቄዎች

1. አንድ ሰው ሁሉንም ነገር የማድረግ ወይም ያለማድረግ የፍላጎት ነጻነት አለው ማለት መብት አለው ማለት ነውን?
2. ሰማያዊና ምድራዊ ሕግ ለምን ተደነገገ?
3. ነጻነትን በአግባቡ መጠቀም ማለት ምን ማለት ነው?
4. ሥጋዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች በምን ይለያያሉ?
5. ኅሊና ለምን ይረዳል?
6. ሰማያዊና ምድራዊ ሕጎች ለምን ይጠቅማሉ?
7. ለምንስ ተደነገጉ?
8. የአንድ መሥሪያ ቤት ሠራተኛ ከመሥሪያ ቤቱ ጋር ባለው ግንኙነት መብቱና ግዴታው ምንና ምን ናቸው?
9. አገር ሰላም የሚሆነው ምን ሲሆን ነው?
10. መብታችን እንዲከበርልን እንደምንፈልግ ሁሉ እኛም የሌላውን ሰው መብት እንድናከብር የሚያዝዘው የመጽሐፍ ቅድስ ጥቅስ ምን የሚለው ነው?
11. በኦሪቱ የተከለከለው ምን ዐይነት መሐላ ነበር?
12. በሐዲስ ኪዳን መሐላን የሚከለክለው ጥቅስ ምን የሚለው ነው?
13. ሐሰት መናገር ወይም መዋሸት ምን ጉዳት እንደሚያመጣ ከሐዲስ ኪዳን አንድ ማስረጃ አቅርብ።
14. መማል እንደማይገባን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ምሳሌነትን ሰጠን?
15. በሐዲስ ኪዳን መሐላ የተከለከለው በምን ምክንያት ነው?



# ዐሥራ አንደኛ ክፍል

## ምዕራፍ 1

## ትምህርት ሃይማኖት

## የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት

መግቢያ:- የክርስቲያን ሃይማኖት ከሌሎች ሃይማኖቶች ተለይቶ ከሚታወቅባቸው ዋነኞቹ ርእሶች መካከል ምሥጢረ ሥላሴ ወይም የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት እምነት አንዱ ነው።

በክርስትና እምነት መሠረት እግዚአብሔር አንድም ሦስትም ነው። አንዱ አምላክ ሦስት አካል አለው። ይህም ማለት እግዚአብሔር አንድ ሲሆን ሦስት አካል አለው ማለት ነው። በሌላ አባባል አንድ መለኮት ሦስት አካል፥ ወይም ሦስት አካል ያለው አንድ መለኮት፥ ማለት አንድ አምላክ በሦስት አካል ማለት ነው።

እግዚአብሔር የማይከፋፈል አንድ መለኮት አለው። ሦስት አካላት ሲኖሩት አንድነቱን የማይከፋፈሉ የመለኮት ግብሮች አሉት።

እንደ ሐዋርያዊው ቅዱስ አትናቴዎስ አባባል:- «ቀጥተኛው እምነት የተመሠረተው ለእግኢዘብሔር ሦስት አካሎች ያሉት በመሆኑ ላይ ነው፤ አብ የአባትነት፥ ወልድ የልጅነት መንፈስ ቅዱስ የመሥረጽ ግብር ስላላቸው ሦስት ናቸው። እነዚህ የሦስትነት ግብሮች ቢሆኑም እንኳ እግዚአብሔር በመለኮት፥ በፈቃድ፥ በባሕርይና በመለኮታዊ ጠባዮች አንድ ነው። ለምሳሌ የእግዚአ ብሔር የአንድነቱ መጠሪያ ስሞች ወይም የጠባዩ መግለጫዎች ዘለዓለማዊነት፥ የማይለወጥ፥ ቀጥተኛ ዳኛ፥ ደግ፥ እውነተኛ፥ ዐዋቂ፥ ኀያልና እነዚህን የመሳ ሰሉ ናቸው። የሦስቱ መለኮታዊ አካሎች አንድነት በማወሐድና በማገናኘት ሳይሆን የማይለያይ የመለኮታዊ አንድነት ባሕርይ ስላላቸው ነው። የሚለያይ የሚከፋፈል ቢሆንማ ኖሮ ሦስቱ አካላት ሦስት አማልክት ናቸው ባልን ነበር። እንደዚህ ያለውን አባባል ደግሞ የክርስትና ሃይማኖት የሚቃወመውና የማይቀበለው ነው። ክርስትና ግን በዘለዓለማዊው አንድነት ያምናል።

«ይህ የእግዚአብሔር አንድነትም ሦስቱ የመለኮት አካሎች መኖራቸውን አይቃረንም። ይህንኑም አባባል በአንድነት ውስጥ ሦስት የተለያዩ ሁናቴዎች በመኖራቸው ምሳሌ ይመለከቷል:- ለምሳሌ አንድ ሰው ፍጹም አንድ ነው። ነገር ግን በአንድ ሰው ውስጥ እስትንፋስ፥ ሐሳብና ንግግር አሉ። ሌላው ምሳሌ ደግሞ ፀሐይ ነው። ፀሐይ አንድ ነው፤ በውስጡ ግን ክበብ፥ ብርሃንና ሙቀት፥ አለው።» (የሚካኤል ሚና ትምህርተ መለኮት 1ኛ መጽሐፍ፥ ገጽ 169–170)።

በዚህም መሠረት የሦስትነት ግብሮች የያንዳንዱ አካል ግብሮች ናቸው። ይሁን እንጂ ሦስቱ አካሎች በመለኮታዊ አንድነት ግብር ላይ አይለያዩም። በሌላ በኩል ደግሞ በመለኮታዊ አንድነት ግብር የማይለያዩ ቢሆኑም እንኳ እነዚያ ግብሮች የአንዳቸው ወይም የሌላው ግብር እንደሆኑ ተለያይተው የሚነገሩበት ጊዜ አለ።

የአንድነትና የሦስትነት ትምህርት በሐዲስ ኪዳን ግልጽ ሆኖ የቀረበ እውነት ነው። በብሉይ ኪዳን ስለ እውነተኛው አንድ አምላክ በዝርዝር ቢቀርብም እንኳ ስለ ሦስትነት ግን የቀረበው ግልጥ ባልሆነና በምሳሌ መልክ ነው። ይህም የሦስትነት ምሥጢር በሐዲስ ኪዳን ግልጥ ሆኖ የቀረበ እውነት ነው። ብሉይ ኪዳን ስለ እውነተኛው አንድ አምላክ በዝርዝር ቢቀርብም እንኳ ስለ ሦስትነት ግን የቀረበው ግልጥ ባልሆነና በምሳሌ መልክ ነው። ይህም የሦስትነት ምሥጢር በሐዲስ ኪዳን ግልጥ ሆኖ ባይቀርብ ኖሮ እንደ አሁኑ ግልጥልጥ ተደርጎ ባልታወቀም ነበር።

ሦስትነትን የተቃወሙ ክሕደቶች:- እነዚህ ተቃውሞዎችና የክሕደት ትምህርቶች የትኞቹ ናቸው?

1. የአርዮስ ክሕደት በአጭሩ:- እንደ አርዮስ እምነት እግዚአብሔር አብ ብቻ እውነተኛውና ትክክለኛው አምላክ ነው። የእግዚአብሔር ልጅና መንፈስ ቅዱስ ግን በሁለተኛ የአምላክነት ደረጃ ላይ ብቻ ያሉ ናቸው። ጠባያቸው ከአብ ጠባይ የተለየ ነው። አብ ወልድን



www.ethiopianorthodox.org

የወለደ በመሆኑ፥ ወልድ እንደ አብ ዘለዓለማዊ ያይደለና አንድ መነሻ ያለው ነው። ይህም ማለት ወልድ ያልነበ ረበት ጊዜ ነበር ማለት ነው። አባባሉም ወልድ ከመለኮታዊው አብ የተገኘ ሳይሆን እንደ ማንኛውም ሌላ ፍጥረት ከምንም ፈጥሮታል ማለት ነው። በአርዮ ስም እምነት መሠረት በዚህ በመጀመሪያው ምርጥ ፍጡር ማለት በወልድ አማካይነት እግዚአብሔር ዓለምን ፈጥሮአል፤ ፍጡርም እንደመሆኑ ከአብ ጋር መለኮታዊ አንድነት የለውም። ፍጡር በመሆኑም ውሱን ነው፤ የእግዚአብሔር ባሕርያት የሆኑት ሁሉን ቻይነትና ሁሉን ዐዋቂነት የእርሱ ገንዘቦች አይደሉም። ፍጡርም እንደመሆኑ ለለውጥ የተጋለጠ ነው። በዚህም ሰብአዊ ጠባዩ ወደ በጎነት ወይም ወደ ክፋት ሊያዘነብል ይችላል። ወደ ክፋት ያልተለወጠም ከሆነ በባሕርዩ ወይም በጠባዩ መለወጥ የሌለበት ሆኖ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጸጋና ቸርነት ስለተሞላ ነው። በመሆኑም የእግዚአብሔር ልጅ እውነተኛ አምላክ አይደለም። አምላክም ሊባል የሚችለው በምሳሌያዊ አነጋገር ነው። በትሩፋቱና በታማኝነቱ ለእግዚአብሔር ፍጹምነት ምሳሌ በመሆኑ እግዚአብሔር ልጁ አድርጎታል።

አርዮስ ስለ ወልድ ይህን ካለ በኋላ መንፈስ ቅዱስም እንደ ወልድ ፍጡር ስለሆነ ውሱን የሆነ የአምላክነት ጠባይ አለው፤ ይሁን እንጂ የእርሱ ማለት የመንፈስ ቅዱስ ክብር ከወልድ ክብር ያነሰ ነው ብሎአል።

እንደ አርዮስ አባባል ጥበበኛው ሰሎሞን በክርስቶስ ልሳን እንደ ተነገረ አድርጎ በማቅረብ ጥበብ፥ ከሁሉ በፊት እግዚአብሔር ፈጠረኝ፤ የመንገዱም መጀመሪያ አደረገኝ» የሚለው ጥቅስ፥ ለወልድ ፍጡርነት ማስረጃ ነው ብሏል (ምሳ:ም:8 ቍ22)። እንዲሁም «አባቴ ከእኔ ይበልጣል» የሚለውን ጥቅስ አቅርቦአል (ዮሐ:ም:14 ቍ:28)። «በሰማይና በምድር ሥልጣን ተሰጠኝ» የሚለውም በአርዮስ የቀረበ ጥቅስ ነው (ማቴ:ም:28 ቍ:18)። ሌሎች በአርዮስ የቀረቡ ጥቅሶች ከአብ በቀር እርሱ የፍርድን ቀን የማያውቅ መሆኑ፥ (ማር:ም:13 ቍ32)፥ «እኔ በራሴ ሥልጣን ምንም ማድረግ አልችልም» ማለቱ (ዮሐ:ም:5 ቍ:30) ናቸው።

ጥበብ የተባለውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ሆነ ድረስ እርሱ ራሱ ፍጡርነቱን መስክሮአል ማለት ነው ብሎአል። እንዲሁም አባቴ ከእኔ ይበልጣል ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ መንገሩ ወልድ ከአብ ስለሚያንስ በመለኮ ትም ስለማይተካከለው ነው ብሎአል። በሰማይና በምድር ሥልጣን ተሰጠኝ ማለቱ አብ ከእርሱ የሚበልጥ በመሆኑ ሥልጣን ሰጥቶታል ማለት ነው ብሎ አል። የፍርድን ቀን ለማወቅ የማይችልና በራሱ ሥልጣን ምንም ማድረግ የማይ ችል ከሆነ የእግዚአብሔር አገልጋይ እንጂ አምላክ ሊሆን አይችልም ብሎአል።

አርዮስ የክርስቶስን መለኮታዊ ክብር በሚክድበት ጊዜ በክርስቶስ አዳኝነት ላይ ያለውን ትልቅ እምነት መካዱ ነው። የክርስቶስም አዳኝነት ክርስቲያኖች የሚያምኑትና የሚተማመኑበት እንደመሆኑ የአርዮስ ክሕደት ክርስቲያናዊ ተስፋን የሚያጨልም ነው። ከላይ ለቀረቡት የአርዮስ መከራከሪያና ለሌሎችም ጥቅሶች በትምህርተ መለኮት ሁለተኛ እትም የመከራከሪያ ጥቅሶችና መልሶቻቸው በሚል ርእስ ከገጽ 123 እስከ ገጽ 155 ድረስ መልስ የተሰጠበት ስለሆነ ያን ይመለከቷል።

2. <u>አቡሊናርዮስ:</u>- ይህ ሰው ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ክብር አርዮሳውያንን በጣም የታገለ ሰው ነበር። ስለ ክርሰቶስ መለኮታዊ ክብር በሚያደርገው ተጋድሎ ግን የክርስቶስን ትስብእት ካደ። መለኮት የተዋሐደው ነፍስ የሌለውን ሥጋ ነው፤ መለኮት እስካለ ድረስ ነፍስ አያስፈልግም፤ መለኮት የነፍስን ተግባር ይዞ ከሥጋ ጋር ተቀላቀለ አለ። በዚያም ሁናቴ ሆኖ ሕማማትንና ሞትን እንደተቀበለ ያምናል። የሦስትነት እምነቱም ቀና አልነበረም። ይኸውም መንፈስ ቅዱስ ትልቅ ነው፤ ወልድ የበለጠ ትልቅ ነው፤ አብ ደግሞ ከሁሉም በላይ ነው ይል ነበር።

3. <u>የሰባልዮስ ክሕደት</u>:- እንደ ሰባልዮስ እምነት አንዱ አምላክ በሦስት የተለያዩ ሁኔታዎች ስለተገለጠ ነው እንጂ ሦስት አካል የለውም፤ አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ የተባሉት የአንዱ እግዚአብሔር የተለያዩ መግለጫዎች ናቸው እንጂ ለሦስት አካላት የተሰጠ ስም አይደለም፤ ኧብ የተባለው ፈጣሪ በመሆኑ ነው፤ ወልድ የተባለው አዳኝ በመሆኑ ነው፥ መንፈስ ቅዱስ የተባለው የሚያጽናና እና የሚቀድስ በመሆኑ ነው ብሎአል።

4. <u>የመቅደንዮስ ክሕደት</u>:- የቍስጥጥንያ ፓትርያርክ የነበረው መቅዶንዮስ፥ መንፈስ ቅዱስ ለወልድ መሣሪያ ይሆን ዘንድ እንደ መላእክት የተፈጠረ ነው ብሎ ያምን ነበር። በተሳሳተ መንገድም እንደ ማስረጃ አድርጎ ያቀረበው «ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጠረ የሚለውን ጥቅስ ነው



(ዮሐ:ም:1 ቍ:3)። እንደ እርሱ አባባል መንፈስ ቅዱስ በአብና በወልድ ፈቃድ በአንድ ወቅት ከአብ የሠረጸ ስለሆነ ፍጡር ነው ብሎአል። በሦስቱ አካሎችም መካከል መበላለጥ አለ በማለቱ የሦስትነትን እምነት ክዶአል ማለት ነው።

እነዚህን ክሕደቶች በመቃወም ቤተ ክርስቲያን ማስረጃዎችን በማቅረቧም በላይ የእምነት ቀኖናዎችንም ደንግጋለች።

ስለ አንድነትና ሦስትነት ትምህርት ሐዋርያዊው ቅዱስ አትናቴዎስ እን ዲህ ብሎአል:- «እግዚአብሔር፥ አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ነው፤ በእርሱ ላይ ሌላ እንግዳ ወይም የውጪ ነገር አይቀላቀልበትም፤ ሁሉም ይፈጥራሉ፤ ሁሉም እኩል ናቸው፤ ባሕርያቸውና ጠባያቸው የሚከፋፈል አይደለም። እንቅ ስቃሴው ሁሉ አንድ ነው፤ አብ በቃል በመንፈስ ቅዱስ ይሠራል፤ አንዱ ጀማሪ፥ ሌላው ፈጣሪ ሳይሆን እግዚአብሔር አንድ ነው። በዚህም ዐይነት የሥላሴ አንድ ነት ይጠበቃል። በቤተ ክርስቲያንም የእግዚአብሔር አንድነት የሚነገረው በዚህ ዐይነት ነው:- «ከሁሉ በላይ የሆነ፥ በሁሉም የሚሠራ፥ በሁሉም የሚኖር፥ የሁሉም አባት የሆነ አንድ አምላክ አለ» የሚባለውም በዚሁ ምክንያት ነው። (ኤፌ:ም.4 ቍ:6)።

«ከሁሉ በላይ የሆነ ሲባል እንደ አባት፥ በሁሉ ሲል በቃል፥ በሁሉም የሚሠራ ሲል በመንፈስ ቅዲስ ማለት ነው፤ ሦስትነቱም በስምና በአካል ብቻ ሳይሆን በክዊንና በግብር ነው። አብ አንድና በሁሉም ላይ አምላክ እንደሆነ እንዲሁም ቃል አንድና በሁሉም ላይ አምላክ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም አንድና በሁሉም ላይ አምላክ ነው» (የዶክተር ሞሪስ ታውድሮስ ትምህርተ መለኮት ሁለተኛ መጽሐፍ፥ ገጽ:63)።

<u>በብሉይ ኪዳን የአንድነት እምነትና የሦስትነት ምልክቶች</u>:- የሦስትነት ምሥጢር ግልጥ ሆኖ የቀረበው በሐዲስ ኪዳን ሲሆን የእግዚአብሔር አንድነት ምሥጢር ግን ተጠናክሮ የቀረበው በብሉይ ኪዳን ነው (ዘጸ: ም:20 ቍ:1–5፥ ዘዳ: ም:6 ቍ: 4–5)። ሆኖም እስራኤል ልጆች መሪዎቻቸው በሞቱ ቍጥር ባዕዳን አማልክትን በማምለክ ኃጢአታቸው ከአባቶቻቸው ኃጢአት የባሰ ስለነበረና (መሳ:ም:2 ቍ:19) በእነርሱም ብዙ አማልክትን የማምለክ ዝንባሌ ምክንያት እግዚአብሔር የሦስትነትን ምሥጢር ግልጽ ሳይሆን እንዲቈይ ያደረገው ይህን የሦስትነት ምሥጢር ለመቀበል የሚችል አስተሳሰብ ያለው ሕዝብ እስከሚነሣበት እስከ ሐዲስ ኪዳን ዘመን ድረስ ግልጥ ሳይሆን እንዲቈይ የአምላክ ፈቃድ ስለሆነ ነው እንጂ በብሉይ ኪዳንም ቢሆን በአንዳንድ ምልክቶች አማካይነት ሳይጠቈም የታለፈ አይደለም። ለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች ይመለከቷል:-

«ሰውን እንፍጠር» (ዘፍ:ም:1 ቍ:26)

ረዳት እንፍጠርለት» (ዘፍ:2፥18)

«አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ» (ዘፍ:ም:3 ቍ22)

«ኑ እንውረድና ቋንቋቸውን እንደባልቀው» (ዘፍ:ም:11 ቍ:7)።

«ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፤ ምድር ሁሉ በክብሩ ተሞልታለች» (ኢሳ:ም:6 ቍ:3)።

ቅዱስ አትናቴዎስ ይህ ሦስት ጊዜ ቅዱስ ተብሎ የቀረበው ምስጋና ስለ አብ፥ ስለ ወልድና ስለ መንፈስ ቅዱስ የቀረበ መሆኑን ገልጦአል። (የዶክተር ሞሪስ ትምህርተ መለኮት ሁለተኛ መጽሐፍ፥ ገጽ 67)

<u>አንድነትና ሦስትነት በሐዲስ ኪዳን</u>:- ከመጀመሪያው ጀምሮ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ስለሦስ ትነት ትምህርት ግልጽ ሆኖ ቀርቦአል። ከሦስትነቱም ትምህርት ጋር በመለኮታዊ ጠባዩ ሳይከ ፈል ስለ እግዚአብሔር አንድነት ተረጋግጦአል። ለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት:-

«ኢየሱስ ተጠምቆ ከውሃው እንደወጣ፥ ወዲያውኑ ሰማይ ተከፈተ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በርግብ አምሳል ወርዶ በኢየሱስ ላይ ሲያርፍ አየ። በዚያኑ ጊዜ ‹እነሆ፥ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው› የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ» (ማቴ :ም:3 ቍ: 16–17፥ ማር: ም:1 ቍ9 –11፥ ሉቃም:3 ቍ:21–22)። «ጴጥሮስ ገና ይህን ሲናገር ሳለ፥ ብሩህ ደመና ጋረዳ ቸው፤ ከደመናውም ውስጥ ‹በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት› የሚል ድምፅ መጣ» (ማቴ: ም:17 ቍ:5)።

www.ethiopianorthodox.org

«እንግዲህ ወደ ዓለም ሕዝብ ሁሉ ሂዱ፤ በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው የእኔ ደቀ መዛሙርት አድርጉአቸው» (ማቴ: ም:28 ቍ:19)።

«እኔ ራሴ አላውቀውም ነበር፤ ነገር ግን በውሃ እንዳጠምቅ የላከኝ፥ ‹መንፈስ ቅዱስ ሲወርድና ሲያርፍበት የምታየው፥ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው› ሲል ነግሮኛል» (ዮሐ: ም:1 ቍ:33–34)።

«መልአኩም እንዲህ ሲል መለሰ:- ‹መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑል እግዚአብሔርም ኃይል በአንቺ ላይ ይሆናል፤ ስለዚህ ከአንቺ ሚወለደው ሕፃን ቅዱስ ነው፤ የእግዚአብሔርም ልጅ ይባላል»› (ሉቃ:ም:1ቍ:35)።

<u>የሦስትነት እምነት በሃይማኖት ቀኖና ውስጥ</u>:- የኒቅያውና የቍስጥንጥንያው ጉባኤ የሃይማኖት ቀኖና የአንድነትንና የሦስትነትን እምነት ያረጋግጣል።

<u>ስለ አብ</u>

«ሁሉን በያዘ፥ ሰማይንና ምድርን፥ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።»

<u>ስለ ወልድ</u>

«ከዘመናት ሁሉ በፊት ከአብ በተወለደ፥ በእግዚአብሔር አንድያ ልጅ በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን። እርሱም ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ፥ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ፥ በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል፥ ሁሉ ነገር በእርሱ የተፈጠረ ነው። ስለ እኛ ስለ ሰው ዘር፥ እኛን ለማዳን፥ ከሰማያት ወረደ፤ በመንፈስ ቅዱስም ከድንግል ማርያም ሥጋን ለብሶ ሰው ሆነ፤ በጰንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ተሰቀለ፤ ሕማማትን ተቀብሎ ሞተ፤ ተቀበረ፤ በሦስተኛውም ቀን ከሞት ተነሣ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈ፥ ወደ ሰማይ ዐረገ፤ በአብ ቀኝም ተቀመጠ፤ በሕያዋንና በሙታን ላይ ለመፍረድ ዳግመኛ ተመልሶ በክብር ይመጣል፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም»

<u>ስለ መንፈስ ቅዱስ</u>

«ሕይወትን በሚሰጥ ጌታ፥ ከአብ በሠረጸ፥ ከአብና ከወልድ ጋር በሚሰገድለት፥ በነቢያት ዐድሮ በተናገረ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን»።

<u>ሦስትነት በአንድነትና አንድነት በሦስትነት</u>:- የእግዚአብሔር ባሕርይ ወይም የእግዚአብሔር ጠባይ የማይከፋፈል ነው። እርሱም ሦስት አካል ያለው አንድ አምላክ ነው። በፍጡር ልንመስለው አይገባም። ሦስት አካል ያለው አንድ አምላክ፥ ወይም አንድ ባሕርይና አንድ ጠባይ ያለው ሦስት አካል ነው። የወልድ አካል አንድ የተከፈለ የመለኮት ክፍል ሳይሆን መለኮት በሙላት ያለው ነው፤ መንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ ነው። እርሱ አምላክ ነው። እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድ፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስንል ሦስት አማልክት ማለታችን ሳይሆን አንድ አምላክ፥ አንድ ባሕርይ፥ አንድ ጠባይ በሦስት አካል ማለታችን ነው።

የእግዚአብሔር መለኮታዊ ባሕርይ የሚከፋፈል አይደለም፤ ለመለኮትም የተከፋፈሉ ክፍሎች የሉትም። የአብ አካል ያለወልድ፥ የወልድ አካል ያለ አብና ወይም የወልድ አካል ያለ መንፈስ ቅዱስ ሊታሰብ አይቻልም። ሦስቱ አካላት የእግዚአብሔርን የመለኮታዊ ባሕርይ ለሦስት እንደማይከፍሉ ሁሉ እንዲሁም የመለኮታዊ ባሕርይ አንድነት የአካላዊ ሦስትነትን ግብር የሚያስቀር አይደለም።

## <u>አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ</u>:-

<u>እግዚአብሔር አብ</u>:- የእግዚአብሔር አባትነት በብሉይ ኪዳንም ችላ የተባለ አይደለም፤ እግዚአብሔር በተለይ ለእስራኤል ሕዝብ አባት ተብሎአል። እግዚአብሔር ለሚፈሩት ሁሉ እንደ አባት ሆኖላቸዋል፤ ይቅርታም አድርጎላቸዋል።

በሐዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር የአባትነት ምሕረት ለዓለም ሁሉ ተዳር ሶአል። ይህም ምሕረት በተለይ ተግባራቸው በጎ ለሆነ፥ በክርስቶስ አምነው በመንፈስ ቅዱስ እንደገና ለተወለዱ፥ ተዳርሶአል። እውነተኞች የእግዚ አብሔር ልጆችም የሚባሉት እነዚህ ናቸው፤ እነዚህም በጸጋ የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑት፥ ከተፈጥሮ ጠባይ በላቀ መንፈሳዊ ልደት ቢወለዱም እንኳ እነርሱ ውሱኖች ፍጥረቶች ናቸው፤ በእነርሱና በክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅነት መካከል ልዩነቱ መታወቅ አለበት። ክርስቶስ ብቻ የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ነው፤ አንድያ የእግዚአብሔር ልጅ የሚባለውም በዚሁ ምክንያት ነው። እርሱ ዘለዓለማዊ ነው፤ በመለኮቱም ከአብ ጋር አንድ ነው።



ከሦስቱ አካላት መካከል ስለ እግዚአብሔር አብ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲህ ይላሉ:-

«የእኛ አምላክ ግን የሁሉ ነገር ፈጣሪ የሆነና እኛም የእርሱ የሆንን እግዚአብሔር አብ ብቻ ነው» (1ኛ: ቆር: ም:8 ቍ:6)።

«በሰማይና በምድር ያለ ቤተሰብ ሁሉ እውነተኛ ስሙን የሚያገኘው ከእግዚአብሔር ነው» (ኤፌ: ም:3 ቍ:15)።

ስለ እግዚአብሔር አባትነት የሚከተሉትን ጥቅሶች ይመለከቷል:- (ዘዳ: ም: 8 ቍ:5፥ ም:32 ቍ6፥ መዝ:68 ቍ:5፥ 103 ቍ:13፥ ኢሳ: ም:63 ቍ:16፥ ም:64 ቍ:8፥ ሆሴ: ም:11ቍ:1፥ ሚል: ም:2 ቍ:10፥ ማቴ። ም:5ቍ: 9፥4–48፥ ዮሐ:ም:1ቍ:12–13፥18)።

<u>እግዚአብሔር ወልድ</u>:- እግዚአብሔር ወልድ የራሱ አካል ያለው ከመሆኑ በቀር ከእግዚአብሔር አብ አይለይም። በሁለቱ መካከል ሁለት የተለያዩ አማልክትን የምናይ አይደለንም። የእግዚአብሔር ወልድ ልጅነት የባሕርይ ልጅነት ነው እንጂ በብሉይ ኪዳን እስራኤላውያንና መላእክት የእግዚአብሔር ልጆች ይባሉ እንደ ነበረው አይደለም (ዘጸ:ም:4 ቍ:22፥ ኢዮ:ም:1 ቍ:6)።

ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅነትና ከእግዚአብሔር አብ ጋር ስላለው ግንኙነት የሚከተሉትን ጥቅሶች ይመለከቷል:-

«አባቴ ሁሉን ነገር ሰጥቶኛል፤ ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ ማንም የለም፤ እንዲሁም ከወልድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም፤ ማንም ወልድ ካልገለጠለት በቀር አብን ሊያውቅ አይችልም» (ማቴ:ም:11 ቍ:27)።

«ቃል በመጀመሪያ ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ይህም ቃል እግዚአብሔር ነበረ። እርሱ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጠረ፤ ከተፈጠረው ሁሉ አንድም ነገር ያለ እርሱ የተፈጠረ የለም» (ዮሐ:ም:1ቍ:1–3)።

«አብ የሞቱትን እንደሚያስነሣና ሕይወትን እንደሚሰጣቸው ወልድም እንዲሁ ለፈለገው ሰው ሕይወትን ይሰጠዋል» (ዮሐ:ም:5 ቍ:21)።

«እኔና አብ አንድ ነን» (ዮሐ:ም:10 ቍ:30)።

«ኢየሱስ ይህን ከተናገረ በኋላ ወደ ሰማይ ቀና ብሎ እንዲህ አለ:- አባት ሆይ፥ እነሆ ሰዓቱ ደርሶአል፤ ልጅህ እንዲያከብርህ ልጅህን አክብረው› (ዮሐ:ም:17 ቍ:1)።

«እነርሱ በትውልዳቸው ከነገድ አባቶች የመጡ ናቸው፤ ክርስቶስም በሥጋ የመጣው ከእነርሱ ነው፤ እርሱ ከሁሉ በላይ የሆነና ለዘለዓለም የተባረከ አምላክ ነው» (ሮሜ:ም:9 ቍ:5)።

«እርሱ የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅ ነው፤ እርሱ በባሕርዩ ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም ትክክል ነው፤ በኀያል ቃሉ ዓለምን ሁሉ ደግፎ ይዞአል፤ ሰዎችንም ከኃጢአት ካነጻ በኋላ በሰማይ በኀያሉ እግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦአል» (ዕብ:ም:1ቍ:3)።

<u>እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ</u>:- በብሉይ ኪዳን ብዙ ጊዜ መንፈስ ተብሎ የተገለጠው ኀይል ለማለት እንጂ አንድ መለኮታዊ አካል ለማለት አልነበረም። በእርግጥ ዐልፎ ዐልፎ መለኮታዊ አካልን የሚመለከት ሐሳብ ቀርቦአል። ለምሳሌ በትንቢተ ኢሳይያስ ም:48 ቍ:16 እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል ሲል መንፈስ ቅዱስን ያመለክታል። እንደዚሁም ኢሳ.6፥9 እና የሐዋ 28፥26ን ያነፃፅሯል። ከዚህም ሌላ፥ የሚከተሉትና ሌሎችም «የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ» (ኢዮ 33፥4)።

«ቅዱስ መንፈስህን ከእኔ አታውጣ» ሲል መንፈስ ቅዱስን ያመለክታል (መዝ:50 ቍ:11)።

በሐዲስ ኪዳን ግን መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ አካል መሆኑ በግልጥ ተመልክቶአል:-

ለምሳሌ ጌታችን በተጠመቀ ጊዜ እግዚአብሔር አብ ከሰማይ ድምፁን ሲያሰማ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በርግብ አምሳል ወርዶአል (ማቴ:ም:3 ቍ:13–17፥ መር:ም:1 ቍ:9–11፥ ሉቃ:ም:3 ቍ:21–22)።

ጌታችን ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ደቀ መዛሙርቱን ወደ አገልግሎት ሲልካቸው በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ አዞአቸዋል (ማቴ:ም:28 ቍ:19)።

www.ethiopianorthodox.org

«መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑል እግዚአብሔርም ኀይል በአንቺ ላይ ይሆናል፤ ስለዚህ ከአንቺ ሚወለደው ሕፃን ቅዱስ ነው፤ የእግዚአ ብሔር ልጅም ይባላል» (ሉቃ:ም:1 ቍ:35)።

«በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሰው በደሉ ይቅር ይባልለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሰው ግን በደሉ ይቅር አይባልለትም» (ሉቃ:ም:12ቍ:10)።

«እኔ አብን እለምነዋለሁ፤ እርሱም ለዘለዓለም ከእናንተ ጋር የሚኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣች ኋል፤ ይህም የእውነት መንፈስ ነው» (ዮሐ:ም:14 ቍ:16–17)።

«አብ በእኔ ስም የሚልከው አጽናኙ መንፈስ ቀዱስ ግን ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል፤ እ የነገርኳችሁንም ሁሉ እንድታስታውሱ ያደርጋችኋል» (ዮሐ:ም:14 ቍ:26)።

«ነገር ግን ከአብ የሚወጣና እኔም ከአብ ዘንድ የምልከላችሁ የእውነቱ መንፈስ አጽናኙ ሲመጣ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል» (ዮሐ:ም:15 ቍ:26)።

«ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለው:- ሐናንያ ሆይ፥ በመንፈስ ቅዱስ ላይ እንድትዋሽና ከመሬቱ ሽያጭ ከፊሉን እንድታስቀር ያደረገህ ሰይጣን ስለምን ወደ ልብህ ገባ? ሳትሸጠው በፊት መሬቱ የአንተ አልነበረምን? ከሸጥከውስ በኋላ ገንዘቡ የአንተ አልነበረምን? ታዲያ ይህን ነገር ስለምን በልብህ አሰብክ? የዋሸኸው በእግዚአብሔር ላይ ነው እንጂ በሰው ላይ አይደለም» (የሐ: ሥ: ም: 5 ቍ:3–4)።

«የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፥ የእግዚአብሔር ፍቅር፥ የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን» (2ኛ:ቆ:ም:13 ቍ:14)።

<u>ስለ ምሥጢረ ሥላሴ የቅዱሳን አባቶች ምስክርነት</u>

<u>ቅዱስ ጎርጎርዮስ የቂሣርያ ኤጲስ ቆጶስ</u>:- «አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ እንላለን።... የእግዚአብሔር አቃኒም ስሞች ናቸው፤ ስሞችም አቃኒም ናቸው። አቃኒም ትርጓሜው በገጽ በመልክ ፍጹማን የሚሆኑ፥ ባለመለወጥ ጸንተው የሚኖሩ አካላት ማለት ነውና ባሕርዩ አንድ ሲሆን ሦስቱ አካላት ጸንተው በሚኖሩ በእሊህ ስሞች ይጠራሉ፤ ሦስት አካላት አንድ መለኮት ናቸው» (ሃ.አበ.ገጽ 39–40)።

<u>ሐዋርያትን መሰሉ ቅዱስ አትናቴዎስ</u>:- «በባሕርይ አንድ እንደሆኑ በሦስቱ እናምናለን፤ እሊህም አብ፥ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ናቸው፤ አብ የሚያድን ነው፤ ወልድም የሚያድን ነው፤ መንፈስ ቅዱስም የሚያድን ነው። አንድ ሲሆኑ ሦስት ናቸው፤ ሦስት ሲሆኑ በባሕርይ፥ በመለ ኮት፥ በክብር በመመስገን በሥልጣን፥ ፍጡራንንም ሁሉ በመፍጠር፥ በፈቃድ፥ ኃጢአትን ይቅር በማለት፥ በማትለወጥ ዕውቀት፥ በረከትን በመስጠት አንድ ናቸው (ሃ.አበ.ገጽ 85)።

<u>ቅዱስ ባስልዮስ የቂሣርያ ኤጲስ ቆጶስ</u>:- የሦስቱ አካላት መለኮት ፍጹም አንድነት ልናውቅ ይገባናል፤ የእነርሱ የሚሆን አንድ መለኮትን አንድ በማድረግ እናዋሕድ። በአብ ወላዲነት፥ አሥራጺነት መለኮት አንድ እንዲሆን ሃማኖትን እንመን፤ ወልድ ከአብ ተወልዷልና መንፈስ ቅዱስም ከአብ ተገኝቷልና፥ አብ ከወልድ ወልድም ከመንፈስ ቅዱስ ሳይቀድም ወልድ ከአብ በመወለዱ መንፈስ ቅዱስም ከአብ በመሥረጹ የፈጣሪአችን የሦስትነቱ መለኮት አንድ ይሆናል» (ሃአበ.ገጽ107)።

<u>የሮም ሊቀ ጳጳስ አቡሊዲስ</u> :- «አብ ወልድን የወለደ ነውና ዳግመኛም በማይነገር በሐሳብም በማይመረመር ግብር መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ ተገኝቷልና አብ ከወልድ ወልድም ከመንፈስ ቅዱስ ሳይቀድም፥ መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ወልድም ከአብ ወደ ኋላ ሳይሆን ነው። ወልድም ለአብ ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ለአብ ለወልድ እስትንፋ ቻው ነው፤ የሦስቱ አካላት መለኮት አንድ እንደሆነ በዚህ ዐውቀን ለእርሱ እንሰግዳለን» (ሃ.አበ.ገጽ137–138)።

<u>የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ዮሐንስ</u> :- «አንድ አምላክ ብለን የምንሰግድላቸው ሥሉስ ቅዱስ በባሕርይ በመለኮት አንድ እንደሆኑ እናምናለን፤ እሊህም አብ፥ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ናቸው። እሊህም ሦስቱ አካላት በገጽ ፍጹማን እንደሆኑ በሥልጣን፥ በባሕርይ፥ ከዘመን አስቀድሞ በመኖር፥ በጌትነት፥ በመፍጠር፥ ሳይለወጡ በመኖር አንድ አንደ ሆኑ እናምናለን፤ ይህን እንዲህ ብሎ የማያምነውን እኛ እናወግዘዋለን» (ሃ:አበ:ገጽ:167)።



www.ethiopianorthodox.org

<u>ቅዱስ ጎርጎርዮስ የእንዚናዙ ኤጲስ ቆጶስ</u> :- «ከሁሉ አስቀድሞ በአካል ልዩ፡ በክብር አንድ የሚሆን ሦስትነትን እናስተምራለን፤ እሊህም አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ ናቸው፤ ሥላሴ በመለኮት አንድነት መለየት የለባቸውም፤ አካላት ግን በባሕርይ መለየት ሳይኖር እያንዳንዱ አካል በገጽ፥ በመልክ ፍጹም ነው። ለአብ የአባትነት ስም፡ የአባትነት ክብር አለው፤ ለወልድም በባሕርይ ክብሩ ከአብ ሳያንስ የልጅነት ስም፥ የልጅነት ክብር አለው፤ መንፈስ ቅዱስም እንዲህ በክብር አይለይም፤ ነገር ግን ተለውጦ አብ ወልድ አይባልም፤ በዚህ ጊዜ ተገኘ አይባልም፤ በመለኮት እንደ አብ፥ እንደ ወልድ ነው እንጂ፤ እስትንፋሳቸው ነውና፥ ሦስቱም ትክክል ናቸውና» (ሃ.አበ.ገጽ 210–211)።

<u>ቅዱስ ቄርሎስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት</u> :- «አንድ መለኮት አንድ ባሕርይ፥ አንድ ኀይል፥ አንድ ልዕልና፥ አንድ ጌትነት፥ አንድ ክብር ከጥንት አስቀድሞ የነበረ አንድ ቀዳማዊነት ነው፤ በሦስት አካላት፥ በሦት ገጻት ፍጹማን ናቸው፤ ግዙፋን አይደሉም፤ ያልተፈጠሩ ናቸው፤ ድካም የማይስማ ማቸው፥ የማይለወጡ ናቸው፤ ለመገኘት ጥንት፥ ለዘመን ፍጻሜ የላቸውም። አብ፥ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በአካል ሦስት በባሕር አንድ ነው ብሎ ማመን ይህ ነው የማይመረ ምር በቅድምና የነበረ» (ሃ.አበ.ገጽ 256)።

<u>ቅዱስ ቴዎዶስዮስ፥ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት</u>:- «በአካል፡ በገጽ ሦስት ነው፤ በመለኮት አንድ ነው፤ ሥሉስ ቅዱስ አንድ ናቸው፤ አንድ አገዛዝ፥ አንድ ጌትነት፤ አንድ መለኮት፥ አንድ መንግሥት ገንዘባቸው ነው። አብ ከወልድ ተለይቶ የኖረበት፥ ኖሮ ኖሮ ወልድን የወለደበት፥ መንፈስ ቅዱስን ያሠረጸበት ዘመን የለም፤ አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ በቅድምና የነበሩ ናቸው እንጂ፤ ወልድ ከእግዚአብሔር አብ ተወለደ፤ መንፈስ ቅዱስም ከአብ ተገኘ፤ ሥሉስ ቅዱስ ያልተፈጠሩ ናቸው» (ሃ.አበ.ገጽ 342)።

<u>ቅዱስ ሳዊሮስ፥ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት</u>:- «ሦስቱ አካላት በመልክ ፍጹማን ናቸው፤ ሦስቱ ገጻት በክብር፥ በብርሃን አንድ ናቸው፤ በባሕርይ አንድ ናቸው፤ በሥልጣን አንድ ናቸው፤ በጌትነት አንድ ናቸው፤ በመለኮት አንድ ናቸው፤ በመስገድ አንድ ናቸው፤ በመመስገን አንድ ናቸው፤ የታመኑ ሰዎች እንደሚያምኑት። .... በሦስቱ አካላት ውስጥ መገዛዛት፥ መታጠቅ መፍታት የለም፤ በማዕረገ መለኮት አንዱ ካንዱ አይበልጥም፤ አንዱ አንዱን እንደ መልክተኛ በሥልጣኑ አያዝዘውም፤ በአንድ መለኮት ክብር፥ በአገዛዝ፥ የሁሉ ፈጣሪ ገንዘብ በሚሆን በባሕርይ ዕውቀት አንድ ናቸው እንጂ» (ሃ.አበ.ገጽ 357)።

## <u>የሕፃናት ጥምቀት</u>

<u>መግቢያ</u>:- አንዳንድ ወገኖች ሕፃናትን አያጠምቁም፤ እኛንም እንዴት ሕፃናትን ታጠምቃላተሁ ብለው ይከራከሩናል። የክርክራቸውም መነሻ የሚከ ተሉት አባባሎች ናቸው:-

አንደኛ/ በማርቆስ ወንጌል ም:16 ቍ:16 ላይ የአመነና የተጠመቀ ይድናል ስለሚልና ሕፃናት ግን ገና ክፉና ደጉን ያልለዩ በመሆናቸው ሊያም ኑም ላያምኑም ስለማይችሉ ያላመኑ ሕፃናትን ማጥመቅ ተገቢ አይደለም ይላሉ።

ሁለተኛ/ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ የተጠመቀው በ30 ዓመት የሥጋ ልደት ዕድሜው ስለሆነ እኛም መጠመቅ ያለብን ካደግንና ክፉንና ደጉን ለይተን በማወቅ ካመንን በኋላ መሆን አለበት ይላሉ።

ቤተ ክርስቲያን በሕፃናት ጥምቀት የምታምነው የቅዱሳት መጻሕፍትንና የቅዱሳን አባቶችን ግልጽ ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ ነው።

<u>ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ጥምቀት ግዴታ ነው</u>:- «አንድ ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም» ሲል ጌታ ለኒቆዲሞስ አረጋግጦ ነግሮታል (ዮሐ:ም:3 ቍ:5)።

ይህ አባባል በማንኛውም ዕድሜ ያለውን ሰው ሁሉ ያጠቃልላል እንጂ ሕፃናትን ለይቶ የሚያስቀር አይደለም። ሕፃናትማ እንዲያውም ለመንግሥተ እግዚአብሔር ቅርብ ናቸው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ:- «መንግሥተ ሰማይ እንደ እነዚህ ላሉት ስለሆነች ሕፃናትን ተዉአቸው ወደ እኔ እንዲመጡ አትከልክሉአቸው» ብሎአል (ማቴ:ም:19: ቍ:14፥ ማር:ም:10 ቍ:15፥ ሉቃ: ም18 ቍ:15–170)።

ሰው ሲወለድ ሳያውቀውና ያለፍላጎቱ የጥንቱን ኃጢአት የሚወርስ ከሆነ፥ ታዲያ ከፉውን ደጉን ለይቶ ከማመኑ በፊት ከዚያች ከጥንተ አብሶ እንዲነጻ ለማድረግ የሚፈጸመው ጥምቀት ከሀ ስሕተቱ እምኑ ላይ ነው? ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት ዋነኛው ግዴታ ጥምቀት ከሆ እግዚአብሔር የሰጣቸውን በረከት እንዳይታደሉ ሕፃናትን የምንከለክላቸው በምን ምክንያት ነው?

ለመጠመቅ ማመን የሚያስፈልገው ክፉንና ደግን ለይቶ ለሚያውቅ ጐልማሳ ነው እንጂ ለሕፃናት አይደለም። ሕፃናት ግን የግል ኃጢአት ያልሠሩ በመሆናቸው የተወረሰውን ኃጢአት ብቻ በጥምቀት ማስወገድ እንጂ ንስሓ መግባት እንኳ አያስፈልጋቸውም። ጌታችን ከኒቆዲሞስ ጋር ሲናገር «እውነት፥ እውነት እልሃለሁ ማንም ሰው እንደገና ካልተወለደ በቀር የእግዚአብ ሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም» ብሎታል (ዮሐ: ም:3 ቍ:3)። የእግዚአብሔርም ቃል የማይታበል ስለሆነ ሕፃናትም ሆኑ ትላልቆች ሰዎች ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለዱ በቀር ድኅነትን አያገኙም (ዮሐ: ም: 3 ቍ:5)።

መንፈስ ቅዱስ በደቀ መዛሙርቱ ላይ በወረደበት በጰንጠቆስጤ በዓል ቀን ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ካደረገው ዝነኛ ንግግር በኋላ አድማጮቹ በጣም ተመስጠው ጴጥሮስንና ሌሎቹን ደቀ መዛሙርት:- ወንድሞች ሆይ ምን እናድርግ ብለው በጠየቁ ጊዜ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በሰጣቸው መልስ እንዲህ ብሎአቸዋል:-

«ንስሓ ግቡ፤ ኃጢአታችሁም ቅር እንዲባልላችሁ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነውን መንፈስ ቅዱስንም ትቀበላላችሁ፤ የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ፥ ጌታ አምላካችን ወደ እርሱ ለሚጠራቸው፥ በሩቅ ላሉትም ሁሉ ነው» (ሐ: ሥ: ም: 2 ቍ:38–39)።

ታዲያ፥ ይህ የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ ለዐዋቂዎች ብቻ ነበርን? ወይስ ለልጆቻቸውም ጭምር ነበር? የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ነው የተባለውን አባባል ቢያስተውሉት ለጥያቄው መልስ በሆነላቸው ነበር።

በብሉይ ኪዳን የነበሩት ብዙዎቹ የሃይማኖት ሥርዓቶች ለሐዲስ ኪዳን ሥርዓት ጥላ ማለት ምሳሌ ነበሩ። ለምሳሌ ግዝረት በእግዚአብሔርና በእስራ ኤል ሕዝብ መካከል የቃል ኪዳን ምል ክት የነበረ ሲሆን እርሱም ለጥምቀት ምሳሌ የነበረ መሆኑን በሚቀጥለው ጥቅስ እንመልከት:-

«በእርሱም በማመናችሁ ተገርዛችኋል፤ ይህም መገረዛችሁ ኃጢአተኛውን ሥጋ ለማስወ ገድ በክርስቶስ የተደረገ ነው እንጂ ሰው ሠራሽ መገረዝ አይደለም፤ በተጠመቃችሁ ጊዜ ከክርስ ቶስ ጋር ተቀበራችሁ፤ ከእርሱም ጋር ከሞት ተነሥታችኋል» (ቆላ:ምዕ:2 ቍ:11–12)።

እንዲሁም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በላከው መልእክቱ እስራኤላውያን ዐዋቂዎችና ሕፃናትን ሳይለዩ በሙሴ አማካይነት ባሕሩን እንዲሻገሩ ተደርገዋል:-

«ወንድሞቼ ሆይ፥ አባቶቻችን ደመና ከበላያቸው ሆኖ ይመራቸው እንደነበረና ሁሉም ቀይ ባሕርን እንደተሻገሩ ላስታውሳችሁ እወድዳለሁ። የሙሴ ተባባሪዎች ለመሆንም በዚህ ደመናና በዚህ ባሕር ተጠመቁ» (1ኛ:ቆሮ:ም:10 ቍ:1–2)።

በእነዚህ ከላይ በተጠቀሱት ጥቅሶች መሠረት ግዝረትን የተገረዙትና ባሕሩንም የተሻገሩት ሽማግሌዎች፥ ወጣቶችና ሕፃናት ሁሉ ናቸው እንጂ ዐዋቂዎቹ ብቻ አልነበሩም።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሕፃናት በወላጆቻቸው አማካይነት የቃል ኪዳኑን ሥርዓት ይፈጽሙ ነበር። ለምሳሌ አብርሃም እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት ልጁን ይስሐቅን በተወለደ በስምንተኛው ቀን ገርዞታል (ዘፍ:ም:17 ቍ:12፥ ም:21 ቍ:4)።

<u>የቢላግዮስ ክሕደት</u>:- በአራተኛው መቶ ዘመን የተነሣው ቢላግዮስ የአዳም ኃጢአት በራሱ የቀረ እንጂ ወደ ትውልድ ያልተላለፈ ስለሆነ ሕፃናት ለተወረሰው ኃጢአት ስርየት መጠመቅ አያስፈልጋቸውም ብሎ አስተምሮ ነበር። ይህን ክሕደት ለመቃወም ብዙ ቅዱሳን ሲኖዶሶች ተሰብስበዋል። ከእነዚህም መካከል በካርቴጅ በ418፥ በ424 እና በኤፌሳን በ431 የተሰበሰቡት ይገኙበታል።

ባለ መዝሙሩ:- «እነሆ፥ በዐመፃ ተፀነስሁ፥ እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ አላለምን! (መዝ:51 ቍ:5)። እንዲሁም ነቢዩ ኢሳይያስ:- «አንተ ፈጽሞ ወንጀለኛ እንደሆንህ ከማሕ ፀንም ጀምረህ ተላላፊ ተብለህ እንደተጠራህ ዐውቄአለሁና» አላለምን? (ኢሳ:ም:48 ቍ:8)።



እንዲሁም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ:- «በአንድ ሰው ምክንያት ኃጢአት ወደ ዓለም ገባ፤ በኃጢአት ምክንያት ሞት መጣ፤ ይኸውም ሰው ሁሉ ኃጢአት ስለ ሠራ በሰው ሁሉ ላይ ሞት መጣ» ብሎአል (ሮሜ:ም:5 ቍ:12)።

<u>ጉባኤው በቢላግዮስ ላይ ያሳለፈው ውሳኔ</u>:- ከእናታቸው ማሕፀን አዲስ የተወለዱ ሕፃናትን ከማጥመቅ የሚከለክልና ጥምቀት የሚጠቅመው ለግል ኃጢአት ማስተስረያ እንጂ ለተወረሰ ኃጢአት አይደለም የሚል የተወገዘ ይሁን በማለት ውግዘቱን አስተላልፎአል። አለበለዚያ ግን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በአንድ ሰው አማካይነት ኃጢአት ወደዓለም ገባ ያለው አባባል ትርጕም ሊኖረው አይችልም (ሮሜ:ም:5 ቍ12)። ስለዚህ ሁሉም በደሉ፤ ኃጢአትም በሰው ሁሉ ላይ መጣ። ይህንንም አባባል ቤተ ክርስቲያን ከምታምንበት እምነት ውጪ ልንረዳው አይገባም። በዚህ እምነት መሠረት ሕፃናት በራሳቸው የሠሩት ኃጢአት አይኑር እንጂ እንደገና ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ በመወለድ ከተወረሰው ኃጢአት መንጻት ይኖርባቸዋል።

<u>ቤተ ሰብ ተጠመቀ ሲባል ሕፃናትን ትቶ ዐዋቂዎች ብቻ ማለት ነውን</u>? ሐዋርያት ብዙ ቤተሰቦችን እንዳጠመቁ ተገልጾአል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ ሊድያንና ቤተ ሰብዋን አጥምቀዋል (የሐ:ሥ:ም:16 ቍ:15)።

የወህኒ ቤቱ ዘበኛ ከነቤተሰቡ ተጠመቀ (የሐ:ሥ:ም:16 ቍ:33)።

ቀርጶስ የሚባል የምኵራብ አለቃ ከቤተሰቡ ሁሉ ጋር በጌታችን አመነ፤ ብዙ የቆሮንቶስ ሰዎችም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲናገር ሰምተው አመኑና ተጠመቁ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም የእስጢፋኖስን ቤተሰብ አጥምቋል (1ኛ:ቆሮ:ም1 ቍ:16)።

በዚህም መሠረት ቤተሰብ ተጠመቀ ሲባል በየቤተሰቡም ሕፃናት ሊኖሩ ስለሚችሉ ሕፃናትም ተጠምቀዋል ማለት ነው።

## ጥያቄዎች

1. ከክርስቲያን ሃይማኖት መታወቂያዎች መካከል አንዱ የትኛው እምነት ነው?
2. እግዚአብሔር ሦስት አካል አለው ማለት ሦስት አማልክት አሉ ማለት ነውን?
3. የሦስትነት ግብሮች የተባሉት ምን ምን ናቸው?
4. ለአንድነትና ለሦስትነት ሁለት ምሳሌዎችን አቅርብ።
5. የሦስቱ አካል ግብሮች ምን ይባላሉ?
6. አርዮስስ ስለወልድና መንፈስ ቅዱስ ምን አለ?
7. አብ ወልድን የወለደ በመሆኑ የአርዮስ ምክንያታዊነት ምንድነው?
8. እንደ አርዮስ አባባል አብ፥ በወልድ አማካይነት ምን አደረገ?
9. በወልድ ጠባይ ውስጥ መለወጥ ከሌለበት በምን ምክንያት ነው አለ?
10. እንደ አርዮስ አባባል ወልድ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው እንዴት ነው?
11. የአርዮስ ክሕደት ታላቁን የክርስትና እምነት ተስፋ የሚቃረነው በምን ዐይነት ነው?
12. አቡሊናርዮስ ስለ ሦስትነት የነበረው ክሕደት እንዴት ነበር?
13. በክርስቶስስ ሥጋ መልበስ ላይ ምን ይል ነበር?
14. የሰባልዮስ ክሕደት ኡንዴት ነበር?
15. የመቅዶንዮስ ክሕደት እንዴት ነበር?
16. ለክሕደቱ መነሻ ያደረገው የትኛውን ጥቅስ ነበር?
17. በብሉይ ኪዳን የሦስትነት ምሥጢር ግልጥ ሆኖ ያልቀረበው ለምን ነበር?
18. በየትኛዎቹ ሲኖዶሶች ወይም ጉባኤዎች ነው ስለምሥጢረ ሥላሴ የተነገረው?
19. አንዳንድ ወገኖች ሕፃናትን ማጥመቅ የሚቃረኑት በምን ምክንያት ነው?
20. ቤተ ክርስቲያን በሕፃናት ጥምቀት የምታምነው በምን መሠረት ነው?
21. ጥምቀት ለምን ይጠቅማል?
22. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሕፃናት ምን አለ?
23. ጥንተ አብሶ ማለት ምን ማለት ነው?
24. ጥንተ አብሶና ጥምቀት ምን ግንኙነት አላቸው?

www.ethiopianorthodox.org

25. ለመጠመቅ አስቀድሞ ማመን የሚያስፈልጋቸው እነማን ናቸው?
26. ሕፃናት ኃጢአት አለባቸውን?
27. ብዙዎቹ የብሉይ ኪዳን ሥርዓቶች ምን ነበሩ?
28. በብሉይ ኪዳን የቃል ኪዳን ምልክት ምን ነበር?
29. ጥላነቱ ወይም ምሳሌነቱ ለምን ነበር?
30. የቢላግዮስ ክሕደት ምን ነበር?
31. ቤተሰብ ተጠመቀ በሚልበት ጊዜ ምንን እንረዳለን?

# ምዕራፍ 2

# መጽሐፍ ቅዱስ

## ብሉይ ኪዳን

ትንቢተ ሕዝቅኤል:- ይህ ነቢይ መጽሐፉን ሲጀምር በሠላሳኛው ዓመት፥ በአራተኛው ወር በአምስተኛው ቀን በሎ ጀመረ። ነቢዩ የተናገረው ዘመን መነሻ መቼ እንደሆነ በትክክል ለማወቅ አስቸጋሪ ቢሆንም እንኳ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የተለያዩ ሐሳቦችን አቅርበዋል። አንዳንዶች እንዳሉት ነቢዩ ሕዝቅኤል ቈጠራውን የጀመረው የይሁዳ ንጉሥ ኢዮስያስ በነገሠ በዐሥራ ስምንተኛው ዓመት የእግዚአብሔር ሕግ መጽሐፍ ከተገኘ በኋላ ከእግዚአ ብሔር ጋር ቃል ኪዳንን በማደስ አምልኮተ እግዚአብሔርን ያጠናከረበትን ጊዜ መነሻ በማድረግ ነው። ሌሎች እንደሚሉት ለአቈጣጠሩ መነሻ ያደረገው የናቡከደነፆር አባት ናቡፖላሳር የተነሣበትን ጊዜ ነው። ቀደም ብላ በአሦራውያን ትገዛ የነበረችውን ባቢሎንን ነጻ ያወጣ ናቡፖላሳር ነው። ለዚህም ድርጊቱ አድናቆት ብዙዎች ሰዎች እርሱን እንደመነሻ አድርገው ይናገሩ ስለነበረ ነቢዩ ሕዝቅኤልም የእነርሱን አርአያነት ተከትሎአል ይላሉ። እንደገና ሌሎች ሦስተኛ ወገኖች ደግሞ የተጠቀሰው ጊዜ የነቢዩ ሕዝቅኤል ዕድሜ ነው ይላሉ። በመጽሐፉም መጀመሪያ ላይ ከካህናት ወገን እንደሆነና አባቱም ቡዚ ይባል እንደነበረ ተናግሮአል። እርሱም ከክርስቶስ በፊት በ597 ዓመት ከንጉሥ ኢኮንያን ጋር ወደ ባቢሎን ከተወሰዱት አንዱ ነው። ለትንቢት አገልግሎትም በእግዚአብሔር የተጠራው በምርኮ ወደ ባቢሎን በተወሰደ በአምስተኛው ዓመት ነው። በዚያም ጊዜ ይኖር የነበረው በከባር ወንዝ አጠገብ ነበር። የትንቢት አገልግሎቱንም ቢያንስ ለኻያ ዓመት አከናውኖአል። እርሱም ኤርምያስና ዳንኤል በነበሩበት ዘመን ነበር።

በሕዝቅኤል ትንቢት እግዚአብሔር ሁለት ዐላማዎች ነበሩት። የመጀመሪያው ዓላማ የሐሰተኞች ምርኮኞች ነቢያትን ትንቢትና የይሁዳ ነቢያትን ትንቢት ለማስተባበል ነው (ኤር: ም:28 ቍ:1–2፥ ኤር: ም: 29 ቍ:24–27)።

በምርኮኞቹ መካከል የነበሩት ሐሰተኞች ነቢያት ኢየሩሳሌምን የባቢሎን ንጉሥ ድል አያደርጋትም፤ ምርኮኞችም በቅርብ ጊዜ ወደ አገራቸው ይመለሳሉ ብለው የሐሰት ትንቢት ተናግረው ነበር። ኤርምያስ ግን ምንም ያኽል ጭንቀት፥ ችግርና እንቅፋቶች ቢደርሱበት ያን ሁሉ ታግሦ በወገኖቹ በአይሁድ ላይ ሊመጣ ስለነበረው ችግርና ወዮታ በትጋት ከመግለጥና ከማስጠንቀቅ የገታውና የአገላለጡንም ጠንከር ያለ ቋንቋ ሊያስለውጠው የቻለ ማንም አልነበረም። እግዚአብሔር የኤርምያስን ትንቢት ለማጠናከርና እነዚያ ሐሰተኞች ነቢያት እስራኤላውያንን ያሳሳቱበትን ሐሰተኛ ትንቢት ለማስተባበል ከምርኮኞቹ አንዱ በነበረው በሕዝቅኤል ተጠቀመ። ይህም የማሳሳቻ ትንቢታቸው ለእስራኤል ልጆች ችግርና ጥፋት ምክንያት ሆኖአል። ኢየሩሳሌምም በከባቢዎችዋ እጅ ወድቃለች እነርሱም ድል አድርገው ሕዝብዋንና ንጉሥዋን ማርከው ወስደዋል (ሕዝ:ም:4 ቍ:1–3 ፥ ም:12 ቍ:1–7)። ይህም የሆነው ለተደበቀና ለታወቀ ኃጢአታቸው ዋጋ ነው (ም:22 ቍ:1–5)።

ስለ ሕዝቅኤል ትንቢት ሁለተኛው የእግዚአብሔር ዐላማ በምርኮ ላይ የነበሩትን አይሁድ ለመገሠጽ ነው። እነርሱም ምንም እንኳ ኃጢአታቸው የበዛ መሆኑን በዐይናቸው የአዩት ቢሆኑ በዐመፃቸውና በእምቢተኛነታቸው ቀጠሉ እንጂ በንስሓ አልተመለሱም። እግዚአብሔርም እርሱን የሚፈሩትን ወደ ንስሓ እንዲመለሱ ጥሪ በማድረግ ጥሪውን ሰምተው ለሚመለሱትም እርሱ ፊቱን ወደ እነርሱ እንደሚመልስ ቃል ገብቶላቸዋል።

www.ethiopianorthodox.org



«ስለዚህ እነሆ፤ እኔ እግዚአብሔር በሰቡና በከሱት በጎች መካከል እፈርዳለሁ። እናንተ በጐናችሁና በትከሻችሁ እየገፋችሁ ደካሞችን እንስሳት በቀንዳችሁ ወጋታችሁ ወደ ሩቅ ቦታ ታባርሩአቸዋላችሁ። ነገር ግን እኔ በጎቼን እታደጋለሁ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ማንም ዘርፎ እንዲወስዳቸው አልፈቅድም፤ በበግና በበግ መካከል እፈርዳለሁ፤ እንደ አገልጋዩ እንደ ዳዊት ያለ ንጉሥ እረኛ አድርጌ አስነሣላቸዋለሁ፤ እርሱም በእንክብካቤ ይጠብቃቸዋል። እኔ እግዚአብሔር አምላካቸው እሆናለሁ፤ እንደ አገልጋዩ እንደ ዳዊት ያለ ንጉሥ ይመራቸዋል፤ ይህን እኔ ተናግሬአለሁ። የሰላም ዋስትና የሚያገኙበትን ቃል ኪዳን ከእነርሱ ጋር እገባለሁ። አደገኞች የሆኑትን አራዊት ከምድራቱ አስወግዳለሁ፤ ስለዚህ በጎቹ በየመስኩ በሰላም ተሠማርተው ሊኖሩና በየጫካውም ሊያድሩ ይችላሉ (ሕዝ: ም: 34 ቍ: 20–25)።

እንዲሁም እንዲህ ብሎአል:- «እኔ እግዚአብሔር ሕዝቤን ሁሉ ከተበተኑባቸው ሕዝቦች መካከል በአንድነት ሰብስቤ ወደ ገዛ ምድራቸው መልሼ የማመጣቸው መሆኔን ንገራቸው። በእስራኤል ምድርና በተራሮችዋ አንድ መንግሥት እንዲሆኑ አደርጋለሁ። ሁሉንም በአንድነት የሚያስተዳድር አንድ ንጉሥ ይኖራቸዋል፤ ዳግመኛም ሁለት ሕዝብ አይሆኑም። መንግሥታቸውም በሁለት አይከፈልም። ዳግመኛ በጣዖቶቻቸው፥ በአጸያፊ ነገሮቻቸው ወይም በሌሎች ኃጢአቶቻቸው ራሳቸውን አያረክሱም፤ ከወደቁበት ክሕደት አውጥቼ አነጻቸዋለሁ። በዚያን ጊዜ እነርሱ ሕዝቤ ይሆናሉ፤ እኔም አምላካቸው እሆናለሁ። እንደ አገልጋዩ እንደ ዳዊት ያለ ንጉሥ ይኖራቸዋል። በአንድ መሪ ሥር ተጠቃልለው ሕግጋቴንና ሥርዓቴን በታማኝነት ይፈጽ ማሉ። ለአገልጋዩ ለያዕቆብ በሰጠሁትና የቀድሞ አባቶቻቸውም በኖሩባት ምድር እነርሱና ልጆቻቸው የልጅ ልጆቻቸውም ሳይቀሩ ለዘለዓለም ይኖራሉ፤ እንደ አገልጋዩ እንደ ዳዊት ያለ ንጉሥ በእነርሱ ላይ ለዘለዓለም ይነግሣል። ከእርሱ ጋር የዘለዓለም ቃል ኪዳን እገባለሁ፤ ያም ቃል ኪዳን ዘለዓለማዊ ነው፤ እነርሱንም እንደገና መሥርቼ የሕዝቡን ቍጥር አበዛለሁ፤ ቤተ መቅደሴንም ለዘለዓለም ጸንቶ በሚቆይበት ስፍራ በምድራቸው አኖራለሁ። ቤቴም ከእነርሱ ጋር እቈያለሁ፤ እኔ አምላካቸው እሆናለሁ፤ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ። ቤተ መቅደሴ በመካከላቸው ለዘለዓለም እንዲኖር በማደርግበት ጊዜ እኔ እስራኤልን ለራሴ የተለየ ሕዝብ የማደርግ መሆኔን ሕዝቦች ሁሉ ያውቃሉ» (ሕዝ:ም:37 ቍ:21–28)። በመጠመቅ ውሃ ስለመንጻትና በሰዎች ልብም ውስጥ ስለሚያከናውነው ተግባር እንዲህ ብሏል:-

«ከመንግሥታትና ከአገሮች ሁሉ አውጥቼ በመሰብሰብ ወደ ገዛ ምድራችሁ እመልሳችኋለሁ፤ በእናንተ ላይ ንጹሕ ውሃ በመርጨት ከጣዖት አምልኳችሁና ከርኵሰታችሁ ሁሉ እንድትነጹ አደርጋለሁ። አዲስ ልብ እሰጣችኋለሁ፤ አዲስ መንፈስንም በውስጣችሁ አኖራለሁ፤ ከሰውነታችሁ እንደ ድንጋይ የጠጠረ ልብን አውጥቼ እንደ ሥጋ የለሰለሰ ልብን እሰጣችኋለሁ። መንፈሴን አሳድርባችኋለሁ፤ የሰጠኋችሁንም ሕግና ሥርዓት ሁሉ በጥንቃቄ መፈጸም እንድትችሉ አደርጋለሁ» (ሕዝ: ም: 36 ቍ: 24–27)።

ይህ መጽሐፍ አርባ ስምንት ምዕራፎች ያሉት ሆኖ ከላይ ከተገለጡት ጉዳዮች ሌላ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል። የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ ሁለት ቍጥር ኻያ ሁለት ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ መልእክቱን እንዲያስተላልፍ ለነቢዩ የተደረገለት ጥሪ፥ የተሰ ጠውን ከባድ ኀላፊነት ሳይጠጣ ቢቀር የተሰጠው የሚቀጥለው ማስመጠንቀቂያ ይገኝበታል።

«የሰው ልጅ ሆይ፥ እኔ ለእስራኤል ሕዝብ ጠባቂ አድርጌሃለሁ፤ ስለዚህ እኔ የምናገረውን ቃል ስማ፤ የምሰጥህንም የማስጠንቀቂያ ቃል ንገራቸው። ክፉ ሰው በኃጢአቱ ምክንያት ሊሞት መቃረቡን ባስታወቅሁት ጊዜ ሕይወቱን ከሞት ያድን ዘንድ ከክፉ ሥራው እንዲመለስ ባታስጠነቅቀው እርሱ ኃጢአተኛ እንደሆነ ይሞታል፤ ነገር ግን ስለ እርሱ ሞት አንተን በኀላፊነት እጠይቅሃለሁ። ኃጢአተኛውን አስጠንቅቀኸው ከኃጢአቱ ባይመለስ እርሱ በኃጢአተኛነቱ ይሞታል፤ አንተም በኀላፊነት ከመጠየቅ ራስህን ታድናለህ። በደግነቱ የታወቀ ጻድቅ ሰው ክፉ ሥራ መሥራት ቢጀምርና እኔም በችግር ላይ እንዲ ወድቅ ባደርገው፤ አንተ ካላስጠነቀቅኸው በቀር በኃጢአቱ ይሞታል፤ ከዚያ በፊት የፈጸመው መልካም ሥራ ሁሉ አይታሰብለትም፤ ስለ እርሱ ሞት አንተን በኀላፊነት እጠይቅሃለሁ፤ በደግነቱ የታወቀ ጻድቅ ሰው ኃጢአት ከመሥራት እንዲገታ ብታስጠነቅቀውና የአንተን ማስጠንቀቂያ ተቀብሎ ኃጢአት ከመሥራት ቢቈጠብ በሕይወት ይኖራል፤ አንተም በኀላፊነት ከመጠየቅ ራስህን ታድናለህ» (ም:3 ቍ:17–21)።

በዚሁ ክፍል ውስጥ ስለ ኪሩቤልና ስለመንኰራኵሮቹ ራእይ ይተርካል፤ እንዲሁም ስለ እግዚአብሔር ግርማ እና ክብር ይተርካል።

ሁለተኛው ክፍል ከምዕራፍ 3ቍ:23 እስከ መዕራፍ ሃያ አራት ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ሕዝቡ ስለ ክፉ ሥራቸው፥ እግዚአብሔርን ትተው ጣዖትን ስለማምለካቸው ወዮታ ያለባቸው መሆኑን በመግለጥ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶበታል። ነቢዩም የኢየሩሳሌም ካርታ በተሠራባት ጡብ ምሳሌነት ገለጻ እንዲያደርግ በካርታውም ዙሪያ ጒድጓድ ምሶ ዐፈር በመቈለል የምሽግ ማፍረሻ እንዲሠራ ታዝዞአል (ም:4 ቍ:1)። ከዚያም ጠጒሩንና ጢሙን ተላጭቶ ከጠጒሩ ከሦስት አንዱን እጅ ከበባው ከተፈጸመ በኋላ እንዲያቃጥለው ታዞአል (ም:5ቍ:1)። ሌላ የታዘዘው ምሳሌያዊ ድርጊት ደግሞ የሚከተለው ነው:-

«የሰው ልጅ ሆይ፥ አንተ የምትኖረው ዐመፀኞች በሆኑ ሕዝብ መካከል ነው፤ እነርሱ ዐመፀኞች ከመሆናቸው የተነሣ ዐይን እያላቸው አያዩም፤ ጆሮም እያላቸው አይሰሙም። ስለዚህ የሰው ልጅ ሆይ፥ እንደ ስደተኛ ጓዝህን ጠቅልለህ ቀኑ ከመምሸቱ በፊት ጒዞ ቀጥል፤ ይህን ስፍራ ለቅቀህ ወደ ሌላ ስትሄድም ሰው ሁሉ ይይህ፤ እነዚያም ዐመፀኞች ምናልባት ያዩህ ይሆናል። ሁሉም አንተን ማየት እንዲችሉ ገና የቀን ብርሃን ሳለ እንደምትሰደድ ሆነህ ጓዝህን ጠቅልል፤ ቀኑ ሲመሽ ግን ወደ ስደት እንደሚሄድ ሰው ስትዘጋጅ ሁሉም ይዩህ። በሚመለከቱህም ጊዜ የቤትህን ግድግዳ ሸንቍረህ ቀዳዳ አብጅ፤ ጓዝህንም በዚያ ቀዳዳ አሹልከህ አውጣው፤ የምትሄድበትን ስፍራ እንዳታይ ጓዝህን በትከሻህ ተሸክመህ ዐይኖችህን በመጨፈን በጨለማ ስትሄድ ይመልከቱህ፤ የምታደርገውም ሁሉ ለእስራኤላውያን ማስጠንቀቂያ ይሆናል (ም:12 ቍ:2–6)።

በዚሁ ክፍል ውስጥ ስለ ሁለት ንስሮች ምሳሌ ተነግሮአል። እነዚህም ሁለት ንስሮች በባቢሎንና በግብጽ ንጉሦች የተመሰሉ ናቸው። የይሁዳው ንጉሥ ከባቢሎኑ ንጉሥ ጋር ቃል ኪዳን ገብቶ ነበር። ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ስም ምሎ የገባውን ቃል ኪዳን ስላፈረሰ እግዚአብሔር በይሁዳ ንጉሥ ላይ በባቢሎን መማረክና በዚያ መሞት ፍርድ ፈረደበት። ከሕዝቡም ብዙዎቹ ተማረኩ፤ የቀሩትም ተበታተኑ (ምዕራፍ: 17)።

በምዕራፍ 24 ላይ ዝገት በበላው የብረት ድስት ምሳሌ በኢየሩሳሌም ላይ ወቀሳ ተሰንዝሮአል። ቅጣትም እንደማይቀርላት ተናግሮአል። ነቢዩ ይወዳትና የዐይኑ መደሰቻ የነበረችው ሚስቱ መሞትዋ ተነግሮአል። እርስዋም በመሞትዋ ምንም የሐዘን ምልክት እንዳያሳይ ታዞአል። ይህም አይሁድ ሊያዩትና ሊጐበኙት የሚወዱት፥ እንዲሁም የሚደሰቱበት ቤተ መቅደስ የሚፈርስ ለመሆኑና ልጆቻቸውም የሚወሰዱባቸው ለመሆናቸው ምሳሌ ነው።

ሦስተኛው ክፍል ከምዕራፍ 25 እስከ ምዕራፍ 33 ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ በይሁዳ አካባቢ ስለነበሩት እንደ አሞን፥ ሞአብ፥ ዔዶም፥ ፍልስጥኤም፥ ጢሮስ፥ ሲዶናና ግብጽ ላይ ትንቢቶች ተነግረዋል።

አራተኛው ክፍል ከምዕራፍ 33 እስከ ምዕራፍ 48 ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሔር ለነቢዩ የሰጠው ኀላፊነት በድጋሚ ቀርቦአል። በምሳሌም ሲናገር በአንድ አገር ላይ ጦርነት በሚነሣበት ጊዜ የዚያ አገር ሰዎች የጠላትን አመጣጥ የሚጠባበቅ ቃፊር ያቆማሉ። የዚያም ቃፊር ኀላፊነት ጠላት ሲመጣ በሚያይበት ጊዜ ምልክት መስጠት ነው። እርሱ ምልክቱን ሰጥቶ ሰዎች እርሱን ማስጠንቀቂያ ምልክት ካላጤኑት ኀላፊነቱ የራሳቸው ነው። በዚህም ምሳሌ ነቢዩ ለኃጢአተኛ የማስጠንቀቂያ ትምህርት መስጠት ኀላፊነት እንዳለበት ተገልጦለታል። በዚሁም ክፍል ስለ ክርስቶስ በምሳሌ ተነገሮአል።

<u>ትንቢተ ሆሴዕ</u>:- ይህ የብኤሪ ልጅ ነቢዩ ሆሴዕ የትንቢት ሥራውን የጀመረው ዖዝያ፥ ኢዮአታም፥ አካዝና ሕዝቅያስ ተከታትለው በይሁድ በነገሡባቸው ዘመናት፥ እንዲሁም የዮአስ ልጅ ኢዮርብዓም የእስራኤል ንጉሥ በነበረበት ዘመን ነው። ይህም ዘመን ወደ ስድሳ ሁለት ዓመት ይሆናል። ይህን ንም የምዕራፍ 1ቍ:1 አባባል ከትንቢተ ኢሳይያስ ም:1ቍ:1ጋር ያነጻጽሯል። ይህ ሁናቴ የሚያመለክተው ሆሴዕና ኢሳይያስ መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን ይሰጡ የነበሩት በአንድ ዘመን መሆኑን ነው። ይሁን እንጂ የኢሳይያስ አገልግሎት በኢየሩሳሌም ሲሆን የሆሴል አገልግሎት ግን በሰማርያ ነበር። እርሱም ዐሥሩን የእስራኤል ነገዶች እግዚአብሔር በአመንዝራ ሴት እንደመሰ ላቸው በማመልከት በቤቴልና በዳን ለቆሙት የወርቅ ጣዖቶች መስገዳቸውን ጠቅሶ ይወቅሳቸዋል።

ትንቢተ ሆሴዕ ዐሥራ አራት ምዕራፎች ያሉት ሲሆን በአምስት ክፍሎች ይከፈላል።



የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ ሦስት ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የእስራኤል ልጆች እግዚአብሔርን ትተው ጣዖት በማምለካቸው ከፍተኛ ወቀሳ ተሰንዝሮባቸዋል። በዚህም መሠረት የእስራኤል ሕዝብ አምላኩን እግዚአብሔርን ትቶ ጣዖት አምላኪነቱን ለማመልከት ሆሴዕ ዘማዊት ሴት እንዲያገባ ምሳሌያዊ ትእዛዝ ተሰጠው። ያገባት ወይም አገባት ተብሎ የተነገረላት ጎሜር የተባለችው ሴት ለእስራኤል ሕዝብ ጣዖት አምላኪነት ምሳሌ ሆነች። እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ቃል ኪዳን በማፍረሳቸው ከእንግዲህ ወዲህ የእኔ ልጆች አይደላችሁም ለማለትና ምሕረት አላደርግላችሁም ለማለት ከጎሜር የተወለዱትን ልጆች «ኢይዝራኤል፥ ሎሩሐማ፥ ሎዓሚ» ብሎ ስም እንዲያወጣላቸው ነገረው (ም1 ቍ:2–9)። ይህም ሁሉ ሆኖ ግን እግዚአብሔር ፍቅሩን ከእስራኤል ሕዝብ ላይ ሙሉ ለሙሉ ያላነሣ በመሆኑ እንደገና መልሶ ይቅርታ እንደሚያ ደርግ ገልጾአል። (ም:1 ቍ:10–ም:2 ቍ1፥ ም:2 ቍ:14–23)። ስለ እስራኤል ልጆችም ኃጢአት ምክንያት «ያለ ንጉሥ፥ ያለ መሪ፥ ያለ መሥዋዕት፥ ወይም ያለ ሐውልት፥ ያለ ልብሰ ተክህኖ፥ ያለ መተንበያ ምስል (ኤፉድና ተራፊም) ለብዙ ዘመን ይኖራሉ» ተብሎአል (ም:3 ቍ:4)።

ሁለተኛው ክፍል ከምዕራፍ 4 እስከ ምዕራፍ 6 ቍ: 3ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ በሕዝቡና በካህናቱ ላይ ስለ ኃጢአታቸው የተለያዩ ወቀሳዎች ተሰንዝረዋል። ከእነዚህም ኃጢቶች መካከል ታማኝነትና ፍቅር እንዲሁም እግዚአብሔርን ማወቅ መጥፋቱ፥ ቃል ኪዳኖች መፍረሳቸው፥ ግድያ፥ ስርቆት፥ ማመንዘርና ሌሎችም የኃጢአት ዐይነቶች መብዛታቸው ይገኙበታል። ስለዚህም በምድሪቱ ላይ ድርቅ እንደሚመጣ፥ ኑዋሪዎቹ እንደሚሞቱ፥ እንስሳት፥ አዕዋፍና የባሕር ዓሣዎች ሁሉ እንደሚያልቁ ትንቢት ተነግሮአል።

በዚሁም ክፍል ውስጥ በንስሐ ለሚመለሱ ተስፋ እንደሚኖር፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን የሚያድነን ለመሆኑ ጥቈማ ተደርጓል። ይህንኑም በሚከተለው የትንቢት ቃል እንመልከት:-

«ሕዝቡ እንዲህ ይላል፤ ኑ ወደ እግዚአብሔር እንመለስ፤ እርሱ እንደሰበረን እርሱ ይፈውሰናል፤ እርሱ እንዳቈሰለን እርሱ ቍስላችንን ይጠግ ናል፤ ከሁለት ቀን በኋላ ያነቃናል፤ በሦስተኛው ቀን ያስነሣናል፤ በፊቱም በሕይወት እንኖራለን፤ ኑ እግዚአብሔርን ለማወቅ ብርቱ ጥረት እናድርግ፤ እርሱም እንደ ንጋት ብርሃንና ምድርን እንደሚያረካ የበልግ ዝናብ በእርግጥ ወደ እኛ ይመጣል» (ሖ:6 ቍ:1–3)።

ሦስተኛው ክፍል ከምዕራፍ 6ቍ 4 እስከ ምዕራፍ 8 ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ በእስራኤል ሕዘብ ላይ እንደገና ወቀሳ ተሰንዝሮአል፤ በተለየም የሃይማኖትም ሆነ የዓለማዊ መሪነትን ቦታ ተገቢ ላልሆኑ ሰዎች በመስጠታቸው ተወቅሰዋል:-

«ያለ እኔ ፈቃድ ነገሥታትን አነገሡ፤ እኔን ሳይጠይቁ መሳፍንትን መርጠው ሾሙ፤ ከብራቸውና ከወርቃቸው ለገዛ ራሳቸው መጥፊያ የሆኑትን ጣዖቶችን ሠሩ። የሰማርያ ሕዝብ ሆይ፥ በጥጃ ምስል የተሠራ ጣዖታችሁን ተጸይፌአለሁ፤ ቍጣዬ በእናንተ ላይ እንደ እሳት ይነዳል፤ ከበደል የማትነጹት እስከ መቼ ነው? ይህ የጥጃ ጣዖት ለእስራኤል ምን ይጠቅመዋል? በአናጢ እጅ የተሠራ ስለሆነ አምላክ ሊሆን አይችልም፤ ስለዚህ በጥጃ ምስል የተሠራው የሰማርያ ጣዖት ተሰባብሮ ይወድቃል። እነርሱ ነፋስ ይዘራሉ፤ ሀውሎ ነፋስ ያጭዳሉ፤ ዛላ የሌለው የእህል ሰብልም ምግብ ሊሆን አይችልም፤ ፍሬ ቢኖረውም እንኳ የሚበሉት ባዕዳን በሆኑ ነበር። የእስራኤል ሕዝብ ከአሕዛብ በመደባለቅ ተውጠው ስለቀሩ እንደተሰበረ የሸክላ ዕቃ ዋጋቢስ ሆነዋል፤ ብቻውን እንደሚባዝን የሜዳ አህያ እየተንከራተቱ ወደ አሦር ሄዱ፤ እንዲጠብቁአቸውም ዋጋ በመክፈል መንግሥታትን ተለማመጡ፤ መንግሥታትን ለመለማመጥ ዋጋ ቢከፍሉም በአንድነት ሰብስቤ አቀጣቸ ዋለሁ፤ የአሦር ንጉሥና መሳፍንቱ ጨቍነው ሲገዙአቸው ከሥቃያቸው ብዛት የተነሣ ወደ እኔ መጮኽ ይጀምራሉ» (ም:8ቍ:4–10)።

አራተኛው ክፍል ከምዕራፍ 9 እስከ ምዕራፍ 13 ቍጥር 13 ድረስ ነው። በዚህም ክፍል በእስራኤል ላይ የእግዚአብሔር ወቀሳ፥ በንስሓ እንዲመለሱ ጥሪና፥ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ከግብጽ ስደት መመለስ ከእስራኤል ልጆች ከግብጽ መውጣት ጋር ምሳሌነት ተነግሮበታል።

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- እስራኤል ሕፃን በነበረ ጊዜ ወደድኩት፤ የምወደውንም ልጄን ከግብጽ እንዲወጣ ጠራሁት። ነገር ግን ሕዝቤን እስራኤልን ይበልጥ ወደ እኔ እንዲቀርቡ

www.ethiopianorthodox.org

በጠራኋቸው መጠን እነርሱ ይበልጥ ከእኔ እየራቁ ሄዱ። በዓል ተብሎ ለሚጠራው ጣዖት መሥዋዕት ከማቅረብና ለምስሎቹም ዕጣን ከማጠን አልተቈጠቡም» (ም:11 ቊ:1–2።

አምስተኛው ክፍል ከምዕራፍ 13 ቊ:14 እስከ ምዕራፍ 14 ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ታዛዦች ለሚሆኑ የእግዚአብሔር አዳኝነት ተስፋ ተሰጥቶበታል።

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- ሕዝቤን ከከዳተኛነታቸው ፈውሼ ወደ እኔ እመልሳቸዋለሁ፤ ቊጣዬንም ከእነርሱ አርቃለሁ። ለእስራኤል ሕዝብ በደረቅ ምድር እንደሚወርድ ዝናብ እሆናለሁ። እንደ አበባ ይፈካሉ፤ እንደ ሊባኖስም ዛፍ ሥር ይሰድዳሉ፤ አዲስ ሕይወትና ዕድገት ያገኛሉ፤ እንደ ወይራ ዛፍ የሚያምሩ ይሆናሉ፤ እንደ ሊባኖስም ዛፍ መልካም መዓዛ ይሰጣሉ፤ ተመልሰውም በእኔ ጥላ ሥር ይሆናሉ፤ እንደ እህል ቡቃያ ይለመልማሉ፤ እንደ ወይን ተክልም ያብባሉ፤ እንደ ሊባኖስ የወይን ጠጅ ዝነኛ ይሆናሉ። የእስራኤል ሕዝብ ከእንግዲህ ወዲህ ከጣዖት ጋር ምንም ግንኙት አይኖራቸውም፤ እኔ ጸሎታቸውን እሰማለሁ፤ እንከባከባቸዋለሁም፤ እንደ ለምለም ዛፍ ጥላ እሆናቸዋለሁ፤ የበረከታቸው ሁሉ መገኛ እኔ እሆናለሁ» (ም:14ቊ:4–8)።

<u>ትንቢተ ኢዩኤል</u>:- ይህ ነቢይ ስላገለገለበት ዘመን ግልጥ የሆነ ማስረጃ የለም፤ ነገር ግን በኢሳይያስና በሆሴዕ ዘመን አገልግሎት እንደሰጠ ይገመታል። ከአነጋገሩ ለመረዳት እንደሚቻለው አገልግሎቱ በይሁዳ መንግሥት ብቻ የተወሰነ ነበር። ወደ አገልግሎት የተጠራበትን ምክንያት ሲያብራራ በሕዝቡ ላይ ሊወርድ ስላለው የአንበጣ መንጋ ጾምና ጸሎት ይደረግ ዘንድ ሕዝቡን እንዲያስጠነቅቅ ነው። ይህንኑ በሚከተለው ሁናቴ ያብራራዋል:-

«እናንተ ሰካራሞች ከእንቅልፋችሁ ነቅታችሁ አልቅሱ፤ እናንተም የወይን ጠጅ መጠጣት የምታዘወትሩ ምርር ብላችሁ አልቅሱ፤ ስፍር ቊጥር የሌለው ብርቱ የአንበጣ መንጋ እንደ ወራሪ ጦር በምድራችን ላይ መጥቶአል፤ ... የወይን ተክሎቻችንን ሁሉ አጠፋ፤ የበለስ ዛፎቻችንንም ቈረጣጥሞ በላ።.... ስለዚህ የሠርጋቸው ዕለት እጮኛዋ እንደሞተባት ሙሽራ ሁላችሁም ማቅ ለብሳችሁ አልቅሱ፤ በእግዚአብሔር ቤት መባ ሆኖ ሚቀርብ እህልም ሆነ የወይን ጠጅ በመታጣቱ የእግዚአብሔር አገልጋዮች የሆኑት ካህናት ያለቅሳሉ፤ እርሻዎች ባዶአቸውን ቀርተዋል፤ እህል ጠፍቶአል፤... ስንዴውና ገብሱ፥ ሌላውም መከር ሁሉ ስለጠፋ እናንተ ገበሬዎች እዘኑ፥ ለአምላካችሁ የምታቀ ርቡት እህልም ሆነ የወይን ጠጅ መባ ስለሌለ እናንተ በመሠዊያው የምታገለግሉ ካህናት ማቅ ለብሳችሁ እዘኑ... ጾምን ዐውጁ፤ ለመንፈሳዊ ስብሰባ ሕዝቡን ጥሩ፤ አለቆችንና የአገሩን ሕዝብ ሁሉ ወደ አምላካችን ወደ እግዚአብሔር ቤት ሰብስቡ፤ በዚያም ወደ እግዚአብሔር ጩኹ» (ም:1 ቊ:5–14)።

መጽሐፉ ሦስት ምዕራፎች ያሉት ሆኖ እያንዳንዱ ምዕራፍ ጠቃሚ ስለሆኑ ጉዳዮች የሚናገር ነው።

የመጀመሪያው ምዕራፍ ያን የመሰለ ሁናቴ ታይቶ የማይታወቅ የአንበጣ መንጋ መጥቶ ሰብልንና ዛፎችን ሁሉ ስለሚያጠፋ ሕዝቡ ሁሉ በጾምና በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ይጮኽ ዘንድ ያሳስባል።

ሁለተኛው ምዕራፍ ወደ እግዚአብሔር የመመለሻውን ዕቅድ ያዘጋጃል፤ እንዴት ንስሓ እንደሚገባ፥ ከንስሓ መግባት በኋላ ድኅነትን ስለመታደል፥ ቁሳዊና መንፈሳዊ በረከቶችን ስለማግኘት፥ ይኸውም ልዑል እግዚአብሔር በሰው ዘር ሁሉ ላይ መንፈሱን በሚያፈስበት ጊዜ መሆኑን ይገልጣል።

በሦስተኛው ምዕራፍ የማይታዘዙትን እግዚአብሔር በቊጣው እንደሚቀ ጣቸውና ለታዛዦች ደግሞ የወንጌልን በረከት እንደሚሰጣቸው ተገልጦአል።

<u>ትንቢተ አሞጽ</u>:- አንዳንድ ሊቃውንት እንደሚሉት ከትንቢት መጻሕፍት መጀመሪያ የተጻፈው ትንቢተ አሞጽ ነው። ሌሎች ደግሞ እንደሚሉት በመጀ መሪያ የተጻፈው ትንቢተ ሆሴዕ ነው፤ ቀጥሎ ኢዩኤል፥ ከዚያ ዮናስ፥ አሞጽና ኢሳይያስ ተከታታይ ናቸው። እንደገና ሌሎች ደግሞ ትንቢተ ዮናስ ከሁሉም ይቀድማል ይላሉ። ይህም ሆነ ያ ወይም ሌላው አስተሳሰብ ነቢዩ አሞጽ የትንቢት ሥራውን የጀመረው በይሁዳ ንጉሥ በዖዝያና በእስራኤል ንጉሥ በዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመን ነው።

አሞጽ በተጠራበት ጊዜ የበግ እረኛና የሾላ ፍሬ ጠባቂ እንጂ ከነቢያት ወገን አልነበረም (ም:7 ቊ:14)። እርሱም በይሁዳ መንግሥት ውስጥ በምትገኘው በተቆዓ ይኖር ነበር። የእርሱ ክፍል በይሁዳ ግዛት ውስጥ ቢሆንም እንኳ እግዚአብሔር እርሱን ለአገልግሎት የጠራው



www.ethiopianorthodox.org

በእስራኤል ግዛት ውስጥ ወደምትገኘው ወደ ቤቴል ነበ። በትምህርቱም ያተኰረበት ጉዳይ ሀብታሞች ከመጠን በላይ በመበልጸግ ድኾችን በጣም የሚጨቊኑ መሆናቸውን ነው። በሚሰጠውም ትምህርትና ተግሣጽ እስራኤልን ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ጊዜ ይሁዳንም ይጨምራል። በመጨረሻም ትንቢቱን ያጠቃለለው ለያዕቆብ ልጆች መልካም ተስፋ ሰጥቶ በዘመነ ወንጌል ከፍ ወዳለ ደረጃ እንደሚደርሱ በመግለጥ ነው። ይህንኑ እንደሚከተለው አቅርቦታል:-

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- ፈራርሶ እንደ ወደቀ ቤት የነበረውን የዳዊትን መንግሥት መልሼ የማቋቊምበት ጊዜ ይመጣል፤ ቅጽሩን እጠግናለሁ፤ ፍርስራሹንም አድሳለሁ፤ በቀድሞ ዘመን እንደነበረውም አድርጌ እሠራዋለሁ» (ም:9 ቊ:11)።

መጽሐፉም ዘጠኝ ምዕራፎች ያሉት ሲሆን በሦስት ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ምዕራፍ አንድና ምዕራፍ ሁለት ነው። በዚህ ክፍል የእግዚአብሔር ፍርድ በእስራኤል ጐረቤት አገሮች በሶርያ፥ በፍልስጥኤም፥ በጢሮስ፥ በኤዶም፥ በዐሞን፥ በሞአብና በይሁዳ በተለየም በራስዋ በእስራኤል ላይ የሚመጣ መሆኑ መግለጫ ተሰጥቶበታል።

ሁለተኛ ክፍል ከምዕራፍ ሦስት እስከ ምዕራፍ ስድስት ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የእስራኤል ሕዝብ የተደረገለትን የንስሓ ጥሪ ባለመቀበሉና ንስሓ ገብቶ ባለመመለሱ በምዕራፍ አንድና ሁለት ላይ የተሰጠው የትንቢት ቃል ተግባራዊ እንደሚሆን ማረጋገጫ ተሰጥቶበታል።

ሦስተኛው ክፍል ከምዕራፍ ሰባት እስከ ምዕራፍ ዘጠኝ ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ስለሚያመጣው ፍርድ ነቢዩ ያያቸው ራእዮች ተዘርዝረዋል:-

<u>1ኛው ራእይ</u>:- «ጌታ እግዚአብሔር ይህን ራእይ አሳየኝ፤ እነሆ፥ የንጉሡ የመከር እህል ከታጨደ በኋላ እንደገና ገቦ ሆኖ በበቀለው እህል ላይ እግዚአብሔር የአንበጣ መንጋ እንዲፈለፈል አደረገ፤ አንበጦቹም የምድሩን ልምላሜ ግጠው በሉት» (ም:7 ቊ:1–2)።

<u>2ኛው ራእይ</u>:- «ጌታ እግዚአብሔር የገለጠልኝ ሌላው ራእይ ይህ ነው፤ እነሆ፥ እግዚአብሔር ሕዝቡን በእሳት ለመቅጣት ሲዘጋጅ አየሁ፤ እሳቱም ከምድር በታች ያለውን ታላቅ ባሕር በልቶ እንደገና ምድርን ማቃጠል ጀመረ» (ም:7 ቊ:4)።

<u>3ኛው ራእይ</u>:- «እግዚአብሔር ሌላ ራእይ ገለጠልኝ፤ እነሆ፥ እግዚአብሔርን የውሃ ልኩ በቱምቢ ተስተካክሎ በተሠራ ቅጽር አጠገብ ቆሞ አየሁት፤ እርሱም በእጁ ቱምቢ ይዞ ነበር፤ እርሱም አሞጽ ሆይ፥ የምታየው ነገር ምንድን ነው? ብሎ ጠየቀኝ። እኔም ቱምቢ ነው አልኩት። እግዚአብ ሔርም እንዲህ አለኝ፤ ሕዝቤ እስራኤል ውሃ ልኩ ተስተካክሎ እንዳልተሠራ ቅጽር ጠማሞች መሆናቸውን በዚህ ቱምቢ አሳይበታለሁ፤ ከእንግዲህ እነርሱን ከመቅጣት አልመለስም» (ም:7 ቊ:7–8)።

<u>4ኛው ራእይ</u>:- አሜስያስ ሆይ፥ እግዚአብሔር ስለ አንተ እንዲህ ይላል:- «ሚስትህ በከተማይቱ አመንዝራ ትሆናለች፤ ልጆችህም በጦርነት ይሞታሉ፤ ርስትህንም ባዕዳን በገመድ ለክተው ይከፋፈሉታል፤ አንተም በአረማውያን ምድር ትሞታለህ፤ የእስራኤልም ሕዝብ ያለ ጥርጥር ተማርከው ከአገራቸው ይወሰዳሉ» (ም:7ቊ:17)።

<u>5ኛው ራእይ</u>:- «ጌታ እግዚአብሔር ሌላ ራእይ ገለጠልኝ፤ እነሆ፥ የጐመራ ፍሬ የሞላበት ቅርጫት አየሁ፤ እግዚአብሔርም ይህ የምታየው ነገር ምንድን ነው ሲል ጠየቀኝ፤ እኔም የጐመራ ፍሬ የሞላበት ቅርጫት አያለሁ አልሁት። እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፤ የሕዝቤ የእስራኤል ፍጻሜ ደርሶአል፤ ከእንግዲህ ወዲህ እነርሱን ከመቅጣት አልመለስም። በቤተ መንግሥት የሚያሰሙት ዘፈን በዚያን ቀን ወደ ለቅሶ ይለወጣል፤ የብዙ ሰው ሬሳ በቦታው ወድቆ ይገኛል፤ በዝምታም በየስፍራው ይጣላል» (ም:8 ቊ:1–3)።

<u>ትንቢተ አብድዩ</u>:- ይህ የትንቢት መጽሐፍ ኻያ አንድ ቊጥር ያለው አንድ ምዕራፍ ብቻ በመሆኑ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ በትንሽነቱ የታወቀ ነው። መጽሐፉ በተለይ ያተኰረው በኤዶም ላይ ትንቢት በመናገር ነው። ኤዶማውያን በኢየሩሳሌም ውድቀት መደሰታቸው ብቻ ሳይሆን እነርሱም ለአይሁድ ጠላቶች እርዳታ በማድረግ ለውድቀታቸው ተባባሪዎች ሆነዋል። በዚህም ምክንያት ነቢዩ አብድዩ በእነርሱ ላይ ስለሚመጣው ችግር ትንቢት ተናግሮአል። መጽሐፉንም በሦስት ክፍል ለመክፈል ይቻላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከቊጥር አንድ እስከ ዘጠኝ ድረስ ሲሆን ይህም በኤዶም ላይ ስለተወሰነው ጥፋት የሚናገር ነው። ከትንቢቱም መካከል እንዲህ የሚል ይገኝበታል።

«ሌቦች ወይም ቀማኞች በሌሊት ቢመጡ የሚበቃቸውን ያህል ብቻ ይወስዳሉ፤ ወይን ለቃሚዎችም ወይን ሲለቅሙ ቃርሚያ ይተዋሉ፤ የአንቺ (የኤዶም) ጠላቶች ግን ፈጽሞ ያጠፉሻል» (ቊ:5)።

ሁለተኛው ክፍል ከቊጥር ዐሥር እስከ ዐሥራ አራት ሲሆን ኤዶም በእስራኤል ላይ ስለ ፈጸመችው በደል ተገልጾበታል።

«(ኤዶም ሆይ፥) አንቺ በሕዝቤ መከራ ቀን መደሰትና በችግራቸው ቀን ሀብታቸውን ለመዝረፍ ወደ ሕዝቤ ከተማ መግባት ባልተገባሽም ነበር» (ቊ:13)።

ሦስተኛው ክፍል ከቊ 15 እስከ ቊጥር 21 ድረስ ሲሆን በዚህ ክፍል ውስጥ ሌሎቹ ሕዝቦች እንደሚደመሰሱና እስራኤላውያን ወደ ሀገራቸው እንደሚመለሱ ተገልጾበታል። ለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት:-

«እኔ እግዚአብሔር በአሕዛብ ሁሉ ላይ የምፈርድበት ጊዜ ደርሶአል፤ ኤዶም ሆይ፥ በሌሎች ላይ ያደረግሽው ግፍ በአንቺም ላይ ይደረግብሻል፤..., ከይሁዳ በስተደቡብ ያሉ ሕዝቦች የኤዶምን ምድር ይወርሳሉ:- ... እስራኤ ላውያን የኤፍሬምንና የሰማርያን ግዛት ይወስዳሉ፤ ... በስደት ላይ የነበሩት የሰሜን እስራኤል ሕዝብ ተመልሰው የከነዓንን ምድር እስከ ስራጵታ ድረስ ይወርሳሉ» (ቊ:15–20)።

<u>ትንቢተ ሚክያስ</u>:- ይህ የሞሬሼት ተወላጅ የሆነው ሚክያስ በአንደኛ ነገሥት ም:22 ቊ:8 ላይ ከተጠቀሰው በይሁዳው ንጉሥ በኢዮሳፍጥና በእስራኤል ንጉሥ በአክዓብ ዘመን ከነበረው ነቢይ የተለየ ነው። ይህን ትንቢት የጻፈው ከይሁዳ ግዛት ሲሆን ያኛው የሚኖረው ግን በእስራኤል ግዛት ውስጥ ነበር። ይህን መጽሐፍ የጻፈው ነቢይ የነበረው በይሁዳ ነገሥታት ኢዮአታም፥ አካዝና ሕዝቅያስ በተከታታይ በነገሡበትና በእስራኤል ደግሞ ፋቁሔና ሆሴዕ በነገሡበት ዘመን ነው። እርሱ በነበረበት ዘመንም የነበሩት ነቢያት ኢሳይያስ፥ ሆሴዕና አሞጽ ናቸው። ትንቢትም የተናገረው ስለ ኢየሩሳሌምና ስለ ሰማርያ ነው። ሰልምናሶር በሰማርያ ላይና ሰናክሬም ደግሞ በይሁዳ ላይ በጠላትነት እንደሚመጡባቸው ትንቢት ተናግሮአል። (2ኛ: ነገ: ም:17 ቊ:4 እና 6፥ ም: 18 ቊ:13)። ሚክያስ በሰባቱ ምዕራፎቹ ኢሳይያስ በትልቁ መጽሐፉ ካቀረባቸው ዋነኞች ጉዳዮች በአጭሩ አቅርቦአል።

በምዕራፍ አንድ በሰማርያና በኢየሩሳሌም ያሉ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በሠሩት በደል ምክንያት እግዚአብሔር ስላስተላለፈባቸው ፍርድ ትንቢት ተነግሮበታል።

በምዕራፍ ሁለት በተፈጸመው በደል ምክንያት ወዮታዎች ተዘርዝረዋል።

በምዕራፍ ሦስት ለያዕቆስብ ልጆች መሪዎች የተደረገ ጥሪ፡ ይኸውም ደጉን ነገር ጠልተው ክፉውን ነገር ስለሚወዱ በሕዝቡ ላይ የሚፈጽሙትን የጭካኔ ሥራ እንዲያቆሙ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአል።

በምዕራፍ አራት በመጨረሻው ቀን የእግዚአብሔር ቤት በተራራው ጫፍ ላይ ስለሚመሠረትበት ሁናቴ ተገልጾአል። እግዚአብሔርም በኢየሩሳሌም ላይ ስለሚነግሥ ለዘለዓለም ሰላም እንደሚሆን ተገልጦአል።

በምዕራፍ አምስት ወደፊት የሚመጣው የእስራኤል ገዢ በኢየሩሳሌም እንደሚወለድ ተነግሮአል።

በምዕራፍ ሰባት ምንም እንኳ ተግባራቸው ሁሉ አስደሳች ባይሆን ለአባ ቶች በገባው ቃል መሠረት እግዚአብሔር ለያዕቆብ ልጆች ይፈርድላቸዋል።

<u>ተረፈ ዳንኤል:- ቤልና ዘንዶው</u>:- በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ የትንቢተ ዳንኤል መጽሐፍ ዐሥራ ሁለት ምዕራፎች ብቻ ያሉት ሲሆን በሰባዎቹ ሊቃውንት ትርጓሜ ግን ዐሥራ አራት ምዕራፎች አሉት። በዚህም መሠረት በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ የሌለው ምዕራፍ ዐሥራ አራት ላይ ቤል ስለተባለው ጣዖትና ስለዘንዶው ታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል። ዳንኤል ለንጉሡ በጣም ቅርብ ነበር። ከቅርብነቱም የተነሣ ንጉሡ ለምን ለቤል አትሰግድም ብሎ ዳንኤልን ጠየቀው። ዳንኤልም ሰማይንና ምድርን ለፈጠረ ሕያው እግዚአብሔር እንጂ በሰው እጅ ለተሠራ ጣዖት አልሰግድም ብሎ መልስ ሰጠው። የጣዖቱ ካህናት ንጉሡንና ሕዝቡን እያታለሉ ለጣዖት የሚቀርበውን ብዙ ምግብና መጠጥ እነርሱ ከነቤተሰባቸው በምሥጢር ገብተው በመብላት ጣዖት የበላው ያስመስሉ ነበር። ንጉሡም ዳንኤልን ቤል ሕይወት የሌለው አምላክ ይመስልሃልን? በየቀኑ የሚበላውንና የሚጠጣውን አታይምን? ሲል ጠየቀው። በዚህ ጊዜ ዳንኤል በንጉሡ ስቆበት ይህ ቤል የምትለው ጣዖት ውስጡ ሸክላ ውጪው ናስ መሆኑን አታውቅምን? እንዴት ሊበላና ሊጠጣ ይችላል? አለው። በዚህ ጊዜ ንጉሡ ተቈጣና ካህናቱን አስጠርቶ ለቤል የሚቀርበውን ምግብ ማን እንደሚበላው ካልነገራችሁኝ ትሞታላችሁ አላቸው። እነርሱም ምግቡን የሚበላው ቤል እንደሆነ፡ ይህ ባይሆን ግን እነርሱ መገደል እንዳለባቸው፡ አለበለዚያም አምላካቸውን ቤልን የሰደበው ዳንኤል መገደል እንደሚገባው ነገሩት። በዚህም መሠረት ቤተ ጣዖቱን ንጉሡና ዳንኤል ዘግተው እንዲያትሙበት ስምምነት ተደረሰ። ዳንኤል ግን ምግብና መጠጥ በተቀመጠበት ቤተ ጣዖት ለንጉሡ ብቻ አሳይቶ አመድ ነሰነሰበት። ከዚያም በሩን ቈልፈው ሄዱና በማግስቱ ጧት ሲመጡ ምግቡና መጠጡ አልቆ አገኙት። ንጉሡም በጣዖቱ የተበላ መስሎት ደነፋ። በዚህ ጊዜ ዳንኤል በንጉሡ ሳቀበትና በነሰነሰው አመድ ላይ ያሉትን የእግር ኮቴዎች አሳየው። ንጉሡም የወንዶችና የልጆች ኮቴዎችን ተመለከተ። በዚህ ጊዜ በጣም ተቈጥቶ ካህናቱን በማስጠራት ሲጠይቃቸው በየዕለቱ ሌሊት ከነቤተ ሰባቸው ወደ ቤተ ጣዖቱ የሚገቡበት የምሥጢር በር መኖሩን አሳይተውት ድርጊታቸውን አመኑ። ካህናቱን ሁሉ ከገደላቸው በኋላ ቤልን ለዳንኤል ሰጠው። ዳንኤልም ጣዖቱን ሰባብሮ ቤቱን አፈረሰው።

የባቢሎን ሰዎች የሚያመልኩት ዘንዶም ነበረ። ንጉሡም ከዳንኤል ጋር ሲነጋገር ይህ ደግሞ ሸክላ ወይም ናስ አይደለም፤ የሚበላና የሚጠጣ ሕያው ነው ና አምላክ ስለሆነ ስገድለት አለው። ዳንኤል ግን በሕያውነት ለሚኖር ለእግ ዚአብሔር ብቻ እንጂ ለሌላ አልሰግድም አለው። እንዲያውም የምትፈቅድልኝ ከሆነ ይህን ዘንዶ ያለሰይፍና ያለ በትር እገድለዋለሁ አለው። ንጉሡም ፈቅጃል ሃለሁ አለው። ዳንኤልም ጠጉር፡ ሰምና ስብ በአንድነት ቀቅሎ ከአድቦለ ቦለው በኋላ ለዘንዶው አጐረሰው። ዘንዶውም ያን በጐረሰ ጊዜ ተሰንጥቆ ሞተ። በዚህ ጊዜ የባቢሎን ሰዎች ንጉሡን በጣም ስላስፈራሩት ዳንኤልን አሳልፎ ሰጣቸው። እርሱንም ወደ አንበሳ ጉድጓድ ውስጥ ጣሉት። በጉድጓድ ውስጥ ሰባት አንበ ሶች ነበሩ። እነርሱንም በየቀኑ ሁለት ሰውና ሁለት በግ ይመግቡአቸው ነበር። ዳንኤል ሰባት ቀኖች በጉድጓድ ውስጥ በቈየበት ጊዜ እርቦአቸው እርሱን እንዲበሉት ስለተፈለገ ለአንበሶቹ ምንም ምግብ አልተሰጣቸውም። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ስለጠበቀው ዳንኤልን አልነኩትም።

በዚያን ጊዜ ነቢዩ ዕንባቆም በይሁዳ ይኖር ነበር። እርሱም የምስር ንፍሮ አስቀቅሎና እንጀራ አስጋግሮ በቅርጫት ውስጥ በማድረግ እህል ለሚያጭዱ ሰዎች እየወሰደ ሳለ የእግዚአ ብሔር መልአክ ይህን ምሳ በባቢሎን በአንበሳ ጉድጓድ ውስጥ ላለው ለዳንኤል ውሰድለት አለው። ወዲያውም የነቢዩን የዕንባ ቆምን ጠጉር በመያዝ በባቢሎን ነቢዩ ዳንኤል ወደ ተጣለበት ጉድጓድ አጠገብ አመጣው። እንባቆምም ድምፁን አሰምቶ ዳንኤልን በመጥራት እግዚአብሔር የሰጠህን ይህን ምሳ ተቀበል አለው። ዳንኤልም እግዚአብሔርን በማመስገን ምግቡን ተቀብሎ በላ። ከዚያ በኋላ መልአኩ ዕንባቆምን ወደ አገሩ መልሶ ወሰደው። ንጉሡም ለዳንኤል ሊያለቅስለት በሰባተኛው ቀን ሲመጣ ደንኤልን በአንበሶቹ መካከል ተቀምጦ አየው። ከዚያም ንጉሡ እግዚአብሔርን አክብሮና አመስግኖ ዳንኤልን ከአንበሶች ጉድጓድ ውስጥ አወጣው። ዳንኤልን ለመግደል ወደ አንበሶቹ ጉድጓድ ውስጥ የጣሉትን ሰዎች ወደ አንበሶቹ ጉድጓድ ውስጥ እንዲጣሉ አስደረገ። አንበሶቹም በጫጭቀው በሉአቸው። ንጉሡም ሁሉም ሰው የዳንኤልን አምላክ ያምልክ ብሎ አዘዘ።

## <u>ሐዲስ ኪዳን</u>

<u>የመጀመሪያው የሐዋርያው የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት</u>:- ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ የዮና ልጅ ሲሆን የሐዋርያው የቅዱስ እንድርያስ ወንድም ነው። እርሱም ከቤተ ሰይዳ ሆኖ ስሙ ስምዖን ነበር። ጌታችን ግን ኬፋ ወይም ጴጥሮስ የሚል ስም ሰጥቶታል። ኬፋ በሶርያ ቋንቋ፡ ጴጥሮስ ደግሞ በግሪክ ቋንቋ አለት ወይም ቋጥኝ ማለት ነው። ይህም የሚያመለክተው የቀናኢነቱን ጥንካሬ ነው። ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው በመጨረሻ ዘመኑ በኔሮን ዘመነ መንግሥት ወደ ሮም ከተማ ሄዶ ሰማዕትነትን ተቀብሎአል።

ይህ መልእክት የተጻፈው በ63 ዓ.ም. በባቢሎን ነው (1ኛ: ጴጥ: ም:5 ቊ:13)።

የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ስለዚህች ባቢሎን ስለተባለችው አገር ሦስት የተለያዩ አስተያቶች አሉአቸው። አንድ አስተያየት ባቢሎን የተባለችው በዚ ያን ጊዜ የጣዖት አምልኮ ይበዛባት የነበረችው የሮም ከተማ ነች የሚል ነው፤ ሌላው አስተያየት በግብጽ የምትገኘው ባቢሎን ነች፤ ሦስተኛው አስተያየት ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ የታወቀችው የመካከለኛ ምሥራቅዋ ባቢሎን ነች የሚል ነው።



www.ethiopianorthodox.org

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ይህን መልእክት ለመጻፍ ያነሣሣው በዚያን ጊዜ የሮማው ንጉሠ ነገሥት ኔሮን በክርስቲያኖች ላይ ያደርገው በነበረው ኀይለኛ ማሳደድ ምክንያት ክርስቲያኖች ምንም ዐይነት ችግር ቢደርስባቸው በእምነታቸው እንዲጸኑ ምክር ለመስጠት ነው። ለዚህም የሰጠው መክር:-

አንደኛ/አዳኛቸው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደታገሠ እነርሱም በግፍ የሚደር ስባቸውን ችግርና መከራ እንዲታገሡ ከመምከሩ ጋር ይህን ቢያደርጉ የትዕግ ሥታቸውን ዋጋ እንደሚቀበሉ ያደረጋግጥላቸዋል (ም:1 ቍ:5–7፤ ም:4 ቍ:12–16)።

ሁለተኛ/በክርስቶስ ደም የተዋጁ በመሆናቸው በንጽሕና እንዲኖሩ ይመክራቸዋል (ም:1 ቍ:13–16)።

ሦስተኛ/ከሥጋዊ ምኞትም ይርቁ ዘንድ ሁሉንም ይመክራቸዋል (ም:4ቍ:1–6)

አራተኛው/ የትሕትና ኑሮ የመሪዎችና የመምህራን መመሪያ እንዲሆን ይመክራቸዋል። ይህም ለፈታኙ ዲያብሎስ ዋና መከላከያ ነው።

ወደ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን በመግባት ክርስትናን የተቀበሉ ሁሉ ታላቅ ለውጥን እንደተለወጡ ተገልጦአል። እርሱም:-

ከተስፋ ቢስነት ወደ እውነተኛ ተስፋ (1፥21)
ከርኵሰት ወደ ቅድስና (1፥18፤4፥3)
ከባርነት ወደ ነጻነት (1፥18)
ከሚጠፋ ወደማይጠፋ ሕይወት (1፥4፥23)
ከድንቍርና ወደ ዕውቀት (1፥14)
ከሥጋዊነት ወደ መንፈሳዊነት (4፥6)
ከሞት ወደ ሕይወት (1፥3)
ከዐመፀኛነት ወደ ታዛዥነት (1፥2፥22)
ሕዝብ ካለመሆን ሕዝብ ወደ መሆን (2፥10)
ምሕረት ከማጣት ምሕረት ወደማግኘት (2፥10)

<u>ሁለተኛው የሐዋርያው የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት</u>:- ይህ መልእክት የተጻፈው በባቢሎን ነው ይባል እንጂ የተጻፈበት ቦታ ግን በትክክል አልተገ ለጠም። በምዕራፍ 3ቍ: 1 ላይ ይህን ሁለተኛ መጽሐፍ የጻፈው እርሱ መሆኑ ንና በምዕራፍ 1 ቍ:18 ላይ በታቦር ተራራ ላይ ስላየው የክርስቶስ ክብር መገ ለጥ ቢመሰክርም እንኳ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ይህን ሁለተኛውን መጽሐፍ የጻፈው ቅዱስ ጴጥሮስ አይደለም ይላሉ።

ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ሁለት አጠቃላይ ዓላማዎች ተጠቅሰዋል። የመጀ መሪያው ዓላማ ለመንፈሳዊው ጥሪና ለምርጫው መትጋት የሚገባ መሆኑን ለማስተማር ነው። ለዚህም የሚከተ ለውን ጥቅስ እናስተውል:-

«በክብሩና በቸርነቱ የጠራን መሆኑን በማወቃችን መለኮታዊ ኀይሉ ለሕይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊ ኑሮ የሚያስፈልጉንን ነገሮች ሁሉ ሰጥቶናል። በእነዚህ በተሰጡት ነገሮች አማካይነት በክፉ ምኞት ምክንያት በዚህ ዓለም ካለው ጥፋት ድናችሁ የመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች ሆናችኋል፤ የእርሱንም ክቡርና እጅግ ታላቅ የሆነውን ተስፋ አግኝታችኋል። በዚህ ምክንያት የሚከተሉት ነገሮች እንዲጨመሩላችሁ ትጉ፤ በእምነት ላይ ደግነትን፥ በደግነት ላይ ዕውቀትን፥ በዕውቀት ላይ ራስ መቈጣጠርን፥ በራስ መቈጣጠር ላይ በትዕግሥት መጽናትን፥ በትዕግሥት በመጽናት ላይ መንፈሳዊነትን፥ በመንፈሳዊነት ላይ ወንድማማችነትን፥ በወንድ ማማችንት ላይ ፍቅርን ጨምሩ። እነዚህ ነገሮች በብዛት ቢኖሩአችሁ ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ለማወቅ የማትጠቅሙ ፍሬቢሶች እንዳትሆኑ ይጠብቁአችኋል» (2ኛ:ጴጥ:ም:1 ቍ:3–8)።

ሁለተኛው ዐላማ ደግሞ ከሐሰተኞች መምህራን ትምህርት ለማስጠንቀቅ ነው። በተለየም ጌታ ዳግመኛ የሚመጣበት ቀን ዐልፎአል ወይም አይመጣም የሚለውን ሐሰተኛ ትምህርት በጣም የተቃወመው መሆኑን ለመረዳት የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት:-

«ወዳጆቼ ሆይ፥ እናንተ ግን በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት፥ ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን መሆኑን ይህን አንድ ነገር አትርሱ፤ አንዳንድ ሰዎች እንደሚመስላቸው ጌታ



ኢየሱስ የተናገረውን የተስፋ ቃል ለመፈጸም አይዘገይም፤ ነገር ግን ሰው ሁሉ ለንስሓ እንዲበቃ እንጂ ማንም ሰው እንዳይ ጠፋ ፈልጎ ስለ እናንተ ይታገሣል» (2ኛ:ጴጥ:ም:3 ቍ:8–9)።

<u>የመጀመሪያው የዮሐንስ መልእክት</u>:- ብዙዎች እንዳመኑት ዮሐንስ ወንጌላዊው ይህን መልእክት የጻፈው በኤፌሶን በ98 ዓ.ም. ነው። ይኸውም ወደ መጀመሪያው መቶ ዓ.ም. መገባደጃ አካባቢ ነው። ምንም እንኳ በመልእ ክቱ ውስጥ ስሙን ባይመዘግብም ከወንጌሉ ጋር ባለው ግንኙነትና ተመሳሳይነት መሠረት አብያተ ክርስቲያን ሁሉ የእርሱ መሆኑን አምነው በታል፤ መስክረውለታልም። ይህን መልእክት የጻፈበት ዋነኛው ምክንያት በጊዜው ተነሥተው የነበሩትን የሐሰተኞች መምህራንን ሐሳብ ዋጋ ለማሳጣት ነው። እነርሱም የክርስቶስን መለኮታዊ ክብር የሚክዱ ነበሩ። መጽሐፉ አምስት ምዕራፎች ያሉት ሆኖ በውስጡ ያሉት ጉዳዮች:-

አንደኛ/ የክርስቶስን መለኮታዊ ክብርና ሥጋ መልበሱን ለማረጋገጥ:- (ም:1 ቍ:1–4፥ ም:4 ቍ:9)።

ሁለተኛ/ማመን በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መሆን እንደሚገባው (ም:2 ቍ:22፥ ም:5 ቍ:6–8)።

ሦስተኛ/ የእግዚአብሔር ምሕረት ለኃጢአተኞች ጠቃሚ የሚሆነው ተጸጽተው ኃጢአታቸውን ከተናዘዙና ንስሓ ከገቡ ብቻ ነው። ይህም የሚሆነው ክርስቶስ ቤዛ ስለሆነላቸው ነው (ም:1 ቍ:9 ም:2 ቍ:1–2)።

አራተኛ/ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸውም የሚረጋገጠው ትእዛዛቱን የሚፈጽሙና እርስ በርሳቸው የሚዋደዱ እንደሆነ ነው። እነዚህም ሁለት ነገሮች በእግዚአብሔር ልጆችና በሰይጣን ልጆች መካከል ያለውን ልዩነት ያሳያሉ (ም:3 ቍ:1–10)።

አምስተኛ/ ስለ ሐሰተኞች መምህራን ማስጠንቀቂያ:- (ም:2 ቍ: 18–29)።

ስድስተኛ/ የምእመናን ጸሎት ከንስሓ ጋር አንዳንድ ኃጢአቶችን የሚያስተሰርይ መሆኑ:- (ም:5 ቍ:13–17)።

<u>ሁለተኛው የዮሐንስ መልእክት</u>:- ሐዋርያው የጻፈላት የተከበረች ሴት የተባለች ብዙዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን እንደተስማሙበት ከታናሽቱ እስያ ካሉት ለአንዲቱ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነ ይገመታል። ይህም የሆነበት ምክንያት ሐሰተኞች መምህራን የሚበዙት በታናሽቱ እስያ ስለነበረ ነው። መጽሐፉ አንድ ምዕራፍ ብቻ ያለው ሆኖ ሁለት ዐላማዎች አሉት። የመጀመሪያው ዐላማ የተጻፈላት እመቤትና ልጆችዋ በእምነትና በፍቅር፥ በትእዛዛቱም በመጽናታቸው አመስግኖአቸዋል። ሁለተኛው ደግሞ ከአታላዮች ተጠብቀው በእምነታቸው እንዲጸኑ አሳስቦ ቀቆአቸዋል።

<u>ሦስተኛው የዮሐንስ መልእክት</u>:- ይህ መልእክት የተጻፈው ጋይዮስ ለተባለ ሰው ነው። ይህም ጋይዮስ በሮሜ መልእክት ም:16 ቍ:23 እና በአንደኛ ቆሮንቶስ ም:1 ቍ:14ላይ ስሙ የተጠቀሰው ነው። ይህም ሰው የወንጌል መል እክተኞችን እንደሚረዳ የተነገረለትና የተመሰገነ ነው። ይህም መልእክት አንድ ምዕራፍ ብቻ ሲሆን በጎ አድራጊ የተመሰገነበትና ክፉ ሰው ግን የተወቀሰበት ነው።

## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን የሰው ልጅ ማለቱ ከምድር የተገኘ የአዳም ልጅ ለማለት ነው። ይህም የሆነው ከተገለጡለት የራእዮች ብዛት የተነሣ ራሱን ከፍ ከፍ እንዳያደርግ፥ ምንም ያኽል ከበሬታ ቢሰጥህ አንተ አሁንም የሰው ልጅ፥ ፍጡር ነህ እንጂ ከዚያ የምትበልጥ አይደለህም ለማለት ነው። ወይም ደግሞ ለአክብሮት የተሰጠው ስም ነው ለማለት ይቻላል። ይህም የሚሆነው ነቢዩ ዳንኤል ስለ ክርስቶስ ባየው ራእይ የሰው ልጅን የሚመስል አየሁ ከማለቱም በላይ ጌታችን ራሱ የሰው ልጅ ስለሆነ ፍርድ ሁሉ ለእርሱ እንደተ ሰጠ ተናገሮአል (ዳን:ም:7 ቍ:13፥ ዮሐ:ም:5 ቍ:27)።

እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን የብራናውን ጥቅል ማለት መጽሐፍ የተጻፈበትን ጥቅል እንዲበላ አዝዞት ሕዝቅኤልም ጣፍጦት እንደበላው ተገልጾአል። አፉንም ከፍቶ መጽሐፉን ከአጐረሰው በኋላ ተነሥተህ ወደ እስራኤል ቤት በመሄድ ቃሌን ንገራቸው ብሎታል (ም:3 ቍ:1–4)።

www.ethiopianorthodox.org

ይህም ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። አባባሉም በኀሊናህ ቅረጸው፡ ነፍስህን መግበህ አበርታበት፡ በእር ሱም ምግብ በልተህ እንደምትጠግብ የተሞላህ ሁን ማለት ነው። ምንም እንኳ ያ ጥቅል በሰቆቃ፡ በሐዘንና በወዮታ የተሞላ ቢሆን ለነቢዩ ግን እንደ ማር ጣፋጭ ነበር። ከዚያ በኋ እርሱ የተመገበውን የእግዚአብሔር ቃል ይዞ ወደ እስራኤል ቤት እንዲሄድና እንዲገሥጻቸው፡ ቃሉን እንዲያደርስላቸው ታዘዘ። ከዚያ በኋላ ሕዝቅኤል በራእይና በምሳሌ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ትምህርት ለእስራኤላውያን ለማዳረስ በመሄድ ስለ ኢየሩሳሌም መከበብና መደም ሰስ ስለ ሕዝቡ ስደት፡ ረሀብና ፍጅት ትንቢት መናገሩን ቀጠለ። የዚህም ምክንያት፡ የሕዝቡ አለመታዘዝና ሀመፅ እየበዛ ስለሄደ፡ እንዲሁም በንስሐ ለመመለስ ፈቃደኞች ባለመሆናቸው ነው።

እግዚአብሔርም የሕዝቅኤልን አቋም ካጠናከረለትና በእስራኤል ቤት ላይ ጠባቂ አድርጎ ከሾመው በኋላ የማስተማር ግዴታ እንዳለበት አስጠንቅቆታል። እርሱ ካለማስተማሩ የተነሣ ኃጢአተኛ በኃጢአቱ ምክንያት በሚሞትበት ጊዜ ለኃጢአተኛው ደም ተጠያቂ እንደሚሆን ገልጦለታል። ይህም አባባል ለሕዝቅኤል ብቻ ሳይሆን ለሁላችንም ማስጠንቀቂያ መሆኑን እናስተውል። ይህንኑ አባባል ቃሬር ጠባቂ ሆኖ በቆመ ወታደር ኀላፊነት ምሳሌ እንደገ ደግሞታል (ም:33)።

ነቢዩ ሆሴዕ ለሥራ የተጠራው አገሪቱ ማለት የእስራኤል ሕዝብ ከእግዚ አብሔር ርቆ በዝሙተኛነት ሥራ በሚመሰለው በጣዖት አምልኮ ኃጢአት ተበክሎ በነበረበት ዘመን ነው፤ እርሱም ጎሞር የተባለች ለባልዋ ታማኝ ያልሆነች ሚስት እንዲያጋባ ታዘዘ። ይህም ምሳሌያዊ አባባል ሲሆን የእስራኤል ልጆች ኃጢአታቸውን በመስተዋት መልኩን ለማየት እንደሚችል ሰው ሊያሳያቸው ስለፈለገ ነው።

የጋብቻው ምሳሌ በሲና ተራራ ላይ የተሰጠው ቃል ኪዳን ሲሆን እግዚአ ብሔርን ትተው ጣዖት ማምለካቸው ደግሞ ለባልዋ ታማኝ ባልሆነችው ሚስት የሚመሰል ሆኖአል። ከዚያች ታማኝ ካልሆነችው ሚስት የሚወለዱት ልጆችም እንደ እናታቸው የማይታመኑ መሆናቸውን ለማመልከት ምሕረት ያልተደረገለት ከሚሉት የልጆቹ ስሞች አንዱ ነው። እንዲሁም የተበታተኑ የተባለው ስም በምርኮ የሚበታተኑ መሆናቸውን ለማመልከት ነው። እንዲያ ውም ከኃጢአታቸው ብዛት የተነሣ ሕዝቤ አይደሉም የሚለው የሦስተኛ ልጅ ስም ነው። የልጆቹም ስም እንደሚከተለው ነው:-

ይዝራኤል — የተበታተነ

ሎሩሓማ — ያልተወደደ፥ ምሕረት ያልተደረገለት

ሎአሚ — ሕዝቤያይደለ።

ሕዝቤ አይደላችሁም የሚለው ትንቢት ወደ አሦር ተማርከው በሄዱ ጊዜ ተግባራዊ ሆኖአል። ነቢያት አልተላኩላቸውም፡ ተስፋም አልተሰጣቸውም። ይህም ለሁለቱ ነገዶች ከተደረገው በተቃራኒ ነው። በኋላ በዘሩባቤል መሪነት አይሁድ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ በተደረገ ጊዜ ከዐሥሩም ነገዶች ብዙ ሆነው ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል። የእግዚአብሔር ሕዝብም ለመባል በቅተዋል።

ሆኖም እግዚአብሔር በዘለዓለማዊ ፍቅሩ ይቅርታ እንደሚያደርግላቸው በነቢዩ በሆሴዕ አማካይነት ቃል ገብቶአል። ይህም የእግዚአብሔርን መሐሪነትና ይቅር ባይነት ያመለክታል (ሆሴ:ም:14)።

ኢዩኤል ያየው የአንበጣ መንጋ ታሪካዊ ሳይሆን ምሳሌያዊ እንደሆነ ይገመታል። የሀገሪቱ በጠላት መወረርን እንደ አንበጣ መንጋ መውረር በምሳሌ አነጋገር የተነገረ ነው የሚለው የሊቃውንት አስተሳሰብ ነው። ይኸውም የይሁዳ ሕዝብ በፈጸመው ታላቅ ኃጢአት ምክንያት በብዙ ሠራዊት እንደሚወረር የእግዚአብሔር ፍርድ መሆኑን ነቢዩ ኢዩኤል የተናገረው ትንቢት ነው። ብዙዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች እንደተስማሙበት ይህ የተጠቀሰው ጦር ሠራዊት በሰናክሬም አማካይነት የይሁዳን ግዛት ያጥለቀለቀው የአሦር ጦር ሠራዊት ነው።

እህሉን ያጠፉት ተምች፥ አንበጣ፡ ደጎብያና ኩብኩባ መሆናቸው በምዕራፍ አንድ ቍጥር አራት ላይ ተገልጦአል። እነዚህ አራት የጥፋት መሣሪያዎች በተከታታይ የተነሡት አራት መንግሥታት እንደሆኑና ከቀድሞው የተረፈው ቀጣዩ መንግሥት እንዳወደመው ያመለክታል የሚሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች አሉ። እነዚህ አጥፊ ነገሮች በእውነትም በይሁዳ ላይ



የመጡ ስለሆነ ቃል በቃል መወሰድ አለበት እንጂ ትርጓሜ አያስፈልገውም የሚሉም ወገኖች አሉ።

ነቢዩም ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር እንዲጮኽ ጥሪ አስተላልፎአል። ሕዝቡ ንስሐ እንዲገባ የነቢዩ ጥያቄና ምክር ነው። ንስሐ ገብተው በፍጹም ልባቸው የሚመለሱ ከሆነ:-

«የሰሜኑን ሠራዊት ከእናንተ አርቃለሁ፤ ወደ በረሓና ወደ ምድረ በዳ፡ ፊቱን ወደ ምሥራቁ ባሕር፥ ጀርባውንም ወደ ምዕራቡ ባሕር አድርጌ አሳድደዋለሁ፡ እርሱም ታብዮአልና፥ ግማቱ ይወጣል፤ ክርፋቱም ይነሣል» ብሎአል (ም:2 ቍ:20)።

ብዙ የመጽሐፈ ቅዱስ ተርጓሚዎች እንደተስማሙበት ይህ የሰሜን ሠራዊት የተባለው ሰናክሬም ነው። በእነዚያም በጥፋት መሣሪያዎች የጠፋው ጥፋት ሀልፎ እንደገና ወደ ብልጽግና እንደሚመልሰው እግዚአብሔር ተስፋ ሰጠ (ም:2 ቍ:21–27)።

ይህ የተሰጠው ቁሳዊ ተስፋ ተግባራዊ ከሆነ በኋላ ያ በብሉይ ኪዳን በቁጠባ ይሰጥ የነበረው የእግዚአብሔር መንፈስ በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ እንደሚወርድ ተስፋ ተሰጠ። ይህም የእግዚአብሔር መንፈስ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በጰንጠቆስጤ በዓል ቀን የጠቀሰው ነው (ኢዩ ም:2 ቍ:28–29፥ ሐዋር: ሥ:ም:2 ቍ:15–21)።

አሞጽ የተናገረው የእግዚአብሔር ቅጣት ትንቢት በጋዛ፥ በጢሮስ፥ በኤዶም፥ በአሞን፥ በሞአብ፥ በይሁዳና በእስራኤል ላይ ነው።

የይሁዳ ሕዝብ ኃጢአት ግን ከሌሎቹ ሕዝቦች ኃጢአት የተለየ ነው። ሌሎቹ ሕዝቦች ቅጣት የሚፈረድባቸው በሌሎች ፍጡር ጓደኞቻቸው ላይ በፈጸሙት በደል ሲሆን የይሁዳ ሕዝብ ግን በደል የፈጸመው ከአምላኩ ጋር ባለው ቃል ኪዳን ባለመጽናት ነው። ሕጉን ንቀዋል፤ ይህም ማለት ትእዛዛቱን አልጠበቁም ማለት ነው። እንዲሁም ሐሰተኛ አማልክትን ማለት ጣዖቶችን አምልከዋል ማለት ነው።

እስራኤልን ከወቀሰበት ምክንያቶች መካከል ባለጸጎች ድኾችን የሚጨቍኑ መሆናቸው ነው።

አሞጽም በእስራኤል ላይ ስለ ቅጣት ፍርድ የተነበየ ብቻ ሳይሆን የንስሐ ጥሪም አስተላልፎአል። ለዚህም የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት:-

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- ‹የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፡ ወደ እኔ ተመለሱ፤ በሕወትም ትኖራላችሁ፤ ለስግደት ወደ ቤርሳቤህ አትሂዱ፤ በቤትኤልም ለማምለክ አትሞክሩ፤ ወደ ጌልጌላም አትሂዱ፤ ቤትኤል ፈራርሳ እንዳልነበረች ትሆናለች፡ በጌለጌላ የሚኖሩ ሕዝቦችም ስደት ተፈርዶባ ቸዋል።› ይልቅስ ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ፤ በሕይወትም ትኖራላችሁ» (ም:5 ቍ:4–6)።

በትንቢተ ሚክያስ የተነገረው ዝነኛው ትንቢት እንዲህ የሚለው ነው:-

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- አንቺ በኤፍራታ ምድር የምትገኚ ቤተል ሔም ሆይ፡ አንቺ ከሁዳ ከተሞች ያነስሽ ብትሆኚም እንኳ፡ አወጣጡ ከጥንት ዘመናት በፊት የነበረ የእስራኤል መሪ መስፍን ከአንቺ ይወጣልኛል» (ም:5ቍ:2)።

ሌላው ትንቢት ያልሆነ ነገር ግን ዝነኛ የሆነ አባባል ደግሞ የሚከተለው ጥቅስ ነው:-

«እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ትክክል የሆነውን ነገር እንድናደርግ፥ ደግነት የተሞላበትን ፍቅር እንድናሳይና ከአምላካችን ጋር በፍጹም ትሕትና እንድንራመድ ነው» (ም:6 ቍ:8)።

በመጽሐፈ ዳንኤል ምዕራፍ 14 ውስጥ የተነገረው የቤልና የድራጎን ታሪክ ነቢዩ ዳንኤል ምን ያኽል እምነተ ጠንካራ የነበረ መሆኑን ያመለክተናል። ሰው ደግሞ በእግዚአብሔር ላይ ያለው እምነት ጠንካራ ከሆነ ጥበብን እንደሚያ ድለውና ከክፉ ነገር ሁሉ እንደሚጠብቀው በዚህ ታሪክ ውስጥ ለመገንዘብ ችለናል። ክፉዎች ግን ራሳቸው ባጠመዱት ወጥመድ ይጠፋሉ። ለዚህም አጭበርባሪዎቹ ካህናት አታላይነታቸው እንዳጠፋቸው፡ ዳንኤልን ከስሰው ወደ አንበሳ ጉድጓድ ውስጥ የጣሉት ወገኖች ደግሞ እነርሱ ራሳቸው በአንበሳዎቹ ተበጫጭቀው እንደጠፉ ያስተውሏል።

ሐዋርያ ቅዱስ ጴጥሮስ በመጀመሪያ መልእክቱ ም:1 ቍ:2 ላይ በእግዚአብሔር አብ ውሳኔ አስቀድሞ የመመረጥን ጉዳይ ገልጾአል። እዚህ የምርጫን ጉዳይ በምንናገርበት ጊዜ ሰው ለምን ጉዳይ ይመረጣል የሚለው ጥያቄ ወደ ሐሳባችን ይመጣል። አንድ ሰው ለሹመት፥ ወይም የተለየ

www.ethiopianorthodox.org

አስደሳች ጥቅምን ለማግኘት፥ ወይም ዘለዓለማዊ ድኅነትን ለማግኘት ይመረጥ ይሆናል። በዚህ ቦታ የተነገረው ስለ ዘለዓለማዊው ድኅነት ምርጫ ነው። የእግዚአብሔርን ዕውቀት ጊዜ የማይወስነው በመሆኑና ገና ከእናታችን ማሕፀን ከመውጣታችን በፊት እያንዳንዳችን ምን ዐይነት ሰዎች እንደምንሆን አስቀድሞ ስለሚያውቅ አስቀድሞ ይመርጠናል።

የሰውን ዘር መዳን ወይም ድኅነትን በተመለከተ ምርጫ የእግዚአብሔር አብ፥ አስታራቂነት የእግዚአብሔር ወልድ፥መቀደስ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብሮች እንደሆኑ ይገለጣል።

የክርስቲያን ነጻነት በመንፈሳዊ አመለካከት ሲታይ ነጻነቱ የክፋት መሸፈኛ መሆን የለበትም። መንፈሳዊ ነጻነት ቢኖራቸውም ለምድራዊ ገገር፥ አለቃ፥ አስተዳዳሪ ላለመታዘዝ ነጻነት የላቸውም። ንጉሥን እንዲያከብሩ፥ አገልጋዮችም ለጌቶቻችሁ በአክብሮት እንዲታዘዙ መክሮአል።

ሐዋርያው የቅዱስ ጴጥሮስ በሁለተኛ መልእክቱ ም:1 ቍ.20–21 ስለ ትንቢት አመጣጥና አተረጓጐም ሲያብራራ እንዲህ ብሎአል:-

«ይህን በመጀመሪያ ዕወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተርጉም አልተፈቀደም፤ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመ ጣምና፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የተናገሩት ነው።»

የሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ መልእክቶች ተራ ስብከቶች ሳይሆኑ ክርስቲያናዊ ሕይወትን ለማጠናከር የታቀዱ ነበሩ (1ኛ: ዮሐ:ም1 :ቍ:4፥ ም:5 ቍ:13)። እንዲሁም በሐሰተኞች መምህራን አማካይነት ተሠራጭተው የነበሩትን የመሠረተ እምነት ስሕተቶች ለማረምም የታቀደ ነበር።

በመጀመሪያው መልእክቱ ተደጋግሞ እንደ ተገለጠው እግዚአብሔርን የማወቅና ከእርሱ ጋር በአንድነት የመኖር ምልክቶች ሦስት ናቸው፤ እነርሱም:- የጻድቅ ሕወትን መኖር፥ በወንድማዊ ፍቅር መኖር፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ የለበሰ አምላክ መሆኑን ማመን ናቸው። እነዚህ ሦስት ምልክቶች የሌሉት ሰው ግን እግዚአብሔርን ዐውቀዋለሁ፥ ወይም ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት አለኝ ቢል ሐሰተኛ ነው። የመልእክቱ አመዛኝ ሐሳብ እግዚአብሔር ብርሃን ነው፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነው በሚሉት ላይ ያተኰረ ነው (ም:1፥1–4፥21)።

በሁለተኛውና በሦስተኛው መልእክቶችም የተተኰረባቸው ጉዳዮች ከመጀመሪያው መልእክት የተለዩ አይደሉም።

## ጥያቄዎች

1. ነቢዩ ሕዝቅኤል በትንቢቱ መነሻ የጠቀሰው ዘመን መነሻ ሦስት ሐሳቦች ምን ምን ናቸው?
2. የሕዝቅኤል አባት ስም ማን ይባል ነበር?
3. ሕዝቅኤል የትንበ.ት አገለግሎቱን የሰጠው ለስንት ዓመት ነው?
4. በሕዝቅኤል ትንቢት እግዚአብሔር ስንት ዐላማዎች እንዳሉት ይገመታል? እነርሱስ ምን ምን ናቸው?
5. በምርኮኞች መካከል የነበሩ ሐሰተኞች ነቢያት ምን ዐይነት የሐሰት ተንቢት ተናግረው ነበር?
6. የትንቢተ ሕዝቅኤል መጽሐፍ ምዕራፎች ስንት ናቸው?
7. መጽሐፉስ በስንት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል?
8. ሁለቱ ንስሮች በምንና በምን ይመሰላሉ?
9. የይሁዳ ንጉሥ ቃል ኪዳኑን ስላፈረሰ ምን ችግር ደረሰበት?
10. የነቢዩ ሕዝቅኤል ሚስት መሞት ለምን ምሳሌ ነበር?
11. ለነቢዩ ሕዝቅኤል የተሰጠው ኀላፊነትና ምሳሌ ምን የሚል ነበር?
12. ኀላፊነቱን ባይወጣ ምን ማስጠንቀቂያ ተሰጠው?
13. ነቢዩ ሆሴዕ ያገለገለበት ዘመን ስንት ዓመት እንደነበረ ይገመታል?
14. ነቢዩ ሆሴዕ የትንቢት አገልግሎቱን ይሰጥ የነበረው በማንኛው ነቢይ ዘመን ነበር?
15. ነቢዩ ሆሴዕ አገልግሎቱን የሰጠው በየትኛዋ ከተማ ነው?
16. የትንቢተ ሆሴዕ መጽሐፍ ስንት ምዕራፎች አሉት?



17. የእስራኤልን ጣዖት አምላኪነት ለማመልከት እግዚአብሔር ሆሴዕን ምን እንዲያደርግ አዘዘው?
18. የሆሴዕ ሦስት ልጆች ማን ማን ይባሉ ነበር?
19. የሚስቱስ ስም ማን ነበር?
20. ነቢዩ ኢዩኤል አገልግሎት የሰጠው በየትኛው አገር ነው?
21. መጽሐፉ ስንት ምዕራፎች አሉት?
22. አሞጽ ከመጠራቱ በፊት ምን ይሠራ ነበር?
23. ይኖርባት የነበረችው ሰፈር ማን ትባል ነበር?
24. ትንቢተ አሞጽ ስንት ምዕራፎች አሉት?
25. ትንቢተ አብድዩ ስንት ምዕራፎች አሉት?
26. ነቢዩ ሚክያስ በነበረበት ዘመን የነበሩት ነቢያት ማን፥ ማን ናቸው?
27. ትንቢት የተናገረውስ ስለማን ነው?
28. ትንቢተ ሚክያስ ስንት ምዕራፎች አሉት?
29. የትኛው ትልቅ መጽሐፍ ነው በትንቢተ ሚክያስ ውስጥ በአጭሩ የቀረበው?
30. በተረፈ ዳንኤል የቀረበው ቤል ምንድነው?
31. ዘንዶውስ ምን ያስገብር ነበረ?
32. በዕብራይስጡና በሰባዎቹ ሊቃውንት ትርጓሜ ያለው የትንቢተ ዳንኤል መጽሐፍ ልዩነት እንዴት ነው?
33. የጣዖት ካህናት ንጉሡንና ሕዝቡን ያታልሉ የነበረው እንዴት ነው?
34. ዳንኤል እንዴት አድርጎ አጋለጣቸው?
35. አታላይነታቸው ሲጋለጥ እንደምን ተቀጡ?
36. ዳንኤል ዘንዶውን በምን ዐይነት አጠፋው?
37. ጣዖት አምላኪዎች ዳንኤልን ምን አደረጉት·
38. እግዚአብሔር ለዳንኤል ምን አደረገለት?
39. ንጉሡስ ለዳንኤል እንዴት ተበቀለለት?
40. ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታችንን ከመከተሉ በፊት ስሙ ማን ነበር?
41. ይኖርበት የነበረው ሰፈር ማን ይባላል?
42. የእርሱስ ወንድም ስም ማን ይባል ነበር?
43. ጴጥሮስ ወይም ኬፋ ማለት ምን ማለት ነው?
44. ሰማዕትነት የተቀበለው በየትኛው አገር ነው?
45. ባቢሎን ስለተባለው አገር ሦስት አስተያየቶች ግለጥ።
46. መልእክቱን ለመጻፍ የተነሣሣበት ዋናው ምክንያት ምን ነበር?
47. ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ያቀረባቸው አራት ምክሮች ምን ምን ናቸው?
48. ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በሦስቱ መልእክቶቹ ውስጥ ስሙን ያልገለጠ እንደመሆኑ እነዚያ መልእክቶች እንዴት የእርሱ መሆናቸው ታወቀ?
49. የመጀመሪያ መልእክቱን የጻፈበት ዋነኛው ምክንያት ምንድነው?
50. በዚህ በመጀመሪያ መልእክቱ ውስጥ ያሉት ስድስት ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?
51. ሁለተኛ መልእክቱ የተጻፈው ለማን ነው?
52. ስለምንስ ጉዳይ ነው?
53. ሦስተኛ መልእክቱ የተጻፈው ለማንና ለምን ጉዳይ ነው?
54. እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን የሰው ልጅ የሚል መጠሪያ የሰጠው በምን ምክንያት ነው?
55. ሕዝቅኤል የብራናውን ጥቅል ብላው መባሉ ምን ለማለት ነው?
56. ለሕዝቅኤል፥ በእርሱም አማካይነት ለእኛ የተሰጠን ኀላፊነትና ማስጠንቀቂያ ምን የሚለው ነው?
57. እግዚአብሔር ሆሴዕን ዘማዊት ሚስት እንዲያገባ ያዘዘው ምንን ለማመልከት ነው?
58. ነቢዩ ኢዩኤል ያየው የአንበጣ መንጋ በምን ይመሰላል?

www.ethiopianorthodox.org

59. እህሉን ያጠፉት ተምች፡ አንበጣ፡ ደጎብያና ኩብኩባ በምን ይመሰላሉ?
60. ነቢዩ ኢዩኤል ለሕዝቡ ምን ምክር ሰጠ?
61. የሰሜን ሠራዊት የተባለው በማን ይመሰላል?
62. በብሉይ ኪዳን በቁጠባ ይሰጥ የነበረውና በሐዲስ ኪዳን ግን ለሁሉም የተሰጠው ምንድነው?
63. ይህ የነቢዩ ኢዩኤል ትንቢት ተግባራዊ የሆነው መቼ ነው?
64. ነቢዩ አሞጽ ትንቢት ከተናገረባቸው አገሮች መካከል የይሁዳ ኃጢአት በምን ይለያል?
65. ነቢዩ ሚክያስ የተናገረው ዝነኛ ትንቢት ምን የሚለው ነው?
66. ከቤልና ድራጎን ታሪክ ምን እንማራለን?
67. እግዚአብሔር አስቀድሞ የሚመርጠው እንዴት ነው?
68. የክርስቲያን ነጻነት የክፋት መሸፈኛ መሆን የለበትም ማለት ምን ማለት ነው?
69. የሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ መጀመሪያ መልእክት ምን ዐላማ ነበረው?
70. እግዚአብሔርን የማወቅ ሦስት ምልክቶች ምን ምን ናቸው?
71. የሐዋርያው የቅዱስ ዮሐንስ መልክቶች ትኩረት ያመዘነው በምን ላይ ነበር?

[stamp]

## ምዕራፍ 3

# ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ

## የጌታችን ትምህርቶች

ስለሚደርስበት ሕማምና ሞት:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙ ርቱን እንዲህ ሲል ማስተማር ጀመረ:- «የሰው ልጅ ብዙ መከራ መቀበል ይገባዋል በሽማግሌዎች፡ በካህናት አለቆችና በሙሴ ሕግ መምህራን ይናቃል፤ ይገደላልም፤ ይሁን እንጂ ከሦስት ቀን በኋላ ይነሣል» ብሎ ይህን ነገር በግልጥ ነገራቸው። በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ ለብቻው ገለል አድርጎት «እንዲህ አትበል» ሲል ከለከለው። ጌታችን ግን ዘወር ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ተመለከተና ጴጥሮስን «አንተ ሰይጣን ከእኔ ወዲያ ሂድ፤ አንተ የሰውን እንጂ የእግዚአ ብሔርን ነገር አታስብም» ሲል ገሠጸው (ማቴ:ም:16 ቊ:21–23፥ ማር:ም:8 ቊ:31–31፥ ሉቃ:ም:9 ቊ:22–27)።

የደቀ መዛሙርቱን እግር ማጠቡ:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከማዕድ ተነሥና ልብሱን አስቀመጠ ፎጣም አንሥቶ በወገቡ ታጠቀ ከዚያ በኋላ በመታጠቢያ ሣህን ውሃ አድርጎ የደቀ መዛሙርቱን እግር ማጠብ ጀመረ፤ በታጠቀውም ፎጣ አግራቸውን አበሰ። ጌታችን ወደ ስምዖን ጴጥሮስ በመጣ ጊዜ ስምዖን ጴጥሮስ «ጌታ ሆይ፥ አንተ የእኔን እግር ታጥባለህን?» አለው። ጌታችንም «እኔ የማደርገውን አንተ አሁን አታውቅም፤ በኋላ ግን ታውቃለህ» አለው። ጴጥሮስም «አንተ የእኔን እግር ከቶ አታጥብም» አለው። ጌታችንም «እኔ እግርህን ካላጠብኩህ ከእኔ ጋር አንድነት አይኖርህም» አለው። ስምዖን ጴጥሮስም «ጌታ ሆይ፥ እንዲህስ ከሆነ እግሬን ብቻ ሳይሆን እጄንም ራሴንም እጠበኝ አለው። ጌታችንም «ሰውነቱን የታጠበ ሁለመናው ንጹሕ በመሆኑ፤ እግሩን ከመታጠብ በቀር ሌላ አያስፈልገውም። እናንተም ንጹሖች ናችሁ፤ ነገር ግን ሁላችሁም ንጹሖች አይደላችሁም» አለው። ጌታችንም ሁላችሁም ንጹሖች አይደላችሁም» ያለው አሳልፎ የሚሰጠው ማን እንደሆነ ያውቅ ስለነበረ ነው።

እግራቸውን ካጠበ በኋላ ልብሱን ለበሰና ወደ ቦታው ተመልሶ ተቀመጠ፤ እንዲህም አላቸው፤ «ምን እንዳደረግሁላችሁ አስተዋላችሁን፥ እናንተ ‹መምህርና ጌታ› ትሉኛላችሁ፤ እኔ መምህርና ጌታ ስለሆንኩ ያላችሁት ትክ ክል ነው። እንግዲህ እኔ ጌታችሁና መምህራችሁ ስሆን እግራችሁን ካጠብኩ እናንተም እርስ በርሳችሁ እግራችሁን መተጣጠብ ይገባችኋል።

እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁት አናንተም እንድታደርጉ ምሳሌ ሰጥቻ ችኋለሁ። በእውነት እላችኋለሁ አገልጋይ ከጌታው አይበልጥም። መልእክ ተኛም ከላኪው አይበልጥም። ይህን ነገር ብታውቁና በሥራ ላይ ብታውሉት የተመሰገናችሁ ናችሁ። ይህን የምናገረው ስለ ሁላችሁም አይደለም፤ እኔ የመረጥኋችሁን አውቃለሁ ነገር ግን ‹እንጀራዬን የበላ በእኔ ላይ በጠላትነት



www.ethiopianorthodox.org

ተነሣብኝ› የሚለው የመጽሐፍ ቃል መፈጸም አለበት። ይህ ከመሆኑ በፊት አሁን አስቀድሜ የምነግራችሁ ከተፈጸመ በኋላ በእኔ ማንነት እንድታምኑ ነው። በእውነት እላችኋለሁ፤ እኔ የምልከውን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበል የላከኝንም ይቀበላል» (ዮሐ:ም:13 ቊ–20)።

የምሥጢረ ቍርባን ምሥረታ:- ራት ሲበሉም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብስት አንሥቶ የምስጋና ጸሎት አደረገ፤ ቈርሶም ለደቀ መዛምርቱ «እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው» ብሎ ሰጣቸው።

ጽዋውንም አነሥቶ የምስጋና ጸሎት ካደረገ በኋላ እንዲህ ሲል ሰጣቸው:- «ሁላችሁም ከዚህ ጽዋ ጠጡ፤ ይህ ስለብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው» አላቸው (ማቴ:ም26 ቊ:ም:26–30፥ ማር:ም:14 ቊ:27–31፥ ሉቃ:ም:22 ቊ:31–34፥ ሐ:ም:13 ቊ:36–38)።

ጌቴሴማኒ:- ከዚህ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ጌቴሴማኒ ወደሚባል ሥፍራ ሄደ፤ እዚያም እንደ ደረሱ ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን «እኔ እዚያ ሄጄ እስከጸልይ እናንተ እዚህ ቆዩ» አላቸው። ከእርሱ ጋር ጴጥሮስንና የዘብዴዎስን ልጆች አስከትሎ ሄደ፤ ማዘንና መጨነቅም ጀመረ። እንዲህም አላቸው:- «ለመሞት እስከደርስ አዝኛለሁ፤ እዚህ ቆዩ፤ ከእኔም ጋር ንቁ።» ከእነርሱ ጥቂት ራቅ ብሎ ሄደና በመሬት ላይ በግንባሩ ተደፍቶ እንዲህ ሲል ጸለየ፥ «አባት ሆይ፥ የሚቻል ከሆነ ይህ የመከራ ጽዋ ከእኔ ወዲያ ይለፍ፤ ነገር ግን እንደ አንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ እንደ እኔ ፈቃድ አይሁን።»

ከዚህ በኋላ ወደ ሦስቱ ደቀ መዛሙርት ተመልሶ በመጣ ጊዜ ተኝተው አገኛቸው፤ ስለዚህ ቅዱስ ጴጥሮስን እንዲህ አለው:- «ከእኔ ጋር አንዲት ሰዓት እንኳ መንቃት አልቻላችሁምን? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ፤ የሰው መንፈስ ሁልጊዜ ዝግጁ ነው፤ ሥጋ ግን ደካማ ነው።»

እንደገናም ጌታችን ለሁለተኛ ጊዜ ርቆ ሄደና «አባቴ ሆይ ይህ የመከራ ጽዋ ሳልጠጣው ሊያልፍ የማይቻል ከሆነ እንደ አንተ ፈቃድ ይሁን» ሲል ጸለየ። ደግሞም ወደ ደቀመዛሙርቱ ተመልሶ በመጣ ጊዜ ዓይኖቻቸው በአንቅልፍ ከብደው ነበርና ተኝታችኋልን? አሁንም ዕረፍት ታደርጋለላ ችሁን? እነሆ ሰዓቱ ደርሶአል፥ የሰው ልጅ በኃጢአተኞች እጅ ተላልፎ ይሰጣል፤ ተነሡ እንሂድ፥ እነሆ አሳልፎ የሚሰጠኝ ቀርቦአል» (ማቴ:ም:26ቊ:36–46)።

የጌታችን መያዝ:- ጌታችን ገና ሲናገር ሳለ እነሆ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ የሆነው ይሁዳ መጣ፤ ከእርሱም ጋም ሰይፍና ዱላ የያዙ ብዙ ሰዎች መጡ፤ እነርሱ ከካህናት አለቆችና ከሕዝብ ሽማግሌዎች የተላኩ ነበሩ። ጌታችንን አሳልፎ የሚሰጠው ይሁዳ ለሰዎቹ «የምትፈልጉት እኔ የምስመው ነውና እርሱን ያዙት» ሲል ምልክት ሰጥቶአቸው ነበር። ይሁዳ ወዲያውኑ መጥቶ ወደ ጌታችን ቀረበና «መምህር ሆይ ሰላም ለአንተ ይሁን» ብሎ ሳመው። ጌታችን ግን ይሁዳ ሆይ፥ የሰውን ልጅ በመሳም አሳልፈህ ትሰጣለህን? አለው። ጌታችንም «ወዳጄ ሆይ፥ እንግዲህ የመጣህበትን ጉዳይ ፈጽም» አለው፤ ከዚህ በኋላ ሰዎቹ ወደ ጌታችን ቀረቡና ያዙት። በዚህ ጊዜ ከጌታችን ጋር ከነበሩት አንዱ ሰይፉን መዘዘና የሊቀ ዛህናቱን አገልጋይ መትቶ ጆሮውን ቈረጠው። ጌታችን ግን እንዲህ አለ:- «ሰይፍን የሚያነሡ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ ሰገባው መልሰህ ክተተው። ለመሆኑ እኔ አባቴን ብለምን እርሱ በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ የመላእክት ሠራዊት ሊልክልኝ የማይችል ይመስልሃልን? እንዲህማ ቢሆን ኖሮ ‹መከራ መቀበል አለበት› የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንዴት ይፈጸማል?»

በዚያን ሰዓት ጌታችን ኢየሱስ ለሕዝቡ እንዲህ አለ:- «ወንበዴን እንደምትይዙ እኔን ለመያዝ ሰይፍና ዱላ ይዛችሁ መጣችሁን? በየቀኑ በቤተ መቀደስ እያስተማርሁ ከእናንተ ጋር ሳለሁ አልያዛችሁኝም ነበር፤ ነገር ግን ይህ ሁሉ የሆነው በነቢያት የተጻፈው እንዲፈጸም ነው።» በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ትተውት ሸሹ (ማቴ: ም:2 6 ቊ:47–56 ማር: ም:14 ቊ:43–50 ሉቃ: ም:22 ቊ47–53–፥ ዮሐ: ም: 18 ቊ:3–11)።

ጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ፍርድ ሸንጎ መቅረቡ:- ከዚህ በኋላ ጌታችንን የያዙት ሰዎች ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ ወሰዱት። በዚያም የሕግ መምህራንና ሽማግሌዎች ተሰብስበው ነበር። ጴጥሮስ ግን እስከ ሊቀካህናቱ ግቢ ድረስ ጌታችንን በሩቅ ተከተለው፤ ወደ ውስጥ ገብቶም የነገሩን ፍጻሜ ለማየት ከሌሎች ጋር ተቀመጠ። የካህናት አለቆችና የሸንጎውም አባሎች

ሁሉ በጌታችን ላይ የሞት ፍርድ ለማስፈረድ የሐሰት ምስክር ይፈልጉ ነበር። ምንም እንኳ ብዙ የሐሰት ምስክሮች ቢቀርቡ ሞት የሚያስፈርድበት ምስክርነት አላገኙም፤ በመጨረሻ ሁለት ምስክሮች ቀርበው፥ «ይህ ሰው የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ አፍርሼ በሦስት ቀን ልሠራው እችላለሁ› ብሎአል» ሲሉ ተናገሩ።

ሊቀ ካህናቱም ተነሣና «እነዚህ ሰዎች ለሚመሰክሩብህ ሁሉ ምንም መልስ አትሰጥምን?» ሲል ጠየቀው። ጌታችን ግን ዝም አለ። ሊቀ ካህናቱም እንደገና ጌታችንን «በሕያው እግዚአብሔር ስም ይገርሃለሁ፤ የእግዚአብሔር ልጅ መሲሕ አንተ እንደሆንክ ንገረን?» አለው። ጌታችንም እንዲህ ሲል መለሰለት:- «አንተ እንዳልከው ነው፤ ነገር ግን ከእንግዲህ ወዲህ የሰው ልጅ በኃያሉ እግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ታዩታላችሁ፤ እንዲሁም በሰማይ ደመና ሆኖ ሲመጣ ታዩታላችሁ እላችኋላሁ።» በዚህ ጊዜ ሊቀ ካህናቱ በብስጭት ልብሱን ቀደደና እንዲህ አለ። «እነሆ በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል ተናግሮአል፥ እናንተም ስድቡን ሰምታችኋል፤ ከእንግዲህ ወዲህ ምን ምስክር ያስፈልጋል? ታዲያ ምን ይመስላችኋል?» እነርሱም «ሞት ይገባዋል» ሲሉ መለሱ።

በዚያን ጊዜ ምራቃቸውን ተፉበት ጐሸሙት፥ በጥፊም እየመቱት «መሲሕ ሆይ፥ ማን ነው የመታህ እስቲ ንገረን› ይሉት ነበር (ማቴ: ም:26 ቁ:57–68፥ ማር ም:14 ቁ: 53–65፥ ሉቃ: ም:22 ቁ:54–57፥ ዮሐ:ም:18 ቁ:13–17፥ 19–24)።

ጴጥሮስ ጌታችንን መካዱ:- ጴጥሮስ ከቤት ውጪ በሊቀ ካህናቱ ግቢ ውስጥ ተቀምጦ ነበር፥ በዚያን ጊዜ አንዲት ገረድ ወደ እርሱ ቀርባ «አንተም እኮ ከገሊላዊው ኢየሱስ ጋር ነበርክ» አለችው። እርሱ ግን «የምትይውን አላውቅም» ሲል በሁሉም ፊት ካደ። ሊወጣ ወደ በሩ ሲሄድ አንዲት ሌላ ገረድ አየችውና እዚያ ለነበሩት ሰዎች «ይህ ሰው ከናዝሬቱ ኢየሱስ ጋር ነበር አለች። ጴጥሮስም ይህን የምትይውን ሰው አላውቀውም» ሲል በመማል እንደገና ካደ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ እዚያ ቆመው የነበሩት ሰዎች ወደ ጴጥሮስ ጠጋ ብለው «አነጋገርህ ያስታውቃልና በእርግጥ አንተም ከእርሱ ወገን ነህ» አሉት። በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ «እኔ ይህን ሰው አላውቀውም» እያለ ራሱን መራገምና መማል ጀመረ። ወዲያውኑ ዶሮ ጮኸ።

ጴጥሮስም «ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ» ብሎ ጌታችን የተናገረው ቃል ትዝ አለው። ወደ ውጪም ወጣና ምርር ብሎ አለቀሰ።

ጌታችን ወደ ጲላጦስ ፊት መቅረቡና መመርመሩ:- ጧት በማለዳ የካህናት አለቆችና የሕዝብ ሽማግሌዎች ሁሉ በጌታችን ላይ የሞት ፍርድ ለማስፈረድ ተማከሩ። ከዚህ በኋላ ጌታችንን አስረው ወሰዱና ለገገርው ለጲላጦስ አሳልፈው ሰጡት።

ጌታችንን አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ ጌታችን እንደተፈረደበት ባየ ጊዜ ተጸጸተ፤ ሠላሳውንም ጠገራ ብር ለካህናት አለቆችና ለሽማግሌዎች እንዲህ በማለት መልሶ ሰጣቸው፤ «ንጹሑን ሰው ለሞት አሳልፌ በመስጠቴ በድዬአ ለሁ»። እነርሱ ግን «ታዲያ እኛ ምን ቸገረን? የራስህ ጉዳይ ነው» አሉት። እርሱም ሠላሳውን ጠገራ ብር በቤተ መቅደስ ውስጥ በትኖ ትቶአቸው ወጣ፥ ሄዶም ታንቆ ሞተ።

የካህናት አለቆች ሠላሳውን ጠገራ ብር አንሥተው «ይህ ገንዘብ የደም ዋጋ ስለሆነ ከቤተ መቅደስ መባ ጋር ልንቀላቅለው አይፈቀድም» አሉ። ስለዚህ ከተመካከሩ በኋላ ለእንግዶች የመቃብር ቦታ እንዲሆን የሸክላ ሠሪውን መሬት ገዙበት። በዚህ ምክንያት ያ መሬት እስከ ዛሬ ድረስ «የደም መሬት» እየተባለ ይጠራል።

በዚህ ሁናቴ፥ «የእስራኤል ልጆች የገመቱትን ለእርሱ ዋጋ የሚሆን ሠላሳ ጠገራ ብር ወሰዱ፤ ጌታም እንዳዘዘኝ ስለ ሸክላ ሠሪው መሬት ከፈሉ» ተብሎ በነቢዩ ኤርምያስ የተነገረው ትንቢት ተፈጸመ (ዘካ:ም:11ቁ:13)።

በዚያን ጊዜ ጌታችን ወደ ገዥው ወደ ጲላጦስ ፊት ቀረበ፤ ገዥውም «አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህን?» ሲል ጠየቀው፤ እርሱም «አንተ እንዳልኸው ነኝ› ሲል መለሰ። ነገር ግን የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች ሲወነጅሉት ምንም መልስ አልሰጠም። ከዚህ በኋላ ጲላጦስ «በስንት ነገር ሲወነጅሉህ አትሰማምን?» አለው። ኢየሱስ ግን ገዥው እስኪደነቅ ድረስ አንዲት ቃል እንኳ አልመለሰለትም (ማቴ:ም:27ቁ:1–14፥ ማር:ም:15 ቁ:1–5፡ ሉቃም:23 ቁ:1–5፥ ዮሐ:ም:18 ቁ:28–38)።



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሞት ፍርድ የተፈረደበት ሁኔታ:- ገዢው ጲላጦስ በየዓመቱ በአይሁድ ፋሲካ በዓል ጊዜ እንዲፈታላቸው ሕዝቡ የጠየቁትን አንድ እስረኛ ፈትቶ መልቀቅ አስለምዶ ነበር። በዚያን ጊዜ በርባን የተባለ በሀመፀኛነቱ የታወቀ እስረኛ ነበራቸው። ስለዚህ ሕዝቡ በተሰበሰበ ጊዜ ጲላጦስ «ማንን እንድፈታላችሁ ትፈልጋላችሁ? በርባንን ነውን ወይስ መሲሕ የተባለውን ኢየሱስን?» ሲል ጠየቃቸው። ይህንን ያለበት መክንያት ጌታችንን በቅናት አሳልፍው እንደሰጡት ያውቅ ስለነበር ነው። ጲላጦስ በፍርድ ወንበር ተቀምጦ ሳለ ሚስቱ «በእርሱ ምክንያት ዛሬ ሌሊት በሕልም ብዙ ተሠቃይቻ ለሁና በዚያ በንጹሕ ሰው ላይ ምንም እንዳታደርግ» ስትል ላከችበት። በዚያን ጊዜ የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች «በርባን ይለቀቅ፥ ኢየሱስ ይገደል» ብለው እንዲጠይቁ ሕዝቡን አግባቡ። ገዢውም ከሁለቱ የትኛውን እንድፈታላችሁ ትፈልጋላችሁ» ሲል ሕዝቡን እንደገና ጠየቀ። እነርሱም «በርባንን እንድትፈታልን እንፈልጋለን» ሲሉ መለሱ። ጲላጦስም «ታዲያ መሲሕ የተባ ለውን ኢየሱስን ምን ላድርገው አላቸው» ሁሉም «ይሰቀል» ሲሉ መለሱ። ገዢውም «እርሱ ያደረገው በደል ምንድን ነው? አላቸው። እነርሱ ግን «ይሰቀል» እያሉ አብዝተው ጮኹ። ስለዚህ ጲላጦስ ይህ ነገር ሁከት እንደሚያስነሣ እንጂ ሌላ ምንም እንደማይጠቅም ባየ ጊዜ ውሃ አስመጥቶ «እኔ ለዚህ ሰው ሞት ኃላፊ አይደለሁም፤ እናንተ እንደፈለጋችሁ አድርጉ» ብሎ በሕዝቡ ፊት እጁን ታጠበ።

ሕዝቡም ሁሉ «በእርሱ ሞት ምክንያት የሚመጣው ቅጣት በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን» አሉ።

በዚያን ጊዜ ጲላጦስ በርባንን ፈትቶ ለቀቀላቸው ጌታችንን ግን ካስገረፈው በኋላ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጣቸው።

በዚያን ጊዜ የገገርው ወታደሮች ወደ ገገርው ግቢ ወሰዱት፡ ወታደሮቹንም ሁሉ በጌታችን ዙሪያ ሰበሰቡ። ልብሱንም ገፍፈው ቀይ ልብስ አለበሱት። የሾኽ አክሊልም ጐንጉነው በራሱ ላይ ደፉበት በቀኝ እጁም መቃ አስያዙት፤ በፊቱም እየተንበረከኩ «የአይሁድ ንጉሥ ሆይ ሰላም ለአንተ ይሁን» እያሉ ያፌዙበት ነበር፡ ምራቃቸውንም ይተፉበት ነበር፡ መቃውንም ከእጁ ወስደው ራስ ራሱን በመቃው ይመቱት ነበር። ካፌዙበትም በኋላ ቀዩን ልብስ አውልቀው የራሱን ልብስ አለበሱት ሊሰቅሉትም ወሰዱት (ማቴ: ም:27 ቁ:15–31፡ ማር: ም:15 ቁ:6–20፥ ሉቃ: ም:23 ቁ:13–25፡ ዮሐ: ም: 18 ቁ:39–40 : ም:19 ቁ:1–16)።

የጌታችን መሰቀል:- ከገገርው ግቢ ሲወጡ ሳሉ ስምዖን የተባለውን የቀሬና አገር ሰው አገኙና የጌታችንን መስቀል እንዲሸከም አስገደዱት። ከዚህ በኋላ ቀራንዮ ወይም የራስ ቅል እየተባለ ወደሚጠራው ሥፍራ ወደ ጎልጎታ ደረሱ። በዚያም ከሐሞት ጋር የተቀላቀለ የወይን ጠጅ እንዲጠጣ ለጌታችን አቀረቡለት፡ እርሱ ግን ቀምሶ አድርጎ ሊጠጣው አልፈለገም።

ጌታችንን ከሰቀሉት በኋላ ልብሱን ዕጣ ተጣጥለው ተካፈሉ። በዚያም ተቀምጠው ይጠብቁት ነበር። ወንጀሉንም የሚያመለክት «ይህ የአይሁድ ንጉሥ ኢየሱስ ነው የሚል ጽሑፍ በጌታችን ራስጌ በመስቀሉ ላይ አኖሩ። በዚያን ጊዜ ሁለት ወንበዴዎች አንዱ በቀኙ አንዱ በግራው ከእርሱ ጋር ተሰቀሉ።

በአጠገቡ ያልፉ የነበሩትም ሰዎች በንቀት ራሳቸውን እየነቀነቁ፡ «አንተ ቤተ መቅደስን የምታፈርስና በሦስት ቀን የምትሠራው እስቲ ራስህን አድን፡ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ እስቲ ከመስቀል ውረድ» በማለት ያላግጡበት ነበር።

በዚሁ ዐይነት የካህናት አለቆች ከሕግ መምህራንና ከሽማግሌዎች ጋር እንዲህ እያሉ ያፌዙበት ነበር:- «ሌሎችን አዳነ፡ ራሱን ግን ማዳን አይችልም። እርሱ የእስራኤል ንጉሥ ከሆነ እስቲ አሁን ከመስቀል ይውረድና እኛም እንመንበት። እርሱ በእግዚአብሔር ታምኖአል። የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሎአል፡ ስለዚህ እግዚአብሔር የሚወድደው ከሆነ እስቲ አሁን ያድነው» ይሉ ነበር። (ማቴ:ም:27 ቁ:32–44)።

ከጌታችን ኢየሱስ ጋር የተሰቀሉት ሁለት ወንጀለኞች:- ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ከተሰቀሉት ወንጀለኞች አንዱ ጌታችንን «አንተ መሲሕ አይደለህምን? እስቲ በል ራስህንና እኛን አድን» እያለ ይሰድበው ነበር። ሌላው ወንጀለኛ ግን እንዲህ ብሎ ገሠጸው:- «አንተ ደግሞ በሞት ፍርድ ላይ እያለህ እንኳ እግዚአብሔርን አትፈራምን? እኛ ባደረግነው በደል ምክንያት ቅጣት መቀበላችን የተገባ ፍርድ ነው፡ ይህ ሰው ግን ምንም ጥፋት አላደረገም።» ቀጥሎም ጌታችንን ኢየሱስን «ጌታ ሆይ ወደ መንግሥትህ ስትገባ አስታ ውሰኝ» አለው። ጌታችንም «በእውነት እልሃለሁ:- ዛሬውኑ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ» አለው (ሉቃ:23፡ 39–43)።



www.ethiopianorthodox.org

የጌታችን ሞት:- ከስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ። ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ኢየሱስ ኤሎሄ፥ ኤሎሄ፥ላማ ሰበቅታኒ?» ሲል በታላቅ ድምፅ ጮኸ፥ ትርጓሜውም «አምላኬ፥ አምላኬ፥ ለምን ተውከኝ?» ማለት ነው። በዚያም ቆመው ከነበሩት ሰዎች አንዳንዶቹ «ይህስ ኤልያስን ይጠራል» አሉ። በዚያን ጊዜ ከእነርሱ አንዱ ስፖንጅ አምጥቶ ሆምጣጤ ሞላበት፤ በመቃ ላይ አድርጎም ጌታችን እንዲጠጣ አቀረበለት። ሌሎችም «ቈይ እስቲ ኤልያስ መጥቶ ያድነው፥ እንደሆነ እንይ» አሉ። ጌታችን እንደገና በታላቅ ድምፅ ጮኸና ነፍሱን ሰጠ።

በዚያን ጊዜ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ተቀዶ ከሁለት ተከፈለ፤ ምድርም ተናወጠች፤ አለቶችም ተሰነጠቁ፤ መቃብሮችም ተከፍተው ሞተው ከነበሩት ብዙ ቅዱሳን ሰዎች ከሞት ተነሡ። ከመቃብርም ወጡና ጌታችን ከሞት ከተነሣ በኋላ ወደ ቅድስት ከተማ ወደ ኢየሩሳሌም ገቡ፤ በዚያም ለብዙ ሰዎች ታዩ።

የመቶ አለቃውና ከእርሱም ጋር ጌታችንን ይጠብቁ የነበሩት የምድርን መናወጥና ሌላውንም ነገር ባዩ ጊዜ እጅግ ፈርተው «በእውነት ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ» አሉ። በሩቅ ሆነው የሚመለከቱት ብዙ ሴቶችም በዚያ ነበሩ። እነርሱ ከገሊላ ጀምረው ጌታችንን እያገለገሉ ይከተሉት የነበሩ ናቸው። ከእነርሱም መካከል መግደላዊት ማርያም፥ የያዕቆብና የዮሴፍ እናት ማርያም፥ የዘብዴዎስ ልጆች እናት ይገኙባቸው ነበር።

በመሸ ጊዜ የአርማትያስ ሰው የሆነ ዮሴፍ የሚባል አንድ ሀብታም ሰው ወደዚያ መጣ። እርሱም የጌታችን ደቀ መዝሙር ነበረ። ይህ ሰው ወደ ጲላጦስ ሄደና የጌታችንን አስከሬን ለመነ፤ ጲላጦስም አስከሬኑ እንዲሰጠው አዘዘ። ስለዚህ ዮሴፍ አስከሬኑን አውርዶ በንጹሕ ጨርቅ ከፈነው። ከአለት ተወቅሮ በተዘጋጀው በራሱ አዲስ መቃብር ውስጥ ቀበረው፤ ከዚህ በኋላ ትልቅ ድንጋይ አንከባልሎ የመቃብሩን በር ዘጋና ሄደ። መግደላዊት ማርያምና ሌላይቱ ማርያም እዚያ በመቃብሩ ፊት ለፊት ተቀምጠው ነበር።

በማግስቱ ቅዳሜ የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን በአንድነት ወደ ጲላጦስ ሄዱና እንዲህ አሉት:- «ጌታ ሆይ፥ ያ አሳሳች ገና በሕይወቱ ሳለ ከሦስት ቀን በኋላ ከሞት እነሣለሁ ያለው ትዝ አለን። ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ ሄደው እንዳይሰርቁትና ለሕዝቡም ‹እነሆ ከሞት ተነሥቶአል› እንዳይሉ መቃብሩ እስከ ሦስት ቀን ድረስ እንዲጠበቅ እዘዝ፤ አለበለዚያ የመጨረሻው ማሳሳት ከመጀመሪያው ይልቅ የባሰ ይሆናል።» ጲላጦስም «እነሆ ጠባቂዎች አሉላችሁ፤ ሂዱና በምትፈልጉት ዐይነት አስጠብቁ» አላቸው። ስለዚህ ሄደው ድንጋዩን በማኅተም አሽጉና መቃብሩን በወታደሮች አስጠበቁ (ማቴ: ም: 27 ቍ: 45–66፥ ማር: ም:15 ቍ:33–47፥ ሉቃ:ም 23 ቍ:44–56 ፥ዮሐ: ም:19 ቍ:28–42)።

## የጌታችን ተአምራት

የቤተ ሳይዳው ሽባ:- ከዚህ በኋላ የአይሁድ በዓል ስለነበረ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ። በኢየሩሳሌም በበጎች በር አጠገብ በዕብራይስጥ ቋንቋ ቤተ ሳይዳ የሚባል አንድ የምንጭ ኩሬ ነበረ፤ በዚያም አምስት ባለ ቅስት መተላለፊያዎች ነበሩ። ብዙ በሽተኞች፥ ዕውሮች፥ አንካሶች፥ ሽባዎች በመተላለፊያዎቹ ተኝተው ነበር። በዚያም ሠላሳ ስምንት ዓመት ሙሉ የታመመ አንድ ሰው ነበረ። ጌታችን ይህን ሰው እዚያ ተኝቶ አየውና ከብዙ ጊዜ ጀምሮ መታመሙን ዐውቆ «መዳን ትፈልጋለህን?» አለው።

በሽተኛውም «ጌታ ሆይ፥ ውሃው በተንቀሳቀሰ ጊዜ እኔን ወስዶ ወደ ኩሬው የሚያስገባኝ ሰው የለኝም፤ እኔ ልሄድ ስል ሌላው ቀድሞኝ ይወርዳል» አለው። ጌታችንም «ተነሥ አልጋህን ተሸከምና ሂድ» አለው። ሰውዬውም ወዲያውኑ ዳነ፤ አልጋውንም ተሸክሞ ሄደ። ይህም የሆነው በሰንበት ቀን ነበር፤ ስለዚህ አይሁድ ያንን የዳነውን ሰው «ዛሬ ሰንበት ስለሆነ አልጋህን መሸከም አልተፈቀደልህም» አሉት።

እርሱ ግን «ያዳነኝ ሰው አልጋህን ተሸከመህ ሂድ» ብሎኛል አላቸው። እነርሱም «አልጋህን ተሸክመህ ሂድ ያለህ ማን ነው?» ሲሉ ጠየቁት። ሕዝብ ስለበዛና ጌታችንም ከዚያ ራቅ ብሎ ስለሄደ ያዳነው ማን መሆኑን አያውቅም ነበር።

ከዚህ በኋላ ጌታችን ሰውዬውን በቤተ መቅደስ አገኘውና «እነሆ አሁን ድነሃል፤ ከዚህ የባሰ ነገር እንዳይደርስብህ ከእንግዲህ ወዲህ ኃጢአት አትሥራ› አለው። ሰውዬውም ሄደና ያዳነው እርሱ መሆኑን ለአይሁድ ነገረ። ይህን ነገር በሰንበት ስላደረገ አይሁድ የጌታችንን ያሳድዱት ጀመር። እርሱ ግን «አባቴ ሁልጊዜ ይሠራል፤ እኔም እሠራለሁ› ሲል መለሰላቸው።



ይህም አባባል አይሁድ ጌታችንን እንዲገድሉት በይበልጥ አነሣሣቸው፤ ምክንያቱም እርሱ ሰንበትን በመሻሩ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር አባቴ ነው» በማለት ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር ስለአስተካከለ ነው (ዮሐ:ም:5 ቍ:1–18)።

የወታደሮች ወደኋላ መውደቅ ተአምር:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ቄድሮን ወንዝ ማዶ ሄደ፤ እዚያ ወደነበረው የአትክልት ቦታ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ገባ። ጌታችን ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ እዚያ ቦታ ዘወትር ይሰበሰቡ ስለነበር አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ ያን ቦታ ያውቅ ነበር። ስለዚህ ይሁዳ ወታደሮቹን ከካህናት አለቆችና ከፈሪሳውያን የተላኩትን ሎሌዎች አስከትሎ ወደዚያ ቦታ መጣ፤ እነርሱም ፋኖስና ችቦ፥ የጦር መሣሪያም ይዘው ነበር። ጌታችን ኢየሱስም የሚደርስበትን ሁሉ ዐውቆ ወደ እነርሱ ሄደና «ማንን ትፈልጋላችሁ?» አላቸው። እነርሱም «የናዝሬቱን ኢየሱስን እንፈልጋለን» አሉት። እርሱም «እኔ ነኝ» አላቸው። አሳልፎ የሰጠው ይሁዳም ከእነርሱ ጋር ቆሞ ነበር። ጌታችን ኢየሱስ «እኔ ነኝ» ባላቸው ጊዜ ወደ ኋላ አፈገፈጉና በምድር ላይ ወደቁ (ዮሐ:ም:18 ቍ:1–6)።

የማልኮስ ጆሮ መፈወስ:- ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ የነበረውን የአስቆሮቱን ይሁዳን መሪ በማድረግ ብዙ ሰዎች ጌታችን ኢየሱስ ወደ ነበረበት ቦታ መጡ። ይሁዳም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሊስመው ወደ እርሱ ቀረበ። ጌታችን ግን ይሁዳ ሆይ፥ የሰውን ልጅ በመሳም አሳልፈህ ትሰጣለህን? አለው። ከጌታችን ኢየሱስ ጋር የነበሩት ደቀ መዛሙርት የነገሩን ሁኔታ ባዩ ጊዜ «ጌታ ሆ፥ በሰይፍ እንምታቸውን? አሉ። ከእነርሱም አንዱ የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ በሰይፍ መታና ቀኝ ጆሮውን ቈረጠው። ጌታችን ኢየሱስ ግን ይህስ አያስፈ ልግም ተው» አለ፤ የሰውዬውንም ጆሮ ዳሶ አዳነው (ሉቃ:22፥47–51)።

## የጌታችን ምሳሌዎች

ድኻዋ መበለትና ዓመፀኛው ዳኛ:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘወትር መጸለይ እንደሚገባቸው ለማስተማር ይህን ምሳሌ ነገራቸው፥ «በአንዲት ከተማ እግዚአብሔርን የማይፈራ፥ ሰውንም የማያፍር አንድ ዳኛ ነበረ። አንዲት መበለትም በዚያች ከተማ ትኖር ነበር፤ እርስዋ ወደ ዳኛው እየመጣች ‹ከባላጋራዬ ጋር ስላለኝ ክርክር ፍርድ ስጠኝ› ትለው ነበር። እርሱም ፍርዱን ሳይሰጣት ብዙ ጊዜ ቈየ፥ በኋላ ግን እንዲህ ሲል አሰበ፤ ‹ምንም እንኳ እግዚአብሔርን ባልፈራ ሰውንም ባላፍር ይህች መበለት ስለነዘነዘችኝ እፈርድ ላታለሁ፥ አለበለዚያ ግን ዘወትር እየተመላለሰች ታሰለቸኛለች።»›

ቀጥሎም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አለ:- «ዓመፀኛው ዳኛ የተናገ ረውን አስተ ውሉ፤ እግዚአብሔር ታዲያ ቀንና ሌሊት እየጮኹ ለሚለምኑት ሕዝቦቹ አይፈርድላቸውምን? ችላ በማለትስ እርዳታውን ያዘገይባቸዋልን? ሳይዘገይ በፍጥነት ይፈርድላቸዋል እላችኋለሁ። ነገር ግን የሰው ልጅ ብሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆን?» (ሉቃ:ም:18 ቍ:1–8)

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መልካም እረኛነት:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አለ:- «በእውነት እላችኋላሁ ወደ በጎች በረት በበር ሳይሆን በሌላ በኩል የሚገባ ሰው ሌባና ወንበዴ ነው። በበሩ የሚገባ ግን የበጎች እረኛ ነው፤ ለእርሱ በር ጠባቂው በሩን ይከፍትለታል፤ በጎቹ ድምፁን ይሰማሉ፤ እርሱም የራሱን በጎች በስማቸው ይጠራቸዋል፥ እየመራም ወደ ውጭ ይወስዳቸዋል። የራሱን በጎች ካስወጣ በኋላም እፊት እፊታቸው ይሄዳል። በጎቹም ድምፁን ስለሚያውቁ ይከተሉታል። የሌላውን ድምፅ ስለማያውቁ ግን ከሌላው ይሸሻሉ እንጂ አይከተሉም።» ጌታችን ይህን ምሳሌ ነገራቸው፤ እነርሱ ግን የተናገረውን አላስተዋሉም።

ስለዚህ ጌታችን እንደገና እንዲህ አላቸው:- «በእውነት እላችኋለሁ፥ እኔ የበጎች በር ነኝ ከእኔ በፊት የመጡት ሁሉ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው፤ በጎቹ ግን አልሰሙአቸውም። በሩ እኔ ነኝ፥ በእኔ በኩል የሚገባ ይድናል፤ ይገባል፤ ይወጣል፥ መሰማርያም ያገኛል። ሌባው የሚመጣው ለመስረቅና ለመግደል፥ ለማጥፋትም ብቻ ነው፤ እኔ ግን የመጣሁት ሕይወት እንዲያገኙና የተትረፈረፈ ሕወት እንዲኖራቸው ነው። መልካም እረኛ እኔ ነኝ፥ መልካም እረኛ ሕይወቱን ስለ በጎቹ አሳልፎ ይሰጣል። በጎቹ የራሱ ያልሆኑ ቅጥረኛ እረኛ ግን ተኵላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል፤ ተኵላውም በጎቹን ነጥቆ ይበታትናቸዋል። እረኛው የሚሸሸውም ቅጥረኛ ስለሆነና ለበጎቹም ስለማያስብ ነው። መልካም እረኛ እኔ ነኝ፥ እኔ በጎቹን አውቃለሁ፥ በጎቹም እኔን ያውቁኛል። እኔ እነርሱን የማውቃቸው አብ እኔን እንደሚያውቀኝና እኔም አብን

www.ethiopianorthodox.org

እንደ ማውቀው ዐይነት ነው፤ እኔ ስለ በጎቼ ሕወቴን አሳልፌ እሰጣለሁ። በዚህ መንጋ ውስጥ ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱንም ማምጣት ይገባኛል፤ እነርሱ ድምፄን ይሰማሉ፤ አንድ መንጋም ይሆናሉ፤ እረኛውም አንድ ይሆናል። ሕይወቴን አሳልፌ ለመስጠትና መልሼም ለመውሰድ ፈቃደኛ ስለሆንኩ አብ እኔን ይወደኛል። ሕይቴን በፈቃዴ አሳልፌ እሰጣለሁ እንጂ ከእኔ የሚወስዳት ማንም የለም፤ ሕይወቴን አሳልፌ ለመስጠትና መልሼም ለመውሰድ መብት አለኝ፤ ይህን ትእዛዝ የተቀበልኩት ከአባቴ ነው።»

ከዚህ ንግግር የተነሣ በአይሁድ መካከል እንደገና መለያየት ሆነ። ከእነ ርሱም ብዙዎቹ «እርሱ ጋኔን አለበት፤ አብዶአል፤ ስለምን ትሰሙታላችሁ? አሉ። ሌሎች «ይህ ንግግር ጋኔን ካለበት ሰው አንደበት የሚወጣ አይደለም፤ ጋኔን የዕውሮችን ዓይን ማዳን ይችላልን?» አሉ (ዮሐ:ም:10 ቍ:1–21)።

## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

በአይሁድ ዘንድ የነበረው አስተሳሰብ እነርሱ ይጠብቁት የነበረው ክርስቶስ በዳዊት ዙፋን ላይ ተቀምጦ እነርሱን ከሮም አገዛዝ ነጻ የሚያወጣቸውን ምድራዊ ንጉሥ ነበር። ይህም አስተሳሰብ በሕዝቡ ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በጌታችን ደቀ መዛሙርት ስሜት ላይም የተዛመተ ነበር። በዚህም ምክንያት የዘብዴዎስ ልጆች ማለት የያዕቆብና የዮሐንስ እናት ከልጆችዋ ጋር ወደ ጌታችን ቀርባ እርሱ ማለት ጌታችን በሚነግሥበት ጊዜ ለሁለቱ ልጆችዋ በቀ ኙና በግራው የመቀመጥን መብት እንዲሰጥላት ለመነችው። ስለዚህ ጌታችን የእርሱ ገገርነት በፍጥረቱ ሁሉ ላይ መሆኑን ባያስተባብልም እንኳ እንደ ምድራዊ ንጉሥ የሚነግሥ አለመሆኑን ገልጾአል። ይህንንም አባባል መንግ ሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለም ሲል ለጲላጦስ አረጋግጦለታል። ደቀ መዛሙ ርቱም እርሱ በዚህ ዓለም ላይ የማይነግሥ መሆኑን ብቻ ሳይሆን በአይሁድ ባለሥል ጣኖች አማካይነት ሕማምና ሞት እንደሚደርስበት በሦስት የተለያዩ ጊዜዎች መላልሶ ገልጦላቸዋል። ሦስት ጊዜ መላልሶ መናገሩም የነገሩን ተፈጻ ሚነት ለማረጋገጥ ነው። መሥዋዕት መቅረብ ያለበት በኢየሩሳሌም ስለነበረ እርሱም ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ትልቁ መሥዋዕት መሆን እንደሚገባው ገለጠ ላቸው። ከዚያ በፊት የነበሩት የተለያዩ መሥዋዕቶች በጥላነት የቀረቡ ብቻ ናቸው። ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ በጸሐፍት፥ በፈሪሳውያንና በሽማግሌዎች አማካይነት ሕማምና ሞት ደርሶበት በሦስተኛው ቀን እንደሚነሣ ነገራቸው። ደቀ መዛሙርቱ አሁንም የነበራቸው አስተሳሰብ ከዚያ የተለየ ስለነበረ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ ማለት አይገባም ብሎ ሊከለክለው ፈለገ። ጌታችን ግን ቅዱስ ጴጥሮስን አንተ ሰይጣን ከእኔ ወዲያ ሂድ አንተ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብም ብሎ ገሠጸው። ይህ አባባል ጌታችን ቀደም ብሎ በሰይጣን በተፈተነ ጊዜ ሰይጣንን የገሠጸበት አባባል ነው። ጌታችን ወደዚህ ዓለም መጥቶ የሰውን ልጅ ሥጋ በመልበስ ራሱን ዝቅ ማድረጉ የሰውን ዘር ሁሉ ከኃጢአት ባርነትና ከሰይጣን ተገዢነት ለመታደግ ነው። ታዲያ፥ ያን መለኮታዊ ዕቅድ የሚያስናክል ሐሳብ ሁሉ የሰይጣን ሥራ ነው። በዚህም መሠረት ሰይጣን የዓለምን ክብር በማሳየት ጌታችንን ከመጣበት ዓላማ ሊያዘናጋው ስለፈለገ ሂድ አንተ ሰይጣን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ብቻ ስገድ ብሎ ገሥጾታል። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም ለጌታችን ያዘነ መስሎት ሕማምና ሞት እንዳይደርስበት ስለተመኘ ሐሳቡ የጌታችንን ዕቅድ የሚቃወም በመሆኑ ሂድ አንተ ሰይጣን ብሎ ገሥጾታል። ሰይጣንም የተባለው ሐሳቡ ነው እንጂ ቅዱስ ጴጥሮስ አይደለም። (ማቴ: ም:4 ቍ:3፥ ም:16 ቍ:21–23፥ ም:20 ቍ:20–28)።

የጌታችን የማስተማሪያ መንገዶች የተለያዩ ነበሩ። እነርሱም ማዘዝና መምከር፥ መከልከልና ማስጠንቀቅ፥ ጥያቄና መልስ፥ ገለጻ ማድረግና ማብራ ራት፥ ስሕተተኛ አስተሳሰብን ማረም፥ ማወዳደርና ማነጻጸር፥ ምክንያታ ዊነትን አቅርቦ ወደ ውጤት መድረስ፥ ተግባራዊ ምሳሌና ተጨባጭ እውነቶ ችን ማቅረብና የአካባቢ ሁኔታዎችን ለማስረጃነት መጠቀም ናቸው። ሌላው የማስተማሪያ ዘዴ ደግሞ ለሰዎች በመራራት ፍላጎታቸውን ማርካት ሲሆኑ ከእነዚህም መካከል ችግረኞችን መርዳት፥ ማበረታታት፥ ወዳጅነትን ማሳየት የመሳሰሉት ናቸው። እንዲሁም ቅጣት፥ ተግሣጽ፥ ማሳፈር፥ መውቀስና ተስፋ መስጠት ይገኙበታል። በበለጠ እርሱ ይጠቀም በት የነበረው የማስተማር መንገድ ግን የራሱን አርአያነት ማሳየት ነበር፤ ማለት እርሱ ለሰዎች አርአያ ይሆን ነበር። የሚናገረውን ራሱ ያደርገው ነበር። ሰዎች እንዲፈጽሙት የሚያዛቸውን ነገር ራሱ ያደርገው ነበር። ሕይወቱ በሙላ ለሰዎች ከፍተኛ ምሳሌ ነበር።



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ማጠቡ ለእነርሱ ተግባራዊ ትምህርት ነበር። ይህንንም ያደረገው የትሕትናን ትምህርት ለደቀ መዛሙርቱ ለማስተማር ነው። በዚያን ጊዜ በደቀ መዛሙርቱ መካከል እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ በማለት ፉክክር ስለ ተነሣ እንደዚህ ያለውን የትዕቢት አስተሳሰብ ከመካከላቸው ለማስወገድ ራሱን ዝቅ አድርጎ የእነርሱን እግር አጠበ። የትልቅነት ምልክትም ትዕቢት ሳይሆን ትሕትና መሆኑን በቃልም፥ በተግባርም አሳያቸው።

በዚህም ዐይነት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎች ሁሉ ከትዕቢት ርቀው በትሕትና መንገድ ይጓዙ ዘንድ ያስጠነቅቃቸው ነበር። እርሱም ለትሕትና ከፍተኛ ምሳሌ በመሆን ይመራቸው ነበር። በትሕትናውም ሰዎች የእርሱን አርአያነት ይከተሉ ዘንድ እንዲህ ሲል አዝዞአል:- «ከእኔ ተማሩ፤ እኔ የዋህና ትሑት ነኝ፤ ለነፍሳችሁም ዕረፍትን ታገኛላችሁ» (ማቴ:ም:11 ቍ:29)። እንዲሁም በሌላ ጊዜ «የሰው ልጅ ለማገልገልና ብዙዎችን ለማዳን፥ ሕይወቱን አሳልፎ ለመስጠት መጣ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም» ብሎአል።

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢረ ቍርባንን በመሠረተ ጊዜ ምን እንዳለ:- የሚያመለክተውን ጥቅስ ቀጥለን እንመልከት:-

«ሲበሉም ኢየሱስ ኅብስት አንሥቶ የምስጋና ጸሎት አደረገ፤ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ‹እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው› ብሎ ሰጣቸው፤ ጽዋውንም አንሥቶ የምስጋና ጸሎት ካደረገ በኋላ እንዲህ ሲል ሰጣቸው:- ‹ይህ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ ሚፈስስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው»› (ማቴ:26 ቍ:26–28)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ላመኑ ለክርስቲያኖች ቤዛ ስለሆነላቸው እርሱ የፋሲካቸው መሥዋዕት ሆኖአል። ይህም እራት ለእነርሱ እስራኤልን ከማዳን የበለጠ አዳኝነት ነው። የብሉይ ኪዳኑ መሥዋዕቶች ሁሉ የክርስቶስን ሞት የሚያመለክቱ ነበሩ። የምሥጢረ ቍርባን ሥርዓት በተመሠረተ ጊዜ እነዚያ የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶችና ሥርዓቶቻቸው አከተ መዋል። አስቀድሞ «እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ» ብሎ ባወጀው መሠረት ጌታችን ሥጋውን በኅብስት አማካይነት አቀብሎአቸዋል። ሥጋዊ ሕይወት ቆሞ ሊሄድ የሚች ለው እንጀራን በመመገብ ሲሆን መንፈሳዊ ሕይወትም የሚኖረው የጌታችንን ሥጋ በመቀበል ነው። ኅብስቱ የእግዚአብሔር ምሥጢር ሲያርፍበት ወደ እውነተኛው የጌታችን ሥጋነት ይለወጣል (ማቴ: ም:4 ቍ:4፥ ም:6 ቍ:1)። ከዚያም በኋላ ጌታችን ወይኑን ለደቀ መዛሙርቱ አቀረበ። ይህም ወይን በእግዚአብሔር ምሥጢር ወደ እውነተኛው የጌታችን ደም የሚለወጠው ነው። እርሱንም የሚጠጣ የክርስቶስን ሞት በረከት ይታደላል። ይህም ለሐዲስ ኪዳን የክርስቶስ ደም ነው። እርሱም ለብሉይ ኪዳን ከነበረው ከእንስሳት መሥዋዕት ደም ይለያል። (ዘጸ: ም:24 ቍ:8፥ ዕብም:9 ቍ:19–20)።

በጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታ፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባደረገው ጸሎት የተለያዩ ትምህርቶችን በተግባር አሳይቶናል። አንደኛ ከደቀ መዛሙርቱ በመለየት ለብቻው ራቅ ብሎ ከሄደ በኋላ መጸለዩ እኛም የግል ጸሎት በምንጸል ይበት ጊዜ በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ብቻ ምሥጢራዊ ግንኙነት ማድረግ የሚገባን መሆኑን ያመለክተናል።

ሁለተኛ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚቻል ቢሆን ይህን የመከራ ጽዋ አሳልፍልኝ፤ ሆኖም ያንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ እንደ እኔ ፈቃድ አይደለም ብሎአል። ይህ አነጋገር የአብንና የወልድን ፈቃድ የተለያዩ ያስመስላቸው ይሆናል። ጌታችንም ሕማማቱንና ሞቱን የሚቀበለው ያለ ፍላጎቱ በግዴታ እንደሆነ ያስመስል ይሆናል። ይህ ግን አለመሆኑን በሚከተሉት ማስረጃዎች እንመልከት:-

«በዚህ ጊዜ ከኢየሱስ ጋር ከነበሩት አንዱ ሰይፉን መዘዘና የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ መትቶ ጆሮውን ቈረጠው፤ ኢየሱስ ግን እንዲህ አለ:- ‹ሰይፍን ሚያነሡ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ ሰገባው መልሰህ ክተተው። ለመሆኑ እኔ አባቴን ብለምን እርሱ በብዙ ሺህ የሚቈጠር የመላእክት ሠራዊት ሊልክልኝ የማይችል ይመስልሃልን? እንዲህማ ቢሆን ኖሮ መከራ መቀበል አለበት የሚለው የመጽሐፍ ቃል እንዴት በተፈጸመ ነበር?» (ማቴ:ም:26 ቍ:51–54)።

«እንደገና መልሼ የምወስዳትን ነፍሴን አሳልፌ ለመስጠት ፈቃደኛ ስለሆንኩ አብ እኔን ይወደኛል። ነፍሴን በፈቃዴ እሰጣለሁ እንጂ ከእኔ የሚወስዳት ማንም የለም፤ ነፍሴን አሳልፌ ለመስጠትና መልሼም ለመውሰድ መብት አለኝ» (ዮሐ:ም:10 ቍ:17–18)።

www.ethiopianorthodox.org

«እኔና አብ አንድ ነን› (ዮሐ:ምº:10 ቊ:30)።
«አባት ሆይ፡ ከዚህች ሰዓት አድነኝ ልበልን? ይህን እንዳልል ግን እኔ የመጣሁት ለዚህች የመከራ ሰዓት ነው» (ዮሐ:ም:12 ቊ:27)
«የአብ የሆነው ሁሉ የእኔ ነው» (ዮሐ:ም:16 ቊ:15)።
ታዲያ እንዲህ ከሆነ ለምን የመሠቃየት ሁናቴ ታየበት? ያልተለያየና ያልተጠፋፋ የመለኮትና የትስብእት ባሕርይ እስካለው ድረስ ሕማም የሚሰማው መሆኑ ሊያስገርመን አይገባም። ለእኛ ቤዛ ለመሆን ሲል ብዙ ሕማም የሚደርስበት ለመሆኑ አስቀድሞ በነቢዩ ኢሳይ ያስ ም.53 ላይ መመልከት ይቻላል።

ሦስተኛ እንደ እኔ ፈቃድ ሳይሆን እንደ አንተ ፈቃድ ቢሆን ይህን የመከራ ጽዋ አሳልፍልኝ ማለቱ ለእኛ ትምህርት ለመስጠት ብሎ እንጂ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ዐላማ ለማስቀረት አይደለም። በዚህ አባባሉ የሚሰጠን ትምህርት እኛ ወደ እግዚአብሔር በምንጸልይበት ጊዜ እነዚያ ምንፈልጋቸው ጉዳዮች በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ወይም የሌላቸው መሆናቸውን ስለማናውቅ ፈቃዱን ለእግዚአብሔር መተው አስፈላጊ መሆኑን ለማስረዳት ነው። በዚህም ምክንያት ነው ጌታ ባስተማረው ጸሎት ውስጥ ፈቃድህ ይሁን የሚለው ሐረግ የሚገ ኘው። ሦስት ጊዜ ተመላልሶ ያንኑ ጸሎት መደጋገሙ ጸሎታችንን ሳንታክት መጸለይ እንደሚ ገባን ለማመልከት ነው። ሳንታክትም ከጸለይን አንድ ዐይነት መልስ ማግኘታችን እንደማይቀር ሲያመለክት የሚያበረታታው መልአክ መጥቶለታል። በዚህም መሠረት አንድ ፈተና በሚያጋ ጥመን ጊዜ ተግተን ከጸለይን አንድም ከፈተናው ችግር ያድነናል፤ ያለዚያም ፈተናውን የመቋ ቋም ኀይል ይሰጠናል።

የሰው ልጅ በደል በጣም ከፍተኛ ስለነበረና ጌታችንም ያን ለማካካስ ማለት ቤዛ ለመሆን ስለመጣ እኛን ከዚያ ችግር ለማውጣት እርሱ በትስብእቱ ያን ሁሉ መከራ ሲቀበል በጣም ሕመም የተሰማው መሆኑ ምንም የማያከራክር እውነት ነው። ይህን እውነት የማናምን ከሆነ ግን ለጌታችን ሕማም ግምት አልሰጠነውም ማለት ነው።

በአስቆሮታዊው ይሁዳ መሪነት ወታደሮችና የካህናት አለቆች አገልጋዮች ጌታችንን እንደ እስረኛ አድርገው በያዙት ጊዜ እንዳያመልጣቸው አጥብቀው ያዙት። እነርሱ አልገባቸው ወይም ጳላኤ ሰናይ ያዩትንና የሰሙትን እንዳያ ስተውሉ አድርጎአቸው ነው እንጂ እርሱ ከእነርሱ እጅ ለማምለጥ ቢፈልግ የዓለም ወታደር እንኳ ተሰብስቦ ቢመጣ ሊገታው ባልቻለም ነበር። በመካ በቤተ መቅደስ ሲያስተምር ሳለ ስንት ጊዜ ነው ሊይዙት ወይም ሊወግሩት ሲፈልጉ ከላቸው ዐልፎ የሄደው? እንዲያውም እዚሁ በቅርቡ ኢየሱስ እኔ ነኝ ብሎ መለኮታዊ መልስ በሰጣቸው ጊዜ በግንባራቸው ተደፍተው መውደቃቸው እንዴት የእርሱን ኀያልነት ሳያስገ ነዝባቸው ቀረ? ራሱን አሳልፎ መስጠቱ ግን ቀደም ተብሎ በተሰጠው መለኮታዊ ውሳኔ ምክንያት ነው። እጁን በመስጠቱ ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢት መጽሐፉ ምዕራፍ 53 ላይ በዝርዝር የገለጠው ትንቢት ተግባራዊ ሆነ። የጌታችንም መንገድ ሰላማዊ እንጂ የኀይል መንገድ ያልነበረ መሆኑን በዚሁ ልንገነዘብ እንችላን። እርሱ የፈቀደውን ማድረግ ሲችል መያዙንና ሕማማትን መቀበሉን አልተቃወመም። እርሱ ግን ለአሳሪዎቹ በጥሞና ያስረዳቸው ዘወትር ከእነርሱ ጋር በቤተ መቅደስ በነበረበት ጊዜ ያልያዙት ሲሆን አሁን በጨለማና ከደቀ መዛሙርት ጋር ብቻውን በሆነበት ጊዜ እንደ ሌባና እንደነፍስ ገዳይ ዱላና ሰይፍ ይዘው መምጣታቸው ያስገረመው መሆኑን ነው። በዚህም ድርጊቱ ለእኛ የሚሰጠን ትምህርት ቃለ እግዚአብሔርን ለማዳረስ ወይም ወደየሰዉ ለማስተላለፍ ምድራዊ ኀይል ሊገታን የማይገባ ማለት ምድራዊ ኀይልን በመፍራት ቃለ እግዚአብሔርን ከማስተላለፍ ወደ ኋላ ማለት የማይገባን መሆኑን ነው። ይሁን እንጂ ያን ለማድረግ ኀይል የማያስፈልግ መሆኑን ለማስረዳት ሐዋርያውን ቅዱስ ጴጥሮስን ሰይፍህን መልስህ ወደ ሰገባው ክተት ብሎታል።

ጌታችንን የያዙትም ሰዎች የአይሁድ ሽማግሌዎችና የሕግ መምህራን ተሰብስበው ወደሚገኙበት ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ ቤት ወሰዱት። እዚያ ተሰብሰበው የነበሩትም ሁሉ ጌታችንን ይዘው እንዲመጡ ተከታዮቻቸውን የላኩ ናቸው። እነርሱ ጌታችንን ለመግደል ዐቅደው የሐሰት ምስክር በመፈለግ ላይ ነበሩ። በተንኰልና በቅናት ሊገድሉት የፈለጉ ስለሆነ ግድያውን ሕጋዊ ለማስመሰል የሐሰት ምስክር ያስፈልጋቸው ነበር፤ የእነርሱ ጉባኤ ለሞት የሚያበቁ ናቸው ብሎ ከሚወስናቸው ወንጀሎች መካከል እግዚአብሔርን መዳፈር (ጽርፈት) እና ከሃይማኖት ተቃራኒ ትምህርትን ማስተማር ናቸው። በዚህም ምክንያት በናዝሬቱ ኢየሱስ ላይ የምመሰክርበት ነገር አለኝ የሚል ሰው ሁሉ ወደ

www.ethiopianorthodox.org



ገኙት የተለያዩ ክፍሎች ጥሪ አስተላልፈው ነበር። ብዙ የሐሰት ምስክሮች ቢቀርቡም እንኳ ምስክርነታቸው የአይሁድን ፍላጎት የሚያረካ ሆኖ አልተገኘም። በመጨረሻ ግን ሁለት የሐሰት ምስክሮች ቀርበው ይህ ሰው ቤተ መቅደስን አፍርሼ በሦስት ቀን እሠራዋለሁ ሲል ሰምተነዋል ብለው መሰከሩ። እነርሱ እንዳሉት አይደለም እንጂ ከዚህ አባባል ጋር የሚቃረብ ነገር ብሎ ነበር። አይሁድ፥ መሲሕ መሆኑን ለማስረዳት ምን ተአምር ታደርግልናለህ ባሉት ጊዜ ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱትና እኔ በሦስት ቀን እሠራዋለሁ ብሎአቸዋል። እነርሱ ግን ቤተ መቅደሱን አፈርሰዋለሁ ብሎአል ነው ያሉት። በዚህም ቤተ መቅደስን የማፍረስ ፍላጎት እንዳለው አድርገው አቀረቡ። እርሱ ግን የተናገረው ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ነበር። እንደተባለውም እነርሱ በገደሉት በሦስተኛው ቀን ከሞት ተነሥቶአል። ይህም እርሱ በሰጠው ምልክት መሠረት መሲሕነቱን አረጋግጦአል ማለት ነው (ዮሐ:ምº:2 ቊ:19)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከእነዚያ ፍርዱን በእርሱ ላይ ከሚያስተላልፉ ሰዎች ጋር ጥያቄና መልስ መሰጣጠት ያልፈለገው እነርሱ ክፉዎች፥ ነፍሰ ገዳዮች፡ ግፈኞች፡ ውሸታሞች፡ ኀሊና የሌላቸው፥ ርኅራኄ በልባቸው የሌለ መሆኑን ስለሚያወቅ ነው። እርሱም ጸጥ አለ። በዚህም ሁናቴ ቀጥሎ የተገለጠው የነቢዩ የኢሳይያስ ትንቢት ተፈጻሚ ሆነ።

«እርሱ ብዙ ግፍ ሲደርስበት መከራን ታግሦ ተቀበለ እንጂ አንድ ቃል እንኳ አልተናገ ረም። እርሱ ለመታረድ እንደሚወሰድ ጠቦትና እንደሚሸለትም በግ ዝም አለ፤ አንድም ቃል አልተናገረም» (ኢሳ:ም:53 ቊ:7)።

ይህ ዝምታው ግን በእርሱ ላይ ሊፈርዱበት የተሰበሰቡትን ሰዎች በጣም አበሳጨ። የካህናት አለቃው ጭንቅ ስላለው አንተ መሲሕ መሆንህንና አለመሆንህን ትገልጥልን ዘንድ አምልሃለሁ አለው። ጌታችንም እርሱ መሲሕ መሆኑን በገለጠላቸው ጊዜ የእርሱን ቃል ለክሳቸው ምክንያት አደረጉት። ከዚያም እርሱን ማዋረድና በእርሱ ላይ መሳለቅ ቀጠሉ። በዚህም:- «ጀርባዬን ለገራ ፊዎች፥ ጉንጬን ለጠጕር ነጪዎች ሰጠሁ፤ ፊቴንም ከውርደትና ከትፋት አልመለስሁም» የሚለው የነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢት ተፈጸመ (ኢሳ:ምº:50ቊ:6)።

ሽማግሌዎችና ሊቃነ ካህናት አዳኛችንን እንደምን አድርገው ሊገድሉት እንደሚችሉ ተማከሩ። ይህንንም ያደረጉት እነርሱ ራሳቸው የሞት ፍርድ የማሳለፍ መብት ስለሌላቸው ነው። ስለዚህ የሞት ፍርድ በተፈረደባቸው ወንጀለኞች ላይ በሚደረገው ዐይነት እጅን የኋሊት አስረው ለአገረ ገዢው ለጳንጤናዊው ለጲላጦስ አስረከቡት። በዚህም ጌታችን ቀደም ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ:- ሊቃነ ካህናቱ በአረማውያን እጅ አሳልፈው እንደሚሰጡት መላልሶ የነገራቸው ትንቢት ተፈጸመ።

ጌታችን የሞት ፍርድ እንደተፈረደበት ባየ ጊዜ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ ተጸጸተና የተቀበለውን ገንዘብ ይዞ ወደ ሊቃነ ካህናቱ በመሄድ ንጹሕ ሰው አሳልፎ በመስጠቱ መጸጸቱን ገለጠላቸው። የጌታችንን ከወንጀል ነጻ መሆን ለመመስከር አሳልፎ የሰጠው ከዳተኛ የመጀመ ሪያው ሰው ሆነ። ሰይጣን ሰዎችን በኃጢአት እንዲወድቁ ካደረጋቸው በኋላ በውድቀታቸው ይሳለቅባቸዋል። በዚህም ዐይነት በአይሁድ ዐድሮ፥ ይሁዳን ያሳተው ሰይጣን በጥፋቱ በተጨነቀ ጊዜ የተሰጠው መልስ እኛ ምንቸገረን፤ የራስህ ጉዳይ ነው ተብሎ ነው። ይህም መልስ የበለጠ ተስፋ አስቈርጦት ራሱን ለመግደል አደረሰው።

ጲላጦስ በፍርድ ወንበር ላይ ተቀምጦ ሳለ ሚስቱ በዚያ በንጹሕ ሰው ላይ ምንም ነገር እንዳታደርግ ብላ ላከችበት። ይህች አረማዊት ሴት ስለክርስቶስ ንጽሕና ለመመስከር ሁለተኛ ሰው ሆነች።

አይሁድ ምንም እንኳ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ በእነርሱ ፊት ቀርቦ ስለ ጌታችን ንጹሕነት ቢመሰክርና ጲላጦስም መርምሮ ምንም ለሞት ሚያደርስ ኃጢአት እንዳላገኘበት ቢነግራቸው እነርሱ የሰጡት መልስ:- «ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይድረስ» ብለው ነው። ይህንንም ኀላፊነት በፈቃዳቸው ስለ ተቀበሉ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ቃል ኪዳን አጡ። ይህ ፍርድ በራሳቸው ላይ እንዲመጣ ከወሰኑበት ከአርባ ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ በሮማውያን ወታደሮች አማካይነት የአይሁድ ሕዝብ በሚያስቅቅ ሁኔታ ተፈጀ፤ ኢየሩሳሌምና ቤተ መቅደ ስዋ ፈራረሱ፤ የተረፈውም የአይሁድ ሕዝብ በዓለም በመላ ተበታተነ።

ጌታችን የሞት ፍርድ ፈርደውበት ሊሰቀል በሚሄድበት ጊዜ መስቀሉን አሸክመውት ነበር። ነገር ግን ብዙ አሠቃይተውት ስለነበረ ሳይሰቀል ይሞታል ብለው ስለሰጉ ስምዖን የተባለውን የቀሬና ሰው መስቀሉን እንዲሸከም አስገደዱት። ሊሰቀልበት ወደ ተወሰነው ጎልጎታ ወደ

ተባለው ስፍራ በደረሱ ጊዜ ከሐሞት ጋር የተቀላቀለ ወይን ጠጅ እንዲጠጣ ለጌታችን አቀረቡለት፤ እርሱ ግን ቀመስ አድርጎ ሊጠጣው አልፈለገም። በተጠማም ጊዜ የበለጠ ተጠምቶ እንዲሠቃይ ለማድረግ ሆምጣጤ አመጡለት። በዚህም ጊዜ:- «በጠማኝ ጊዜ በውሃ ፈንታ ሆምጣጣ ሰጡኝ» የተባለው የትንቢት ቃል ተፈጸመ (መዝ:69፥ 21)።

ጌታችን ተሰቅሎ በነበረበት ቦታ ያልፉ የነበሩት ሰዎች ራሱን ማዳን አልቻለም በማለት ራሳቸውን እየነቀነቁ ያፌዙበት ነበር። ጌታችን ቢፈልግ ኖሮ ከመስቀሉ ላይ ለመውረድም ሆነ ሕማምና ሞት እንዳይደርስበት ለማድረግ ምንም ባልተሳነውም ነበር። እርሱ ግን ወደዚህ ዓለም የመጣበት የቤዛነትና የአዳኝነት ጉዳይ በዚያ ወቅት መፈጸም ነበረበት። ይህም ዘለዓለማዊ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነበር።

ብዙ ከተሳለቁበትና ሕማማትን ካደረሱበት በኋላ በሰቀሉት ጊዜ የበለጠ ዝቀተኛ ግምት በመስጠት ከሁለት ወንበዴዎች ጋር በአንድነት ሰቀሉት። አንዱን ወንበዴ በቀኙ ሌላውን ወንበዴ በግራው ሰቀሉ። ይህም ሁናቴ «ከዐመፀኞች ጋር ተቈጠረ» ተብሎ የተነገረውን ትንቢት ተፈጻሚነት ያመለክታል (ኢሳ: ም:53 ቍ:12)። ከሁለቱ ወንበዴዎች አንዱ በጌታችን ላይ እንደዚህ ብሎ የድፍረት ንግግር ተናገረ:-አንተ መሲሕ ከሆንክ ራስህን አድን፤ እኛንም አድነን» ሲል ተሳለቀበት። ሌላው ወንበዴ ግን:- «አንተ በእንደዚህ ያለ ፍርድ ላይ ሆነህ እግዚአብሔርን አትፈራምን? እኛስ ተገቢ ቅጣታችንን በመቀበል ላይ ነን፤ ይህ ግን ምንም ሳይበድል የተቀጣ ነው» ካለ በኋላ ወደ ጌታችን መለስ ብሎ:-» በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስታውሰኝ› አለው። ጌታችንም በዚያቹ ሌሊት ከእርሱ ጋር በገነት እንደሚሆን ተስፋ ሰጠው።

ወንበዴውም ለጓደኛው ያን መልስ እንደሰጠው እግዚአብሔር ልቡን ለእምነት ከፈተለትና ጌታችን ከላይ የተናገረውን መልስ ሰጠው። ያ ወንበዴ በሕይወቱ መጨረሻ ላይ አማኝ ሆኖ በመገኘቱ ሊድን ችሎአል። በዚህም ዐይነት ማንም ሰው በሕይወቱ መጨረሻ ላይ እንኳ አምኖ ንስሐ ከገባ ይድናል ማለት ነው።

የቤተ ክርስቲያን ትውፊት እንደሚገልጥልን በመስቀል ላይ ባለው በክርስቶስ አምኖ ንስሓ የገባው ወንበዴ በክርስቶስ አምላክነት ያመነ መሆኑ የሚታወቀው በመንግሥትህ ስትመጣ በማለቱ ነው። ጌታችን ለፍርድ ወደዚህ ዓለም የሚመጣ መሆኑን አምኖአል ማለት ነው። እርሱም በቀኝ በኩል የተሰቀለው ወንበዴ ነው። ያም ቀኝ ጐን በወታደር ጦር ተወግቶ ደምና ውሃ የፈሰሰበት ነው። በቤተ ክርስቲያን የትውፊት መጻሕፍት ተመዝግቦ እንደሚገኘው ይህ በቀኝ በኩል የተሰቀለው ወንበዴ ስም ዲማስ ነበር፤ ሌሎች ጥጦስ ይሉታል። ከጌታችንም ጋር መሞቱ እንደ ጥምቀት ይቈጠርለታል። ቅዱስ መጽሐፍ እንዳለው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድ ለመሆን የተጠመቀ ሁሉ የሞቱም ተካፋይ ነው፤ በጥምቀት ከእርሱ ጋር በተቀበረ ጊዜ የሞቱ ተካፋ ሆኖአል (ሮሜ:ም:6 ቍ:3–4)። ይህም የደም ወይም የሰማዕትነት ጥምቀት ነው። ይህ ዐይነቱ ጥምቀት አንደኛ ደረጃ ጥምቀት ነው: ይህም የሆነበት ምክንያት የጥምቀት መሠረቱ ከክርስቶስ ጋር መሞት፥ ከእርሱ ጋር መቀበር፥ በእርሱና ከእርሱ ጋር መነሣት ነው። ስለዚህም ወደ ቈላስይስ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት እንዲህ ተብሎአል:- «በተጠመቃችሁ ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ተቀበራችሁ፤ ከእርሱም ጋር ከሞት ተነሥታችኋል» (ቈላ:ም:2 ቍ:12)።

ጌታችን በቀኙ በኩል ለነበረው ወንበዴ «ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ» ሲለው በአብርሃምና በድኻው አልዓዛር ምሳሌ ካልሆነ በቀር በገነት የመኖር ጉዳይ በኃጢአታቸው ምክንያት አዳምና ሔዋን ከተባረሩበት ጊዜ ጀምሮ ከብዙ ሺህ ዓመቶች በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ መነገሩ ነው። ይህም ማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውን መንገድ ከፍቶአል ማለት ነው። ይህም ማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስቅለቱና በሞቱ የገነትን በር ከፍቶአል ማለት ነው። መስቀሉም የሕይወት በር መክፈቻ ነው። ለክርስቲያኖችም የሁልጊዜ ምልክታቸው ነው። የገነት መግቢያ በርም በተከፈተ ጊዜ በሲኦል ታስረው የነበሩት ሁሉ ወደዚያ ገቡ። ጌታችንም አዳምንና ልጆቹን ሁሉ ወደ ገነት መለሳቸው።ይህን በተመለከተ ቃለ እግዚአብሔር ምን እንደሚል እንመልከት:-

«ክርስቶስ ራሱ ወደ እግዚአብሔር ያቀርበን ዘንድ እራሱ ጻድቅ ሆኖ ሳለ፥ ጽድቅ ለሌለን ለእኛ በኃጢአታችን ምክንያት በማያዳግም ሁኔታ አንድ ጊዜ መከራን በመቀበል ሞቶአል፤



እርሱ በሥጋ ሞተ፤ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፤ በእስር ላይ ወደሚገኙት መናፍስት በመንፈስ ሄደ፤ እዚያ ለነበሩትም ፍርድን ዐወጀላቸው» (1ኛ:ጴጥ:ም:3 ቍ:18–19)።

ወደ ታች ወርዶ ምርኮን ማርኮ እንደመጣም በኤፌሶን መልእክት ም:4 ቍ:8–9 ተገልጾአል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ ሕማሙ በበረታ ጊዜ «አምላኬ፥ አምላኬ ለምን ተውከኝ» ብሎ ከፍተኛ ድምፅ ማሰማቱ ያልተጠፋፋ፥ ያልተለወጠ፥ ያልተዋዋጠና ያልተቀላቀለ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው በመሆኑ ነው። እራሱም የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ አንድ ባሕርይ እንጂ ሁለት ባሕርይ አለው የምንል አይደለም። ፍጹም ሰውም እንደመ ሆኑ በሰውነቱ ሕማም ተሰምቶት አምላኬ፥ አምላኬ ብሎአል። ሕማም አልተሰማውም ወይም ሊሰማው አይችልም የምንል ከሆነ አንድም እንደ አውጣኬ እምነት መለኮት ትሰብእትን ውጦታል ማለታችን ነው፤ ወይም እንደ እነ ማኒ በምትሐት መልክ ስለሳለፈው ክርስቶስ ሕማም አልተሰማውም ማለት ይሆንብናል። ለምን ተውከኝ ማለቱ መለኮቱ ከትስብእቱ ተለየ ማለት አይደለም። ነገር ገን ጌታችን በትስብእቱ ሕማማትን መቀበሉን የሚያመለክት ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እንዳለው ጌታችን በሥጋው ሞተ፤ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ። ሳይቀላቀል ከትስብእት ጋር የተዋሐደው መለኮት የትስብእትን ሕማም አለማቃለሉን ያመለክታል። ይሁን እንጂ መለኮት ምንጊዜም ቢሆን ከትስብእት አልተለየም። ተዋሕዶአል የምንለውም በዚህ ምክንያት ነው።

ጌታ በሞተ ጊዜ ከተፈጥሮ ጠባይ ወጪ የሆኑ ሁናቴዎች ተከሠቱ። ይህም የሆነው ይህ የሞተው ተራ ሰው አለመሆኑን ለማመልከት ነው። እዚህ ላይ አምላክ በትስብእቱ መሞቱን እንረዳለን።

የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ለሁለት ተቀደደ። ይህም መጋረጃ የመቅደሱንና የቅድስተ ቅዱሳኑን ክፍል የሚለይ ነበር። እርሱም የተቀደደው የክርስቶስ ነፍስ ከሥጋው ስትለይ ነው። ቤተ መቅደሱ በክርስቶስ ሥጋ የሚመሰል መሆኑን የክርስቶስ ነፍስ ከሥጋው ስትለይ የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ለሁለት ተቀደደ። መጋረጃው በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ የነበሩትን የእግዚአብሔርን ምሥጢራት ከተራው ሕዝብ የሚሸፍን ነበር። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት መጋረጃው በተቀደደ ጊዜ እነዚህ ምሥጢራት ለሕዝቡ ሁሉ ግልጥ ሆነው ምሥጢ ርነታቸው ቀርቶአል ለማለት ነው።

መሬት ተንቀጠቀጠ፤ አለቶች ተሰነጠቁ፤ ይህም የሆነው ፍጡራን በፈጣሪአቸው ሞት ሐዘናቸውን ለመግለጥና እርሱ ምንም በደል የሌለበት ሆኖ ሳለ የግፍ ጽዋ እንዲጠጣ ባደረጉት ክፉዎች ሰዎች ላይ ተቃውሞአቸውን ለመግለጥ ነው።

መቃብሮች ተከፍተው ሞተው የነበሩ ብዙ ቅዱሳን ሰዎች ከሞት ተነሡ። ከመቃብርም ወጥተው ወደ ቅድስት ከተማ ወደ ኢየሩሳሌም ገቡ፤ በዚያም ለብዙ ሰዎች ታዩ።

ጌታችንን ይጠብቁ የነበሩት ሮማዊው መቶ አለቃና ወታደሮቹ ይህን ሁሉ ነገር ባዩ ጊዜ ፈርተው በእውነት ይህ ሰው የእግዚአበሔር ልጅ ነበር አሉ። ምንም እንኳ ባለጌዎች፥ ጨካኞች፥ ኩራተኞች ትዕቢተኞች ቢሆኑና በእግዚአብሔርና በነቢያቱ የማያምኑ፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን የማያውቁና በዚያን ጊዜ በፊታቸውም እየተፈጸመ ያለውን የነቢያት ቃል የማያውቁ ቢሆኑ እነርሱ እያዩት በተከሠተው ሁናቴ ምክንያት ይህ እነርሱ ይሳለቁበትና ያፌዙበት የነበረውና እርሱን ማሠቃየት ያስደስታቸው የነበረው ሰማይንና ምድርን የፈጠረና የፍጥረት ሁሉ ጌታ መሆኑን አመኑ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ የአምላክ ልጅነቱን በአንደበቱ የገለጠላቸው ደቀ መዛሙርቱ ግን ጥለውት ሸሽተዋል። ሊቃነ ካህናትም ቅዱሳት መሳሕፍትን ያነበቡና ስለክር ስቶስም የተነገረውን ትንቢት መርምረው ማወቅ ሲገባቸው የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ባላቸው ጊዜ በበለጠ ጠላት ሆነው እንዲሰቀል ያስደረጉት እነርሱ ናቸው። በተለየም በመስቀል ላይ ተሰጥቅሎ ባዩት ጊዜ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም የሚለውን ሐሳባቸውን አጠናከሩ። ኢ. አማንያን የነበሩት ሐሳባቸውን አጠናከሩ። ኢ. አማንያን የነበሩት ወታደሮች ግን በጌታችን ሞት ጊዜ በቤተ መቅደሱ መጋረጃ መቀደድ፥ በምድር መንቀጥቀጥ፥ በአለቶች መሰንጠቅ፥ በሙታን መነሣትና ከመቃብራቸው የመውጣትን ተአምራት ባዩ ጊዜ በጌታችን አመኑ። ይህም ብቻ ሳይሆን ከጌታችን በስተቀኝ ተሰቅሎ የነበረው ወንበዴ የጌታችንን ማንነት ዐውቆ:- ጌታ ሆይ፥ በጌትነትህ በምትመጣበት ጊዜ አስታ ውሰኝ ብሎታል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ በተቀበረ ጊዜ ቀደም ብሎ ከሞትሁ በኋላ በሦስተኛ ቀኔ እነሣለሁ ማለቱን ስላስታወሱና እርሱ እንዳለውም ከሦስት ቀኖች በኋላ ቢነሣ ስለሚያሳ

www.ethiopianorthodox.org

ፍራቸውና ወንጀላቸውም ስላሰጋቸው አንድ የሐሰት ወሬ ለማመቻቸት ብለው ወደ ጲላጦስ
ሄዱ። እዚያም ለጲላጦስ ጌታ ሆይ፥ ያ አሳሳች ገና በሕይወቱ ሳለ ከሦስት ቀን በኋላ ከሞት
እነሣለሁ ያለው ትዝ አለን። ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ ሄደው እንዳይሰርቁትና ለሕዝቡ እነሆ፥
ከሞት ተነሥቶአል እንዳይሉ መቃብሩ እስከ ሦስት ቀን ድረስ እንዲጠበቅ እዘዝ፤ አለበለዚያ
የመጨረሻው ማሳሳት ከመጀመሪያው ይልቅ የባሰ ይሆናል አሉት። ይህ አስመሳይ ስጋታቸው
ሐሰተኛነቱ የሚጋለጠው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው።

የጌታችን ደቀ መዛሙርት በመምህራቸው ላይ አደጋ ሲደርስበት በሚያዩበት ጊዜ ጥለውት
የሚሸሹ ደካሞች እንጂ የሮማን ወታደሮችና አይሁድን ተዳፍረው የጌታችንን አስከሬን
ለመስረቅ የሚመጡ ሰዎች አለመሆናቸውን አይሁድ ደኅና አድርገው ያውቁ ነበር።
መምህራቸው የሰጣቸው ተስፋ ሰማያዊ ክብር እንጂ ምድራዊ ክብር አልነበረም። ይኸውም
እርሱ ከሞት ከተነሣ በኋላ የሚሆን ነው። እርሱ ከሞት የማይነሣ ከሆነ አስከሬኑን ምን ሊያደ
ርጉበት ነው የሚሰርቁት? በተአምር እንኳ ያን አስከሬን ሰርቀውት ቢሆን ምን ይጠቅማቸዋል?
ከሞት ያልተነሣውንስ በውሸት ተነሥቶአል ብለው ቢያወሩ ምን ጥቅም አለው? እነርሱም
ቢሆኑ ያለ መምህራቸው እርዳታ ሰማያዊም ሆነ ምድራዊ ዓላማ በሥራ ላይ ሊያውሉ
አይችሉም።

በእነዚህም ምክንያቶች ደቀ መዛሙርቱ የጌታችንን አስከሬን የመስረቅ ፍላጎትም ሆነ
ችሎታ የሌላቸው መሆናቸውን የአይሁድ ባለ ሥልጣኖች ያውቃሉ፤ እያወቁ ግን ያስመስላሉ።
የቤተ ሳይዳው ኩሬ ውሃ ሲንቀሳቀስ በመጀመሪያ የገባ ሰው መዳኑ በክርስቶስ ለማመን
የሚሽቀዳደም ሰው እርሱ በሚመጣበት ጊዜ የድኅነት ድልን የሚጐናጸፍ መሆኑን ያመለክታል።
ከመጀመሪያው ሰው በኋላ ወደ ኩሬው የሚገቡ ሰዎች ከበሽታቸው የማይፈወሱ መሆናቸው
ክርስቶስ መጥቶ እስኪፈውሳቸው ድረስ እግዚአብሔር የሰዎችን ትዕግሥት የሚፈትን መሆኑን
ያመለክታል።

ጌታችን ሠላሳ ስምንት ዓመት ሙሉ ታሞ የነበረውን ሰው መዳን ትፈልጋለህን? ብሎ
መጠየቁ ያለ ምክንያት አልነበረም። ያ ሰው ወደዚያ መጥቶ ያን ያኽል ዘመን መጠበቁ ለመዳን
ፈልጎ መሆኑን የማያውቅ አይደለም። ነገር ግን የራራለትና ያሰበለት መሆኑን እንዲገነዘብ
ለማድረግ፥ እንዲሁም ለሚደረገው ተአምር ትኩረት እንዲሰጥ ለማድረግ ያን ጥያቄ ጠየቀ።
በሌላ በኩል ደግሞ ለሰው ልጆች የተሰጠውን ነጻ ፈቃድ ለማክበር ፍላጎቱን ጠየቀው። የሰው
ልጆች ለደግም ሆነ ለክፉ ነገሮች የፍላጎት ነጻነት አላቸው። የእግዚአብሔርም በረከቶችና
ስጦታዎች ያለ ሰው ፍላጎት አይሰጡም። ይህም አባባል ከኃጢአትና ከሕመም መፈወስንም
ያጠቃልላል። የጌታችን ጥያቄ ምናልባት ወደ ሰውዬው ውስጣዊ ሁኔታ የሚያተኩር ይሆን
ይሆናል። ጥያቄው ሰውዬው በውነት ለመዳን ይፈልጋልን? ለሕመሙ ምክንያት ከሆነው ኃጢ
አትስ ይጠበቃልን? ይህም ስለ መፈወሱ የግድ መከፈል ያለበት ዋጋ ነው። ጌታችንም ይህን
ሰው ከፈወሰው በኋላ በቤተ መቅደስ አግኝቶት እነሆ፥ አሁን ድነሃል፤ ከዚህ የባሰ ነገር
እንዳይደርስብህ ደግመህ ኃጢአት አትሥራ ማለቱ ያ የነበረበት ሕመም ምክንያት ኃጢአት
መሆኑን የሚያመለክት ነው። ውሃው በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ወደ ኩሬው የሚወስደኝ ሰው የለኝም
ማለቱ ሰው ሁሉ የተወውና ወዳጅ ወይም ረዳት የሚሆን ሰው የሌለው መሆኑን ያመለክታል።
ይህም ሁኔታ ያ ሰው ክፉና ባለጌ ከመሆኑ የተነሣ ሁሉም ሰው ስለጠላው ወዳጅና ዘመድ ሁሉ
የራቀው መሆኑን ያመለክታል። እዚህ ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጸሎት ሳይሆን በሥልጣኑ
በትእዛዝ የፈወሰው መሆኑን እናስተውል። ብዙዎቹን ተአምራት የሚያደርገው እንደ ነቢያት
ወደ እግዚአብሔር በመጸለይ ሳይሆን በትእዛዙ ነበር። ይህም መለኮታዊ ክብሩን የሚያመለክት
ነው።

በቤተ ክርስቲያን ትውፊት መሠረት ይህ ሰው ማለት ያ የተፈወሰው ሰው ወደ ኃጢአቱ
ተመልሶአል። እንዲያውም እመቤታችን ድንግል ማርያም ባረፈች ጊዜ መቃብር ለመከልከል
የሁከት መሪ የነበረው እርሱ እንደሆነ ይነገራል። የአስከሬኑን ሳጥን በያዘ ጊዜ ሊቀ መላእክት
ሸሰይፉ መትቶ እጁን ከሰውነቱ ለይቶታል። በሌላ ትውፊታዊ ትርጓሜ ደግሞ ይኸው ሰው
በዕለተ ዓርብ ጌታችንን በጥፊ መቶታል

በአስቆሮቱ በይሁዳ መሪነት ወታደሮችና የካህናት አለቆች ሎሌዎች ጌታችንን ለመያዝ ወደ
ጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታ በመጡ ጊዜ ምን አጋጠማቸው? ጌታችን እነዚያን ወታደሮች ማንን
ትፈልጋላችሁ? ብሎ ጠየቃቸው እነርሱም የናዝሬቱን ኢየሱስን እንፈልጋለን አሉት። እርሱም
እኔ ነኝ ባላቸው ጊዜ ወደ ኋላቸው አፈግፍገው ወደቁ። ይህም የሚያመለክተው እነርሱ



እንደመሰላቸው ጌታችንን አስገድደው የወሰዱት አለመሆናቸውን ነው። እርሱ ቢፈልግ ኖሮ እንደወደቁ
መላልሶ እንዳደረገው በመካከላቸው ዐልፎ መሄድ በቻለ ነበር። እርሱ ቢፈልግ ኖሮ እንደወደቁ
እንዲቀሩ ባደረጋቸው ነበር። የእግዚአብሔር ዕቅዶች በየተወሰነላቸው ወቅቶች የሚፈጸሙ
ናቸው እንጂ እንደ አጋጣሚ የሚፈጸሙ አይደሉም። በዚህም መሠረት ከዚያ በፊት በነበሩት
ጊዜዎች ሁሉ ሊይዙት ወይም ሊወግሩት ሲፈልጉ በመካከላቸው ዐልፎ በመሄድ ተሰውሮባ
ቸዋል (ዮሐ: ም:8 ቁ:59፥ ም:12 ቁ:36)። ይህም የሆነው ያች የተወሰነችው ሰዓት ስላልደረ
ሰች ነው። እርሱ እንዳለው ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጠው እርሱ ሲፈልግ እንጂ በማንም አስገዳ
ጅነት አይደለም (ዮሐ: ም:10 ቁ:17–18)። ያም የሚሆነው በመለኮታዊ ዕቅድ መሠረት ሰዓቱ
ሲደርስ ነው። አሁን ሰዓቱ ደርሶ እርሱ እጁን በሚሰጥበት ጊዜ በእርሱ ፈቃድ እንጂ በእነርሱ
አስገዳጅነት አለመሆኑን ሲያመለክታቸው በግንባራቸው እንዲደፉ አድርጎአል። ይሁን እንጂ
ጸላኤ ሰናይ ልባቸውን አደንድኖ በወንጀላቸው እንዲቀጥሉ አደረጋቸው እንጂ የእርሱን
ኀያልነት አይተው ሊያስተውሉ አልቻሉም። ከዚያም በኋላ ደቀ መዛሙርቱን እንዲለቋቸው
በማድረግ ሊይዙት የመጡት ሰዎች በእርሱ ላይ የፈለጉትን እንዲያደርጉ እጁን ሰጣቸው።

በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ገና በአጠገቡ ስለነበሩ በቍጣ ተነሣሥተው በሰይፍ እንምታ
ቸውን ብለው ጌታችንን ጠየቁት። እንዲያውም ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ሰይፉን መዞ ማልኮስ
የተባለውን የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ ጆሮ ቈረጠ። ጌታችን ግን ቅዱስ ጴጥሮስን ተቈጥቶ
የተቈረጠውን ጆሮ በመዳሰስ ፈወሰው። በዚህም ድርጊቱ እርሱ ቢፈልግ ኖሮ እነርሱን
የሚበታትንበት መለኮታዊ ኀይል እንዳለው አመለከተ። እርሱ ግን እስከ መስቀልና መሞት
ድረስ ያለውን የሰውን ልጆች በቤዛነት የማዳን መለኮታዊ ዕቅድ ያለምንም ተቃውሞ በሥራ
ላይ እንዲውል ፈቃዱ ስለነበረ የሚደርስበትን ሕማም ሁሉ አልተቃወመም ወይም አልተከ
ላከለም። ለሰው ዘርም የነበረውን ፍቅርና ርኅራኄ ከማሳየት አልተቈጠበም። አስረው ሊገድሉት
በእርሱ ላይ በተሰባሰቡ ጊዜ እንኳ ይቅርታ አድርጎላቸዋል። ምን ዐነት ይቅርታና ምን ዐይነት
ፍቅር ነው? ክፉ ላደረገበትና ለበደለው ሰው ይህን መሰል ይቅርታ ያደረገና ይህን የመሰለ ፍቅር
ያሳየ ከቶ ማነው? በዚህም ድርጊቱ ጌታችን ያዘዘውን ትእዛዝ ሁሉ ራሱ እንደሚፈጽመው
እንመለከታለን። (እኔ ግን እላችኋለሁ፤ በሰማይ ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን
ወደዱ፤ የሚረግሙአችሁን መርቁ፤ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ (ማቴ:ም:5
ቁ:44–45)።

ጌታችን በየጊዜው ይጸልይ እንደነበረ ሁሉ እኛም ሳናስታጕልና ሳንታክት እንድንጸልይ
ለማመልከት የድኻዋን መበለት በመብትዋ ያዘናል: በዚህም መሠረት ሳያስታጕሉና ሳይታክቱ መጸለይ እንደሚገባ
ለማመልከት የድኻዋን መበለት በመብትዋ
ያዘናል: በዚህም መሠረት ሳያስታጕሉና ሳይታክቱ መጸለይ እንደሚገባ ለማመልከት የድኻዋን
ምሳሌ ነገራቸው: በታሪኩም መሠረት ድኻዋ መበለት በመብትዋ ልመናዋን የተቀበለና
መበለትና የዐመፀኛውን ዳኛ ምሳሌ ነገራቸው: በታሪኩም መሠረት ድኻዋ መበለት በመብትዋ
አምና ሳትታክት አዘውትራ ወደ ግፈኛው ዳኛ አቤት አቤት በማለትዋ ልመናዋን የተቀበለና
ከባላጋራዋ ጋር ባላት ክርክር የፈረደላት ከሆነ ፍጹም፥ ቅን ፍርድን ፈራጁ፥ ይቅር ባዩ፥ ቸሩና
ርኅሩኁ አምላክ በእርሱ ተማምነው ለሚለምኑት ምእመናን ከሚበድሉአቸው በደለኞች፥
ከሚጨቍኑአቸው ጨቋኞች፥ መብታቸውን ከሚጋፉባቸው ክፉ ሰዎች፥ ከሚያሳድዱአቸው
አሳዳጆች እጅ ለማዳን እንዴት አይፈርድላቸውም? ብሎ ይጠይቃል።
እግዚአብሔር ጸሎታችንን ሰምቶ

በዚህም አባባሉ እኛ ሳንታክት ዘወትር የጸለይን እንደሆነ እግዚአብሔር ጸሎታችንን ሰምቶ
መልስ እንደሚሰጠን ያረጋግጥልናል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መልካም የበጎች እረኛነቱን በምሳሌ የሚገልጠው ይመጣል
ብለው ነቢያት የተናገሩለት መሲሕ እርሱ ራሱ መሆኑን ለማመልከት ነው። አይሁድ
እንደመሰላቸው እርሱ ሐሳዌ መሲህ አይደለም። እርሱ እውነተኛው መሲሕ የሰውን ዘር ሁሉ
የሚጠብቅ ነው። የሰው ዘርም ለእርሱ በበግ መንጋ የሚመሰልለት ነው። እርሱ እውነተኛ
መልካም እረኛ ባይሆን ስለበጎቹ ብሎ አደገኛ ወደ ሆነው ወደ ሰው ዘር ዓለም በመጣበት
መንገድ ባልመጣም ነበር። በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን ውስጥ ሥጋን
ለበሰ፤ ማለት መለኮት ከትስብእት ጋር ተዋሐደ። የተወለደውም በሰው ዘር አማካይነት ሳይሆን
በመንፈስ ቅዱስ ነው። እርሱም በእግዚአብሔር ልጅነቱም ሆነ በሰው ልጅነቱ የእግዚአብሔር
ፍጹምነት ሁሉ ነበረው። እንደ ሰው ልጅነቱ ሰው ሁሉ ለእግዚአብሔር እንደሚታዘዝ እርሱም
ስለእኛ ለእግዚአብሔር ታዛዥ ነበር። እንደ እግዚአብሔር ልጅነቱ የእግዚአብሔር የፍጹምነት
ጠባይና ባሕርይ ነበረው። እርሱ የመጣው በሰው ዘር አማካይነት ቢሆን ኖሮ የተወረሰውን
ኃጢአት በወረሰ ነበር።



www.ethiopianorthodox.org

ሐሰተኛ መሲሕ ቢሆን ኖሮ ወደ በጎቹ በረት በበሩ ለመግባት ባልደፈረም ነበር። ነገር ግን እንደ ሌባው ሌላ መግቢያ በር በፈለገ ነበር። በዚያ በዋናው በር ሳይሆን በሌላ በር የሚገባ ሊሰርቅ እንጂ ሊጠብቅ የሚገባ አይደለም። በዚህም ምክንያት ጠባቂው የሚገባበት በር ዋናው በር ነው። እርሱም የጽድቅ፥ የእውነት፥ የምሕረትና፥ የፍትሕ በር ነው። ሌቦች በዚያ በር በኩል ለመግባት አይደፍሩም። ሌቦችም የተባሉት ሐሳውያን መሲሖችና ሐሰተኞች ነቢያት ናቸው። እነርሱ የሚገቡበት በር የከዳተኛነት፥ የሐሰተኛነትና የአታላይነት በር ነው። ጌታችንም ከሰዎች መካከል የእርሱ የሆኑትን ያውቃቸዋል።

## ጥያቄዎች

1. ጌታችን ስለ ሕማሙና ስለ ሞቱ ለደቀ መዛሙርቱ አስቀድሞ የነገራቸው ምን ብሎ ነው?
2. በዚህ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ ምን አለ?
3. ጌታችንስ ቅዱስ ጴጥሮስን ምን ብሎ ገሠጸው?
4. ጌታችን የደቀ መዛሙርቱን እግር ባጠበ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ ምን አለ?
5. ጌታችንስ ምን መልስ ሰጠው?
6. ቅዱስ ጴጥሮስ ከዚያ በኋላ ምን ብሎ ሐሳቡን ለወጠ?
7. ከዚያ በኋላስ ጌታችን ምን አለው?
8. ጌታችን የደቀ መዛሙርቱን እግር ካጠበ በኋላ ምን ብሎ ትምህርት ሰጣቸው?
9. ጌታችን የምሥጢረ ቍርባንን ሥርዓት የመሠረተው ለደቀ መዛሙርቱ ምን ብሎ በመናገር ነው?
10. ጌታችን ለመጸለይ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የሄደበት ቦታ ምን ይባላል?
11. እዚያስ ምን ብሎ ጸለየ?
12. ከሚጸልይበት ቦታ ወደ ደቀ መዛሙርቱ የተመላለሰው ስንት ጊዜ ነው?
13. ለደቀ መዛሙርቱ ምን ምክር ሰጣቸው?
14. በዚህ ዐይነት ወደ የትኞቹ ደቀ መዛሙርት ተመላለሰ? ስንት ደቀ መዛሙርት ናቸው? እነርሱስ እነማን ናቸው?
15. ጌታችንን ለመያዝ የመጡት ሰዎች ምን ይዘው ነበር?
16. ይሁዳ ለሰዎቹ ምን ዐይነት ምልክት ሰጥቶአቸው ነበር?
17. ጌታችንን ለሚይዙት ሰዎች ምን አላቸው?
18. ጌታችንን የያዙት ሰዎች መጀመሪያ ወዴት ወሰዱት?
19. የአይሁድ ሸንጎ አባሎች በጌታችን ላይ ያቀዱት ምን ነበር?
20. ጌታችንም ምን ስላለ ነው የስድብ ቃል ተናግሮአል ብሎ ሊቀ ካህናት ልብሱን ቀደደው?
21. ከዚያ ቀጥሎ አይሁድ ምን ዐይነት ግፍ ፈጸሙ?
22. ዶሮ በጮኸ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ ምን ትዝ ብሎት አለቀሰ?
23. ይሁዳ የተጸጸተው ምን ጊዜ ነው?
24. ተጸጽቶስ ምን አደረገ?
25. ጲላጦስ ጌታችንን ምን ብሎ ጠየቀው?
26. ጌታችንስ ምን መልስ ሰጠው?
27. ጲላጦስ ለአይሁድ ምን ምርጫ ሰጣቸው?
28. የእነርሱስ ምርጫ ምን ነበር?
29. አይሁድ በራሳቸው ላይ የፈረዱት ምን ብለው ነው?
30. ከዚያ በኋላ ጲላጦስ ምን አደረገ?
31. ጌታችንን ለመስቀል በሚወስዱት ጊዜ በእርሱ ላይ አይሁድ የሠሩት ተጨማሪ ግፍ ምን ምን ነበር?
32. የጌታችንን መስቀል ያሸከሙት ሰው ማን ባላል?
33. ወደ ጎልጎታ በደረሱ ጊዜ እንዲጠጣ ያቀረቡለት ምን ነበር?
34. ከጌታችን ጋር በግራው በኩል የተሰቀለው ወንበዴ ጌታችንን ምን አለው?



35. በቀኝ በኩል የተሰቀለውስ ምን መልስ ሰጠው?
36. ጌታችንስ በቀኝ በኩል ለተሰቀለው ወንበዴ ምን ዐይነት ተስፋ ሰጠው?
37. ጌታችን በተሰቀለ ጊዜ ከስድስት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ምን አዲስ ነገር ተከሠተ?
38. ጌታችንስ በዘጠኝ ሰዓት ምን ብሎ ጮኸ?
39. ጌታችን በሞተ ጊዜ ምን ምን ተአምራት ታዩ?
40. የጌታችንን አስከሬን ለምኖ የተሰጠው ማነው?
41. የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ወደ ጲላጦስ ሄደው መቃብሩ እስከ ሦስት ቀን ድረስ እንዲጠበቅ የለመኑት በምን ምክንያት ነው?
42. የቤተ ሳይዳው ሽባ ከታመመ ስንት ዘመኑ ነበር?
43. ጌታችን ሽባውን በመፈወሱ ከአይሁድ ተቃውሞ የደረሰበት በምን ምክንያት ነው?
44. ሊይዙት ለመጡት ሰዎች ጌታችን ማንነቱን በገለጸላቸው ጊዜ ምን ደረሰባቸው?
45. ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ ምን አደረገው?
46. በጌታችን በኩልስ ያለው መልስና ድርጊት ምን ነበር?
47. የድኻዋ መበለትና የዐመፀኛው ዳኛን ምሳሌ ታሪክ ተርክ።
48. አይሁድ የሚጠብቁት መሲሕ እንዴት ያለ ነበር?
49. የጌታችን ደቀ መዛሙርትም አስተሳሰብ ከዚያ የተለየ እንዳልነበረ የምንረዳው እንዴት ነው?
50. ጌታችን ግን የእነርሱ አስተሳሰብ ልክ አለመሆኑን እንዴት አድርጎ አስረዳቸው?
51. ጌታችን ቅዱስ ጴጥሮስን ሰይጣን ብሎ የገሠጸው ምን ለማለት ነው?

# ምዕራፍ 4

# ቤተ ክርስቲያን

## ሰባቱ አብያተ ክርስቲያን

በዮሐንስ ራእይ ውስጥ ወንጌላዊው ዮሐንስ ስለ ሰባት አብያተ ክርስቲያን ባየው ራእይ ለያንዳንዳቸው መልእክት የላከላቸው መሆኑ ተመልክቶአል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ስለ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያን የተለያየ አስተያየት አላቸው።

አንዳንድ ምሁራን፥ እነዚህ ሰባት አብያተ ክርስቲያን ራእዩ በታየበት ጊዜ በተለያዩ ቦታዎች የነበሩ ናቸው ይላሉ።

ሌሎች ወገኖች ደግሞ ሰባት ቍጥር የሙሉነት ምሳሌ ስለሚሰጠው በየቦታውና በየዘመናት ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያን የተሰጠ ምሳሌ ነው እንጂ በስም ለተቈጠሩ አብያተ ክርስቲያን ብቻ የተሰጠ ታሪክ አይደለም ይላሉ።

ሦስተኛዎቹ ወገኖች የሚያቀርቡት አሳብ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሲሆን እነዚህ ሰባት አብያተ ክርስቲያን የተባሉት ለተለያዩ ዘመናት የተነገሩ ትንቢቶች ናቸው የሚለው ነው። እነዚህም አብያተ ክርስቲያን የሚከተሉት ናቸው:-

1. <u>የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን</u>:- የሐዋርያትን ዘመን የሚያመለክት ሲሆን የቃሉም ትርጓሜ ተወዳጅዋ ማለት ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ወንጌልን በዓለም በሙላ ያሠራጩች በመሆንዋ ለእግዚአብሔር ተወዳጅ ነች ለማለት ነው። በምዕራፍ 2 ቍ:1–7 ላይ የተገለጸችው የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ጢሞቴዎስ ነበር። ቅዱስ ጳውሎስ ስለጢሞቴዎስ የሰጣቸው መግለጫዎች ለቤተ ክርስቲያኖች ሁሉ እንጂ ለጢሞቴዎስ ብቻ የተሰጠ አይደለም። እነርሱም:- ከእኔ ጋር የሚሠራው ማለት የሥራዬ ተባባሪ (ሮሜ: ም:16 ቍ:21)፡ በጌታ ታማኝ የሆነው (1ኛ: ቆሮ:ም:4 ቍ:17)፥ በእምነት እውነተኛ ልጂ (1ኛ: ጢሞ: ም:1 ቍ:2)።

2. <u>የሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን</u>:- (ትርጒሙ አንድ ጊዜ) በዘመነ ሰማዕታት ትመሰላለች። እርሱም ስለ ዐሥሩ ቀኖች ጭንቀትና ከኔሮን እስከ ዲዮቅልጥልጥያኖስ (እርሱም የዐሥሩ መሳደድ ምሳሌን ነው)። እስከ መጨረሻው ታማኝ ስለሆነች በምንም ነገር አይወቅሳትም። በምዕ

www.ethiopianorthodox.org

ራፍ 2 ቍ:8–11 ላይ የተገለጠችው የሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ፖሊካርፖስ ነበር። (ትርጕሙም ባለ ብዙ ፍሬ ማለት ነው)። እርሱም በ169 ዓ.ም. በእሳት በመቃጠል ሰማዕትነትን ተቀብሏል። የሐዋርያው ዮሐንስ ደቀ መዝሙር ነበር። በፍቅር የተሞላ ትጉህ አገልጋይ ነበር። ሊያቃጥሉት በእሳት ውስጥ በጨመሩት ጊዜ ምንም እሳት የማይጐዳው ሆኖ በመገኘቱ ወታደሩ መጥቶ በጦር ስለወጋው ከእርሱ የፈሰሰው ደም እሳቱን አጠፋው።

ይህችም ቤተ ክርስቲያን የሰማዕታት ቤተ ክርስቲያን፥ ሕይወትን አሳልፎ የመስጠት የፍቅር ቤተ ክርስቲያን ስለሆነች ምንም አትወቀስም።

3. <u>የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን</u>:- (ትርጕሙ ማወዳደር ነው) እርስዋም በዘመነ ሲኖዶስ ትመሰላለች። እነዚያ ዘመናት ከዓለማዊ ሁናቴዎች ጋር እየተወዳደሩ የቀረቡበት ዘመናት ናቸው። በነዚያ ሲኖዶሶች ዓለማውያን ገገርዎች በእምነት ጉዳዮች ውስጥ በብዛት እጆቻቸውን ያስገቡ ነበር። አሠራሩም ስሕተት ስለነበረ ብዙ ግፎች ተፈጽመውበታል። ነገር ግን ያቺ ቤተ ክርስቲያን ነች የሃይማኖትን ቀኖና ያስረከበችን።

በምዕራፍ 2ቍ 12–17 ላይ የተገለጠችው የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ ካርፑስ ይባል ነበር።

4. <u>የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን</u>:- (ማሳያ ማለት ነው) እርስዋም በመካከለኛው ታይታ በበዛበት ዘመን ትመሰላለች። በዚያ ዘመን ለታይታ የሚሠራበትና የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት የደከመበት፥ በምድራዊ ሀብት በልጽጋ በዓለማዊ ገገሮችና ነገሥታት ላይ የምትፈርድበት ዘመን ነበር። (ም:2 ቍ:18–29) – ኤጲስ ቆጶስዋ ኢሬናዎስ (ኤሬኔዎስ) ነበር።

5. <u>የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን</u>:- (ትርጕሙ ቀሪ ማለት ነው)። እርስዋም በዘመነ ተሐድሶ ትመሰላለች። ተሐድሶው በአንድ በኩል መንፈሳዊ ዝቅጠቱ በሌላ በኩል በስም ሕያው ነህ ነገር ግን ሞተሃል አሰኝቶታል። ከውስጥና ከውጭ በተደረገው ተሐድሶ ምክንያት ቀሪ አሰኝቶታል። (ም:3 ቍ:1–6)።

6. <u>የፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን</u>:- (ትርጕሙ የወንድማማች መዋደድ ማለት ነው)። እርስዋም በአሁኑ ዘመን ትመሰላለች። ይኸውም በታወረ አክራሪነት ሳይጠመዱ አብያተ ክርስቲያ ዓለም ዐቀፋዊነትን የተላበሰ ግንኙነት የሚያደርጉበት ዘመን ማለት ነው። ምንም እንኳ በነገረ መለኮት ልዩነት ያለ ቢሆን የእምነት አንድነትን ለማምጣት በፍቅር የመገናኘት ስሜት እያየለ ሄዶአል። (ም:3ቍ:7–13)።

7. <u>የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን</u>:- (ም:3 ቍ:14–22) (ትርጕሙ የሕዝብ ፍርድ ማለት ነው)። ቸልተኛነት ሰፍኖ ወደኋላ ማለት ዝንባሌ በሚታይበት መጨረሻው ዘመን ትመሰላለች።

(አባ ሙሴ በተባሉ የግብጽ ጳጳስ ከተጻፈው ዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ትርጓሜ ከገጽ 24 እስከ ገጽ 44 ካለው ክፍል በአጭሩ የተወሰደ።)

## <u>የአንዳንድ ወገኖች ማንነት</u>

ጌታችን ኢየሱስ ያስተምር በነበረበት ዘመን የተለያዩ እምነትና ሥርዐት የሚያካሂዱ ክፍሎች ነበሩ። ከእነርሱም መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

<u>ፈሪሳውያን</u> :- በሐዲስ ኪዳን ዘመን መግቢያ ላይ እጅግ የተጠናከረና በአይሁድ ኅብረተ ሰብእ ዘንድ ተሰሚነትን ያገኘው የፈሪሳውያን ክፍል ነበር። ፈሪሳዊ ማለት የተለየ ማለት ነው። ፈሪሳውያን በአይሁድ እምነት ራሳቸውን ጻድቃንና ንጹሐን አድርገው የሚቈጥሩ ነበሩ። ልዩ ቡድን ሆነው የተነሡትም ከመቃብያን በኋላ በ135 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ነበር። ትምህርተ ሃማኖታቸው በሦስቱ የብሉይ ኪዳን ክፍሎች በሕግ (በኦሪት) በነቢያትና በጽሑፋት ላይ የተመሠረተ ነበር። ይሁን እንጂ የተጻፈውን ሕግ ብቻ ሳይሆን የቃሉንም ትውፊት በጥብቅ ይከታተሉ ነበር። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን በፊደላዊ ትርጓሜ ሳይሆን በመንፈሳዊ ትርጓሜ በመተርጐም ይጠቀማሉ። ከሁሉም ይልቅ ለትውፊታዊው ሕግ ከፍተኛ ዋጋ ይሰጣሉ።

ፈሪሳውያን በመላእክትና በሌሎችም መናፍስት መኖር፥ በነፍስ ሕያውነትና በሥጋ ትንሣኤ ያምናሉ። ከትንሣኤም በኋላ ጽድቅና ኵነኔ መኖሩን አምነው ያስተምራሉ (የሐዋ: 23፥ 7–8)። የምጽዋት፥ የጾምና የጸሎት፥ ከማናቸውም ገቢአቸው ሁሉ ዐሥራት የማውጣት፥ እንደዚሁም የማንጻት ሥርዐት ነበራቸው (ሉቃ:11:42 ማር.7:4–5 ማቴ: 23:23–5)። ነገር ግን ይህን ሁሉ በሚፈጽሙበት ጊዜ ፍጹም ግብዝነት ይታይባቸው እንደነበር በወንጌል በዚ ጊዜ ተወ

www.ethiopianorthodox.org



ቅሶአል (ሉቃ:18:1–8) ። የሰንበት (ቅዳሜ) አከባበራቸውም እጅግ የጠበቀ ነበር። እሸት ቍርጦ መብላትን እንኳ ይከለክሉ ነበር (ማቴ:12፥ 1–2)።

ፈሪሳውያን የእግዚአብሔር ጸጋና ክብር ለአይሁድ ብቻ እንደሆነ ያምኑ ስለ ነበር የአካባቢያቸውን አሕዛብ በጣም ይጸየፉ ነበር። ስለዚህና ስለሌላው የማይረባ ወጋቸው ሁሉ ጌታችን ነቅፎአቸዋል (ማቴ:15:3)። ፈረሳውያን ከግብዝነታቸው ብዛት የተነሣ ሴትን ላለማየት ዐይናቸውን ይሸፍኑ ስለነበር ጌታችን ኢየሱስ እያንዳንዳቸውን «አንተ ዕውር ፈረሳዊ» በማለት ገሥጾአቸዋል (ማቴ:23፥ 6)። ፈሪሳውያን ጌታችን ኢየሱስ በሰንበት ቀን በፈጸማቸው ተአምራቱ የእግዚአብሔር ልጅና አምላክ መሆኑን በሚገልጡ ትምህርቶቹ ሁሉ አጥብቀው ይቃወሙት ነበር። ፈሪሳውያን አገራቸውን ከሮማውያን አገዛዝ ነጻ ለማውጣት ጥረት ያደርጉ ነበር። ከዚህም የተነሣ ቀናዕያን የተባሉ ክፍሎች ከእነርሱ የተውጣጡ ነበሩ። ቀናዕያንም ማለት የሀገር ፍቅር ቅንዐት ያላቸው ማለት ነው።

<u>ሰዱቃውያን</u>:- ሰዱቃውያን በትውፊት እንደሚነገረው ስማቸው በዳዊትና በሰሎሞን ዘመን ሊቀ ካህናት በነበረው በሳዶቅ ስም የተሰየመ ነው። የሳዶቅ ልጆች በባቢሎን ምርኮ ጊዜ በክህነት መዓርግ እንደ ነበሩ በምርኮው ጊዜና በኋላ የተጻፉት፥ መጻሕፍት ያስረዳሉ (2ዜና 31፥10፤ ሕዝ:40፥46: 44፥ 15፥ 48፥ 11)።

ሰዱቃውያን ሳንሄድረን በተባለው የአይሁድ የፍርድ ሸንጎ አባላት ነበሩ። ጌታችን ኢየሱስም በሚያስተምርበት ጊዜ ከነበሩት ካህናት አብዛኛዎቹ ከሰዱቃውያን ወገን ነበሩ። የማኅበራቸው አባላት ቁጥር ከፈሪሳውያን ያንስ ነበር። ከሄሮድሳውያን በታች በአገዛዝ ሥልጣን ውስጥ ከፍተኛ የፖለቲካ ኃይል እንደ ነበራቸው ይተረካል።

ሰዱቃውያን የኦሪትን ፊደላዊ ትርጓሜ እንጂ መንፈሳዊ ትርጓሜ አይጠቀሙም ነበር። ከነቢያትና ከጽሑፋት ይልቅ አምስቱን የሙሴን መጻሕፍት በቀኖና ያበልጣሉ። የተጻፈውን እንጂ ትውፊታዊውን ወይም የቃሉን ሕግ አይቀበሉም ነበር። የመላእክትንና የሌሎችን መናፍስት ህላዌ፥ የነፍስን ሕያውነት፥ የሙታንንም ትንሣኤ አያምኑም (የሐዋ:23፥8)። ጽድቅና ኵነኔ አሉ የሚለውን እምነትም በጣም ያቃልሉ ነበር (ሉቃ 20፥27–38)። በፖለቲካም ረገድ ሰዱቃውያን ከማንኛውም ባለሥልጣን ጋር ተስማምቶ ከመኖር በቀር የሀገርና የወገን ፍቅር ከቶ አልነበራቸውም። ትንሣኤ ሙታንን በተመለከተ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አጥብቀው ተከራክረውታል (ማቴ:22፥23–33)።

<u>ጸሐፍት</u>:- በሐዲስ ኪዳን ጸሐፍት እየተባሉ የሚጠሩት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን እየጻፉ ያባዙ የነበሩ ናቸው። የጸሐፍት አነሣሥ በባቢሎን ምርኮ ጊዜ እንደሆነ ይታመናል። ስለዚህም ጸሓፊው ዕዝራ ከእነርሱ አንዱ መሆኑ ታውቋል። ዋና ተግባራቸውም ቅዱሳት መጻሕፍትን ማጥናት፥ መተርጐምና ማብራራት፥ እየጻፉም ማባዛት ነበር። የሕጉን መጽሐፍ አዘውትረው ከማጥናታቸው የተነሣም የሕግ መምህራን ተብለዋል። ስለዚህም ረበናት (መምህራን) እየተባሉ ይጠሩ ነበር (ዕዝ.7፥11፤ ሉቃ.5፥17)። ሳንሄድረን በተባለውም የአይሁድ ፍርድ ሸንጎ ውስጥ ሥልጣን ነበራቸው።

ጸሐፍት የተለየ የዘርዕ ግንድ ያላቸው ሳይሆኑ ከፈረሳውያንና ከሰዱቃውያን የተውጣጡ ነበሩ። በእምነታቸውም አንዳንዶቹ የፈሪሳውያንን እምነት ሲይዙ አንዳንዶቹ የሰዱቃውያንን እምነት ይከተሉ ነበር። ጸሐፍት በቤታቸውም ሆነ በምኵራብ ወጣቶቹን እየሰበሰቡ የኦሪትን ምሥጢራዊ ትርጓሜ ያስተምሩ ነበር። በቤተ መቅደስም እየተገኙ ሃይማኖትን በተመለከተ ንግግር የሚያደርጉ እነዚሁ ጸሐፍት ነበሩ። ጸሐፍት ብዙ ጊዜ ጌታችንን ይፈታተኑትና ይቃወሙት ነበር፤ የሚቃወሙትም እነርሱ የሚከተሉትን ከተጻፈው ሕግ ውጭ የሆነውን የቃሉን ትውፊት (ወግ) አይቀበልም በማለት ነበር። ከጸሐፍት አብዛኞዎቹ የሚኖሩት በኢየሩሳሌም ሲሆን የኦሪት ሕግ በሚነገርበትም ቦታ ሁሉ ይገኙ ነበር።

<u>ኢሴኒያውያን</u>:- ኢሴኒ ማለት ቅዱስ ማለት ነው። ኢሴኒያውያን በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱ አይደሉም። የኢሴያውያን ኑሮ እንደ ፈሪሳውያንና እንደ ሰዱቃውያን ኑሮ አልነበረም። ለሕጋቸውና ለሥርዓታቸው ተገዢ ለመሆን ፈቃደኛ የሆነ ሰው ብቻ በሚገባበት ገዳማዊ ኑሮ ይኖሩ ነበር። በኢሴ ኒያውያን ማኅበራዊ ኑሮ ጋብቻ አይፈቀድም። ማኅበራቸውን የሚያስፋፉት የሌሎችን ልጆች በመመልመልና ከውጭ አዲስ አማኞችን በመቀበል ነበር። ከአባሎቻቸው መካከል ባለጸጋም ድኻም እንዳይኖር ንብረታቸው ሁሉ የጋራ እንጂ የግል አልነበረም።

ምግባቸውም የላመና የጣመ አልነበረም፡ ሥራ በማይሠሩበት ጊዜ ነጭ ይለብሱ ነበር። ያውም የሞቀና የደመቀ አልነበረም።

ኢሴኒያውያን በጠባያቸው ራሳቸውን መቈጣጠር የቻሉ፥ ጠንካሮች፥ ከቍጣ የራቁና ከመሓላ የተቈጠቡ ነበሩ፤ ሰንበትን አጥብቀው ያከብራሉ። የማኅበራቸውን ሥርዓት የሚተላለፈውን በከባድ ቅጣት ይቀጣሉ፤ በሃይማኖታቸው በተለየም ሕግ በመጠበቅ ከፈሪሳውያን ጋር የቀረበ አመለካከት አላቸው። የሰው ነፍስ ረቂቅና የማትሞት፥ ፈራሽ በሆነ ሥጋም የታሰረች ሆና እንደምትኖር ያስተምራሉ። በሞት ጊዜ ግን ደግ የሆነች ነፍስ ቀዝቃዛ አየር ወደአለበት ወደ ብርሃናዊ ቦታ ትሄዳለች። ኃጢአተኛ የሆነች ነፍስ ደግሞ ጨለማና ጥቅል ነፋስ ወደ አለበት ቦታ ትሄዳለች ብለው ያምናሉ። በኢሴኒ ያውያን ሥርዓት አምልኮ መሥዋዕት የለም። ፍቅረ እግዚአብሔርንና ፍቅረ ቢፅን፥ ፍቅረ ሀገርም ማጠናከር ዋና አላማቸው ነበር።

እ:ኤ:አ:በ1947 (1940) በሙት ባሕር ዳር የተገኙት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጥቅልሎች ኢሴኒያውያን ጽፈው የተዉአቸው እንደሆኑ በሊቃውንት ተጠንቶ ታውቋል። የማኅበራቸው አለቃ መምህረ ጽድቅ ይባል ነበር። ወደ ማኅበራቸው በአባልነት የሚገባውን ሰው ሦስት ዓመት የሙከራ ጊዜ ይሰጡታል። ከሦስት ዓመትም በኋላ የመንጻት ሥርዓት ይደረግለትና የማኅበሩ አባል ይሆን ነበር።

<u>ሽማግሎች</u>:- በሐዲስ ኪዳን ውስጥ በብዙ ቦታ «ሽማግሎች» ከካህናት አለቆች፥ ከጸሐፍትና ከፈሪሳውያን ጋር ተጠቅሰው ይገኛሉ (ማቴ:27፥12–20)። እነዚህ ሽማግሎች የተባሉት ከፍሎች ከጠቢባንና ከፍተኛ የሥራና የባህል ልምድ ካላቸው መካከል የተመረጡ ናቸው። ከመካከላ ቸውም አንዳንዶች ካህናት፥ አንዳንዶችም እንደ ዕዝራ ጸሐፍትና የሕግ ምሁራን ነበሩ። አንዳንዶችም ከዕውቀታቸውና ከሕግ ምሁርነታቸው ሌላ ከሀብ ታሞችና ከመሬት ከበርቴዎች መካከል የሚመረጡ ነበሩ። ከእምነት ክፍሎችም ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን የተመረጡ አባላት ነበሩ።

የሽማግሎች መቋቋም የተጀመረው በሙሴ ዘመን እንደሆነ በብሉይ ኪዳን ተገልጦአል (ዘጸ፥3፥16)። ቍጥራቸውም:- ከዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል አምስት፥ አምስት ተወካዮች ስለሚመረጡ ሰባ ነበረ። የወቅቱ ሊቀ ካህናት ሲጨምር ቁጥራቸው ሰባ አንድ ይሆናል። (ዘጸ:24፥1: ዘኍል:11፥24–25። ዋና ሥራቸውም በመጀመሪያ ሙሴን በፍርድ ሥራ መርዳት፥ ሕግንና ሥነ ሥርዓትን ማስከበር ሲሆን እየቈየ ደግሞ በሕዝቡ ላይ ግብር የመጣል ሥልጣን ነበራቸው (ዘኍ፥11፥16–24)።

ስብዓው ሽማግሎች የሚሰበሰቡበት ቦታ ክነሴት ወይም ስንሄድረን ይባላል። የፍርድ ሸንጎ ማለት ነው። ማንኛውም ፍርድ ነክ ጉዳይ ለማየት የሚሰበሰቡት በዚሁ የፍርድ ሸንጎ ነበር። ሽማግሎቹ ከቅዳሜና ከበዓላት ቀን በቀር በማንኛውም ቀን እየተሰበሰቡ የዳኝነት ሥራ ይሠሩ ነበር።

ሽማግሎች ጌታችን ኢየሱስ ያስተምር በነበረበት ጊዜ በምድረ እስራኤል ሁሉ በሃይማኖታዊና በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ማንኛውንም ነገር ለመወሰንና ለማስፈጸም ሥልጣን ነበራቸው። ነገር ግን የሞት ቅጣትን ለማስፈጸም ሙሉ ሥልጣን አልነበራቸውም። በጌታችን ላይ እንዲሞት ከፈረዱ በኋላ ወደ ጲላጦስ እንዲሄድ የታደረገውም በዚህ ምክንያት ነበር። ሸንጎው ከምድረ እስራኤልም ውጭ በሚኖሩ አይሁድ ላይ ትእዛዝ ማስተላለፍ ሥልጣን ነበረው (የሐዋ:9፥2)

በጌታችን ላይ የሞት ቅጣትን የመወሰንና የመፈጸም ሥልጣን ባይኖራቸውም የሞት ፍርድን የፈረዱ የዚሁ ፍርድ ሸንጎ ሽማግሎች ነበሩ። (ማር:14፥55–64 ሉቃ:22፥ 66–71። ዮሐ:11፥47። 19፥7)። በሐዋርያትም ላይ የተለያየ የቅጣት ፍርድን የፈረዱ የዚሁ የፍርድ ሸንጎ አባላት ነበሩ (ሐዋ.4፥15–18። 5፥17–18። 6፥12–15። 22፥ 30። 24፥ 20። ፍርድ ሸንጎው በቤተ መቅደስ አካባቢ ሆኖ ጸጥታን የሚያስከብርና ወንጀለኛ የሚባለውን የሚይዝ ወይም ከሚያስይዙት ጋር የሚሄድ የጥበቃ ክፍል ነበረው (ዮሐ:18:3)። ከሽማግሎች አንዳንዶች የሮማውያንን አገዛዝ ይቃወሙ ስለነበር ሸንጎው እስከ መድከምና ሥልጣኑን እስከማጣት ደርሶአል። በ70 ዓ.ም. ኢየሩሳሌም በጠፉች ጊዜ ሸንጎው እንደ ተበተነ ቀርቷል።

Ref.:- The new Testament, A Historical & Analytic SErey, By Merrill C. Tenney, Ph.D 1954 London



www.ethiopianorthodox.org

በሐዲስ ኪዳን ግን የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በሚባሉበት ጊዜ ከተደጋገመው [illegible] ያለ ነው። በሐዲስ ኪዳን አባባል ሽማግሌ ሲባል ካህን ወይም ቄስ ማለት ነው። በኦሪት ሕግ ሽማግሌዎች የሚባሉት በአስተዳደርና በፍርድ ሥራ ላይ የተመደቡ ናቸው። በሐዲስ ኪዳን ግን ሽማግሌዎች የሚባሉት በማስተማር ሥራ ላይ የተመደቡ ናቸው። ለዚህም አባባል በዋቢነት የሚጠቀሱ የሐዋርያት ትምህርት የሆነው ዲድስቅልያና መጽሐፍ ቅዱስ ናቸው።

በዲድስቅልያ መቅድም ላይ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የሥራ መደብ በሚዘረዘርበት ጊዜ የካህናት ማለት የቀሳውስት ሥራ ማስተማር ወይም አስተማሪነት መሆኑ ተገልጦአል። እንዲሁም በአንቀጽ 34 ላይ የቄሱ ሥልጣን ማስተማር፥ ማጥመቅ፡ ቅዳሴ መቀደስና መባረክ ነው ተብሎአል።

ወደ ሐዲስ ኪዳን መለስ ያልን እንደሆነ ደግሞ ሽማግሌዎች የሚል ስም የተሰጣቸው የቀሳውስት ተግባር ማስተማር መሆኑ ተዘርዝሮ እናገኛዋለን።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ከመሄዱ በፊት የኤፌሶንን የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አስጠርቶ እግዚአብሔር በገዛ ደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን እንዲጠብቁ ዐደራ ብሎአቸዋል። ይህንንም ያለው መንፈስ ቅዱስ እነርሱን የመንጋው ጠባቂ አድርጎ የሾማቸው መሆኑን ከገለጠላቸው በኋላ ነው (የሐ:ሥ:ም:20 ቍ:28)።

በቤተ ክርስቲያን ትውፊትና በዲድስቅልያ አንቀጽ ኻያ አንድ መሠረት ቀሳውስት የሚሾሙት በኤጲስ ቆጶሳት መሆኑ ግልጽ ነው። በዚህም መሠረት ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የቀርጤስ ኤጲስ ቆጶስ የነበረውን ቲቶን ሽማግሌዎችን እንዲሾም ያዘዘው (ቲቶ:1፥5)።

በሐዋርያው የቅዱስ ያዕቆብ መልእክት ም:5ቍ:14ላይ የታመመ ሰው ቢኖር እንዲጸልዩለት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች እንዲጠሩ የታዘዘው እነርሱ ካህናት ስለሆኑ ነው እንጂ ያስተዳደር ሹማምንት ስለሆኑ አይደለም።

## <u>የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን</u>

<u>መጥምቁ ዮሐንስ</u>:- ስለ መጥምቁ ዮሐንስ አወላለድ በሉቃስ ወንጌል ም:1ላይ የተዘረዘረ ስለሆነ ያንን መድገም አስፈላጊ አይሆንም። በወንጌል ውስጥ ያልቀረበውን ታሪክ ቀጥለን እንመለከታለን።

ዮሐንስ መጥምቁ ወደ ምድረ በዳ የሄደው ሄሮድስ ሕፃናትን ለማስፈጀት በወሰነበት ጊዜ ነው። ሰበአ ሰገል ወደ እርሱ አለመመለሳቸውን አይቶ ሕፃናትን ለማስፈጀት በተነሣበት ጊዜ አጠገቡ ከነበሩት ሰዎች አንዱ በዚህ በአቅራቢያችን እኮ ዘካርያስ የተባለ ካህን አንድ ወንድ ልጅ የተወለደለት ሲሆን ሰዎች ክርስቶስ ነው ይላሉ አለው። በዚህ ጊዜ ሄሮድስ ዘካርያስን አስጠርቶ ልጁን እንዲያመጣ ነገረው።

የዮሐንስ ወደ ምድር በዳ መወሰድ ሁለት የተለያዩ ታሪኮች አሉት። የመጀመሪያው ታሪክ ዘካርያስ በሄሮድስ እንደታዘዘው ወደ ቤቱ በተመለሰ ጊዜ የልጁ እናት ኤልሣቤት ጉዳዩን አስቀድማ ስለሰማች ልጁን ይዛ ወደ ምድረ በዳ ሄደች። ዘካርያስም ሄሮድስን ፈርቶ በቤተ መቅደስ ውስጥ ተሸሸገ። ሁለተኛው ታሪክ ደግሞ ዘካርያስ ልጁን እንዲያመጣ ሄሮድስ በጠየቀው ጊዜ ልጁን የተረከብኩበት ቦታ አለና የማስረክበው እዚያ ነው ብሎ መልስ ሰጥቶት ልጁን የክህነት ልብስ በማልበስ ካህን አድርጎ ከሾመው በኋላ በቤተ መቅደሱ ውስጥ እንዳስቀመጠው የእግዚአብሔር መልአክ መጥቶ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው የሚለው ነው። ልጁ ከቤተ መቅደስ እንዴት እንደተወሰደ አለማወቁን ለመልእክተኞቹ በነገራቸው ጊዜ በቤተ መቅደስና በመሠዊያው መካከል ገደሉት። ይህም ጌታችን በማቴዎስ ወንጌል ም:23ቍ:35 ላይ ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ በቤተ መቅደስና በመሠዊያው መካከል እስከ ገደላችሁት እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ የሚለው የጌታችን አባባል ይህን ታሪክ የተከተለ መሆኑን ባስልዮስና ጎርጎርዮስ በትርጓሜ ተስማምተውበታል። ዮሐንስም በምድረ በዳ ዕድሜው 30 ዓመት እስኪሞላው ድረስ ቈይቶ ሰዎችን ለንስሓ ለማጥመቅና የጌታችንን መንገድ ለማዘጋጀት ሐናና ቀያፋ ሊቃነ ካህናት በነበሩበት ዘመን መጣ። ስለጌታችንም በሰጣቸው ምስክርነቶች እርሱ ራሱ ክርስቶስ እንዳይደለና ክርስቶስ ግን በሕዝቡ መካከል እንደሚገኝ ገልጾአል። እርሱ የጫማውን ክር እንኳ ለመፍታት ብቁ አለመሆኑንና እርሱ ማለት ጌታችን ከፍ ከፍ ሲል ራሱ ዮሐንስ ግን ዝቅ እንደሚል በትሕትና ገለጠ። ሄሮድስ የወንድሙን ሚስት አግብቶ ስለነበረ ስሕተተኛነቱን በገለጠለት ጊዜ አስሮት ነበር። በሚስቱና በእንጀራ ልጁም ጥያቄ መሠረት የዮሐንስን ራስ

ቈርጦ ሰጣቸው። ራሱ ተቈርጦ ሳለ የወንድምህን ሚስት ለራስህ መውሰድ የለብህም እያለ ይናገር ነበር ይባላል (የመስከረም 2 ቀን ስንክሳር ይመለከቷል)።

ጎርጎርዮስ (ገባሬ ተአምር):- በቂሣርያ ጥቁር ባሕር በሦስተኛው መቶ ዓመት ባለጸጎችና አረማውያን ከነበሩ ወላጆች ተወለደ። ገና በልጅነቱ ወላጆቹ ሞተውበት ከወንድሙ ጋር አብረው በፍልስጥኤል ቂሣርያ ባል አግብታ ወደምትኖረው እኅታቸው ሄዱና በዚያ ኖሩ። ከዚያም የሕግ ትምህርት ለመማር ወደ ቤይሩት ሄዱ። ወደ ፍልስጥኤም ቂሣርያ በተመለሱ ጊዜ ጎርጎርዮስ ከኦርጌኖስ ጋር ተገናኘ። ኦርጌኖስም ስለክርስትና ሃይማኖት አስተምሮት መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያነብ አደረገው። ከዚያም ወደ እስክንድርያ ሄዶ የሕክምናና የፍልሰፍና ትምህርት ተማረ። ከዚያም የክርስትናን ሃይማኖት በመቀበል ተጠመቀ። ቅን የሆነ መንገድንም መከተል ጀመረ። ወደ አገሩም ተመልሶ ለአምልኮተ እግዚአብሔር በምድረ በዳ ብሕትውናን ተከተለ። የአገሩ ሕዝብም ኤጲስ ቆጶስ እንዲሆንላቸው አስገደዱት። ይህም በሆነበት ጊዜ ክርስቶናን ከተቀበለ ገና ከሰባት ወር አልበለጠውም ነበር። ገና ወደ አገሩ እንደተመለሰ የሀገሩ ኤጲስ ቆጶስ በሥራ እንዲረዳው ፈልጎት ነበር። እርሱ ግን ሸሽቶ ወደ ምድረ በዳ ሄደና ለአምልኮተ እግዚአብሔር ራሱን ለየ። ኤጲስ ቆጶሱ በሞት ቢተለየ ጊዜ ሕዝቡ ጎርጎርዮስን ለመሾም ፈልጎ ወዴት እንዳለ ግን ሊያገኙት አልቻሉም። ሕዝቡ ከነባቤ መለኮት ቅዱስ ጎርጎርዮስ ጋር ተሰብስቦ ሳለ ባሕታዊውን ጎርጎርዮስን ጳጳሳችሁ እንዲሆን ጠይቁት የሚል ድምፅ ሰሙ። በዚህም መሠረት ወደ ምድረ በዳና ወደ ተራራዎች ለፍለጋ ሰዎች ተላኩ። ነገር ግን ሊያገኙት አልቻሉም። ባጡት ጊዜ የወሰኑት ውሳኔ አንድ ወንጌል አስቀምጠው የጵጵስና ሹመት ሥነ ሥርዓት እንዲያካሄዱ ነው። ቀድሞ ቴዎድሮስ ይባል የነበረ ኾኖ አሁን ጎርጎርዮስ ብለው በመሰየም ሥርዓቱን አከናወኑ። ጸሎቱን ያከናወነው ነባቤ መለኮት ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነው በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ጎርጎርዮስ ወደነበረበት ቦታ ሄዶ ጵጵስና ሾመውሃልና ተነሥተህ ወደ አገርህ ሂድ አለው። ይህ ጉዳይ ከእግዚአብሔር ስለሆነ ላለመቀበል አታወላውል አለው። እርሱም ምንም ሳያወላውል ተነሥቶ ሄደ፤ ሕዝቡም በደስታ ተቀበለው። በስብከቱ፥ በተአምራቱ፥ በበጎ ተግባሩ ሥራው የተሳካለት ስለሆነ ከዚህ ዓለም በሞት በተለየ ጊዜ ከአገሩ ሕዝብ ክርስቲያን ያልሆነ ሰው ብዛት ዐሥራ ሰባት ብቻ ነበር።

ገባሬ ተአምራት፡ ማለት ተአምራት አድራጊው የሚል ቅጽል ስም የተሰጠው በሚያደርጋቸው የታምራት ብዛት ምክንያት ነው። ከታምራቱም ጥቂት መሳሌዎችን ቀጥለን እናቀርባለን።

እስክንድርያ የነበሩ አረማውያን ወጣቶች በሀዋቂነቱ ቀንተውበት አንዲት ሴተኛ ዐዳሪ በማስነሣት አብሯት የተኛበትን ዋጋ ከፈለኝ ብላ እንድትጠይቀው አደረጉ። እርሱ ግን ምንም ሳይደነግጥ ደቀ መዝሙሩን የጠየቀችውን እንዲሰጣት ነገረው። ገንዘቡን እንደተቀበለች ርኩስ መንፈስ ይዞ በመሬት ላይ ጣላት። ውሸት መናገርዋን ተናዝዛ የንጹሕን ሰው ስም እንድታጠፋ ያደረጉአትን ሰዎች ረገመች። ቅዱስ ጎርጎርዮስም ጸልዮ ሰይጣኑን አላቀቃት። የታምራት አድራጊነቱን ዝና ለማቃለል ብለው ሁለት የአይሁድ እምነት ተከታዮች በመስማማት አንዱ የሞተ በመምሰል እንዲተኛ ሁለተኛው ደግሞ ለመቃብር የሚሆን ገንዘብ ከቅዱስ ጎርጎርዮስ እንዲለምን ሆነ። ልመናውንም በመቀበል ልብሱን ሲሰጠው እየሳቀበት ሄደና ጓደኛውን ቢጠራው ሞቶ ተገኘ። ይህ የተደረገው በፍልስጥኤም ነው።

ወደ ጥቁር ባሕሩ ቂሣርያ በሄደ ጊዜ ከጸሎቱ የተነሣ ሰይጣናት እየጮኹ በመሸሽ ከየጣዖት ቤቱ ወጥተው ሄዱ። የቤተ ጣዖቱ ካህን ጉዳዩን አይቶ በመረዳቱ ወደ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ሄዶ እባክህን ሰይጣኑ እንዲመለስ አድርግልኝ ብሎ ለመነው። እርሱም ከጎርጎርዮስ ወደ ሰይጣን፥ ወደ ቤተ ጣዖቱ ተመለስ የሚል ጽሑፍ ሰጥቶት በቤት ጣዖቱ ባስቀመጠው ጊዜ ሰይጣን ተመልሶ መጥቷል። ካህኑም ከቅዱሱ አምላክ ጋር የሰይጣንን ደካማነት በማነጻጸር ተጠምቆ ወደ ክርስትና ተመልሶአል። ብዙ አረማውያንም ከእርሱ ጋር ተጠመቁ። የተሾመው በ244 ዓ.ም. ሲሆን ያረፈው በ270 ዓ.ም. ነው። (የኅዳር 21 ቀን ስንክሳር ይመለከቷል)።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ፥ (የቅዱስ ባስልዮስ ወንድም) :- ይህ ትልቅ አባት ከወንድሞቹ ሁሉ ጋር ደግ ሰው ነበር። በግሪክ ቋንቋና በፍልስፍና ትምህርትም የበለጸገ ነበር። ለቀጥተኛው እምነትም ከፍተኛ ቅናት (ቀናኢነት) ነበረው። ይህም በጎ ተግባሩ ስለታወቀለት እርሱ እንኳን የማይፈልግ ቢሆን በግድ ለኤጲስ ቆጶስነት ተሰየመ። ሀገረ ስብከቱም የኒሲስ ከተማ ነበረች። ዐደራ የተሰጠውንም የክርስቶስ መንጋ መልካም አጠባበቅ አደረገላቸው። በትምህርቱ ለብዙዎች ብርሃንን ያበራላቸው ነበር። አብዛኞዎቹን የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች ተርጕሟል። በንጉሡ በዋልስ



ዘመንና በእርሱም ትእዛዝ ወደ ግዞት ተወስዶ ነበር። ነገር ግን በትልቁ ቴዎዶስዮስ ትእዛዝ ተመልሶ በ378 ዓ.ም. ወደ ኒሲስ እንዲሄድ ተደርጓል።

በንጉሡ በቴዎዶስዮስ ትእዛዝ በቁስጥንጥንያው ፓትርያርክ በመቅዶንዮስ ኑፋቄ ምክንያት አንድ መቶ ኀምሳ አባቶች በተሰበሰቡ ጊዜ ከተሰብሳቢዎቹ አንዱ ይህ የኒሲሱ ጎርጎርዮስ ነበር። ይህ አባት ለሰባልዮስ፥ ለመቅዶንዮስና ለአቡሊናርዮስ የኑፋቄ ትምህርቶች መልስ ሰጥቶባቸዋል።

አምላካዊውን ቅዳሴ ይቀድስ በነበረበት ጊዜ በመንበሩ ላይ ኪሩቤልን ያይ ነበር ይባላል። የኤጲስ ቆጶስነት ዘመኑ 33 ዓመት በሞላው ጊዜ ወንድሙ ቅዱስ ባስልዮስ ሊጠይቀው መጣ። ከብሕትውናውም ብዛት የተነሣ ታሞ ነበር። ወንድሙንም በደስታ ተቀበለው። ቅዳሴ እንዲቀድስ በወተወተው ጊዜ እንደ ማንቀላፋት አድርጎት እመቤታችን ድንግል ማርያም ተገልጣለት ዛሬ ወደ እኛ ትመጣለህ አለችው። በዚያም ቀን ዐረፈና ወንድሙ ቅዱስ ባስልዮስ ጸልዮለት በክብር ተቀበረ (የጥር 21 ቀን ስንክሳር ይመለከቷል)።

ዘጠኙ ቅዱሳን:- ኢትዮጵያ በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ቅዱሳን ያሉአት ሀገር ናት። ቅዱሳኑ የሀገር ተወላጆች ብቻ ሳይሆኑ የውጭ ሀገር ተወላጆችም ናቸው። ዘጠኙ ቅዱሳን የሚባሉትም የውጭ ሀገር ተወላጆች ከሆኑት፥ ነገር ግን በሃማኖታቸውና በሐዋርያዊ ተግባራቸው ኢትዮጵያውያን ሆነው በኢትዮጵያ ከኖሩት ቅዱሳን መካከል ናቸው።

ዘጠኙ ቅዱሳን፥ በ5ኛው ምእት ዓመት (460–470) በዚያ ጊዜ የሮማ ግዛት ከነበሩት ከተለያዩ አገሮች በአልዓሜዳ ዘመነ መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል። የመጡበትም ምክንያት አንዲት የነበረችው የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በ451 ዓ.ም. ስለ ምሥጢረ ተዋሕዶ ትምህርት በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል በተከሠተው አለመግባባት ምክንያት ለሁለት በተከፈለች ጊዜ የተከሠተውን ጠብና ክርክር በመጥላት የሰላም ሀገር ፈልገው ነው። ይህም ብቻ አይደለም፤ የኬልቄዶንን ጉባኤና የሁለት ባሕርይን እምነት ውሳኔ አንቀበልም በማለታቸው ይህን ጉባኤና ውሳኔውን በሚደግፉ የቢዘንታይን ነገሥታት አሰቃቂ ሥቃይና በደል ስለደረሰባቸው በአንድ ባሕርይ እምነት መሰሎቻቸው የሆኑ ክርስቲያኖች ወደ አሉባት ሀገር ወደ ኢትዮጵያ መሰደድ ግድ ሆኖባቸዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብም ከጥንት ጀምሮ ባለው የእንግዳ ተቀባይነት ልማዱ በአክብሮትና በአፍቅሮት ተቀብሎአቸዋል። እነዚህ ቅዱሳን ከሀገራቸው ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ ከአልዓሜዳ እስከ ካሌብ ዘመነ መንግሥት ድረስ በአክሱም ውስጥ ልዩ ስሙ ቤተ ቀጢን በተባለው ቦታ በአንድነት ኖረዋል። የዘጠኙ ቅዱሳን ስማቸውና የመጡበት አገራቸው በገድላቸው እንደ ተጻፈው የሚከተለው ነው:-

| ስማቸው | የመጡበት ሀገር |
|---|---|
| 1ኛ. አባ አሌፍ | ቂሣርያ |
| 2ኛ አባ አረጋዊ (ዘሚካኤል) | ቍስጥንጥንያ |
| 3ኛ. አባ አፍጼ | እስያ |
| 4ኛ. አባ ሊቃኖስ | ቍስጥንጥንያ |
| 5ኛ. አባ ገሪማ (ይስሐቅ) | ቍስጥንጥንያ |
| 6ኛ. አባ ጕባ | ኪልቅያ |
| 7ኛ. አባ ምዓታ | ቆስያ |
| 8ኛ. አባ ጳንጠሌዎስ | ቍስጥንጥንያ |
| 9ኛ. አባ ጽሕማ | አንጾኪያ |

ዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ኢትዮጵያን እንደ ስደት ሀገራቸው ሳይሆን እንደ ትውልድ ሀገራቸው በመቍጠር ሲኖሩ በሃይማኖ ታቸው፡ በመንፈሳዊነታቸውና በመልካም ሥራቸው ውጤት በኢትዮጵያ ውያን ዘንድ ተወዳጅነትንና ተሰሚነትን አግኝተዋል። ከዚህም የተነሣ ብዙዎች መንፈሳውያት ተግባራትን አከናውነዋል። ከአከናወኑአቸው መንፈሳውያት ተግባራትም መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

የኢትዮጳያን ቋንቋ ግእዝን አጥንተው ቅዱስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የተረጐማቸውን ቅዱሳት መጻሕፍት እንደገና ከዕርዕና ከሱርስት ከተጻፉት መጻሕፍት ጋር በማመሳከር አርመዋል። በቅዱስ አባ ሰላማ ጊዜ ያልተተረጐሙ መጻሕፍትንም ከብሔራውያን ሊቃውንት ጋር በመሆን ከዕርዕና ከሱርስት ወደ ግእዝ ተርጕመዋል። በቅዱስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን

www.ethiopianorthodox.org

የተገለጠውን የወንጌል ብርሃን በኢትዮጵያ በአብዛኛው ክፍል እንዲያበራ አድርገዋል። ስለ ምሥጢረ ተዋሕዶ አንድ ባሕርይ ትምህርትን በማጠናከር እስከ መኻል አገር ድረስ ተዘዋውረው አስተምረዋል። አምልኮተ ባዕድን አስወግደዋል። በየአውራጃና በየክፍለ ሀገሩ አብያተ ክርስቲያንን አሳንጸዋል፥ ገዳማትን መሥርተዋል። በየገዳማቱና በየአድባራቱ መሠረታውያን ትምህርት ቤቶችን አቋቁመዋል። ምናኔን፥ ምንኵስናንና ገዳማዊ ሕይወትን (ኑሮን) አስተምረዋል። በተለየም አባ አረጋዊ የአባ ጳኩሚስ ተከታይ የነበረው የአባ ቴዎድሮስ ደቀ መዝሙር ስለ ነበረ የምንኵስና ትምህርትና ሥርዐት በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ አድርጓል።

እነዚህ ዘጠኙ ቅዱሳን ያስተማሩትን ምናኔንና ምንኵስናን አጥብቀው የተከታተሉ የኢትዮጵያ ነገሥታትም መንግሥታቸውን ትተው ወደ ገዳም በመግባት ዘመናቸውን አሳልፈዋል። ከእነዚህም መካከል አጼ ካሌብና ልጃቸው አጼ ገብረ መስቀል በምሳሌነት ይጠቀሳሉ።

ዘጠኙ ቅዱሳን ጾምና ጸሎትን የሚያዘወትሩ፥ ገድልና ትሩፋትን አብዝተው የሚሠሩ፥ በፍጹም ልባቸው፥ በፍጹም ኀይላቸው፥ በፍጹም ነፍሳቸውም እግዚአብሔርን የሚያፈቅሩ ለቅድስና የበቁ፥ ይህን ዓለም የናቁ ስለነበሩ፥ እግዚአብሔር በእነርሱ ዐድሮ የተለያየ ድንቅ ሥራ ይሠራና ተአምራት ያደርግ ነበር። ቀጥሎም ከዘጠኙ በሦስቱ ቅዱሳን ከተደረጉት ድንቅ ሥራዎችና ተአምራት የሚከተሉት በአጭሩ ቀርበዋል።

1. <u>አባ ጰንጠሌዎን</u>

አባ ጰንጠሌዎን ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በአክሱም ቤተ ቀጢን በተባለው ቦታ ከሌሎች ጓደኞቹ ጋር ከኖረ በኋላ በሚለያዩበት ጊዜ በአክሱም አጠገብ አንድ በአት (ገዳም) መሥርቶአል። ቦታው ተራራማ ነው። በዚህ ተራራማ ቦታ ቋጥኙን ፈልፍሎ ዋሻ ሠርቶአል። የዋሻው ርዝመት አምስት ክንድ ሲሆን ስፋቱ ሁለት በሦስት ክንድ ነው። ከላይ ጣራው አንድ ድንጋይ ነው። አንድ,ሰው በጭንቅ ሊያስገባ ከሚችል ቀዳዳ በቀር በር የለውም። አባ ጰንጠሌዎን በዚህ ጠባብ ዋሻ ውስጥ ለ40 ቀናት ያኽል እህልና ውሃ ሳይቀምስ በጾምና በጸሎት ቈይቶአል።

አባ ጰንጠሌዎን ከዕለታት አንድ ቀን በጥዋት ወይራ ተከለ፤ ወይራውም በዚያው ዕለት ዐድጎ ዛፍ ሆነና ደረቀ፤ ደቀ መዝሙሩም ቆርጦ ፈለጠው። መሥዋዕት ለመሥራትም አነደደው። አባ ጰንጠሌዎንም ፍሕሙን በልብሱ ቋጥሮ ወስዶ በጥና ውስጥ በመጨመር በዚያው ዕለት በቅዳሴ ጊዜ ማዕጠንት አጠነበት።

2. <u>አባ ይስሐቅ (ገሪማ)</u>

አባ ገሪማ በየአውራጃው እየተዘዋወረ ወንጌልን ሲያስተምር ከኖረ በኋላ በትግራይ ክፍለ ሀገር መደራ በተባለው ቦታ እስካሁን በስሙ የሚጠራውን ገዳም መሥርቶአል። በዚህም ለ27 ዓመታት ቆይቶአል።

ከዕለታት አንድ ቀን ጥዋት ስንዴ ዘራ፤ የተዘራውም ስንዴ ወዲያው በቀለ፥ ፍሬም አፈራ፤ ለመከርም ደረሰ በሰዓትም አባ ይስሐቅ ያን ስንዴ አጭዶ ከወቃ በኋላ አዘጋጅቶ ለሠርክ መሥዋዕት አድርሶታል። እንደዚሁም ጢት ወይን ተክሎ፥ የተተከለው ወይን በዕለቱ አፍርቶ፥ በዚያው ዕለት ለቅዳሴ ቍርባን ደርሶአል። እንደዚሁም መጽሐፍ ሲጽፍ ፀሐይ ለመጥለቅ በተቃረበ ጊዜ እንዲቆም አዘዘው። መጽሐፉን እስኪጨርስ ቆመ። የሚጽፍበትም የመቃ ብርዕ ከእጁ በወደቀ ጊዜ ወዲያው በቀለና ለመለመ።

አንድ ጊዜም አባ ይስሐቅ (ገሪማ) ምግብ ከበላ በኋላ ቀድሶ እንደ ቈረበ ነገር ሠሪዎች በሐሰት በዘምኑ ለነበረው ለግብጻዊው ጳጳስ ለብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ነገሩአቸው። አባ ጰንጤሌዎንም ይህን ሐሜት ሰምቶ ወደ አባ ይስሐቅ ሄደና «ልጄ ይስሐቅ ሆይ፥ የምነግርህ ምሥጢር አለና ከአንተ ጋር ያሉ ሰዎች ገለል እንዲሉ አድርግ» አለው። አባ ይስሐቅም « ገለል ማለት ያለባቸው ሰዎች ብቻ አይደሉም፤ ዛፎችም ድንጋዮችም ገለል ማለት አለባቸው» አለው። በዚህ ጊዜ አባ ይስሐቅ በተናገረው መሠረት ዛፎችና ድንጋዮች ሁሉ ከነበሩበት ቦታ በመንቀሳቀስ አምስት ምዕራፍ ያኽል ርቀው ቆሙ። አባ ተንጠሌዎንም በዚህ ተአምር እየተደነቀ «ልጄ ይስሐቅ ሆይ፥ ገረምከኝ (አስፈራኸኝ)» አለው። በዚህም ምክንያት ቀድሞ ይጠራበት የነበረው ስሙ ይስሐቅ ተለውጦ ገሪማ ተባለ።



አባ ገሪማ ብዙ የጽድቅ ሥራን ሲሠራ ከኖረ በኋላ እንደ ኤልያስ በብርሃን ሠረገላ ወደ ሰማይ መወሰዱ በስንክሳርና በገድሉ ተጽፎአል።

3. <u>አባ አረጋዊ</u> (ዘሚካኤል):- ከዘጠኙ ቅዱሳን መካከል አረጋዊ የተባለው ዘሚካኤል በጣም ስመ ጥሩ ጻድቅ ነው። ይህ ጻድቅ ዛሬ በስሙ ወደሚጠራው ገዳም ወደ ደብረ ዳሞ ለመውጣት ተቸግሮ ነበረ። ከዕለታት አንድ ቀን ከተራራው ሥር ሆኖ እግዚአብሔር የልቡን ምኞት እንዲፈጽምለት ሲጸልይ ረጅም ዘንዶ ከተራራው ጫፍ ላይ ሆኖ ጅራቱን ወደ ታች ዘረጋ፤ አባ አረጋዊም እግዚአብሔር የላከለት ምክንያት መሆኑን ተረድቶ የዘንዶውን ጅራት ሲይዝ ዘንዶው ተመንጥቆ ከተራራው ላይ አወጣው። ከዚያ በኋላ ደብረ ዳሞን ገዳም መሠረተ። ከአባ ጳኩሚስ ገዳም በተማረው መሠረት የምንኵስናን ሥርዓት ለተከታዮች መነኮሳት ልጆቹ አቋቋመ። ለኢትዮጵያውያን መነኮሳት ሁሉ መሪ ሆነ።

በዚህም ገዳም ውስጥ ብዙ ገድልን ሲጋደልና የትሩፋት ሥራን ሲሠራ ከኖረ በኋላ ሞትን ሳያይ እንደ ተሰወረ በስንክሳርና በገድሉ ተነግሮአል። ደብረ ዳሞ ገዳም በኢትዮጵያ የመጀሪያው ገዳም ነው። ዛሬ ወደዚህ ገዳም ለመውጣት የሚቻለው በተራራው ላይ በተተከለ የብረት ችካል ላይ በታሰረ ገመድ ነው። በሌላ ግን መውጣት አይቻልም።

ከዚህም ሌላ ከዘጠኙ ቅዱሳን መካከል አንዳንዶቹ ቆመው በሚጸልዩበት ጊዜ ዐሥሩ የእጃቸው ጣቶች በመቅረዝ ላይ እንዳለ መብራት የሚያበሩላቸው ነበር። ውሃ በወንፊት ቀድተው ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚያቃርቡም ነበሩ። በሞቱም ጊዜ በመላእክት የተገነዙ አሉ።

ዘጠኙ ቅዱሳን በተቀደሰ ተግባራቸውና እግዚአብሔር በእነርሱ ዐድሮ ባሳየው ድንቅ ሥራና ልዩ ልዩ ተአምር በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ወይም ጻድቃን ተብለው ይከበራሉ። በስማቸው ቤተ ክርስቲያን ተሰይሞላቸዋል። ጽላት ተቀርፆላቸዋል። ባረፉበት ወይም ከዚህ ዓለም በተለዩበት ቀንም እንዲታሰቡ በቤተ ክርስቲያኒቱ ቀኖና ተወስኖአል።

የዘጠኙ ቅዱሳን ገዳማቸውና መታሰቢያ ቀናቸው የሚከተለው ነው።

| ስም | ገዳም | መታሰቢያ ቀን |
|---|---|---|
| 1ኛ. አባ አሌፍ | ብሕዛን (አህስአ) | መጋቢት 11 |
| 2ኛ. አባ አረጋዊ | ደብረ ዳሞ | ጥቅምት 14 |
| 3ኛ. » አፍጼ | የሓ | ግንቦት 12 |
| 4ኛ. » ሊቃኖስ | ደብረ ቈናጽል | ኅዳር 26 |
| 5ኛ. » ገሪማ | መደራ | ሰኔ 17 |
| 6ኛ. » ጉባ | ገርዓልታ | ግንቦት 27 |
| 7ኛ. » ይምዓታ | ገርዓልታ | ጥቅምት 23 |
| 8ኛ. አባ ጰንጠሌዎን | በአክሱም አጠገብ | ጥቅምት 6 |
| 9ኛ. » ጽሕማ | ጼድያ | ጥር 16 |

የዘጠኙ ቅዱሳን ታሪክ መሠረት የሚከተሉት መጻሕፍት ናቸው:-

1. ገድለ አረጋዊ
2. ገድለ ገሪማ
3 . ስንክሳር በተጠቀሰው የዕረፍት ቀናቸው
4. የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ አክሱም ከተክለ ጻድቅ መኩሪያ 1951 ዓ.ም. አዲስ አበባ ገጽ 328 – 331
5. መጽሐፈ ምሥጢር ዘአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ

www.ethiopianorthodox.org

## የቤተ ክርስቲያን የዜማ ጸሎት

ባለፉት ክፍሎች በተከታታይ የቀረበው የቅዳሴ ተሰጥዎ ብቻ ነበር። ቤተ ክርስቲያን ግን ያሉአት የዜማ ጸሎቶች በጣም ብዙዎች ናቸው እንጂ በቅዳሴ ጸሎት ብቻ የተወሰነች አይደለችም። ከእነርሱም አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያኽል የቅኔ ማኅሌቱ ስብሐተ እግዚአብሔር፣ የሰዓታቱ ጸሎት፣ የነግህና የሠርክ ጸሎት፣ የሰሙነ ሕማማት ጸሎት፣ በተለያዩ በዓላትና በተለያዩ የሃይማኖት ሥርዓት አገልግሎቶች በዜማ የሚቀርቡ ጸሎቶች ይገኙበታል። እነዚህ የዜማ ጸሎቶች ግን ራሳቸውን የቻሉ ብዙ ዘመናት የሚፈጁና ለማስተማርም የተለያዩ ባለሙያ ዎች የሚያስፈልጉአቸው ስለሆነ እንዲሁ በቀላሉ በዚህ ተከታታይ የትምህርት መጽሐፍ ውስጥ ሊቀርቡ አልቻሉም።

በቅዳሴው ጸሎት ውስጥ የሕዝብ ተሳትፎ በጣም አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት የሕዝብ ተሰጥዎ እንደቀረበው ሁሉ የምህላ ጸሎት፣ ከሠርክ ጸሎት አንድ ክፍልና በሕማማት ሳምንት ተደጋግመው ከሚቀርቡት የስግደት ጸሎቶች መካከል ሕዝብ ሊያጠናቸው ይገባል ተብሎ የታመነባቸው ቀጥለው የቀረቡት ናቸው።

### በግዕዝ

#### ጸሎተ ምህላ

መሐረነ: አብ፣ ሃሌ ሉያ፣ ተሣሃለነ ወልድ፣ ሃሌ ሉያ፣ መንፈስ ቅዱስ መሐሪ ተዘከረነ በሣህልከ። (3 ጊዜ በል።)

ለከ ንፌኑ ስብሐተ ወለከ ናዐርግ አኰቴተ። – መሐረነ መሐሪ ኃጢአተነ አስተሥሪ፣ ወአድኅነነ ወተማኅፀን ነፍስነ ወሥጋነ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር፣ – አምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ተሣሃለነ። – በብዝኃ ምሕረትከ ደምስስ አበሳነ ወፈኑ ሣህለከ ላዕለነ። – እስመ እምኀቤከ ውእቱ ሣህል ሃሌ ሉያ መሐረነ አብ መሐሪ። – ወተሣሃለነ ሀብ ሣህለከ መሐሪ ኢታጠፍአነ ተዘኪረከ ዘትካት። – በምሕረትከ እስመ መሐሪ አንተ ወብዙኅ ሣህልከ ለኵሎሙ እለ ይጼውዑከ። – ይጼውዑከ በጽድቅ ሰማዒ ወትረ ከሃሊ ዘውስተ አድኅኖ። – ከሃሊ ዘውስተ አድኅኖ ለአምላክነ ጻድቅ እስመ ጽድቅ ቃሉ። – ንስአሎ ለአብ ይፈኑ ለነ ሣህሎ እስመ አብ የአክል ለዘሰአሎ። – ሃሌ ሉያ ስብሐት ሎቱ ይደሉ። ሃሌ ሉያ አኰቴት ሎቱ ይደሉ። ሃሌ ሉያ ለክርስቶስ ለእግዚእ ኵሉ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ። – ወይእዜኒ መኑ ተስፋየ አኮኑ እግዚአብሔር ውስተ እዴከ እግዚኦ አመኀፅን ነፍስየ። – ኀበ አምላከ ምሕረት አመኀፅን ነፍስየ ኀበ ንጉሠ ስብሐት አመኀ ፅን ነፍስ። በእግዚእየ ወአምላኪየ አመኀፅን ነፍስየ እምኵሉ ምግባረ እኩይ አድኅና ለነፍስየ። – ሀቡ ንስአሎ ንስአሎ ናስተምሕሮ ለአምላክነ ጻድቅ እስመ ድድቅ ቃሉ።–

ዘይክል ኵሎ ወአልቦ ዘይሰአኖ አምላክ ንጹያን ወተስፋ ቅቡፃን ንሕነ ኀቤከ ተማኅፀነ። (3 ጊዜ በል።)

ጸሎት ዘእምደረድ:- አድኅነነ ሕዝበከ፣ ወባርከ ርስተከ ሀበነ ኀይለ ወመዊዐ ለእግብርቲከ ለእለ ንጼውዕ ስመከ፣ ዕቀበነ ውሉደ ሕዝብከ፣ ወሕፅረነ በኃይለ መላእክቲከ ወትረ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት። በኀይለ መስቀልከ ርድአነ በዕፀ መስቀልከ ቤዝወነ።

በእንተ አብርሃም ፍቁርከ ወበእንተ ይስሐቅ ቍልዔከ ወበእንተ እስራኤል ቅዱስከ ተዘከረ እግዚኦ ኪዳነከ። ፍጡነ ፈኑ ሣህለከ መሐር ኪያነ ዘፈጠርከ። ሥረይ ኃጢአተ ሕዝብከ ወመሐር ተግባረከ እግዚኦ ኢታጥፍአነ ሐሰ ለከ።

በእንተ ማርያም ወላዲትከ ወበእንተ ዮሐንስ መጥምቅከ። ወበእንተ ኵሎሙ ቅዱሳኒከ ርድአነ ወትረ በኀይለ መስቀልከ፣ ኢታስተኃፍረነ እግዚኦ በቅድሜከ።

እግዝእትነ ነጽሪ ኀቤነ ጸሊ ለነ ለደቂቅኪ ወአድኅነነ እምኵሉ ምንዳቤ ወኀዘን።

መዐልተ ምስሌነ ወሌሊተ ማዕከሌነ አንተ እግዚኦ ኢትርኃቅ እምኔነ ሀሉ ምስሌነ ረዳኤ ኮነነ ኢትግድፈነ ወኢትመንነነ አምላክ ሰላም ተራድአነ።

ኢትግድፈነ ኢትግድፈነ ወኢትመንነነ አምላክ ለላም ተራድአነ (3 ጊዜ በል)።



እግዝእትነ እግዝእትነ ነጽሪ ኀቤነ ሰላመ ወልድኪ የሀሉ ምስሌነ (3ጊዜ በል)

እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ።

እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ።

እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ

### በአማርኛ

የምህላ ጸሎት:-

አብ ሆይ ማረን፤ ሃሌ ሉያ፤ ወልድ ሆይ ይቅር በለን፤ ሃሌ ሉያ፤ ይቅር ባይ መንፈስ ቅዱስ ሆይ በይቅርታህ አስበን። (3ጊዜ በል)

ለአንተ ፍጹም ምስጋናን እናቀርባለን። ቸር ይቅር ባይ ሆይ ማረን፤ ኃጢአታችንን አስተሥርይልን፤ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ አድነን በነፍስ በሥጋም ጠብቀን። አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ይቅር በለን። በቸርነትህ ብዛት በደላችንን ደምስስ ይቅርታህንም ላክልን። ይቅርታ ከንተ ዘንድ ነውና፤ ሃሌ ሉያ ይቅር ባይ አብ ሆይ ማረን። ይቅር በለን። መሐሪ የሆንህ አቤቱ ይቅርታህን ስጠን፤ የቀድሞ ኃጢአታችንንም አስበህ አታጥፋን። በቸርነትህ አንተ ይቅር ባይ ነህና፤ ለሚጠሩህ ለሚለምኑህ ሁሉ ይቅርታህ ብዙ ነው። በአውነት ይጠሩሃል፤ ለሚጠሩህ ለሚለምኑህ ሁሉ ይቅርታህ ብዙ ነው። በእውነት ይጠሩሃል፤ አንተም ዘወትር ትሰማለህ፤ ሁሉን ለማድረግ የምትችል ነህ። ሁሉን ለማድረግ የሚችል አምላካችን ቃሉ እውነት ነውና። ይቅርታውን ይልክልን ዘንድ አብን እንለምነው፤ አብ ለለመነው ሁሉ ይበቃልና። ሃሌ ሉያ ለርሱ ምስጋና ይገባል፤ ሃሌ ሉያ ለርሱ ክብር ምስጋና ይገባል። ሃሌ ሉያ ለሁሉ ጌታ ለክርስቶስ፤ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ። ዛሬስ ተስፋዬ ማነው እግዚአብሔር አይደለምን? አቤቱ ነፍሴን ላንተ ዐደራ አስጠብቃለሁ። ከምሕረት አምላክ ዘንድ ነፍሴን አደራ አስጠብቃለሁ ፤ ከምስጋና አምላክ ዘንድ ነፍሴን ዐደራ አስጠብቃለሁ። በጌታዬና በአምላኬ ነፍሴን ዐደራ አስጠብቃለሁ፤ ከክፉ ሥራ ሁሉ ነፍሴን (ሰውነቴን) አድናት። ኑ እንለምነው ፤ እንለምንው እንማልደው፤ የአምላካችን ቃሉ እውነት ነውና።

ሁሉን የሚችል የሚሳነውም የሌለ እርሱ ነው፤ የድኾች አምላክ ተስፋ ላጡ ተስፋቸው የምትሆን አቤቱ እኛ ወዳንተ ተማጥነናል (3ጊዜ በል)።

### ከያሬድ የዜማ መጽሐፍ የተቀዳ ጸሎት:-

እኛን ወገኖችህን አድነን፤ የጥንት ተገዦችህንምም ባርከን፤ ስምህን ለምንጠራ ለኛ ለአገልጋዮችህ ድል መንሣትንና ኃይልን ስጠን። የወገኖችህን ልጆች እኛን ጠብቀን፤ በየጊዜውና በየሰዓቱ በመላእክት ታዳጊነት በውስጥ በአፍአ ጠብቀን። በመስቀልህ ታዳጊነት እርዳን። በመስቀልህ ተቤዠን። ስለ ባለሟልህ ስለ አብርሃም፤ ስለ ወዳጅህ ስለ ይስሐቅ፤ ስለ መረጥከው ስለ እስራኤል አቤቱ ቃል ኪዳንህን አስብ። ይቅርታህን ፈጥነህ ላክ፤ የፈጠርከን እኛን ማረን። የወገኖችህንም ኃጢአት አስተሥርይ፤ የእጅህን ፍጥረቶች እኛን ማረን፤ አቤቱ አታጥፋን፤ ይህ በአንተ ዘንድ አይደረግ። በእናትህ በማርያም አማላጅነት፤ በአጥማቂህ በዮሐንስና በቅዱሳንህም ሁሉ አማላጅነት ሁል ጊዜ በመስቀልህ ታዳጊነት እርዳን፤ አቤቱ በፊትህ አታሳፍረን። እመቤታችን ሆ ወደኛ ተመልከቺ፤ ለኛ ለልጆችሽ ለምኚልን፤ ከችግርና ከሐዘን ሁሉ አድኚን።

ቀን ከኛ ጋር ሌሊትም በመካከላችን ሁን። አቤቱ አንተ ከእኛ አትለይ። ከኛ ጋራ ኑር፤ ረዳትም ሁነን፤ አትተወን አትናቀንም፤ የሰላም አምላክ ሆይ ተራዳን።

አትተወን አትተወን አትናቀንም የሰላም አምላክ ሆይ ተራዳን (3ጊዜ በል)።

እመቤታችን ሆይ እመቤታችን ሆይ ወደኛ ተመልከቺ፤ የልጅሽም ሰላም በኛ ላይ አድሮ ይኑር (3 ጊዜ በል)።

አቤቱ ክርስቶስ ማረን።

አቤቱ ክርስቶስ ማረን።

አቤቱ ክርስቶስ ማረን።

www.ethiopianorthodox.org

## የሰሙነ ሕማማት የስግደት ጸሎት

ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወፅዘዝ ለዓለመ ዓለም፤

አማኑኤል አምላኪየ ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወፅዘዝ ለዓለመ ዓለም

ኃይልየ ወፀወንየ ውእቱ እግዚእየ እብል በአኰቴት።

– 111–

ለአምላክ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወፅዘዝ ለዓለመ ዓለም

ለሥሉስ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወፅዘዝ ለዓለመ ዓለም

ለማሕየዊ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወፅዘዝ ለዓለመ ዓለም

ለፅዘዙ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወፅዘዝ ለዓለመ ዓለም

ለመንግሥቱ ደሉ ክብር ወስብሐት ወፅዘዝ ለዓለመ ዓለም

ለኢየሱስ ይደሉ ክብር ስብሐት ወፅዘዝ ለዓለመ ዓለም

ለክርስቶስ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወፅዘዝ ለዓለመ ዓለም

ለሕማሙ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወፅዘዝ ለዓለመ ዓለም

ለመስቀሉ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወፅዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለከ ይደሉ ኃይል፤ ለከ ይደሉ ስብሐት ወለከ ይደሉ አኰቴት ኦእግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለመ ዓለም።

ክርስቶስ አምላክነ ዘመጽአ ወሐመ በእንቲአነ በሕማማቲሁ ቤዘወነ። ንስብሐ ወናልዕል ስሞ ኅቡረ እስመ ውእቱ ገብረ መድኃኒተ በብዝኃ ሣህሉ።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን፤ ታዖስ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ማስያስ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን፤ ክርስቶስ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን፤ አማኑኤል ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን፤ ትስቡጣ ናይናን ኪርያላሶን።

ከምስባክ አስቀድሞ ቄሱ ጥቁር ልብስ ለብሶ ከቤተ መቅደስ ገብቶ በሐዘን ዜማ ድምፁን አስምቶ እንዲህ ይበል።

ይካ. አምንስቲቲ ሙኪርያ አንቲ ፋሲልያሱ።

ይሕ. አምንስቲቲ ሙኪርያ አንቲ ፋሲልያሱ።

ይካ. አምንስቲቲ ሙዓግያ አንቲ ፋሲልያሱ።

ይሕ. አምንስቲቲ ሙዓግያ አንቲ ፋሲልያሱ።

ይካ. አምንስቲቲ ሙዳሱጣ አንቲ ፋሲልያሱ።

ይሕ. አምንስቲቲ ሙዳሱጣ አንቲ ፋሲልያሱ።

ትእ. ከዚያ ቀጥሎ ካህን ወይም ሌላ አንባቢ በውርድ ንባብ ዜማ ከዚህ በታች ያለውን ያንብብ።

ይካ. አስበን አቤቱ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ።

አስበን አቤቱ ቅዱስ ሆይ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ።

አስበን አቤቱ አስታራቂያችን ሆይ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ።



## ጥያቄዎች

1. የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን በሰባቱ አብያተ ክርስቲያን ትርጓሜ ላይ የሚለያዩት እንዴት ነው?
2. የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን በማንኛው ዘመን ትመሰላለች?
3. ኤፌሶን የሚለው ቃል ትርጉም ምንን ያመለክታል?
4. የመጀመሪያው የኤፌሶን ኤጲስ ቆጶስ ማን ነበር?
5. የሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን በማንኛው ዘመን ትመሰላለች?
6. የሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን ለምን ሳትወቀስ ቀረች?
7. የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን በማንኛው ዘመን ትመሰላለች?
8. በዚያ ዘመን ብዙ ግፎች የተሠሩት በምን ምክንያት ነው?
9. ያቺ ዘመን ግን ምንን አስተላለፋልናለች?
10. የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን በማንኛው ዘመን ትመሰላለች?
11. ያ ዘመን ምን ዐይነት ዘመን ነበር?
12. የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን በማንኛው ዘመን ትመሰላለች
13. ዘመኑ ምን የመሰለ ዘመን ነበር?
14. የፊላዴልፊያ ቤ/ክ በማንኛው ዘመን ትመሰላለች?
15. የዚያስ ዘመን ሁናቴ እንዴት ነው?
16. የሎዶቅያ ቤተ/ክ በማንኛው ዘመን ትመሰላለች?
17. መጥምቁ ዮሐንስ ወደ ምድረ በዳ የሄደው መቼ ነው?
18. ዮሐንስ መጥምቁ ወደ ምድረ በዳ የተወሰደባቸውን ሁለት የተለያዩ ታሪኮች ተርክ።
19. ዘካርያስ እንዴትና ለምን ተገደለ?
20. የእርሱ አሟሟት ምን ከሚለው የጌታችን አባባል ጋር የተያያዘ ነው?
21. ዮሐንስ መጥምቁ ከምድረ በዳ የመጣው መቼ ነው?
22. የመጣውስ ምን ለማድረግ ነው?
23. መጥምቁ ዮሐንስ በሕዝብ ፊት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ያከበረው ምን ብሎ ነው?
24. ሄሮድስ ዮሐንስን ያሳሰረው ለምን ነበር?
25. ገባሬ ተአምር ቅዱስ ጎርጎርዮስ የተወለደው ከእንዴት ያለ ቤተሰብ ነው?
26. ጎርጎርዮስን ስለ ክርስትና ሃይማኖት ያስተማረው ማነው?
27. ጎርጎርዮስ ሸሽቶ ወደ ምድረ በዳ የሄደው በምን ምክንያት ነው?
28. ሕዝቡ ተሰብስበው ሳሉ ስለ ጎርጎርዮስ ምን የሚል ድምፅ ሰሙ?
29. ጎርጎርዮስ የተሾመው እንዴት ነው? የሾመውስ ማነው?
30. የእግዚአብሔር መልአክ ለገባሬ ተአምር ጎርጎርዮስ ምን አለው?
31. እርሱ ከዚህ ዓለም በተለየ ጊዜ ከአገሩ ሕዝብ ክርስቲያን ያልሆነ ዐሥራ ሰባት ብቻ መቅረቱ ምንን ያመለክታል?
33. በቂሣርያ ያደረገው ተአምር ምን ነበር?
34. የቅዱስ ባስልዮስ ወንድም ጎርጎርዮስ ሀገረ ስብከት ምን ይባል ነበር?
35. ማንኛው ንጉሥ ነው ወደ ግዞት የላከው? በኋላስ የፈታው ንጉሥ ማነው?
36. በማንኛው ሲኖዶስ ላይ ነው የተገኘው?
37. ለማንኞቹ የኑፋቄ ትምህርቶች ነው መልስ የሰጠባቸው?
38. ቅዳሴ ሲቀድስ ምን ያይ ነበር ይባላል?
39. በኤጲስ ቆጶስነት ስንት ዘመን ኖረ?
40. ወንድሙ ቅዱስ ባስልዮስ ሊጠይቀው ሲመጣ ከምን የተነሣ ታምሞ ነበር?
41. እመቤታችን ድንግል ማርያም በቅዳሴ መካከል በራእይ ተገልጣ ምን ነገረችው?
42. ዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ በምን ምክንያት መጡ?
43. የመጡትስ በማን ዘመን ነው?

www.ethiopianorthodox.org

44. በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተወዳጅነትንና ተሰሚነትን ያገኙት በምን ምክንያት ነው?
45. ዘጠኙ ቅዱሳን ያከናወኑአቸው መንፈሳውያት ተግባራት ምን ምን ናቸው?
46. ከእነርሱ መካከል የምንኵስናን ትምህርትና ሥርዓት በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ ያደረገ ማነው?
47. የእነርሱን ትምህርት አጥብቆ በመከተል ወደ ገዳም የገቡ ነገሥታት ማንና ማን ናቸው?
48. በአባ ጰንጠሌዎን የተደረጉትን ተአምራት ተናገር።
49.በአባ ገሪማ የተደረጉትን ተአምራት ተናገር።
50. በአባ አረጋዊ የተደረጉትን ተአምራት ተናገር።

# ምዕራፍ 5

# መንፈሳዊነትና ገብረ ገብነት

## ተገቢ በሆነ መንገድ በችሎታ መጠቀም

ቀደም ተብሎ በአምስተኛ ክፍል መጽሐፍ በምዕራፍ 1 ላይ እንደተገ ለጠው እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተለያዩ ስጦታዎችን ሰጥቶአቸዋል፤ ይሰጣቸዋልም። እነዚህም ስጦታዎች አንድን ድርጊት የማድረግ ወይም ያለማ ድረግ ችሎታዎች ናቸው። እነዚህን ችሎታዎች አግባብ ለሆነ ጉዳይ ወይም አግባብ በሆነ መንገድ እንድናውላቸው በእግዚአብሔርና በኅብረተሰቡ ዘንድ ይጠበቅብናል።

አንድ ሰው በእግዚአብሔር እርዳታ አዳዲስ ነገሮችን የመፈልሰፍ ችሎታ ኖሮት ለሰው ልጆች ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን በመፈልሰፍ ፈንታ ለሰው ልጆች ጉጂ የሆኑ ነገሮችን ቢፈለስፍ እግዚአብሔር የሰጠውን ችሎታ በተገቢው መንገድ አልተጠቀመበትም ማለት ነው። የሰው ልጆችን የሚጐዳ ነገር መፈል ሰፍ ደግሞ ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌለው ሰው መሆን ነው። ቃለ እግዚአብሔር ግን «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው» ይላል (ምሳ:ም:1 ቊ:7)። እንዲያውም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ:- «የዚህ ዓለም ጥበብ በእግዚ አብሔር ፊት ሞኝነት ነው» ይላል (1ኛ:ቆሮ:ም:3ቊ:19)።

ሌላ ምሳሌ ደግሞ አንድ ሰው የተሙአላ ጤንነትና ጉልበት ያለው ቢሆንና ያን ጉልበቱን በሥራ ላይ አውሎት በሚያገኘው ገቢ ሕይወቱን ከመምራት ይልቅ ሰውን ለማጥቂያና የሰውን ሀብት ለመዝረፊያ ቢያውለው ያን ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ጤንነትና ጉልበት በአግባቡ አልተጠቀመበትም ማለት ነው። ቅዱስ መጽሐፍ ግን የሚያዝዘን የማንንም ሀብት አትውሰድ ብሎ ብቻ ሳይሆን እንዲያውም የሌላ ሰው የሆነውን ማንኛውንም ነገር አትመኝ ብሎ ነው (ዘጸ:ም:20 ቊ:17) ። ሌላው ቅዱስ መጽሐፍ የሚያስጠነቅቀን ደግሞ ጠቢብ በጥበቡ፥ ኃያልም በኀይሉ ሳይሆን በእኔ ይመካ ብሎ ነው (ኤር:ም:9 ቊ:23–24)። የሰው ኀይሉ ከንቱ መሆኑንና ኀይል የእግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ለማመልከት ነው የጦር መሣሪያ የያዘው ትልቁ ጎልያድ የበግ እረኛ በነበረው ብላቴና በዳዊት በተወነጨፈ ድንጋይ የተገደለው። ለዚህም የዳዊትን የእምነት ምስክርነት እንመልከት:-

«አንተ ሰይፍ፥ ጦርና ሾተል ይዘህ መጥተህብኛል፤ እኔ ደግሞ አንተ በምትገዳደረው በእስራኤል ሠራዊት አምላክ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ፤ በዚህች ቀን እግዚአብሔር አንተን በእጄ ይጥልልኛል» (1ኛ:ሳሙ:ም:17 ቊ:45–46)።

እንደገና ሌላ ምሳሌ ደግሞ እግዚአብሔር የንግግር ችሎታን የሰጠው ሰው ቢኖርና ያን ችሎታውን ለሰው የሚጠቅም ትምህርት ሰጪ መግለጫ ከሚሰጥበት ይልቅ በሌላ ሰው ላይ በማፌዝ መሳቂያና መሳለቂያ ካደረገው ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ችሎታ በተገቢ መንገድ አልተጠቀመበትም ማለት ነው። ቅዱስ መጽሐፍ በዚህ ጉዳይ ላይ ምን እንደሚል እንመልከት:-



www.ethiopianorthodox.org

«በእውነት እላችኋለሁ፥ ሰዎች በግዴለሽነት በሚናገሩት በያንዳንዱ ቃል በፍርድ ቀን ይጠየቁበታል፥ ከቃልህ የተነሣ ይፈረድብሃል፤ ከቃልህም የተነሣ ይፈረድልሃልና» (ማቴ: ም:12 ቊ:36–37)።

«ከቶ ከአፋችሁ ክፉ ቃል አይውጣ፤ ነገር ግን ለሚሰሙት ጸጋን የሚሰጥና ለማነጽ የሚጠቅም፥ ለሰዎችም አስፈላጊ የሆነውን ቃል ተናገሩ» (ኤፌ: ም:4 ቊ:29)።

እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረው ጊዜ የፈቃድና የፍላጎት ነጻነትን ሰጥቶታል። ይሁን እንጂ ጉጂና ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን ለይቶ እንዲያውቅ ያደረገው ያን ፍሬ ብትበላ ትሞታለህ፤ ባትበላ ግን አትሞትም ብሎ ነው። ሰው ግን የፈቃድና የፍላጎት ነጻነት ተሰጥቶት በነበረው የመምረጥ ችሎታ ፍሬዋን በልቶ መሞትን ስለመረጠ ችሎታውን በተገቢ መንገድ ሳይጠቀምበት ቀረ። በዚህም ምክንያት በሰው ዘር ሁሉ ላይ የሞትን ፍዳ አመጣ። በተመሳሳይ ሁኔታ ለሁላችንም የሕይወትና የሞት ምርጫ በፊታችን ቀርበውልናል። ብዙዎቻችን ግን ሟቹ ሥጋችን እየሳበን አግባብ ባልሆነ መንገድ ሞትን መርጠን ወደ ዘለዓለማዊው የሙታን ዓለም እንሄዳለን። ይህ ሊሆን የቻለው በምን ምክንያት ነው? ይህ ሊሆን የቻለው አድርግ ወይም አታድርግ የሚሉትን የእግዚአ ብሔርን ትእዛዞች በማክበር ፈንታ በተቃራኒ መንገድ የሚመራውን የሰይጣንን መንገድ ስለምንከተል ነው።

## ሰውን እንደ ሰውነቱ ማየት

ሰውን እንደ ሰውነቱ ማየት በሚባልበት ጊዜ ለተለያዩ ጉዳዮች ሰዎች ሁሉ እኩል መብት ያላቸው እንጂ የተለያዩ ሰዎች በሀብታቸው፥ በሹመታቸው፥ በኑሮ ደረጃቸው፥ ወይም በትውልዳቸው ምክንያት የተለየ አስተያየት ሊደረግላቸው ወይም ሊደረግባቸው የማይገባ መሆኑን ለማመልከት ነው። ለምሳሌ ሁለት ሰዎች በአንድ ጉዳይ ላይ ሳይስማሙ ቀርተው ወደ ፍርድ ቤት ወይም ወደ አስታራቂ ሽማግሌ በሚሄዱበት ጊዜ ዳኛውም ሆነ አስታራቂው የጉዳዩን አካሄድ መርምሮ አስተማማኝ በሆነው ማስረጃ መሠረት ይፍረድ እንጂ ትክክለኛነቱ አስተማማኝ ባልሆነ ማስረጃ፥ ወይም የተከራካ ሪዎቹን የኑሮ ደረጃ፥ በኅብረተሰቡ ዘንድ ያላቸው የሥልጣን እርከን፥ ከዳኛው ወይም ከአስታራቂው ጋር ያላቸው ዝምድና ወይም ሌላ ግንኙነት ለፍርዱ ውሳኔ መሠረት መሆን የለበትም። ምናልባት ሁለቱ ተከራካሪዎች በኑሮ ደረጃ ቸው ለፍርዱ... ከፍና ዝቅ ያሉ ቢሆኑና በዕድሜ ልዩነት የሌላቸው ቢሆኑ በዚሁ በኑሮ ደረጃቸው የተለያዩ በመሆናቸው ብቻ ዳኝነት ወይም ሽምግልና የተቀመጡት ሰዎች ሀብታሙን እርስዎ ሲሉ ድኻውን አንተ ሊሉት አግባብ አይደለም። ወይም ደግሞ ለአቀማመጣቸው የተለያየ የክብር ደረጃ ሊሰጣቸው አይገባም። እንዲሁም በዳኛውም ሆነ በአስታራቂው ሽማግሌ ለተከራካሪዎቹ ጥያቄ በሚቀርብ ጊዜ የሁሉንም መልስ በጥሞና ማዳመጥ እንጂ አንዱን አዳምጦ ለሌላው መልስም ሆነ መግለጫ ትኵረት አለመስጠት አድላዊነት ይሆናል። ይህም ሰውን እንደ ሰውነቱ አለመመልከት ነው። በፍርድ አድልዎ ማድረግ እንደማይገባ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሉትን እንመልከት:-

«የፍርድ ውሳኔ በምትሰጥበት ጊዜ ታማኝና ትክክለኛ ሁን፤ ለሁሉም በትክክል ፍረድ እንጂ ድኻውን ስለ ድኽነቱ አድልዎ አታድርግለት፤ ባለጸጋውንም ስለ ሀብቱ ብዛት አትፍ ራው» (ዘሌ;ም:19 ቊ:15)።

«በሕዝባችሁ መካከል የሚነሣውን የጠብና የክርክር አቤቱታ አድምጡ፤ በራሳችሁ ሕዝብ ወይም በእናንተ ውስጥ በሚኖሩት መጻተኞች መካከል ስለሚነሣው ጠብና ክርክር ሁሉ በትክክል ፍረዱ። በምትሰጡትም ውሳኔ አድልዎ አታድርጉ፤ ስለማንኛውም ታላቅም ሆነ ታናሽ ሰው ያለ አድልዎ በእኩልነት ደረጃ ፍረዱ» (ዘዳ: ም:1 ቊ:16–17)።

«በምታደርገው ነገር ሁሉ አንዱን ከሌላው ሳታበላልጥ ወይም ለማንም ሳታዳላ ይህን ምክሬን ሁሉ እንድትፈጽም በእግዚአብሔርና በኢየሱስ ክርስቶስ በተመረጡትም መላእክት ፊት ዐደራ እልሃለሁ» (1ኛ:ጢሞ:ም:5 ቊ:21)።

እግዚአብሔር አምላክ አስቀድሞ ነቢያትን በመረጠ ጊዜ እንደ ኢሳይያስ ያሉትን የነገሥታት ዘሮች ብቻ የመረጠ ሳይሆን እንደ አሞጽ ያለውንም የበግ እረኛ መርጦአል። ይህም የሚያመለክተው እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ የሚመለከተው እንደ ሰውነቱ እንጂ በኅብረተሰቡ ዘንድ ባለው ግምት አለመሆኑን ያመለክታል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን በመረጠ ጊዜ በአብዛኛው ድኾችንና ተራ ሰዎችን የመረጠ መሆኑ ተስተውሎአል። እንደ ናትናኤል ያሉ ተንኰል የሌለባቸውን ሰዎች ብቻ ሳይሆን አሳልፎ የሰጠውን ይሁዳን መርጦአል። ይህንንም ያደረገው ሰውን በሰውነቱ ብቻ መመልከት እንደሚገባን ሲያመለክተን ነው።

የተለያዩ አገልግሎቶችን ለሰዎች በምናቀርብበት ጊዜ ሰውን በሰውነቱ እንጂ በሌላ መልክ ማየት የለብንም። ቃለ እግዚአብሔርን መማር የሚያስፈ ልጋቸው ሰዎች ሁሉ እንጂ የተለዩ ወገኖች ብቻ አይደሉም። እርዳታ ሊደረግ ላቸው የሚገባው ለተቸገሩ ሰዎች ሁሉ እንጂ ለተለዩና ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ አይደለም። ማንኛውም መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጣቸው ያ አገልግሎት ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ እንጂ ለተለዩና ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ አይደለም።

በእግዚአብሔር ዘንድ ከሰው ሰው፥ ከዘር ዘር ልዩነት የሌለ መሆኑን ከሚያ ረጋግጡት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

«እንግዲህ አንዱ ጌታ የሁሉም ጌታ ስለሆነ በአይሁዳዊና በአረማዊ መካከል ልዩነት የለም» (ሮሜ: ም:10 ቍ:12)።

«ሁላችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ስለሆናችሁ በአይሁዳዊና በግሪካዊ፥ በአገልጋይና በጌታ፥ በወንድና በሴት መካከል ምንም ልዩነት የለም» (ገላ: ም:3 ቍ:28)።

## ፈተና ሲያጋጥም በእግዚአብሔር መታመን

አንድ ሰው አንድ ዐይነት ችግር፥ መከራ፥ ጭንቀትና ሌሎችም የሕይወት ፈተናዎች ሲያጋጥሙት መፍትሔ ሊያገኝ የሚችለው እምነቱን በእግዚአ ብሔር ላይ በማሳረፍ ብቻ ነው። ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ደግሞ ማንኛውም ነገር አይሆንም፥ አይደረግም፤ አይፈጸምም። ስለዚህ ነው ነቢዩ ዳዊት እግዚአ ብሔር ቤትን ካልሠራና ከተማን ካልጠበቀ፥ ግንበኞችና ጠባቂዎች በከንቱ ይደክማሉ ያለው (መዝ: 127 ቍ:1)።

ችግሮች በሰው ላይ የሚደርሱት አንድም ለቅጣት ነው፤ ወይም ለፈተና ነው። በጸሎታችን ውስጥ ወደ ፈተና አታግባን፤ በደላችንን ይቅር በልልን ብለን የምንጸልየው በዚሁ ምክንያት ነው።

እግዚአብሔርም ከተማመኑበት ከብዙ ችግርና ጭንቀት ያወጣል። ለምሳሌ ነቢዩ ዳዊት ግዙፍ የነበረውን ፍልስጥኤማዊውን ጎልያድን እንደ ቀላል ነገር በወንጭፍ የገደለው በዚህች ቀን እግዚአብሔር አንተን በእጄ ይጥልልኛል ብሎ እምነቱን በእግዚአብሔር ላይ ስላሳረፈ ነው (1ኛ: ሳሙ: ም:17 :ቍ:46)።

ሌላው በእግዚአብሔር የመታመን ምሳሌ ደግሞ ሦስቱ ወጣቶች ናቸው። ንጉሥ ናቡከደነፆር ሕዝቡ ሁሉ እንዲሰግድለት ጣዖት ባሠራ ጊዜ ሦስቱ ወጣቶች ለጣዖቱ ላለመስገድ የወሰኑት እንዲህ በማለት ነው:- «እኛ የምናገለግለው እምላክ ከዚህ ከሚነድደው ከእሳት ነበልባልም ሆነ ከአንተ እጅ ሊያድነን ይችላል» (ዳን:ም:3 ቍ:17)።

ይህን ተናግረው በንጉሡ ትእዛዝ ወደ እሳት ውስጥ ቢጣሉም በእግዚአብሔር ላይ ባላቸው ጠንካራ እምነት ምክንያት እሳቱ ምንም ሳይጐዳቸው ስለወጡ አምላካቸውን አስከብረዋል።

እንደገና ሌላ ምሳሌ ደግሞ ነቢዩ ዳንኤል ነው። ዳንኤል በንጉሥ ዳርዮስ ዘንድ በጣም የታመነና የተከበረ ስለነበረ መኳንንቱ ቀንተውበት አምልኮ እግዚ አብሔርን በተመለከተ ተከስሶ በአንበሳ ጕድጓድ ውስጥ እንዲጣል አድርገውት ነበር። እግዚአብሔር ግን የአንበሶቹን አፍ ዘግቶለት ምንም ሳይደርስበት ስለቀረ ንጉሡ እጅግ ደስ አለው፥ ዳንኤልንም ከጕድጓድ ውስጥ



www.ethiopianorthodox.org

እንዲያወጡት ትእዛዝ ሰጠ፤ ባወጡትም ጊዜ በእግዚአብሔር በመታመኑ በሰውነቱ ላይ ምንም ጉዳት እንዳልደረሰበት ታወቀ (ዳን: ም:6)።

በእግዚብሔር መታመንን በተመለከተ ከሚቀርቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

«ሕዝቅያስ በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ተማመነ፤ ከእርሱም በፊት፥ ከእርሱም በኋላ ከነበሩት ከይሁዳ ነገሥታት ሁሉ እርሱን የሚመስል ሌላ ንጉሥ አልተነሣም» (2ኛ: ነገ:ም:18 ቍ:5)።

«መንገድህን ለእግዚአብሔር ዐደራ ስጥ በእርሱሙም ታመን እርሱም ያደርግልሃል» (መዝ:37ቍ5)።

«በእግዚአብሔር የታመኑ እንደማይታወክ፥ ለዘለዓለም እንደሚኖር እንደ ጽዮን ተራራ ናቸው» (መዝ:125 ቍ:1)።

«በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን እንጂ በራስህ ማስተዋል አትደገፍ» (ምሳ:ም:3 ቍ:5)።

«በእኔ ብቻ ተማምኖ የሚኖር ሰው ግን የተባረከ ነው። እርሱም በወራጅ ምንጭ አጠገብ እንደተተከለና በውሃም ውስጥ ሥር እንደሰደደ ዛፍ ይሆናል፤ ዘወትር ቅጠሉ ለምለም ሆኖ የሚኖር ይህ ዐይነቱ ዛፍ የፀሐይ ሐሩር እንኳ አያሰጋውም፤ ዝናብ ባይዘንብለትም እንኳ ፍሬ ከማፍራት አይገታም» (ኤር:ም:17 ቍ:7–8)።

## ጥያቄያዎች

1. እግዚአብሔር የሰጠንን ችሎታዎች ምን እንድናደርጋቸው ነው በእግዚአብሔርና በኅብረተሰቡ ዘንድ የሚጠበቅብን?
2. አንድ ሰው እግዚአብሔር በሰጠው ችሎታ ደግ ነገርን ትቶ ክፉ ነገርን ቢፈለስፍ ምን አለማድረጉ ነው?
3. በምሳሌ የቀረበው ጤንነትና ጉልበት ያለው ሰው በምን ሁለት ዐይነት ሁናቴ ቀረበ?
4. የንግግር ችሎታ ያለው ሰውስ በምን ሁለት ዐይነት ሁኔታ ቀረበ?
5. አዳም የተከለከለውን ፍሬ በመብላቱ ምን አደረገ?
6. የቀረቡልን ሁለት ነገሮች ምንና ምን ናቸው?
7. ሰውን እንደ ሰውነቱ ማየት ሲባል ምን ማለት ነው?
8. የፍርድ ውሳኔ በምን መሠረት መሆን አለበት?
9. እግዚአብሔር ነቢያትን በመረጠ ጊዜ አመራረጡ እንዴት ነበር?
10. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን በመረጠ ጊዜ አመራረጡ እንዴት ነበር?
11. ፈተና ሲገጥማቸው በእግዚአብሔር ስለታመኑ እግዚአብሔር የረዳቸውን ሰዎች ታሪክ ዘርዝር።

# ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል

## ምዕራፍ 1

## ትምህርተ ሃይማኖት

### የእግዚአብሔር ህልውና

ከትምህርተ መለኮት ምሁራን አንዱ እንዳለው:- ይህ ዓለም አንድም ዘለዓለማዊ ነው፤ ወይም በአንድ በተወሰነ ጊዜ የተገኘ ነው። ዓለም ግን ተለዋዋጭ ስለሆነ ዘለዓለማዊ ሊሆን አይችልም። መለወጥ ደግሞ የነበረበትን ሁናቴ ማጥፋት ስለሆነ ይህ ዓለም በአንድ በተወሰነ ጊዜ የተገኘ እንጂ ዘለዓለማዊ አለመሆኑን ያመክታል። እንግዲህ ይህ ዓለም ዘለዓለማዊ ካልሆነና በአንድ በተወሰነ ጊዜ የተገኘ ከሆነ አንድ አስገኚ አለው ማለት ነው።

ከፈላስፎች አንዱ እንዳለው አንድ ድርጊት ወይም ፍጥረት የግድ አድራጊ ወይም ፈጣሪ አለው። ያለ አድራጊ ድርጊት ያለ ፈጣሪ ፍጡር ከቶ ሊኖር አይችልም። ይህም ዓለም በአንድ በኩል ተለዋዋጭ በመሆኑ፥ በሌላ በኩል ደግሞ የሚታይና የሚዳሰስ በመሆኑ የተፈጠረ መሆኑ ግልጥ ነው። ሊዳሰስና በሕዋሳት አመካይነት ሊታወቅ የሚችል ቁሳዊ ነገር ሁሉ የተሠራ ወይም የተፈጠረ ነው።

ይህን ዓለም ያስገኘ የግድ ከኀይላት ሁሉ የላቀ ኀያል፥ ከሁሉ የበለጠ ጥበበኛ መሆን አለበት።

ይህ ይህን ዓለም ያስገኘ ወይም እግዚአብሔር ራሱን እንዳስገኘና እርሱ ያልነበረበት ጊዜ እንደነበረ ማሰብ ከንቱ አስተሳሰብ ነው። እግዚአብሔር መነሻ ወይም መጀመሪያ ያልነበረው ዘለዓለማዊ ነው። ፍጥረትን ሁሉ ከምንም የፈጠረ እርሱ ነው። አፈጣጠሩም ከምንም ነው እንጂ ቀድሞ ከነበረ ቁስ አካል በመነሣት አይደለም። ፍጥረቶችም ለዘለዓለም በሐሳቡ ነበሩና በየዐይነታቸው እንዲፈጠሩ እርሱ የፈቀደላቸው ናቸው።

ስለ እግዚአብሔር ህላዌ ማስረጃ ከሚቀርብባቸው አርእስት መካከል:- የፍጥረቱ ሥነ ሥርዓታዊ አሠራር፥ የኅሊና ምስክርነት፥ በተፈጠሮ ዝንባሌ የዓለም ሕዝብ መስማማትና፥ የመጽሐፍ ቅዱስና የታሪክ ማስረጃዎች ይገኙባቸዋል።

<u>የፍጥረቱ ሥነ ሥርዓታዊ አሠራር:-</u> እግዚአብሔር ነጻነትን ሰጣቸው እንጂ ሰዎች እንዲያውቁት ያደረገው በቅዱሳት መጻሕፍት አማካይነት ብቻ አይደለም፤ ህልውናውንና ባሕርያቱን እንዲያውቁም አላስገደዳቸውም፤ ነገር ግን ሰው ሁሉ የፈለገውን እምነት እንዲከተል የፈቃድና የፍላጎት ነጻነትን ሰጠ። ድርጊት ያለ አድራጊ፥ ስሜት ያለ ምክንያት ስለማይኖር የዐዋቂነቱን፥ የኀያልነቱንና የደግነት ባሕርዩን ምልክቶች በማሳየት ህልውናውን ገለጠ።

ለምሳሌ በአስደናቂ ሁኔታ ትልቅና በአሠራሩም ዐይንን የሚማርክ ሆኖ የተሠራ አንድ ቤት በምናይበት ጊዜ ያን ቤት የሠራ መሐንዲስ ብልኀና ጐበዝ መሆኑና ያንንም ቤት ለአንድ ዓላማ የሠራው መሆኑ ወደ ሐሳባችን አይመጣምን? የአሠራሩንም ትክክለኛነትና አስደናቂነት በምናይበት ጊዜ እንደዚህ አስተካክሎ ለመሥራት መሣሪያዎች ያሉት ብልኅ ሰው መሆን አለበት ማለታችን አይቀርም። ይህን መሣሪያም የሠራ ታላቅ ዕውቀት ያለው ሰው መሆን አለበት ብለን በሐሳባችን እንወስናለን? ወይስ ያ መሣሪያና ያ ሥራ በአጋጣሚ የተገኘ እንደሆነ እንገምታለን? አእምሮአችንስ እንዲህ ያለውን አስተሳሰብ ይቀበለዋልን? የሰው አእምሮ አንድ የተሠራ ሥራ ባየ ጊዜ ለዚያ ሥራ ሠሪ እንዳለው በፍጥነት ወደ ሐሳቡ ይመጣል።

እንግዲህ በትልቁ ቤት አሠራርና በመሣሪያው ጉዳይ አንድ ብልኅና አስተዋይ ሠሪ ያለ መሆኑ የሰው አእምሮ የሚገምት ከሆነ አእምሮ ሊረዳውና እንደበት ሊያብራራ የማይችለውን የዚህን ዓለም አስደናቂ አፈጣጠር በሚመለከትበት ጊዜ ሰው የእግዚአብሔርን ህልውና ሊያረጋግጥ አይችልምን?

የዓለም ፍጥረትም በሥርዓት የሚመራው በእግዚአብሔር መሪነት እንጂ አንዳንዶች እንደሚሉት በአጋጣሚ አለመሆኑን እርግጠኞች እንሁን።



በሰውነታችን ውስጥ ያሉትን የአካል ክፍሎች አዘገጃጀት፤ በዐይኖቻችን ለማየት፤ በጆሮዎቻችን ለመስማት፤ በእግሮቻችን ለመራመድ በአፍንጫችን ለማሽተት፤ በእጆቻችን ለመሥራትና ለመያዝ መመቻቸታቸው በአጋጣሚ የሆነ ነገር ነው ለማለት ይቻላልን?

እነዚህ እያንዳንዳቸው የአካል ክፍሎችም ዝም ብለው በሰውነታችን ላይ ተሰክተው የሚገኙ ተለጣፊ ነገሮች ሳይሆኑ ከውስጣዊ አካላችን ጋር በቀላሉ ልንረዳው በማንችለው በአስደናቂ ሁናቴ የተያያዙ ናቸው። ታዲያ ይህንንስ የተወሳሰበ አስደናቂ ሥርዓት በአጋጣሚ የተገኘ ነው ለማለት እንደፍራለንን? እነዚህ ሁሉ ነገሮች መነሻና መጀመሪያ የሌለውን አንድ ታላቅ ብልኅ ፈጣሪ አይገልጡምን?

እስቲ በመተንፈስ አማካይነት ስለምንኖርበት ስለ አየር እናስተውል። ይህ አየር በውስጡ ኦክስጂን የተባለ ንጥረ ነገር አለበት፤ በአየሩ ውስጥ ያለው ኦክስጂን ብቻ ቢሆን ኖሮ በቅጽበት ዓለምን በሙሉ ባቃጠለ ነበር። ብልኁ ፈጣሪ ግን ከፍተኛ ጉዳት እንዳይደርስ የተቃጠለውን የሚያጠፋ ናይትሮጂን የተባለውን ንጥረ ነገር ፈጠረለት። በሁለቱ ንጥረ ነገሮች መዋሐድ ለሕይወት አስፈላጊ የሆነው አየር ተገኘ። ይህ ጥበባዊ ሥራ የሆነው ረቂቅ ሥነ ሥርዓት በአጋጣሚ ተገኘ ለማለት ይቻላልን? ይህስ ከፍተኛ ዝግጅት ያለ አንድ አዘጋጅ ሊገኝ ይቻላልን?

ስለ ኣየር የምናሰላስለውን ተወት አድርገን ለዓለም ከሚሰጠው ጠቀሜታ ጋር በማገናዘብ ስለ ሙቀት ብናስተውል ስለ ጥበበኛውና ስለ ሁሉን ቻዩ እግዚአብሔር ህላዌ ብዙ ማስረጃዎችን ለማግኘት እንችላለን። ሙቀት በሕይወት ለመቀጠል ዋነኛው ምክንያት ነው ተብሎአል። ሙቀት እንፋሎትን ወደ ላይ እንዲወጣ በማድረግ ኀይሉ ዝናብን ለማስገኛ ምክንያት ነው፥ ለጠቅላላ የዕድገት ኀይልም ታላቅ እርዳታ የሚያደርግ ነው።

ሌሊትና ቀን በቋሚ ሥነ ሥርዓት ይቀያየራሉ፤ የዓመቱ ወቅቶችም ሁናቴአቸው ሳይለወጥ ጊዜአቸውን ጠብቀው ይፈራረቃሉ፤ ወንዞች ሞልተው ወደ ባሕሮች ይመለሳሉ።

በአጠቃላይም ፍጥረት ማለት ወንዞችና ባሕሮች፤ ተራሮችና ሸለቆዎች፤ አትክልቶችና እንስሳት ሁሉ አስደናቂና ግልጥ በሆኑ ምልክቶች፤ ትክክለኛና ጠቃሚ በሆነ ትርጉም እነርሱን ያስገኛቸው ማለት የፈጠራቸው እግዚአብሔር መኖሩንና በሥነ ሥርዓት ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ የሚያደርጋቸው መሆኑን ይመሰክራሉ። ይህንንም የሚያደርገው ከትልቁ እስከትንሹ ፍጥረት ድረስ ነው። በዚህ ጉዳይ ቅዱሳት መጻሕፍት ምን እንደሚሉ እንመልከት:-

«ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ለሰዎች የማይታየው የእግዚአብሔር ባሕርይ፤ ይኸውም ዘለዓለማዊ ኀይሉና አምላክነቱ እርሱ በፈጠራቸው ነገሮች ግልጥ ሆኖ ስለታየ ሰዎች ለሚያጠፉት ጥፋት ምክንያት የላቸውም» (ሮሜ:ም:1 ቁ:20)።

«ሕወትንና እስትንፋስን፤ ሌሎችንም ነገሮች ለሰው ሁሉ የሚሰጥ እርሱ ስለሆነ ምንም ነገር አይጐድለውም፤ የሰውም እርዳታ አያስፈልገውም» (የሐ:ሥ:ም:17 ቁ:25)።

ባለመዝሙሩም እንዲህ ብሎአል:- «ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፤ የሰማይ ጠፈሮችም የእግዚአብሔርን ሥራ ያውጃሉ» (መዝ:19 ቁ:1)። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዳለው:- «እግዚአብሔር ስለ ህልውናው ያስተማረን በመጻሕፍት አማካይነት ብቻ ቢሆን ኖሮ እርሱን ማወቅ የሚቻላቸው መጻሕፍትን ማንበብ የሚችሉ ሰዎች ብቻ በሆኑ ነበር። መጻሕፍትን ማንበብ ለማይችሉ ሰዎች ማንበብ በሚችሉ ሰዎች ገለጣ ካልተደረገላቸው በቀር እግዚአብሔርን ማወቅ ባልተቻላቸውም ነበር። ስለ እግዚአብሔር የተጻፉትን መጻሕፍትም ለማግኘት የሚችሉት ባለጸጎች ብቻ ስለሚሆኑና ድኾች መጻሕፍቱን መግዛት ዐቅም ስለማይኖራቸው እግዚአብሔርን ማወቅ በባለጸጎች ብቻ በተወሰነ ነበር። ከዚያም በላይ በእነዚያ መጻሕፍት ለመጠቀም የሚችል እነዚያ መጻሕፍት የተጻፉበትን ቋንቋ የሚያውቅ ሰው ብቻ በሆነ ነበር። እነዚህ ችግሮች ግን በተፈጥሮ መጻሕፍት ውስጥ የሌሉ ናቸው። ይህም የሆነበት ምክንያት ተፈጥሮ የሚናገረው የተማሩና ያልተማሩ፤ ሀብታሞችና ድኾች ሊረዱ በሚችሉት በትርኢት ቋንቋ እንጂ በጽሑፍና በአንደበት ንግግር ቋንቋ ስላልሆነ ሁሉም ይህን ትልቅ መጽሐፍ በመመልከት የዚያን ሠሪ (ፈጣሪ) ትልቅነትና ክብር ለማንበብ ይችላል።

በእርግጥም ተፈጥሮ የሚናገርበት ድምፅ አለው። ተፈጥሮን መመልከት በአንደበት ከሚነገር ንግግር ይበልጣል። (ቆሞስ ሚካኤል ሚና:- የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ መለኮት 1ኛ መጽሐፍ ገጽ 112)።



www.ethiopianorthodox.org

የኅሊና ምስክርነት:- ኅሊና ማለት በሰው ውስጥ የሚገኝ የስሜቶች አባል ነው። ዐይን በማየት አንድን ነገር ከሌላው እንደሚለይ በዚሁም ዐይነት ኅሊና ትክክለኛውን ሥራ ከስሕተት ሥራ ይለያል። ምንም እንኳ አንዳንድ ጊዜ ቢሳሳት ይህ ጠባዩ ነው ተብሎ በአጠቃላይ የሚነገርበት አይደለም:

አገስጢኖስ የተባለው መምህር እንዳለው:-

«እግዚአብሔር ክብሩ ይስፋና በሰው ልብ ውስጥ ፍርድን ሲመሠርት አእምሮን ዳኛ፥ ኅሊናን ዐቃቤ ሕግና ሐሳብን ምስክር አድርጓቸዋል። በተወዳጆች ጣቶቹም በልብ ወረቀትነት ላይ የህላዌው ምልክቶች፥ አንድነቱ፥ ዘለዓለማዊነቱ፥ ዓለምን መፍጠሩና መግቦቱ ተጽፈዋል» (ሚካኤል ሚና:- 1ኛ: መጽ: ገጽ:114)።

አንድ ብርቱ ሰው ከእርሱ ደካማ የሆነውን ሰው መብት መግፈፍ ችሎታ ይኖረውና ያን ላለማድረግ ምንም የሚያግደው ነገር ባይኖር ያን በደል ሲፈጽም ግን ኅሊናው ዕረፍት ይነሣዋል። ይህም የሚያመለክተው የሰው ኅሊና የደካሞችን መብት ለማስከበር ግፈኝነትንና በደልን የሚበቀል አምላክ መኖሩን የሚገልጥለት መሆኑን ነው።

ስለዚህ ኅሊና የሰው ተፈጥሮአዊ ሕግ መሆኑን እንገነዘባለን።

በዚህ ጉዳይ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሎአል:-

በዚህም «ሕግ የሌላቸው አረማውያን በተፈጥሮአቸው ሕግ የሚአዘውን ነገር ይፈጽማሉ፤ ምክንያት የአሪት ሕግ ባይኖራቸውም የራሳቸው የተፈጥሮ ሕግ ስላላቸው ማድረግ የሚገባቸውን ያውቃሉ። ይህም ሁኔታቸው ሕግ የሚያዘው ነገር ሁሉ በልባቸው የተጻፈ መሆኑን ያሳያል፤ ደግሞም ኅሊናቸው ይመሰክርባቸዋል፤ ኅሊናቸው አንዳንዴ ይወቅሳቸዋል፤ አንዳንዴም ይደግፉቸዋል» (ሮሜ:ም:2 ቊ:14–15)።

በተፈጥሮ ዝንባሌ የዓለም ሕዝብ ስምምነት:- የዓለም ሕዝቦች የተፈጥሮ ዝንባሌ ስምምነት አንድ የሚጠብቃቸውና የሚረዳቸው የበላይ ጠባቂ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን በማመን ላይ ነው። ስለዚህ የሃይማኖት ፍላጎት ከሰው ጋር አብሮ የተፈጠረ ነው ማለት ይቻላል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሊመለክ የሚገባ አምላክ መኖሩን ለአቴና ፈላስፎች የገለጠላቸው የተፈጥሮ ዝንባሌን መነሻ በማድረግ እንዲህ በሎ ነው:-

«በከተማችሁ እየተዘዋወርኩ የአምልኮ ስፍራዎቻችሁን ስመለከት ለማይታወቅ አምላክ ተብሎ ተጻፈበትን የመሠዊያ ቦታ አገኘሁ፤ እንግዲህ እኔ አሁን የምነግራችሁ ስለዚሁ ሳታውቁ ስለምታመልኩት አምላክ ነው» (የሐ:ሥ:ም:17 ቊ:23)።

ሕይወት ያለ እግዚአብሔር ጐደሎ ሕይወት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። እግዚአብሔርን ለማያውቅ ሰው ዓለም ጨለማ፥ ዘለዓለማዊነት የማይታወቅ ስለሚሆንበት ብቸኝነት ተሰምቶት በዚህ በሰፊው ዓለም ውስጥ ግራ የተጋባ ይሆናል። እግዚአብሔር ስለ ሃይማኖት አስፈላጊነት የተፈጥሮ ስሜትን በሰዎች አእምሮ ውስጥ ስለፈጠረ በብዙዎች ዘንድ የህልውናው እምነት የተጠናከረ ነው። ይህ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የዓለም ሕዝብ የሚስማማበት የተፈጥሮ ጠባይ ሐሰት ወይም አታላይነት አለመሆኑ መታወቅ አለበት። በሰው አእምሮ ውስጥ እግዚአብሔር የፈጠረው ሃይማኖታዊ ዝንባሌ እንዴት ሐሰትና ማታለል ሊሆን ይችላል?

ዓለምን ዞረው የጐበኙ ሰዎች እንደመሰከሩት በሰዎች ሁሉ ዘንድ የሚገኘው የሃይማኖት ፍላጎት ለሕይወት አስፈላጊ ከሆኑ ጉዳዮች ልዩነት እንደ ሌላቸው ገልጸዋል።

የሰውን ልጅ ሃይማኖታዊ ዝንባሌ በተመለከተ ቆርኔሌዎስ የተባለው የመቶ አለቃ ከመ ጽሐፍ ቅዱስ በማስረጃነት ይቀርባል።

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10 ላይ እንደተገለጠው ይህ ሰው በዚያን ጊዜ አረማውያን ከነበሩት ከሮማውያን ወገን እንጂ እግዚአብሔርን ከሚያመልኩ ከአይሁድ ወገን አልነበረም። እርሱ ግን በተፈጥሮ ዝንባሌው ምክንያት እግዚአብሔርን ያመልክ ነበር። በምድራዊ አስተሳሰብና ለሥጋዊ ጥቅም ቢሆን ኖሮ በዚያን ጊዜ ለእርሱ የሚጠቅመው እንደ ሮማውያን ሁሉ ጣዖት ማምለክ ነበር። እርሱ ሃይማኖታዊ ዝንባሌው አስገድዶት ዓለማዊ ጥቅሙን እንቢ አለ (የሐ:ሥ:ም:10)።

የቅዱሳት መጻሕፍትና የታሪክ ማስረጃዎች:- ቅዱሳት መጻሕፍት በትንቢቶችና በምሳሌዎች (ጥላዎች) የተሞሉ ናቸው። በቅዱሳት መጻሕፍትም ውስጥ የተነገሩት ትንቢቶች በጊዜአቸው የተፈጸሙ መሆናቸውን ታሪክ አረጋግጦአል። ታዲያ የእነዚህ የተነገሩ ትንቢቶች በትክክል መፈጸም ሰዎች ገምተው በመናገር የተፈጸመ የሰዎች ብልጠት ነው ብለን እናስብ ይሆንን? ወይስ በትንቢት የተነገረው ጉዳይ ሆን ተብሎ የተቀነባበረና ታሪክ ተቀብሎ ያስተጋባለት ድርሰት ይሆንን?

ጉዳዩ ይህ ወይም ያ አይደለም። የትንቢት ሁኔታ የሰው ልጅ ከሚያስበው የራቀ ነው።

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙት ትንቢቶች በፍጡር ሁሉ ላይ ፈጣሪ አምላክ ለመኖሩ ማስረጃዎች ናቸው። የእግዚአብሔርም ፍጹም ዐዋቂነት የሚታየው አስቀድሞ በነቢያቱ አማካይነት ያናገረው ትንቢት ጊዜው ሲደርስ ተፈጽሞ በመገኘቱ ነው። የትንቢቱንም ትክክለኛነት ያረጋገጠው ታሪክ ብቻ ሳይሆን የጥንት ቅርሶች ውጤትም ነው፤ አሁንም እያረጋገጠ ነው።

በፍጹም ሥልጣኑ ለፍጥረቱ ወቅቶችንና ዘመናትን የፈጠረ አምላክ መኖሩን እንድናምን ታሪክ ያረጋገጣቸውን ትንቢቶች ቀጥለን እንመልከት:-

በትንቢተ ኢሳይያስ ስለ ባቢሎን እንዲህ የሚል ትንቢት ተነግሮ ነበር:-

«የባቢሎን መንግሥት ከመንግሥታት ሁሉ እጅግ የተዋበች ናት፤ ለሕዝቡዋም መመኪያ ናት፤ ነገር ግን እኔ እግዚአብሔር ባቢሎንን እንደ ሰዶምና እንደ ገሞራ እገለብጣታለሁ። ዳግመኛ የሚኖርባትም አይገኝም፤ የበረሓ ዘላኖች የሆኑ ዐረቦችም ድንኳን አይተክሉባትም፤ እረኞችም መንጋ አያሰማሩባትም። የምድረ በዳ አራዊት መፈንጫ ትሆናለች፤ ጉጉቶችም ጎጆ ይሠሩባታል፤ ሰጎኖች በዚያ ይኖራሉ፤ ፍርስራሽዋንም የበረሓ ፍየሎች ይዛለሉበታል። በታላላቅ ሕንጻዎችና በቤተ መንግሥትዋ ውስጥ የጅቦችና የተኲላዎች ጩኸት ያስተጋባል፤ እነሆ በዚህ ዐይነት ባቢሎን የምትጠፋበት ጊዜ ደርሶአል» (ኢሳ:ም:13 ቊ:19–22)።

ይህ ትንቢት የሚያመለክተው ምንም ጥፋት ሊደርስባት የማይችል ትመስል የነበረችውን የባቢሎንን ሁናቴ ነው። አሁን ግን ያችን ቦታ የሚጐበኝ ሰው በሁናቴው በጣም ይገረማል። የነገሥታት ክብርና ጌጣቸው የነበረችው ባቢሎን አሁን የምትታየው ከፍተኛዎቹ ቅጥሮችዋና ምሽጎችዋ ፈራርሰው፤ ክብርዋና ገናናነትዋ ጠፍቶ፤ በረሓማ ደረቅ ቦታ፤ ሰው የማይኖርባት ባዶ ሆና ነው። ዘላኖች እንኳ ድንኳናቸውን እዚያ መትከል ፈርተው ለነብሮች፤ ለአንበሶች፤ ለእባቦችና ለቀበሮዎች መጠለያነት ትተውላቸው ሄዱ። በዚያም የሚሰማው መልካም የሙዚቃ መሣሪያ ድምፅ ሳይሆን የአውሬዎች ድምፅ ነው።

ስለ ነነዌ ደግሞ በትንቢተ ሶፎንያስ እንዲህ ተብሎአል:-

«እግዚአብሔር በሰሜን ሕዝብ ላይ ኀይሉን ያሳያል፤ አሦርንም ያጠፋል፤ የነነዌንም ከተማ ውሃ በሌለበት ምድረ በዳ እንደፈረሰች ከተማ ባድማ ያደርጋታል። የበግና የፍየል መንጋዎች፤ የከብቶችና የምድር አራዊት መሰማሪያ ትሆናለች፤ ጉጉቶች በፍርስራሹ ውስጥ ይኖራሉ፤ በየመስኮቱም ይጮኻሉ፤ ቁራዎች በየደጃፉ ድምፃቸውን ያሰማሉ፤ ቤቶቹ የተሠሩባቸው ዝግባዎች ዕርቃናቸውን ይቀራሉ፤ ይህች ከተማ ከኔ በቀር ማንም የለም በማለት በኩራት ተዝናንታ ትኖር ነበር፤ አሁን ግን አራዊት የሚመሰጉባት ውድማ ሆና ትቀራለች፤ በዚያም የሚያልፉ ሁሉ እጅግ በመገረም እጃቸውን እያወዛወዙ ያፉጩባታል» (ሶፎ:ም:2 ቊ:13–15)።

ነቢይ ስለ እርስዋ ተናግሮ ታሪክም ስለ ትንቢቱ ያረጋገጠላት ነነዌ በዚያን ጊዜ የቅጽሮችዋ ርዝመት አንድ መቶ ጫማና ዙሪያም ስድሳ ማይል ነበር፤ በአንድ ሺህ አምስት መቶ ምሽጎችም የተጌጠች ነበረች፤ የምሽጎቹ ርዝመት ሁለት መቶ ጫማ ነበር። የተነገሩት ትንቢቶች ሁሉ የተፈጸሙ መሆናቸው በታሪክ መዝገብ ተረጋግጦአል። ዘለዓለማዊ ጥፋትና ውድመት የደረሰባት በእግዚአብሔር ፍርድ መሠረት ነው። የቅጽሮችዋም ፍርስራሽ የአሸዋና የአዋራ ክምር ሆኖአል።

ማነው እነዚህን ተጨባጭ ማስረጃዎች አይቶ ሁሉን የፈጠረና እርሱ የፈቀደውን ለማድረግ የሚችል ፈጣሪ አምላክ መኖሩን የሚክድ? ማንስ ነው ሞኝ ካልሆነ በቀር እነዚህ ድርጊቶች በአጋጣሚ ተደረጉ ወይም ተፈጸሙ ብሎ የሚያምን? (ሚካኤል ሚና 1ኛ:መጽሐፍ፤ ገጽ 107–121)።

ስለ እግዚአብሔር ህልውና የቅዱሳት መጻሕፍትን ጥቅሶች እንመልከት:-

«ነገር ግን እንስሶችን፤ ያስተምሩሃል፤ የሰማይንም ወፎች ጠይቅ ይነግሩህማል፤ ወይም ተናገር እርስዋም ታስተምርሃለች፤ የባሕርም ዓሣዎች ይነግሩሃል። ከእነዚህ ሁሉ መካከል የእግዚአብሔር እጅ ይህን እንደሠራ የማያውቅ ማነው? ሕያወት ያለው ፍጥረት ሁሉና የያንዳንዱም ሰው ነፍስ በእግዚ አብሔር ሥልጣን ሥር ነው» (ኢዮ:ም:12 ቊ:7–10)።


www.ethiopianorthodox.org

«ክፉዎች ስለ እግዚአብሔር ግድ የላቸውም፤ በትዕቢታቸውም እግዚአ ብሔር የለም ብለው ያስባሉ» (መዝ:10 ቍ:54)።

«ሞኝ በልቡ አግዚአብሔር የለም ይላል» (መዝ:14 ቍ:1)።

«በሚታዩት መልካም ነገሮች አመካይነት እግዚአብሔርን ሊያውቁና ማንነቱን ሊረዱ ያልቻሉ፥ ወይም ሥራውን በማጥናት ሠሪውን ማወቅ ያቃታ ቸው ሰዎች ሁሉ በተፈጥሮአቸው የአእምሮ ብስለት የጐደላቸው ናቸው» (ጥ:ሰ:ም:13 ቍ:1)።

«ለእግዚአብሔር የሚያበድርና ያበደረውን መልሶ የሚወስድ ማነው? ሁሉም ነገር የተገኘው ከእርሱ፥ በእርሱና ለእርሱ ነው፤ ለዘለዓለም ክብር ለእርሱ ይሁን፤ አሜን» (ሮሜ: ም:11 ቍ:35–36)።

## የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ክብር

<u>መግቢያ</u>:- ከክርስትና መሠረተ እምነት መካከል የክርስቶስን አምላክነት ጠንቅቆ ማወቅ የመጀመሪያና ዋነኛው ጉዳይ ነው። በክርስቶስ ማመንም በእግዚአብሔር ለማመን መሠረቱ ነው። ስለዚህ ነው። ጌታችን በእግዚአብሔር እመኑ በእኔም እመኑ ያለው (ዮሐ:ም:14 ቍ:1)። እግዚአብሔርንም የማመ ኛው መንገድ ክርስቶስ መሆኑን ለመግለጥ:- «እግዚአብሔርን ያየው ከቶ ማንም የለም፤ ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ያለው አንድ ልጁ ገልጦታል» ተብሎአል። (ዮሐ:ም:1 ቍ:18)። ይህም ማለት ስለ እግዚአብሔር የነገረን ማለት እግዚአብሔርን ያሳወቀን ሥጋ የለበሰው አምላክ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ማለት ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እንዳለው በእግዚአብሔር የምናምነው በክርስቶስ አማካይነት ነው (1ኛ:ጴጥ:ም:1 ቍ:21)።

<u>ነቢያት ለክርስቶስ አምላክነት መስክረዋል</u>:- ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት ነቢያት በትንቢቶቻቸው መስክረዋል:-

«እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች» (ኢሳ.ም.7 ቍ.14)።

«እነሆ ሕፃን ተወልዶልናል፤ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል፤ እርሱም መሪ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ፥ መካር፥ ኀያል አምላክ፥ የዘለዓለም አባት፥ የሰላም አለቃ ይባላል» (ኢሳ.ም.9 ቍ.6)።

«በእውነት እርሱ ድካማችንን ተቀበለ፤ ሐዘናችንንም ተሸከመ፤ እኛ ግን በእግዚአብሔር ተመትቶ እንደ ቈሰለ አድርገን ቈጠርነው። ይሁን እንጂ እርሱ ተወግቶ የቈሰለው ስለ ኃጢአታችን ሲሆን በመገረፍ የደቀቀውም እኛ ስለ ፈጸምነው በደል ነው፤ እርሱ በተቀበለው ቅጣት እኛ ሰላምን አገኘን፤ እርሱም በመቍሰሉ እኛ ተፈወስን» (ኢሳ: ም:53 ቍ: 4–5)።

«በሌሊት ራእይ አየሁ፤ እነሆም የሰው ልጅን የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ፤ በዘመናት ወደ ሸምገለውም ደረሰ፤ ወደፊቱም አቀረቡት፤ ወገኖ ችና አሕዛብ፥ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር፥ መንግሥትም ተሰጠው፤ ግዛቱም የማያልፍ የዘለዓለም ግዛት ነው፤ መንግ ሥቱም የማይጠፋ ነው» (ዳን.ም.7 ቍ.13–14)።

«ዐመፃ ይጨረስ፥ ኃጢአትም ይፈጸም፥ በደልም ይሰረይ፥ የዘለዓለም ጽድቅ ይገባ፥ ራእይና ትንቢት ይታተም፥ ቅዱስ ቅዱሳኑም ይቀባ ዘንድ ለሕዝ ብህና ለቅድስት ከተማህ የሰባ ሱባዔ ጊዜ ተወስኗል።

ትእዛዙ ከሚወጣበት ጊዜ ጀምሮ መሲሑ እስከሚመጣበት እስከ ሰባት ሱባዔና ስድሳ ሁለት ሱባዔ ድረስ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰህ እንደገና እንድት ጠግንና እንድትሠራ ዕወቅ፤ አስተውል። መንገዱና ግንቡ በሚታደሱበት ጊዜ የጭንቀት ጊዜ ይሆናል። ከስድሳ ሁለትና ከሰባ ሱባዔ በኋላ መሲሕ ይገደላል፤ የሚሞተውም ለራሱ አይደለም። የሚመጣውም አለቃ ሕዝብ ከተማይቱንና መቅደሱን ያጠፋሉ። ... እርሱም ከብዙ ሰዎች ጋር ጽኑ ቃል ኪዳን ለአንድ ሳምንት ያደርጋል፤ በሳምንቱም አኩሌታ መሥዋዕቱንና ቁርባኑን ያስቀራል» (ዳን.ም.9 ቍ.24–27)።

«አንቺም ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ካንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘለዓለም የሆነ በእስራኤል ላይ ገገር የሚሆን ይወጣልኛል» (ሚክ.ም.5 ቍ.2)።



«የጽዮን ልጅ ሆይ፥ እነሆ መጥቼ በመካከልሽ እኖራለሁና ዘምሪ፥ ደስም ይበልሽ ይላል እግዚአብሔር፤ በዚያም ቀን ብዙ አሕዛብ ወደ እግዚአብሔር ይጠጋሉ፤ ሕዝብም ይሆኑኛል፥ በመካከልሽም እኖራለሁ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም ወደ አንቺ እንደላከኝ ታውቂአለሽ» (ዘካ.ም. 2ቍ.10–11)።

«ከዚህ በኋላ ከሙሴና ከነቢያት መጻሕፍት ጀምሮ በቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ስለ እርሱ የተነገረውን እየጠቀሰ አስረዳቸው» (ሉቃ:ም:24 ቍ:27)።

«ከእናንተ ጋር በነበርኩ ጊዜ በኦሪት ሕግ፥ በነቢያትና በመዝሙር መጻሕ ፍት ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ መፈጸም አለበት ብዬ የነገርኳችሁ ቃል ይህ ነው» (ሉቃ:ም:24 ቍ:44)።

«እናንተ በቅዱሳት መጻሕፍት የዘለዓለምን ሕይወት የምታገኙ ስለሚመስላችሁ እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው» (ዮሐ:ም:5 ቍ:39)።

«በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአት ይቅርታ እንደሚያገኝ ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል» (የሐ:ሥ:ም:10 ቍ:43።

## ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ክርስቶስ መለኮታዊ ክብር

## መመስከራቸው:-

<u>ብሉይ ኪዳን</u>:- የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ለክርስቶስ ምሳሌ (ጥላ) በሆኑ ጉዳዮች የተሞሉ ናቸው። ለምሳሌ እንደ አዳም፥ ይስሐቅ፥ ዮሴፍና ሙሴ ያሉ ሰዎች፥ እንደ የፋሲካ በግ፥ ቍጥቋጦው፥ መና፥ የምድረ በዳው አለት፥ ከነሐስ የተሠራው እባብ፥ የመገናኛው ድንኳን በውስጡ ካሉት ዕቃዎች ሁሉ ጋር ያሉ ተናጋሪ ያልሆኑ ፍጥረቶች ወይም በሕጉ መሠረት መሥዋዕትና ከለምጽ መንጻትን የመሰሉና በዚያን ጊዜ ይከናወኑ የነበሩ የሃይማኖት ሥርዓቶችና ሌሎችም ናቸው።

<u>ሐዲስ ኪዳን</u>:- በሐዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኘው የጌታችን መለኮታዊ ክብር ማስረጃዎች በተናገራቸው ንግግሮች፥ ባደረጋቸው ተአምራት፥ በአምላካዊ ኀይሉ የተጠናከሩ ናቸው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም ሲመሰክር እንዲህ ብሎአል– «ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኀይልና ስለ መምጣቱም በነገርናችሁ ጊዜ ራሳችን ግርማውን አይተን እንጂ ከሰው ብልኀት የተፈጠረውን ተረት ተከትለን አይደለም (2ኛ: ጴጥ: ም:1 ቍ: 16) (ዮሐ: ም: 5ቍ: 19–24፥ ም:14 ቍ:11፥ ም:15 ቍ:24)። ይመለከቷል።

## በሁሉም ነገር ላይ የክርስቶስ ፍጹም ሥልጣን

1. <u>ሕይወታችን በሆነውና ዘለዓለማዊ ሕይወትን በሚሰጠን በእግዚአብሔር ልጅ ማመን</u>:-

«ምስክርነቱም እግዚአብሔር የዘለዓለም ሕይወት እንደሰጠንና ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ የሚመሰክር ነው። የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ግን ሕይወት የለውም» (1ኛ:ዮሐ:ም:5 ቍ:11–12)።

«እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም የላከው፥ ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም ላይ ለመፍረድ አይደለም። በእርሱ የሚያምን አይፈረድበትም፤ በእርሱ የማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስላላመነ ገና ድሮ ተፈርዶበታል» (ዮሐ:ም:3ቍ:17–18)።

«በወልድ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ በወልድ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖርበታል እንጂ ሕይወትን አያገኝም» (ዮሐ:ም:3 ቍ:36)።

2. <u>ክርስቶስ ኃጢአታችንን የሚያስተሰርይና ስጦታን የሚሰጠን አምላክ ነው</u>:- ክርስቶስ ለሰው ዘር የሰጠው ስጦታ ማንኛውም ሰው፥ ነቢይ ወይም መልአክ ሊሰጠው የማይችለው ስጦታ ነው፤ ትንቢትን የተናገረ ወይም ማስጠ ንቀቂያ ትምህርት ያስተማረ ሁሉ የሰጠው ንግግርን ነው፤ ክርስቶስ ግን የሰጠን የሰው ልጅ ለመስጠት ከሚደፍረውና ከሚችለው የላቀ ነው።

1. እርሱ የዘለዓለም ሕወትን ሰጠን። (ዮሐ:6፥68)።
2.እርሱ ለዘለዓለም ሕይወት ነፍሱን፥ ሥጋውንና ደሙን ሰጠ (ዮሐ:ም:6)።:
3. እርሱ ከሰይጣን እስራት ለነፍሳት ነጻነትን ሰጠ (ዮሐ:ም:8ቍ:36)።



www.ethiopianorthodox.org

4. ሰው እርሱን ጠጥቶ ለዘለዓለም የማይጠማበትን የሕይወት ውሃ ሰጠ (ዮሐ: ም:4ቍ:13–14)።
5. እርሱ የዓለም ብርሃን ነው (ዮሐ:ም:8ቍ:12)።
6. ክርስቶስ በር ነው፤ በእርሱ የሚገባ ይድናል፤ ይገባል፤ ይወጣል፤ መሰማርያም ያገኛል (ዮሐ:10፥9)።
7. እርሱ መልካም እረኛ ነው (ዮሐ:10፥11፥ዕብ:13፥20)።
8. እርሱ ትንሣኤና ሕይወት ነው (ዮሐ:ም:11ቍ:25)።
9. እርሱ መንገድና እውነት ነው (ዮሐ:ም:14ቍ:25)።
10. እርሱ ፈዋሽ ሐኪም ነው (ማቴ:ም:4ቍ:24፥ም:9ቍ:35)።
11. በዙፋኑ ከራሱ ጋር የሚያስቀምጠን እርሱ ነው (ራእ:3፥2:)።
12. የዘለዓለማዊ ደስታን እንድንወርስ ያደርገናል (ማቴ:ም: 25ቍ: 34፥ ያዕ:ም: 2ቍ:5)።

## በትምህርተ ሥላሴ ውስጥ የክርስቶስ መለኮታዊ ክብር

ክርስቶስ (ሎጎስ)፥ ቃል፥ ቃለ እግዚአብሔር ነው:- በዮሐንስ ወንጌል መጀመሪያ ላይ የተነገረው ቃል ተራ ቃል አይደለም።

ክርስቶስ ቃል ነበረ፤ እርሱም እግዚአብሔር ነበረ:- «በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ» (ዮሐ: ም:1 ቍ:1)።

የክርስቶስ ክብር እንደ አብ ክብር ነው:- «እኔን ያየ አብን አየ» (ዮሐ: ም:14ቍ:9):

ክርስቶስ ለማይታየው አምላክ ምሳሌ ነው:- «ክርስቶስ ለማይታየው እግዚአብሔር እውነተኛ ምሳሌ ነው» (ቆላ:ም:1 ቍ:15)። እርሱ ሥጋ በለበሰ ጊዜ እግዚአብሔርን በእርሱ አየነው (1ኛ:ጢሞ:ም:3 ቍ:16)።

ጌታችን የሦስቱን መለኮታዊ እኩልነት አመልክቶአል:- ደቀ መዛሙርቱን ሲያዝዛቸው:- በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ ብሎአቸዋል (ማቴ:ም:28 ቍ:19)።

የአብና የወልድ ግንኙት:- አብና ወልድ አንድ ናቸው (ዮሐ: ም:10 ቍ:30፥ ም:17 ቍ:11 እና 22)።

ክርስቶስ በአብ፥ አብ ደግሞ በክርስቶስ ነው (ዮሐ:ም:14 ቍ:10)።

የክርስቶስ የሆነ የአብ ነው፤ የአብ የሆነ ውም የክርስቶስ ነው (ዮሐ:17፥10)። አብ ሚያደርገውን እርሱም ያደርጋል (ዮሐ:ም: 5ቍ: 17፥ ም:10 ቍ: 37–38)።

በክብርና በእምነት እኩል መሆናቸው (ዮሐ:ም: 5ቍ: 22፥ ም:14 ቍ1)።

አብን በወልድ ሰውነት እናየዋለን። (ዕብ:ም:1 ቍ:3፥ዮሐ:ም:1 ቍ:18)

## የክርስቶስ መለኮታዊ መጠሪያዎች

1. በፍጥረቱ ላይ ያለው የበላይነት:- ሰማይንና ምድርን የፈጠረ እግዚአብሔር ነው (ዘፍ:ም: 1 ቍ1፥ ኢሳ:ም: 44 ቍ: 24፥ ኢሳ:ም: 45 ቍ:7)። ይህ ከላይ ሰማይንና ምድርን የፈጠረ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ቃለ እግዚአብሔር ማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ሲያመለክት ወንጌላዊው ዮሐንስ:- «ሁሉ ነገር የተፈጠረው በእርሱ ነው፤ ያለ እርሱ ምንም የተፈጠረ ነገር የለም» ብሎአል (ዮሐ:ም:1 ቍ:3) ። ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጣሪ ይባላል።

2. ክርስቶስ ሕይወትን ሰጪ ነው:- «ኢየሱስም እንዲህ አላቸው:- የሕይ ወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ፈጽሞ አይራብም፤ በእኔ የሚያምንም ከቶ አይጠማም» (ዮሐ:ም:6 ቍ:35)።

«ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው:- እውነት እውነተ እላችኋለሁ፤ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ፥ ደሙንም ካልጠጣችሁ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን የሚበላና ደሜን የሚጠጣ



ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ እኔም በመጨረሻው ቀን ከሞት አስነሣዋለሁ» (ዮሐ: ም:6 ቍ: 53–54)።

ጌታችንም በጸሎትና በልመና ሳይሆን በትእዛዙ ሙታንን ማስነሣቱ መለኮታዊ ኀይሉን ያመለክታል:- (የኢያኢሮስን ልጅ ማር:5፥22–23 እና 35–42፥ የመበለቲቱን ልጅ:- ሉቃ:7፥11–17፥ አልዓዛርን ዮሐ:ም:11)።

በእኔ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት ይኖረዋል (ዮሐ:3፥16)።

እርሱ የሚሰጠው ውሃ ለዘለዓለም ሕይወት የሚፈልቅ ምንጭ ነው (ዮሐ:ም:4 ቍ:10–14)።

«በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤ ... እኔም የዘለዓለምን ሕይወት እሰጣቸዋለሁ» (ዮሐ:ም:10 ቍ:27–28)።

3. በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ጌታ የሚለው የክብር መጠሪያ ለእግዚአብሔር ብቻ የተሰጠ ሲሆን በብዙ ቦታ ይኸው ቃል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተጠራበት ገልጽ ነው።

እንደገናም «ጌታ» የሚለው መጠሪያ ያህዌ የሚለውን የዕብራይስጡን በመተርጐም ወደ አማርኛ የተወሰደ ነው። ስለዚህ ክርስቶስ ራሱ እግዚአብሔር ያህዌ እንደሚባል ያህዌ ተብሎ ይጠራል ማለት ነው።

ዛዳ:ም 10 ቍ:17
ኢሳ:ም 45 ቍ:5
ማቴ:ም 4 ቍ:7
ማቴ:ም 4 ቍ:10
ማቴ:ም 7 ቍ:21
ማቴ:ም 7 ቍ:22
ማቴ:ም12 ቍ:8
ማቴ:ም14 ቍ:30
ማቴ:ም22 ቍ:43–45
ማቴ:ም25 ቍ:37–44
ማር:ም11 ቍ:3
ማር:ም16 ቍ:19፥20
ሉቃ:ም1 ቍ:43
ሉቃ:ም2 ቍ:11
ሉቃ:ም4 ቍ:8
ሉቃ:ም5 ቍ:8
ሉቃ:ም6 ቍ:46
ሉቃ:ም7 ቍ:13
ሉቃ:ም10 ቍ:17
ሉቃ:ም13 ቍ:25
ሉቃ:ም19 ቍ:8
ሉቃ:ም19 ቍ:31
ሉቃ:ም22 ቍ:33፥38፥49፥61
ሉቃ:ም23 ቍ።42
ዮሐ:ም20 ቍ:28
ዮሐ:ም21 ቍ:7፥12
የሐ:ሥም5 ቍ:9

www.ethiopianorthodox.org

የሐ:ሥ:ም7 ቊ:59
የሐ:ሥ:ም12 ቊ:11
የሐ:ሥ:ም16 ቊ:31
1ኛ:ቆሮ:ም2 ቊ:8
1ኛ:ቆሮ:ም8 ቊ:6
2ኛ:ቆሮ:ም13 ቊ14
ፊል፡ም2 ቊ:11
ቆላ:ም3 ቊ:17
ዕብ:ም1 ቊ:10
ያዕ:ም2 ቊ:1
2ኛ:ጴጥም:3 ቊ:18
ራእ:ዮ:ም17 ቊ:14
ራእ:ዮ:ም19 ቊ:16
ራእ:ዮ:ም22 ቊ:20–21

## የመከራከሪያ ጥቅሶችና መልሶቻቸው

የጌታችን የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት በመካድ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን የሚያቀርቡ ወገኖች አሉ። ከሚያቀ ርቡአቸውም ጥቅሶች መካከል የሚከተሉት የሚገኙባቸው ሲሆን ለእነርሱም መልስ ተሰጥቶባቸዋል።

«ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ። ቃሌ ንም በአፉ አደርጋለሁ፤ ያዘዝሁትን ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል፤ በስሜም የሚነ ገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ (ዘዳ:ም:18 ቊ:18–19)።

በኦሪት ዘዳግም ም.18 ቊ 15 እና 18 ላይ እንደተገለጠው እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ ያስነሣላቸዋል ተብሎ የተነገረውን አባባል በዮሐንስ ወንጌል ም.5 ቊ46 በሐዋርያት ሥራ ም.3 ቊ 22 እና ም.7ቊ 37 ላይ ስለጌታችን ስለመድኃኒታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተነ ገረ ተደርጎ መቅረቡ በመድኃኒታችን መለኮታዊ ክብር ከምናምነው እምነት ጋር እንዴት ይታረቃል ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል።

ሙሴ ለጌታችን እንደምሳሌ መቅረቡ ምንም የሚያስገረመን ጉዳይ መሆን የለበትም። ምክንያቱም ለምሳሌ በትንቢተ ሆሴዕ ም.11 ቊ1 ላይ ልጄን ከግብጽ ጠራሁት ተብሎ ስለ እስራኤል የተነገረውን በመጥቀስ ወንጌላዊው ማቴዎስ በም. 2ቊ 15 ላይ ለጌታችን እንደተነገረ አድርጎ አቅርቦታል።

በሙሴ በተጻፈው ኦሪት ዘፍጥረት ም. 3ቊ 15 ላይ እግዚአብሔር እባብን የረገመው በአን ተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ ብሎ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ገላትያ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም4ቊ 4 ላይ «ጊዜው ሲደርስ ከሴት የተወለደውን ልጁን እግዚአብሔር ላከልን» በማለት የሙሴን ጽሑፍ አገናዝቦታል። ሌላው ሙሴ ከጌታችን ጋር በተመሳሳይነት የቀረበበት ሁናቴ ደግሞ ሙሴ በመሪነቱ የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ሕዝብ የባርነት ቀንበር እንዳወጣ ሁሉ ጌታችንም በቤዛነቱ ዓለምን ከሰይጣን ባርነት ነጻ አውጥቷል።

ብዙ ጊዜ ተመላልሶ እንደተገለጠው እንደማንኛውም ሰው ስለጌታችን በሚነገርበት ጊዜ ሁሉ መለኮት በተዋሐደው ትስብእቱ መሆኑ መረሳት የለበትም።

ይህን ጉዳይ በተመለከተ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ.ወርቅ የሰጠው ትርጓሜ ደግሞ እንደሚከተለው ነው።

«ስለሚሰሙት ሰዎች አእምሮ ደካማነትም በወገኖቹ ሁሉ ዘንድ እንደ ሙሴ ነው አለ። ስለሚሰሙት ሰዎች የአእምሮ ደካማነት ነው እንጂ በሙሴ ለምን ይመስለው ነበር? ይህን ነገር ከመስማት ጆሮአቸውን እንዳይከለክሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ካመኑ በኋላ ዕብራውያን በዚህ ሰው በሙሴ የሚያምኑት እምነት የሚያከብሩት ክብር ጥቂት አይደለምና ሰው ስለሆነ



ስለዚህ በሙሴ መስሎ ይናገር ጀመር። ከዚህ በኋላ አምላክነቱን ጥቂቱ ተናገረ። ለሙሴ ገዢ ፈጣሪ መሆኑን እስኪያስረዳቸው ድረስ በወገኖቹ ላይ እንደ ሙሴ ነው በማለቱ በፊት ከእርሱ ጋር አስተካከሉት ነበር፤ የሙሴ ወገኖች ሕዝብ ናቸውና» (ሃ.አበ.ገጽ 224)።

ስለዚህ ጌታችን በሙሴ ምሳሌነት መቅረቡ ከላይ በተመለከተው የአቀራረብ ዘይቤ ለማቅረብ ተብሎ ነው እንጂ የጌታችንን መለኮታዊ ክብር ለመካድ ታስቦ አይደለምና አለመሆኑን ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠንቀቅ።

<u>መንግሥትህ የዘለዓለም መንግሥት ናት፤ ግዛትህም ለልጅ ልጅ ነው</u> (መዝ:145፥13)።

«እርሱ የመለኮት ባሕርይ አለው፤ ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል የሚያደርገውን የመለኮት ባሕርይ እንደያዘ መቅረት አልፈለገም። ይልቁንም ያለውን ክብር በገዛ ፈቃዱ ትቶ አገልጋይ መሆንን መረጠ፤ በሰው ምሳሌም ተገለጠ። እንደ ሰው ሆኖም በትሕትና ራሱን ዝቅ አደረገ፤ እስከ ሞት ድረስ ያውም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ» (ፊልጵ:ም:2 ቊ:6–8)።

እነዚህ ከላይ የቀረቡት ሁለት ጥቅሶች ተቃራኒ ከመምሰላቸውም በላይ አብ ከወልድ የበለጠ ሥልጣን ያለው ይመስል ይሆናል። ስለዚህስ ምን እንላለን?

ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የክርስቶስን መንግሥት በሦስት ዐይነት ያቀርቡታል።

**የመጀመሪያው:-** ክርስቶስ አምላክ ስለሆነ መለኮታዊ ገገርነቱን የሚመለከት እንደመሆኑ ይህ ገዢነት ወይም ንጉሥነት ዘለዓለም ከእርሱ ጋር የሚኖር እንጂ ለማንም ታልፎ የማይሰጥ ንጉሥነት ነው። የእግዚአብሔር ወልድን ዘለዓለማዊ ንግሥ በሚመለከት ወደ ዕብራውያን በተላከው መልእክት ም.1ቊ:8 ላይ እን ዲህ ተብሏል:- «አምላክ ሆይ ዙፋንህ እስከ ዘለዓለም ድረስ ይኖራል፤ የመንግ ሥትህም በትር የቅንነት በትር ነው።»

በትንቢተ ኢሳይያስ ም.44 ቊ.6 ላይ «የእስራኤል ንጉሥና አዳኝ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። የመጀመሪያውም የመጨረሻ ውም እኔ ነኝ፤ ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ.የለም» ተብሎ የተገለጸውን አባባል በራዕየ ዮሐንስ ም.2 ቊ:12 እና 13 ላይ ሲደግመው እንዲህ ብሏል «እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፤ ለያንዳንዱም እንደሥራው መጠን የምሰጠውን ዋጋ ይገኛለሁ አልፋና ዖሜጋ፥ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ።» ይህ ነው መለኮታዊ ንጉሥነቱን የሚያመለክተው።

ሁለተኛው ዐይነት ንጉሥነት ሥጋን የለበሰ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ በተቤዠው ሕዝቡ ላይ ያለው እልቅናና ጌትነት እንደመሆኑ ይህም ዘለዓለማዊ ንግሥ እንጂ ለማንም ታልፎ የማይሰጥ ንጉሥነት ነው።

ይህን በሚመለከት ሐዋርያው ቅ. ዮሐንስ በራእይ መጽሐፉ ም.7 ቊ.16 እና 17 ላይ እንዲህ ብሏል:- «ከእንግዲህ ወዲህ አይራቡም፤ አይጠሙምም፤ ፀሐይ አይመታቸውም፤ ሙቀት አያገኛቸውም፤ በዙፋኑ መካከል ያለው በግ እረኛቸው ይሆናል፤ ወደ ሕይወት ውሃ ምንጭም ይመራቸዋል፤ እግዚአብሔር እንባን ሁሉ ከዐይኖቻቸው ይጠርግላቸዋል።»

በምዕራፍ 22 ቊ:3: ላይ «ከእንግዲህ ወዲህ ምንም ዐይነት እርግማን አይኖርም። የእግዚአብሔርና የበጉ ዙፋን በከተማይቱ ውስጥ ይሆናል፤ አገልጋዮቹም ያመልኩታል፤ ፊቱንም ያያሉ።

ሦስተኛው ዐይነት ንግሥ በፈቃዱ ለሰው ዘር ቤዛ ለመሆን ራሱን በአህያ ላይ አስከማስቀመጥ ድረስ ለፈጸመው ትሕትና ያገኘው ሥልጣን ነው።» ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ» (ማቴ. ም. 28 ቊ18)።

እንግዲህ ይህ ሥልጣን የሰውን ልጆች ለመቤዠት የነበረው ሥልጣን እንደመሆኑና ቤዛ የመሆኑና የሰውን ልጅ ከኀጢአት ባርነት ነጻ የማውጣቱ ጉዳይ እስካለቀ ድረስ ያን ሥልጣን ማቆየት አስፈላጊ ባለመሆኑ ያንን ሥልጣን ነው የሚያስረክበው። ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለው መለኮታዊ ሥልጣኑ ግን ለማንም ታልፎ የማይሰጥ ዘለዓለማዊ ሥልጣን ነው። ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው በመሆኑ በፍጹም ሰውነቱ ሥልጣኑን ለእግዚአብሔር ሰጠ ተባለ።

በአንደኛ ቆሮንቶስ ም.15ቊ:28 ላይ «<u>ሁሉ ነገር በክርስቶስ ሥልጣን ሥር ከሆነ በኋላ እግዚአብሔር አብ</u> <u>ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ ወልድ ራሱ ሁሉን ነገር በሥልጣኑ ሥር በአደረገለት በእግዚአብሔር አብ ሥልጣን</u> <u>ሥር ይሆናል</u>» የሚለው ደግሞ መድኃኒታችን ከሦስቱ አካሎች

www.ethiopianorthodox.org

አንዱ በመሆን የሰውን ልጅ ለማዳን በተለየ አካሉ የወሰደውን መሲሕነት ኀላፊነት እንዳስረከበ ሁሉ በዚሁ የሰውን ልጅ ለማዳን ሲል በለበሰው ሥጋ ታዛዥ ለመሆን የፈቀደ መሆኑን ሲያመለክት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም.2 ቍ:6–8 እንዲህ ብሏል:-

«እርሱ የመለኮት ባሕርይ አለው፤ ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል የሚያደርገውን የመለኮት ባሕርይ እንደያዘ መቅረት አልፈለገም: ያለውን ክብር ትቶ እንደ ባሪያ ሆነ፤ እንደ ሰውም ተወለደ፤ በሰው አምሳልም ተገለጠ፤ በትሕትና ራሱን ዝቅ አደረገ፤ እስከ ሞት ድረስ፥ ያውም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ»።

ይህም ማለት ጌታችን መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው የባሕርይ አምላክ ሆኖ ሳለ ለሰው ልጅ ደኅንነት ሲል ለክብሩና ለጌትነቱ የማይገባውን የባርያውን ሥጋ ለብሶ በዚያው በለበሰው ሥጋ ሕማምና ሞትን መቀበልንና እንደ ሰው መታዘዝን ሲፈጽም ተቀዳሚ የሌለኝ ቃለ እግዚአብሔር በመሆኔ ይህን አላደርግም አላለም ማለት ነው።

<u>(ጥበብ) ከሁሉ በፊት ጌታ ፈጠረኝ (አለች) (ምሳ.ም.8 ቍ.22)</u>

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው የመጀመሪያ መልእክቱ ም.1 ቍ.24 ላይ በገለጸው መሠረት ጥበብ የተባለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን እንዴት ጌታ ፈጠረኝ አለ ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል።

ያለ እርሱ ፈጣሪነት ምንም የተፈጠረ ነገር የሌለና አብን በመልክ የሚመስለውና በክብር የሚተካከለው ወልድ የተፈጠረ ነው ማለት ድፍረትም ኃጢአትም ነው።

ተፈጠረ የተባለው ግን የሰውን ዘር ለማዳን በለበሰው ሥጋ ነው። በዚህም መሠረት «ጥበብ ለራስዋ ቤት ሠራች» ተብሎ ተገልጾአል (ምሳ.ም.9 ቍ.1)። የኑሲሱ ቅዱስ ጎርጎርዮስም «ክርስቶስ ማለት ፈጣሪና ፍጡር በአንድ አካልና አንድ ባሕርይ አንድ የሆነ ማለት ነው» ብሏል (ሃይ. አበ፥ ገጽ. 119)።

የቂሣርያው ቅዱስ ባስልዮስ ከፍጥረቱ አስቀድሞ እግዚአብሔር ፈጠረኝ ያለውን የሰሎሞንን ቃል ሲተረጉም እንዲህ ብሏል:- «የጽድቅ የሕይወት ጐዳና እኔ ነኝ፤ በእኔ ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ ማንም ማን የለም አለ፤ የእግዚአብሔር አብ ቃል ይህ አንድ ነገር ነው፤ ዳግመኛም እርሱ በነቢይ ቃል እግዚአብሔር ፈጠረኝ ለፍጥረቱ ተቀዳሚ አደረገኝ አለ። ሰው ከእግዚአብሔር ተወለደ ተብሎ እንደተጻፈ ሰው እንደመሆኑ በሥጋ ስለተወለደው ልደት ይህን ተናገረ» (ሃይ. አበ. ገጽ 107)።

ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ይህን ጥቅስ በተረጐመበት ድርሰቱ እንዲህ ብሏል:- «በምሥጢር አንድ ሲሆን በንባብ እርስ በርሱ የተለያየ ይመስላል፤ እግዚአብሔር ከፍጥረት ሁሉ አስቀድሞ ፈጠረኝ፤ ዓለም፥ ኮረብታም ሁሉ ሳይፈጠር አስቀድሞ ተወለድኩ። የተወለደ ሲሆን እንደምን ተፈጠረ? ካልተፈጠረስ ባልተወለደም ነበር፥ ቀዳማዊ አምላክ ሲሆን እንደምን ተፈጠረ ይባላል? እኛም የምንወልደውን የምንፈጥረው አይደለም። እኛ ፍጡራን ነን፤ የምንወልዳቸው እነርሱም ዳግመኛ፥ ፍጡራን ናቸው። ያልተፈጠረ እግዚአብሔር ቃል ግን መወለዱ ከፈጡር አባት አይደለም፤ እርሱም የተፈጠረ አይደለም፤ ከተፈጠረስ በኋላ ከተወለደ ቀድሞ እንደምን ተፈጠረ? ዳግመኛ ከተፈጠረ በኋላ እንደምን ተወለደ? ተፈጠረ መባሉ ሰው በመሆኑ ምሥጢር ይፈጸማል፤ ስለዚህም አስቀድሞ ደኃራዊ ልደቱን ተናገረ፤ ቅሩባን የሚሆኑ ሰዎችን ልቡና ደስ ሊያሰኝ ወዶ ስለዚህም የሰውነቱን ነገር ይናገር ጀመር (ሃይ አበ ገጽ 186)።

ቅዱስ ቄርሎስ የመጽሐፈ ምሳሌን ም.8 ቍ. 22 ጥቅስ በተረጐመበት ድርሰቱ እንዲህ ብሏል።

«ጥበብ ተፈጠረ፥ ይኸውም ቃል ነው። ከፍጥረቱ አስቀድሞ የነበረ ቃል ሥጋ በመሆኑ ይህ አምላክ ያለ መለወጥ ከንጽሕት ድንግል ከነሣው ሥጋ ጋር አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆኖአልና የእግዚአብሔር ፍጥረቶች ከጥበብ ተገኝተው በባሕርያቸው ጸንተው ይኖራሉና፤ አሁን ግን ጥበብ ከፍጥረት አስቀድሞ የነበርኩ እኔን ጌታ ፈጠረኝ አለች። ተገዥ ባሕርይን ገንዘብ ልታደርግ ሰው ሆነች፤ አብ ፈጠረኝ አላለችም፤ ጌታ ፈጠረኝ አለች እንጂ። ወልድ አባቱን ብቻ ለማመልከት በሚናገርበት ጊዜ አባቴ ይለዋል፤ ተገዥ ባሕርይን ገንዘብ በማድረጉ እርሱ ራሱ ሰው ሆነ፤ ስለዚህም ጌታ ፈጠረኝ አለ፤ አባቴ ፈጠረኝ አላለም» (ሃይ አበ፥ ገጽ 298)።



በሌላ በኩል ደግሞ ወልድ የእግዚአብሔር ጥበቡ ሲሆን የእግዚአብሔር ጥበብ ዘለዓለም ከእግዚአብሔር ጋር አለ እንጂ የተጠፈረ ሊሆን አይችልም። በዚህም መሠረት ፈጠረ የተባለው ቃል በሌሎች ደግሞ ወለደ ወይም ገንዘብ አደረገ ተብሎ ተተርጉሟል።

የእስክንድርያም ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ ቴዎዶስዮስ ይህንን ጥቅስ ሲተረጉም እንዲህ ብሏል «ጠቢብ ሰሎሞን እግዚአብሔር ቃል ያለ ወንድ ዘር ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣውን ሥጋ አየ፤ ወልድ ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ አንድ እንደሆነ ሰው ከሆነ በኋላም ከሥጋ ጋር አንድ አካል በመሆን እርሱ አንድ እንዲሆን ባየ ጊዜ ስለዚህ ሰሎሞን ይህ ቅዱስ ሥጋ እንደተናገረ አድርጎ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ አስቀድሞ የነበረ ልሆን አደረገኝ አለ ብሎ ተናገረ፤ በብዙ አንቀጽ ጥበብ ተብሎ የተነገረለት አካላዊ ቃል የተዋሐደው ይህ ሥጋ ነውና» (ሃይ. አበ፡ ገጽ 349)።

## <u>ለአንዳንድ በትንቢት ለተነገሩ አባባሎች ማብራሪያ</u>

በትንቢት ኢሳይያስ ም:42 ቍ:6–8:- «እኔ እግዚአብሔር ጠርቼሃለሁ፤ በምድር ላይ ፍትሕን ታስገኝ ዘንድ ኀይልን ሰጠሁህ፤ በአንተም አማካይነት ከሕዝቦች ሁሉ ጋር ቃል ኪዳን እገባለሁ፥ ለአረማውያን ሁሉ ብርሃን አደርግ ሃለሁ፤ የዕውሮችን ዐይን ታበራለህ፤ በጨለማ ስፍራ በግዞት የተቀመጡትን ነጻ ታወጣለህ። ስሜ እግዚአብሔር ነው፤ የእኔንም ክብር የሚጋራ ሌላ አምላክ የለም፤ ጣዖታትም ምስጋናዬን እንዲካፈሉ አልፈቅድም።» በምዕራፍ 50 ቍ 4–7:- «ደካሞችን አበረታ ዘንድ ጌታ እግዚአብሔር የምሁር አንደበት ሰጥቶኛል፤ እርሱ የሚያስተምረኝን መስማት እንድችል በየማለዳው ቀስቅሶ ትጋትን ይሰጠኛል። እግዚአብሔር ማስተዋልን ሰጥቶኛል፤ ዐመፀኛም በመሆን ከእርሱ ርቄ አልኰበለልኩም። ለሚገርፉኝ ጀርባዬን ሰጠኋቸው፤ ሲሰድቡኝና ጢሜን ሲነጩ፥ እየተፉም ሲያፌዙብኝ ፊቴን ከእነርሱ በማዞር አልሸሸ ግሁም። ጌታ እግዚአብሔር ስለሚረዳኝ የእነርሱ ስድብ ሊያዋርደኝ አይችልም፤ ይህን ሁሉ በትዕግሥት ለመቀበል ራሴን አዘጋጀሁ፤ በዚህ ሁሉ እንደማ ላፍ ዐውቃለሁ።» በምዕራፍ 52 ቍ:13 ላይ:- «እነሆ፡ አገልጋዩ ሥራው ሁሉ ይከናውንለታል፤ በክብርም እጅግ ከፍ ይላል።» በምዕራፍ 53 ቍ:6 ላይ:- «እኛ እያንዳንዳችን ከመንገድ ወጥተን በመባዘን እንደ ጠፉ በጎች ሆነን ነበር፤ እያንዳንዳችን በየራሳችን መንገድ ሄደን ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር እኛ ልንቀበለው የሚገባንን ቅጣት ሁሉ በእርሱ ላይ አኖረ» በቍጥር 10 ላይ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- «ይህን ሁሉ መከራ እንዲቀበል የእኔ ፈቃድ ነበር፤ የእርሱም ሞት የኃጢአትን ይቅርታ የሚያስገኝ መሥዋዕት ነበር፤ ስለዚህ እርሱ ዘሩን ያያል፤ አገልጋዩም ዘሩን ለማየት ይኖራል፤ በእርሱም አማካይነት የእኔ ዓላማ ይፈጸማል።» በቍጥር 12 ላይ:- «ሕይወቱን ለሞት አሳልፎ ስለ ሰጠ፥ የብዙዎችን ኃጢአት ስለ ተሸከመ፡ ለበደለኞችም ስለማለደ ከታላላቆች ጋር ድርሻ እሰጠዋለሁ፤ ከኀያላንም ጋር ምርኮን ይካፈላል» ተብለው በተገለጹት የተለያዩ ትንቢቶች የወልድ ክብር ከአብ ክብር ያነሰ ተደርጎ እንደተነገረ የሚመስላቸው ወገኖች የሚከተሉትን ጥቅሶች ትክ ብለው ሊመለከቱአቸው ይገባል።

«ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ፥ መካር፥ ኀያል አምላክ፥ የዘለዓለም አባት፡ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል» (ኢሳ. ም.9 ቍ:6)።

«አንቺም ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘለዓለም የሆነ በእስራኤልም ላይ ገዢ የሚሆን ይወጣልኛል» (ሚክ.ም.5 ቍ:2)።

«የጽዮን ልጅ ሆይ፥ እነሆ፥ መጥቼ በመካከልሽ እኖራለሁና ዘምሪ፥ ደስም ይበልሽ ይላል እግዚአብሔር። በዚያም ቀን ብዙ ሕዝቦች ወደ እግዚአብሔር ይጠጋሉ፤ ሕዝብም ይሆኑኛል፤ በመካከልሽ እኖራለሁ፤ የሠራዊት ጌታ እግዚ አብሔርም ወደ አንቺ እንደ ላከኝ ታውቂአለሽ» (ዘካ. ም.3 ቍ:10–11)።

በተለያዩ አርእስት እንደተገለጸው እግዚአብሔር ወልድ ከሦስቱ መለኮታውያን አካላት አንዱና ፈጣሪ አምላክ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም የሰውን ልጅ ለማዳን የእኛን ሥጋ በመልበሱ ስለእርሱ በሚነገርበት ጊዜ እንደ አምላክነቱም እንደ ሰውነቱም መነገሩ ሊያስገርመን አይገባም፤ ምክንያቱም የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ ተግባራዊ የሆነው ባለ መቀላቀል፥ ባለመደባለቅ፥ ባለመለያየት፥ ባለመለዋወጥ፡ ባለመጠፋፋትና ባለመዋዋጥ ነውና። ይህም በመሆኑ በአንድ ቦታ የእግዚአብሔር ባሪያና የእግዚአብሔር መልእክተኛ እንደተባለ ሁሉ በሌላ ቦታ ደግሞ ድንቅ፥

www.ethiopianorthodox.org

መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘለዓለም አባትና የሰላም አለቃ መባሉን እናስተውል። የሰውን ልጅ ሥጋ የለበሰ እንደመሆኑ ሕማም እንዲቀበል ያደረገው እግዚአብሔር ነው ቢባልም የእርሱ ክብር ከአብ ክብር የማያንስ መሆኑን ለማመልከት ደግሞ በትንቢት ኢሳይያስ ም.53ቍ:12 ላይ «እርሱ ሕይወቱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአል» ተብሎአል።

ነቢዩ ዘካርያስም ያ ወደዚህ ዓለም መጥቶ በሰው ልጆች መካከል ሊኖር ያቀደው እግዚአብሔር እንጂ ሌላ አለመሆኑን ሲያመለክት «የጽዮን ልጅ ሆይ እነሆ መጥቼ በመካከልሽ እኖራለሁና ዘምሪ፤ ደስም ይበልሽ ይላል እግዚአብሔር» በማለት አረጋግጦአል።

የእግዚአብሔርና የመሲሑ ግንኙትም በአምላክና በፍጡሩ ወይም በአገልጋዩ መካከል ያለና የመሲሑ ድርጊቶችም በእግዚአብሔር ሥልጣን ሥርና በእርሱም ፈቃድ ብቻ እንደሆኑ የሚመስላቸው ወገኖች ይኖሩ ይሆናል።

ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው እግዚአብሔር ወልድ ከተዋሕዶ በኋላ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ሆኗል። ፍጹም ሰው በመሆኑ ለሞት ታልፎ ቢሰጥም ሕይወቱን ለሞት አሳልፎ የሚሰጠው ግን በገዛ ፈቃዱ ነው እንጂ ማንም አስገድዶት አይደለም። ስለዚህም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል ም.10 ቍ: 17–18 ላይ ነፍሱን ሊያኖራትም፥ ሊያነሣትም የሚችለው እርሱ ራሱ ብቻ መሆኑን ገልጾአል።

ጌታችን በሰውነቱ ለመለኮት ተገቢ ክብሩን መስጠት ስላለበት ባሪያ ወይም አገልጋይ ተባለ፤ እንዲሁም በፈጣሪና በፍጡር መካከል ያለ ግንኙነት መሰል አነጋገር ተነገረለት። በመለኮት ያልተዋጠው ትስብእት የመለኮትን ክብር ቢገልጽም መቼም ቢሆን መለኮት ከትስብእት የተለየበት ጊዜ አይገኝም።

ወልድ የሰውን ሥጋ ለብሶ ለሰው ልጆች ቤዛ እንዲሆን የተላለፈው መለኮ ታዊ ውሳኔ በሰብአዊ ቋንቋ በሚገለጥበት ጊዜ ያንን ሁሉ መከራ እንዲቀበል የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበር ተብሏል።

እግዚአብሔር ለእርሱ የክብር ቦታ ሰጠው የሚለውን አባባል በምንመለ ከትበት ጊዜ ሟችና በስባሽ የሆነው የሰው ልጅ ሰውነት ከመለኮት ጋር ተዋሕዶ ማድረጉ ለትስብእት ክብር የተሰጠው መሆኑን ያመለክተናል። ከሟችነት ወደ ሕያውነት ከሰውነት ደግሞ ወደ አምላክነት ደረጃ ከፍ ማለት በቀላሉ የሚገመት አይደለም።

ስለዚህ ስለ ጌታችን የተነገሩት በአንድ ፍጡር ላይ እንጂ በፈጣሪ ላይ ሊነገሩ የማይገባቸው ቋንቋዎች መነገራቸው ያልተጠፋፋውን የመለኮትንና የትስብእትን ውሕደት የሚያመለክቱ በመሆናቸው ሊያስገርሙን ወይም ሊያስደነግጡን አይገባቸውም።

<u>«ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ፤ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአል»</u> (ማቴ:ም:4 ቍ:10)።

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈታኙን ሰይጣን «ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ፤ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአል» ብሎ በኦሪት ዘዳግም ም.6 ቍ:13 – 15 ያለውን ጥቅስ በመጥቀስ መልስ የሰጠው ሲሆን ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች በተላከው በሐዋርያው በቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ም. 2 ቍ:10 ላይ «ለኢየሱስ ስም ክብር በሰማይና በምድር፥ ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በጕልበታቸው ይንበረከካሉ» በመባሉ ሁለቱ አባባሎች ተቃራኒ ይመስሉ ይሆናል።

በየጊዜው ተመላልሶ እንደተነገረው መድኀኒታችን ሳይጠፋፋ የተዋሐደ የመለኮትና የትስብእት ባሕርይ ያለው በመሆኑ አንዳንድ ጊዜ እንደፍጹም አምላክ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እንደ ፍጹም ሰው ሆኖ ይነገርለታል። ወደ ዕብራውያን በተላከው መልእክት ም.2 ቍ:17 ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሁሉም ነገር ሰዎችን መምሰል እንደተገባው ተገልጾአል። በማቴዎስ ወንጌል ም.12 ቍ:32 ላይ በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሰነዘረ ኃጢአቱ ይቅር ይባልለታል ማለቱና በሉቃስ ወንጌል ም.2 ቍ:52 ላይ ጌታችን ኢየሱስ በጥበብና በቁመት ዐደገ መባሉ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው እንደመሆኑ በፍጹም ሰውነቱ ስለማንኛውም ሰው የሚነገር አባባል ነው።

ጌታችን ለእኛ ቤዛና አርአያ ለመሆን በሚጸልበት ጊዜ እርሱ ጸሎት የሚያስፈልገው ሆኖ አይደለም። እርሱ በሁሉም ነገር ሰውን ስለመሰለ እንደ ሰው በሚጸልይበትም ጊዜ አምላኬ ብሎ መጸለይ ነበረበት። ሰው ሁሉ የሚጸልየው ለእግዚአብሔር እንደ መሆኑ እርሱም



እግዚአብሔር ብቻህን እውነተኛ አምላክ ብሎ ለአብ የጸለየ መሆኑ በዮሐንስ ወንጌል ም.17 ቍ: 3 ላይ ተገልጾአል። ምንም እንኳ ጌታችን ወደዚህ ዓለም መጥቶ የእኛን ሥጋ የለበሰው እኛን በቤዛነቱ ለማዳን ፈቅዶ መሆኑ ቢታወቅ ሕማሙን ተቀብሎ የሚሞትበት ጊዜ ሲቃረብ ያቺ የመከራ ጽዋ ትቀርለት ዘንድ መጸለዩ በችግር ጊዜ ከችግርና ከመከራ እንዲያድነን የእግዚአብሔርን እርዳታ መለመን እንደሚገባን ለእኛ አርአያ ለመሆን ነው። በዚህም ጊዜ የሚያበረታታው መልአክ መታየቱ የእርሱን ፍጹም ሰውነትና የሰው ልጅ ደግሞ ያለ እግዚአብሔር እርዳታ ደካማ መሆኑን ሲያመለክተን ነው (ሉቃ.ም.22 ቍ:42–43)።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ልዩ ልዩ ምሳሌዎች የሚያመለክቱት መድኀኒ ታችን ያልተጠፋፋ ፍጹም የመለኮትና ፍጹም የሰውነት ባሕርይ ያለው በመሆኑ እንደማንኛውም ሰው የሰውነትን ግብር የሚፈጽም መሆኑን ነው። ሰውም በመሆኑ ከኃጢአት በቀር የሰው ልጅ በሰብአዊ ተፈጥሮው የሚከተላቸውን እርምጃዎች ሁሉ ተከትሎ ዐልፎአል ማለት ነው።

ቀደም ብሎ በቀረበው ጥቅስ «ለአምላክህ ብቻ ስገድ፤ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአል» ብሎ መልስ በሰጠበት ጊዜ እኔ አምላክ አይደለሁምና ለኔ አትስገድ፤ ወይም እኔን አታምልክ አላለም። ይህም በመሆኑ ሁለቱ ጥቅሶች ተቃራኒ አይደሉም።

## <u>የሙታን ትንሣኤ በኵር</u>

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ም.9 ቍ. 25 ላይ የመኰንኑን ልጅ፥ በሉቃስ ወንጌል ም. 7 ቍ. 15 ላይ የመበለቲቱን ልጅ፥ በዮሐንስ ወንጌል ም.11ቍ. 44 ላይ ደግሞ አልዓዛርን ከሞት ማስነሣቱ የተገለጸ ከመሆኑም በላይ በማቴዎስ ወንጌል ም.27 ቍ. 53 ላይ ጌታችን ነፍሱን በሰጠ ጊዜ ሞተው ከነበሩት ቅዱሳን ብዙዎች ከመቃብር ወጥተው መታየታቸው ተገልጾአል።

ታዲያ ይህ ሆኖ ሳለ መጀመሪያ መደ ቆሮንቶስ ሰዎች በተላከው የሐዋ ርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ም.15 ቍ.20 ላይ፥ እንዲሁም ወደ ቆላ ስይስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም.1ቍ. 18 እና በራእየ ዮሐንስ ም. 1ቍ.5 እንደተገለጸው ክርስቶስ የሙታን ትንሣኤ በኵር ነው በመባሉ አባባሎቹ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ይመስሉን ይሆናል።

እነዚያ ከሞት ተነሡ ተብሎ የተነገረላቸው ሰዎች ሁሉ ለየተወሰነ ጊዜያ ከኖሩ በኋላ ሞቱ እንጂ እንደተነሡ የቀሩ አይደሉም። በመጨረሻው ትንሣኤ ሙታን ጊዜ እንደሌሎቹ ሁሉ እንደገና ይነሣሉ። የጌታችን ትንሣኤ ግን እንደገና ላለመሞት በመጨረሻው ዘመን ለሚደረገው የሙታን ትንሣኤ የመጀመሪያ በመሆኑ ለሙታን ትንሣኤ በኵር ተባለ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሙታን ትንሣኤ በኵርነት በሚናገርበት ጊዜ ሙታን ሁሉ ወደፊት ጌታችን ለፍርድ ወደዚህ ዓለም ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ ከሞት እንደሚነሡ ማስረጃ ለማቅረብ ብሎ ነው። ጌታችን በብዙ ነገሮች እርሱን እንድን መስል እንደሚያደርገን በትንሣኤውም እርሱን ሊያስመስለን አስቀድሞ ተነሥቶአል ማለትም ለሙታን ትንሣኤ በኵር ሆኖአል።

<u>«በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ በደሉ ይቅር ይባልለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ ግን በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው በደሉ ይቅር አይባልለትም»</u> (ማቴ: ም:12 ቍ:32)።

ይህ አባባል ከሦስቱ የመለኮት አካሎች በአንዱ ላይ ብቻ የስድብ ቃል የሰነዘረ ማለት ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ ተብሎ በሚነገርበት ጊዜ እግዚአብሔር ወይም አምላክ የሚለውን መለኮታዊ መጠሪያ ተክቶ ስለሚገባ ነው። በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ በደሉ ይቅር ይባልለታል ማለቱ ተሳዳ ቢው ሰው የጌታችንን አምላክነት ሳያውቅ ተራ ሰው መስሎት ከኃጢአተኞች ጋር የሚበላና የሚጠጣ የኃጢአተኞች ወዳጅ ብሎ የሚሳደብ ሰው ስለበደሉ በልቡ እስከተጸጸተ ድረስ ኃጢአቱ ይቅር ይባልለታል። ነገር ግን በእግዚአብሔር ኃይል በቀር በሰው ኃይል ሊፈጸሙ የማይችሉትን የመንፈስ ቅዱስን ክንዋኔዎች ጸሐፍትና ፈሪሳውያን እንዳደረጉት የሰይጣን ሥራ አድርጎ ማውራት ወይም የስድብ ቃል መሰንዘር ይቅርታ የማይደረግለት ኃጢአት ነው። ጌታችንም ሊል የፈለገው ይህንኑ አባባል ነው።

ጌታችን የሰው ልጅ በሚልበት ጊዜ ስለራሱ መናገሩ እንደመሆኑና የተዋሐደ እንጂ ያልተቀላቀለና ያልተጠፋፋ መለኮትና ትስብእት ባሕርይ ያለው እንደመሆኑ ከኀጢአት በቀር በዚህ ዓለም በሰዎች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ችግሮች ደርሰውበታል። ጌታችን በዚህ ዓለም እንደ ማንኛውም ሰው ይኖር በነበረበት ዘመን በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ መለኮታዊ ክብሩ ያልታወቀ

www.ethiopianorthodox.org

በመሆኑ ሕማም አድርሰውበት በሚሰቅሉት ጊዜ «አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁትምና ይቅር በላቸው ብሎ ጸልዮላቸዋል። ይህንኑ የጌታችንን አባባል በመመርኰዝ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መጀመሪያ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ምዕ. 2 ቁ. 8 ላይ «ዐውቀውትስ ቢሆኑ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር» ያለው።

በሌላ በኩል ደግሞ የሰው ልጅ በሚልበት ጊዜ ስለ ራሱ ማለቱ ሳይሆን ምናልባት ስለማንኛውም ሰው ማለቱ ሊሆን ስለሚችል በእግዚአብሔር ላይ ሳይሆን በሰው ላይ ለተሰነዘረ ስድብ በንስሐ የእግዚአብሔር ይቅርታ ይገኛል ማለቱ ሊሆን ይችላል።

«<u>ለምን ደግ ትለኛለህ? ከአንድ ከእግዚአብሔር በቀር ደግ የለም</u>» <u>(ማቴ. ምዕ.16 ቁ.17፡ ማር. ምዕ.12ቁ. 18፡ ሉቃ. ምዕ. 18ቁ.18–18)።</u>

በዚህ አነጋገሩ እግዚአብሔር ሳልሆን እንዴት ለእግዚአብሔር ብቻ መጠሪያ በሆነ ስም ትጠራኛለህ በማለት መለኮታዊ ክብር የሌለው መሆኑን እንደተናገረ አስመስለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ።

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የሰውን ጥልቅ ሐሳብ የሚያውቅ እንደመሆኑ ደጉ መምህር ሆይ፡ ባለው ጊዜ በዚያ በተናጋሪው ሰው አስተሳሰብ ጌታችንን እንደ ተራ ሰው እንጂ እንደ አምላክነቱ ያላመነው ሆኖ ሳለ አምላክ ብቻ ሊጠራበት በሚገባ ቅጽል ስም መጥራቱን ስላልፈቀደ ነው እንጂ እኔ ደግ አይደለሁም ወይም እኔ እግዚአብሔር አይደለሁም ለማለት አይደለም። አንድን ተራ ሰው ለአምላክ ብቻ መጠሪያ በሆነ ስም ጠርቶ ማወደስ እንደሚያስደስተው በመገመት የጌታችንን መለኮታዊ ክብር ያልተገነዘበው ሰው ጌታችንን ደጉ መምህር ሆይ ብሎ የጠራው በዚያን ጊዜ በሃይማኖት መሪዎቻቸው ዘንድ በዚህ ስም መጠራት የተለመደ ስለነበረ ነው።

የጌታችን የአስተሳሰብ የሰውዬውን አስተሳሰብ ለመቃወምና ቀናውን ትምህርት ለማስተማር እንጂ እርሱ ራሱ ደግ መባልን ለመቃወም አለመሆኑን ለመገንዘብ በዮሐንስ ወንጌል ምዕ. 10 ቁ.11 እና 14 ላይ «እኔ ደጉ እረኛ ነኝ» ብሎ የተናገረ መሆኑን እንመልከት።

ከናትናኤል ጋር አብሮ ባልነበረበት ጊዜ «ፊልጶስ ሳይጠራህ ከበለስ በታች ሆነህ አየሁህ» ያለውና የሰማርያዪቱ ሴት ባል የለኝም ባለችው ጊዜ አምስት ባሎች የነበሩአት መሆኑን የገለጸላት ጌታችን በሁሉም ቦታ ሙሉ ሆኖ የሰውን ውሳጣዊ አስተሳሰብ በትክክል የሚያውቅ እንደመሆኑ ደጉ መምህር ሆይ ብሎ ጌታችንን ያነጋገረው ሰው በጌታችን መለኮታዊ ባሕርይ የማያምን መሆኑን ስላወቀ እኔን ደግ ለማለት አንድም በእኔ መለኮታዊ ባሕር ማመን አለብህ አለበለዚያ ግን ደግ ልትለኝ አይገባህም ማለቱ ነው እንጂ እኔ ደግ አይደለሁም ወይም እኔ እግዚአብሔር አይደለሁም ማለቱ አይደለም (ዮሐ፡ምዕ፡1ቁ፡49፡ ምዕ፡4ቁ፡18)።

ደግ መባልን መቃወሙ ላለመሆኑ «መልካም እረኛ እኔ ነኝ» ያለውን ማረጋገጫ መመልከት ይቻላል (ዮሐ፡ምዕ፡10ቁ፡11)።

«<u>በቀኜና በግራዬ መቀመጥ ግን ከአባቴ ዘንድ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም</u>» (ማቴ፡ምዕ20 ቁ፡23)።

በማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 25 ቁ፡30 – 46፡ በዮሐንስ ወንጌል ምዕ.5 ቁ፡22 ሁለተኛ ወደ ጢሞቴዎስ በተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ምዕ.4 ቁ፡8፡ በዮሐንስ ራእይ ምዕ. 22 ቁ፡12 እና እንዲሁም በተለያዩ የመጽ ሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ለሰው ሁሉ እንደየሥራው ዋጋውንና ፍርዱን የሚሰጠው ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ በግልጽ ተጠቅሶአል።

ለሰው ሁሉ እንደየሥራው ዋጋውን የሚሰጠው እርሱ ራሱ ሆኖ ሳለ ከአባቴ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም ያለባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

መጀመሪያው ምክንያት የዘብዴዎስ ልጆች እናት ከድንግል ማርያም ጋር የነበራትን የሥጋ ዝምድና ተገን በማድረግና የጌታችንን ማንነት ባለመገንዘብ ምድራዊ ገዢ ለመሆን እንደተዘጋጀ ጋምታ አንተ በምትነግሥበት ጊዜ ለአንዳቸው በቀኝህ ለአንዳቸው ደግሞ በግራህ የመቀመጥን ሥልጣን ለሁለቱ ልጆቼ ስጥልኝ ብላ በመለመንዋ የምትለምኑትን አታውቁም ብሎ ይጀምርና በዚህ ዓለም ለእርሱ ተዘጋጅቶ የሚጠብቀው በምድራዊ ዙፋን ላይ ተቀምጦ የመንገሥ ምድራዊ ክብር ሳይሆን የመከራ ጽዋና የመከራ ጥምቀት መሆኑን ገለጸላቸው። የምትለምኑትን አታውቁም ያለው በማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 6 ቁ. 33 ላይ «እናንተ ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን ፈልጉ» ብሎ በተናገረው መሠረት መለመን የነበረባችሁ የሰማዩን እንጂ



የምድሩን ክብር አልነበረም ሲላቸው ነው። እንዲሁም በዮሐንስ ወንጌል ምዕ. 18 ቁ. 36 ላይ «መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለም» በማለት ፊተኛውን አባባል አጠናክሮአል።

በቀኜና በግራዬ መቀመጥ ከአባቴ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም ማለቱ እናንተ እንዳሰባችሁት የዚህን ዓለም ክብር የምሰጣችሁ ሳይሆን ለወዲያኛው ዓለም ክብር ከሆነ ግን ያ ክብር የሚገኘው ለዚያ ክብር ብቁ በመሆን ነው እንጂ በዝምድናና በደጅ ጥናት አይደለም ብሎ ሲያረጋግጥላቸው ነው።

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ የሦስቱን የመለኮት አካሎች ግብር የሚመለከት ነው። አፍአውያን ግብሮች የመለኮታዊ አንድነት ግብሮች ቢሆኑም እነዚህ አፍአውያን ግብሮች በየንዳንዳቸው ስም ለሦስቱም አካሎች ይከፋፈላሉ። ለምሳሌ ከሃሊነትና አዘጋጅነት የአብ፡ ጥበብ የወልድ፡ ስጦታ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ግብሮች ናቸው ቢባልም ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከሃሊነት የላቸውም ማለት አይደለም፡ አብና መንፈስ ቅዱስ ጥበብ የላቸውም ማለት አይደለም። እንዲሁም አብና ወልድ መንፈሳዊ ስጦታን አይሰጡም ማለት አይደለም። ይሁን እንጂ እነዚህ አፍአውያን ግብሮች ለአብ፡ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ተከፋፍለው ስለሚነገሩና ማዘጋጀት ደግሞ የአብ ግብር ስለሆነ መድኀኒታችን ይህንኑ ለማመልከት ሲል ከአባቴ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ በሚልበት ጊዜ ዝግጅት የአብ ግብር መሆኑን ይጠቍምና በወዲያኛው ዓለም በጌታችን ግራና ቀኝ የመቀመጥን ክብር ለመስጠት የግድ መለኮታዊ ውሳኔና ዝግጅት እንደሚያስፈልገው ለመግለጽ ነው። ዝግጅቱ የአብ ግብር ነው ይባል እንጂ ለሰው ሁሉ ዋጋውን የሚሰጠው እርሱ ራሱ መሆኑን አልካደም። እንዲያውም በዮሐንስ ወንጌል ምዕ.5 ቁ.22 ላይ «አብ በማንም ላይ አይፈርድም፡ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ» በማለት አረጋግጧል።

## <u>ፍሬ ያልተገኘባት በለስ</u>

በማቴዎስ ወንጌል ምዕ.21 ቁ. 18 – 19 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራበ ጊዜ አንዲት በለስ አይቶ ፍሬ ይገኝባት እንደሆን በማለት ቢጠጋት ከቅጠል በቀር ምንም በማጣቱ ስለረገማት ወዲያው መድረቋን የሚናገር ሲሆን በማርቆስ ወንጌል ምዕ. 11 ቁ. 13፡ 14 እና 20 ላይ ደግሞ በለሲቱ ደርቃ የተገኘችው በሌላ ቀን ነው።

ወንጌላዊው ማርቆስ እንደገለጸው ጊዜው የበለስ ማፍሪያ ጊዜ አልነበረም።

ታዲያ፡ ጌታችን በአንድ በኩል የበለስ ጊዜ አለመሆኑን እያወቀ፡ በሌላ በኩል ደግሞ ውሱን ባልሆነው መለኮታዊ ዕውቀቱ እንዴት በዚያች ዛፍ ላይ ፍሬ አለመኖሩን ሳያውቅ ቀርቶ ለመፈለግ ሄደ? ማቴዎስና ማርቆስስ ለምን የተለያየ ታሪክ አቀረቡ? ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል።

ፍሬ ፍለጋ መሄዱ በአንድ በኩል ያልተጠፋፋና በመለኮት ባሕርይ ያልተዋጠ የትስብእት ባሕርይ ያለው መሆኑን ለማመልከትና ደቀ መዛሙርቱም እምነት ካላቸው ታላላቅ ታምራትን ለማድረግ እንደሚችሉ ሊገልጽ ላቸው ስለፈለገ ነው። ለምሳሌ አዳም የተከለከለውን ፍሬ በልቶ ራቍትነት በተሰማውና ከእግዚአብሔር መደበቅ በሞከረ ጊዜ እግዚአብሔር አዳምን ወዴት ነው ያለኸው ብሎ መጠየቁ አዳም ያለበትን ቦታ የማያውቅ ሆኖ አይደለም (ዘፍ.ምዕ.3 ቁ.9)። ወንድምህ አቤል ወዴት ነው ብሎ ቃየንን መጠየቁ ቃየን አቤልን እንደገደለው የማያውቅ ሆኖ አይደለም (ዘፍ.ምዕ.4 ቁ.9)። ልብሱን ብቻ ከነካሁ እድናለሁ ብላ በማመን በብዙ ግፊያ መካከል አንዲት ሕመምተኛ ሴት ከጌታችን በስተኋላ መጥታ ልብሱን በነካች ጊዜ ልብሴን የነካ ማነው ብሎ መጠየቁ ማን እንደነካው የማያውቅ ሆኖ አይደለም። እንዲያውም ኀይል ከእኔ እንደወጣ ተሰምቶኛል በማለት ያላወቀ አለመሆኑን ገልጾአል (ሉቃ. ምዕ.8 ቁ.45 – 46)።

ጌታችን ግን እነዚህን ጥያቄዎች የጠየቀባቸው ምክንያቶች በአንድ በኩል ጥፋታቸውን ዐውቀው እንዲናዘዙ ስለፈለገና በሌላ በኩል ደግሞ እርሱ ሁሉን ነገር የሚያውቅና አንዳችም ከእርሱ ሊደበቅ የሚችል ነገር እንደሌለ ሊያመለክታቸው ፈልጎ ነው።

በዚህም መሠረት የበለሱ ዛፍ ፍሬ የሌለበት መሆኑ ሳያውቅ ቀርቶ ሳይሆን የደቀ መዛሙርቱ እምነት እንዲጠናከር ፈልጎ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ፍሬ ተፈልጎ ያልተገኘባት የበለስ ዛፍ የጌታችንን ትምህርት ላልተቀበሉትና ባዶ የአምልኮ ሥርዐትን ብቻ በመያዝ የበጎ ተግባር ፍሬ ለሌለባቸው ለአይሁድ ሕዝብ ምሳሌ ነው።

የማቴዎስንና የማርቆስን የታሪክ አቀራረብ ልዩነት በሚመለከት ደግሞ ማቴዎስ የሆነውን ሁናቴ አጠቃልሎ የተናገረው ሲሆን ማርቆስ ግን ስለበለሲቱ ዛፍ በየጊዜው የታየውንና የተተቸውን በዝርዝር አቅርቦታል። ምናልባትም ጌታችን በለሲቱን እንደረገማት መድረቅ

www.ethiopianorthodox.org

ጀምራ በሌላ ጊዜ ሲመለሱ ሙሉ በሙሉ ደርቃ ያገኟዋት ሊሆን ይችላል። በዚህም አድናቆ ታቸውን ገልጸዋል።

«አባት ሆይ፡ የሚቻል ከሆነ ይህ የመከራ ጽዋ ከእኔ ይለፍ፡ ነገር ግን እንደፈቃድህ እንጂ እንደ እኔ ፈቃድ አይሁን» (ማቴ.ም.26 ቍ.39)።

ጌታችን ይህን ጸሎት በመጸለዩ ሕማምና ሞት የደረሰበት በፈቃዱ ሳይሆን ያለፈቃዱ እንደሆነና በዚህም የአብ ክብር ከወልድ ክብር እንደሚበልጥ አድር ገው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ።

በስቅለቱ ዋዜማ ጌታችን በጌቴሴማኒ ያትክልት ቦታ ያደረጋቸው ድርጊቶች ሁሉ በጭንቀት ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚገባን ለእኛ ትምህርት ሊሰጠን ፈልጎ ብቻ ነው። ወደ ፈተና አታግባን የሚለውን ጸሎት ባስተማረን መሠረት በተፈጥሮ ደካማነታችን ምክንያት በፍላጎታችን ሕማማትን ለመቀበል እንዳንቸኩል ሊያስተምረን ፈልጎ ነው እንጂ የሕማማቱና የሞቱ ጽዋ እንዲቀርለት ለመጸለይ አይደለም። ሕማሙን ላለመቀበልና ላለመሞት ቢፈልግ ኖሮ ምንም ባላስቸገረውም ነበር።

ለምሳሌ ከምኵራብ አስወጥተው ከተማቸው ከተሠራችባት ከተራራው አፋፍ ወደታች ሊጥሉት ሲፈልጉ በመካከላቸው ዐልፎ የሄደ መሆኑን በዮሐንስ ወንጌል ም. 8 ቍ.59 ለመመልከት እንችላለን። እርሱ በፍላጎቱ ራሱን ሰጠ እንጂ ሊይዙት የመጡት ሰዎች ኢየሱስን እንፈልጋለን ባሉት ጊዜ እኔ ነኝ በማለት መለኮታዊ መልስ ሲሰጣቸው ወደኋላ አፈግፍገው በምድር ላይ የወደቁ እንደመሆናቸው እርሱ ቢፈልግ ኖሮ ራሱን ለማዳን ባላቃተውም ነበር (ዘጸ. ም3 ቍ. 14፡ ዮሐ ም. 18 ቁ. 6)።

እንዲያውም ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታችንን ሊይዙ ከመጡት ሰዎች መካከል ማልኮስ የተባለውን የሊቀ ካህናቱን አሽከር በሰይፍ ጆሮውን በቈረጠው ጊዜ ሰይፍን የሚመዝዙ በሰይፍ የሚጠፉ መሆናቸውን ገልጾ ቅዱስ ጴጥሮስን ከገሠጸው በኋላ የተቈረጠውን ጆሮ እንደነበረ መልሶለታል (ሉቃ. ም. 22 ቍ. 50–51፡ ዮሐ. ም. 18 ቍ. 10–11)። ይህም ብቻ ሳይሆን የመጻሕፍት አባባል ይፈጸም ዘንድ ሕማም ተቀብሎ ይሞታል እንጂ እርሱ ቢፈልግ ብዙ የመላእክት ሠራዊት አብ ሊልክለት እንደሚችል ገልጾአል (ማቴ. ም. 26 ቍ. 52– 54 ሉቃ. ም. 22 ቍ. 51)።

በሌላ ጊዜ ደግሞ በዮሐንስ ወንጌል ም. 10 ቍ. 17 ላይ «ሕይወቴን አሳልፌ ለመስጠትና መልሼም ለመውሰድ ፈቃደኛ ስለሆንኩ አብ እኔን ይወደኛል። ሕይወቴን በፈቃዴ አሳልፌ እሰጣለሁ እንጂ ከእኔ የሚወስዳት ማንም የለም፤ ሕይወቴን አሳልፌ ለመስጠትና መልሼም ለመውሰድ መብት አለኝ» ከማለቱም በላይ ይህን አባባሉን በተግባር ሲገልጸው ነፍሱ ከሥጋው በምትለይበት ጊዜ «አባት ሆይ፡ ነፍሴን በእጅህ ዐደራ እሰጣለሁ» በማለት በዐደራ መልክ አብ ዘንድ እንዲቈይለት ከማድረጉ በቀር ነፍሱን ለማንም አሳልፎ አልሰጠም (ሉቃ. ም. 23 ቍ. 46)።

ጌቴሴማኒ ሆኖ ባደረገው ጸሎት በሁሉም ነገር እኛን እንደሚመስል ያስተምረናል። ባይጸልይ ኖሮ አብን ብቻ እንጂ እኛን አይመስለንም ነበር።

በዚህም መሠረት ፈተና በሚያጋጥመን ጊዜ ሁሉ በጸሎት እንድንተጋ ሊያስተምረን ፈልጎ ነው እንጂ ጽዋው እንዲቀርለት ፈልጎ አይደለም።

«አምላኬ፡ አምላኬ ለምን ተውከኝ» (ማቴ፡ም፡27 ቍ፡46)።

ይህ አባባል የተነገረው በደካማነቱ ምክንያት ወይም መለኮቱ ከእርሱ በመለየቱ እርዳታ ለመጠየቅ ተብሎ ሳይሆን ችግር በሚያጋጥመን ጊዜ የእግዚአብሔርን እርዳታ መለመን እንደሚገባን እኛን ደካማዎቹን ፍጥረቶች ለማስተማር ብሎ ነው። ስለዚህም ነው በማቴዎስ ወንጌል ም. 11 ቍ. 29 ላይ «ከእኔ ተማሩ» ያለው። በሌላ በኩል ደግሞ ሰው የሆነ አምላክ ማለት ያልተጠፋፋ የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ በመሆኑ ሕማም ሊሰማው እንደሚችል ግልጽ ነው። ለእኛ ለሰው ልጆች ደኅንነት ሲል ሕማም የተቀበለ መሆኑን ለመረዳት በትንቢተ ኢሳይያስ ም. 53 ቍ. 4–5 እና በመጀመሪያው የሐዋርያው የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት ም. 2 ቍ. 21 እንዲሁም በምዕራፍ 3 ቍ.18 ላይ ያሉትን ጥቅሶች ለመመልከት እንችላለን። ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአት በቀር በሁሉም ነገር የሰውን ልጅ መስሏል። እንደዚህ መሆኑንማ ካላመንን የደረሰበትን ሕማም ሁሉ በምትሐት መልክ አሳለፈው እንጂ ሌላ ሰው ቢሆን ኖሮ ሊሰማው የሚችለው የሕማም ስሜት አልደረሰበትም ብለው የጌታችንን መሥዋዕትነት ዋጋ ከሚያሳጡት መናፍቃን ከነማኒ ከነመርቅ...



እንደመሰለፍ ይቈጠርብናል። በእርግጥ ሕማምና ሞት መቀበልን በፈቃዱ አደረገው እንጂ ማንም አላስገደደውም። ስለዚህ ነው ጌታችን «መልካም እረኛ እኔ ነኝ መልካም እረኛ ስለበጎቹ ሕይወቱን አሳልፎ ይሰጣል» ያለው (ዮሐ. ም. 10 ቍ. 11)። ይህም ማለት ጌታችንን እስከ ሞት ድረስ ሊያደርሰው የቻለው የሰውን ልጅ ለማዳን ያለው ፈቃድና በሰው ልጅ ላይ ያለው ፍቅር ነው እንጂ ማንም አስገድዶት አለመሆኑን በዮሐንስ ወንጌል ም. 10 ቍ. 17–18 ገልጾ አል። በምዕራፍ 2ቍ. 19–23 ደግሞ «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱትና እኔ በሦስት ቀኖች እሠራዋለሁ በማለት ስለሞቱ እንዲሁም በኀይሉና በሥልጣኑ ከሞት እንደሚነሣ በምሳሌ ተናግሮአል። እንዲሁም በሌሎች ወቅቶች ወደፊት ስለሚደርስበት ሕማምና ሞት ከዚያም ሞትን ድል አድርጎ እንደሚነሣ በማቴዎስ ወንጌል ም. 26 ቍ. 17–23፡ በማርቆስ ወንጌል ም. 10 ቍ. 17 –28፡ በሉቃስ ወንጌል ም. 22 ቍ 14–22 እንደተገለጸው አስቀድሞ መናገሩ ሕማሙንና ሞቱን አስቀድሞ ራሱ የወሰናቸውና በፍላጎቱ የተፈጸሙ ሁኔቴዎች ናቸው እንጂ በሕማሙና በሞቱ ጊዜ የተናገራቸው አነጋገሮች እኛን ለማስተማር የተነገሩ ከመሆናቸው በቀር እርሱ የማንንም እርዳታ የማይጠይቅ መሆኑን ተረድተን ከመሳሳት እንጠንቀቅ።

«ነገር ግን ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ከአብ በቀር የሚያውቅ የለም፡ የሰማይ መላእክትም አያውቁም፡ ወልድም አያውቅም» (ማር. ም. 13 ቍ:32)።

አብ የሚያውቀውን ቀንና ሰዓት ወልድ የማያውቅ ከሆነ የወልድ ክብርና ሥልጣን ከአብ ክብርና ሥልጣን ያንሳል ማለት ነው የሚሉ ወገኖች አሉ።

በማርቆስ ወንጌል ም. 13 ቍ.32 ላይ፡- «ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ከአብ በቀር የሚያውቅ የለም፤ የሰማይ መላእክትም አያውቁም፡ ወልድም አያውቅም» ያለ ሲሆን በዮሐንስ ወንጌል ም. 10 ቍ.30 ላይ፡- «እኔና አብ አንድ ነን፡» በምዕራፍ 14 ቍ.11 ላይ፡- «እኔ በአብ እንዳለሁና አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፡» በምዕራፍ 16ቍ:15 ላይ፡- «የአብ የሆነው ሁሉ የእኔ ነው» ከማለቱም በላይ በማቴዎስ ወንጌል ም. 24 ቍ.29–35 እና በሉቃስ ወንጌል ም.21 ቍ.25 –22 ዳግመኛ ስለሚመጣበት ጊዜ ሁናቴ ልዩ ልዩ ምልክቶችን በመዘርዘር አስረድቷል። እንግዲህ በአንድ በኩል ዳግመኛ የሚመጣበትን ጊዜ ከነመልክቱ ዘርዝሮ ያስረዳና በሌላ በኩል ደግሞ ከአብ ጋር ያለውን እኩልነት መላልሶ ያረጋገጠ ከሆነ ለምንድነው ታዲያ ወልድም አያውቅም የተባለው ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል።

ለዚህ ጥያቄ ሁለት አማራጭ መልሶች አሉ።

አንደኛ ወልድ ቢያውቅም ይህን ዕውቀት ለሰው ልጆች አይገልጽላቸውም። ይህም የሚሆንበት ምክንያት ተመልሶ የሚመጣበት ጊዜ ሩቅ መሆኑን ካወቁ ንቅተውና ተዘጋጅተው በመጠበቅ ፈንታ ችላ ሊሉ ስለሚ ችሉና ጊዜው ቅርብ መሆኑን ካወቁ ደግሞ በጣም ከመፍራትና ከመደንገጣቸው የተነሣ የጌታችንን ዳግመና መምጫ ጊዜ ብቻ በማሰብ የዚህን ዓለም ኀላፊነ ታቸውን እንዳይዘነጉ ታስቦ ነው። ሁለተኛው ትርጓሜ ደግሞ ወልድ በመለኮቱ ወይም በትስ ብእቱ የሚያውቀው መሆኑን ለመካድ ሳይሆን የዕውቀቱ ምንጭ ያለመለኮት ትስብእት ብቻ አለመሆኑን ለመግለጽ ነው። ያልተጠፋፋ የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ ባሕርይ ያለው በመሆኑ ወልድ ስንል ሰው የሆነ አምላክ ማለታችን ነው። ስለዚህ እዚህ ላይ ወልድም አያውቅም የተባለው ወልድ በትስብእቱ ለማለት ነው።

«ኢየሱስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት የተወደደ ሆኖ በጥበብና በቁመት እያደገ ይሄድ ነበር» (ሉቃ፡ም.2 ቍ.52)።

ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን ሰው መሆን እንዳስ ፈለገው ለመረዳት በዕብራውያን መልእክት እንዲህ ተብሏል፡- «ልጆች ሥጋና ደም ያላቸው ሰዎች እንደ መሆናቸው ኢየሱስም እንደ እነርሱ ሰው ሆነ። ይህንንም ያደረገው በሞቱ አማካይነት በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን ዲያብሎስን ለመሻር ነው። እንዲሁም ሞትን በመፍራት ምክንያት ዕድሜ ልካቸውን በባርነት ይገዙ የነበሩትን ለመዋጀት ነው፤ የኢየሱስ ፍላጎት መላእክትን ለመርዳት ሳይሆን የአብርሃምን ዘር ለመርዳት አስቦ ነው። ስለዚህ በሁሉም ነገር ወንድሞቹን መምሰል ተገባው» (ዕብ.ም.2 ቍ14–17)።

በም. 4 ቍ:15 ላይ ደግሞ፡- «እኛ ያለን ሊቀ ካህናት በድካማችን ሊራራልን የሚችል ነው፤ ምንም እንኳ እርሱ በሁሉ ነገር የተፈተነ ቢሆን ምንም ኃጢአት አልሠራም» ይላል።

እነዚህ ... ኀኒታችን የሰውን ልጅ ከሞት ለማዳን ከሰው ... ኃጢአት በቀር የሰው ልጅ በተፈጥሮአዊ ተፈጥሮው የሚያልፍባቸውን እርምጃዎች

www.ethiopianorthodox.org

ሁሉ ተከትሎ አልፎአል ማለት ነው። ማንኛውም የሰው ልጅ የቁመትና የጥበብ ዕድገቱ ከዕድሜው ጋር አብሮ የሚሄድ እንደመሆኑ መለኮታዊ ተዋሕዶው ባይለየውም እንኳ መድኀኒታችን ከሰው የተለየ ሁናቴ ማሳየት አላስፈለገውም እንጂ እርሱ ከፈቀደ ምንም የሚሳ ነው ነገር እንደሌለ መገንዘብ አለብን።

በሁሉም ነገር ወንድሞቹን መምሰል ተገባው በተባለውም መሠረት መለኮትን በተዋሐደ ትስብእቱ በቁመትና በጥበብ ማደግን ገንዘብ አደረገ። ዲያብሎስን በመሻር የሰውን ልጅ ከኃጢአት ባርነትና ከሞት ፍርድ ነጻ ለማውጣት ሲል ከሰው ተወልዶ ከኃጢአት በቀር በሁሉም ነገር ከሰው ልጆች ያልተለየ ኑሮ በመኖሩ ስለ እርሱ በሚነገርበት ጊዜ ስለማንኛውም የሰው ልጅ የሚነገረው የንግግር ዐይነት በመሆኑ ሊያስገርመን አይገባም፤ ሰው የሆነ አምላክ ነውና።

«<u>አባት ሆይ፥ ፈቃድህ ቢሆን ይህን ጽዋ ከእኔ አርቅልኝ ነገር ግን የአንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ የእኔ ፈቃድ አይሁን</u>» (ሉቃ:ም:22ቍ:42)።

ይህ ጌታችን የጸለየው ጸሎት በዮሐንስ ወንጌል ም.10 ቍ17–18 «ሕይወቴን አሳልፌ ለመስጠና መልሼም ለመውሰድ ፈቃደኛ ስለሆንኩ አብ እኔን ይወድደኛል፤ ሕይወቴን በፈቃዴ አሳልፌ እሰጣለሁ እንጂ ከእኔ የሚወ ስዳት ማንም የለም፥ ሕይወቴን አሳልፌ ለመስጠትና መልሼም ለመውሰድ መብት አለኝ» ከሚለው ማረጋገጫ ጋር እንዴት ይታረቃል።

በዚህ ጸሎቱ ጌታችን ሞትን እንደፈራና የሚደርስበትም ሕማም ያለፈ ቃዱና ያለፍለጎቱ እንደሚደርስበት ተደርጎ ይገመት ይሆናል።

መድኀኒታችን የሰውን ዘር ለመቤገርት የግድ መሞት እንደነበረበት ስለፈቀደ ነው እንጂ ሊይዙት የመጡት ሰዎች እንኳ ለመያዝ አልደፈሩም ነበር። የምትፈልጉኝ እኔ ነኝ በማለት ካደፋፈራቸው በኋላ ነው የያዙት። ሐሙስ ዕለት ማለት በተሰቀለበት ዋዜማ በአይሁድ እንደሚያዝና ሕማማትና ሞት እንደሚያደርሱበት ለደቀ መዛሙርቱ ነገሮአቸዋል። ለመሞት የፈራ ወይም የማይፈልግ ቢሆን ኖሮ ተዘጋጅቶ ባልጠበቃቸውም ነበር? ሁሉን ነገር ከማወቅ ጊዜና ቦታ የማይወስነው በመሆኑ ቅዱስ ጴጥሮስ የሚክደው መሆኑን በማቴ. ም. 26 ቍ34፥ አህያዋንና ውርንጫዋን እንዲያመጡ ያዘዛቸው ደቀ መዛሙርት ምን እንደሚያጋጥማቸው በማቴ. ም. 21 ቍ:1–4፥ ቅዱስ ጴጥሮስ በዓሣው ሆድ ውስጥ ምን እንደሚያገኝ በማቴ. ም. 17 ቍ:27፥ በደቀ መዛሙርቱ መካከል ከእነርሱ ማን እንደሚበልጥ ይከራከሩ የነበረውን ሐሳብ ማወቁ በማርቆስ ወንጌል ም.9 ቍ:33፥ የሰማርያይቱን ሴት ምሥጢር በዮሐ. ም.4 ቍ18፥ የአልዓዛርን ሞት በዮሐ. ም. 11 ቍ11፥ የፋሲካን ምግብ እንዲያዘጋጁ ለላካቸው ሁለት ደቀ መዛሙርቱ ምን እንደሚያጋጥማቸው በማር ም. 14 ቍ. 13፥ ናትናኤልን በበለሱ ዛፍ ሥር ሆኖ ማየቱ በዮሐ. ም.1 ቍ 48፥ የኢየሩሳሌምና የቤተ መቅደስ መፍረስ ለደቀ መዛሙርቱ መንገሩ በማቴ. ም. 24 ቍ2፥ የትንሣኤ ሙታንና የዓለም ኀልፈት ምልክቶች ለደቀ መዛሙርቱ መንገሩ በማቴ. ም. 24 ቍ 29–31 የገለጠ እንደመሆኑ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ እንዳለው «እርሱ በሰው ልብ ያለውን ሁሉ ያውቅ ስለነበር ስለ ሰው ማንም እንዲነግረው አያስፈልገውም ነበር» (ዮሐ. ም. 2 ቍ 25)። ስለዚህ በእርሱ ላይ የሚደርሰውን ሕማምና ሞት አስቀድሞ ስለሚያውቅ ሞትን ፈርቶ ቢሆን ወይም ለመሞት ፈቃደኛ ባይሆን ራሱን ለማዳን ባልተሳነውም ነበር።

ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያን ጸሎት በጸለየበት ጊዜ የአንድ የክፍል መምህር ለተማሪዎቹ ትምህርት የሚሰጠው በገለጻና በሠርቶ ማሳየት እንደሚያደርገው አደረገ። መድኀኒታችን ለደቀመዛሙርቱ ምን ዐይነት ጸሎት መጸለይ እንደሚገባቸው ቀደም ብሎ ገለጻ አድርጎላቸው ነበር። አሁን በጌተሴማኒ ያትክልት ቦታ ግን የሠርቶ ማሳየት ትምህርቱን አስተ ማራቸው። ይህም ማለት ተመሳሳይ ችግር በሚያጋጥማቸው ጊዜ እንዴት መጸለይ እንደሚ ገባቸው አሳያቸው ማለት ነው እንጂ ጌታችን ሕማማትን ላልመቀበልና ላለመ ሞት ፈልጎ ቢሆን ኖሮ ምንም ባልተሳነውም ነበርና ይህንኑ ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠንቀቅ።

«<u>በዚያን ጊዜ የሚያበረታታው መልአክ ከሰማይ መጥቶ ታየው</u>» (ሉቃ. ም. 22 ቍ. 48)።

መልአክ ሊያበረታታው የሚችለው አንድን ፍጡር እንጂ ፈጣሪን ስለማይሆን ይህ ሁናቴ እርሱ ፍጡር መሆኑን የሚያመለክት በቂ ማስረጃ ነው ብለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ።

የመላእክት ተፈጥሮ ርኅራኄ የተሞላበት በመሆኑና በችግር ላይ የሚያገኙትን ማንኛውንም ሰው ለመርዳት ዝግጁ ሆነው ስለሚገኙ በጌታችን ላይ የደረሰው ሕማም በፍላጎቱና በፈቃዱ መሆኑን ባለማወቁ ይህ የተጠቀሰው መልአክ የማንም እርዳታ የማያስፈልገውን ጌታችንን



ለመርዳት ብቅ አለ። ሆኖም ሊያበረታታው ታየ አለ እንጂ አበረታታው አላለም። በሌላ በኩል ደግሞ ጌታችን በትስብእቱ መልአክ አበረታታው ቢባል ምንም የሚያስገርም አይደለም። ምክንያቱም መድኀኒታችን በዚህ ዓለም በነበረበት ጊዜ ከኀጢአት በቀር በሁሉም ነገር የሰውን ልጅ መስሎአልና።

የዚህ መልአክ ጌታችንን ለማበረታታት መታየት ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ሰይፉን መዝዞ ማልኮስ የተባለውን የሊቀ ካህናቱን አሽከር ጆሮ ከመቍረጥ ጋር ተመሳሳይ ነው። ጌታችን ግን ለቅዱስ ጴጥሮስ አድራጎት የነበረው አስተሳሰብ እንደሚከተለው ነው። «ሰይፍን የሚያነሡ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን መልሰህ ወደ ሰገባው ክተት። ለመሆኑ እኔ አባቴን ብለምን እርሱ በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ የመላእክት ሠራዊት ሊልክልኝ የማይችል ይመስልሃልን? እንዲህ ከተደረገ ደግሞ መከራ መቀበል አለበት የሚለው የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል እንዴት ይፈጸማል?» (ማቴ. ም. 26 ቍ. 52 – 54)። ይህንንም ከተናገረ በኋላ የተቈረጠውን ጆሮ በመፈወስ ቀድሞ እንደነበረ የመለሰለት መሆኑን በሉቃስ ወንጌል ም. 22 ቍ 51 ላይ ይመለከቷል።

<u>የፍጥረት ሁሉ በኵር ነው</u>

በዮሐንስ ወንጌል ም. 1 ቍ 3 ላይ ማንኛውም የተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ያለወልድ ፈጣሪነት የተፈጠረ እንደሌለ የተገለጸ ሲሆን ወደ ቆላስይስ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ም.1 ቍ:15 ላይ «ክርስቶስ ለማይታየው እግዚአብሔር እውነተኛ ምሳሌ ነው። እርሱ ሁሉ ነገር ከመፈጠሩ በፊት የነበረ የፍጥረት ሁሉ በኵር ነው» በመባሉ ሁለቱ አባባሎች ተቃራኒ ይመስሉ ይሆናል።

ሁለተኛውን ጥቅስ መሠረት በማድረግ አንዳንድ ወገኖች ጌታችንን ፍጡር ነው የማለት ድፍረትን የተሞላ ክርክር ያቀርባሉ።

አንደኛ( ሁሉ ነገር ከመፈጠሩ በፊት የነበረ አለ እንጂ ተፈጠረ አላለም።

ሁለተኛ የፍጥረት ሁሉ በኵር ነው ማለት በመጀመሪያ የተፈጠረ ነው ሊባል የማይቻልበት ምክንያት በኦሪት ዘፍጥረት ም:1ቍ:1 ላይ እግዚአ ብሔር በመጀመሪያ የፈጠረው ሰማይንና ምድር መሆኑ ስለተገለጠ ነው። በመጀመሪያው ጥቅስ መሠረት ሁሉን ነገር የፈጠረ ቃል ነው ተብሎአል። ይህ ሁሉን ነገር የፈጠረው በኦሪት ዘፍጥረት ም. 1 ላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔር ነው። ታዲያ ሁሉን ነገር የፈጠረው እግዚአብሔር በኵር በመባሉ ብቻ እንዴት ከፈጣሪ አምላክነት ወደ ፍጡርነት ሊያዛውሩት በቁ? ችግራቸው በኵር የሚለው ቃል በጥቅሱ ውስጥ እንዴት ሊገባ ቻለ የሚል ከሆነ እዚህ ላይ በኵር ማለት ከተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ በፊት የነበረ መሆኑን የሚያመለክት ነው እንጂ ፍጡር መሆኑን የሚያመለክት አይደለም። ይህም ለመሆኑ ከዚያ ቀጥሎ በቍጥር 16 እና 17 ላይ በሰማይም ሆነ በምድር ከተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ አንዳችም ያለ እርሱ ፈጣሪነት የተፈጠረ ነገር እንደሌለ ተገልጾአል። ይህም የሚያመ ለክተው እርሱ ከፍጥረት ሁሉ በፊት የነበረ መሆኑንና ሁሉንም ነገር የፈጠረ መሆኑን ነው እንጂ ፍጡር መሆኑን አይደለም። ፈጣሪ እስከሆነ ድረስ ደግሞ ፍጡር ሊሆን አይችልም። ወደ ዕብራውያን በተላከው መልእክት ም.1 ቍ.2 ላይ እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠ ረው በልጁ አማካይነት ነው ስለተባለ እግዚአብሔር የመፍጠርን ሥልጣን ብቻ ሰለሰጠው ነው እንጂ እርሱ መለኮታዊ ክብር ኖሮት አይደለም ይላሉ። ይህ አስተሳሰብ ግን ትክክል አለመሆኑን የምንገነዘበው በዮሐንስ ወንጌል ም.1 ቍ.2 እና ወደ ቆላስይስ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ም.1 ቍ.16–17 ላይ ያለእርሱ ፈጣሪነት ምንም ነገር ያልተፈጠረ መሆኑ ከመገለጹ በቀር የመፍጠር ሥልጣን ከሌላ እንደተቀበለ አልተገለጸም።

እዚህ ላይ የሥላሴን ያንድነትና የሦስትነት ግብር በምንዘረዝርበት ጊዜ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በአብ ልብነት ያስባሉ፤ አብና መንፈስ ቅዱስ በወልድ ቃልነት ይናገራሉ፤ አብና ወልድ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት ይተነፍሳሉ ወይም በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት ይኖራሉ እንላለን። በዚህም መሠረት በወልድ ቃልነት ማለት ይሁን በማለት ስለተፈጠረ በወልድ አማካ ይነት ተፈጠረ ተባለ። እግዚአብሔር ማለት ደግሞ የአብ፡ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ የአንድነት ስም መሆኑን ማወቅ አለብን።

<u>ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም</u>

በዮሐንስ ወንጌል ም.5 ቍ.19 ላይ «እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም፤ ያ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ይህን እንዲሁ ያደርጋል» በማለቱ ወልድ የሚያደርጋቸው ድርጊቶች ሁሉ በአብ ተቈጣጣሪነት

www.ethiopianorthodox.org

እንደሚደረጉ በመገመት ይህን ጥቅስ አብ ከወልድ የሚበልጥበት ማስረጃ አድርገው የሚያቀርቡ ወገኖች አሉ።

ይህ አባባል ግን የመለኮት አንድነትንና የምሥጢረ ሥጋዌን ሁናቴ የሚገልጽ እንጂ የወልድን የበታችነት የሚያመለክት አይደለም። በቊጥር 17 ላይ አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል፤ እኔም እሠራለሁ ብሎአቸዋል። በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት እንደተገለጠው አፍአውያን የሥላሴ ግብሮች ሁሉ የመለኮታዊ አንድነት ግብሮች ናቸው ተብሎአል። ስለዚህ መውለድ፥ ማሥረጽ፥ መወለድና መሥረጽ የተባሉት ውሳጣውያን ግብሮች ካልሆኑ በቀር ሌሎቹ ገብሮች ሁሉ የመለኮታዊ አንድነት ግብሮች ናቸው። ስለዚህ ነው «አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም» የተባለው። ወልድ ከራሱ ምንም ማድረግ አይችልም ማለት ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የጋራ ማለት የመለኮታዊ አንድነት ግብር ነው እንጂ የወልድ ግብር ብቻ አይደለም ለማለት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወልድ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ የሰውን ሥጋ ሲለብስ መለኮትንና ትስብእትን ያዋሐደው ያለማጠፋፋት በመሆኑ አንዳንድ ጊዜ ወልድ በመለኮቱ፥ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ወልድ መለኮቱ ማለቱ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል።

በዚህም መሠረት አይችልም የሚለው ቃል አንድም የመለኮታዊ አንድነት ግብር ነው እንጂ የአንድ አካል ግብር ብቻ አይደለም ለማለት ነው፤ ወይም ደግሞ ወልድ በተዋሕዶ ባሕርይ እንጂ በትስብእቱ ብቻ አይችልም ለማለት ነውና ከዚህ የተለየ አለመሆኑን ተገንዝበን ከመሳሳት እንጠንቀቅ።

«<u>ትምህርቴስ ከላከኝ ነው እንጂ ከእኔ አይደለም</u>» (ዮሐ.ም.7 ቊ16)።

ጌታችን በዚህ አነጋገሩ ከአብ ከመማሩ በቀር እርሱ ራሱ ምንም ዕውቀት እንዳልነበረውና የዕውቀት ምንጭ አለመሆኑን እንደመሰከረ የሚመስላቸው ወገኖች አሉ።

ጌታችን ይህን የተናገረው ይህ ሰው ሳይማር እንዴት መጻሕፍን ሊያውቅ ቻለ ብለው አይሁድ እርስ በርሳቸው ለተጠያየቁት ጥያቄ መልስ ለመስጠት ነው። በአይሁድ ዘንድ አንዳንድ የታወቁ ዝነኞች ምሁራን ነበሩ። የሰውም ዐዋቂነቱ የሚገመተው በአስተማሪው ዝነኛነት ነበር። ለምሳሌ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የራሱን ማንነት ሲያስተዋውቅ በገማልያል እግር አጠገብ እንዳደገ ማለት ገማልያል የተባለው ዝነኛ መምህር እንዳስተማረው ገልጾአል (ሐ.ሥ.ም.22 ቊ.3)።

ጌታችን የገለጸላቸው አገላለጽ የእርሱ መምህር ምድራዊ አለመሆኑንና እንደ እነርሱ በምድራዊ መምህር የማይመካ መሆኑን ለማመልከት ነው እንጂ የአብ የሆነው ሁሉ ማለት ሥልጣኑ፥ ገዢነቱና ዕውቀቱ የእርሱም ገንዘቦች ሳይሆኑ ቀርተው አይደለም (ዮሐ.ም.16 ቊ.15)።

እንደሚታወቀው ጌታችን ሰው የሆነ አምላክ በመሆኑና በዚህ ዓለምም እንደ ሰው በኖረባቸው ዘመናት እኛን መምሰል ስለተገባው አብዛኛውን ጊዜ ያደርጋቸው የነበሩት ድርጊቶችና ይናገራቸው የነበሩ አነጋገሮች በሰውነቱ ነበር (ዕብ.ም.2ቊ? 11–17)። ስለዚህም ነው ሐዋርየው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም.2 ቊ.6–8 ላይ ጌታችን የመለኮታዊ ክብር ያለው ሆኖ ሳለ ራሱን በፈቃዱ ዝቅ አድርጎ አስከሞት ድረስ ታዛዥ በመሆን ራሱን ባዶ አደረገ ያለው። ስለ መለኮታዊ ክብር በሚናገርበት ጊዜ ያን ክብር የአብ ክብር ብቻ እንደሆነ አድርጎ መናገሩ ሊያስገርመን አይገባም። ምክንያቱም እንደዚህ ያለውን አነጋገሩን በሌሎች ጊዜያት ሲያብራራ «እኔና አብ አንድ ነን» «የአብ ሆነው ሁሉ የእኔ ነው» በማለት ገልጾታልና» (ዮሐ.ም.10 ቊ.30 ም.16 ቊ. 15)።

«<u>አባቴ ከእኔ ይበልጣል</u>» (ዮሐ.ም.14 ቊ.28)።

አባቴ ከእኔ ይበልጣል ማለቱ በመለኮታዊ ክብር ከአባቱ ጋር እኩል ቢሆንም የፈጠረውን የሰውን ሥጋ ለብሶ በለበሰው ሥጋ ለሕማምና ለሞት የተዳረገ መሆኑን ለመግለጽ ነው እንጂ ከአብ የሚያንስ መሆኑን ለመግለጽ አይደለም።

አባቴ ከእኔ ይበልጣል ከማለቱ በፊት ብትወዱኝስ ኖሮ ወደ አብ እሄዳለሁ ስላችሁ ደስ ባላችሁ ነበር ብሎአቸዋል። ይህም ማለት እኔ በዚህ ዓለም ላይ እንደማንኛውም ተራ ሰው ሆኜ ባለሁበት ጊዜ ሕማም፥ ውርደትና ሞት የሚጠ ብቀኝ ሲሆን ወደ አባቴ በምሄድበት ጊዜ ግን ከአብ ቀኝ የመቀመጥ ክብር ይጠብቀኛል ማለቱ ነው። ሆኖም ግን ይህን ሕማም ተቀብሎ



በመጨረሻ ለሞት የበቃው በገዛ ፈቃዱ እንጂ ማንም አስገድዶት አይደለም" (ዮሐ.ም.10 ቊ.17–18)።

ለደቀ መዛሙርቱ ወደ አብ እሄዳለሁ ብሎ በነገራቸው ጊዜ ከእነርሱ መለየቱ ስላሳዘናቸው ሊያጽናናቸው ፈልጎ ምንም እንኳ በመለኮታዊ ክብሬ ከአብ ጋር እኩል ብሆን የሰውን ሥጋ በመልበሴና በለበስኩት ሥጋም ሕማምና ሞት የሚደርስብኝ ስለሆነ በዚህ ምክንያት አባቴ ከእኔ ይበልጣልና ከአብ ጋር ባለኝ ዘለዓለማዊው የክብር ዙፋኔ ላይ ሆኜ ወደምመለከበት ወደ አብ እሄዳለሁ ስላችሁ የምትወዱኝስ ከሆነ ልትደሰቱ እንጂ ልታዝኑ ባልተገባችሁም ነበር ብሎአቸዋል ማለት ነው።

ከአብ ጋር ያለውን እኩልነት በተለያዩ ጊዜያት የገለጸ ቢሆንም በተለየ ሕማማትንና ሞትን ለመቀበል ተዘጋጅቶ በነበረበት ዋዜማ «አባት ሆይ፥ ልጅህ እንዲያከብርህ ልጅህን አክብረው» ብሎ የእኩልነት ውል የሚደራደር መሆኑን በዮሐንስ ወንጌል ም.17 ቊ1 እንመለከት።

«<u>እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ፤ አትክልተኛውም አባቴ ነው</u>» (ዮሐ. ም. 16ቊ:1)።

አትክልተኛው የወይኑን ግንድ ተክሎና ተንከባክቦ እንደሚያሳድገው አብም ወልድን ፈጥሮና ሥልጣንን ሰጥቶ ከፍ በማድረጉ በአትክልተኛ እና በወይን ግንድ መካከል ባለው የክብር ልዩነት መጠን የአብ ክብር ከወልድ ክብር ይበልጣል ብለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ።

እዚህ ላይ ጌታችን ስለራሱ የወይን ግንድነትና ስለ አባቱ አትክልተኛነት በሚገልጽበት ጊዜ «እኔና አብ አንድ ነን» ያለውን የራሱን አባባል ለመቃረን ሳይሆን ምሳሌነቱ በመዝሙር 80 ቊ.8–15 ላይ እንደ ተገለጸው እስራኤላውያን ከምድረ ግብጽ ሲወጡ ፍሬ የሚያፈሩ የወይን ግንዶች እንዲሆኑ ታስቦ የነበረ መሆኑን የሚመለከት ነው። ይሁን እንጂ እነዚህ የወይን ግንዶች በትንቢተ ኢሳይያስ ም.5 ቊ.1–7 እንደተገለጸው ወይን በማፍራት ፈንታ ሐምጣጣ ፍሬዎችን አፍርተዋል። ጌታችን ግን በዚህ ዓለም ላይ እንደሰው በኖረባቸው ዘመናት ተገቢውን ፍሬ የማፍራት ምሳሌ ስለሆነ «እኔ እውነተኛው የወይን ግንድ ነኝ፤ አትክልተኛውም አባቴ ነው» ካለ በኋላ በቊጥር 5 ላይ ደግሞ «እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ» ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ገልጾላቸዋል። ይህም ቅርንጫፍነት የሚያመለክተው አንድ የዛፍ ቅርንጫፍ በዛፉ ግንድ ላይ እንዳለ ካልቀጠለ በቀር ሊለመልምና ፍሬ ሊያፈራ እንደማይችል ሁሉ ማንኛውም ምእመን በጌታችንና በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ካልሆነ በቀር ሃይማኖታዊ ፍሬ ሊያፈራ አለመቻሉን ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ደሙን በወይን አማካይነት ስለሰጠን ራሱን በወይን ግንድ ምሳሌነት ገልጾልናል።

እንደሚታወቀው አብና ወልድ የሚለያዩት በመለኮታዊ ክብር በመበላለጠ ሳይሆን ወልድ ከሰው በመወለዱና አብ ግን ከሰው ባለመወለዱ ነው። ወልድ የሰውን ልጅ ከሰይጣን ተገዢነት ነጻ ለማውጣት ሰው መሆን ስለነበረበት መለኮትንና ትስብእትን ባዋሐደ ጊዜ ያልተጠፋፋ ተዋሕዶ በመሆኑ አምላኬ፥ አባቴ ከእኔ ይበልጣል፤ አባቴ አትክልተኛ እኔ የወይን ግንድ ነኝ፤ እኔ የአባቴን ፈቃድ እፈጽማለሁ ብሎ በየጊዜው የተናገራቸው የትሕትና አነጋገሮች ሊያስገርሙን አይገባም። በትስብእቱ ለመለኮት ተገቢውን ክብር መስጠቱ ነውና። ወደ ዕብራውያን በተላከው መልእክት ም. 2 ቊ14–17 በሚነበበው ቃለ እግዚአብሔር እንደተገለጸው ጌታችን ሰው የሆነበት ምክንያት የሰውን ልጅ ከኃጢአት ባርነት ነጻ ለማውጣት ስለሆነ በሁሉም ነገር ወንድሞቹን መምሰል ተገባው ተብሏል።

«<u>የዘለዓለም ሕይወትም ብቻህን እውነተኛ አምላክ የሆንከውን አንተንና የላክኸውን ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ ነው</u>» (ዮሐ.ም.17ቊ3)።

ብቻህን እውነተኛ አምላክ የሆንከውን አንተንና የላክኸውን ኢየሱስ ክርስቶስን በሚልበት ጊዜ ራሱን ከአምላክነት በማግለል አምላክነት የአብ ብቻ መሆኑንና እርሱ ከአብ እንደሚያንስ ማረጋገጡ ነው ብለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ።

ቀደም ተብሎ በሌሎች አርእስት እንደተመለከተው መድኀኒታችን የሰውን ልጅ ከኃጢአት ባርነት ነጻ ለማውጣት መለኮትንና ትስብእትን ባዋሐደ ጊዜ ከኃጢአት በቀር የሰው ልጅ በሰብአዊ ተፈጥሮው የሚያልፍባቸውን እርምጃዎች ሁሉ ተከትሎ ዐልፎአል (ዕብ ም.2 ቊ.14 – 17፥ ም. 4 ቊ15)። እንደ ሰው ጥቂት በጥቂት ዐድጓል፤ እንደ ሰው ተርቧል። እንደ ሰው ተጠምቶአል፤ እንደ ሰው በልቶአል ጠጥቶአል፤ እንደ ሰው ተኝቷል፤ እንደ ሰው ከእንቅልፉ ... ጸሎት አቅርቧል፤ እንደ ሰው ሕማምና ሞት

www.ethiopianorthodox.org

ደርሶበታል። በዚህ ሁሉ ጊዜ መለኮቱ አልተ ለየውም። ይህም አባባላችን መለኮት ታመመ ወይም መለኮት ሞተ ማለታችን አይደለም። አባባላችን ግን ግልጽ መሆን ያለበት ወልድ በሰውነቱ ሞተ ማለታ ችንና መለኮት ከትስብእት የተለየበት ጊዜ አለመኖሩን ነው።

ጌታችን እንደ ሰው በሚጸልይበት ጊዜ ሰው ሁሉ የሚጸልየው ለእግዚአብሔር እንደመሆኑ እርሱም ለአባቱ አንተ ብቻ እውነተኛ አምላክ ነህ ሲል ጸለየ። የዚህም ጸሎት ዋና ዐላማ ጣዖት አምልኮትን ለማውገዝ ነው። እንደ ሰው አምላኬ ወይም እግዚአብሔር ብሎ ካልጸለየ በእርሱ ዘንድ ትስብእት የለም፤ ወይም መለኮት ትስብእትን ውጦ አጥፍቶታል፤ ወይም መለኮትና ትስብእት ተቀላቅለዋል በሚለው በአውጣኪ ክሕደት እንደማመን ይቈጠርብናል።

በዮሐንስ ወንጌል ም.17 ቊ.3 እግዚአብሔር አብ ብቻውን እውነተኛ አምላክ እንደሆነ ተገልጾአል። በመልእክተ ይሁዳ ቊ 25 ላይ እግዚአብሔር ወልድ ብቸኛ አምላክ ነወ ተብሏል። በማቴዎስ ወንጌል ም.12 ቊ.32 ላይ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የተደረገ ስድብ ብቻ ምሕረት እንደማይደረግለት ተገልጾአል። ስለዚህ ተመሳሳይ ጥቅሶች በሚያጋጥሙን ጊዜ ሊያስናክሉን አይገባም።

«<u>ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፥ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ እወ ጣለሁ</u>» (ዮሐ. ም20 ቊ.17)።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህን ጥቅስ በተረጐመበት ድርሳኑ እንዲህ ብሏል፤ «ነገር ግን እርሱ በዚህ ክርስቶስ በእውነት ሰው እንደሆነ አስረዳ፤ ዳግመኛም በትንሣ ጊዜ ከዚህ ከአዳም ባሕርይ ሰው መሆኑን አስረዳ፥ ፈጽሞ ከእርሱ ወደ አልተለየው ወደ አብም ከማረጉ አስቀድሞ ለደቀ መዛሙርቱ አምላኬ፥ አምላካችሁ አለ። ይህን በሰሙ ጊዜ ይህን የተናገረ ሥጋ ብቻ እንዳይመስላቸው ሰው የሆነ እርሱ እግዚአብሔር ቃል አስቀድሞ አባቴ ብሎ ከዚያ በኋላ አምላኬ አለ እንጂ። እኔ ሰው የሆንኩ አምላክ ነኝና እኔም አንድ ነኝና ይህንንም ያንንም እኔ እላለሁ ይላል፤ የሰውን ባሕርይ ገንዘብ አድርጋ አለሁና፤ ኃጢአት የሌለበት እርሱ እኔ ነፍስን ሥጋን በእውነት ተዋሕጄአለሁና ከእኔ ጋር አንድ አካል አንድ ባሕርይ ላደረግሁት ለሥጋ ሥርዓት እንደሚገባ እንዲህ አባቴን አምላኬ ብዮ ጠራሁት ይላል» (ሃይ. አበ.ገጽ 248)።

የጌታችን ልጅነት በመዝሙር 2 ቊ.7 ላይ «እግዚአብሔር አንተ ልጄ ነህ አለኝ» በሚለውና እንዲሁም በዮርዳኖስ ጥምቀትና በደብረ ታቦር መገለጽ ጊዜ ከሰማይ ከእግዚአብሔር አብ ዘንድ «የምወደው ልጄ ይህ ነውና እርሱን ስሙት» ተብሎ በተሰጠው ምስክርነት መሠረት ሲሆን የደቀ መዛሙርቱ ልጅነት ግን ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢቱ «አቤቱ አንተ አባታችን ነህ፤ እኛ ጭቃ ነን፤ አንተም ሠሪአችን ነህ፤ እኛ ሁላችንም የእጅህ ሥራ ነን ተብሎ በተነገረው መሠረት ነው (ኢሳ.ም.64 ቊ.8፥ ማቴ. ም.3 ቊ.17 እና ም .17 ቊ.5)።

አምላኬ ያለውም መለኮትና ትስብእት ሳይጠፋፉ የተዋሐዱ በመሆናቸው ነው። አምላካችሁ ሲል ግን እውነተኛ ፈጣሪያችሁ ማለቱ ነው። በእርሱና በእነርሱ መካከል ያለውን ልዩነት ለማሳየት አባታችንና አምላካችን በማለት ፈንታ አባቴና አባታችሁ አምላኬና አምላካችሁ ብሎአቸዋል።

ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ዝቅ አድርጎ አምላኬ እስከ ማለት ድረስ ያደረሰውን የትሕትና ምሳሌነት ሲተነትን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:- «በዚህ ዐይነት ኢየሱስ ክርስቶስ ያሳየው የትሕትና ጠባይ በእናንተም ሊኖር ይገባል። እርሱ የመለኮት ባሕርይ ያለው ሆኖ ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን የእኩልነት ሥልጣን ላለመልቀቅ አልተከራከርም። ይልቁንም ያለውን ሥልጣን ሁሉ በገዛ ፈቃዱ ትቶ እንደ አገልጋይ ሆነ፤ ሰው ሆኖም በሰው ምሳሌ ተገለጸ» (ፊልጵ.ም.2 ቊ 5–7)።

በሌላ በኩል ደግሞ በቅዱሳት መጻሕፍት ልዩ ልዩ ክፍሎች አንድ ጊዜ ለእግዚአብሔር አብ ሌላ ጊዜ ለእግዚአብሔር ወልድ በሌላ ጊዜ ደግሞ ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ብቻ የአምላክነት ክብር ተሰጥቶ የሚነገርበት ምክንያት በመለኮታዊ ሥልጣን አንድ ስለሆኑ ነው።

በዮሐንስ ወንጌል ም.17 ቊ.3 እግዚአብሔር አብ ብቻውን እውነተኛ አምላክ እንደሆነ ተገልጾአል። በመልእክተ ይሁዳ ቊ.25 ላይ እግዚአብሔር ወልድ ብቸኛ አምላክ ነው ተብሏል። በማቴዎስ ወንጌል ም.12 ቊ.32 ላይ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የተደረገ ስድብ ብቻ ምሕረት እንደማይደረግለት ተገልጾአል። ስለዚህ ተመሳሳይ ጥቅሶች በሚያጋጥሙን ጊዜ ሊያስናክሉን አይገባም።



«<u>በኋላም መንግሥቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ፥ አለቅነትንም ሁሉና ሥልጣንን ሁሉ፥ ኀይልንም በሻረ ጊዜ ፍጻሜ ይሆናል። ... ሁሉ ነገር ከተገዛለት በኋላ እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያን ጊዜ ወልድ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ተገዢ ይሆናል</u>» (1ኛ. ቆሮ. ም.15 ቊ. 24 እና 28)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሰውነቱ ሥልጣን ተሰጥቶት እንደ ነበረ ገልጾአል። ይህም ሥልጣን የተሰጠው የሰውን ልጅ ከኃጢአት ባርነት ነጻ እንዲያወጣበት ነበር። በመጨረሻ ግን በዚያ በተሰጠው ሥልጣን ለሰው ልጅ ቤዛ ሆኖ ነፍሳትን የቀደሰ በመሆኑና ከዚያ በኋላ ያ ያስታራቂነት ሥልጣን አስፈላጊ ባለመሆኑ ያንን ሥልጣን አስረክቦ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባለው መለኮታዊ ክብሩ ለዘለዓለም ይኖራል ማለት ነው ( ማቴ. ም.28 ቊ.18)።

እግዚአብሔር ሁሉን ነገር በክርስቶስ እግር ሥር ካስገዛለት በኋላ ወልድ ሁሉን ላስገዛለት ተገዢ ይሆናል የተባለው በመለኮታዊ ባሕርዩ ከአብ የሚያንስ ሆኖ ሳይሆን ራሱን ዝቅ አድርጎ በለበሰው የሰው ልጅ ሰውነት ተገዢ ለመሆን ስለፈቀደ ነው። የሰውን ልጅ ሥጋ ከለበሰ በኋላ ከኃጢአት በቀር በሁሉም ነገር የሰውን ልጅ መስሏል እንደተባለው የሰው ልጅ ለእግዚአብሔር ተገዢ እንደሚሆን ሁሉ ጌታችንም በለበሰው ሥጋ ተገዢ ሆኗል።

በሌላ በኩል ደግሞ:- በዕለተ ምጽአት የተወጋ ጎኑን፥ የተቸነከሩ እጆቹንና እግሮቹን ስለሚያሳይና በከበበ ትስብእት ስለሚገለጥ ነው እንጂ ወልድ ከአብ ምንጊዜም የሚያንስ ሆኖ አይደለም (ዘካ: ም:12 ቊ:10፥ ዮሐ:19፥7)።

«<u>የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ</u>» (ኤፌ.ም.ቊ.17 1ኛ ጴጥ.ም1 ቊ.7)።

ወደ ኤፌሶን ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ም.1 ቊ 17 እና በመጀመሪያይቱ የሐዋርያው የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት ም.1 ቊ3 ላይ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ የተባለ ሲሆን በዮሐንስ ወንጌል ም.1 ቊ1፥ በሐዋርያት ሥራ ም. 20 ቊ 28፥ ወደ ሮሜ ሰዎች በተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ም.2 ቊ 13 እና በመጀመሪያይቱ የሐዋርያው የቅዱስ ዮሐንስ. መልእክት ም.5 ቊ.20 ላይ ጌታችን ራሱ እግዚአብሔርና አምላክ በመባሉ አባባሎቹ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ከመምሰላቸውም በላይ ጌታችንን ፍጡር ነው የሚሉ መናፍቃን እንደ ማስረጃ ያቀርቡአቸዋል።

ቀደም ተብሎ በሌሎች አርእስት እንደተገለጸው ጌታችን የሰውን ልጅ ሥጋ በለበሰ ጊዜ መለኮት ትስብእትን የተወሐደው ያለመጠፋፋት፥ ያለመቀላቀልና ያለመለዋወጥ ስለሆነ ስለጌታችን በሚነገርበት ጊዜ እንደፍጹም አምላክነቱ ወይም እንደፍጹም ሰውነቱ ስለሚነገር ሊያስገርመንና ሊያስደነግጠን አይገባም። ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው መሆኑን መገንዘብ አለብን። ለምሳሌ በዮሐንስ ወንጌል ም. 15ቊ 1 ላይ እርሱ ስለራሱ «እኔ እውነተኛ የወይን ግንድ ነኝ፤ አትክልተኛውም አባቴ ነው» በሚልበት ጊዜ የክርስትና እምነት በእርሱ አዳኝነት ላይ ተመሥርቶ የማይቀበለው ካለ የሚፈረድበት መሆኑንና አባቴ በሚልበት ጊዜ መለኮትን የሚያመለክት ሲሆን ወይን ግንድነቱ ግን ትስብእቱ ነውና የወልድ ከአብ ማነስ ሆኖ መገመት የለበትም። እንዲሁም በሐዋርያት ሥራ ም.10 ቊ.38 ላይ እግዚአብሔር ጌታችንን ቀባው በሚልበት ጊዜ ትስብእቱን እንጂ መለኮቱን አይደለም። አንድ ሰው የሹመት ቅባት የሚቀባው አንድ የተወሰነ መንፈሳዊ ወይም መንግሥታዊ ክብር ሲሰጠው ነው። ሚሺ፥ ፈራሽና በስባሽ የሆነው የሰው ልጅ ሥጋ ከመለኮት ጋር ተዋሕዶ እንዲያደርግ እግዚአብሔር አከበሮ የእግዚአብሔር ልጅ ለመባል ስላበቃው ተቀባ ተባለ እንጂ መለኮትማ የክብር ጌታ ነው።

በሌላ ጊዜ ደግሞ በዮሐንስ ወንጌል ም.5 ቊ.19 ላይ «አብ ሲሠራ ያየውን ከመሥራት በቀር ወልድ በራሱ ሥልጣን ምንም አይሠራም። አብ የሚያደርገውን ወልድም እንዲሁ ያደርጋል» ማለቱ ወልድ ከአብ ያነሰ ክብር አለው ማለት ሳይሆን አብና ወልድ ፍጹም መለኮታዊ አንድነት ይኸውም የፈቃድ አንድነት ስላላቸው ስለመለኮታዊ አንድነታቸው መናገሩ ነው።

ታዲያ ከላይ የተጠቀሱትን ጥቅሶች እንደማስረጃ በማቅረብ አብ ከወልድ በላይ እንደሆነና ጌታችን ደግሞ መቼም ቢሆን ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል አድርጎ እንዳልገመተ በማስመሰል የሚከራከሩ ወገኖች አሉ።

ጌታችን ግን መለኮታዊ ክብር ያለው መሆኑን በልዩ ልዩ ሁኔታዎች የገለጸ ሲሆን ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

በሲና ተራራ ላይ የሃይማኖት ሕግጋትን የሰጠው የሕግጋቱ ባለቤት እግዚአብሔር አምላክ መሆኑ የታወቀ ነው። ታዲያ ከሕግጋት አንዱ ስለሆነው ስለሰንበት መከበርና መሻር ፈሪሳውያን

www.ethiopianorthodox.org

ባነጋገሩት ጊዜ የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነው የሚል መልስ መስጠቱ ቀድሞውንም ቢሆን ሰንበት እንዲከበር ትእዛዝ ያስተላለፍኩ እኔው ነኝ ማለቱ ነው (ማቴ.ም.12ቊ8)።

አይሁድ ጌታችንን ሊገድሉ የፈለጉበት ዋነኛው ምክንያት ቅዳሜን በመሻሩ ብቻ ሳይሆን ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር በማስተካከሉ ነው ተብሏል (ዮሐ. ም. 5ቊ18)።

ጌታችን የተቸነከሩ እጆቹንና የተወጋ ጐኑን ባሳየው ጊዜ ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ ጌታዬ አምላኬ ብሎ መልስ ሲሰጠው ለምን አምላክ ትለኛለህ ብሎ የገሠጸው ሳይሆን እንዲያውም በእኔ አምላክነት የምታምነው ስላየኸኝ ነውን? ሳያዩኝ በእኔ የሚያምኑ ግን የተመሰገኑ ናቸው በማለት አምላክነቱን አረጋግጦለታል (ዮሐ.ም.20 ቊ28–29)።

ስለዚህ በመጀመሪያ የተጠቀሰው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ የሚለው ጥቅስ አንድም ትስብእቱን በሚመለከት የተነገረ ነው፤ አለበለዚያም ቀድሞ ሳናውቀው ኖረን ጌታችን እንድናውቀው ያደረገን አምላክ ማለት ነውና አባባሎቹ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም (ዮሐ. ም.1ቊ18)።

«<u>እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም፤ ነገር ግን የባርያውን መልክ ይዞ፡ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ</u>» (ፊልጵ.ም.2 ቊ: 6–7)።

ከእግዚአብሔር አብ ጋር በመለኮታዊ ባሕርዩ እኩል ነው እንጂ በመቀማት የሚያገኘው አይደለም። ሆኖም በትሕትና ራሱን ዝቅ አድርጎ ሰው በመሆን ሕማምና ሞት እንዲደረስበት ስለፈቀደ ራሱን ባዶ አደረገ አሰኝቶታል። ሕማምና ሞት የማይደርስበት አምላክ በለበሰው ሥጋ ሕማምና ሞት ደርሰውበታል። ይህንንም ያደረገው እርሱ ምንም የሚያስፈልገው ነገር ኖሮት አይደለም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው እርሱ ሀብታም ሲሆን እኛ በእርሱ ድኽነት ባለጠጎች እንሆን ዘንድ ስለ እኛ ድኻ ሆነ (2ኛ.ቆሮ.ም.8 ቊ.9)።

<u>የቅዱሳን አባቶች ትርጓሜ</u>፡

<u>ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ</u>:- «በምንም በምን ሕማም የሌለበት እውነተኛ የባሕርይ አምላክ፥ እውነተኛ ብርሃን፡ የእግዚአብሔር አብ ኀይሉ የሚሆን ለሕማም፥ ለሞት የማይደፈር እርሱን መናፍቃን በክሕደታቸው እንደ ሰው የግድ ታመመ፤ ደከመ፡ ሞተ እንደምን ይሉታል? ለሞቱ ሰዎች ሕይወትን የሰጠውን ሙታንን ያስነሣውን፥ ያልነበሩትን ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ያስገኛቸውን ታመመ፤ ሞተ እንደምን ይሉታል? ከባሕርዩ ሳይለወጥ ከእመቤታችን ነፍስን ሥጋን ነሥቶ ሰው የሆነ እርሱ እንደ እኛ በላ፤ ጠጣ፤ ከእኛ በነሣው በሰው ባሕርይ ሰው ሆኖ ታመመ፤ ተሰቀለ፤ ሞተ እንጂ እርሱ የባሕርይ አምላክ ሲሆን ሰው ሆነ። ከባሕርዩ ከተለወጠማ ወደ ገነት መግባትን በስተቀኝ ለተሰቀለው ወንበዴ እንደ ምን በአበሠረው ነበር? በመለኮቱ፡ በሥራውም ሁሉ የሚታመም የሚሞት ከሆነ ሥጋውን ከሙታን ለይቶ እንደምን አስነሣ?» (ሃይ አበ፥ ገጽ 76)።

<u>ቅዱስ ቴዎዶጦስ፥ የዕንቈራ ኤጲስ ቆጶስ</u>:- «የሥጋን ሕማም ለመለኮት ገንዘብ በአደረገ ጊዜ የእግዚአብሔር አካል በባሕርዩ በግድ ሕማምን አልተቀበለም፤ ሕማም በሚስማማው ባሕርዩ ኀይልን እንጂ፤ ሞትም በሥጋ ለእግዚአብሔር ቃል ገንዘብ በሆነ ጊዜ ሞትን አጠፋ፤ ከሞትም በኋላ ፈርሶ በስብሶ መቅረትን አጠፋ» (ሃይ አበ፥ ገጽ 175)።

<u>ቅዱስ ቄርሎስ፥ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት</u>:- «የወለደው አብን በመልክ የሚመስለው፥ እርሱ ነው፤ ሽቶ ቀምቶ ከእግዚአብሔር ጋር የተካከለ አይደለም፤ ራሱን አዋርዶ ከድንግል ማርያም የአዳምን ባሕርይ ነሥቶ በሰው ባሕርይ ተገኘ፤ በሰውም መልክ ተገለጠ እንጂ፤ እርሱ ብቻ ተዋርዶ እስከ መሞት ደርሶ እሺ በጄ አለ፤ ሞቱም በመስቀል የሆነው ነው። ከፍጹም ክብሩ ለሁሉ የሚሰጥ እርሱ እስከዚህ ሰው እስከ መሆን ደርሶ ተዋረደ፤ ማንም ማን ግድ ሳይለው እርሱ ብቻ ወረደ በባሕርዩ መገዛት የሌለበት እርሱ ብቻ እኛን ለማዳን የአዳምን ባሕርይ በፈቃዱ ተዋሐደ፥ ከፍጥረት ሁሉ የራቀ እርሱ በእኛ ባሕርይ ተገኘ፤ ሁሉን የሚያድን እርሱ በሞት ከተያዙ ጋር ተቈጠረ፤ ከሰማይ የወረደ፡ ለዓለም ሕይወትን የሚሰጥ የሕይወት ምግብ እርሱ ነው» (ሃይ. አበ፡ ገጽ 293)።

<u>እግዚአብሔር ከሞት ያስነሣው</u>

ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች በተላከው በመጀመሪያው መልእክት ም. 1 ቊ.10 ላይ «እግዚአብሔር ከሞት ያስነሣውን... የልጁን የኢየሱስን ከሰማይ መምጣት»፥ በምዕራፍ 4 ቊ14 ላይ «በኢየሱስ አምነው የሞቱትን እግዚአብሔር ከኢየሱስ ጋር ያመጣቸዋል» የተባለውንና



በሐዋርያት ሥራ ም.2 ቊ24፥ 32፥ ም.2ቊ15፡ ም.4 ቊ10፡ ም.10 ቊ40፡ ም.13 ቊ 30–34፥ 1 ም.17 ቊ31፡ ሮሜ ም. 4 ቊ24፡ ም.8 ቊ11፡ 1ኛ ቆሮ. ም.6 ቊ14፡ ም.15 ቊ15፥ 2ኛ ቆሮ. ም.4 ቊ14፥ ገላ.ም.1 ቊ1፡ ኤፌ. ም. 1ቊ 20፡ ቆላ. ም.2 ቊ:12፡ 1ኛ ተሰ. ም.1 ቊ10፥ ዕብ.ም. 13 ቊ20፥ 1ኛ ጴጥ.ም.1 ቊ. 21 የተነገሩትን ተመሳሳይ አባበሎች በመመልከት ጌታችን በራሱ ከሞት የመነሣት ኀይልና ሥልጣን እንደሌለው የሚመስላቸው ሰዎች ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል።

በተለያዩ ጥያቄዎች ተመላልሶ እንደተገለጸው ጌታችን ሰው የሆነ አምላክ በመሆኑ ስለእርሱ በሚነገርበት ጊዜ እንደፍጹም ሰውነቱ ወይም እንደ ፍጹም አምላክነቱ ይነገራል። ትስብእት ብቻውን ከሞት ሊነሣ የማይችል በመሆኑ በመለኮት ኀይልና ሥልጣኑ የተዋሐደውን ትስብእት ከሞት አስነሣው እንጂ በሦስቱ አካሎች መካከል የሥልጣን መበላለጥ ኖሮ አይደለም።

ጌታችንም በራሱ ፈቃድ እንደሚሞትና በራሱም ፈቃድ ከሞት እንደሚነሣ በግልጽ ሲያብራራ በዮሐንስ ወንጌል ም.2ቊ19 ላይ «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱትና እኔ በሦስት ቀን እሠራዋለሁ» በምዕራፍ 10 ቊ. 18 ላይ ደግሞ «ሕይወቴን በፈቃዴ አሳልፌ እሰጣለሁ እንጂ ከእኔ ሚወስዳት ማንም የለም፤ ሕይወቴን አሳልፌ ለመስጠትና መልሼም ለመውሰድ መብት አለኝ» ብሏል።

እግዚአብሔር የሚለው ቃል የሥሉስ ቅዱስ የጋራ ስም እንደመሆኑ የእግዚአብሔር አፍአዊ ድርጊት ሁሉ የሥሉስ ቅዱስ መለኮታዊ አንድነት ግብር መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል።

<u>ከእግዚአብሔር አብ ምስጋናና ክብርን መቀበል</u>

በሁለተኛው የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት ም.1 ቊ.17 ላይ:- «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ድምፅ ከታላቁ ክብር በመጣለት ጊዜ ከእግዚአብሔር አብ ምስጋናንና ክብርን ተቀብሎአል» የሚለው ጥቅስ በዚሁ ምዕራፍ ቊ.1 ላይ– «አምላካችንና አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ» ከሚለው ጋር እንዴት ይታረቃል ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል።

በተመሳሳይ አባባል በዮሐንስ ወንጌል ም.7 ቊ.39 ላይ:- «ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበር» ተብሎአል። እንዲሁም በም:12 ቊ:16 ላይ «ደቀ መዛሙርቱም ይህን ነገር በመጀመሪያ አላስተዋሉም ነበር፤ ነገር ግን ኢየሱስ ከከበረ በኋላ በዚያን ጊዜ ይህ ስለእርሱ እንደተጻፈ፥ ይህንም እንዳደረጉለት ትዝ አላቸው።» ተብሏል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአት በቀር እንደማንኛውም ሰው በዚህ ዓለም ይኖር በነበረበት ጊዜ ሕማማትን ተቀብሎ፥ ተሰቅሎ፥ ሞቶ፥ ተቀብሮ፥ ከሙታን ተለይቶ በመነሣት ለተከታዮቹ እስከተገለጠበት ጊዜ ድረስ ሐዋርያቱም ሆኑ ሌሎች ስለመለኮታዊ ክብሩ እርግጠኞች አልነበሩም።

ለምሳሌ ለጌታችን በጣም ቅርብ መሆናቸው ከሚነገርላቸው ከጴጥሮስ ከያዕቆብና ከዮሐንስ መካከል ወንድማማቾቹ ያዕቆብና ዮሐንስ ወደ ጌታችን ቀርበው በሚነግሥበት ጊዜ ለአንዳቸው በቀኙና ለአንዳቸው ደግሞ በግራው የመቀመጥ ክብር እንዲሰጣቸው መለመናቸው በምድራዊ ክብሩ እንጂ በሰማያዊ ክብሩ ያላመኑበት መሆናቸውን ያመለክታል (ማር. ም.10 ቊ 35–37)።

በዮሐንስ ወንጌል ም. 11 ላይ ሞቶ የነበረው የአልዓዛር እኅቶች ማርታና ማርያም ጌታችንን ባገኙት ጊዜ እርሱ አጠገባቸው ቢሆን ኖሮ ወንድማቸው ባልሞተም ነበር በማለት በጊዜና በቦታ የማይወሰን መለኮታዊ ኀይል እንዳለው አለማመናቸው ተመልክቶአል።

በማቴዎስ ወንጌል ም. 26 ቊ. 56 ላይ እንደተገለጠው ጌታችን በተያዘ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ጥለውት መሸሻቸው እምነታቸው በጌታችን ምድራዊ ክብር ላይ ብቻ የነበረ መሆኑን ያመለክታል።

ስለዚህ ጌታችን ከሞት በመነሣትና በዐይናቸው እያዩትም ወደ ሰማይ በማረጉ በጌታችን ተራ ሰውነት ላይ ብቻ የነበረው አስተሳሰባቸው ተለውጦ በአምላክነቱ አመኑበት፡ መክበር የተባለውም የትስብእት ነው እንጂ መለኮትማ የክብር ጌታ ነው። አብ አከበረው የተባለውም ወልድ ከትስብእት ጋር ቢዋሐድም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ያልተለየ ክብር ያለው መሆኑን መስከረለት ማለት ነው እንጂ በፊት ያልነበረውን ክብር ሰጠው ለማለት አይደለምና አለመሆኑን ተረድተን ከመሳሳት እንጠንቀቅ። (ከትምህርት መለኮትና ከፍኖተ ብርሃን መጻሕፍት የተወሰደ)

www.ethiopianorthodox.org

## ጥያቄዎች

1. ይህ ዓለም ዘለዓለማዊ አለመሆኑን የምንገነዘብው በምንድነው?
2. ከፈላስፎችት አንዱ አንድ ድርጊት የግድ ምን አለው አለ?
3. ሊዳሰስ ወይም በሕዋሳታችን አማካይነት ሊታወቅ የሚችል ቁሳዊ ነገር ምን መሆኑን ያመለክታል?
4. የእግዚአብሔር አፈጣጠርና የፍልስፍና ግኝቶች የሚለያዩበት ሁናቴ እንዴት ነው?
5. ኦክሲጂን ዓለምን እንዳያቃጥል እግዚአብሔር ምን አደረገ?
6. የሙቀት ጥቅም ምንድነው?
7. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደገለጠው የተማሩና ያልተማሩ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ህልውና እኩል ሊያውቁ የሚችሉበት መንገድ የትኛው ነው?
8. ትንቢቶች ለእግዚአብሔር ህላዌ ማስረጃ የሚሆኑት በምን መንገድ ነው?
9. በክርስትና መሠረተ እምነት ውስጥ ዋነኛውና መጀመሪያው ጉዳይ የትኛው ነው?
10. በምሥጢረ ሥላሴ አመካይነት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮታዊ ክብር አብራራ።
11. ብዙዎች የእግዚአብሔር ወዳጆች ተአምራት ያደረጉ ቢሆኑም ጌታችን ያደረጋቸው ተአምራት ለመለኮታዊ ክብሩ ማስረጃ ናቸው የተባለው እንዴት ነው?
12. ጥበብ ጌታ ፈጠረኝ አለች የሚለው ጥቅስ እንዴት ይተረጐማል?
13. ክርስቶስ የሙታን ትንሣኤ በኲር ነው የሚለው ጥቅስ እንዴት ይተረጐማል?
14. ክርስቶስ የፍጥረቱ ሁሉ በኲር ነው የሚለው ጥቅስ እንዴት ይተረጐማል?

# ምዕራፍ 2

# መጽሐፍ ቅዱስ

## ብሉይ ኪዳን

ነቢዩ ኤልሳዕ:- ይህ ነቢይ ለአገልግሎት የተጠራው «የአቤል መሖላ ተወላጅ የሆነውን የሣፋጥን ልጅ ኤልሳዕን ቀብተህ በአንተ እግር ነቢይ እንዲሆን አድርገው» ተብሎ ኤልያስ በታዘዘው ትእዛዝ መሠረት ነው (1ኛ:ነገ:ም:19 ቊ:16)።

ኤልያስም የእርሻ ሥራውን ያካሄድ ወደነበረው ወደ ኤልሳዕ ሄዶ ካባውን በኤልሳዕ ላይ ደረበለት። ኤልሳዕም ከኤልያስ ፈቃድ ተቀብሎ ወደ ቤቱ ሄዶ አባትና እናቱን ተሰናብቶና ጥማድ በሬዎቹን ዐርዶ ሕዝቡን ከጋበዘ በኋላ ኤልያስን ተከትሎ ሄደ (1ኛ:ነገ:ም:19 ቊ:19–21)።

እግዚአብሔር ኤልያስን በዐውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ የሚወስድበት ጊዜ ሲደርስ ከኤልሳዕ ጋር በመሆን ከጌልጌላ ተነሥተው ጉዞ ጀመሩ። በጉዞ ላይ እንዳሉም ኤልያስ ኤልሳዕን ለሦስት ጊዜ እዚያ ሆኖ እንዲጠብቀው በጌልጌላ፥ በቤቴልና በኢያሪኮ ሳለ ቢነግረው እንቢ ብሎት ከእርሱ ጋር ሄደ። በመጨረሻም ኤልሳዕ እያየ ኤልያስ በዐውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ተወሰደ።

ኤልሳዕ ያደረጋቸው ተአምራት:- ኤልያስ ወደሰማይ ከተወሰደ በኋላ ከእርሱ የወደቀውን ካባ ኤልሳዕ አንሥቶ የኤልያስ አምላክ ወዴት ነው በማለት በካባው የዮርዳኖስን ወንዝ በመታው ጊዜ ወንዙ ለሁለት ተከፍሎለት ለመሻገር ችሎአል።

ጥቂት ሰዎች ከኢያሪኮ መጥተው የዚያች ምድር ውሃ መጥፎ በመሆኑ የአገሩ እርጉዞች እንዲጨነግፉ የሚያደርግ መሆኑን ገለጡለት። ኤልሳኤም በአዲስ ሸክላ ድስት ጨው እንዲያመጡለት ካደረገ በኋላ ወደ ውሃው ምንጭ ሄዶ በመጨመር ጤነኛ እንዲሆን አድርጎታል።

ኤልሳዕ ወደ ቤቴል በሚሄድበት ጊዜ በርከት ያሉ ልጆች ወጥተው አንተ ራሰ መላጣ ከዚህ ውጣ እያሉ በመሳደባቸው ስለ ረገማቸው ሁለት ድቦች ከጫካ ወጥተው አርባ ሁለቱን ሰባብረው ጣሉአቸው።



የእስራኤል፥ የይሁዳና የኤዶም ነገሥታት በሞአብ ላይ በዘመቱ ጊዜ ውሃ አልቆባቸው በጸሎቱ ይረዳቸው ዘንድ ወደ ነቢዩ ኤልሳዕ ሄዱ። ኤልሳዕም በገና የሚደረድር ሰው አስጠርቶ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ ወረደ ዝናብና ነፋስ ባያዩም እንኳ ሸለቆው በውሃ እንደሚሞላ ነገራቸው። እርሱ እንደተ ናገረውም ከኤዶም በኩል የውሃ ምንጭ ፈልቶ ምድሩን ሸፈነው። እነርሱም ሞአብን ድል አድርገው ወደየሀገራቸው ተመለሱ (2ኛ: ነገ:ም:3)።

የነቢያት ጉባኤ አባል የነበረ ባልዋ የሞተባት አንዲት ሴት ለባልዋ ገንዘብ አበድሮት የነበረ አንድ ሰው ሁለት ልጆችዋን ባሪያ አድርጎ ሊገዛቸው እንደሚፈልግ ችግርዋን ነገረችው። ኤልሳዕም ለመበለቲቱ በቤትዋ በሚገኘው ትንሽ ማሰሮ ውስጥ የሚገኘውን ጥቂት ዘይት በብዙ ማድጋዎች ውስጥ እንድትገለብጠው ነገራት።

ኤልሳዕ በተናገረው መሠረት በትንሹ ማሰሮ ውስጥ የነበረው ዘይት በርክቶ መበለቲቱ እንደተነገራት ካደረገች በኋላ ያን የወይራ ዘይት ሸጣ ዕዳዋን እንድትከፍልና የተረፈው ለእርስዋና ለልጆችዋ መኖሪያ እንዲሆን ነገራት (2ኛ:ነገ:ም:4 ቊ:1–7)።

ሱኔም በሚባል ከተማ አንዲት ሴት ነቢዩ ኤልሳዕ ወደዚያች ከተማ በሄደ ቍጥር ብዙ ውለታ ስለዋለችለት የውለታዋን ዋጋ ለመክፈል ፈለገ። እርስዋ መኻን ስለነበረች ወንድ ልጅ እንድትወልድ ጸለየላትና ወለደች። ልጁ ጥቂት ካደገ በኋላ በድንገት ታሞ ሞተ። ነቢዩ ኤልሳዕ ግን ወደ እግዚአብሔር ጸለዮ ከሞት አስነሣው (2ኛ:ነገ:ም:4 ቊ:8–37)።

በመላ ሀገሪቱ ረሀብ በነበረበት በአንድ ወቅት ነቢዩ ኤልሳዕ የነቢያትን ጉባኤ እያስተማረ ነበር። በዚያን ጊዜ ኤልሳዕ አገልጋዩን በትልቅ ድስት ወጥ እንዲሠራላቸው አዘዘው። ከነቢያቱም አንዱ ጎመን የሚመስል ቅጠላቅጠል ለመልቀም ሄዶ በስሕተት የቅል ሐረግ ለቅሞ ስላመጣ በወጥ ውስጥ ተጨምሮ ተሠርቶ በቀረበ ጊዜ በጣም መራራ ሆኖ ሊበላ አልተቻለም። ነቢዩ ኤልሳዕ ዱቄት እንዲሰጡት ጠይቶ በድስቱ ውስጥ በጨመረው ጊዜ መራራነቱ ቀርቶ ሊበላ ተችሎአል (2ኛ:ነገ:ም:4 ቊ:38–41)።

በዓልሻሊሻ ተብሎ ከሚጠራ ስፍራ አንድ ሰው በመከር ጊዜ ሃያ የዳቦ ሙልሙሎችና አዲስ የተቈረጠ እሸት ለኤልሳዕ አመጣለት። ኤልሳዕም ብዛታቸው መቶ ለነበረ የነቢያት ጉባኤ እንዲቀርብላቸው አዝዞ እግዚአብሔር በፈቀደው መሠረት ነቢያቱ በልተው ተርፎአቸዋል (2ኛ:ነገ:ም:4 ቊ:42–44)።

የሶርያ ጦር አዛዥ የነበረው ንዕማን የለምጽ በሽታ ነበረበት። ነቢዩ ኤልሳዕ ከሕመሙ እንደሚያድነው ስለተነገረው ወደ እስራኤል አገር ሄደ ነቢዩ ከለምጹ ፈውሶታል።

ንዕማንም ለነቢዩ ገንዘብ ሊሰጠው ቢፈልግ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቶአል። ንዕማን ተፈውሶ ከሄደ በኋላ የኤልሳዕ አገልጋይ ተደብቆ ንዕማንን በመከታተል ነቢዩ ገንዘብ ላክልኝ ብሎሃል ብሎ በሐሰት ስለወሰደ ነቢዩ ዐውቆበት ለምጽ እንዲወጣበት በማድረግ ቀጥቶታል።

በኤልሳዕ ኀላፊነት ሥር የነበሩት የነቢያት ጉባኤ አባላት ቤት ለመሥራት ፈልገው ዛፍ ለመቍረጥ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ወረዱ። ዛፉንም ሲቈርጡ ሳለ በድንገት የአንዳቸው መጥረቢያው ከዛቢያው ላይ ወልቆ በውሃው ውስጥ ገባ። ያ ሰው ያን መጥረቢያ ከሌላ ሰው ተውሶት ስለነበረ በጣም ተጨነቀ። ነቢዩ ኤልሳዕ ግን አንድ እንጨት ቈርጦ መጥረቢያው በወደቀበት አቅጣጫ በውሃው ውስጥ ስለጣለው መጥረቢያው እንዲንሳፈፍ አድርጎት ሊወጣ ችሎአል (2ኛ:ነገ:ም:6 ቊ:1–7)።

የእስራኤል መንግሥት ከሶርያ ጋር በጦርነት ላይ በነበረበት ጊዜ የሶርያው ንጉሥ በምሥጢር የሚያቅደውን የጦር ዕቅድ ሁሉ ነቢዩ ኤልሳዕ ለእስራኤሉ ንጉሥ ይነግረው ነበር። በዚህም ምክንያት ጉዳዩን ሲመረምር ስለ ኤልሳዕ ሰማ። ኤልሳዕ የሚገኝበትን ቦታ ጠይቶ በዶታን የሚገኝ መሆኑ ስለተነገረው በፈረሶችና በሠረገሎች የተጠናከረ ሠራዊት ወደዚያ ላከ።

የኤልሳዕ አገልጋይ በማለዳ ሲነሣ የሠራዊቱን ብዛት ባየ ጊዜ ደንግጦ ለኤልሳዕ ነገረው። ኤልሳዕ ግን አይዞህ አትፍራ ከእነርሱ ጋር ከተሰለፈው ይልቅ ከእኛ ጋር የተሰለፈው ይበልጣል አለው። ኤልሳዕ ወደ እግዚአብሔር በመጸለይ ዐይኖቹ እንዲከፈቱለት ስላደረገ የኤልሳዕ አገልጋይ በኮረብታው ጐን ብዙ የእሳት ፈረሶችና ሠረገሎች በኤልሳዕ ዙሪያ ተሰልፈው የሚጠብቁ መሆናቸውን ተመለከተ።

በኤልሳዕም ጸሎት አማካይነት የተሰለፉት የሶርያ ወታደሮች ዐይኖቻቸው ታወሩ። ከዚያም ኤልሳዕ እየመራ ወደ ሰማርያ ከወሰዳቸው በኋላ ዐይኖቻቸው እንደገና ለማየት እንዲችሉ ተደርገዋል። የእስራኤልም ንጉሥ ታላቅ ግብዣ ከጋበዛቸው በኋላ ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ

www.ethiopianorthodox.org

ተደርገዋል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሶርያውን በእስራኤል ላይ ወረራ ማድረጋቸውን አቆሙ (2ኛ: ነገ: ም:6 ቁ:8–23)።

የሶርያው ንጉሥ ቤንሀዳድ ሰማርያን በከበበ ጊዜ የምግብ እጥረትና ረሀብ ተከሠተ። የእስራኤሉም ንጉሥ በጣም ተበሳጭቶ ወደ ነቢዩ ኤልሳዕ ሄደ። ኤልሳዕም ነገ በአሁኑ ሰዓት በሰማርያ ሦስት ኪሎ ምርጥ ስንዴ ወይም ስድስት ኪሎ ገብስ በአንድ ጥሬ ብር ይሸመታል አለው። የንጉሡ ባለሟል የኤልሳዕን አባባል በማቃለል እግዚአብሔር የሰማይ መስኮቶችን ከፍቶ እህልን እንደ ዝናብ ቢያዘንብ እንኳ ይህ ሊሆን አይችልም አለው። ኤልሳዕም መልሶ ያን እህል በዐይንህ ታየዋለህ፤ ነገር ግን ከእርሱ ምንም አትቀምስም አለው። እግዚአብሔር ሶርያውንን በእነርሱ ላይ የዘመተ የሚመስል የሠራዊት ድምፅ እንዲሰሙ ስላደረጋቸው ሰፈራቸውን ጥለው ሸሹ። የእስራኤል ሠራዊትም የሶርያውንን ሰፈር ስለማረከ ነቢዩ ኤልሳዕ የተናገረው ትንቢት ደረሰ። ከሰውም ብዛት የተነሣ ያ የንጉሡ ባለሟል በሕዝብ ተረጋግጦ ሞተ። እህሉም ኤልሳዕ በተናገረው መጠን ረከሰ በዐይንህ ታየዋለህ ከእርሱ ግን ምንም አትበላም ያለው የነቢዩ ኤልሳዕ ትንቢት በዚያ ሰው ላይ ደረሰ (2ኛ)ነ:ም:6 ቁ:24–ም:7)።

ሰዎች አንድ ሰው ሲቀብሩ አደጋ ጣዮችን አዩ፤ ሬሳውንም በኤልሳዕ መቃብር ውስጥ ጥለውት ሸሹ፤ የኤልሳዕንም አጥንት በነካ ጊዜ ሰውዬው ድኖ በእግሩ ቆመ። (2ኛ:ነገ.13፥21)።

<u>ትንቢተ ናሆም</u>:- ስለዚህ ነቢይ ሁናቴ የአልቆሽ ከተማ ሰው ከመሆኑ በቀር ሌላ ብዙ የሚታወቅ ነገር የለም። የነበረበትም ዘመን ከአንዳንድ ሁናቴዎች ጋር በማገናዘብ ካልሆነ በቀር መቼ እንደሆነ አይታወቅም። ከአነጋገሩ እንደሚገመተው ግን በንጉሥ ሕዝቅያስና በነቢዩ ኢሳይያስ ዘመን እንደነበረ ይገመታል።

የመጽሐፉ ዋና መልእክት በቀል የእኔ ነው በሚለው የእግዚአብሔር ቃል መሠረት የእስራኤል ሕዝብ ጠላት የነበረችውን ነነዌን እግዚአብሔር የሚበቀላት መሆኑን የሚገልጸው ትንቢት ነው። ይህንንም ትንቢት እንዲህ በማለት ይጀምራል:-

«እግዚአብሔር ተቀናቃኞቹን አይታገሥም፤ ጠላቶቹንና የሚቃወሙትን ሁሉ ይቀጣል፤ ምንም ኀይሉ ታላቅ ቢሆን እግዚአብሔር ለቍጣ የሚቸኩል አይደለም፤ ሆኖም በደለኛውን ሳይቀጣው አይቀርም» (ም:1 ቁ:2–3)።

በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ የተነገረው ስለ ነነዌ ጥፋት ብቻ ሳይሆን፥ አሦራውያን እንደሚደመሰሱና የእግዚአብሔር ሕዝብም ከአሦራውያን ጭቈና እግዚአብሔር የሚታደጋቸው መሆኑን የሚገልጸውን ጥቅስ ቀጥለን እንመልከት:-

«ነነዌ ሆይ፥ በእግዚአብሔር ላይ ሤራ የሚያሤርና ክፉ ምክር የሚመክር ሰው ከመካከልሽ ተነሥቶአል፤ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ለእስራኤል እንዲህ ይላል:- ‹ምንም እንኳ አሦራውያን ኀይለኞችና ቍጥራቸው የበዛ ቢሆን፥ ተደምስሰው እንዳልነበሩ ይሆናሉ። ሕዝቤ ሆይ፥ ምንም እንኳ ከዚህ በፊት መከራ ያጸናሁባችሁ ቢሆን፥ ከእንግዲህ ወዲህ ይህን አላደርግባችሁም። አሦራውያን በእናንተ ላይ የጫኑትን የጭቈና አገዛዝ አስወግዳለሁ፤ እናንተን ያሰሩበትንም እግር ብረት እሰብራለሁ»› (ም:1 ቁ:11–13)።

በተጨማሪ ናሆም ያወገዛቸው ሁለት ኃጢአቶችን ጠቅሶአል። የመጀመሪያው ኃጢአት ጭካኔ የተሞላበት ወታደራዊ ኀይል ነው። የዚህም ውጤት የብዙ ሰዎችን ደም ማፍሰስ፥ የሕዝቦች መፈጀት፥ የድርጅቶች መፍረስ፥ ጦርነቱ የሚካሄደው ከሰውነት ስሜት ወጪ በሆነ ጭካኔ ነበር። እንደዚህ አድርገው ከሰብአዊ ርኅራኄ የራቀ ድርጊት የፈጸሙት ሰዎች:- «በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር:- ‹እነሆ፥ እኔ በጣላትነት ተነሥቼብሻለሁ› ተብለዋል» (ም:2 ቁ:13)።

ሁለተኛው፥ ናሆም ያወገዘው ኃጢአት ደግሞ ገንዘብ ለማግኘት ሲባል የሚደረገው አጸያፊ ንግድ ነው። በዚህም አሠራር ግብረ ገብነትና ታማኝነት ጠፍተው በቦታቸው ገንዘብ ማግበስበስ እንዲተካ ሆኖአል። ይህንንም እንዲህ ሲል ይገልጠዋል:-

«የብዙዎችን ነፍስ ላጠፋች፥ በሐሰት ለተሞላች፥ በዘረፋና በቅሚያ ሀብት ለበለጸገች፥ ለነነዌ ከተማ ወዮላት» (ም:3ቁ:1)።

እንደ ብዙዎቹ ምሁራን አባባል ይህ ትንቢት የተነገረበት ጊዜ ከክርስቶስ ልደት በፊት በሰባተኛው መቶ ዓመት ነው። ይኸውም ቴቤስ የተባለችው የግብጽ ከተማ በአሦራውያን እጅ



መውደቅዋ እንደ ምሳሌ መጠቀሱ ትንቢቱ የተነገረበት ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ666 ዓመት በኋላ መሆኑ ነው (ም:3ቁ:8–10)። ትንቢት የተነገረበት የነነዌ አወዳደቅ ከክርስቶስ በፊት በ612 ዓመት ነው። ታሪክ የተናገረው የቴብስ አወዳደቅ ወደ 666 ከክርስቶስ በፊት ከሆነና ትንቢት የተነገረላት የነነዌ አወዳደቅ ደግሞ በ612 ከክርስቶስ ልደት በፊት ከሆነ የትንቢቱም ዘመን በእነዚህ ዓመቶች መካከል መሆኑ ነው። ሌሎች ምሁራን እንደሚሉት ደግሞ ስለ ቴቤስ ታሪክ የተነገረ በመሆኑ የናሆም የትንቢት ዘመን የቴቤስ ነጻነት ከተመለሰበት ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ654 ዓመትና ከ666 ዓመት መካከል መሆን አለበት። አንዳንድ ምሁራን ደግሞ የናሆምን የትንቢት ዘመን በአርበኞቹ በመቃብያን ዘመን እንደሆነ ገልጸዋል። በዚህም ሆነ በዚያ መጽሐፉ የእግዚአብሔርን ታላቅነትና በደልን የበደለ ሁሉ ከእግዚአብሔር ቅጣት እንደማያመልጥ ይናገራል።

<u>ትንቢተ ዕንባቆም</u>:- ትንቢቶቻቸው በተለይ በሌሎች ሕዝቦች ማለት በአረማውያን ሀገሮች ላይ ያተኰሩት ነቢያት አብድዩ፥ ናሆምና እንባቆም ናቸው። አብድዩ በኤዶማውያን ላይ ጥፋትን የተነበየው የኤዶም ሕዝብ የአይሁድን ጠላቶች በመርዳት ብዙ ችግር እንዲደርስባቸው በማድረጋቸው ነው። ናሆም በነነዌና በአሦር ሕዝብ ላይ ጥፋትን የተነበየው የይሁድን መንግሥት በማጥፋታቸውና ሕዝቡን በመፍጀታቸው ነው። አሁን የምንነጋገርበት የዕንባቆም ትንቢት ደግሞ በባበሎን ጥፋት ላይ ያተኰረው ዐሥሩን የእስራኤል ነገዶች በምርኮ በመውሰዳቸውና የቀሩትንም ሁለቱን ነገዶች በቅርብ ጊዜ ውስጥ የሚወስዱአቸው በመሆኑ ነው። ይህም የሚያመለክተው ትንቢቱን የተናገረበት በመጀመሪያዎቹ የኢዮዓቄም ግዛትና ነቢዩ ኤርምያስ የነበረበት ዘመን መሆኑን ነው።

መጽሐፉ ሦስት ምዕራፎች አሉት። የመጀመሪያው ምዕራፍ የእግዚአብሔር ሕዝብ በፈጸሙት በደል ምክንያት የሚመጣባቸውን ቅጣት የሚመለከት ነው። ዕንባቆምም ፍትሕ መጓደሉንና ኃጢአት መብዛቱን በሚመለከት ወደ እግዚአብሔር ጸሎቱን አቅርቦአል። እግዚአብሔርም በሰጠው መልስ በባቢሎናውያን መሣሪያነት ቅጣትን እንደሚያመጣ ገልጾአል።

ዕንባቆምም ለእግዚአብሔር ያቀረበው ጸሎት እንዲህ የሚል ነው:-

«ዐይኖችህ እጅግ ንጹሓን ስለሆኑ ክፉ ነገርን አይመለከቱም፤ ክፉ ነገር ሲሠራ አይተህ መታገሥ አይሆንልህም፤ ታዲያ እነዚህን ዐመፀኞች እንዴት ዝም ብለህ ትመለከታቸዋለህ? ኃጢአተኞችስ ከእነርሱ ይሰልጥ ደጋግ የሆኑ ሰዎችን ሊያጠፉ ሲነሡ ስለምን ዝም ትላለህ?» (ም:1 ቁ:13)።

ሁለተኛው ምዕራፍ ከለዳውያን፥ ማለት ባቢሎናውያን በትዕቢታቸው፥ በግፍ ሥራቸው፥ ሌሎችን አገሮች በግድ በማስገበራቸው፥ በዝርፊያቸውና ጣዖትን በማምለካቸው ምክንያት ስለሚደርስባቸው ችግር የሚናገር ነው።

ቀደም ብሎ በምዕራፍ አንድ ላይ ዕንባቆም ለጸለየው ጸሎት እግዚአብሔር መልስ ሲሰጠው በምዕራፍ 2 መነሻ ላይ ልቡ የሚታበይበት ዐመፀኛ የመኖር ተስፋ የለውም፤ ጻድቅ ግን በእምነቱ ሕወትን ያገኛልና በትዕግሥት ጠብቅ ብሎታል (ም:2 ቁ:1–4)።

የእነዚያን የግፈኞች ክፉ ተግባርና ወዮታ በሚከተሉት ጥቅሶች ዘርዝሮአቸዋል:-

«የሀብት ብዛት ሰውን ያታልላል፤ ለሀብት የሚስገበገቡም ሰዎች ትዕቢተ ኞች ናቸው፤ በአንድ ስፍራም ዐርፈው አይቀመጡም፤ ሞትና መቃብር በቃኝ ማለትን እንደማያውቁ እነርሱም በቃኝ ማለትን አያውቁም፤ መንግሥታትን የሚወሩትና ሕዝቦችን የሚማርኩት ለዚህ ነው» (:2 ቁ:5)።

«በግፍ በተሰበሰበ ሀብት ቤታችሁን የሞላችሁ፥ አደጋም እንዳይደርስባችሁ መኖሪያችሁን ከፍ ባለ አምባ ላይ ያደረጋችሁ ወዮላችሁ» (ም:2 ቁ:9)።

«ከተማን በዐመፅ ለምትመሠርቱና በሰው ደምም ለምትገነቡት ወዮላችሁ፤ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይህን ወስኖአል፤ ስለዚህም አሕዛብ የሚሠሩት ሁሉ በእሳት ይወድማል፤ የመንግሥታትም ድካም ሁሉ ከንቱ ሆኖ ይቀራል» (ም:2 ቁ:12–13)።

«ኧረ ለመሆኑ የጣዖት ጥቅሙ ምንድነው? እርሱ በሰው እጅ ተቀርጾ የተሠራ ነገር ነው፤ ከሐሰት በቀር ከእርሱ ምንም አይገኝም፤ ታዲያ፥ እርሱን ቀርጾ የሠራው ሰው ምንም መናገር በማይችል በዚህ ጣዖት መታመኑ ምን ሊጠቅመው ነው? ከእንጨት ተጠርቦ የተሠራውን ነገር

www.ethiopianorthodox.org

ንቃ፥ ከድንጋይ ተቀርጾ የተሠራውን ነገር ተነሥ ለምትል ለአንተ ወዮልህ» (ም:2 ቊ:18–19)።

ሦስተኛው ምዕራፍ የነቢዩ ጸሎት ነው። በጸሎቱም ውስጥ እግዚአብሔር በአለፉት ዘመናት ሕዝቡን እንዴት እንደጠበቀ በመዘርዘር ምስጋና ካቀረበ በኋላ ወደፊትም እንደ ቀድሞው ዘመን ጥበቃ ያቀርብ ዘንድ እግዚአብሔርን ተማጽኖአል። ምንም እንኳ ብዙ ችግሮች ቢያካብቡአቸው የእግዚአብሔርን አዳኝነት በተስፋና በትዕግሥት ለሚጠባበቁ ደጋግ ሰዎች ጸሎቱ የሚያጽናና ነው።

<u>ትንቢተ ሶፎንያስ</u>:- ይህ ነቢይ በንጉሥ ኢዮስያስ ዘመን የነበረና ምናልባትም በኢዮስያስ የሃይማኖት ተሐድሶ እንቅስቃሴ ላይ የረዳ ነው። በእር ሱም ዘመን ነቢዩ ኤርምያስ ሥራውን ጀምሮ የነበረ በመሆኑ በትንቢቱ አገልግሎት ከእርሱ ጋር እንደተባበረ ይገመታል። አገልሎቱም ትንቢት ብቻ ሳይሆን ወራሪው የባቢሎን ሠራዊት በቅርብ ጊዜ ውስጥ ጥቃቱን በአይሁድ ሕዝብ ላይ እንደሚሰነዝር ማስጠንቀቂያ መስጠትም ጭምር ነው። ይህም ወራሪ ወታደር በጣም ጨካኝ በመሆኑ ለሕፃናትም ሆነ ለሽማግሌዎች አይራራም። ያ አረማዊ ሠራዊት በጣዖት አምላኪነትና በተለያዩ ክፋቶች የተበከለ ነበር።

መጽሐፉ ሦስት ምዕራፎች ያሉት ሲሆን በአራት አርእስተ ጉዳዮች የተከፋፈለ ነው።

የመጀመሪያው በምዕራፍ አንድ ውስጥ ያለው ሲሆን እርሱም በኃጢአታቸው ምክንያት በሕዝቡ ላይ ስለሚመጣው የእግዚአብሔር ቍጣና ቅጣት ይዘረዝራል። እግዚአብሔር መሐሪና ይቅር ባይ ቢሆንም እርሱ ይቅርታ የሚያደርገው ግን ጥፋቱን አምኖና ተጸጽቶ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ለሚ ለምን ሰው ነው። ይህም በመሆኑ «ከእኔ የራቁትን፣ እኔን መከተል የተዉትንና ወደ እኔ መጥተው እኔ እንድመራቸው ያልጠየቁኝን አጠፋለሁ» ብሏል (ም:1 ቊ:6)። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከተገለጡት ቅጣቶች መካከል የሚከተለው ጥቅስ ይገኝበታል:-

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- ‹በዚያን ቀን ከኢየሩሳሌም ቅጽር በዓሣ በር በኩል ኡኡታ ይሰማል፤ ከአዲሱም አደባባይ የዋይታ ድምፅ ያስተጋባል፤ በኮረብታዎችም አካባቢ ሽብር ይሆናል። እናንተ ከከተማው በታችኛው ክፍል የምትኖሩ ሁሉ ይህን ድምፅ በምትሰሙበት ጊዜ ዋይ፥ ዋይ እያላችሁ አል ቅሱ፤ በዚያ የሚነግዱና ብር ለዋጮች ሁሉ ይሞታሉ» (ም:1 ቊ:10–11)።

ሁለተኛው ክፍል ም:2ቊ:1–3 ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የአይሁድ ሕዝብ እንዲጸጸቱና ንስሓ እንዲገቡ፥ አካሄዳቸውን እንዲያሳምሩ ጥሪ ቀርቦላቸዋል። ይህን ያደረጉ እንደሆነ ከሚመጣው ቍጣ የሚድኑ መሆናቸው ተገልጦላቸዋል።

ሦስተኛው ክፍል የምዕራፍ 2 ቀሪው ክፍል ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የአይሁድ ጐረቤቶች በሆኑት አገሮች ላይ የጥፋት ትንቢት ተነግሮባቸዋል። ይህም የሆነበት ምክንያት እነርሱ በአይሁድ ሕዝብ ላይ ስላደረሱት ችግር እግዚአብሔር የሚበቀላቸው ስለሆነ ነው። ስለዚህ ጉዳይ የተነገረውን ቀጥለን እንመልከት።

«ጋዛ ሰው የማይኖርበት ባድማ ትሆናለች፤ አስቀሎናም ምድረ በዳ ትሆናለች፥ የአሽዶድ ነዋሪዎች በቀትር ከመኖሪያቸው ይባረራሉ፤ የዔቅሮንም ሰዎች ከከተማይቱ ተጠራርገው ይወጣሉ። እናንተ በባሕር ዳር የምትኖሩ ፍልስጥኤማውያን ወዮላችሁ፤ የእግዚአብሔር ፍርድ በእናንተ ላይ ደርሶአል፤ ስለዚህ ከእናንተ አንድ እንኳ ሳያስቀር ያጠፋችኋል።.... ከምርኮ የቀሩት የይሁዳ ሰዎች ርስታችሁን ወስደው የመንጋዎቻቸው መሰማሪያ ያደርጉታል» (ም:2 ቊ:4–7)።

በተመሳሳይ ሁኔታ በአሦርና በነነዌ ላይ ትንቢት ተነግሮባቸዋል።

አራተኛው ክፍል ምዕራፍ 3 ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ አረማውያን በክርስትናው እምነት ውስጥ ተቀባይነት እንደሚያገኙ ትንቢት ተነግሮአል። ይህንንም የሚያመለክቱት ቀጥለው የቀረቡት ጥቅሶች ናቸው።

«በዚያን ጊዜ የሕዝቦችን አሳብ እለውጣለሁ፤ ይኸውም ወደ ሐሰተኞች አማልክት ሳይሆን ወደ እኔ በንጹሕ ኅሊና እንዲጸልዩ አደርጋለሁ፤ ሁሉም በአንድነት እኔን ያገለግላሉ» (ም:3 ቊ:9)።



«ከመካከላችሁ ራሳቸውን ዝቅ ያደረጉ ትሑታን ሕዝቦችን አስቀራለሁ፤ እነርሱም በእኔ የሚተማመኑና የእኔንም እርዳታ የሚሹ ይሆናሉ» (ም:3 ቊ:12)።

<u>ትንቢት ሐጌ</u>:- ቀደም ብለው የቀረቡት የትንቢት መጻሕፍት ጊዜዎች ከባቢሎን ምርኮ በፊት፥ ወይም በምርኮው ጊዜና የምርኮው የዓይን ምስክሮችና በምርኮው ዘመን የነበሩ ነቢያት የጻፉአቸው ናቸው። ከምርኮው መልስ በኋላ የትንቢት መጻሕፍታቸውን ያዘጋጁት ነቢያት ግን ሐጌ፥ ዘካርያስና ሚልክያስ ናቸው።

እነዚህ ከምርኮ መልስ በኋላ መጻሕፍታቸውን ያዘጋጁት ነቢያት ያተኰሩት በሁለት ዋና፡ ዋና ነገሮች ላይ ነው። የመጀመሪያ ትኵረታቸው የቤተ መቅደሱ አድሳትና በምርኮውና በስደቱ ምክንያት ተጓጉሎ የነበረውን የአምልኮ ሥርዓት መልሶ በሥራ ላይ የማዋሉ ጉዳይ ነበር። ሁለተኛው ትኵረታቸው ደግሞ ስለ ክርስቶስ መምጣትና እርሱም ለሰው ዘር ሁሉ በረከትንና መልካም ነገሮችን እንደሚዐድል የተነገረው ትንቢት ነው። ከእነዚህም ነቢያት የመጀመሪያውና ከክርስቶስ ልደት በፊት በ536 ዓመት ከዘሩባቤል ጋር ከምርኮ የተመለሰው ሐጌ ነው። ከምርኮ የመመለስ ዐዋጅም የታወጀው ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት ነው።

መጽሐፉም ሁለት ምዕራፎች ያሉት ሆኖ በሁለት ዋና፡ ዋና ጉዳዮች ላይ ያተኰረ ነው። የመጀመሪያው ትኵረት አይሁድ ቤተ መቅደሳቸውን እንዲሠሩ ፈቃድ በተሰጣቸው ጊዜ ሁለት ችግሮች የአጋጠሙአቸው መሆኑ ነው። አንዱ ችግር ሥራውን እንዳይሠሩ በአካባቢአቸው ያሉ የጐረቤት አገሮች ተቃውሞ ነው። ይህ ችግር ግን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ መፍትሔ አግኝቶ ተቃውሞው ተወግዶአል። ሁለተኛው ችግር ደግሞ በራሳቸው በአይሁድ ዘንድ የተከሠተው ችግር ነው። ይኸውም አይሁድ ፍርሃት ያደረባቸው ከመሆኑም በላይ ቤተ መቅደሱን ለመሥራት አሁን ጊዜው አይደለም በሚል አስተሳሰብ የራሳቸውን መኖሪያ ቤት በመሥራት ላይ አተኰሩ። በዚህም ምክንያት የሚከተለው ወቀሳ ቀርቦባቸዋል:-

«የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሐጌን:- ‹ይህ ሕዝብ ቤተ መቅደሱ እንደገና ታድሶ የሚሠራበት ጊዜ ገና አልደረሰም› ይላል፤ ... ሕዝቤ ሆይ የእኔ ቤት ፈርሶ ሳለ እናንተ ተሸላል መው በተሠሩ ቤቶቻችሁ ለመኖር ጊዜው ነውን?» (ም:1 ቊ:2–4)።

ሐጌና ዘካርያስ ሕዝቡ ቤተ መቅደሱን የመሥራትና የማደስ ዕቅዱን እንዲ ቀጥል ለማግባባት ብዙ ጥረት ካደረጉ በኋላ ጥረታቸው ተሳክቶላቸው ለማግ ባባት ችለዋል።

ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የቀድሞውን ቤተ መቅደስ ያዩ ሽማግሌዎች አሁን ከተሠራው ቤተ መቅደስ ጋር በትልቅነቱ በአሠራሩና በግርማው በማነጻጸር ታላቅ የሐዘንና የወዮታ ድምፅ ማሰማት ጀመሩ። ነቢዩ ሐጌ ይህን የሐዘን ዝንባሌ ባስተዋለ ጊዜ የእነርሱን የሐዘን ስሜት ለመለወጥ ማባበልና ማጽናናት ጀመረ። የማጽናናት ንግግሩም እንዲህ የሚል ነበር:- በእርግጥ የቀድሞው ቤተ መቅደስ በትልቅነቱ፣ በአሠራሩ፣ በወርቅና በብር በተንጸባረቀው ጌጡ፣ በግድግዳዎቹና በዐምዶቹ ማማር፣ በመሠዊያዎቹና በመጋረጃዎቹ አሠራር ከአሁኑ ቤተ መቅደስ ይበልጥ ነበር። የአሁኑ ቤተ መቅደስ ግን በመንፈሳዊ ጌጡ ከፊተኛው ይበልጣል።

እስቲ ነቢዩ ሐጌ በምን ዐይነት የእግዚአብሔርን ቃል እየጠቀሰ እንደተናገረ እንመልከት:-

«መንግሥታትን እገለብጣለሁ፤ ሀብታቸውንም ሁሉ ወደዚህ እንዲመጣ አደርጋለሁ፤ ስለዚህም ቤተ መቅደሱ በሀብት የተሞላ ይሆናል። በዓለም የሚገኝ ወርቅና ብር ሁሉ የእኔ ነው። አዲሱ ቤተ መቅደስ ከፊተኛው ይበልጥ የተዋበ ሆኖአል፤ እኔም በዚያ ለሕዝቤ ብልጽግናንና ሰላምን እሰጣለሁ፤ እኔ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይህን ተናግሬአለሁ» (ም:2 ቊ:7–9)።

የዚህ ጥቅስ መግለጫ የሚያመለክተው የክርስቶስ ሰው ሆኖ የመምጣት ትንቢት ነው። ይህም ትንቢት አሕዛብ ወደ ክርስትናው እምነት የሚገቡ መሆናቸውን ያመለክታል።

በትንቢቱ ዘሩባቤልን በዳዊት ቤት የዘር ሰንሰለት ውስጥ ተመለከተው። ያም ሰንሰለት ሳይቋረጥ ወደ ክርስቶስ የሚያደርሰው ነው። እንዲሁም አንድ ቀን ሕዝቦች ሁሉ ወደ እዚያ እንደ ውሃ የሚጐርፉበትን የመንግሥቱን ክብር ተመለከተ።

በሐጌ አማካይነት እግዚአብሔር ለሕዝቡና ለመሪዎቻቸው ጥሪ ያቀረበው የተጀመረውን ሥራ እንዲጨርሱ ነው።

<u>ትንቢተ ዘካርያስ</u>:- ይህ ዘካርያስ የበራክዩ ልጅ፣ የዒዶ የልጅ ልጅ ነው። እርሱም ከምርኮ መልስ በኋላ ስለቤተ መቅደሱ እድሳትና ከምርኮ የተመለሱትን አይሁድ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ በማስተማር ረገድ ከነቢዩ ሐጌ ጋር አብሮ የሠራ ነው። በነቢዩ ሐጌ ትንቢት

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር በሐጌ አማካይነት:- «የደረሰባችሁን ነገር ሁሉ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፤ እነሆ፥ ብዙ ዘርታችሁ ጥቂት ሰበሰባችሁ፤ ትበላላችሁ፥ ነገር ግን አትጠግቡም፤ ትጠጣላችሁ ነገር ግን አትረኩም፤ ደራርባችሁ ትለብሳላችሁ፤ ነገር ግን አይሞቃችሁም፤ ሠርታችሁ የምታገኙት ደመወዝ ስለማይበረክትላችሁ፥ በቀዳዳ ኪስ ውስጥ የማኖር ያኽል ይሆናል፤ ... እናንተ ብዙ መከር ለመሰብሰብ ዐቅዳችሁ ነበር፤ ነገር ግን ጥቂት ሆነ፤ ያንኑም ወደ ቤት ባስገባችሁ ጊዜ እኔ እፍ ስላልሁበት ጠፋ፤ ይህንንስ ያደረግሁት ለምን ይመስላችኋል? እኔ ይህን ያደረግሁት ከእናንተ እያንዳንዱ ቤቱን አስጊጦ እየሠራ የእኔ ቤተ መቅደስ ፍርስራሽ ሆኖ በመቅረቱ ነው» ብሎአቸዋል (ሐጌ:ም:1 ቊ:5–9)።

ዘካርያስ የሐጌን ትምህርታዊ ማስጠንቀቂያና የራሱንም አቀራረብ በጠባቡ ሳይሆን በሰፊው ቀጥሎ እነዚያ ሐጌ የዘረዘራቸው በሕዝቡ ላይ የደረሱ ችግሮች የሚወገዱበት የመፍትሔ ሐሳብ የሕዝቡ ወደ እግዘአብሔር መመለስ መሆኑን ገልጦአል።

ትንቢተ ዘካርያስ ዐሥራ አራት ምዕራፎች ያሉት ሲሆን በሦስተ ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ክፍል ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 6 ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የተለያዩ ራእዮችን ማየቱ ተገልጾአል። እነዚህም ራእዮች እግዚአ ብሔር በምርኮ ተመላሾቹ ምን ዐይነት ታዛዥነት የሚጠብቅባቸው መሆኑን የሚገልጡ ናቸው። እንዲሁም ስለ ቤተ መቅደሱ አሠራርና፥ ስለ ካህኑ ዘውድ መጫን፥ ስለ ክህነት ሥራዎች፥ ሕግጋቱን በሚያፈርሱ ላይ ስለሚደርስ እርግማን፥ ይህም በተለየ በሌብነትና በሐሰት በሚምሉ ላይ ስለሚሰጠው ቅጣት ተገልጦአል። ስለ ክርስቶስ መምጣትና ከአብ ጋር ስላለው እኩልነትና ስለ መለኮታዊ ክብሩ የተገለጠው እንዲህ ተብሎ ነው:-

«እናንተን የሚነካ ውድ የሆነውን የዐይኔን ብሌን እንደሚነካ ነው፤ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለበዘበዙት አሕዛብ ይህን ቃል እንድናገር ክብሩን በመግለጥ ልኮኛል፤ እግዚአብሔር ራሱ እናንተን ይዋጋል፤ አገልጋዮቻችሁ የነበሩ ሕዝቦች መልሰው እናንተን ምርኮኞች ያደርጋሉ፤ ይህም ሁሉ በሚሆንበት ጊዜ እኔን የላከኝ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንደሆነ ሰው ሁሉ ያውቃል። የጽዮን ልጅ ሆይ፥ እነሆ፥ መጥቼ በመካከልሽ እኖራለሁና ዘምሪ፤ ደስም ይበልሽ ይላል እግዚአብሔር» (ም:2 ቊ.8–10)።

ሁለተኛው ክፍል ምዕራፍ 7 እና 8 ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ በአይሁድ ላይ ስለደረሰው ጠንካራ ተግሣጽና ቊጣ ተገልጾአል። ለዚህም ምክንያቱ እነርሱ የሃይማኖትን መሠረት ሳይሆን አፍአዊውን ሥርዓት ብቻ አጥብቀው በመያዛቸው ነው። ለዚህም አባባል መነሻ የሆነው የቤቴል ሰዎች ወደ ቤተ መቅደስ የላኩት መልእክት ነው። መልእክቱም ላለፉት ብዙ ዓመታት ስለ ቤተ መቅደሱ መፍረስ ሐዘናትንን ለመግለጥ በአምስተኛው ወር እንጾም እንደ ነበረ አሁንም እንቀጥልን? የሚል ነበር። ለትሩፋት፥ ምሕረት ለማግኘትና የእግዚአብሔር ሕግጋትን ለመጠበቅ የሚጾሙ አጽዋማት የደስታና በዓላትን የማክበሪያ እንጂ የሐዘን ቀኖች ተብለው መጠራት የለባቸውም ተብሎ ተነግሮአቸዋል። ይህ አባባል የክርስትናንም ምእመናን የሚመለከት ነው (ም:8 ቊ:18–19)።

ሦስተኛው ክፍል ከምዕራፍ 9 እስከ ምዕራፍ 14 ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ስለ ክርስቶስ ትንቢትና ምሳሌዎች (ጥላዎች)፥ ስለ መለኮቱ፥ ወንጌል ስለሚሰበክበት ዘመን፥ ከዚያም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአህያ ውርንጫ ላይ ሆኖ ወደ ኢየሩሳሌም ስለመግባቱ (9፥9)፥ አይሁድ የክርስቶስን ሕይወት ለማጥፋት የከፈሉት የገንዘብ ተመን (1፥12)፥ የጌታችን ጐን መወጋትና አይሁድ ወደ ክርስቶስ ሲመለሱ አባቶቻቸው ያደረሱበትን ሕማም በማስታወስ የሚያዝኑ መሆናቸው (12፥10)፥ የወንጌል ትምህርት መስፋፋትና እምነቱን ለተቀበሉ ሰዎች የሚወርድላቸው በረከት (13፥ 1–6)፥ ጌታችን፥ ሕማም በደረሰበት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ጥለውት መሸሻቸው፥ (13፥7) የቤተ ክርስ ቲያን አባላት አይሁድና አረማውያን ምእመናን የሚገኙበት መሆኑ (ም:14) ይገኙበታል። እነዚህ ስለ ክርስቶስ የተነገሩት መግለጫዎችና ማብራሪያዎች በትንቢተ ኢሳይያስ ትንቢት ተብራርተው በመቅረባቸው ነቢዩ ኢሳይያስን ወንጌላዊው ነቢይ አሰኝቶታል።

ትንቢተ ሚልክያስ:- ይህ ነቢይ የነበረበት ዘመን በግልጥ ባይታወቅም አንዳንድ ሰዎች ግን አነጋገሩን በማገናዘብ በነህምያ ዘመን እንደነበረ ወይም በነህምያ እንደተተካ ይገምታሉ። ይህንንም የሚያሰኘው ሚልክያስ ሕዝቡን የወቀሰው ነህምያ ሕዝቡን ይወቅስበት በነበረው



ኃጢአት ስለሆነ ነው። ይህም ነህምያን ያሳዘነው የነበረው ኃጢአት ወንዶቹ የአይሁድ ሴቶችን እየተዉ የውጪ አገር ሴቶችን ማግባታቸው ነው (ም:2 ቊ:11–16)።

መጽሐፉ አራት ምዕራፎች ያሉት ሲሆን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል። የመጀመሪያው ክፍል ምዕራፍ አንድና ምዕራፍ ሁለት ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የአይሁድ ካህናትና ሕዝብ ሁሉ የተከለከለውን በማድረግ፥ ከሃይማኖት አገልግሎታቸው በስተኋላ ትርፍ ማጋበሳቸው፥ የክህነት ተግባራቸውን በማጓደል፥ የግገርና የሽያጭ ሥራ ማድረጋቸውን በመሳሰሉ የርኵሰት ተግባር ተወቅሰውበታል። ከነቢያት ከበድ ያሉ ወቀሳዎች ለመረዳት እንደሚቻለው በዘመኑ ጕድለት የነበረባቸው፥ ብልግናና አሳፋሪ ተግባር የሚታይባቸው፥ የማይረቡ ሥራዎችንና ስሕተትን የሚፈጽሙ ካህናት የነበሩ መሆናቸው ይታያል። ለምሳሌ ከነቢያት አንዱ ካህናትን እንደዚህ ብሎ ገሥጾአቸዋል:-

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- ‹እኔ ቅሬታዬን የምገልጠው በእናንተ በካህናት ላይ ስለሆነ ሕዝቡን የሚከስስ ወይም የሚገሥጽ አይኑር። ቀንና ሌሊት ትደናበራላችሁ፤ ነቢያቱም እንደ እናንተ የሚደናበሩ ሆነዋል፤ ስለዚህ እናታ ችሁን እስራኤልን አጠፋታለሁ። ሕዝቤ ዕውቀት ከማጣት የተነሣ ጠፍቶአል፤ እናንተም እኔን ስለረሳችሁኝ እኔም ካህናት ሆናችሁ እንድታገለግሉኝ አልፈልጋችሁም፤ ትእዛዛቴንም ስላቃላላችሁና ስለረሳችሁ ልጆቻችሁ በእኔ ዘንድ የተረሱ ይሆናሉ። እናንተ ካህናት ቊጥራችሁ በበዛ መጠን በደላችሁም በፊቴ እየበዛ ሄዶአል፤ ስለዚህ ክብራችሁን ገፍፌ አዋርዳችኋለሁ። የሕዝቤ ኃጢአት ለእናንተ መበልጸጊያ በመሆኑ ሕዝቡ ኃጢአትን አብዝተው እንዲሠሩ ትፈልጋላችሁ» (ሆሴ:ም:4 ቊ:4–8)።

እንዲሁም ሌላው ነቢይ እንዲህ ብሎአል:-

«እናንተ ኢየሩሳሌምን የምትገነቡት በደምና በዐመፅ ነው፤ የከተማይቱ ሹማምንት የሚፈርዱት በጉቦ ነው፤ ካህናቱ ያለ ዋጋ አያስተምሩም፤ ይህም ሁሉ ሆኖ ‹እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ስለሆነ ምንም ዐይነት ክፉ ነገር አይደርስብንም› በማለት በእግዚአብሔር ይመካሉ» (ሚክ:ም:3 ቊ:10–11)።

በዚሁም አነጋገር ሚልክያስ በዘመኑ ለነበሩት ካህናት እንዲህ ብሎአቸዋል:-

«የእግዚአብሔርን እውነተኛ ዕውቀት ማስተማር የካህናት ተግባር ነው፤ ካህናት የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር መልእክተኞች ስለሆኑ የእኔ ፈቃድ ምን እንደሆነ ለመማር ሕዝቡ ወደ ካህናት መሄድ አለባቸው። አሁን ግን እናንተ ከእውነተኛው መንገድ ፈቀቅ ብላችኋል፤ በትምህርታችሁም ብዙዎችን አሳስታችኋል፤ ከእናንተ ጋር የገባሁትንም ቃል ኪዳን አፍርሳችኋል። ለእኔ ፈቃድ ባለመታዘዛችሁና ስታስተምሩም ሰዎችን በእኩልነት ባለመመልከ ታችሁ ምክንያት እኔም ደግሞ በእስራኤል ሕዝብ ፊት የተናቃችሁና የተዋረዳችሁ እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ» (ም:2 ቊ:7–9)።

የትንቢተ ሚልክያስ ሁለተኛው ክፍል ምዕራፍ 3 እና 4 ሲሆን በዚህ ክፍል ውስጥ ስለ ዮሐንስ መጥምቁ መምጣት ትንቢት ተነግሮአል። በዚሁ ክፍል ውስጥ ስለ ዐሥራት ክፍያ ማስተጓጐል አይሁድ ተወቅሰውበታል። የክርስቶስ መምጫ ቀን መቅረቡንና ለዚያም ምልክቱ ኤልያስ ተብሎ የተሰመው ዮሐንስ መጥምቁ ሁናቴውን ለማመቻቸት እንደሚመጣ ተገልጦአል።

መጽሐፈ መቃብያን:- መቃብያን ጀግኖች ማለት ነው። የመቃብያንን ታሪክ የያዙና ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ትምህርት ያለባቸው ስምንት መጻሕፍተ መቃብያን መኖራቸው ታውቋል። በግእዝና በአማርኛ ተተርጒመው የሚገኙት ሦስቱ የመቃብያን መጻሕፍት ከስምንቱ መካከል የተወሰዱ ናቸው። እዚህ የቀረበው የመቃብያን ታሪክ ከስምንቱ መጻሕፍት መካከል ከአንደኛና ከሁለተኛ መጻሕፍተ መቃብያን የተወሰደ ነው። ከምርኮ የተመለሱት አይሁድ ለሁለት መቶ ዘመን ያኽል በፋርስ ነገሥታት አገዛዝ ሥር ሆነው በሰላም ኖረው ነበር። ይህ ሰላማቸው በታላቁ እስክንድር ጊዜ እንኳ አልተቃወሰም። ታላቁ እስክንድር በሕይወት ዘመኑ ሁሉ በእነርሱ ላይ የነበረው አስተሳሰብ መልካም ነበር። እርሱ በሞተ ጊዜ ግን የመቄዶንያ ንጉሠ ነገሥታዊ ግዛት ወደ ተለያዩ ክፍሎች ስለተከፋፈለ በአይሁድ ላይ ክፉ ቀን መጣባቸው። በዚያን ጊዜ የይሁዳ ግዛት በሶርያና በግብጽ ነገሥታት መካከል መፋለሚያ ሆና ብዙ ችግር ደረሰባት።

አይሁድ በጣም አሰቃቂ ሁናቴ የደረሰባቸው ትዕቢተኛና ጨካኝ በነበረው በሶርያው ንጉሥ በአንጥያኮስ ግዛት ሥር በወደቁ ጊዜ ነው። ይህ ንጉሥ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲቃጠሉ አዘዘ፤ ቤተ መቅደሱን አረከሰ፤ የአይሁድ የሃይማኖት ሕጎች እንዳይጠበቁ ከለከለ፤ እነዚያን ሕጎች

www.ethiopianorthodox.org

የሚጠብቅ ቢኖር በሞት እንዲቀጣ ወሰነ። እዚህ ላይ የሚያሳዝነው ጉዳይ ከአይሁድ ብዙዎች ቅጣቱን በመፍራት የንጉሡን ትእዛዝ ማክበራቸው ነው። ይሁን እንጂ ከእነርሱ አብዛኞዎቹ የእግዚብሔርን ትእዛዛት ከማፍረስ ይልቅ ሞትን መረጡ። ከእነርሱም መካከል አልዓዛር የተባለው የዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሽማግሌ ይገኝ በታል። አልዓዛር፥ በሙሴ ሕግ የተከለከለውን የዐሣማ ሥጋ አልበላም ባለ ጊዜ አፉን በግድ ከፍተው ሊያበሉት ፈልገው ነበር። እርሱ ግን የእግዚ አብሔርን ትእዛዝ በማፍረስ ነፍሴን ከማረክሳት ምንም ዐይነት ሥቃይ ቢደርስብኝ ይሻላል ብሎ በግድ ያጐረሱትን በመትፋት እምቢ አለ። እዚያ ቆመው ከነበሩት ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ ለሽማግሌው በመራራት ሌላ ያልተከለከለ ሥጋ በመብላት የዐሣማ ሥጋ የበላና የንጉሡን ትእዛዝ ያከበረ እንዲያስመስል መከረውት ነበር። እርሱ ግን አስመሳይነት ለእርሱ ዕድሜ የማይስማማ መሆኑን ገለጠላቸው። ንግግሩንም በመቀጠል ያልሆነ ምክር ለሰጡት ወዳጆቹ እኔ የንጉሡን ትእዛዝ ያከበርሁ ባስመስል ወጣቶች ሊኖራቸው በሚችለው ዝንባሌ ላይ ተጽዕኖ አሳድራለሁ፤ ይህም ማለት ሽማግሌው አልዓዛር ወደ አረመኔነት የዞረ ከሆነ እኛስ ለምን እንደ እርሱ አናደርግም የሚል ስሜት ያድርባቸዋል አላቸው። እንዲሁም ደግሞ አሁን ከጊዜያዊው ቅጣት ባመልጥ በሕይወትም ሆኜ ወይም ከሞት በኋላ ከእግዚአብሔር ቍጣ አመልጣለሁን? ሲል ጠየቀ። ይህን ከተናገረ በኋላ ይህ ቅዱስ ሽማግሌ ወደሚገደልበት ቦታ ተጐትቶ በመሄድ ክብር ያለው ሞትን ሞተ (2ኛ: መቃብያን: ም:6 ቍ:18–31)።

ሌላው ምሳሌ ደግሞ ከሰባት ልጆችዋ ጋር ሰማዕትነትን የተቀበለችው እናት ነች።

አንጥያኮስ፥ አንዲት ባልዋ የሞተባት መበለትና ሰባት ልጆችዋ ወደ እርሱ እንዲቀርቡና በሃይማኖት የተከለከለውን ሥጋ ተገድደው እንዲበሉ አዘዘ። ሁላቸውም በአንድ ዐይነት አባባል የሃይማኖት ሕጋቸው ስለማይፈቅድላቸው የማይታዘዙ መሆናቸውን ገለጡለት። በዚህ ጊዜ ሁሉም በአለንጋ እንዲገረፉ አዘዘ።

ታላቅ ወንድማቸው እኛ የአምላካችንን ሕግ ከመተላለፍ ይልቅ መሞት ይሻለናል ብሎ ለንጉሡ ነገረው። ንጉሡ በዚህ ንግግር በጣም ተቈጥቶ ምላሱ እንዲቈረጥ፥ የራሱ ቈዳ እንዲላጥ፥ እጆቹና እግሮቹ እንዲቈረጡ፥ በመጨረሻ እናቱና ወንድሞቹ እያዩ ከእነሕይወቱ በእሳት እንዲቃጠል አዘዘ። በዚህ ሥቃይ ላይ እያለ እናቱና ወንድሞቹ በድፍረት እንዲሞት አይዞህ እያሉ ያበረታቱት ነበር።

ታላቅ ወንድማቸው በዚህ ዐይነት ከሞተ በኋላ ሁለተኛውን የራሱን ቆዳ በመግፈፍ ሌሎቹን ሥቃዮች ከመቀጠላቸው በፊት ያን ሥጋ ይበላ እንደሆነ ጠየቁት። እርሱ ግን ከታላቅ ወንድሙ ባላነሰ ድፍረት እምቢ ስላላቸው እስኪሞት ድረስ በወንድሙ ዐይነት አሠቃዩት። እርሱም በሚሞትበት ጊዜ «አንተ በጣም ክፉ ሰው ሆይ፥ በዚህ በአሁኑ ሕይወት ብትገድለን የዘለዓለሙ ንጉሥ እኛን ስለ ሕጉ የሞትነውን በዘለዓለማዊ ሕይወት ትንሣኤ ጊዜ ያስነሣናል» አለው።

ሦስተኛው ወንድም እጆቹንና እግሮቹን እንዲቈረጡ በመስጠት :- «እነዚህን ያገኘኋቸው ከሰማይ ነው፤ ነገር ግን መልሼ ከእግዚአብሔር እንደምቀበላቸው ተስፋ ስለማደርግ ለእግዚአብ ሔር ሕግ ስል እንቃቸዋለሁ። ከመሞቱ ከጥቂት ጊዜ በፊት እንደ ወንድሞቹ ስለ እግዚአብሔር ሕግ ለመሞት ፈቃደኛ እንደሆነ ገለጠ።

አራተኛው፥ አምስተኛውና ስድስተኛው ወንድሞች ሁሉ በዚያው ታላላቅ ወንድሞቻቸው በተሠቃዩበት ሥቃይና ጠንካራ መንፈስ ሞቱ። ንጉሡና ባለሟሎቹ በወንድማማቾቹ ጠንካራ መንፈስ ተደነቁ።

በጣም ትንሽ ልጅ የነበረው ሰባተኛው ልጅ በተጠራ ጊዜ ንጉሡ:- «ትእዛዜን ብታከብር ባለጸጋና የተደሰትህ አደርግሃለሁ» አለው። የንጉሡ ንግግር በልጁ ላይ ምንም ለውጥ እንዳላመጣ ባየ ጊዜ እናቱን ጠርቶ «ልጅሽን ብትመክሪው ይሻላል» አላት።

እናትዮዋም በጉዳዩ ተስማማች። በእናትነት ፍቅር አነጋገር «ልጄ ሆይ፥ ሰማይንና ምድርን፥ በእነርሱም ውስጥ ያለውን ሁሉ ተመልከት፤ እግዚአብሔርም ከምንም እንዳስገኛቸው አስተ ውል፤ እንዲሁም የሰው ዘር ከምንም የተገኘ ነው። ስለዚህ ይህን ሥቃይ አትፍራ፤ ነገር ግን ሞትን በመቀበል ከወንድሞችህ ጋር ተባበር» አለችው። እርስዋም ይህን እየተናገረች ሳለች ልጁ እኔ በሙሴ አማካይነት የተሰጠንን ሕግ እንጂ የንጉሡን ትእዛዝ አላከብርም ካለ በኋላ ወደ ንጉሡ ዞር ብሎ አንተ በዕብራውያን ላይ ባደረስከው ችግር ምክንያት ከእግዚአብሔር እጅ አታመልጥም አለው። ንጉሡም በጣም በመቈጣት ከሌሎች ሁሉ ይበልጥ አሠቃይቶት ሞተ። በመጨረሻም እናትዮዋ ተገደለች (2ኛ:መቃ:ም:7)።



አንጥያኮስ አይሁድን እንደዚህ አድርጎ ያሠቃይ በነበረበት ጊዜ በይሁዳ ክፍለ ሀገር አምስት ልጆች ያሉት ማታትያስ የሚባል ካህን ነበር። ይህ ካህን፣ አንጥያኮስ ቤተ መቅደስን ማርከሱንና በጠቅላላ የእግዚአብሔርን አምልኮ መከልከሉን ሰምቶ በጣም አዘነ። አይሁድ ጠንካራ ተቃውሞ ካላደረጉ በቀር ይህ ኃጢአተኛ ንጉሥ ክፉ ዐላማውን በተግባር እንደሚያደውል ዐወቀ። ስለዚህ ለእግዚአብሔር ሕግጋት ቀናተኛ የሆነ ሰው ሁሉ ለተቀደሰ ሙብቱ ለመከላከል ከእርሱ ጋር እንዲነሣ ጠራ። ከዚያ በኋላ እርሱና ልጆቹ እንዲሁም የእስራኤል ጐበዞች ከእነርሱ ጋር ተባብረው ወደ ተራራው በመሸሽ አንድ ጠንካራ የጦር ኀይል አቋቋሙ። እነርሱም የጣዖት መሠዊያዎችን አፈረሱ፤ ለእግዚአብሔር ሕግ በጀግንነት ተከላከሉ፤ ሃይማኖታቸውን የካዱ አይሁድን አባረሩ።

ከማታትያስ ሞት በኋላ ልጁ መቃብዮስ የተባለው ይሁዳ የአይሁድ ጦር ሠራዊት አዛዥ ሆነ። በጦርነት ጊዜ እርሱ እንደ አንበሳ ደፋር ነበር። ከሶርያ ወታደሮች ጋር ብዙ ጦርነቶችን ተዋግቶአል፤ ኢየሩሳሌምንና ቤተ መቅደስን አስመልሶአል። ቤተ መቅደሱ በጣም ተጐሳቍሎ ስለነበረ በሐዘን ተመልክቶታል። መሠዊያው እንዲረክስ ተደርጎ ባድማ በሆነው የቤተ መቅደስ አደባባይ ሣር በቅሎበት አይቶአል። ከዚያ በኋላ ቤተ መቅደሱን አነጻ፤ ድሉን በትልቅ በዓል አከበረው፤ መሠዊያውን በአዲስ መልክ እንዲነጻ አደረገ፤ ይህንንም ያደረገው በበገና፥ በማሲንቆ፥ በጸናጽልና በመዝሙር ነው። አንጥያኮስ የይሁዳ መቃብዮስን ድል በሰማ ጊዜ እርሱ ራሱ በሚመራው ጦር ሠራዊት አማካይነት በኢየሩሳሌም ላይ ለመዝመት ተነሣ። ነገር ግን በጦር ሠረገላው ላይ በከፍተኛ ፍጥነት ይጋልብ በነበረበት ጊዜ በመሬት ላይ ወድቆ በጣም ቈሰለ። ወዲያውም ከዚያ ከኃጢአተኛ ንጉሥ ሰውነት ላይ ትል መውጣት ጀመረ። ሥጋው በአጥንቱ ላይ በሰበሰ። እርሱም ማንም ሰው ሊቀርበው የማይችል አስደንጋጭና የሚያስጠላ ሰው ሆነ። ከቅርብ ጊዜ በፊት የሰማይ ከዋክብት እንኳ ሊታዘዙለት እንደሚገባ ያስብ የነበረው ያ ሰው በገዛ አገልጋዮቹ ሳይቀር የተተወ ሆነ።

የትዕቢቱን ክፋትና ሞኝነት በመገንዘብ ራሱን በእግዚአብሔር ፊት ዝቅ አድርጎ የፈጸመውን በደል ሁሉ እንደሚያርምና የአይሁድ ሕዝብ ከሚያመልኩት ታላቅ አምላክ በቀር በምድር ሁሉ ላይ ሌላ አምላክ አለመኖሩን እንደሚያውጅ ቃል ገባ። የእርሱ ንስሓ ግን ሞትንና ጊዜያዊ ቅጣትን ከመፍራት የተነሣ ብቻ በመሆኑ በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ አላገኘም። ሥቃዩም ምንም ሳይሻለው ቀጥሎ በመጨረሻ ይህ ክፉ፥ እግዚአብሔርን ተሳዳቢና ሕዝቡን ጨቋኝ ንጉሥ በሥቃይ ሞተ።

ወራሹ የነበረው የአንጥያኮስ ልጅ በጣም የታወቁትን የጦር መሪዎች ከብዙ ሠራዊት ጋር ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን መልሶ ለመያዝ ላካቸው። ይሁዳ መቃብዮስና የእርሱ ጥቂት ሠራዊት በእነርሱ ላይ የተሰለፈውን ግዙፍ ሠራዊት በመመልከት የትሕትና ጸሎታቸውን ወደ እግዚአ ብሔር አቀረቡ። ከዚያም በእግዚአብሔር ተማምነው የጠላትን ሠራዊት ለመግጠም ወጡ።

በጦርነቱ መካከል በአየር ላይ አምስት ፈረሰኞች በአይሁድ ሠራዊት በኩል የሚያንጸባርቅ የጦር ለብስ ለብሰው የጠላት ሠራዊት አያቸው። ከአምስቱ ሁለቱ የሰማይ ተዋጊዎች፥ ሁለቱ ይሁዳ መቃብዮስ አደጋ እንዳይደርስበት ይጠብቁት የነበረ ሲሆን ሦስቱ ግን በሶርያ ሠራዊት ላይ ጦራቸውን እየወረወሩ ነበር። የጠላት ሠራዊት ይህን አስደናቂ ሁኔታ ባዩ ጊዜ በፍርሃት ተዋጡና ግራ በመጋባት ሸሹ። በሸሹበትም ጊዜ ሠላሳ ሺህ ወታደር ሞቶባቸው ነበር።

በዚህ ዐይነት በመለኮታዊ ኀይል እየተረዳ ይሁዳ መቃብዮስ በብዙ ጦርነቶች ሶርያውያንን ድል አድርጎአል። ነገር ግን ከእነዚህ ጦርነቶች በአንዱ ከአይሁድ ሠራዊት ጥቂቶች ተገደሉ። በሚቀጥለው ቀን ሟቾቹን ለመቅበር ይሁዳ መቃብዮስና ወታደሮቹ በመጡ ጊዜ በሟቾቹ ኪስ የጥንቈላ ዕቃ ተገኘ። ይህም ዕቃ በአይሁድ ዘንድ ለመንካት እንኳ የተከለከለ የአረማውያን የጥንቈላ ዕቃ ነበር። እነዚያ ሰዎች የተገደሉት በዚያ በጥንቈላው ኃጢአት ምክንያት መሆኑ በታወቀ ጊዜ እግዚአብሔር ለሟቾቹ ኃጢአት ይቅርታ ያደርግላቸው ዘንድ ጸሎት ተደረገ። ይሁዳ መቃብዮስ ግን ሁለት ሺህ ድራህማ ሰብስቦ ለሟቾቹ ወታደሮች ይጸለይላቸው ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም ላከ።

ይሁዳ መቃብዮስ ከተዋጋቸው ከብዙዎቹ ጦርነቶች ከአንዱ ጦርነት በፊት አንድ ራእይ አየ። በራእዩም ያየው ሟቹ ሊቀ ካህናት ኦንያስ እጁን ይዞ ለአይሁድ ሕዝብ ሲጸልይ ነው። ከዚያ በኋላ ሌላ ሰው በታላቅ ክብር ተገለጠ። ኦንያስም:- «ይህ ሰው ለሕዝቡና ለቅድስቲቱ ከተማ ብዙ ጊዜ የሚጸልየው የእግዚአብሔር ነቢይ ኤርምያስ ነው» አለ። ከዚያ በኋላ ኤርምያስ

www.ethiopianorthodox.org

«የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነውን ይህን ሰይፍ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የእስራኤልን ጠላቶች እንድታሸንፍበት ውሰድ» ብሎ ሰጠው። ይሁዳም በእነዚያ ከሰማይ በሆኑ እርዳታዎች ተበረታቶ ብዙ ጦርነቶችን ድል አደረገ። በመጨረሻም አንድ ጊዜ ከጠላት ጋር ባልተመጣጠነ የወታደር ብዛት ጦርነት በማድረግ ተሸንፎ እርሱ ተገደለ። ሕዝቡም ለብዙ ቀኖች አለቀሱለት። ከዚያ በኋላ በወንድሙ በዮናታን ከዚያም በተከታዩ ወንድሙ በስምዖን መሪነት ተጋድሎው ቀጥሎ በየጊዜው ብዙ ድሎችን ተቀዳጅተዋል።

## ሐዲስ ኪዳን

ራእየ ዮሐንስ:- ይህ የራእይ መጽሐፍ ሐዋርያው ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት በግዞት ተወስኖ በነበረ ጊዜ የተገለጠለትን እንዲጽፍ ከእግዚአብሔር ታዝዞ ያዘጋጀው ነው።

መጽሐፉ ኻያ ሁለት ምዕራፎች ያሉት ሲሆን በሰባት ራእዮች ይከፈላል።

የመጀመሪያው ራእይ ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 3 ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ያየው ራእይ በአጠቃላይ ስለ ምድራዊው ቤተ ክርስቲያን ነው። በምዕራፍ አንድ ውስጥ ስለ መጽሐፉ ጸሐፊ ማንነት፥ ዮሐንስ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያን መልእክት መላኩ ተገልጦአል። ዮሐንስም በራእዩ ውስጥ ድምፅ ከሰማ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አይቶታል። በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ዮሐንስ ያየውን ነገር እንዲጽፍ ታዞአል።

ሁለተኛው ምዕራፍ ለአራቱ አብያተ ክርስያን የተላከውን መልእክት የሚመለከት ነው። እነርሱም የኤፌሶን፥ የሰምርኔስ፥ የጴርጋሞንና የትያጥሮን አብያተ ክርስቲያን ናቸው። ለያንዳንዱም ቤተ ክርስቲያን እንደየሁኔታው ወቀሳ፥ ማስጠንቀቂያ ወይም ምስጋና ተሰጥቶታል። ከዚያም ግዴታን ያዘለ ተስፋ ተሰጥቶበታል።

ሦስተኛው ምዕራፍ ለሦስቱ አብያተ ክርስቲያን የተላከውን መልእክት የሚመለከት ነው፤ እነርሱም:- የሰርዴስ፥ የፊላዴልፍያና የሎዶቅያ አብያተ ክርስቲያን ናቸው።

ሁለተኛው ራእይ ከምዕራፍ 4 እስከ ምዕራፍ 7ድረስ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ያለው ራእይ በአጠቃላይ ስለ ሰባቱ ማኅተም ነው።

በምዕራፍ 4 ውስጥ የተገለጠው ስለ ሰማያዊ ትርኢት ነው። በዚህ ትርኢት:- ዙፋን፥ በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው፥ በዙፋኑ ዙሪያ ሌሎችም 24 ዙፋኖች፥ የመስታወት ባሕር፥ አራት እንስሶች፥ የእነርሱም ውዳሴና ምስጋና ተመልክቶአል።

በመዕራፍ 5 ውስጥ የተገለጠው ስለ በጉና ስለ ታሸገው መጽሐፍ ነው። ያን የታሸገ መጽሐፍ ማንም ሊከፍተው የማይችል መሆኑን አንድ መልአክ በገለጠ ጊዜ ዮሐንስ በጉዳዩ አለቀሰ። ከካህናቱ አንዱ ወደ ዮሐንስ መጥቶ አይዞህ አታልቅስ፤ ከይሁዳ ነገድ የሆነው የዳዊት ልጅ ያ አንበሳ አሸንፎአል፤ እርሱ መጽሐፉን ይከፍታል ማኅተሙንም ይፈታል አለው።

በምዕራፍ 6 ውስጥ የተገለጠው ስለ መጀመሪያዎቹ ስድስቱ ማኅተሞች ነው። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በሕጉ የመጀመሪያዎቹን ስድስት ማኅተሞች መከፈቱ ተገልጦአል። የመጀመሪያው ማኅተም ሲከፈት በነጭ ፈረስ ላይ የተቀ መጠ፥ ሁለተኛው ማኅተም ሲከፈት በቀይ ፈረስ ላይ የተቀመጠ፥ ሦስተኛው ማኅተም ሲከፈት በጥቍር ፈረስ ላይ የተቀመጠ፥ አራተኛው ማኅተም ሲከፈት በግራጫ ፈረስ ላይ የተቀመጠ ወጡ። አምስተኛው ማኅተም ሲከፈት ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ሰጡት ምስክርነት የተገደሉት ሰዎች ነፍሶች ከመሠዊ ያው በታች ታዩ። ስድስተኛው ማኅተም ሲከፈት በብዙዎች ዘንድ ብዙ ፍርሃ ትና መረበድበድ ሆነ።

በሰባተኛው ምዕራፍ የተነገረው ስለ ሰማያውያን ድል ነው። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከሕዝብና ከነገድ፥ ከወገንና ከቋንቋ የተውጣጡ ነጭ ልብስ የለብሱ ብዙ ሰዎችን ዮሐንስ ካየ በኋላ ከሽማግሌዎቹ አንዱ እነርሱ ታላቁን መከራ ዐልፈው የመጡ መሆናቸውን ነገረው። በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ በአምላክ አገልጋይነታቸው በግንባራቸው ላይ የታተመባቸው ከዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል አንደ መቶ አርባ አራት ሺህ መቈጠራቸውም ተሰምቶአል።

ሦስተኛው ራእይ:- ስለ ሰባቱ መለከቶች ነው። ይህም የሚገኘው ከምዕራፍ 8 እስከ ምዕራፍ 11 ድረስ ነው።

ስምንተኛው ምዕራፍ ስለ መጀመሪያዎቹ አራቱ መለከቶች የሚናገር ነው። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ሰባተኛው ማኅተም መከፈት ተነግሮአል። ሰባተኛው ማኅተም በተከፈተ ጊዜ ለግማሽ ሰዓት ያኽል ጸጥታ ሆኖአል፤ ይህም የሆነው ከፍተኞች ለሆኑ ድርጊቶች ዝግጅት ነበር።

የመጀመሪያው መለከት ሲነፋ ደም የተቀላቀለበት እሳትና በረዶ ወደ ምድር ተጣለ።



ሁለተኛው መለከት ሲነፋ የሚቃጠል ተራራ የሚመስል ነገር ወደ ባሕር ተጣለ።

ሦስተኛው መለከት ሲነፋ እንደ ችቦ የሚቃጠል ታላቅ ኮከብ ከሰማይ ወደቀ።

አራተኛው መለከት ሲነፋ የፀሐይ አንድ ሦስተኛ፥ የጨረቃ አንድ ሦስተኛ፥ የኮከቦች አንድ ሦስተኛ ተመታ።

በዘጠነኛው ምዕራፍ አምስተኛውና ስድስተኛው መለከት ተነፋ። አምስተኛው መለከት ሲነፋ ከሰማይ ወደ ምድር አንድ ኮከብ ወደቀ: ይህም የመጀመሪያው ወዮ ጊዜ ነው።

ስድስተኛው መለከት በተነፋ ጊዜ ለዚህ ሰዓትና ስለዚህ ቀን፥ ለዚህ ወርና ለዚህ ዓመት የተዘጋጁት አራቱ መላእክት የሰዎችን አንድ ሦስተኛ እንዲገድሉ ተፈቱ።

በዐሥረኛው ምዕራፍ የተነገረው ስለ ነጐድጓድና ስለ ትንሿ መጽሐፍ ነው። ደመና የለበሰ መልአክ ከሰማይ ወረደ። እርሱም የአንበሳ ድምፅ በመሰለ ታላቅ ድምፅ በጮኸ ጊዜ ሰባቱ ነጐድጓዶች በየድምፃቸው ተናገሩ።

በዐሥራ አንደኛው ምዕራፍ ስለ ሁለቱ ምስክሮችና ስለ ሰባተኛው መለከት ተነግሮአል። ሁለቱ ምስክሮች ለአንድ ሺህ ሁለት መቶ ስድሳ ቀኖች ትንቢት ተናገሩ። ምስክርነታቸውን ከጨረሱ በኋላ ከጥልቁ ጕድጓድ የሚወጣው አውሬ ከእነርሱ ጋር ተዋግቶ በማሸነፍ ገደላቸው። ከሦስት ቀን ተኩል በኋላ ግን ጠላቶቻቸው እያዩ ተነሥተው በደመና ወደ ሰማይ እንዲወጡ ተደረገ። በዚሁ ምዕራፍ ስለ ሰባተኛው መለከት መነፋት ተነግሮአል። መለከቱ በተነፋ ጊዜ የዓለም መንግሥት የጌታ የአምላካችንና የመሲሑ ሆናለች የሚሉ ታላላቅ ድምፆች ተሰሙ። በእግዚአብሔር ፊት በዙፋኖቻቸው ላይ የተቀመጡት ኻያ አራቱ ሽማግሌዎች በግንባራቸው ተደፍተው ለእግዚአብሔር ሰገዱ።

አራተኛው ራእይ:- ሴቲቱንና ዘንዶውን እንዲሁም ሁለቱን አውሬዎች የሚመለከት ነው። ይህም የሚገኘው ከምዕራፍ ዐሥራ ሁለት እስከ ምዕራፍ ዐሥራ አራት ድረስ ባለው ክፍል ነው።

በምዕራፍ 12 ውስጥ የተነገረው ስለ ሴቲቱና ስለ ዘንዶው ነው። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ፀሐይ የለበሰች፥ ጨረቃን ከእግርዋ በታች ያደረገች፥ ዐሥራ ሁለት ኮከቦችን እንደ አክሊል በራስዋ ላይ የደፋች አንዲት ሴት ታየች። እርስዋም ነፍሰ ጡር ስለነበረች ምጥ ይዞአት ተጨንቃ ትጮኽ ነበር። እርስዋም ሕዝቦችን ሁሉ በብረት በትር የሚገዛ ወንድ ልጅ ወለደች። እንዲሁም ሚካኤልና የእርሱ መላእክት ከዘንዶውና ከመላእክቱ ጋር ጦርነት ገጥመው ዘንዶውና መላእክቱ መሸነፋቸው ተገልጦአል። ዘንዶውና መላእክቱ ወደ ምድር ተጥለዋል።

ዘንዶውም ከሴቲቱ የተወለደውን ልጅ ሊበላ አሰፍስፎ ነበር። ብዙም አሳደዳት። እርስዋ ግን ወደ በረሓ ተወስዳ እንክብካቤ እየተደረገላት ለሦስት ዓመት ተኩል ተቀመጠች።

በምዕራፍ ዐሥራ ሦስት ስለ ሁለቱ አውሬዎች ተገልጦአል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ አንድ ከባሕር ውስጥ ስለወጣ አውሬ ሁናቴ ተገልጦአል። ከባሕር ውስጥ የወጣው አውሬ ዐሥር ቀንዶች፥ ሰባት ራሶች፥ በቀንዶቹ ላይ ዐሥር ዘውዶች፥ በራሶቹም ላይ የስድብ ስሞች ነበሩ። ዘንዶው የራሱን ኀይልና የራሱን ዙፋን፥ ትልቅም ሥልጣን ለአውሬው ሰጠው። ያም አውሬ ነብር ይመስል ነበር፤ እግሮቹ የድብ እግሮች፥ አፉ የአንበሳ አፍ ይመስል ነበር።

የበግ ቀንዶች የሚመስሉ ሁለት ቀንዶች የነበሩት፥ አነጋገሩም እንደ ዘንዶው የነበረ ሌላ አውሬ ከምድር ወጣ። ይህ ሁለተኛው አውሬ በሰዎች ፊት እሳት ከሰማይ እስከማውረድ ድረስ ባለው ሥልጣን ታላላቅ ተአመራትን ያደርግ ነበር።

ዐሥራ አራተኛው ምዕራፍ ስለ ድልና ስለ ሰማያዊ ዜማዎች የተነገረበት ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የበጉና የአባቱ ስሞች በግንባሮቻቸው ላይ የተጻፉባቸው አንድ መቶ አርባ አራት ሺህ ሰዎች መታየታቸው ተገልጾአል። እንዲሁም የበገና ደርዳሪዎችም ድምፅ ተሰምቶአል። በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ሦስት መላእክት ተከታትለው በሰማይ ላይ ሲበርሩ ታይተዋል። የመጀመሪያው መልአክ ሁሉን ለፈጠረ አምላክ ሰገዱ እያለ፥ ሁለተኛው መልአክ ታላቂቱ ባቢሎን መውደቅዋን እየተናገረ፥ ሦስተኛው መልአክ ደግሞ ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግዱ ሰዎች የሚደርስባቸውን የእግዚአብሔር ቅጣት እያወጀ ተከታትለው ይበርሩ ነበር። በዚሁም ምዕራፍ ውስጥ በነጭ ደመና ውስጥ የወርቅ አክሊል ያደረገና በእጁ ስለታም ማጭድ የያዘ የሰው ልጅን የሚመስል ተቀምጦ ታየ። ማጭዱን ወደ ምድር ሰደደው ምድርም ታጨደች።

አምስትኛው ራእይ:- ሰባቱ መቅሠፍቶች። ይህም የሚገኘው በምዕራፍ 15 እና 16 ላ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

በምዕራፍ 15 ውስጥ መላእክቱ መቅሠፍቶቹን ይዘው መዘጋጀታቸው፥ ሰባቱም መላእክት ሰባቱን መቅሠፍቶች ይዘው ከቤተ መቅደሱ መውጣታቸው ተመልክቶአል።

በምዕራፍ 16 ሰባቱ መላእክት ሰባቱን የእግዚአብሔር ቍጣ ጽዋዎች በምድር ላይ እንዲያፈሱ ታዝዘው፥ እነርሱም እያንዳንዳቸው የቍጣውን ጽዋ ባፈሰሱ ጊዜ በሰዎች ላይ የተለያዩ ቅጣቶች መድረሳቸው ተገልጦአል።

<u>ስድስተኛው ራእይ:- የባቢሎን አወዳደቅ</u>። ይህም የሚገኘው በምዕራፍ 17–19 ነው።

በምዕራፍ 17 ዘማዊቱ ባቢሎን ያለችበት ሁኔታ ማለት የእርስዋ ማንነት ተገልጦአል።

በምዕራፍ 18 ዘማዊቱ ባቢሎን ስለተፈረደባት ፍርድ የሚመለከት ነው። በዚሁ ምዕራፍ አንድ ከሰማይ የወረደ መልአክ ድምፁን ከፍ አድርጎ ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፥ ወደቀች፤ የአጋንንት መኖሪያ ሆነች፤ የርኩሳን መናፍስት ማደሪያ ሆነች፤ ይህም የሆነው የሚያስከረውን የዝሙትዋን ወይን ጠጅ ሕዝቦችን ሁሉ ስላጠጣችና የምድር ነገሥታት ከእርስዋ ጋር ስላመነዘሩ ነው።

በምዕራፍ 19 ስለ በጉ ሠርግ ግብዣ ተነግሮአል። የበጉ ሠርግ ስለደረሰና የእርሱም ሙሽራ ስለ ተዘጋጀች ደስ ይበለን፤ ደስታም እናድርግ፤ እናክብረውም የሚል ድምፅ ተሰማ። መልአኩም ዮሐንስን ወደ በጉ ሠርግ ግብዣ የተጠሩ ዕድለኞች ናቸው ብሎ እንዲጽፍ ነገረው።

በምዕራፍ 20 የተነገረው ስለ ሺህ ዓመቱ መንግሥትና ስለመጨረሻው ዘመን ነው።

የዚህ የሺህ ዓመት ራእይ ጉዳይ በብዙዎች ዘንድ አከራካሪ በመሆኑ ቀደም ተብሎ በ5ኛው መጽሐፍ የተተቸ ስለሆነ በአጭሩ ከማቅረብ ይልቅ የመጽሐፉ አባባል ሙሉ ለሙሉ ቀርቦአል።

ከዚህ በኋላ የጥልቁን ጕድጓድ መክፈቻና ትልቅ ሰንሰለት በእጁ የያዘ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፥ ዘንዶውንም ይዞ ሺህ ዓመት አሰረው፤ ይህም ዘንዶ ዲያብሎስ ወይም ሰይጣን የሚባለው የቀድሞው እባብ ነው፤ ሺሁ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ ሕዝቦችን እንዳያስት መልአኩ ዘንዶውን ወደ ጥልቁ ጕድጓድ ጣለው፥ ዘግቶም በማኅተም አሸገው፤ ከዚያ በኋላ ለጥቂት ጊዜ መፈታት ይገባዋል።

ከዚህ በኋላ ዙፋኖችን አየሁ፤ በዙፋኖቹም ላይ የመፍረድ ሥልጣን የተሰጣቸው ተቀምጠው አየሁ፤ ስለ ኢየሱስ ምስክርነትና ስለ እግዚአብሔር ቃል ራሶቻቸው የተቈረጡባቸውን ሰዎች ነፍሶች አየሁ፤ እነርሱ ለአውሬውና ለምስሉ ያልሰገዱ፤ ምልክቱንም በግምባራቸውም ሆነ በእጃቸው ላይ ያላደረጉ ናቸው፤ እነርሱ ከሞት ተነሥተው ከክርስቶስ ጋር ሺህ ዓመት ነገሡ። የቀሩት ሙታን ግን ሺሁ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ ከሞት አልተነሡም፤ ይህም የመጀመሪያው ትንሣኤ ነው፤ የመጀመሪያው ትንሣኤ ተካፋይ የሆኑ የተመሰገኑና ቅዱሳን ናቸው፤ ሁለተኛው ሞት በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም፤ እነርሱ የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ፤ ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ይነግሣሉ።

ሺሁ ዓመት ከተፈጸመ በኋላ ሰይጣን ከእስራቱ ይፈታል፤ በዓለም ሁሉ የሚገኙትን፥ ጎግና ማጎግ የሆኑትን ሕዝቦች ሊያስትና ለጦርነትም ሊያስከትት ይወጣል፤ ቍጥራቸው በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ ነው፤ እነርሱ ወደ ምድር ሁሉ ተሠራጭተው የቅዱሳንን ሰፈርና የተወደደችውን ከተማ ከበቡ፤ ነገር ግን እሳት ከሰማይ ወርዶ በማቃጠል ደመሰሳቸው። ያሳታቸው ዲያብሎስ፥ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት በዲን በሚቃጠል እሳት ባሕር ውስጥ ተጣሉ፥ ሌሊትና ቀን ለዘለዓለም ይሠቃያሉ።

ከዚህ በኋላ ታላቅ ነጭ ዙፋንና በዙፋኑም ላይ የተቀመጠውን አየሁ፤ ምድርና ሰማይ ከፊቱ ሸሹ፥ ስፍራም አልተገኘላቸውም፤ ታናናሾችንና ታላላቆችን ሙታን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ፤ መጻሕፍትም ተከፈቱ፤ የሕይወት መጽሐፍ የሆነ ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ፥ ሙታንም በመጻሕፍቱ ተጽፎ በተገኘው ሥራቸው መሠረት ፍርድ ተቀበሉ፤ ባሕርም በውስጡ ያሉትን ሙታን ሰጠ፤ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ውስጥ የነበሩትን ሙታን ሰጡ፤ እያንዳንዱም ሰው በሥራው መሠረት ፍርድ ተቀበለ። ሞትና ሲኦልም ወደ እሳት ባሕር ተጣሉ፤ ይህም የእሳት ባሕር ሁለተኛው ሞት ነው፤ ስሙ በሕይወት መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘ ሁሉ ወደ እሳት ባሕር ተጣለ።

<u>ሰባተኛው ራእይ:-</u> ሰማያዊትዋ ቤተ ክርስቲያን ነች። የሚገኘውም በምዕራፍ 21 እና በምዕራፍ 22 ውስጥ ነው።

በምዕራፍ 21 የቀረበው ስለ ሰማያዊትዋ ከተማ ሲሆን በቀጥታ ከመጽሐፉ የተቀዳውን ቀጥለን እንመልከት:-



ከዚህ በኋላ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር አየሁ፤ የመጀመሪያው ሰማይና የመጀመሪያይቱ ምድር ዐልፈው ነበር፤ ባሕርም ከእንግዲህ ወዲህ አልነበረም፤ ቅድስቲቱ ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፥ ለባልዋ እንዳጌጠች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ፤ እንዲህም የሚል ታላቅ ድምፅ ከዙፋኑ ሲወጣ ሰማሁ፥ «እነሆ የእግዚአብሔር ማደሪያ ከሰዎች ጋር ነው፤ ከእነርሱም ጋር ይኖራል፤ እነርሱም የእርሱ ሕዝብ ይሆናሉ። እግዚአብሔር ራሱ ከእነርሱ ጋር ይሆናል፤ አምላካቸውም ይሆናል፤ እንባን ሁሉ ከዐይናቸው ላይ ይጠርጋል፤ ሞት ወይም ሐዘን ወይም ለቅሶ ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይኖርም፤ ምክንያቱም የቀድሞዎቹ ነገሮች ሥርዓት ዐልፎአል።»

በዙፋኑ ላይ የተቀመጠውም «እነሆ እኔ ሁሉን ነገር አዲስ አደርጋለሁ» አለ፤ ቀጥሎም «ይህ ቃል የታመነና እውነት ስለሆነ ጻፍ» አለኝ:- ከዚህም በኋላ እንዲህ አለኝ:- «ተፈጸመ፤ አልፋና ዖሜጋ፥ የመጀመሪያውና የመጨረሻው እኔ ነኝ፤ ለተጠማ ከሕይወት ውሃ ምንጭ ያለ ምንም ዋጋ በነጻ እሰጠዋለሁ፤ ድል የነሣ ይህን ይወርሳል፤ እኔ አምላክ እሆነዋለሁ፤ እርሱም ልጄ ይሆናል። ነገር ግን ፈሪዎች፥ እምነተ ቢሶች፥ ርኩሶች፥ ነፍሰ ገዳዮች፥ አመንዝሮች፥ አስማተኞች፥ ጣዖት አምላኪዎች፥ ውሸታሞች ሁሉ ዕጣ ክፍላቸው በዲን በሚቃጠለው በእሳት ባሕር ውስጥ ይሆናል፤ ይህም ሁለተኛው ሞት ነው።»

የመጨረሻዎቹ ሰባት መቅሠፍቶች የሞሉባቸውን ሰባቱን ጽዋዎች ከያዙት ከሰባቱ መላእክት አንዱ መጥቶ «ና የበጉ ሚስት የሆነችውን ሙሽራይቱን አሳይሃለሁ» አለኝ። በመንፈስም ወደ አንድ ትልቅ ረጅም ተራራ ወሰደኝና ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ ስትወርድ አሳየኝ፤ በእግዚአብሔር ክብር ታበራ ነበር፤ የብርሃንዋም ድምቀት እጅግ እንደ ከበረ ድንጋይ፥ እንደ እያስጲድ ዕንቍና እንደ ብሩህ መስተዋት የጠራ ነበረ።

በምዕራፍ 22 ውስጥ ማጠቃለያ አቀራረብ ነው።

## <u>ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት</u>

ከነቢዩ ኤልሳዕ ታሪክ ብዙ ትምህርት የምንማር ቢሆንም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው:-

የእግዚአብሔር ምርጫ በምሁርነት፥ በኑሮ ደረጃ፥ በኅብረተሰቡ ዘንድ ባለው አመለካከት አለመሆኑንና እኛ አፍአዊውን ስንመለከት እግዚአብሔር ግን ውሳጣዊውን የሚመለከት መሆኑን የምንረዳው ለዚያ ለታላቅ ነቢይነት ደረጃ ኤልሳዕ የተመረጠው በእርሻ ሥራ ላይ በነበረበት ጊዜ በመሆኑ ነው።

ሌላው ከነቢዩ ኤልሳዕ ታሪክ የምንማረው ደግሞ በእግዚአብሔር ላይ ፍጹም እምነት ካለን ምን ያኽል ታምራትንና ድንቅ ነገሮችን ለማድረግ የምንችል መሆናችን ነው። በነቢዩ ኤልሳዕ ታሪክ ውስጥ እንደምናስተውለው ለቀረቡለት ችግሮች ሁሉ ተአምራታዊ መፍትሔ ሳይሰጥ አላለፈም። ስለዚህም ነው ጌታችን የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያኽል እምነት እንኳ ቢኖራችሁ ተራራን ለማንቀሳቀስ ትችላላችሁ ያለው (ማቴ:ም:17 ቍ:20)።

የሶርያ ንጉሥ በእስራኤል መንግሥት ላይ አደጋ ለመጣል አስቦ የሚያወጣቸውን ዕቅዶች ሁሉ ኤልሳዕ በእግዚአብሔር እርዳታ እያወቀ ያስጠነቅቅ የነበረ መሆኑ እግዚአብሔር ለታማኞች አገልጋዮቹ የተደበቀ ምሥጢርን እንኳ እንደሚገልጥላቸው ያመለክተናል።

ይህ የሶርያ ንጉሥ ኤልሳዕን ለመያዝ ብዙ ሠራዊት በላከ ጊዜ የኤልሳዕ አገልጋይ በድንጋጤ መሸበሩን በመገንዘቡ ከእነርሱ ጋር ከተሰለፈው ይልቅ ከእኛ ጋር የተሰለፈው ይበልጣል ብሎ አበረታታው። ይህም የሚያመለክተው የእግዚአአብሔር ታማኞች አገልጋዮች ከሆንን በችግር ጊዜ ሁሉ እኛ በዐይናችን ልናይ የማንችለው የእግዚአብሔር እርዳታ አይለየንም ማለት ነው። ኤልሳዕ ግን ለእግዚአብሔር በጣም ቅርብ ስለነበረ የእግዚአብሔርን እርዳታ በዐይኑ ያየው ነበር፤ እንዲያውም በጸሎቱ ለአገልጋዩ እንኳ እንዲገለጥለት አድርጓል።

ከመጽሐፈ መቃብያን ብዙ ትምህርቶችን ለመቅሰም የምንችል ቢሆንም ለጊዜው ግን ጥቂቶቹን ቀጥለን እናቀርባለን።

ሽማግሌው አልዓዛር አፉን በግድ ከፍተው የዐሣማ ሥጋ ባጐረሱት ጊዜ ተፋው እንጂ አልበላውም። እርሱ ችግር እንዳይደርስበት በሃይማኖት ያልተከለከለ ሥጋ በልቶ ዐሣማ የበላ እንዲያስመስል ለተሰጠው ምክር የሰጣቸው ምክንያታውያን መልሶች የሚከተሉት ናቸው:-

1. ይህ አስመሳይነት ለዕድሜው የማይስማማ በመሆኑ፥

www.ethiopianorthodox.org

2. እርሱ፥ በተሰጠው መክር መሠረት አስመስሎ ሌላ ሥጋ ቢበላ ወጣቱ ትውል ሽማግሌው
አልዓዛር ሃይማኖቱን ክዶ አረማዊ ሆነ ስለሚልና ሽማግሌው አልዓዛር እንዲህ ካደረገ እኛም
እንደ እርሱ ብናደርግ ምን ይከለክለናል ብለው ሊያስቡ ስለሚችሉ፥
3. እኔ አሁን ምድራዊ ፓርጋና የምት ቅጣትን ፈርቼ ሕጉን ባፈርስ ወይም ባስመስል በዚህ
ዓለም ወይም በወዲያኛው ዓለም ከሚመጣውስ የእግዚአብሔር ቅጣት ላመልጥ እችላለሁን?
ብሎ ጠየቀ።
አስመሳይነትን መጥላቱ ጌታችን በሰው ፊት ያፈረብኝ እኔም በሰማዩ አባቴ ፊት እፈርድበ
ታለሁ ያለውን አባባል ገና ከመነገሩ በፊት ያከበረ እንደመሆኑ ለሁላችንም ታላቅ ትምህርት
ነው።
በሁለተኛው መልሱ ደግሞ የራሱ ጊዜያዊ ደኅንነት ሳያጓጓው መሰናከል በመሆን ለሌሎች
ጥፋት ማሰቡ እኛም እንዲሁ እንድናደርግ የሚረዳን ጠቃሚ ትምህርት ነው።
በሦስተኛው መልሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ዓለሙን ሁሉ አትርፎ ነፍሱን ግን
ቢያጣ ምን ይጠቅመዋል? ብሎ የጠየቀውን ጥያቄ ያስታውሰናል። ስለዚህ ለዚህች ለአጭር
ዘመን ብለን የዘለዓለማዊውን ሕይወት ችላ ማለት ምንኛ ሞኝነት እንደሆነ ያሳስበናል።
ከሰባት ልጆችዋ ጋር ሰማዕትነትን የተቀበለችው እናት እርስዋም ሆነች ልጆችዋ ምንኛ
የመንፈስ ጥንካሬ እንደነበራቸው በጣም የሚያስደንቅ ተግባር በመሆኑ ትልቅ አርአያነት ያለው
ነው። እንደዚህ አድርጎ መንፈሰ ጠንካራ መሆን ደግሞ መታደል ነው።
ሌላው ለሃይማኖቱ ቀናኢና መንፈሰ ጠንካራ ሰው ካህኑ ማታትያስ ነው። ምንም እንኳ
በዚያን ጊዜ አይሁድ በቍጥር አነስተኞች ቢሆኑና ከጠላቶቻቸው ብዛትና ጥንካሬ ጋር የማይ
መጣጠኑ ቢሆኑ ለእግዚአብሔር ሕግና ለቤተ መቅደሱ ያለው ታማኝነትና ቀናተኛነት ከፍተኛ
በመሆኑ በሶርያ ሠራዊት ላይ ለማመፅ ወሰነ። ዐላማው ሃይማኖታዊና ቅን በመሆኑ ጥቂት ሰዎችን
በማስተባበር ብቻ አይሁዳዊ ሠራዊት ለመመሥረት ችሎአል። እርሱና ከእርሱም በኋላ ልጆቹ
ከግዙፉ አንጥያኮስ ሠራዊት ጋር ተዋግተው ኢየሩሳሌምንና ቤተ መቅደሱን ለማስመለስ
ችለዋል። ይህም የሚያመለክተው ማንኛውም የጦርነት ድል የሚገኘው በእግዚአብሔር ፈቃድ
እንጂ በሰው ብዛትና ብርታት አለመሆኑን ነው። መጽሐፉ እንደሚናገረው ይሁዳ መቃብዮስ
የጠላትን ሠራዊት ብዛት ከእርሱ አነስተኛ ቍጥር ሠራዊት ጋር ካስተያየ በኋላ ወደ ጦርነት
ከመውጣቱ በፊት ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። ከዚያ በኋላ አምስት ሰማያውያን ፈረሰኞች
ከዕብራውያን ጋር መሰለፋቸው ታየ። ምንም እንኳ የእርሱ ሠራዊት በቍጥር ከጠላት ሠራዊት
በጣም ያነሰ መሆኑን ቢገነዘብ እርሱ ግን በአምላኩ ተማምኖ ስለተሰለፈ በእግዚአብሔር እርዳታ
ድሉ የእርሱ ሆነ። ስለዚህም ነው በመጽሐፈ መዝሙር 33 ቍጥር 16 ላይ:- «ንጉሥ በሠራዊቱ
ብዛት አይድንም ኀያልም በኀይሉ ብዛት አያመልጥም» የተባለው። ስለዚህም ነው ግዙፉና
ትዕቢተኛው ጎልያድ በኲሳሳው በግ እረኛ በዳዊት የተገደለው (1ኛ:ሳሙ:ም:17 ቍ:45–46)።
ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ በራእይ መጽሐፉ ለሰባት አብያተ ክርስቲያን የላከው መልእክት
ሦስት የተለያዩ ትርጓሜዎች ተሰጥተውበታል:-
1. የመጀመሪያው የትርጓሜ አቅጣጫ እነዚያ ሰባት አብያተ ክርስቲያን በዚያን ጊዜ የነበሩና
መልእክቱም የተላከው በተለየ ማለት ለያንዳንዳቸው በግል ነው የሚል ነው።
2. ሁለተኛው የትርጓሜ አቅጣጫ ሰባት የሚለው ቍጥር ሙሉ ማለት እንደሆነ ተወስዶ
በጊዜና በቦታ አጠቃላይ የሆነች የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ለማለት ነው የሚል ነው።
3. ሦስተኛው የትርጓሜ አቅጣጫ ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የተለያዩ ሰባት
ዘመናትን የሚመለከት ነው።

በዚህም መሠረት:-
የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ዘመነ ሐዋርያት
የሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን ዘመነ ሰማዕታት
የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን የሲኖዶሶች ዘመን
የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን የታይታ ዘመን (መካከለኛው ዘመን)
የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን የአውሮፓ ተሐድሶ ዘመን
የፊላዴልፍያ ቤተ ክርስቲያን የመገናኛት ዘመን
የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን የመጨረሻው ወላዋይነት ዘመን



ስለዚህ ጉዳይ ዐሥራ አንደኛ መጽሐፍ ምዕራፍ አራትን ይመለከቷል።
ሁለተኛው ራእይ በቤተ ክርስቲያንና በክፉ ኀይላት መካከል የተካሄደውንና፡ በቤተ ክርስ
ቲያን ድል አድራጊነት የተፈጸመውን ትግል የሚመለከት ነው። እርሱም ከምዕራፍ 4 እስከ
ምዕራፍ 7 ድረስ ባለው ክፍል ውስጥ ይገኛል። በዚሁ ክፍል ውስጥ የሰው፡ የአንበሳ፡ የላምና
የንስር መልክ ያላቸው አራት እንስሳት ታይተዋል። እነዚህም አራቱ እንስሳት የእግዚአብሔርን
ፍጹምነትና ባሕርዩን ያመለክታሉ ተብሎአል። ይኸውም፡- አንበሳ የኀያልነቱ ምሳሌ፡ ላም
የአገልግሎት ምሳሌ፥ ሰው የጥበበኛነት ምሳሌ፤ ንስር የልዕልናው ምሳሌ ናቸው።
በሌላ በኩል ደገሞ እነዚህ አራቱ እንስሳት ለአራቱ ወንጌላውያን ማለት ማቴዎስ፡ ማርቆስ
ሉቃስና ዮሐንስ ምሳሌ ናቸው የሚሉት ወገኖች ይበዛሉ። እነዚህም እንስሳት ማናቸው ለየትኛው
ምሳሌ ናቸው በሚለው ሐሳብ ላይ ልዩነት ቢኖርም የቅዱስ አትቴቴዎስ አስተሳሰብና በብዙዎች
ዘንድ ተቀባይነት ያገኘው ሐሳብ በመጻሕፍቱ አጀማመር ላይ መሠረት ያደረገው ነው።
ማቴዎስ የዘር ሐረግን በመዘርዘር ስለሚጀምር የሰው መልክ ባለው እንስሳ ይመሰላል፤
ማርቆስ በበረሓ ድምፁን እንደ አንበሳ በሚያሰማው በዮሐንስ መጥምቁ ስለሚጀምር በአንበሳ
ተመስሎአል፤ ሉቃስ መጽሐፉን በመሥዋዕት ስለሚጀምር የላም መልክ ያለው እንስሳ ምሳሌ
ተሰጥቶታል፤ ዮሐንስ የሚጀምረው በቃል ስለሆነ የንስር መልክ ያለው እንስሳ ምሳሌ
ተሰጥቶታል።
በሦስተኛው ራእይ የሚታየው ስለ ሰባቱ መለከቶች ነው። ይህም እንደገና የሚያመለክተው
ቤተ ክርስቲያን ወደ ሰማይ በምታደርገው ጕዞ ዋ ከክፉ ኀይላት ጋር የምታደርገውን ፍልሚያ
ነው። እርሱም ከምዕራፍ 8 እስከ ም:12 ባለው ክፍል ይገኛል። ከቤተ ክርስቲያን ጋር ፍልሚያ
የሚያደርግ አንድ ኀይል ብቻ አይደለም። የአይሁድ ሃይማኖት፡ ጣዖት አምላኪዎች፡
ከሐዲዎች፥ የሃይማኖትና የፖሊቲካ ኅብረት፥ ቁሳዊ ምኞት፤ እንደ የኮሚኒስት አስተሳሰብ
ያሉ የሃይማኖት ጠላቶች የመሳሰሉት ሁሉ ከክርስትና ጋር ፍልሚያ አድርገዋል።
መለከቶቹ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለሰው ልጆች የተላኩ ማስጠንቀቂያዎች ናቸው። የሰው
ልጆች ንስሐ እንዲገቡ ማስጠንቀቂያዎች ናቸው ማለት ነው።
በአራተኛው ራእይ፥ የሚታየው ስለሴቱት፥ ስለ ዘንዶውና ስለሁለቱ አውሬዎች ነው።
ይህም የሚገኘው ከምዕራፍ 12 እስከ ምዕራፍ 14 ባለው ክፍል ነው። በዚህም ክፍል ውስጥ
የሚታው በቤተ ክርስቲያንና በክፉ ኀይል መካከል የሚካሄደው ትግል ነው። ድሉ መቼም
በአዳኙ ጠቦት፥ ማለት በድል አድራጊው አንበሳ መሆኑ የተረጋገጠ ነው። ትግሉ በደግና በክፉ
መካከል ነው፤ ፍልሚያው በክፉ መንፈስና በእግዚአብሔር መንፈስ መካከል ነው፤ ትግሉ
በክርስትናና ክርስትና ባልሆነ መካከል ሳይሆን በክርስትናና በክርስትና ጠላት መካከል ማለት
ክርስትናን ለማጥፋት በሚሞክር በክፉ ኀይል መካከል ነው።
አምስተኛው ራእይ ስለ ሰባቱ መቅሠፍቶች ሲሆን የሚገኘው በምዕራፍ ዐሥራ አምስትና
ዐሥራ ስድስት ነው። ይህም እንደገና የቤተ ክርስቲያንንና የክፋት ኀየልን ፍልሚያ
የሚያመለክት ነው። እነዚህም በየተራ በሰባት መላእክት የፈሰሱት የእግዚአብሔር ቍጣ ጽዋዎች
የመጨረሻ ፍርድን ያመለክታሉ። ከመላእክቱም ብዙዎቹ ዜማ ያዜሙ የነበረው በመጨረሻው
ላይ ድሉ የእነርሱ መሆኑን ያመለክታል።
ስድስተኛው ራእይ ስለባቢሎንና አወዳደቅዋ፥ የበጉ ሠርግ ግብዣ፥ ስለ ሺህ ዓመት ንግሥና
ስለ መጨረሻይቱ ዘመን የሚናገር ነው።
ባቢሎን የሚለው ቃል ክርስቶስንና ልጆቹን የተቃወሙት የክፋት ኀይሎች ለማለት ነው።
ባቢሎን በምሳሌነት የተወሰደችው በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ እንደተመለከተው
የእስራኤልን ሕዝብ በምርኮኛነት ወስዳ ለሰባ ዓመት ሙሉ በባርነት ደረጃ የገዛች ጨካኝ አገር
ሆና በመቈጠርዋ ነው።
በባቢሎን ላይ የተነገረባት ዝሙት፥ የወይን ጠጅ ስካር፥ ገንዘብ ወዳድነት ሕይወትን
የሚያጠፉ ሦስት ኃጢአቶች በመሆናቸው ነው።
የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሠርግ የተሰኘው እርሱ የቤተ ክርስቲያን ራስ መሆኑንና
ዘለዓለማዊ ድል አድራጊነቱን በተመለከተ ነው። ሙሽሪቱ ቤተ ክርስቲያን የሚያንጸባርቅና
ንጹሕ የሆነ ቀጭን ልብስ እንድትለብስ የተሰጣት የቅዱሳን ጽድቅ ሥራ እነርሱን ለክርስቶስ
ደም ብቁዎች ስላደረጋቸው ነው።

www.ethiopianorthodox.org

በምዕራፍ 20 የተመለከተው የሺህ ዓመት ንግሥ ጉዳይ በአምስተኛው መጽሐፍ ምዕራፍ 1 ውስጥ የተገለጠ ስለሆነ ያን ገለጻ እንደገና ማቅረብ አስፈላጊ ስላልሆነ ታልፎአል።

ሰባተኛው ራእይ በሰማይ ስላለችው ቤተ ክርስቲያን ነው። ምዕራፍ 21 እና ምዕራፍ 22 ስለዚሁ ጉዳይ የተብራሩበት ናቸው።

በዚህ ራእይ ወደ መጽሐፉ ፍጻሜ እንደርሳለን። ትግሉ፥ ማለት ፍልሚያው ተፈጸመ፤ ማኅተሞቹ በመግለጫዎቻችው፥ መለከቶቹ በማስጠንቀቂያዎቻቸው፥ መቅሠፍቶቹ በፍርዶቻቸው ተፈጸሙ። በሴቲቱና በዘንዶው፥ በአውሬው፥ በሐሰኛው ነቢይ መካከል የነበረው ፍልሚያ አለቀ። ቅዱሳንን ያሳደደች አመንዝራይቱ ባቢሎን ወደቀች ሰይጣን ወደ ዘለዓለማዊው ሥቃይ ከተጣለ በኋላ ሁሉም ፍጹም ዕረፍትን ዐረፉ። ነፍሶቻችን የሚያርፉባት ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም ምን ትመስላለች? ይህ የመጨረሻው ራእይ ነው፤ ቤተ ክርስቲያንም በሰማይ ላይ ዐረፈች።

## ጥያቄዎች

1. ኤልሳዕን በነቢይነት እንዲቀባው የታዘዘው ማነው?
2. ኤልሳዕ ለነቢይነት የተጠራው ከምን ሥራ ላይ ነው?
3. ኤልሳዕ በኤልያስ ካባ ምን አደረገ?
4. ኤልሳዕ ለመራራው ውሃ ምን መፍትሔ ሰጠ?
5. በሰደቡት ሕፃናት ላይ ኤልሳዕ ምን አደረገ?
6. የእስራኤል፥ የይሁዳና የኤዶም ነገሥታት ውሃ ባለቀባቸው ጊዜ ኤልሳዕ ምን አደረገላቸው?
7. ባልዋ የሞተባት የነቢያት ጉባኤ አባል ሚስት ነቢዩን ምን ጠይቃው ምን አደረገላት?
8. ለሹኔም ከተማ ሀብታም ሴት ኤልሳዕ ምን አደረገላት?
9. የቅል ሐረግ ስለገባበት ወጥ ኤልሳዕ ምን አደረገ?
10. በዓልሻሊስ ከሚባለው ቦታ አንድ ሰው በመከር ጊዜ በአመጣው ስጦታ ኤልሳዕ ምን አደረገ?
11. ነቢዩ ኤልሳዕ ለሶርያዊው ንዕማን ምን አደረገለት?
12. ኤልሳዕ፥ አገልጋዩን ምን ስላደረገ ነው በለምጽ የቀጣው?
13. ዛፍ ለመቍረጥ ሄደው በነበሩት የነቢያት ጉባኤ አባላት መካከል ምን ተአምር ተደረገ?
14. የሶርያ ንጉሥ ኤልሳዕን ለማስያዝ ወታደሮች በላከ ጊዜ ምን ተአምር ተደረገ?
15. የኤልሳዕ አገልጋይ ሲደነግጥ ኤልሳዕ ምን አለው? ምንስ አደረገለት?
16. የሶርያ ንጉሥ ቤንሀዳድ ሰማርያን በከበበ ጊዜ ምን ተደረገ?
17. ነቢዩ ናሆም የነበረበት ዘመን መቼ እንደሆነ ይገመታል?
18. የመጽሐፉ ዋና መልእክት ምንድነው?
19. ነቢዩ ናሆም ያወገዛቸው ሁለት ኃጢአቶች ምንና ምን ናቸው?
20. ትንቢቶቻቸውን እስራኤላውያን ባልሆኑ ሕዝቦች ላይ ያተኰሩ ሦስት ነቢያት ማን ማን ናቸው?
21. ዕንባቆም ስለ ምን ጉዳይ ጸልዮ እግዚአብሔር ምን መልስ ሰጠው?
22. ነቢዩ ሰፎንያስ በማን ዘመን ነበር?
23. ከአይሁድ ምርኮ መልስ በኋላ የትንቢት መጻሕፍታቸውን ያዘጋጁ ነቢያት እነማን ናቸው?
24. እነዚህስ ነቢያት ትኩረት የሰጡባቸው ጉዳዮች ምንና ምን ናቸው?
25. የቀድሞውን ቤተ መቅደስ በኋላ ከተሠራው ጋር በማነጻጸር ሐዘን የተሰማቸውን ሰዎች ሐጌ ምን ብሎ አጽናናቸው?
26. ነቢዩ ሚልክያስ በነህምያ ዘመን እንደነበረ የተገመተው በምን ምክንያት ነው?
27. ከምርኮ የተመለሱት አይሁድ የሰላም ኑሮአቸው የተቃወሰው መቼ ነው?



28. አንጥያኮስ የተባለው ንጉሥ አይሁድን ሰላም የነሣቸው በምን ዐይነት ነው?
29. አልዓዛር የተባለው ሽማግሌ ምን ዐይነት ችግር ደርሶበት ሞተ?
30. ይህ ሽማግሌ ላለማስመሰል ምን መልስ ሰጠ?
31. አንድ እናትና ሰባት ልጆችዋ ሰማዕትነትን የተቀበሉት በምን ዐይነት ነው?
32. በአንጥያኮስ ላይ የመጀመሪያውን ዐመፅ ያስነሣ ሰው ማን ይባላል?
33. ከእርሱስ በኋላ በተከታታይ የዐመፁ መሪዎች የነበሩት ማን፥ ማን ይባሉ ነበር?
34. ለዚህ ዐመፃቸው እርዳታ የሚያገኙት ከማን ነበረ?
35. የአንጥያኮስ አሟሟት እንዴት ነበር?
36. ይሁዳ መቃብዮስ ምን ራእይ አየ?
37. የራእይ ዮሐንስ መጽሐፍ በስንት ራእዮች ተከፋፍሎ ቀረበ?
38. ዮሐንስ በራእዩ መልእክት የላከላቸው አብያተ ክርስቲያን ማን ማን ይባላሉ?
39. እያንዳንዳቸውስ የተመሰሉባቸው ዘመኖች የትኞቹ ናቸው?
40. ባቢሎን የተባለው ምን ለማለት ነው?
41. ሙሽራና ሙሽሪት ማንና ማን ናቸው?

# ምዕራፍ 3

# ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ

## የጌታችን ትምህርቶችና ታሪክ

### የጌታችን ቀብር:-

የአይሁድን ባለሥጣኖች በመፍራት በስውር የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር የነበረው የአርማትያሱ ዮሴፍ የጌታችንን አስከሬን ለመውሰድ ጲላጦስን ለመነ። ጲላጦስም ፈቀደለት። ስለዚህ ዮሴፍ ሄዶ አስከሬኑን ወሰደ። ከዚህ በፊት በሌሊት ወደጌታችን ሄዶ የነበረው ኒቆዲሞስ ኻያ አምስት ኪሎ ግራም የሚያኽል ከርቤና የሬት ቅልቅል ይዞ መጣ። ሁለቱ ሰዎች የጌታችንን አስከሬን ወስደው እንደ አይሁድ አገናነዝ ልማድ ከሽቶ ጋር በቀጭን ልብስ ከፈኑት። ጌታችን ተሰቅሎ በነበረበት ቦታ አንድ የአትክልት ስፍራ ነበር፤ በዚያም አትክልት ስፍራ ውስጥ ማንም ያልተቀበረበት አዲስ መቃብር ነበር። የአይሁድ ሰንበት ዝግጅት ቀን ስለ ነበረና መቃብሩም ቅርብ ስለነበረ፥ የጌታችንን አስከሬን እዚያ ቀበሩት።» (ዮሐ:ም19 ቍ:38–42)።

## የጌታችን ከሞት መነሣት

### እንደ ወንጌላዊው ማቴዎስ አቀራረብ

«ሰንበት ካለፈ በኋላ እሑድ ጧት በማለዳ መግደላዊት ማርያምና ሌላይቱ ማርያም መቃብሩን ለማየት ሄዱ። እነሆ በድንገት ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፥ የእግዚአብሔር መልአክ ከሰማይ ወርዶ መቃብሩ የተዘጋበትን ድንጋይ አንከባለለና በላዩ ተቀመጠ። የመልአኩ ፊት እንደ መብረቅ ያበራ ነበር፤ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ። ጠባቂዎቹ መልአኩን ከመፍራት የተነሣ በመንቀጥቀጥ እንደ በድን ሆኑ መልአኩ ግን ሴቶቹን እንዲህ አላቸው፤ «እናንተስ አትፍሩ፤ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንደምትፈልጉ ዐውቃለሁ፤ እርሱ «ከሞት እነሣለሁ› ብሎ እንደተናገረው ተነሥቶአልና እዚህ የለም፥ ተኝቶበት የነበረውን ስፍራ ኑና እዩ። እንግዲህ በፍጥነት ሄዳችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ‹ከሞት ተነሥቶአል፥ እነሆ ወደ ገሊላ ቀድሞአችሁ ይሄዳል፤ በዚያ ታገኙታላችሁ› ብላችሁ ንገሩአቸው፤ እነሆ ነግሬአችኋለሁ» አላቸው (ማቴ: ም:28 ቍ:1–7)።

### እንደ ወንጌላዊው ማርቆስ አቀራረብ

የሰንበት ቀን ካለፈ በኋላ መግደላዊት ማርያም፥ የያዕቆብ እናት ማርያም ሰሎሜም ሆነው፥ የኢየሱስን አስከሬን ለመቀባት ከመልካም ቅመም የተዘጋጀ ሽቶ ገዙ። እሑድ ጧት በማለዳ፥ ልክ ፀሐይ ስትወጣ፥ ወደ መቃብሩ ሄዱ። እነርሱ «ድንጋዩን ከመቃብሩ ደጃፍ ማን አንከባሎ

www.ethiopianorthodox.org

ይከፍትልናል» በማለት እየተነጋገሩ ይሄዱ ነበር። ይህንንም ያሉት መቃብሩ የተዘጋበት ድንጋ እጅግ ትልቅ ስለነበረ ነው። ቀና ብለውም በተመለከቱ ጊዜ ድንጋዩ ወደ ጐን ተንከባሎ አዩት። ወደ መቃብሩም በገቡ ጊዜ ነጭ ልብስ የለበሰ ጐልማሳ በስተቀኝ በኩል ተቀምጦ በማየታቸው ደነገጡ።

እርሱ ግን እንዲህ አላቸው:- «አይዞአችሁ፤ አትደንግጡ፤ እናንተ የምትፈልጉት ተሰቅሎ የነበረውን የናዝሬቱን ኢየሱስ እንደሆነ ዐውቃለሁ፤ እርሱ ተነሥቶአል፤ እዚህ የለም፤ የተቀበረበትም ቦታ ይኸውላችሁ፤ ተመ ልከቱ። አሁንም ሂዱ፤ ለደቀ መዛሙርቱና ለጴጥሮስ ‹ከዚህ በፊት ኢየሱስ እንደነገራችሁ እርሱ ወደ ገሊላ ቀድሞአችሁ ይሄዳል፤ በዚያም ታዩታ ላችሁ› ብላችሁ ንገሩአቸው።»

ሴቶቹም በፍርሃት እየተንቀጠቀጡ ከመቃብሩ ቦታ ወጥተው ሸሹ፤ እጅግ ፈርተው ስለነበር ምንም ነገር ለማንም አልተናገሩም (ማር:16÷1–8)።

## እንደ ወንጌላዊው ሉቃስ አቀራረብ

«ሴቶቹ ያዘጋጁትን ሽቶ ይዘው እሑድ ጧት በማለዳ ወደ መቃብሩ ሄዱ፤ መቃብሩ የተዘጋበትን ድንጋይ ከመቃብሩ ወዲያ ተንከባሎ አገኙት። ወደ ውስጥ በገቡ ጊዜ ግን የጌታችን ኢየሱስን አስከሬን አላገኙም። ስለዚህም ነገር በመገረም ላይ ሳሉ እነሆ የሚያንጸባርቅ ብሩህ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በድንገት መጥተው በአጠገባቸው ቆሙ። ሴቶቹም እጅግ ፈርተው ወደ መሬት አቀርቅረው ሳሉ ሰዎቹ እንዲህ አሉአቸው፤ ሕያው የሆነውን ኢየሱስን በሙታን መካከል ስለምን ትፈልጉታላችሁ? እርሱ እዚህ የለም፥ ተነሥቶአል፤ በገሊላ በነበረበት ጊዜ የነገራችሁን አስታውሱ፤ ‹የሰው ልጅ ለኃጢአተኞች ተላልፎ መሰጠት፥ መሰቀልና በሦስተኛ ውም ቀን ከሞት መነሣት ይገባዋል› ብሎአችሁ ነበር።»

ሴቶቹም የኢየሱስን ቃል አስታወሱ፤ ከመቃብርም ተመልሰው ይህን ሁሉ ለዐሥራ አንዱና ለቀሩትም ነገሩአቸው፤ ይህን ለሐዋርያት የተናገሩት መግደላዊት ማርያም፥ ዮሐናና የያዕቆብ እናት ማርያም እንዲሁም ሌሎች ሴቶች ነበሩ። እነርሱ ግን ይህ ነገር ቅዠት ስለመሰላቸው አላመኑአቸውም። ነገር ግን ጴጥሮስ ተነሥቶ ወደ መቃብሩ ሮጠ፤ እዚያም ሲደርስ ጐንበስ ብሎ በተመለከተ ጊዜ አስከሬኑ የተከፈነበትን ቀጭን ሐር ልብስ ብቻ አየ፤ በሆነውም ነገር እየተደነቀ ወደ ቤት ተመለሰ» (ሉቃ:ም:24 ቍ:1–12)።

## እንደ ወንጌላዊው ዮሐንስ አቀራረብ

«እሑድ ቿት በማለዳ ገና ጎሕ ሳይቀድ፥ መግደላዊት ማርያም ወደ ኢየሱስ መቃብር ሄደች። እዚያም እንደደረሰች መቃብሩ ተዘግቶበት የነበረው ድንጋይ ከመቃብሩ በር ላይ ተነሥቶ አየች። ስለዚህ እርስዋ ወደ ስምዖን ጴጥሮስና ኢየሱስ ወደሚወደው ወደ ሌላው ደቀ መዝሙር እየሮጠች ሄደችና ጌታን ከመቃብሩ አውጥተው ወስደውታል፤ የት እንዳኖሩት አላውቅም አለቻቸው።

በዚህ ጊዜ ጴጥሮስና ሌላው ደቀ መዝሙር ወጡና ወደ መቃብሩ ሄዱ: ሁለቱም አብረው ይሮጡ ነበር፤ ነገር ግን ሌላው ደቀ መዝሙር ከጴጥሮስ ይበልጥ ፈጥኖ ሮጠና ቀድሞ ወደ መቃብሩ ደረሰ። ጐንበስ ብሎም ወደ መቃብሩ ቢመለከት የከፈኑ ጨርቅ እዚያ ተቀምጦ አየ፤ ነገር ግን ወደ ውስጥ አልገባም። ስምዖን ጴጥሮስም ተከትሎት መጣና ወደ መቃብሩ ውስጥ ገባ፥ እርሱም የከፈኑን ጨርቅ እዚያ ተቀምጦ አየ፤ የጌታችን ራስ ተጠምጥሞ የነበረበት ጨርቅ ከከፈኑ ጨርቅ ጋር ሳይሆን ለብቻው በሌላ ስፍራ ተጠቅልሎ እንደተቀመጠ አየ። ቀጥሎም ያ ቀድሞ የደረሰው ደቀ መዝሙር ወደ መቃብሩ ውስጥ ገብቶ አየና አመነ። እነርሱ:- ከሞት መነሣት ይገባዋል የሚለውን የመጽሐፍ ቃል ገና አልተገነዘቡም ነበር። ከዚህ በኋላ ሁለቱም ደቀ መዛሙርት ተመልሰው ወደ ቤታቸው ሄዱ» (ዮሐ:ም:20 ቍ:1–10)።

## ጌታችን ለሁለት ደቀመዛሙርት መታየቱ:-

«በዚያኑ ቀን ከጌታችን ደቀ መዛሙርት ሁለቱ ወደ ኤማሁስ ይጓዙ ነበር፤ ኤማሁስ ከኢየሩሳሌም ዐሥራ አንድ ኪሎ ሜትር ያኽል ርቃ የምትገኝ መንደር ናት። እነርሱም ይህን የሆነውን ነገር ሁሉ አንሥተው እርስ በእርሳቸው ይወያዩ ነበር። ይህንንም በሚያወሩበትና በሚወያዩበት ጊዜ ጌታችን ራሱ ወደ እነርሱ ቀርቦ አብሮአቸው ይጓዝ ጀመር። ነገር ግን በዐይና ቸው እያዩት ማን እንደሆነ ማወቅ አልቻሉም። እርሱም «በጉዞ ላይ ሳላችሁ የምትነጋገሩበት ይህ ነገር ምንድነው?» አላቸው።



እነርሱም እያዘኑ ቀጥ ብለው ቆሙ። ከእነርሱም አንዱ ቀለዮጳ የሚባለው «በኢየሩሳሌም ከተማ ሆነህ በእነዚህ ቀኖች በዚያ የተፈጸመውን ነገር ሁሉ የማታውቅ አንተ ብቻ ነህን?» አለ።

ጌታችንም ምንድነው እርሱ? አላቸው። እነርሱም እንዲህ ሲሉ መለሱለት፥ በናዝሬቱ ኢየሱስ ላይ ስለተፈጸመው ነገር ነዋ፤ እርሱ በእግዚአብሔርና በሰዎች ሁሉ ፊት በቃልና በሥራ ብርቱ የሆነ ነቢይ ነበር። የካህናት አለቆችና መሪዎቻችን ለሞት ፍርድ አሳልፈው ከሰጡት በኋላ ሰቀሉት። እኛ ግን ‹እስራኤልን የሚያድን እርሱ ነው› ብለን ተስፋ አድርገን ነበር። ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ ነገር ከተፈጸመ እነሆ ዛሬ ሦስተኛ ቀኑ ነው። እንዲያውም በእኛ መካከል ያሉ አንዳንድ ሴቶች አስገርመውናል፤ እነርሱ ዛሬ በማለዳ ወደ መቃብሩ ሄደው ነበር፤ ነገር ግን የእርሱን አስከሬን አላገኙም፤ ‹ሕያው ሆኖአል› የሚሉ የመላእክትን መልክ አየን እያሉም ተመልሰው መጡ። ከእኛም አንዳንዶቹ ወደ መቃብሩ ሄደው ልክ ሴቶቹ እንዳሉት ሆኖ አገኙ፤ ኢየሱስን ግን አላዩትም።

ጌታችንም እንዲህ አላቸው:- እናንተ የማታስተውሉና ነቢያት የተናገሩትንም ሁሉ ከማመን የዘገያችሁ፥ መሲሕ ይህንን ሁሉ መከራ መቀበልና ወደ ክብሩ መግባት ይገባው የለምን? ከዚህ በኋላ ከሙሴና ከነቢያት መጻሕፍት ጀምሮ በቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ስለ እርሱ የተነገረውን እየጠቀሰ አስረዳቸው።

እነርሱ ወደሚሄዱበት መንደር በቀረቡ ጊዜ ኢየሱስ ዐልፎ የሚሄድ መሰለ። እነርሱ ግን ቀኑ መሽቶአል፥ ፀሐይም መጥለቅዋ ነው፥ ስለዚህ ከእኛ ጋር እዚህ ዕደር ብለው አጥብቀው ለመኑት። በዚህ ምክንያት ከእነርሱ ጋር ሊያድር ወደ ቤት ገባ። ከእነርሱም ጋር በማእድ ተቀመጠ። እንጀራ አንሥቶ የምስጋና ጸሎት ካደረገ በኋላ ቈርሶ ሰጣቸው። በዚያን ጊዜ ዐይናቸው ተከፈተና ኢየሱስ መሆኑን ዐወቁ፥ እርሱ ገን ወዲያው ከዐይናቸው ተሰወረ። እነርሱም እርስ በርሳቸው «በመንገድ ሳለን ሲነግረንና ቅዱሳት መጻሕፍትንም እየጠቀሰ ሲያስረዳን ልባችን እንደ እሳት ይቃጠል አልነበረምን?» ተባባሉ።

እነርሱም በዚያችው ሰዓት ተነሡና ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው ሄዱ፥ በዚያም ዐሥራ አንዱን ከጓደኞቻቸው ጋር በአንድነት ተሰብስበው አገኙአቸው። በዚያን ጊዜ ዐሥራ አንዱ «ጌታ ኢየሱስ በእርግጥ ተነሥቶአል፤ ለስምዖንም ታይቶአል» ይሉ ነበር።

ሁለቱም ደቀ መዛሙርት በበኩላቸው በመንገድ ላይ የሆነውን ነገርና ጌታችን ኢየሱስ እንጀ ራውን በቈረሰ ጊዜ እንዴት እንዳወቁትም ተረኩላቸው» (ሉቃ:ም:24 ቍ:13–35)።

## ለደቀ መዛሙርቱ መገለጡ:-

### እንደ ወንጌላዊው ዮሐንስ አቀራረብ

በዚያኑ ቀን እሑድ ማታ ደቀ መዛሙርቱ የአይሁድ ባለሥልጣኖችን በመፍራት በራፎቹን ዘግተው በቤት ውስጥ ተሰብስበው ነበር፤ በሮቹ ተዘግተው ሳለ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ተሰበሰቡበት ቤት ገባ፤ በመካከላቸውም ቆሞ «ሰላም ለእናንተ ይሁን» አላቸው። ይህንንም ብሎ እጆቹንና ጐኑን አሳያቸው፤ ደቀ መዛሙርቱም ጌታችንን ባዩ ጊዜ ደስ አላቸው። ከዚህ በኋላ ኢየሱስ እንደገና ‹ሰላም ለእናንተ ይሁን፤ አብ እኔን እንደላከኝ እኔም እናንተን እልካ ችኋለሁ» አላቸው። ይህን ብሎ እፍ አለባቸውና «መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፤ እናንተ የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ብትሉ ይቅር ይባልላቸዋል፤ እናንተ የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ባትሉ ግን ይቅር አይባልላቸውም» አላቸው (ዮሐ:ም:20 ቍ:19–23)።

### እንደ ወንጌላዊው ሉቃስ አቀራረብ

እነርሱም ይህን ሲናገሩ ሳሉ ኢየሱስ ራሱ በመካከላቸው ቆሞ «ሰላም ለእናንተ ይሁን» አላቸው።

እነርሱ ግን መንፈስ የሚያዩ መስሎአቸው ደንግጠው በፍርሃት ተዋጡ። ኢየሱስ ግን እንዲህ አላቸው:- «ስለምን ትደነግጣላችሁ? ስለምንስ በልባችሁ ትጠራጠራላችሁ?

እጆቼንና እግሮቼን አይታችሁ እኔ ራሴ መሆኔን ዕወቁ፥ ዳስሳችሁም እዩኝ በእኔ እንደምታዩት መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውም።»

ይህንንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው። እነርሱም ከደስታና ከአድናቆት ብዛት የተነሣ ገና አላመኑም ነበር። ኢየሱስም፥ «አንዳች የሚበላ ነገር አላችሁን?» ሲል ጠየቃቸው። እነርሱም ትንሽ የተጠበሰ ዓሣ ሰጡት። እርሱም ተቀብሎ በፊታቸው በላ።

www.ethiopianorthodox.org

እንዲህም አላቸው:- «ከእናንተ ጋር በነበርኩ ጊዜ በሙሴ ሕግ፥ በነቢያትና በመዝሙር መጻሕፍት ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ መፈጸም አለበት ብዩ የነገርኳችሁ ቃል ይህ ነው።»

ከዚህ በኋላ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማስተዋል እንዲችሉ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው። እንዲህም አላቸው:- «መሲሕ መከራ እንደሚቀበልና በሦስተኛው ቀን ከሞት እንደሚነሣ አስቀድሞ ተጽፎአል፤ እንዲሁም በስሙ ንስሓና የኃጢአት ይቅርታ ወንጌል ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በየአገሩ ለሕዝብ ሁሉ እንደሚሰበክ ተነግሮአል። እናንተም የዚህ ሁሉ ነገር ምስክሮች ናችሁ፤ እነሆ እኔ የአባቴን የተስፋ ስጦታ እልክላችኋለሁ፥ እናንተም ኀይል ከላይ እስኪሰጣችሁ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቈዩ» (ሉቃ:ም24 ቍ:37–49)።

## ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያው ቶማስ:-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ደቀ መዛሙርቱ በመጣ ጊዜ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ፥ ዲዲሞስ የተባለው ቶማስ ከእነርሱ ጋር አልነበረም። ስለዚህ ሌሎች ደቀ መዛሙርት ቶማስን «ጌታን እኮ አየነው» አሉት።

እርሱ ግን «በምስማር የተወጉትን እጆቹን ካላየሁና ጣቴን ካላገባሁ፥ እጄንም በጐኑ ቍስል ካላገባሁ አላምንም» አላቸው።

ከስምንት ቀን በኋላ ደቀ መዛሙርቱ እንደገና በቤት ውስጥ ነበሩ፤ ቶማስም አብሮአቸው ነበር፥ በሮቹ ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጥቶ በመካከላቸው ቆመና «ሰላም ለእናንተ ይሁን» አላቸው። ከዚህ በኋላ ቶማስን፥ «ጣትህን ወዲህ አምጣና እጆቼን እይ፥ እጅህንም አምጣና በጐኔ ውስጥ አግባው፥ እመን እንጂ እመነተ ቢስ አትሁን» አለው።

ቶማስም «ጌታዬ አምላኬ» ሲል መለሰለት።

ጌታችንም ቶማስን «አንተስ ስለአየኸኝ አመንህ? ሳያዩኝ የሚያምኑ ግን የተመሰገኑ ናቸው» አለው (ዮሐ:ም:20 ቍ:24–29)።

## ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ መታየቱ:-

ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በጥብርያዶስ ባሕር አጠገብ ለደቀ መዛሙርቱ እንደገና ታየ፤ የታየውም እንዲህ ነው፥ ስምዖን ጴጥሮስ፥ ዲዲሞስ የተባለው ቶማስ፥ የገሊላ ቃና የሆነው ናትናኤል፥ የዘብዴዎስ ልጆችና ሌሎች ሁለት ደቀ መዛሙርትም አብረው ነበሩ። ስምዖን ጴጥሮስ «ዓሣ ለማጥመድ መሄዴ ነው» አላቸው።

እነርሱም «ከአንተ ጋር እንሄዳለን» አሉት። ወጥተውም ሄዱና ወደ ጀልባ ገቡ፤ ነገር ግን በዚያች ሌሊት አንድ ዓሣ እንኳ አልያዙም። ሲነጋ ኢየሱስ በባሕሩ ዳር ቆመ፥ ደቀ መዛሙርቱ ግን ኢየሱስ መሆኑን አላወቁም። ኢየሱስም «ልጆች ሆይ፥ ዓሣ አላችሁን?» አላቸው። እነርሱም «ምንም የለንም» አሉት። እርሱም «መረቡን ከጀልባው በስተቀኝ ጣሉና ታገኛላችሁ» አላቸው። ስለዚህ መረቡን በባሕሩ ውስጥ ጣሉት፤ ብዙ ዓሣም ከመያዛቸው የተነሣ መረቡን መጐተት አቃታቸው።

በዚህ ጊዜ ኢየሱስ የሚወደው ደቀ መዝሙር ጴጥሮስን፥ «ጌታ ነው እኮ» አለው። ስምዖን ጴጥሮስ «ጌታ ነው እኮ» ማለትን በሰማ ጊዜ፥ ለሥራ ብሎ ልብሱን አውልቆ ስለነበረ ወዲያው ልብሱን ለበሰና ወደ ባሕሩ ዘልሎ ገባ። ሌሎች ደቀ መዛሙርት ግን ከምድር የራቁት መቶ ሜትር ያኽል ብቻ ስለነበረ ዓሣ የሞላበትን መረብ እየሳቡ በጀልባ መጡ። ከጀልባው በወረዱ ጊዜ ዓሣ በላዩ የነበረበት የከሰል ፍምና እንጀራ አዩ። ጌታችንም «አሁን ካጠመዳችሁት ዓሣ አምጡ» አላቸው።

ስለዚህ ስምዖን ጴጥሮስ ወደ ጀልባው ገብቶ መቶ ኀምሳ ሦስት ትልልቅ ዓሣዎች የሞሉበትን መረብ ወደ ምድር ጐተተ፤ ይህን ያኽል ብዙ ዓሣ ቢይዝም መረቡ አልተቀደደም። ከዚህ በኋላ ኢየሱስ «ኑ ብሉ» አላቸው: ጌታችን ኢየሱስ መሆኑን ሁሉም ዐውቀው ስለ ነበረ «አንተ ማን ነህ? ብሎ ሊጠይቀው የደፈረ አልነበረም። ጌታችን ኢየሱስም እንጀራውንና እንዲሁም ዓሣውን አንሥቶ ሰጣቸው።

ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ ወዲህ ደቀ መዛሙርቱ ሲያዩት ይህ ሦስተኛ ጊዜ ነበር (ዮሐ:ም:21 ቍ:1–14)።



## ጌታችንና ሐዋርያው ጴጥሮስ:-

ከበሉ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስምዖን ጴጥሮስን የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ እነዚህ ከሚወዱኝ ይበልጥ ትወደኛለህን?» አለው። እርሱም «አዎ ጌታዩ ሆይ፥ እኔ እንደምወድድህ አንተ ታውቃለህ» ሲል መለሰለት። ኢየሱስም «ግልገሎቼን መግብ» አለው። ሁለተኛ ጊዜም «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ትወደኛለህን?» አለው። እርሱም «አዎ ጌታዩ ሆይ፥ እንደምወድድህ ታውቃለህ» አለው።

ኢየሱስም «ጠቦቶቼን ጠብቅ» አለው። ሦስተኛ ጊዜም «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ትወደኛለህን?» አለው።

ሦስተኛ ጊዜ «ትወደኛለህን?» ስላለው ጴጥሮስ አዘነና «ጌታ ሆይ፥ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤ እኔ እንደምወድድህም ታውቃለህ» አለው። ኢየሱስም እንዲህ አለው፥ «በጎቼን አሰማራ፤ እውነት፥ እውነት እልሃለሁ፥ አንተ ጐልማሳ ሳለህ ቀበቶህን በገዛ እጅህ ታጥቀህ ወደ ፈለግህበት ትሄድ ነበር፥ በሸመገልህ ጊዜ ግን አንተ እጆችህን ትዘረጋና ሌላ ሰው ያስታጥቅሃል፤ ወደማትፈልግበትም ይወስድሃል።» ይህንንም ያለው ጴጥሮስ በምን ዐይነት ሞት እግዚአብሔርን ማክበር እንዳለበት ሲያመለክት ነው፥ ከዚህ በኋላ ጴጥሮስን «ተከተለኝ» አለው (ዮሐ:ም:21 ቍ:15–19)።

## ጌታችንና ሌላው ደቀ መዝሙር:-

ጴጥሮስ ዘወር ብሎ ጌታችን ኢየሱስ የሚወደው ደቀ መዝሙር ሲከተለው አየ፥ ይህ ደቀ መዝሙር በራት ጊዜ ወደ ኢየሱስ ጎሮ ተጠግቶ «ጌታ ሆይ፥ አሳልፎ የሚሰጥህ ማን ነው?» ብሎ የጠየቀው ነው። ጴጥሮስ እርሱን አየና «ጌታ ሆይ፥ ይህስ ሰው ምን ይሆናል?› ሲል ኢየሱስን ጠየቀ። ኢየሱስም «እኔ እስክመጣ ድረስ እንዲኖር ብፈቅድ አንተን ምን አገባህ? አንተ ተከተለኝ» አለው።

በዚህ ምክንያት በወንድሞች መካከል «ይህ ደቀ መዝሙር አይሞትም» የሚል ወሬ ተሠራጨ፥ ነገር ግን ኢየሱስ «እኔ እስክመጣ ድረስ እንዲኖር ብፈቅድ አንተ ምን አገባህ» አለ እንጂ «አይሞትም» አላለም። ስለ እነዚህ ነገሮች ሁሉ የመሰከረና እነዚህንም ነገሮች የጻፈ ይህ ደቀ መዝሙር ነው፥ የእርሱም ምስክርነት እውነት እንደሆነ እናውቃለን።

«ኢየሱስ ያደረጋቸው ሌሎች ብዙ ነገሮች ደግሞ አሉ። እኔ እንደሚመስለኝ እርሱ ያደረጋቸው ነገሮችሁሉ አንድ በአንድ ቢጻፉ ኖሮ የሚጻፉትን መጻሕፍት ዓለም ራሱ መሸከም ባልቻለም ነበር » (ዮሐ:ም:21 ቍ:20–25)።

## የጌታችን ዕርገት:-

እነርሱ በአንድነት ተሰብስበው ሳሉ «ጌታ ሆይ! መንግሥትን ለእስራኤል መልሰህ የምትሰጥበት ጊዜ አሁን ነውን? ሲሉ ጠቁት።»

ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው:- «አብ በገዛ ሥልጣኑ የወሰነውን ጊዜና ዘመን እናንተ ልታውቁት አትችሉም። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ፤ በዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም፥ በይሁዳ አገር ሁሉ፥ በሰማርያ እስከ ምድርም ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ።» ይህንንም ካለ በኋላ እነርሱ እያዩት ወደ ሰማይ ወጣ፤ ደመናም ከዐይናቸው ሰወረው።

እርሱ በሚሄድበት ጊዜ እነርሱ ወደ ሰማይ ሲመለከቱ፥ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች አጠገባቸው ቆመው፥ «እናንተ የገሊላ ሰዎች፥ ስለምን ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ቆማችኋል? ይህ ወደ ሰማይ ሲወጣ ያያችሁት ኢየሱስ፥ ወደ ሰማይ ሲወጣ ባያችሁት ዐይነት ተመልሶ ይመጣል» አሉአቸው (ዮሐ:ሥ:ም:1 ቍ:6–11)።

## የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራት

በተዘጋ ቤት ውስጥ የመግባት ተአምር:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተነሣበት ቀን እሑድ ማታ ደቀ መዛሙርቱ የአይሁድ ባለሥልጣኖችን በመፍ ራት በራፎቹን ዘግተው በቤት ውስጥ ተሰብስበው ነበር፤ በሮቹ ተዘግተው ሳለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ተሰበሰቡበት ቤት ገባ፤ በመካከላቸውም ቆሞ «ሰላም ለእናንተ ይሁን» አላቸው። ከስምንት ቀን በኋላ ደቀ መዛሙርቱ እንደገና በቤት ውስጥ ነበሩ፤ በሮቹ ተዘግተው ሳሉ ጌታችን ኢየሱስ መጥቶ በመካከላቸው ቆመና «ሰላም ለእናንተ ይሁን» አላቸው (ዮሐ:ም:20 ቍ:19፥26)።

www.ethiopianorthodox.org

የመሰወሩ ተአምር:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአይሁድ፥ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ ባላቸው ጊዜ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ። ጌታችን ግን ተሰወረባቸውና ከቤተ መቅደስ ወጥቶ ሄደ (ዮሐ:ም:8 ቍ:58:59)።

## የጌታችን ምሳሌዎች

የዮናስ ምሳሌነት:- ብዙ ሰዎች ወደ እርሱ መጥተው በተሰበሰቡ ጊዜ ጌታችን እንዲህ አለ:- «የዚህ ዘመን ሰዎች እንዴት ክፉዎች ናቸው? ምልክት ለማየት ይፈልጋሉ፤ ነገር ግን ከነቢዩ ከዮናስ ምልክት በቀር ሌላ ምልክት አይሰጣቸውም። ነቢዩ ዮናስ ለነነዌ ከተማ ሰዎች ምልክት እንደነበረ፥ እንዲሁም የሰው ልጅ ለዚህ ዘመን ሰዎች ምልክት ይሆናል። የደቡብ ንግሥት በፍርድ ቀን ከዚህ ዘመን ሰዎች ጋር ተነሥታ በእነርሱ ላይ ትፈርዳለች። እርስዋ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከዓለም ዳርቻ መጥታለች፤ ነገር ግን እነሆ ከሰሎሞን የሚበልጥ እዚህ አለ፤ እንዲሁም የነነዌ ከተማ ሰዎች በፍርድ ቀን ከዚህ ዘመን ሰዎች ጋር ተነሥተው በእነርሱ ላይ ይፈርዱባቸዋል፤ የነነዌ ሰዎች የዮናስን ስብከት በሰሙ ጊዜ በኃጢአታቸው ተጸጽተው ንስሓ ገብተዋል። ነገር ግን እነሆ ከዮናስ የሚበልጥ እዚህ አለ» (ሉቃ:ም:11 ቍ:29-32)።

የቤተ መቅደስ ማፍረስና መሥራት ምሳሌ:- ከዚህ በኋላ የአይሁድ ባለሥልጣኖች ጌታችን «አንተ ይህን ለማድረግ መብት እንዳለህ ምን ተአምር ታሳየናለህ? » አሉት። ጌታችንም «ይህን ቤተመቅደስ አፍርሱትና እኔ በሦስት ቀን እሠራዋለሁ» አላቸው። እነርሱም «ይህን ቤተ መቅደስ ለመሥራት አርባ ስድስት ዓመት ፈጅቶአል፤ ታዲያ አንተ በሦስት ቀን ውስጥ ትሠራዋለህን? » አሉት። ጌታችን ግን «ቤተ መቅደስ» ብሎ የተናገረው ስለ ሰውነቱ ነበር። ስለዚህ ኢየሱስ ከሞት በተነሣ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ይህን አስታወሱ፤ በዚህ ምክንያት በመጽሐፍ የተጻፈውንና ጌታችን የተናገረውን ቃል አመኑ (ዮሐ: ም:2 ቍ:18-22)።

የምድረ በዳው የሙሴ እባብ ምሳሌ:- «ሙሴ በበረሓ እባብን ከፍ አድርጎ እንደ ሰቀለ እንዲሁም የሰው ልጅ ከፍ ብሎ ሊሰቀል ይገባዋል። ይህም የሚሆነው በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለምን ሕይወት እንዲያገኝ ነው (ዮሐ: ም:3 ቍ:14-15)።

## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

ጌታችን ተሰቅሎ ሞቶ በተቀበረ ጊዜ በነቢዩ ኢሳይያስ በግልጥ የተነገረው ትንቢት ተፈጸመ። «ምንም ወንጀል ሳይፈጽም፥ በአንደበቱም ሐሰት ሳይገኝበት በሞቱ ከክፉ አድራጊዎች ጋር ተቈጠረ፤ በባለጸጋም መቃብር ተቀበረ» (ኢሳ:ም:53 ቍ:9)።

ጌታችን፥ እንደ ወንጀለኛ ከሁለት ወንጀለኞች ጋር በመሰቀሉና በመሞቱ ከክፉ አድራጊዎች ጋር የተቈጠረ መሆኑንና ባለጸጋው የአርማትያሱ ዮሴፍ ለራሱ ባሠራው መቃብር ስለቀበረው በባለጸጋ መቃብር ተቀበረ ብሎ ኢሳይያስ ከብዙ ዘመን በፊት ተናግሮ ነበር።

ነቢያት አስቀድመው በተናገሩትና ጌታችን ራሱ መላልሶ ለደቀ መዛሙርቱ በነገራቸው መሠረት ጌታችን ሞቶ በተቀበረ በሦስተኛው ቀን ከሞት ተነሣ። ሲሞትም ሆነ ሲነሣ እርሱ በገዛ ፈቃዱ አደረገው እንጂ በማንም ሥልጣን ያደረገው አለመሆኑን ለማመልከት እንዲህ ብሏል:- «እንደገና መልሼ የምወስዳትን ነፍሴን የምሰጥ ስለሆንሁ አብ እኔን ይወደኛል፤ ነፍሴን በፈቃዴ አሳ ልፌ እሰጣለሁ እንጂ ከእኔ የሚወስዳት ማንም የለም፤ ነፍሴን አሳልፌ ለመስጠትና መልሼም ለመውሰድ ሥልጣን አለኝ» (ዮሐ:ም:10 ቍ:17-18)።

ኤማሁስ ተብላ ወደምትጠራው መንደር ለመሄድ ሁለት የጌታችን ደቀ መዛሙርት በጕዞ ላይ በነበሩበት ጊዜ እነርሱ ማንነቱን ሳያውቁት ጌታችን ከእነርሱ ጋር አብሮ መጓዝ ጀመረ። ከሁለቱ አንዱ ቀልዮጳ መሆኑን ወንጌላዊው ሉቃስ ሲገልጥ ሁለተኛው ማን እንደሆነ አለመግለጡ እርሱ ራሱ መሆኑን ያመለክታል። ይኸውም የሆነው ስለ ትሕትና ነው። ጌታችን ደግሞ ለሁለቱ ደቀ መዛሙርት ማንነቱን ያልገለጠላቸው በአንድ በኩል እንዳይደነግጡ ብሎ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በስሜት ይነጋገሩበት የነበረውን ጉዳይ አቋርጠ ጣልቃ ላልመግባትና ሙሉ ነጻነት ሊሰጣቸው ስለ ፈቀደ ነው። እነማርያም መግደላዊትና እነ ጴጥሮስ ወደ መቃብር ቦታ ሄደው ካዩ በኋላ የመሰከሩት ምስክርነት ግራ የተጋቡ መሆኑን ያመለክታል እንጂ ጌታችን የሰውን ዘር ከኃጢአት ባርነት ነጻ ለማውጣት የሚመጣው ክርስቶስ እርሱ ለመሆኑ ያመኑበት አይመስልም። ሆኖም እነርሱ የሚጠብቁት ክርስቶስ የአይሁድን ሕዝብ ከሮማውያን አገዛዝ ነጻ



የሚያወጣ፥ በዳዊት ዙፋን ላይ ተቀምጦ ገናና የሚሆን ንጉሥ ነበር እንጂ ሕማማትንና ሞትን ተቀብሎ ለዓለም ቤዛ የሚሆነውን የእግዚአብሔር ልጅ አልነበረም። በዚህም መሠረት ጌታችን ከመሰቀሉ በፊት መቼ ይነግሣል? እኛስ የንጉሥ ባለሟሎች የምንሆነው መቼ ነው እያሉ በሚጠባበቁበት ጊዜ የእርሱ ተሰቅሎ መሞት ተስፋ አስቈረጣቸው። እርሱ ከዚያ በፊት ስለ ሕማሙና ስለ ሞቱ መላልሶ የተናገራቸውን ትንቢቶች በጥሞና ያዳምጡአቸው ስላልነበረ አሁን እርሱ ከሞት ተነሥቶአል ተብሎ ሲነገራቸው ማመን አቃታቸው። እውነትንም ማመን ስለ አቃታቸው አስተሳሰባቸው ግራ ተጋባ።

ወደ ኤማሁስ ሲጓዙ የነበሩት ደቀ መዛሙርት ሌሎቹ ጓደኞቻቸው ደቀ መዛሙርት ወደሚገኙበት ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው ጌታችን እንደተገለጠላቸው በተዘጋ ቤት ውስጥ ሆነው በሚናገሩበት ጊዜ በድንገት ጌታችን በመካከላቸው ተገኝቶ ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። ሳይታሰብ በተዘጋው ቤት ውስጥ በመገኘቱ እርሱ ራሱ መሆኑን ተጠራጠሩ። እርሱ ግን እርሱነቱን ለመግለጥ የተቸነከሩ እጆቹንና እግሮቹን እንዲሁም በጦር የተወጋ ጐኑን እንዲዳስሱ አደረጋቸው። የተጠበሰ ዓሣና ማር አቅርበውለት በፊታቸው በላ፤ በዚህም ዐይነት ቀድሞ በነበረው በሚዳሰስ ሥጋ ለመነሣቱ ማስረጃ ነው። በሙታን ትንሣኤ ጊዜ የሰው ዘር ሁሉ በዚሁ ዐይነትና ዳግመኛ ላለመሞት የሚነሣ ስለሆነ ጌታችን የሙታን ትንሣኤ በኵር ተባለ።

ለተራ ሰው በተዘጋ ቤት ውስጥ ገብቶ መገኘት እንዴት ይቻላል? ለእኛ ለተራ ሰዎች በእር ግጥ የማይቻል ነው። ክርስቶስ ግን ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው በመሆኑ ይቻለዋል።

ደቀ መዛሙርቱ ወደሚኖሩበት ከውስጡ ወደ ተቈለፈ ቤት ውስጥ ገብቶ እንደወጣ እንዲሁም ከድንግል ማርያም በተወለደ ጊዜ ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ ከማኅፀንዋ ወጥቶአል (ሕዝ:ም.44 ቍ:2)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ጴጥሮስን ሦስት ጊዜ መላልሶ መጠየቁ እምነቱንና ጌታችንን የሚወድ መሆኑን እንዲናዘዝ ለማድረግ ነው። ይኸውም ቀደም ብሎ ሁሉም እንኳ ቢክዱህ እኔ አልክድህም ካለ በኋላ በፍጹም አላውቀውም ብሎ ሦስት ጊዜ የካደውን የክሕደት ኃጢአት ለማረም ነው። በዚህም ኑዛዜ ጌታችን ኃጢአቱን ይቅር ያለለት መሆኑን ያመለክታል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብርሃም በፊት እኔ አለሁ ብሎ ለአይሁድ በነገራቸው ጊዜ ይህን ማለት ዘለዓለማዊነት በመሆኑና ዘለዓለማዊነት ደግሞ የእግዚአብሔር ብቻ በመሆኑ በድንጋይ ሊወግሩት ሲነሡ በመካከላቸው ዐልፎ ሄደ፤ ማለት ተሰወረባቸው። ጌታችን ብዙ ጊዜ እንደዚህ ተሰውሮአል፤ ለምሳሌ በኤማሁስ ከደቀ መዛሙርቱ ተሰውሮአል (ሉቃ:24፥ 31)፤ አይሁድ ከተማቸው ከተመሠረተችበት አጠገብ ወደ ታች ሊጥሉት በወሰዱት ጊዜ በመካከላቸው ዐልፎ ሄዶአል (ሉቃ:ም:4 ቍ:2830)፤ ሌላ ጊዜም ሊይዙት ሲፈልጉ ከእጃቸው አምልጦአል (ዮሐ:ም:7 ቍ:30፥ 32፥ 40፥ 44)።

አይሁድ ከጌታችን ተአምራትን እንደሚፈልጉ ባየ ጊዜ ከነቢዩ ዮናስ ምልክትነት በቀር ሌላ ምልክት አይሰጣቸውም ብሎአል። ዮናስ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በዓሣ ሆድ ቈይቶ ለነነዌ ከተማ ሰዎች ሰብኮላቸው ንስሓ ገብተው ድነዋል። ጌታችንም ሕማማትን ከተቀበለ በኋላ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በከርሰ መቃብር ውስጥ ቈይቶ በመነሣት ለዓለም ሕዝብ ቤዛ ሆኖአል።

እንደገና በሌላ ጊዜ ተአምር እንዲያሳያቸው ሲጠይቁት ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱትና እኔ በሦስት ቀን እሠራዋለሁ ብሎአል። ይህንንም ሲል የሰውነቱን ቤተ መቅደስ ማለቱ ስለሆነ እናንተ ከገደላችሁኝ ከሦስት ቀን በኋላ ከሞት እነሣለሁ ማለቱ ነው።

በሌላ ጊዜ ደግሞ ጌታችን የራሱን ስቅለት ሙሴ በምድረ በዳ ከሰቀለው እባብ ጋር አመሳስሎአል። የእስራኤል ልጆች በበደሉ ጊዜ እግዚአብሔር በእባብ እየተነደፉ እንዲሞቱ አድርጎአቸው ነበር። በኋላ ግን በንስሓ ወደ እግዚአብሔር በጮኹ ጊዜ የነሐስ እባብ ሠርቶ እንዲሰቅለው እግዚአብሔር ሙሴን አዘዘው። በእባቡ የተነደፈ ሰው ሁሉ ወደ ተሰቀለው የነሐስ እባብ በተመለከተ ጊዜ መዳን እንደ ቻለ ሁሉ ስለ እኛ ስለ ሰው ዘር በተሰቀለው በክርስቶስ አምኖ ትእዛዙን የሚፈጽም ሁሉ ይድናል ማለት ነው።

## ጥያቄዎች

1. ጌታችንን ገንዘው የቀበሩት እነማን ናቸው?
2. የጌታችንን አስከሬን ከጲላጦስ የለመነ ማን ነው?
3. እሑድ ጧዋት በማለዳ ወደ ጌታችን መቃብር የሄዱ እነማን ናቸው?

www.ethiopianorthodox.org

4. መቃብሩ የተዘጋበትን ድንጋይ ያንከባለለ ማን ነው?
5. እንደ መብረቅ የሚያበራው የማን ፊት ነበር?
6. ጠባቂዎቹ በመንቀጥቀጥ እንደ በድን የሆኑት እነማንን በመፍራት ነው?
7. ሴቶቹ ምን እንዲሉ ነው ወደ ደቀ መዛሙርቱ የተላኩት?
8. ለደቀ መዛሙርቱ ቅገሮት የመሰላቸው ምኑ ነው?
9. ጌታችን ለሁለት ደቀ መዛመርቱ የተገለጠላቸው ወዴት ሲሄዱ አግኝቶአቸው ነው? እነርሱስ እነማን ነበሩ?
10. የተገለጠላቸውስ እንዴት ነው?
11. ጌታችን ለደቀ መዛመርቱ የተገለጠላቸው እንዴትና መቼ ነው?
12. ጌታችን ከሞት ከተነሣ በኋላ በመጀመሪያ የተገለጠው ለማን ነው?
13. ጌታችን እርሱነቱን ለመግለጥ ለደቀ መዛሙርቱ ምን አደረገላቸው?
14. እርሱ ራሱ በሥጋው መሆኑን ለማመልከት ምን ምን አደረገ?
15. ጌታችን ቶማስን እመን እንጂ እምነተ ቢስ አትሁን ያለው በምን ምክንያት ነው?
16. ጌታችን ቶማስን የተገናኘው ከሞት ከተነሣ ከስንት ጊዜ በኋላ ነው?
17. ደቀ መዛሙርቱ አንድ መቶ ኀምሳ ሦስት ትልልቅ ዓሣዎችን የያዙት እንዴትና መቼ ነው?
18. ጌታችን፡ ቅዱስ ጴጥሮስን ትወደኛለህን ብሎ ሦስት ጊዜ የጠየቀው በምን ምክንያት ነው?
19. ጌታችን የሚወደው ደቀ መዝሙር አይሞትም የሚል ወሬ የተሠራጨው በምን ምክንያት ነው?
20. ጌታችን በተዘጋ ቤት ውስጥ የገባው ስንት ጊዜ ነው?
21. ጌታችን፡ በተአምር የተሰወረባቸውን ሁኔታዎች ግለጥ።
22. የነቢዩ ዮናስን ምሳሌነት ገለጥ።
23. የቤተ መቅደስ መፍረስና እንደገና መሠራት ምሳሌ ግለጥ
24. የምድረ በዳውን እባብ ምሳሌ ግለጥ።
25. ስለ ጌታችን መሰቀል፡ መሞትና መቀበር የነቢዩ ኢሳይያስን ትንቢት እያገናዘብክ ግለጥ።
26. ጌታችን የሞተውም ሆነ ከሞት የተነሣው በገዛ ሥልጣኑና ፈቃዱ መሆኑን የሚገልጠውን ጥቅስ አቅርብ።
27. ወደ ኤማሁስ ይጓዙ ለነበሩት ደቀ መዛሙርት ማንነቱን ያልገለጠላቸው በምን ምክንያት ነው?
28. አይሁድ ይጠብቁ የነበሩት እንዴት ያለ መሲሕ ነበር?
29. የጌታችን ደቀ መዛሙርት በጊዜው መምህራቸው ስለ ሕማሙና ስለ ሞቱ ይነግራቸው የነበረውን ትንቢት በጥሞና አዳምጠው ያላመኑት ለምን ነበር?
30. ጌታችን በተቈለፈ ቤት ውስጥ ገብቶ መውጣቱ ምሳሌነቱ ከምን ጋር ነው?

# ምዕራፍ 4

# ቤተ ክርስቲያን

## የቤተ ክርስቲያን ማእከልነት

ማእከል የሚለው ቃል ሌላ ትርጒም ሊኖረው የሚችል ቢሆንም እንኳ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ሊባል የተፈለገው ግን በተለያዩ ቦታዎች ለሚገኙ የአንድ ተቋም አባሎች በአንድ ቦታ ሆኖ መመሪያ የሚሰጥ የበላይ አካል ማለት ነው። አባባሉን የበለጠ ግልጥ ለማድረግ ለምሳሌ የአንድ ቤተ ክርስቲያን ማእከል በሚባልበት ጊዜ የዚያች ቤተ ክርስቲያን አባሎች በሚገኙባቸው ቦታዎች ሁሉ መከተል የሚገባቸውን የቅዱሳት መጻሕፍት አተረጓጐም ስልት፡ መሠረታዊ እምነትና የአገልግሎት ሥነ ሥርዓት መመሪያዎችን አዘጋጅቶ የሚሰጥ የበላይ መንፈሳዊ አካል

www.ethiopianorthodox.org



ማለት ነው። ይህም የበላይ አካል የሚሰጠው መመሪያ በሥሩ ባሉ አባሎች ሁሉ ዘንድ በትክክል የሚሠራበት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት። የቤተ ክርስቲያን ማእከልነት የተባለውም ይህ የዚህ ዐይነቱ አሠራር ነው።

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአባቱ ከእግዚአብሔር አብ ጋር አንድ እንደሆነ እንዲሁም ደቀ መዛሙርቱና የቤተ ክርስቲያን ልጆች አንድ ይሆኑ ዘንድ እንደ ሰውነቱ የጸለየ መሆኑን በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 17 ቍ:11፥ 22፥ 23 መመልከት እንችላለን። በዚህም መሠረት የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሳይለያዩ በአንድነት እንዲኖሩ እንጂ በተለያዩ ምክንያቶች እንዲለያዩ የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዕቅድ አልነበረም። የእርሱ ፈቃድ ግን ክርስቲያኖች ሁሉ በያሉበት ሆነው ለእርሱ ለአንዱ ጌታ የሚገዙት በዘር፥ በጐሣ፥ በብሔር፥ በቋንቋና በሌሎችም ምክንያቶች ሳይለያዩና ሳይናናቁ፥ በወንድማማ ችነትና በእኅትማማችነት፡ ወይም በእኅቶችና በወንድሞች መካከል በሚኖር የአንድነት ስሜት ኅብረት እንዲኖራቸው ነው። ይህ አንድነት ወይም ኅብረት ሊኖርም የሚችለው የቤተ ክርስቲያኒቱ ማእከላዊ አመራር ሲኖር ነው።

የቤተ ክርስቲያንም ማእከላዊ አመራር ተግባራዊ ሊሆን ከሚችልባቸው አሠራሮች መካከል የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም፥ የመሠረተ እምነትና የአገልግሎት ሥርዓት አመራሮች ይገኙባቸዋል።

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም ማእከልነት</u>:- እንደሚታወቀው መጽሐፍ ቅዱስ ለእኛ ለምእመናን የቀረበልን በታሪክ፥ በሕግ፥ በጥበብና በትንቢት መልክ ነው። የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎችም በመንፈስ ቅዱስ ጠባቂነትና መሪነት የጻፉአቸው ስለሆነ ምንም ስሕተት እንደሌለባቸው እናምናለን።

በምሳሌ፥ በጥበብ፥ በራእይና በትንቢት የቀረቡልንን የቃለ እግዚአብሔር ክፍሎች መንፈስ ቅዱስ የገለጠላቸው ሰዎች አስተላልፈውልንና የእነርሱን ትምህርት ተከትለን ካልሆነ በቀር በዓለማዊ የሙሴነት ዘዴ ትርጓሜ ለመስጠት መሞከር ጉዳት እንጂ ምንም ጥቅም የለውም። የሰው ሁሉ አስተሳሰብ አንድ ስላልሆነ እያንዳንዱ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን የመተርጐም ነጻነት ከተሰጠው አንዱ ተርጓሚ ከሌላው ተርጓሚ ተለይቶ ብዙ ዐይነት ትርጓሜዎችን ስለሚያ ስከትል ብዙ የሃይማኖት ቡድኖች በየበኩላቸው ሊቋቋሙ ነው። ይህም አሠራር እግዚአብሔር ከሚፈቅደው የቤተ ክርስቲያን አንድነት ተቃራኒ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስን ደግሞ ማንም ሰው እንደፈለገው ሊተረጒመው የማይችል መሆኑን በሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች ለማስተዋል ይቻላል።

በትንሣኤ ሙታን የማያምኑት ሰዱቃውያን ጌታችንን ለመፈተን ብለው ጥያቄ በጠየቁት ጊዜ እነርሱ የተሳሳቱት ቅዱሳት መጻሕፍትንና የእግዚአ ብሔርን ኀይል ካለማወቃቸው የተነሣ መሆኑን ጌታችን የገለጠላቸው የመጽ ሐፉ መንፈስ ማለት የመጽሐፉ ትርጓሜ እነርሱ እንደመሰላቸው አለመሆኑን ሲያመለክታቸው ነው። ስሕተታቸውንም በበለጠ ሲያብራራላቸው እግዚአብሔር በሕይወት በዚህ ዓለም ያልነበሩት የአብርሃም፡ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ነኝ ማለቱ እነ አብርሃም በወዲያኛው ዓለም በሕይወት ያሉ በመሆናቸው ነው እንጂ ሞተው የሚቀሩ ቢሆኑ ኖሮ የሙታን አምላክ ነኝ በላለም ነበር ብሎአቸዋል። እነርሱም የሙታን መነሣት አይኖርም ወደሚል ከፍተኛ ክሕደት የወደቁት የመጽሐፉን ትርጓሜ ካለማወቃቸው የተነሣ ነው (ማቴ: ም:22 ቍ:29–33)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አብዛኛውን ጊዜ የሚናገረው በምሳሌ ነበር። እርሱ ይናገራቸው የነበሩት ምሳሌዎች ምን ትርጒም እንዳላቸው ለማወቅ ቀላል ስላልነበረ ብቻቸውን ሲሆኑ ለደቀ መዛሙርቱ ያስረዳቸው ነበር (ማር:ም:4 ቍ:33–34)።

በኤልያስ ስም ስለ መጥምቁ ዮሐንስ የተነገረውን ትንቢት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት እንዳብራራ ቀጥለን እንመልከት።

የተነገረው ትንቢት እንዲህ የሚል ነበር:- «ነገር ግን ታላቅና አስፈሪ የሆነው የጌታ ቀን ከመምጣቱ በፊት ነቢዩን ኤልያስን ወደ እናንተ እልክላችኋለሁ፤ እርሱም መጥቼ ምድራችሁን እንዳላጠፋ ተለያይተው የነበሩትን አባቶችና ልጆች ልብ ለልብ እንዲቀራረቡ ያደርጋቸዋል» (ሚል:ም:4 ቍ:5–6)።

የዮሐንስ መጥምቁ ደቀ መዛሙርት መምህራቸው ወደ ጌታችን ልኮአቸው መልእክታቸውን አድርሰው ከተመለሱ በኋላ ጌታችን ስለ ዮሐንስ ከተናገራ ቸው ንግግሮች መካከል እንዲህ የሚል ይገኝበታል:-

«መላው የነቢያት ትምህርትና የኦሪት ሕግ እስከ መጥምቁ ዮሐንስ ድረስ ሲናገሩ ቈይተዋል። እንግዲህ እነርሱ የተናገሩትን ለመቀበል ከፈቀዳችሁ ያ ይመጣል የተባለው ኤልያስ እነሆ፥ ይህ ዮሐንስ ነው» (ማቴ:ም:1 ቍ:13–14)።

ከክርስቶስ በፊት አስቀድሞ ነቢዩ ኤልያስ ይመጣል ብለው የሙሴ ሕግ መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት በመጥቀስ የጌታችን ደቀ መዛሙርት መምህራቸውን በጠየቁት ጊዜ የሚከተለውን መልስ ሰጥቶአቸዋል:-

«እርግጥ ነው፤ ኤልያስማ አስቀድሞ ይመጣል፤ እርሱ ሁሉንም ያስተካክላል። ነገር ግን ኤልያስ ገና ድሮ መጥቶአል እላችኋለሁ፤ ሰዎች ግን አላወቁትም፤ ስለዚህ የፈለጉትን አደረጉበት» (ማቴ: ም:17 ቍ:11–12)።

በዚህም ዐይነት በኤልያስ ስም የተነገረው ትንቢት ስለ መጥምቁ ዮሐንስ መሆኑን ጌታችን እስከ ገለጠበት ጊዜ ድረስ የትንቢቱ ትክክለኛነት አይታወቅም ነበር ማለት ነው።

ስለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ ሲል ያረጋገጠው:- «ከሁሉ በፊት ማስተዋል የሚገባችሁ በመጽሐፍ የሚገኘውን ማንኛውንም ትንቢት፥ ማንም ሰው በራሱ ግላዊ አስተሳሰብ ሊተረጉም አለመቻሉን ነው፤ ማንኛውም ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣም፤ ነገር ግን ትንቢት በመንፈስ ቅዱስ የተመሩ ሰዎች ከእግዚአብሔር ተቀብለው የተናገሩት ነው» (2ኛ:ጴጥ:ም:1 ቍ:20–21)።

ሊቀርቡ ከሚችሉ ብዙ ማስረጃዎች መካከል እነዚህ ከላይ የቀረቡት ምሳሌዎችና ጥቅሶች እንደሚያስረዱት እግዚአብሔር ካልገለጠለት በቀር ማንም ሰው ቢሆን የእግዚአብሔርን ቃል የመተርጐም ችሎታ አይኖረውም ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ማንም ሰው እንደፈለገው ይተርጒመው ከተባለ ቤተ ክርስቲያን አንድ መሆንዋ ቀርቶ ትበታተን ማለት ነው። ይህ ዐይነቱ አስተሳሰብ ደግሞ የክርስቶስን ፈቃድ የሚቃረን ይሆናል።

በዚህም ምክንያት ነው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ማእከላዊነት ያስፈልገዋል የሚባለው።

<u>የመሠረተ እምነት ማእከልነት</u>:- በአንድ ሃይማኖት ውስጥ ባለ የትምህርተ መለኮት አመለካከት ላይ የዚያ ሃይማኖት አባሎች ሁሉ አንድ ካልሆኑ በአንድ ሃይማኖት ሥር ናቸው ለማለት አይቻልም።

ለምሳሌ እግዚአብሔር ዓለምን ከምንም ፈጠረ። እግዚአብሔር ብቻ ዘለዓለማዊ ነው ለሚለው እምነት ምእመናን የተለያየ አስተሳሰብ ካላቸው በአንድ ሃይማኖታዊ ማእከል አይመሩም ማለት ነው።

በሰው አፈጣጠር እምነት ረገድ ሰው የሕይወት እስትንፋስ እፍ የተባለበት ፍጡር ስለመሆኑ ምእመናን የተለያየ አስተሳሰብ ካላቸው በአንድ የሃይማኖት ማእከል ሥር አልተሰባሰቡም ማለት ነው።

ሰው ነጻ ፈቃድ አለው ሲባል ማንም ሰው በፍላጎቱ በድርጊቱና በእምነቱ አይገደድም ማለት ነው። ከምእመናን መካከል ከፊሉ በሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ የሚያምን ሆኖ ከፊሉ ደግሞ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው አንድም ለጽድቅ ያለዚያም ለኵነኔ ነው የሚሉ ከሆነ እነዚህ ሁለት ተቃራኒ አስተሳሰቦች በመሆናቸው ሁለቱ ወገኖች በአንድ የሃይማኖት ማእከል ሥር ሊሆኑ አይችሉም።

በምሥጢረ ሥጋዌና በጌታችን ቤዛነት ትምህርት ላይ በየጊዜው የተለያዩ አስተሳሰቦች ተነሥተው የሲኖዶስ ውሳኔዎች ተላልፈውባቸዋል። ከነዚህም መካከል አቡሊናርዮስና ቢላግዮስ የተባሉ ሰዎች ይገኙባቸዋል።

<u>አቡሊናርዮስ:-</u> ጌታ የተዋሐደው ነፍስ የሌለውን ሥጋ ነው ሲል ቢላግዮስ ደግሞ የአዳም ኃጢአት ወደ ልጆቹ አልተላለፈም ብሎአል። እነርሱም በቍስጥንጥንያና በኤፌሶን ጉባኤዎች ተወግዘዋል። እንግዲህ፥ በዚህ እምነት ላይ ቤተ ክርስቲያን ከምታስተላልፈው መመሪያ የተለየ አስተሳሰብ ያላቸው ምእመናን ቢኖሩ ከዚያ ሃይማኖታዊ ማእከል ውጪ ናቸው ማለት ነው። ለምሳሌ ቢላግዮስ የአዳም ኃጢአት ከራሱ ዐልፎ ወደ ልጆቹ አልተላለፈም በሚልበት ጊዜ የክርስቶስን አዳኝነት መቃወሙ ነው።



በክርስትና ሃይማኖት ውስጥ [illegible] ከም[illegible]ው ማእከላዊ መመሪያ የተለየ ዘለዓለማዊ ሕይወት ነው። በዚህ ረገድ ቤተ ክርስቲያን ከማእከላዊው እምነት መመሪያ ወጥተዋል ማለት ነው።
አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ካሉ

በሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ላይ የሚኖረው አስተሳሰብ የተለያየ ከሆነ መመሪያ ሰጪ ማእከሉም የተለያየ ነው ማለት ነው።

የክርስትና ሃይማኖት ከሌሎች ሃይማኖቶች ከሚለይባቸው ከዋነኞቹ መሠረተ እምነቶች አንዱ ምሥጢረ ሥላሴ ነው። በዚህ እምነት ላይ እንደ አርዮስና እንደ መቅዶንዮስ ያሉ ሰዎች ተነሥተው በጊዜአቸው የነበሩ ሲኖዶሶች አውግዘዋቸዋል። አሁንም ቢሆን ምሥጢረ ሥላሴን በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የሚቃወሙ ሰዎች አብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያን በማእከልነት ከሚአቀርቡአቸው መመሪያዎች ውጪ ናቸው።

እንዲሁም ትውፊትን፥ እምነትንና ተግባርን፥ መንፈሳውያን በዓላትን፥ ሥርዓተ ጾምን፥ ጸሎተ ፍትሐትን፥ የሕፃናትን ጥምቀት በተመለከተ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያን የተለያዩ የእምነት መመሪያዎች አላቸው። አንድ ሰው የየትኛው የሃይማኖት ማእከል አባል መሆኑን የሚያሳየው በሚከተላቸው የሃይማኖት መመሪዎች አማካይነት ነው።

አብዛኛውን ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም ማእከልነት ያላት ቤተ ክርስቲያን የመሠረተ እምነት ማእከልነትዋም ጠንካራ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም ልቅ ከሆነ መሠረተ እምነቱም ጥንካሬ አይኖረውም።

<u>የአምልኮ ሥርዓት ማእከልነት</u>:- የአንድ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሥነ ሥርዓት ሲባል የአገልግሎቱ ጊዜ መነሻና መድረሻ፥ የጸሎቱ ቅደም ተከተል፥ በአገልግሎቱ ጊዜ፥ የጳጳሱ ወይም የካህኑ ድርሻ፥ የዲያቆኑ ድርሻ፥ የሕዝቡ ድርሻ፥ ሁሉም ድርሻውን በምን ዐይነት መወጣት የሚገባው ስለመሆኑ፥ ቤተክርስቲያንም የጸሎት ቦታና የእግዚአብሔር መገኛ እንደ መሆኑ ሊሰጠው የሚገባ አክብሮትና እነዚህን የመሳሰሉ ሁኔቴዎች ይገኙባቸዋል። እነዚህም ሥርዓቶች የአንድ ቤተ ክርስቲያን አባሎች በሚገኙባቸው ቦታዎች ሁሉ ያለምንም ለውጥ ተገባራዊ መሆን ይገባቸዋል።

በዲድስቅልያው መመሪያ መሠረት በምድር ባለችው ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ወኪል የሆነው የበላይ ኀላፊ ኤጲስ ቆጶሱ ሲሆን ቀሳውስቱ አስተማሪዎችና ዲያቆናቱ ደግሞ አገልጋዮች ናቸው።

በመጽሐፈ ዲድስቅልያ መቅድም እንደ ተገለጠው:- «ቤተ ክርስቲያን በሰማያዊ ሥርዓት መመራት ያለባት ስለሆነ ሁሉም አመስግኖ ጌታ በወሰነለት በየሥራ ደረጃው ይጸና ዘንድ የሚከተለው ተወስኖአል:- ኤጲስ ቆጶሱ እንደ ጠባቂ፥ ቀሳውስቱ እንደ አስተማሪዎች፥ ዲያቆናቱ እንደ አገልጋዮች፥ ንፍቅ ዲያቆናቱ እንደ ረዳቶች፥ አናጕንስጢሳውያኑ እንደ አንባቢዎች። መዘምራኑ በመረዳት እንደ ዘማሪዎች፥ አገልጋዮቹ እንደ ጠባቂዎች ሆነው፥ ሌላው ሕዝብ ደግሞ የወንጌልን ቃል በአክብሮትና በጸጥታ የሚያዳምጡ ናቸው» (የመጽሐፈ ዲድስቅልያ መቅድም)።

ሌላው በመጽሐፈ ዲድስቅልያ አንቀጽ 10 ላይ የተገለጠው ቤተ ክርስቲያን በትልቅ መርከብ የምትመሰል መሆንዋ ነው። በውስጥዋ ለጸሎት የተሰበሰቡት ምእመናን በመርከቡ ተሳፋሪዎች ይመሰላሉ፥ ዲያቆናቱ ደግሞ በመርከበኛው ወይም በመርከቡ ረዳት ይመሰላሉ። በመርከቡ ውስጥ ያሉት ተሳፋሪዎች በሰላም ወደሚሄዱበት ቦታ እንዲደርሱ የመርከቡ ረዳት ጥረት ያደረጋል። በዚህም ዐይነት ዲያቆናቱ እያንዳንዱን ምእመን በተገቢው ቦታ በማስቀመጥ፥ ሰዎች እንቅልፍ ይዞአቸው እንዳይተኙ፥ ወይም በአጠገባቸው ካለ ሰው ጋር ወሬ በማውራት መሳቅና መሳለቅ እንዳይጀምሩ፥ በዚህም ድርጊታቸው ቃለ እግዚአብሔር በጥሞና እንዳይሰማና ጸሎቱም በተመስጦ እንዳይካሄድ እንቅፋት ከሚሆኑት ሰዎች ይጠብቃሉ። የሕዝበ ክርስቲያኑ ዐላማ ከግቡ ሊደርስ የሚችለው ሁሉም በበኩሉ አምልኮውን በሥርዓትና በመንፈሳዊነት ስሜት ተግባራዊ ሲያደርግ ነው እንጂ በአጠገብ ከሚገኝ ሰው ጋር እየተነጋገሩ በመሳቅና በመሳለቅ አይደለም። ይህማ ቢሆን ኖሮ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንኳ መምጣት ባላስፈለገም ነበር።

<u>ማጠቃለያ</u>:- ቤተ ክርስቲያን ለልጆችዋ መመሪያ እየሰጠች በማእከላዊነት በመቈጣጠር ፈንታ እነርሱ የመሰላቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ እንዲከተሉ፥ በመንፈሳዊ ሳይሆን በሰብአዊ ምርምር እንዲጓዙ መረን ከለቀቀቻቸው ወደ አልታሰበ ክሕደት ሊያመሩ ይችላሉ። እንደዚህ ከዚህ አትለፉ የሚላቸው መመሪያ ከሌለ ከክሕደት ሰዎች ጋር ይተባበሩ ይሆናል።



www.ethiopianorthodox.org

ያለውን ሰው ጸላኤ ሠናይ ሲያገኘው ደጉን ነገር ከፋ፣ ከፋውን ነገር ደግሞ ደግ አስመስሎ ያቀርብለታል።

የቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነት ይህ ነው፤ ከዚህ የተለየው ከቤተ ክርስቲያን እምነት ውጪ ነው ተብሎ በማስረጃ የሚቀርብ መመሪያ ሳይኖር ቀርቶ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል ሲጠየቅም ሆነ ሲያስተምር ለእርሱ የመሰለውን ብቻ የሚናገር ከሆነ በጠያቂውና በሚማረውም ምእመን ዘንድ ትዝብትንና ንቀትን ያተርፋል። በጣም የሚያሳዝነው ውጤት ግን ያ የታዘበ ምእመን በትዝብትና በንቀት ዐልፎ ለችግሩ መፍትሔ በመፈለግ ፈንታ ራስን ከዶ ወደ ሌላ ወገንነት መኰብለሉ ነው። በእርግጥ ሁሉም እንደዚህ ነው ለማለት አይቻልም። ግን ዐልፎ ዐልፎም ቢሆን እንደዚህ ያለ ሁናቴ መከሠቱ በኀላፊነት አያስጠይቀንምን?

የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ ማእከልነት:- የትምህርተ መለኮት ማእከላዊ መመሪያ እንዲሁም የሥርዓታዊ አሠራርና ትርጒሙ በምእመናን አእምሮ ውስጥ ሠርጎ እንዲገባ ከተደረገ ወደ ሌላ የመሄዳቸው፣ የመነጠቃቸው፣ ወይም የመኰብለላቸው ስጋት ላይኖር ይችላል። ነገር ግን ማእከላዊ መመሪያ ኖረም አልኖረ፣ ያልተማረው ወይም ጥራዝ ነጠቅ አስተማሪ ነኝ ባይ ሲጠየቅ መልስ ለመስጠት የማይችል፣ ወይም ያልተጠየቀውን የሚያወራ፣ ወይም ሁሉም ሲያቅተው ጠያቂውን የሚሳደብ ከሆነ፣ ይህ እንደዚህ ያለው ነው ምእመናንን እያስኰበለለ ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚያደኸይ።

## የቤተ ክርስያን ቅዱሳን

ትልቁ ባስልዮስ:- ቅዱስ ባስልዮስ በ329 ዓ.ም. በሰብስጥያ ከተማ ተወለደ። የፍልስፍናን ደንቦች ከአባቱ ካጠና በኋላ ወደ ፍልስጥኤም ቂሣርያ ትምህርት ቤት ገባ። ከዚያም ወደ ቍስጥንጥንያ ሄደ። ቀጥሎም ወደ አቴና ሄዶ ከ351 እስከ 355 ዓ.ም. ድረስ ቈይቶአል። እዚያ በነበረ ጊዜ በትምህርቱ የላቀ ነበር። ከጓደኛው ከነባቤ መለኮት ጎርጎርዮስ የተገናኘው አቴና በነበረ ጊዜ ሲሆን ጓደኝነታቸው በጣም የተጠናከረ ነበር። በ357 ዓ.ም. ወዲ ናጥሩን በነበረ ጊዜ ሲሆን ጓደኝነታቸው በጣም የተጠናከረ ነበር። በ357 ዓ.ም. ወዲ ናጥሩን ወደሚባለው የግብጽ ገዳም ከሄደ በኋላ ወደ አገሩ ተመልሶ በቀጰዶቅያ ተራሮች ለአምልኮተ እግዚአብሔር ብሕትውናውን ቀጠለ። በዚያ ቦታ ከቅዱስ ጎርጎርዮስ ጋር አብረው በመሆን እግዚአብሔርን እያመለኩና መሬትም እያረሱ እንዲያመርቱ ተስማሙ። ቅዱስ ባስልዮስ፣ ንጉሥ ነገሥት ዮልያኖስ በጌታችን ኢየሱስ ላይ ጽፎት ለነበረው መልስ በመስጠት ረገድ በደፋርነቱ በጣም ዝነኛ ሆኖ ነበር። በ370 ዓ.ም. የቀጰዶቅያ ጳጳስ ሆኖ ተሾመ። አርዮሳዊ በነበረው በንጉሥ ነገሥቱ በቫሌንስ አማካይነት በክርስቲያኖች ላይ የደረሰው ጭንቀትና ስደት ተካፋይ ሆኖአል። ለንጉሥ ነገሥቱ ትእዛዞች ተገዢ ሆኖ ባለመገኘቱ የጦር አዛዡ እንዲህ አለው:- «የትልቁን ንጉሠ ነገሥት ትእዛዝ ስትቃወም በገንዘብህና በነፍስህ ላይ ሥልጣን እንዳለው አታውቅምን? ሕይወትህን ለማጥፋት ችሎታ አለው።» ቅዱስ ባስልዮስም እንዲህ ሲል መለሰ:- የለበስኩትን ልብስ ልታራቍቱኝና ወይም የእኔ ሀብቶች የሆኑትን ጥቂት መጻሕፍ የምትነጥቁኝ የለበስኩትን ልብስ ልታራቍቱኝና ወይም የእኔ ሀብቶች የሆኑትን ጥቂት መጻሕፍ የምትነጥቁኝ ካልሆነ በቀር እኔ ምንም ንብረት ስለሌለኝ ምንም የሚጠፋብኝ ነገር የለም። በአንድ ቦታ የተወሰንሁ ስላይደለሁ ግዞቱን አላውቀውም። ምድር ሁሉ የእግዚአብሔር ነው፤ እርሱም የእንግድነቴ ቦታ ነው፤ ሞትንም አልፈራውም። ለእውነተኛው ሕይወት ስለምበቃ ሞት ለእኔ ጸጋ ነው። ያም የጦር አዛዥ እንደዚህ ያለ የድፍረት አነጋገር ከማንም ሰምቼ አላውቅም አለው። ባስልዮስ ደግሞ መልስ ሲሰጠው የአንተ ዐይነቱ አነጋገር ለአንድ ጳጳስ የሚነገር አይደለም አለው። የጦር አዛዡም በእርሱና በጳጳሱ መካከል የተካሄደውን ንግግር ለአለቃው በነገረው ጊዜ አለቃው ፍርሃት አደረበት።

በጥምቀት በዓል ቀን አለቃው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደ። እዚያም ቅዱስ ባስልዮስን በመቅደሱ ፊት ለፊት ራሱን ዝቅ አድርጎ አየው። ቅዱስ ባስልዮስም ጎሊናውን ከፍ አድርጎ በመቅደሱ ፊት ለፊት ራሱን ዝቅ አድርጎ አየው። ቅዱስ ባስልዮስም ጎሊናውን ከፍ አድርጎ መቆሙና እንዲሁም የቤተ ክርስቲያኑን ሥርዓትና የባስልዮስን አለባበስ በመመልከቱ ታላቅ ስሜት ተሰማው። በዚያን ጊዜ ንጉሡ ልጁ ስለታመመበት ጊዜ አጥቶ ነው እንጂ አርዮሳውያን ባስልዮስን ወደ ግዞት እንዲሰደው ጠይቀውት ነበር። ስለዚህ ንጉሡ ለልጁ እንዲጸይለት ባስልዮስን ለምኖት ከጸለየለት በኋላ ድኖአል። አርዮሳውያን ግን መጥተው ስላጠመቁት ሞተ። በዚህ ጊዜ ንጉሡ በባስልዮስ ላይ በመቈጣት ወደ ግዞት ሊልከው ፈልጎ ውሳኔውን ለመፈረም ሲሞክር ብዕሩ ተሰበረበት። ሦስት ጊዜ ሞክሮ ሦስቱንም ጊዜ ተሰብሮበታል። ከዚያ በኋላ ወረቀቱን ቀድዶ ጣለውና ቅዱስ ባስልዮስ ምእመናኑን እንዲመራና ቤተ ክርስቲያኑን በሰላም እንዲያስተዳድር ተወው።



ቅዱስ ባስልዮስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ [illegible] አል። እግዚአብሔርም በእርሱ እጅ ብዙ ተአምራትን ሠርቶአል።

ቅዱስ ኤፍሬም ከምድር እስከ ሰማይ የደረሰ ዐምድ ካየ በኋላ ያ ያየው ዐምድ ቅዱስ ባስልዮስ መሆኑ ስለተገለጠለት ቅዱስ ባስልዮስን ለመገናኘት ወደ ቂሣርያ ሄዶአል። እዚያም ሄዶ ቅዱስ ባስልዮስ በጣም የከበረ ልብስ ለብሶ ስላየው ይህ ነው ወይ ባስልዮስ ማለት ብሎ ታዘበው። እርሱ ግን ያን ልብስ የለበሰው ስለ ቤተ ክርስቲያን ማዕረግና ስለ ወንጌል ክብር እንጂ ስለ ራሱ ክብር አልነበረም። ቅዱስ ባስልዮስም ለቅዱስ ኤፍሬም የዲቁና ማዕረግ ሰጥቶታል።

አንዲት ሴት ኃጢአትዋን በዝርዝር ጽፋ እንዲጸልይላት ወደ ቅዱስ ባስልዮስ ሄደች። እርሱም በዚያ በቀረበለት የኃጢአት ዝርዝር ላይ ከጸለየላት በኋላ ከአንድ ኃጢአት በቀር በዝርዝር የቀረበው ኃጢአት ሁሉ ተደምስሶላት ተገኘ። እርሱም ለዚያ ለቀረው ለአንዱ ኃጢአት ይጸል ይላት ዘንድ ወደ ቅዱስ ኤፍሬም ላካት። እዚያ ስትደርስ ግን ቅዱስ ባልዮስን ሞቶ አገኘችው። እርስዋም አልቅሳ ጽሑፉን በአስከሬኑ ላይ ብታስቀምጠው ያ የቀረው ኃጢአት ተደመሰሰላት።

በመጨረሻም ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው በ379 ዓ.ም. ነው።

የጥር 6 ቀን ስንክሳርን ይመለከቷል።

## ሥርዓተ በዓል ዘሆሣዕና

### በግዕዝ

ትእ በሠርከ ቀዳሚት ዘውእቱ ዋዜማ ሆሣዕና ይጸልዩ ጸሎተ ሠርክ ከመ ዘዘወትር ወምንባባትስ ነዮሙ ሥሩዓን በግጻዌሁ።

ትእ. ወበሌሊተ እሑድ ዘሆሣዕና በቀዳሚ ያብጽሑ ጸሎተ ነግህ ዘከመ ሥሩዕ በጸሎተ አኰቴት ወማዕጠንት በጊዜ ምንባብ ዘእምብሉይ ኪዳን ያንብቡ አርባዕተ ምንባባት እምብሉይ ኪዳን እለ ሥሩዓን ለበዓሉ ወእምድኅሬሁ ምስባክ ወወንጌል ይትሉ።

ትእ. ወእምድኅረ ንባባተ ወንጌል ይንሣእ ቀሲስ ጸበርተ ወየሀበሙ ለሕዝብ እንዘ ይብል።

ይካ. እንበለ ደዌ ወሕማም እንበለ ፃማ ወድካም አበ ከመ ዮም ያብጽሐኒ ያብጽሕክሙ እግዚአብሔር በፍሥሓ ወበሰላም

ይሕ. አሜን።

ትእ ወሕዝብኒ ይትወከፉ ጸበርተ እምእደ ቀሲስ እንዘ ይብሉ አሜን።

ትእ. ወእምድኅረዝ ይበል ካህን በቅድመ ሕዝብ ዘንተ መዝሙረ ዳዊት ዘ117 ወሕዝብኒ ያውሥኡ እንዘ ይብሉ፤ ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር በከመ ሥሩዕ ዝየ።

መዝሙር፡ (117መዝ፡ 118)።

ይካ:- ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመ ኄር። እስመ ለዓለም ምሕረቱ።

ይሕ:- ቡሩክ ዘይመጽእ በስሜ እግዚአብሔር።

ይካ:- ንግሩ ቤተ እስራኤል ከመ ኄር። ከመ ለዓለም ምሕረቱ።

ይሕ:- ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር።

ይካ:- ንግሩ ቤተ አሮን ከመ ኄር። ከመ ለዓለም ምሕረቱ።

ይሕ:- ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር።

ይካ:- ንግሩ ኵልክሙ እለ ትፈርህዎ ለእግዚአብሔር ከመ ኄር። ከመ ለዓለም ምሕረቱ።

ይሕ:- ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር።

ይካ:- ሶበ ተመንደኩ ጸዋዕክዎ ለእግዚአብሔር። ሰምዐኒ ወአርኀበ ሊተ።
እግዚአብሔር ይረድአኒ ኢይፈርህ እጓለ እመሕያው ምንተ ይሬስየኒ።
እግዚአብሔር ይረድአኒ ወአነ እሬእዮሙ ለጸላእትየ።
ይኄይስ ተአምኖ በእግዚአብሔር እምተአምኖ በእጓለ እመሕያው።
ይኄይስ ተሰፍዎ በእግዚአብሔር እምተሰፍዎ በመላእክት።
ኵሎሙ አሕዛብ ዐገቱኒ። ወበስመ እግዚአብሔር ሞዕክዎሙ።
ዐጊተሰ ዐገቱኒ። ወበስመ እግዚአብሔር ሞዕክዎሙ።
ዖገቱኒ ከመ ንህብ መዓረ። ወነዱ ከመ እሳት ወውስተ አሥዋክ።



www.ethiopianorthodox.org

ወበስመ እግዚአብሔር ሞዕክዎሙ።
ተንተንኩ ለወዲቅ ወእግዚአብሔር አንሥአኒ።
ኃይልየኒ ወዝክርየኒ እግዚአብሔር። ወውእቱ ኮነኒ መድኃንየ።
ቃለ ትፍሥሕት ውስተ አብያቲሆሙ ለጻድቃን።
የማነ እግዚአብሔር ገብረት ኃይለ።
የማነ እግዚአብሔር አልዐለተኒ።
የማነ እግዚአብሔር ገብረት ኃይለ።
ኢይመውት ዘእንበለ ዘአሐዩ። ወእነግር ግብሮ ለእግዚአብሔር
ገሥፆሰ ገሠፀኒ እግዚአብሔር። ወለሞትሰ ባሕቱ ኢመጠወኒ።
አርኅዉ ሊተ አናቅጸ ጽድቅ፤ እባእ ውስቴቶን ወእግነይ ለእግዚአብሔር።
ይሕ.ብሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር።
ይካ. ዛ አንቀጽ እንተ እግዚአብሔር። ጻድቃን ይበውኡ ውስቴታ።
ይሕ. ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር።
ይካ. እገኒ ለከ እግዚኦ እስመ ሰማዕከኒ። ወኮንከኒ መድኃንየ።
ይሕ. ቡሩክ ዘመጽእ በስመ እግዚአብሔር።
ይካ. እብን ዘመነንዋ ነደቅት ወይእቲ ኮነት ውስተ ርእሰ ማዕዘንት።
ይሕ. ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር።
ይካ. እምኀበ እግዚአብሔር ኮነት ዛቲ። ወነካር ይእቲ ለአዕይንቲነ።
ይሕ. ቡሩክ ዘመጽእ በስመ እግዚአብሔር።
ይካ. ዛቲ ዕለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር። ንትፈሣሕ፥ ወንትሐሠ ባቲ።
ይሕ. ቡሩክ ዘመጽአ በስመ እግዚአብሔር።
ይካ. ኦእግዚኦ አድኅንሶ። ኦእግዚኦ ሠርሕሶ።
ይሕ. ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር።
ይካ. ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር። ባረክናክሙ እምቤተ እግዚአብሔር። እግዚአብሔር እግዚእ አስተርአየ ለነ። ግበሩ በዓለ በትፍሥሕት በኀበ እለ ያስተሐምምዎ እስከ አቅርንቲሁ ለምሥዋዕ።
ይሕ. ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር።
ይካ. አምላኪየ አንተ እገኒ ለከ። አምላኪየ አንተ ወአሌዕለከ።
ይሕ. ቡሩክ ዘመጽእ በስመ እግዚአብሔር።
ይካ. እገኒ ለከ እግዚእ እስመ ሰማዕከኒ። ወኮንከኒ መድኃንየ።
ይሕ. ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር።
ይካ. ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመ ኄር። እስመ ለዓለም ምሕረቱ።
ይሕ. ቡሩክ ዘመጽእ በስመ እግዚአብሔር።
ስብሐት፥ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ።
ለዓለም ወለዓለመ ዓለም፤ አሜን።
ትእ. ወእምዝ ይንበሩ ሕዝብ።

ጸሎተ፥ ስምዖን (ሉቃ:2/29/32)

ይእዜ ትስእሮ ለገብርከ። በሰላም እግዚኦ በከመ አዘዝከ።
እስመ ርእያ አዕየንትየ አድኅኖተከ።
ዘአስተዳሎከ ቅድመ ኵሉ ሕዝብከ።
ከመ ትከሥት ብርሃነ ለአሕዛብ።
ወክብረ ለሕዝብከ እስራኤል።
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ።
ለዓለም ወለዓለመ ዓለም አሜን።
ትእ. ወእምዝ. እንዘ ቅውማን ሕዝብ ይሚጥ ካህን ገጾ መንገለ ሕዝብ ወይበል ዘንተ።
ወይትረኀዋ ኖኅት እለ እምፍጥረት።



ይካ. አርኀው ኖኀተ መኳንንት
ወይባእ ንጉሠ ስብሐት።
ይሕ. መኑ ውእቱ ዝንቱ ንጉሠ ስብሐት።
ይካ. እግዚአብሔር አምላከ ኃያላን ውእቱ ዝንቱ ንጉሠ ስብሐት።
ይሕ. ይባእ ንጉሠ ስብሐት። ይባእ አምላከ ምሕረት።
ትእ. ወእምዝ ይንበሩ ሕዝብ ወካህንስ ቀዊሞ ያስምዖሙ ለሕዝብ ቃለ ስብከት ዘበእንተ ፍቅረ ክርስቶስ አው ካልእ ስብከተ ዘይደሉ ለበዓሉ።

## በአማርኛ

## የሆሣዕና በዓል ሥርዓት

ትእ. በሆሣዕና፥ ዜማ ቅዳሜ ማታ የዘወትሩ የማታ ጸሎት ይጸለያል፤ ምንባቦች ግን ለበዓሉ በተለይ የተሠሩት ይነበባሉ።

ትእ. እንደዚሁ ደግሞ እሑድ ሌሊት መጀመሪያ የጧቱ ጸሎት እንደተለመደው ይደረጋል፤ ጸሎተ፥ አኰቴት ካለቀና ማዕጠንት ከተደረገ በኋላ የብሉይ ኪዳን በሚነበብበት ጊዜ ለበዓሉ የተሠሩት 4ቱ የብሉይ ኪዳን ምንባቦች ይነበባሉ። ከዚያም በኋላ ምስባክ ይሰበክና ወንጌል ይከተላል።

ትእ. ወንጌል ከተነበበ በኋላ ቄሱ የሰሌኑን ቅጠል (ዘምባባውን) ይዞ ለሕዝቡ ሁሉ እንዲህ እያለ ይሰጣቸው።

ይካ. ያለ ደዌና ያለ ሕማም ያለ ፃማና ያለ ድካም እግዚአብሔር እንደ ዛሬ ቀን በደስታና በፍቅር በአንድነት ያድርሰኝ ያድርሳችሁ።

ይሕ. አሜን።

ትእ. ሕዝቡም ዘምባባውን ከቄሱ እጅ አሜን እያሉ ይቀበሉ።

ትእ. ከዚያም በኋላ ቄሱ በሕዝቡ ፊት 117ኛውን መዝሙር በከፍተኛው ድምፅ ሲናገር ሕዝቡም እንደሥርዓቱ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው እያሉ ይመልሱለት። (ይህ:መዝሙር የሚባለው በጸሎተ ዘካርያስ ምትክ ገብቶ ነው)።

መዝሙር 117 (መዝ:118)።

ይካ. እግዚአብሔርን አመስግኑ ቸር ነውና ቸርነቱም ለዘለዓለም ነውና።
ይሕ. በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው።
ይካ. የእስራኤል ወገኖች ተናገሩ፤ ቸር እንደሆነ ቸርነቱም ለዘለዓለም እንደሆነ።
ይሕ. በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው።
ይካ. የአሮን ወገኖች ተናገሩ፤ ቸር እንደሆነና ቸርነቱም ለዘለዓለም እንደሆነ ተናገሩ።
ይሕ. በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው።
ይካ. እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሁላችሁ ተናገሩ፤ ቸር እንደሆነ ቸርነቱም ለዘለዓለም እንደሆነ።
ይሕ. በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው።
ይካ. በተጨነቅሁ ጊዜ እግዚአብሔርን ለመንኩት፤ ልመናዬን ሰምቶ ደስታውን አበዛልኝ።
እግዚአብሔር ይረዳኛልና አልፈራም፤ ሰው ምን ያደርገኛል።
እግዚአብሔር ይረዳኛል ጠላቶቼንም ሲጠፉ አያቸዋለሁ።
በሰው ከመታመን በእግዚአብሔር መታመን ይሻላል።
አለቆችን ተስፋ ከማድረግ እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግ ይሻላል።
አሕዛብ ሁሉ ከበቡኝ፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ስም አምኜ ድል አደረግኋቸው።
መክበብስ ከበቡኝ ነገር ግን በእግዚብሔር ስም ድል አደረግኋቸው።
ንብ ማርን እንዲከብ ከበቡኝ፤ እሾህ በእሳት እንዲነድ ነደዱ።
በእግዚአብሔርም ስም ድል አደረግኋቸው።
ለመውደቅ ፍግምግም አልሁ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር አነሣኝ።
ኃይሌም መታሰቢያዬም እግዚአብሔር ነው፤ እርሱም መድኃኒቴ ሆነልኝ።

www.ethiopianorthodox.org

የደስታ ቃል በጻድቃን ቤት ይሰማል።
የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች።
የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገችኝ።
የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች።
እድናለሁ እንጂ አልሞትም፤ የእግዚአብሔርንም ሥራ እናገራለሁ።
እግዚአብሔር መቄጣትስ ተቄጣኝ። ለሞት ግን አሳልፎ አልሰጠኝም።
ወደርሳቸው ገብቼ እግዚአብሔርን አመሰግን ዘንድ የጽድቅን ደጅ ክፈቱልኝ።
ይሕ. በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው።
ይካ. ይህች በር የእግዚአብሔር በር ናት። ጻድቃን ወደርሷ ይገባሉ።
ይሕ. በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው።
ይካ. ልመናዬን ሰምተኸኛልና መድኃኒትም ሆነኸኛልና አቤቱ እገዛልሃለሁ።
ይሕ. በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ብሩክ ነው።
ይካ. አናጾች የናቁት ደንጊያ የማዕዘን ራስ ሆነች።
ይሕ. በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ብሩክ ነው።
ይካ. ይህችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች፤ ለዓይናችንም ድንቅ ናት።
ይሕ. በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው።
ይካ. እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች ናት፥ በርሷም ሐሤት እናድርግ፤ ደስም ይበለን።
ይሕ. በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው።
ይካ. አቤቱ አድነን፤ አቤቱ አቅናልን።
ይሕ. በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው።
ይካ. በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው። ከእግዚአብሔር ቤት ባረከናችሁ።

እግዚአብሔር አምላክ ነው፤ እርሱም አበራልን። የበዓሉን መሥዋዕት እስከ መሠዊያው ቀንዶች ድረስ በአበባ አስጊጡት።

ይሕ. በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው።
ይካ. አምላኬ ነህ አመሰግንሃለሁ። አምላኬ ነህ ከፍ ከፍ አደርግሀለሁ።
ይሕ. በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው።
ይካ. ልመናዬን ሰምተኸኛልና መድኃኒትም ሆንኸኛልና አቤቱ እገዛልሃለሁ።
ይሕ. በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው።
የካ. እግዚአብሔርን አመስግኑ መልካም ነውና፤ ቸርነቱም ለዘለዓለም፥ ነውና፡
ይሕ. በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው።
ምስጋና ይሁን ለአብ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ።
መቼም መች ለዘለዓለሙ፤ አሜን።
ትእ. ከዚህ በኋላ ሕዝቡ ይቀመጡ።

ትእ. ከዚህም ቀጥሎ የዑደት ሥርዓት ይደረጋል፥ በዑደት ጊዜ መጀመሪያ በመቅደስ ውስጥ የጳውሎስ ንባብ ይነበባል። ወዲያው ምስባክ ይከተላል። ቀጥሎም ከአራቱ ወንጌላት እንደ ሥርዓቱ ይነበባል፤ ለያንዳንዱ ወንጌል ምስባክ ተሠርቶለታል። ዳግም በምዕራብና በደቡብ በምሥራቅና በሰሜን በኩል እየተዞረ፥ መጀመሪያ ምስባክ እየተባለ በግጻዌው የተመለከተው ወንጌል ይነበባል፤ ይህንንም በሆሣዕና በዓል የምንባብ ማውጫ ላይ መመልከት ነው (ቍ 224.እይ)።

ስለ ቍርባን የሚነበበውም ከዚያው ይገኛል።

ትእ. በዑደቱ ላይ የሚነበበው ወንጌል ተነብቦ ከተፈጸመ በኋላ ከዚህ በታች የተጻፈውን የስምዖንን ምስጋና ሕዝቡም ቄሱም በአንድነት ይበሉት።

<u>የስምዖን ምስጋና</u> (ሉቃ: 2፥ 29፥ 32)
አቤቱ እንደቃልህ በሰላም ዛሬ አገልጋይህን ታሰናብተዋለህ።
ዓይኖቼ ማዳንህን አይተዋልና።
በሕዝብህ ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን።



ብርሃንን ለአሕዛብ ትገልጽ ዘንድ።
ክብርህንም ለሕዝብህ ለእስራኤል።
ምስጋና ይሁን ለአብ፥ ለወልድ፡ ለመንፈስ ቅዱስ።
መቼም መች ለዘለዓለሙ አሜን።

ትእ. ከዚህ በኋላ ሕዝቡ ይቀመጡ፤ ቄሱ ግን ቆሞ በእሑድ የጧት ጸሎት እንደተሠራው መስተብቍዖችን ይበል፤

ከመስተብቍዖች በኋላ ሕዝቡ ይቁሙና ጸሎተ ሃይማኖትን (አመክንዮ ከቄሱ ጋር በአንድ ድምፅ ይበሉ።

ከዚህ በኋላ ሕዝቡ እንደቆሙ ቄሱ ፊቱን ወደሕዝቡ መልሶ እንዲህ ይበል።
ይካ. ደጆች ራሳችሁን አንሡ።
የዘለዓለም ደጆች ተከፈቱ።
የክብር ንጉሥ ይግባ።
ይሕ. ማነው እርሱ የክብር ንጉሥ።
ይካ. እግዚአብሔር የጭፍሮች አምላክ እርሱ ነው የክብር ንጉሥ።
ይሕ. የክብር ንጉሥ ይግባ፤ የምሕረት አምላክ ይግባ (አሜን)።

ትእ. ከዚህ በኋላ ሕዝቡ ይቀመጡ። ቄሱ ግን በክርስቶስ ፍቅር ስለ መጽናት የሚለውን ስብከት ቆሞ ለሕዝቡ ያሰማቸው። ወይም ለበዓሉ የሚስማማ አጭር ስብከት ያሰማቸው።

ትእ. ከዚያም በኋላ ኑዛዜ ይከተላል። ይህንንም ቍ.35፥ እይ።

ቀጥሎም ቅዳሴ ይከተላል። ከቅዳሴም በኋላ ቄሱ ስለሙታን ጸሎት የሚደግመውን እግዚአ ሕያዋንን ይጸልይ። ቍ.190 እይ።

ቀጥሎም ኑዛዜ አድርጎ ሕዝቡን ያሰናብታቸው።

## <u>ጥያቄዎች</u>

1. በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ማእከል የሚለው ቃል ምን ማለት ነው?
2. የአንድ ቤተ ክርስቲያን ማእከልነት ሲባል ምን ማለት ነው?
3. ጌታችን እንደ ሰውነቱ የጸለየው ስለምን ጉዳይ ነው?
4. ስለ ክርስቲያን አንድነት የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዴት ነበር?
5. በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የቀረቡት ሦስት የማእከልነት ርእሶች ምን ምን ናቸው?
6. ማንም ሰው እንዳሻው ለቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ ሊሰጥ የማይችል ለመሆኑ ከቀረቡት ማስረጃዎች መካከል ቢያንስ ሁለት አቅርብ።
7. ቤተ ክርስቲያን ልጆችዋን መረን ከለቀቀቻቸው ምንን ያስከትላል?
8. ቤተ ክርስቲያን በትልቅ መርከብ በምትመሰልበት ጊዜ ምእመናኑና ዲያቆናቱ በምን ይመሰላሉ?
9. ቅዱስ ባስልዮስ በትምህርቱ የላቀ የሆነው የት በነበረ ጊዜ ነው?
10. ከጓደኛው ከጎርጎርዮስ ጋር የተገናኘው የት ነው?
11. ቅዱስ ባስልዮስ በብሕትውና የኖረው የት ነው?
12. ከጎርጎርዮስ ጋር ምን ለማድረግ ተስማሙ?
13. ቅዱስ ባስልዮስ በምን ዝነኛ ሆነ?
14. ንጉሡ ቅዱስ ባስልዮስን ያላጋዘው በምን ምክንያት ነው?
16. ንጉሡ በቅዱስ ባስልዮስ ላይ ለምን ተቈጣ?
17. ቅዱስ ኤፍሬም ለምን ወደ ቅዱስ ባስልዮስ ሄደ?
18. ቅዱስ ኤፍሬም ለምን ቅዱስ ባስልዮስን ታዘበው?
19. ወደ ቅዱስ ባስልዮስ የኃጢትዋን ዝርዝር ይዛ የሄደችው ሴት ቀሪው አንዱ ኃጢአትዋ የተሠረላት በምን ዐይነት ነው?
20. ቅዱስ ባስልዮስ በስንት ዓመተ ምሕረት ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ?

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ 5

# መንፈሳዊነትና ግብረ ገብነት

## መከራከር አስፈላጊ አለመሆኑ

አንድ ሰው የማያውቀውን ትምህርት ለማስተማር፥ ወይም የተሳሳተውን እምነት ገለጻ በማድረግ ለማስረዳ ካልሆነ በቀር ከሰው ጋር መከራከር ጠቃሚም፥ አስፈላጊም አይደለም። ተቃራኒ አስተሳሰብ አጥብቆ ከያዘ ሰው ጋር መከራከር የራስን አስተሳሰብ ማሰደብ ወይም ማዋረድ ነው።

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ:- «በእግራቸው እንዳይረ ግጡትና ተመልሰው እንዳይነክሱአችሁ የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ፤ ዕንቋችሁንም በዕያሪዎች ፊት አትጣሉ» ማለቱ፥ ተቀባይነት በማይኖረው ወይም ተገቢው ክብር በማይሰጠው ቦታ የእግዚአብሔርን ቃል ለማቅረብ አትሞክሩ ማለቱ ነው (ማቴ: ም:7 ቍ:6)።

በመጽሐፈ ምሳሌ የቀረቡ ተመሳሳይ አባባሎች የሚከተሉት ናቸው:-

«ትዕቢተኛን ሰው ብታርመው ስድብን ታተርፋለህ፤ ክፉውን ሰው ብትገ ሥጸው ጉዳት ይደርስብሃል፤ ጠቢብ ሰው ብታርመው ግን ይወድድሃል» (ምሳ:9፥ 7–8)።

«ጥበብ የሞላበትን ምክርህን ስለሚንቅብህ ለሞኝ ሰው ቁም ነገር አታጫውተው» (ምሳ: ም:23 ቍ:9)።

በእነዚህ ከላይ በቀረቡት ጥቅሶች መሠረት አስፈላጊ አለመሆኑ የተገለጠው መከራከር ብቻ ሳይሆን በሚቀርብለት ሰው ዘንድ ተቀባይነት የሌለው መሆኑ እስከታወቀ ድረስ ትምህርትን፥ ምክርንና ተግሣጽን ማቅረብ ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚያመዝን ተመልክቶአል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች ሁሉም በየኩላቸው ተቃራኒ አስተሳሰቦች ካሉአቸውና ሁሉም በአስተሳሰባቸው የጸኑ ከሆኑ እያንዳንዱ ወገን አስተሳሰቡን በሌላው ወገን ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ አስቦ ክርክር ማድረግ የለበትም። በዚህ ዐይነት ክርክር ለማድረጊ የሚነሡ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ የራሳቸውን አስተሳሰብ ከፍ ከፍ በማድረግ የሌላውን አስተሳሰብ ማጣጣል ይቃጣቸዋል። በዚህ ጊዜ አስተሳሰቡ የተናቀበት ሰው ደግሞ የቁጭት ስሜት ይሰማዋል፤ ለአስተሳሰቡ መከላከል ይፈልጋል፤ የራሱ አስተሳሰብ እንደተናቀ እርሱም በበኩሉ የንቀት ወይም የስድብ ቃላትን ለመሰንዘር የበቀል ፍላጎት ያድርበታል። ከዚያ በኋላ ሁሉም በየበኩላቸው የማያስደስቱ ቃላትን መወራወር ይጀምራሉ። ያ ሁናቴ ደግሞ ጉዳት እንጂ ጠቀሜታ የለውም። ስለዚህ በማንኛውም ጊዜ ከክርክር መራቅና በሰላም መኖር እንጂ ክርክርን እየተጋፈጡ ችግር ላይ መውደቅ አስፈላጊ አይደለም።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ክርክርን በተመለከተ ያቃረባቸውን ምክሮች ቀጥለን እንመልከት:-

«ወንድሞቼ ሆይ፥ እኔ ያስተማርኋችሁ ሥጋውያንና በክርስቶስ ገና ያልጠ ነከራችሁ ሕፃናት እንደመሆናችሁ መጠን ነው እንጂ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ መጠን አይደለም። ጠንካራ ምግብ መብላት የማትችሉ ስለሆናችሁ እኔ የመገብኋችሁ ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም፤ አሁንም ቢሆን ጠንካራ ምግብ መመገብ ገና የማትችሉ ናችሁ። እናንተ አሁንም ገና ሥጋውያን ናችሁ፤ እርስ በርሳችሁ ስለምትቀናኑና ስለምትከራከሩ ሥጋው ያን መሆናችሁ አይደለምን? የምትሠሩትስ እንደ ተራ ሰው አይደለምን?» (1ኛ:ቆሮ:ም:3 ቍ:1–3)።

«ከእውነተኛ የሃይማኖት ትምህርት ጋር ተስማሚ የሆነውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ንጹሕ ቃል ትቶ የተለየ ትምህርት የሚያስተምር ማንም ሰው ቢኖር በትዕቢት የተወጠረና ምንም የማያውቅ ነው፤ ነገር ግን ስለ ቃላት የመከራከርና የመጨቃጨቅ ክፉ ምኞት አድሮበታል፤ ይህም የሚያስከትለው ቅንአትን፥ ጠብን፥ ስድብን፥ መጥፎ ጥርጣሬን፥ አእምሮአቸው በረከሰና እው ነት በጠፋባቸው ሰዎች የሚደረግ የማያቋርጥ ክርክርን ነው፤ እንደነዚህ ያሉት ሰዎች ሃይማኖት የሀብት ማግኛ ዘዴ መስሎ ይታያቸዋል» (1ኛ:ጢሞ:ም:6 ቍ:3–5)።



«ነገር ግን ከማይረባ ክርክር፥ ከትውልድ ቈጠራ ከጭቅጭቅ፥ በኦሪት ሕግ ምክንያት ከሚነሣው ጠብ ራቅ፤ እነዚህ ነገሮች ጥቅም የሌላቸውና ዋጋቢ ሶች ናቸው» (ቲቶ:ም:3 ቍ:9)።

ከላይ በሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የቀረቡት ጥቅሶች እንዳመለከቱት ክርክሮች ምን ያኽል መንፈሳዊ ሕይወትን እንደሚጐዱ ተገልጦአል። ክርክ ሮች ደግሞ በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ ብቻ ሳይሆን በዓለማዊ ሕወትም ቢሆን ብዙ ችግሮችን ያስከትላሉ። በክርክር ምክንያት ጠብ ሊነሣ ይችላል፤ ጠቡም ሌላውን ወገን እስከ መጐዳትና በራስም በኩል እስከ መጐዳት፥ እንዲያውም እስከ መገዳደልም ሊያደርስ ይችላል።

ስለዚህ እነዚህ ከላይ የተገለጡት ችግሮች እንዳይደርሱ ከክርክር መራቅ አስፈላጊ ነው።

## ምንም ያኽል ደግነት ያለን ቢመስለን መኵራራት የለብንም

መኵራራት የለብንም ማለት በቂ እምነት ስላለንና በተግባራችንም ፍጹሞች ስለሆንን በመንገሥተ ሰማያት ከፍተኛውን ቦታ እንደምናገኝ እርግጠኞች ነን ብለን አንኵራራ ማለት ነው።

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱና ለሕዝቡ ባቀረባቸው ትምህርቶች ብዙውን ጊዜ ስለትሕትና አስፈላጊነት ይገልጥ ነበር። ከእነዚህም የትሕትናን አስፈላጊነትና የመኵራራትን ጐጂነት ከገለጠባቸው ትምህርቶቹ መካከል የሚከተሉት ሁለት ምሳሌዎች ቀርበዋል።

«ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ፥ ከእናንተ አንዱ በእርሻ ሥራ የተሰማራ ወይም በጎች የሚጠብቅ አገልጋይ ቢኖረው፥ አገልጋዩ ከሥራው በተመለሰ ጊዜ ወዲያውኑ ‹ና ተቀመጥና ራትህን ብላ› ይለዋልን? ይልቅስ፥ ‹ብል ራቴን አዘጋጅልኝ፥ እስክበላና እስከጠጣም አደግድገህ አገልግለኝ፤ ከዚህ በኋላ አንተ ደግሞ ትመገባለህ› ይለው የለምን? ታዲያ አገልጋዩ የታዘዘውን ስለፈጸመ ጌታው የሚያመሰግነው ይመስላችኋልን? እናንተም እንዲሁ የታዘዛችሁትን ሁሉ ከፈጸማችሁ በኋላ ‹የማንጠቅም አገልጋዮች ነን፤ የፈጸምነውም ግዳጃችንን ብቻ ነው› በሉ» (ሉቃ:ም:17 ቍ:7–10)።

ቀጥሎም ኢየሱስ ጻድቃን ነን እያሉ ለሚመኩና ሌሎችንም ለሚንቁ ሰዎች ይህን ምሳሌ ተናገረ:- «ሁለት ሰዎች ለመጸለይ ወደ ቤተ መቅደስ ሄዱ፥ አንዱ ፈሪሳዊ ሲሆን ሌላው ቀራጭ ነበር።

«ፈሪሳዊው ቆሞ እንዲህ ሲል በልቡ ጸለየ፤ ‹እግዚአብሔር ሆይ፥ እኔ እንደ ሌሎች ሰዎች ቀማኛ፥ ዐመፀኛ፥ አመንዝራ ስላልሆንኩ አመሰግንሃለሁ፥ ይልቁንም እንደዚህ እንደ ቀራጭ ስላልሆንኩ አመሰግንሃለሁ። እኔ በሳምንት ሁለት ቀን እጾማለሁ፤ ከማገኘው ሁሉ ዐሥራት እያወጣሁ እሰጣለሁ።» «ቀራጩ ግን በሩቅ ቆመና፥ ቀና ብሎ ወደ ሰማይ ለማየት እንኳ አልደፈረም፤ ነገር ግን በእጁ ደረቱን እየመታ፥ ‹አምላክ ሆይ፥ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ› ይል ነበር። ጽድቅን አግኝቶ ወደ ቤቱ የተመለሰው ይህ ቀራጭ ነው እንጂ ፈሪሳዊው አይደለም እላችኋለሁ። ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ዝቅ ይላል፤ ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ግን ከፍ ይላል» (ሉቃ:ም:18 ቍ:9–14)።

እንግዲህ አሁን ትክ ብለን ብናስተውል እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ዋና ነገር እኛ የፈጸምነው በጎ ተግባር ግዳጃችን ከመሆኑ በቀር ለእግዚአብሔር ውለታ እንደከፈልንና ለዚያ ውለታ ምላሽ ከእግዚአብሔር የምንጠብቀው ነገር እንዳለ አድርገን ማሰብ የሌለብን መሆኑን እንድናውቅ ነው።

በሌላ በኵል ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍት በግልጥ እንዳመለከቱት በእግዚ አብሔር ምሕረትና አዳኝነት ካልሆነ በቀር ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ መሆኑን ከሚገ ልጹት የቅዱሳት መጻሕፈት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

«ሰው ንጹሕ ሊሆን ይችላልን? ሥጋ ለባሽስ ጻድቅ ሊሆን ይችላልን? እግዚአብሔር በመላእክቱ እንኳ አይተማመንም፤ ሰማያትም በእርሱ ፊት ንጹ ሓን አይደሉም፤ የተበላሸውና የረከሰው፥ ኃጢአትንም እንደ ውሃ የሚጠጣ ሰውማ ምንኛ ያነሰ ነው?» (ኢዮ:ም:15 ቍ:14–16)።

«እንዴት ሰው በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆኖ ሊገኝ ይችላል? ሰብአዊ ፍጡር ሆኖ እንዴት ንጹሕ ሊሆን ይችላል? እነሆ፥ በእግዚአብሔር ፊት ጨረቃ እንኳ ደማቅ አይደለችም፤

www.ethiopianorthodox.org

ከዋክብትም በእርሱ ፊት ንጹሐች አይደ ሉም፤ በስባሽና ትል የሆነው ሟች ሰውማ ምንኛ ያነሰ ነው?» (ኢዮ:ም:25 ቍ:4–6)።

«እግዚአብሔር የለም የሚል ሞኝ ብቻ ነው፤ እንደነዚህ ያሉት ሰዎች ዋጋ ቢሶችና ርኅራኄ የሌለቸው ጨካኞች ናቸው። በጎ ነገርን ከቶ አያደርጉም። በጥበብ የሚሠሩና እግዚአብሔርን የሚፈልጉ እንዳሉ ያይ ዘንድ እግዚአብሔር ከሰማይ ወደ ሰው ዘር ሁሉ ተመለከተ። ነገር ግን ሁሉም ባዝነዋል፤ ሁሉም በአንድነት ተበላሽተዋል፤ አንድም እንኳ መልካም ነገር የሚያደርግ የለም» (መዝ:14 ቍ:1–3)።

«ከተፀነስኩበት ጊዜ ጀምሮ ኃጢአተኛ ነኝ፤ ከተወለድኩበት ጊዜ ጀምሮ በደለኛ ነኝ» (መዝ:51 ቍ:5)።

«ከሰው ባሕርይ ደካማነት የተነሣ ሕግ ሊያደርገው ያልቻለውን እግዚ አብሔር አድርጎታል። የገዛ ልጁንም በኃጢአት ምሳሌነት የኃጢአት መሥ ዋዕት ባደረገው በዚሁ በልጁ ሥጋ ኃጢአትን በፍርድ አስወገደ» (ሮሜ:ም:8 ቍ:3)።

«በአንድ ሰው ምክንያት ኀጢአት ወደ ዓለም ገባ፤ በኀጢአት ምክንያትም ሞት መጣ። የአንዱ የአዳም ኃጢአት የቅጣትን ፍርድ በሰው ሁሉ ላይ እንዳ መጣ፤ እንዲሁም የአንዱ የክርስቶስ የጽድቅ ሥራ ብዙዎችን ከቅጣት ነጻ አድርጎ ሕይወትን ይሰጣል» (ሮሜ: ም5 ቍ:12 እና 18)።

«ኀጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናታልላለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም» (1ኛ ዮሐ: ም.1 ቍ8)።

ታዲያ፥ ከላይ በተዘረዘሩት የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች መሠረት የሰው ኃጢአተኛነት የተረጋገጠ ከሆነ እኛ ጻድቃን ነን ብለን በሙሉ ልብ መናገር ከምን ያገኘነው ነው?

ስለዚህ የእግዚአብሔርን አዳኝነት፥ ማለት የክርስቶስን ቤዛነት እያመ ሰገንን ስለ ኃጢአታችን ይቅርታ እንለምን እንጂ ለጽድቅ የሚያበቃ እምነትና ተግባር አለን በማለት በራሳችን አንመካ።

## ጥያቄዎች

1. ተቃራኒ አስተሳሰብ ካለው ሰው ጋር መከራከር ምን ችግር ያመጣል?
2. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ በሚልበት ጊዜ ምን ማለቱ ነው?
3. የሌላውን አስተሳሰብ የሚያጣጥል ሰው ምን ይደርስበታል?
4. ክርክሮች በዓለማዊ ሕይወት ላይ ምን ዐይነት ችግሮችን ያስከትላሉ?
5. ክርክሮች እስከምን ድረስ ሊያደርሱ ይችላሉ?
6. ጻድቃን ነን ብለን መኵራራት የሌለብን በምን ምክንያት ነው?
7. መኵራራት የሌለብን መሆኑን ለማመልከት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያቀረባቸውን ሁለት ምሳሌዎች ተናገር።
8. በሁለቱ ምሳሌዎች አማካይነት እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ምን እንደሆነ ግለጥ።



## መክሥተ አርእስት

## በፊደል ተራ ቅደም ተከተል

ሀብታሙ ወጣት፥ መጽ:1፥ ገጽ 309
ሁሉም እንዲድን የአምላክ ፈቃድ መሆኑ፥ መጽ:1፥ ገጽ 118
ሄሮድስ ሕፃናትን ማስፈጀቱ፥ መጽ:1፥ ገጽ 66
ለወላጆች ታዛገሮች የነበሩ ልጆች፥ መጽ:1፥ ገጽ፥ 108
ለወደፊት የሚወረስ የሰማያዊ ርስት ተስፋ መጽ 1፥ ገጽ 115
ሊቀ መላእክት፥ መጽ:1፥ ገጽ 24
ልደት፥ (የጌታችን)፥ መጽ:1፥ ገጽ 61
ሐሜት፥ መጽ:3፥ ገጽ: 63
ሐናንያና ሰጲራ፥ መጽ:1፥ ገጽ 145
ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን፥ መጽ:1፥ ገጽ 168
ሕጎች (የእግዚአብሔር)፥ መጽ:2፥ ገጽ 91
ሕፃናት መባረካቸው፥ መጽ:3፥ ገጽ 90
መላእክት፥ መጽ:1፥ ገጽ 22
መለኮታዊ መጠሪያ መጽ:3፥ ገጽ 179
መልስ የሚያገኝና የማያገኝ ጸሎት፥ መጽ:1፥ ገጽ 105
መልእክተኞች (ከመጥምቁ ዮሐንስ)፥ መጽ:2፥ ገጽ 304
መልእክተ ዮሐንስ (1ኛ)፥ መጽ:3፥ ገጽ 136
መልእክተ ዮሐንስ (2ኛ)፥ መጽ:3፥ ገጽ 136
መልእክተ ዮሐንስ (3ኛ)፥ ገጽ 136
መልእክተ ጴጥሮስ (1ኛ)፥ መጽ:3፥ ገጽ 134
መልእክተ ጴጥሮስ (2ኛ)፥ መጽ:3፥ ገጽ 135
መልከጼዴቅ፥ መጽ:1፥ ገጽ 41፥ መጽ:2 ገጽ 271
መማል ሳይሆን እውነትን መናገር መጽ:3 ገጽ 116
መሞከር፥ መጽ:2፥ ገጽ 156
መሥዋዕት:- የሚቃጠል፥ መጽ:2፥ ገጽ 112
የእህል መባ፥ መጽ:2፥ ገጽ 113
የደኅንነት፥ መጽ:2፥ ገጽ 112
ባለማወቅ ስለተፈጸመ በደል፥ መጽ:2፥ ገጽ 112
ስለ ኃጢአት ስርየት፥ መጽ:2፥ ገጽ 114
መስማማትና አለመስማማት... መጽ:2፥ ገጽ 252
መሶበ ወርቅ መጽ:1፥ ገጽ 172
መቅሠፍት (በግብጽ ላይ የወረደ)፥ መጽ:2፥ ገጽ 29
መባረክ፥ መጽ:2፥ ገጽ 324
መብትንና ግዴታን ጠንቅቆ ማወቅ፥ መጽ:3፥ ገጽ 115
መንግሥት (የእግዚአብሔር)፥ መጽ:1፥ ገጽ 113
መንፈሳዊ ስጦታዎች፥ መጽ:2፥ ገጽ 11
መንፈሳዊነት፥ መጽ:1፥ ገጽ 100
መከራከር አስፈላጊ አለመሆኑ፥ መጽ:3፥ ገጽ 233

www.ethiopianorthodox.org

መኰራረት፥ መጽ:3፥ገጽ 234
መዘምራን፥ መጽ:2፥ገጽ 138
መገለጥ (የጌታ)፥ መጽ:3፥ገጽ 218
መገረዝ የቃል ኪዳን ምልክት መጽ:1፥ ገጽ 42
መጽሐፈ መሳፍንት፥ መጽ:2፥ገጽ 285
መጽሐፈ መቃብያን፥ መጽ:3፥ገጽ 206
መጽሐፈ ሩት፥ መጽ:1፥ገጽ 217
መጽሐፈ ሳሙኤል (ቀዳማዊ)፥ መጽ:3፥ገጽ 30
መጽሐፈ: ሳሙኤል (ካልዕ)፥ መጽ:3፥ገጽ 32
መጽሐፈ ነገሥት (ቀዳማዊ፥ መጽ:3፥ገጽ 33
መጽሐፈ: ነገሥት (ካልዕ)፥ መጽ:3፥ ገጽ 35
መጽሐፈ: አስቴር፥ መጽ:2፥ ገጽ 199
መጽሐፈ: ኢያሱ ወልደ ነዌ፥ መጽ:2፥ ገጽ
መጽሐፈ ዕዝራ፥ መጽ:2፥ ገጽ 34
መጽሐፈ : ዮዲት፥ መጽ:2፥ ገጽ 203
መፈተን (የጌታችን)፥ መጽ:1፥ገጽ 70
መፍጠር ከምንም መጽ:1፥ገጽ 19
ሙሴ ( ነቢዩ)፥ ልደቱ፥ መጽ:1፥ ገጽ 288
ሽሽቱ፥ መጽ:1፥ገጽ 290
ጥሪው፥ መጽ:1፥ ገጽ 292
ሙከራ (ክፉ ነገርን) መጽ:2፥ ገጽ 156
ማመስገን፥ (እግዚአብሔርን)፥ መጽ:1፥ገጽ 189
ማማተብና ትርጉሙ፥ መጽ:1፥ገጽ 87
ማስታረቅ፥ (የተጣሉትን) መጽ:2፥ ገጽ 324
ማስታወሻ (የኢትዮጵያና የግብጽ ቤ/ክ ግንኙት፥ መጽ:2፥ ገጽ 63
ማቴዎስ (መጠራቱ)፥ መጽ:1፥ገጽ 238 (ታሪኩ) መጽ:1፥ገጽ 255
ማኅፈድ መጽ:1፥ገጽ 173
ማዕከልነት (የቤተ ክርስቲያን)፥ መጽ:3፥ገጽ 223
ማጽናናት (ያዘኑትን)፥ መጽ:2፥ ገጽ 137
ምሥጢረ ተዋሕዶ፥ መጽ:2፥ገጽ 185
ምሥጢረ ሥጋዌ፥ መጽ:1፥ ገጽ 200
ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፥ መጽ:1፥ገጽ 322
ምሳሌ መሆን (ለትክክለኛ ኑሮ)፥ መጽ:1፥ ገጽ 268
ምሳሌዎች (የጌታችን)
የዘሪው፥ መጽ:1: ገጽ 77
በአለት ወይም በአሸዋ ላይ የተሠሩ ቤቶች፥ መጽ:1፥ ገጽ 77
ጠፍቶ የተገኘው ልጅ፥ መጽ:1፥ ገጽ 78
የተሸሸገ ሀብት፥ መጽ:1፥ ገጽ 162
የዕንቍ ምሳሌ፥ መጽ:1፥ ገጽ 162
የሕይወት እንጀራነት፥ መጽ:1፥ ገጽ 162
ደጉና ክፉው አገልጋይ፥ መጽ:1፥ ገጽ



ክፉ አገልጋይ፥ መጽ:1፥ ገጽ 242
የሠራተኞች አቀጣጠር፥ መጽ1፥ ገጽ 313
የሁለት ልጆች ምሳሌ፥ መጽ:1፥ ገጽ 314
የአገልጋዮች ትጋት፥ መጽ:1፥ ገጽ 314
የወይኑ አትክልት ገበሬዎች፥ መጽ:2፥ ገጽ 49
የዐሥሩ ልጃገረዶች ምሳሌ፥ መጽ:2፥ ገጽ 50
የሚያድግ ዘር፥ መጽ: 2፥ ገጽ 128
ስውር መብራት፥ መጽ: 2፥ ገጽ 128
ትዕቢተኛው ፈሪሳዊና ትሑቱ ቀራጭ፥ መጽ: 2፥ ገጽ 226
የሀብታሙ ሰው ሞኝነት፥ መጽ: 2፥ ገጽ 227
ሀብታሙ ሰውና ድኻው አልዓዛር፥ መጽ: 2፥ ገጽ 306
ጠፍቶ የተገኘው ልጅ፥ መጽ: 2፥ ገጽ 307
የብልጉ መጋቢ ምሳሌ፥ መጽ: 2፥ ገጽ 307
የማታፈራ በለስ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 43
የአገልጋይ ግዳጅ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 44
የደጉ ሳምራዊ ምሳሌ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 44
የበለስ ዛፍ ምሳሌ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 91
የሠርጉ ግብዣ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 91
የሦስቱ አገልጋዮች፥ መጽ: 3፥ ገጽ 92
ድኻዋ መበለትና ዐመፀኛው ዳኛ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 146
መልካም እረኛነቱ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 146
የነቢዩ ዮናስ ምሳሌነት፥ መጽ: 3፥ ገጽ 221
የቤተ መቅደስ መፍረስና መሠራት፥ መጽ:3፥ ገጽ: 221
የሙሴ የነሐስ እባብ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 221
የመረብ ምሳሌ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 117
የእንክርዳድ ምሳሌ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 117
የሰናፍጭ ዘር ምሳሌ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 117
የእርሾ ምሳሌ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 118
ምንጮች (የመንፈሳዊነትና የግብረገብነት) መጽ: 2 ገጽ 157
ምእመናን (የቤተ ክርስቲያን)፥ መጽ: 2፥ ገጽ 320፥ 326
ሞት (የጌታ) ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 145
ሥርዓት (የቤተ ክርስቲያን) መጽ: 1፥ ገጽ 170
ሥነ ሥርዓት (የአጽዋማት) መጽ: 1፥ ገጽ 124
ሥነ ፍጥረት መጽ: 1፥ ገጽ 21
ራስን ሳይሆን ሌላውን ሰው ማመስገን፥ መጽ: 1፥ ገጽ 193
ራስን መግታት፥ መጽ: 2፥ ገጽ 152
ራስ ወዳድነት፥ መጽ 3፥ ገጽ 62
ራእየ ዮሐንስ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 209
ርኅራኄ መጽ: 3፥ ገጽ 7
ርኩስ መ□ንፈስ ያደረበት ሰው መፈወስ መጽ: 3፥ ገጽ 43
ሰማርያ[illegible] መጽ:1፥ ገጽ 157

www.ethiopianorthodox.org

ሰቆቅወ ኤርምያስ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 80
ሰባቱ አብያተ ክርስቲያን፥ መጽ: 3፥ ገጽ 156
ሰባው ደቀ መዛሙርት፥ መጽ: 2፥ ገጽ 46
ሰብአ ሰገል፥ መጽ: 1፥ ገጽ 65
ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ስለሆነ ጸሎት ያስፈልገዋል። መጽ: 1፥ ገጽ 104
ሰውን እንደሰውነቱ ማየት፥ መጽ: 3፥ ገጽ 170
ሰይጣን፥ መጽ: 1፥ ገጽ 26
ሰዱቃውያን መጽ: 3 ገጽ 158
ሰጪ ከተቀባይ ይልቅ፥ መጽ: 2፥ ገጽ 88
ሳውል በደማስቆና በኢየሩሳሌም፥ መጽ: 1፥ ገጽ 297
ስለሚደርስበት ሕማምና ሞት መናገሩ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 141
ስሕተትን አምኖ ይቅርታ መጠየቅ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 186
ስቅለት (የጌታ)፥ መጽ: 3፥ ገጽ 144
ስዕሎችና አይቆኖች፥ መጽ: 1፥ ገጽ 252
ስደት በቤተ ክርስቲያን፥ መጽ: 2፥ ገጽ 39
ስጦታ (የእግዚአብሔር)፥ መጽ: 2፥ ገጽ 11
ሶስና፥ መጽ:1፥ ገጽ 215
ሺህ ዓመት፥ መጽ: 2፥ ገጽ 21
ሽማግሌዎች መጽ: 3 ገጽ 159
ሽሽት (ወደ ግብጽ)፥ መጽ: 1፥ ገጽ 66
ሽቶ የቀባችው ሴት (ጌታችንን) መጽ: 3፥ ገጽ 43
ቀሳውስት፥ መጽ: 2፥ ገጽ 137
ቀብር (የጌታ)፥ መጽ: 3፥ ገጽ 216
ቅዳሜ ስዑር መጽ:3 ገጽ 18
ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 109
ቅጣቶች (የእግዚአብሔር)፥ መጽ: 2፥ ገጽ 257
ቍጣ፥ መጽ: 2፥ ገጽ 93፥ 156
በማመንዘር የተያዘች ሴት፥ መጽ: 1፥ ገጽ 309
በምሥጢረ ሥጋዌ ላይ የተነሡ መናፍቃን፥ መጽ:1፥ ገጽ 205
በረከት፥ መጽ: 2፥ ገጽ 324
በቤተ መቅደስ የሚገበያዩ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 43
በታላቅ ክብር ወደ ኢየሩሳሌም፥ መጽ: 3፥ ገጽ 42
በእውነት መጽናት፥ መጽ: 1፥ ገጽ 345
በጊዜ የማይወሰነው የእግዚአብሔር ዕውቀትና ነጻ ፈቃድ፥ መጽ:1፥ ገጽ 121
በጌታ ግራና ቀኝ የተሰቀሉት፥ መጽ: 3፥ ገጽ 14
በጎ አድራጊዎችን ማመስገን፥ መጽ: 1፥ ገጽ 267
ቢላግዮስ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 206
ቤልና ዘንዶው፥ መጽ: 3፥ ገጽ 173
ቤተ ክርስቲያንና ሲኖዶሶችዋ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 100
ኒቅያ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 100
ቍስጥንጥንያ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 104



ኤፌሶን፥ መጽ: 3፥ ገጽ 106
ብሥራት፥ መጽ: 1፥ ገጽ 60
ተመልሶ የሚመጣው አንድ ጊዜ ብቻ ነው፥ መጽ: 2፥ ገጽ 26
ተረፈ ዳንኤል፥ መጽ: 3፥ ገጽ 133
ተስፋ መቍረጥ፥ መጽ: 2፥ ገጽ 252
ተቃውሞ (በናዝሬት)፥ መጽ: 1፥ ገጽ 238
ተአምራት (የጌታችን)
ውሃን ወደ ወይን መለወጥ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 73
የብዙ ዓሣዎች መገኘት፥ መጽ: 1፥ ገጽ 74
አምስት ሺህ ሰዎችን መመገቡ፥ መጽ1፥ ገጽ 75
ማዕበሉን ጸጥ ማድረግ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 76
የመቶ አለቃው አገልጋይ መፈወስ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 160
ስምዖን ዐማትና የሌሎች መፈወስ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 161
በአጋንንት የተያዙ ሁለት ሰዎች፥ መጽ፥ 1፥ገጽ161፥312
የጌታችንን ልብስ የነካች ሴት፥ መጽ: 1፥ ገጽ 239
የኢያኢሮስ ልጅ ከሞት መነሣት፥ መጽ:1፥ ገጽ 240
የሽባው መፈወስ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 50
የከነዓናዊትዋ ልጅ መፈወስ፥ መጽ:1፥ ገጽ 309
በባሕር ላይ የመራመድ ተአምር፥ መጽ: 1፥ ገጽ 312
ጋኔን ያደረበት ልጅ መፈወስ፥ መጽ: 2፥ ገጽ 47
አራት ሺህ ሰዎችን መመገቡ፥ መጽ: 2፥ ገጽ 48
ደንቆሮና ድዳ የነበረው ሰው፥ መጽ: 2፥ ገጽ 48
የዐሥር ለምጻሞች መፈወስ፥ መጽ: 2፥ ገጽ 126
የአልዓዛር ከሞት መነሣት፥ መጽ: ፥ ገጽ 126
የሹሙ ልጅ መፈወስ፥ መጽ: 2፥ ገጽ 127
የመበለቲቱን ልጅ ከሞት ማስነሣት፥ መጽ: 2፥ ገጽ 224
የሽባው መፈወስ፥ መጽ: 2፥ ገጽ 225
የሁለቱ ዕውሮች መፈወስ፥ መጽ: 2፥ ገጽ 226
ዕውርና ድዳ የነበረው ሰው፥ መጽ: 2፥ ገጽ 226
የአንዲት ጐባጣ ሴት መፈወስ፥ መጽ: 2፥ ገጽ 304
ዕውር ሆኖ የተወለደው ሰው፥ መጽ: 2፥ ገጽ 305
ያለ ፍሬ የተገኘ የበለስ ዛፍ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 43
ርኩስ መንፈስ ያደረበት ሰው፥ መጽ: 3፥ ገጽ 43
የአንድ ዕውር መፈወስ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 91
የአንድ ድዳ መፈወስ፥ መጽ:3፥ ገጽ 91
የአንድ ለመጻም መፈወስ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 91
ከዓሣ ሆድ ውስጥ ገንዘብ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 91
የቤተሳይዳው ሽባ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 145
ወታደሮች ወደ ኋላ መውደቃቸው፥ መጽ: 3፥ ገጽ 146
የማልኮስ ጆሮ መፈወስ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 146
በተዘጋ ቤት ውስጥ የመግባት ተአምር፥ መጽ: 3፥ ገጽ 290

www.ethiopianorthodox.org

የመሰወሩ ተአምር፡ መጽ: 3፡ ገጽ 221
ተገቢ በሆነ መንገድ በችሎታ መጠቀም፡ መጽ: 3፡ ገጽ 169
ተጽዕኖ (ጠቃሚ ያልሆነ) መጽ: 2፡ ገጽ 343
ትንሣኤ (የሙታን)፡ መጽ: 2፡ ገጽ 14
ትንሣኤ (የጌታችን) ፡ መጽ መጽ: 3፡ ገጽ 216
ትንቢተ ሆሴዕ፡ መጽ: 3፡ ገጽ 129
ትንቢተ ሐጌ፡ መጽ: 3፡ ገጽ 204
ትንቢተ ሕዝቅኤል፡ መጽ: 3፡ ገጽ 127
ትንቢተ ሚልክያስ፡ መጽ: 3፡ ገጽ 205
ትንቢተ ሚክያስ፡ መጽ: 3፡ ገጽ 133
ትንቢተ ሰፎንያስ፡ መጽ: 3፡ገጽ 203
ትንቢተ ናሆም፡ መጽ: 3፡ ገጽ 201
ትንቢተ አሞጽ፡ መጽ: 3፡ ገጽ 231
ትንቢተ አብድዩ፡ መጽ: 3፡ ገጽ 132
ትንቢተ ኢሳይያስ፡ መጽ: 3፡ ገጽ 77
ትንቢተ ዘካርያስ፡ መጽ: 3፡ ገጽ 204
ትንቢተ ኤርምያስ፡ መጽ: 3፡ ገጽ 79
ትንቢተ ዕንባቆም፡ መጽ: 3፡ ገጽ 202
ትንቢተ ኢዩኤል፡ መጽ 3፡ ገጽ 131
ትውፊት፡ መጽ: 2፡ ገጽ 95
ትዕቢት፡ መጽ: 2፡ ገጽ 155
ችግረኞችን መርዳት፡ መጽ፡ 2፡ ገጽ 238
ችግር (በቅዱስ ጳውሎስ ላይ)፡ መጽ: 2፡ ገጽ 288
ኀላፊነት (የቤተ ክርስቲያን) ፡ መጽ: 2፡ ገጽ 235
ኃጢአተኛ ( ሰው ሁሉ) ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 104
ነገረ ማርያም፡ መጽ: 2: ገጽ 99
ነጻነትን በአግባቡ መጠቀም፡ መጽ: 3፡ ገጽ 114
ነጻ ፈቃድ (የሰው ልጅ)፡ መጽ: 1፡ ገጽ 118
ነጻ ፈቃድ (የመላእክት)፡ መጽ:1፡ ገጽ 23
ነጻ ፈቃድና የእግዚአብሔር ውሳኔ አለመለወጥ፡ መጽ:1፡ ገጽ 120
ነፍስ፡ መጽ: 2፡ ገጽ 16
ንስሐ መግባት፡ መጽ: 1፡ ገጽ 342
ንዋያተ ቅድሳት፡ መጽ: 1፡ ገጽ 171
ኖኅና የጥፋት ውሃ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 36
አለመለወጥ (የእግዚአብሔር ውሳኔ)፡ መጽ:1፡ ገጽ 102
አሉባልታ፡ መጽ:2፡ ገጽ 86
አልባሳት፡ መጽ:1፡ ገጽ 173
አማላጅነት፡ መጽ:1፡ ገጽ 278
አሥርቶት፡ መጽ: 3፡ ገጽ 22
አራቱ የቤተ ክርስቲያን መጠሪያዎች፡ መጽ: 2፡ ገጽ
አቡሊናርዮስ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 205



አባታችን ሆይ፡ መጽ:1፡ ገጽ 106
አባትንና እናትን ማክበር፡ መጽ: 1፡ ገጽ 108
አብርሃም፡ (መጠራቱ)፡ መጽ: 1፡ ገጽ 39
መፈተኑ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 44
እንግዶችን መቀበሉ፡ መጽ: 1፡ገጽ 42
ሎጥን ነጻ ማውጣቱ፡ መጽ: 1፡ገጽ 40
አንቀጸ፡ ብፁዓን፡ መጽ: 2፡ ገጽ 254
እንደበትን መጠበቅ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 109
አክብሮትና ትሕትና፡ መጽ: 1፡ ገጽ 347
አወዳደቅ (የሰይጣን)፡ መጽ:1፡ገጽ 28
አውዶክስያ፡ መጽ: 2፡ ገጽ 335
አዳምና ሔዋን፡ መጽ: 1፡ ገጽ 33
አገልግሎት (የቤተ ክርስቲያን፡) መጽ: 2፡ ገጽ 321
አጋርና እስማኤል፡ መጽ: 1፡ ገጽ 41
ኤሴኒያውያን መጽ 3 ገጽ 158
ኢያሱ ወልደ ነዌ፡ መጽ: 2፡ ገጽ 280
ኤልሳዕ (ነቢዩ)፡ መጽ: 3፡ ገጽ 199
ኤልያስ (ነቢዩ)፡ መጽ1፡ ገጽ 140
ኤማሁስ፡ መጽ: 3፡ ገጽ 217
ኤጲስ ቆጶስ፡ መጽ: 2፡ ገጽ 137
እምነትና ተግባር፡ መጽ: 2፡ ገጽ
እምነትን በእግዚአብሔር ላይ ማድረግ፡ መጽ፡2 ገጽ 261
እረኞችና መላእክት፡ መጽ: 1፡ ገጽ 62
እስጢፋኖስ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 220
እውነትን መናገር፡ መጽ: 3፡ ገጽ 116
እግዚአብሔር በሾማቸው ገገርዎች ወይም ነሥታት አማካይነት መጽ: 1፡ ገጽ 116
እግዚአብሔር በፍጥረቱ ላይ ያለው ገገርነት መጽ: 1፡ ገጽ 114
እግዚአብሔር የማይለወጥና ጸሎት ተቀባይ ነው መጽ: 1፡ ገጽ 102
እግዚአብሔር በሾማቸው ሰዎች የሚካሄድ መንግሥት መጽ:1፡ገጽ 116
እግዚአብሔርን ማመስገን፡ መጽ፡ 2 ገጽ 189
አሪት ዘሌዋውያን፡ መጽ፡ 2፡ ገጽ 112
ከምሥራቅ የመጡ ጠቢባን፡ መጽ፡ 1፡ ገጽ 65
ከባለ ሥልጣን፡ ወይም ከአሠሪ ተጽዕኖ ... መጽ: 2፡ ገጽ 343
ከዘመድ፡ ከጓደኛ፡ ከወዳጅ ተጽዕኖ ... መጽ: 2፡ ገጽ 344
ከዓለማዊ ፍላጎት ተጽዕኖ ... መጽ: 2፡ ገጽ 345
ከፍትወት መጠበቅ፡ መጽ: 2፡ ገጽ 154
ክርክር፡ መጽ:3፡ ገጽ 305
ክፉ ሁናቴ ማየት፡ መጽ: 2: ገጽ 83፡153
ክፉ ሐሳብና ክፉ ምኞት፡ መጽ: 2፡ ገጽ 153
ክፉ መጻሕፍትን ማንበብ፡ መጽ: 2፡ ገጽ 85
ክፉ ትውስታ፡ መጽ: 2፡ ገጽ 154

www.ethiopianorthodox.org

ክፉ ነገርን መናገር፡ መጽ: 2፡ ገጽ 156
ክፉ ነገር መስማት፡ መጽ: 2፡ ገጽ 84
ክፉ አሉባልታ፡ መጽ: 2፡ ገጽ 86
ክፍለ ዓመት፡ መጽ: 3፡ ገጽ 16
ወደ ቤተ መቅደስ መወሰዱ (ጌታችን)፡ መጽ: 1፡ ገጽ 63
ወቀሳ (በጸሐፍትና በፈሪሳውያን ላይ)፡ መጽ: 1፡ ገጽ 307
ወደ ኃጢአት ከሚገፋፉ ሁኔታዎች መጠበቅ፡ መጽ: 2፡ ገጽ 83
ወግ: ( የአባቶች)፡ መጽ: 2፡ ገጽ 224
ዐይ፡ መጽ: 2፡ ገጽ 283
ዐመፀኛነት (የእስራኤል)፡ መጽ: 2፡ ገጽ 195
ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት፡ መጽ: 1 ገጽ 239
ዐሥራት መጽ: 2 ገጽ 327
ዐዋቂነት (የእግዚአብሔር)፡ መጽ: 1፡ ገጽ 121
ዓለማዊ ስጦታ፡ መጽ: 2፡ ገጽ 13
ዓካን መጽ: 2 ገጽ 283
ዔሳውና ያዕቆብ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 138
ዕርፈ መስቀል መጽ: 1፡ ገጽ 172
ዘለዓለማዊ ፍርድ፡ መጽ: 2፡ ገጽ 19
ዘጠኙ ቅዱሳን፡ መጽ: 3 ገጽ 162
ዜና መዋዕል (1ኛ)፡ መጽ: 3፡ ገጽ 73
ዜና መዋዕል (2ኛ)፡ መጽ: 3፡ ገጽ 74
የሃይማኖት ትምህርት፡ መጽ: 2፡ ገጽ 321
የሄሮድስ አሟሟት፡ መጽ: 2፡ ገጽ 40
የልደት (የነቢያት) ጾም: መጽ: 1 ገጽ 125
የሐዋርያት ጾም መጽ: 1፡ ገጽ 125
የሐዋርያት የያዕቆብ መልዕክት፡ መጽ: 3፡ ገጽ 83
የሐዋርያው ጳውሎስ የማስተማር ጉዞ፡ መጽ: 2፡ ገጽ 208
የሕፃናት ጥምቀት፡ መጽ: 3፡ ገጽ 12
የሥጋ መልበስና የመስቀል ምክንያት (በሰው በኩል) መጽ: 1፡ ገጽ 201
የሥጋ መልበስና የመስቀል ምክንያት (በእግዚአብሔር በኩል) መጽ: 1፡ ገጽ 203
የመንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ መውረድ መጽ: 1፡ ገጽ 49
የመንፈሳዊነትና የግብረገብነት ምንጮች መጽ 2፡ ገጽ 157
የመንፈሳውያን በዓላት አከባበር፡ መጽ: 3፡ ገጽ 15
የመከራከሪያ ጥቅሶችና መልሶቻቸው መጽ: 3፡ ገጽ 181
የመዋያየት ውጤት፡ መጽ: 2፡ ገጽ 251
የማስተማር ሥራውን መጀመሩ መጽ: 1፡ ገጽ 72
የማትያስ መመረጥ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 48
የምሥጢረ ቍርባን ምሥረታ፡ መጽ: 3፡ ገጽ 142
የምእመናን ሚና፡ መጽ: 2፡ ገጽ 326
የረቡዕና የዓርብ ቀኖች ጾም መጽ: 1፡ ገጽ 126
የሰባት ዲያቆናት መመረጥ መጽ: 1፡ ገጽ 219



የሳውል በክርስቶስ ማመን መጽ: 1፡ ገጽ 295
የባቢሎን ግንብ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 38
የቤተ ክርስቲያን መሥራች፡ መጽ: 1፡ ገጽ 250
የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን:-
ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 89
ሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 92
ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ የእልፍዮስ ልጅ፡ መጽ 1፡ ገጽ 94
ሐዋርያው ቅዱስ ታዴዎስ፡ መጽ 1፡ ገጽ 94
ቂርቆስና ኢየሉጣ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 94
ሐዋርያው በርተሎሜዎስ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 177
ሐዋርያው ፊልጶስ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 178
ቅዱስ ኤጲፋንዮስ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 178
ወንጌላዊው ማቴዎስ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 255
ወንጌላዊው ዮሐንስ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 256
ሐዋርያው ቶማስ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 328
ሐዋርያው ማትያስ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 329
ሰማዕቱ ጊዮርጊስ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 329
ሐዋርያው ያዕቆብ (የዘብዴዎስ ልጅ)፡ መጽ: 2፡ ገጽ
ሐዋርያው ስምዖን (ቀናኢ)፡ መጽ: 2፡ ገጽ 60
ቅዱስ እንጦንስ፡ መመጽ: 2፡ ገጽ 61
ወንጌላዊው ማርቆስ፡ መጽ: 2፡ ገጽ 138
ወንጌላዊው ሉቃስ፡ መጽ: 2፡ ገጽ 140
ቅዱስ ፍሬምናጦስ፡ መጽ: 2፡ ገጽ 141
ማርያም መግደላዊት፡ መጽ: 2፡ ገጽ 241
ቅዱስ ሙሴ ጸሊም፡ መጽ: 2፡ ገጽ 241
ተፍጻሜተ ሰማዕት ጴጥሮስ፡ መጽ: 2፡ ገጽ 327
ቅዱስ አትናቴዎስ፡ መስ: 2፡ ገጽ 329
ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፡ መጽ: 2፡ ገጽ 334
ቅዱስ ቴዎዶጦስ የዕንቄራ ኤ?ጳስ ቆጶስ መጽ: 2፡ ገጽ 142
ቅዱስ ሳዊሮስ የአንጾኪያ ኤጲስ ቆጶስ መጽ: 2፡ ገጽ 142
አባ: ሕርያቆስ ዘብሕንሳ መጽ: 2፡ ገጽ 144
ቅዱስ በርናባስ መጽ: 2፡ ገጽ 145
ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ መጽ: 2፡ ገጽ 240
ቅዱስ አቡሊዲስ መጽ: 2፡ ገጽ 242
ቅዱስ ዮሐንስ መጽ: 2፡ ገጽ 336
ቅዱስ ቴዎዶስዮስ መጽ: 2፡ ገጽ 337
ቅዱስ ድሜጥሮስ፡ መጽ: 3፡ ገጽ 51
ቅዱስ ጎርጎርዮስ (ነባቤ መለኮት)፡ መጽ: 3፡ ገጽ 52
ቅዱስ መርቆርዮስ፡ መጽ: 3፡ ገጽ 53
ቅዱስ ያሬድ፡ መጽ: 3፡ ገጽ 54
አቡነ ተክለ ሃይማኖት፡ መጽ: 3፡ ገጽ 55

www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ቄርሎስ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 108
ቀዱስ ዲዮስቆሮስ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 109
ቅዱስ ኤፍሬም፥ መጽ: 3፥ ገጽ 109
መጥምቁ ዮሐንስ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 160
ቅዱስ ጎርጎርዮስ (ገባሬ ተአምር)፥ መጽ: 3፥ ገጽ 161
ቅዱስ ጎርጎርዮስ (የባስልዮስ ወንድም) መጽ: 3፥ ገጽ 161
ዘጠኙ ቅዱሳን፥ መጽ: 3፥ ገጽ 162
ትልቁ ባስልዮስ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 227
የቤተ ክርስቲያን መከፋፈል፥ መጽ: 2 ገጽ 190
የቤተ ክርስቲያን ትርጉም፥ መጽ: 1 ገጽ 85
ምእመናን፥ መጽ: 1፥ ገጽ 85
የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፥ መጽ: 1፥ ገጽ 85
የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር፥ መጽ፥ 1፥ ገጽ 86
ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን፥ መጽ: 1፥ ገጽ 86
የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር፥ መጽ: 3፥ ገጽ 50
የቤተ ክርስቲያን ጸሎት ውጤት፥ መጽ:2፥ገጽ 39
የተራራው ላይ ስብከት፥ መጽ: 1፥ ገጽ 234
የተፈጥሮ ዝንባሌ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 175
የንግሥ በዓል፥ መጽ: 3፥ ገጽ 20
የኅሊና ምስክርነት፥ መጽ: 3፥ ገጽ 175
የአማኞች የኅብረት ኑሮ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 50
የአብርሃምና የሎጥ መለያየት መጽ: 1፥ ገጽ 40
የአብርሃም ሞት መጽ: 1፥ ገጽ 46
የአንድነትና የሦስትነት እምነት፥ መጽ: 3፥ ገጽ 118
የአይሁድ አለማመን፥ መጽ: 1፥ ገጽ 159
የአገልጋይ ግዳጅ፥ መጽ: 3 ገጽ 44
የእመቤታችን ድንግልና፥ መጽ: 2 ገጽ 100
የእስራኤል ሕዝብና የሚኖሩባት ምድር ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 114
የእስራኤላውያን የበረሓ ጉዞ፥ መጽ: 2፥ ገጽ 32
የእግዚአብሔር ህልውና፥ መጽ: 3፥ ገጽ 173
የእግዚአብሔር ሕጎች መጽ 2 ገጽ 91
የእግዚአብሔር መንግሥት፥ መጽ: 1፥ ገጽ 113
የእግዚአብሔር መጠሪያዎች፥ መጽ: 3፥ ገጽ 14
የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን፥ መጽ: 3፥ ገጽ 67
ከኖኅ ጋር፥ መጽ: 3፥ ገጽ 67
ከአብርሃም ጋር፥ መጽ: 1፥ ገጽ 41፥ መጽ: 3፥ ገጽ 68
ከይስሐቅ ጋር፥ መጽ: 3፥ ገጽ 68
ከያዕቆብ ጋር፥ መጽ: 3፥ ገጽ 68
ለፊንሐስ የገባለት፥ መጽ: 3፥ ገጽ 68
ከዳዊት ጋር፥ መጽ: 3፥ ገጽ 68
የእግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ታማኝነት፥ መጽ: 3፥ ገጽ 68



የእግዚአብሔር ብቸኛ [illegible] መጽ: [illegible]
የእግዚአብሔር አዳኝነት፡ መጽ: 1፡ ገጽ 271
የእግዚአብሔር ክብር፡ መጽ 3፡ ገጽ 10
በተአምራቱ፡ መጽ: 3፡ ገጽ 13
በሕማማቱና በሞቱ፡ መጽ: 3፡ ገጽ 13
በዳግም ምጽአቱ፡ መጽ: 3፡ ገጽ 13
በሰዎች ተግባር፡ መጽ: 3፡ ገጽ 13
አብ ወልድን፡ ወልድ አብን በማክበራቸው፡ መጽ: 3፡ገጽ 13
የእግዚአብሔር የክብር ጌታነት፡ መጽ: 3፡ ገጽ 13
እግዚአብሔርን የማክበር ግዴታ፡ መጽ3፡ ገጽ 14
የእግዚብሔር አዳኝነት፥ መጽ: 1፡ ገጽ 271
የእግዚብሔር ለክብሩ ቀናተኛነት፥ መጽ: 3፡ ገጽ 14
የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም፡ መጽ፡ ገጽ 198
የእግዚአብሔር ፍቅር፥ መጽ: 1፥ ገጽ 198
የክርስቲያናዊ ሕይወት መመሪያ ... መጽ 3፡ ገጽ 59
ጥላቻ ወይም ፍትወት ሳይሆን ንጹሕ ፍቅር መጽ: 3፡ ገጽ 59
ሰውን ማሳዘን ሳይሆን ሰውን ማጽናናት መጽ: 3፡ ገጽ 59
ቍጣ ሳይሆን ፈገግታ መጽ:3፡ ገጽ 60
ጭካኔ ሳይሆን ርኅራኄ መጽ: 3፡ ገጽ 60
ጥረት ማድረግ እንጂ አለመጨነቅ መጽ: 3፡ ገጽ 61
ንፉግነት ሳይሆን ለጋስነት መጽ: 3፡ ገጽ 61
ግዴለሽነት ሳይሆን ለሰው ስሜት መጠንቀቅ መጽ: 3፡ ገጽ 62
ራስ ወዳድነት ሳይሆን ለሌላውም ማሰብ መጽ: 3፡ ገጽ 62
ለጥያቄ መልስ መስጠት ካልሆነ ከክርክር መራቅ መጽ:3፡ገጽ 63
ከሐሜት መራቅ መጽ: 3፡ ገጽ 63
ግዴታን አክብሮ መወጣት መጽ: 3፡ ገጽ 63
የወልድ ሥጋ መልበስ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 200
የዘመን አቈጣጠር ስሌት፡ መጽ: 3፡ ገጽ 16
የዘብዴዎስ ልጆች እናት ልመና፡ መጽ: 3፡ ገጽ 90
የያዕቆብ ወደ ካራን ጉዞ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 140
የይሁዳ መልእክት፡ መጽ: 1፡ ገጽ 227
የይስሐቅና የርብቃ ጋብቻ መጽ: 1፡ ገጽ 45
የዮሴፍ ወንድሞች በግብጽ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 214
የዮፍታሔ ልጅ፡ መጽ: 1፡ ገጽ 109
የደቀ መዛሙርቱን እግር ማጠቡ፡ መጽ: 3፡ ገጽ 14
የደጉ ዛምራዊ ሳምራዊ ምሳሌ መጽ: 3፡ ገጽ 44
የዲና ወንድሞች የበቀል እርምጃ መጽ: 1፡ ገጽ 210
የዳስ በዓል፡ መጽ: 3፡ ገጽ 15
የጌታችን መያዝ፡ መጽ: 3፡ ገጽ 142
የጌታችን መፈተን፡ መጽ: 1፡ ገጽ 70
የጌታችን ተከታዮች፡ መጽ: 2፡ ገጽ 125
የጌታችን መለኮታዊ ክብር፡ መጽ:3፡ ገጽ 177
የጌታችን ጾም፡ መጽ: 1፡ ገጽ 124
የገሃድ ጾም፡ መጽ: 1፡ ገጽ 127



www.ethiopianorthodox.org

የፍልሰታ ጾም፥ መጽ: 1፥ ገጽ 126
የግብጽና የኢትዮጵያ ቤ/ክ ግንኙት ታሪክ (ባጭሩ) መጽ: 2፥ ገጽ 63
የግብጾች ዘመን አቈጣጠር፥ መጽ: 3፥ ገጽ 26
የፈርዖን ሕልም፥ መጽ: 1፥ ገጽ 213
የፈርዖን አገልጋዮች፥ መጽ: 1፥ ገጽ 212
የፍጥረቱ ሥነ ሥርዓታዊ አሠራር፥ መጽ: 3፥ ገጽ 173
የፍጥረትና የጊዜ ግንኙት፥ መጽ: 1፥ ገጽ 20
ይስሐቅ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 43
ይስሐቅና ርብቃ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 138
ይቅርታ ማድረግ እንጂ ቂም አለመያዝ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 263
ዮሐንስ መጥምቁ፥ መጽ:1፥ ገጽ 46
ዮሴፍ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 211
ዮናስ (ነቢይ)፥ መጽ: 1፥ ገጽ 294
ደብረ ታቦር፥ መጽ: 2፥ ገጽ 45
ደግና ክፉ ነገሮች በድምፅ ብልጫ አይወሰኑም፥ መጽ:2፥ ገጽ 89
ደግነት፥ መጽ: 1፥ ገጽ 265
ዲያቆናትና ኀላፊነታቸው፥ መጽ: 2፥ ገጽ 137
ድምፅ ብልጫ፥ መጽ: 2፥ ገጽ 89
ድንግልና (የእምቤታችን)፥ መጽ: 2፥ ገጽ 100
ገባያን፥ መጽ: 2 ገጽ 283
ጉባኤ (የኢየሩሳሌም)፥ መጽ: 2፥ ገጽ 115
ጊብዓ፥ መጽ: 2፥ ገጽ 283
ጊዜያዊ ስጦታዎች (የእግዚአብሔር) መጽ 2፥ ገጽ 13
ጋብቻ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 309
ጌልጌላ፥ መጽ: 2፥ ገጽ 282
ጌሪዚም ተራራ መጽ: 2፥ ገጽ 283
ጌታችን የሰጠው ተስፋ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 90
ጌታችን በቤተ መቅደስ (ከምሁራን ጋር)፥ መጽ: 1፥ ገጽ 67
ጌታችንና ሐዋርያው ጴጥሮስ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 220
ጌታችንና ኒቆዲሞስ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 155
ጌታችን የማስተማር ሥራውን መጀመሩ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 72
ጌታችን ከአብርሃም በፊት ነበር፥ መጽ: 1፥ገጽ 159
ጌቴሴማኒ፥ ጽ: 3፥ ገጽ 142
ግርዘት፥ መጽ: 1፥ ገጽ 42
ግብረገብነት፥ መጽ: 1፥ ገጽ 100
ግዴለሽነት፥ መጽ: 3 ገጽ 62
ግዴታ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 64
ጥመቀት (የጌታችን) መጽ: 1፥ ገጽ 68
ጲላጦስ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 187
ጳውሎስና መልእክቶቹ:-
ወደ ሮሜ ሰዎች፥ መጽ: 1፥ ገጽ 146
ወደ ገላትያ ሰዎች፥ መጽ: 1፥ ገጽ 149
ወደ ቲቶ፥ መጽ: 1፥ ገጽ
ወደ ፊልሞና፥ መጽ: 1፥ ገጽ 150




www.ethiopianorthodox.org


አንደኛ ቆሮ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 223
ሁለተኛ ቆሮ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 298
ወደ ኤፌሶን ሰዎች፥ መጽ: 2፥ ገጽ 212
ወደ ፊልጵ፥ መጽ: 2፥ ገጽ 290
ወደ ቆላስይስ መጽ: 2፥ ገጽ 293
አንደኛ ተሰ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 37
ሁለተኛ ተሰ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 38
ወደ ቲቶ የተላከ መጽ: ገጽ 150
አንደኛ ጢሞ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 81
ሁለተኛ ጢሞ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 82
ወደ ዕብራውያን ሰዎች፥ መጽ: 2፥ ገጽ 117
ጴጥሮስና ቆርኔሌዎስ፥ መጽ: 2፥ ገጽ 37
ጴጥሮስ በልዳና በኢዮጴ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 296
ጴጥሮስና ዮሐንስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት፥ መጽ: 1፥ ገጽ 52
ጴጥሮስ ጌታችንን መካዱ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 143
ጠቃሚ ካልሆነ ተጽዕኖ መጠንቀቅ፥ መጽ: 2፥ ገጽ 117
ጠባብዋ በር፥ መጽ: 2፥ ገጽ 304
ጠባዮች (የእግዚአብሔር)፥ መጽ: 2፥ ገጽ 164
ጠንቅቆ ማወቅ (መብትንና ግዴታን)፥ መጽ: 3፥ ገጽ 148
ጥምቀት (የጌታችን) ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 68
ጥበበ ሰሎሞን፥ መጽ: 3፥ ገጽ 81
ጥና (ጽና)፥ መጽ: 1፥ ገጽ 173
ጥያቄ (ስለ ጾም)፥ መጽ: 2፥ ገጽ 47
ጦቢት፥ መጽ: 1፥ ገጽ 292
ጭንቀት መጽ: 3፥ ገጽ 61
ጸሎተ ፍትሐት፥ መጽ: 3፥ ገጽ 69
ጸሎት፥ መጽ: 1፥ ገጽ 102
ጸሐፍት መጽ:3 ገጽ 158
ጸሕል መጽ: 1፥ ገጽ 171
ጽላቶች (ሁለቱ)፥ መጽ: 2፥ ገጽ 109
ጽዋ ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 171
ጾመ ነነዌ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 126
ጾም፥ መጽ: 1፥ ገጽ 123
ፈቃዱን መፈጸም፥ መጽ: 1፥ ገጽ 192
ፈተና ሲያጋጥም በእግዚአብሔር መታመን፥ መጽ: 3፥ ገጽ 171
ፈጣሪነት፥ መጽ: 1፥ ገጽ 18
ፈሪሳውያን መጽ: 3 ገጽ 157
ፈገግታ መጽ: 3፥ ገጽ 60
ፊልጶስ፥ መጽ: 1፥ ገጽ 221
ፍቅር፥ መጽ 2፥ ገጽ 222 መጽ: 3፥ ገጽ 59
ፍርሃት፥ መጽ: 2፥ ገጽ 155
ፍርድ ሸንጎ፥ መጽ: 3፥ ገጽ 142
ፍርድ (የሞት) በጌታችን ላይ፥ መጽ:3፥ ገጽ 144
ፍትወት፥ መጽ: 2፥ ገጽ 154

# የተነበቡ መጻሕፍት

## በአማርኛ የተነበቡ


ሃይማኖተ አበው፥ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ፥ 1967 ዓ.ም

መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት)፥ የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ፥ ንባቡ ከነትርጓሜው፥ አዲስ አበባ፥ 1948 ዓ.ም.

መሐሪ ትርፌ (ሊቀ፡ ሊቃውንት)፡ መጻሕፍት ሐዲሳት ሠለስቱ፥ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ፥ 1989 ዓ.ም.

መዝሙረ ዳዊት፡- ንባቡ ከነትርጓሜው፥ አዲስ አበባ፥ 1973 ዓ.ም.

መጽሐፈ ቅዳሴ (በግዕዝና በአማርኛ)፥ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ፥ 1974 ዓ.ም.

መጽሐፈ ምሥጢር ዘአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ።

ሥርዓተ ቅዳሴ፥ (የሕዝብ ተሰጥዎ)፥ ቼምበር ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ፥ 1979 ዓ.ም.

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፥ የኢትዮጵያ ታሪክ ኖብያ – አክሱም፥ 1951 ዓ.ም፥ አዲስ አበባ

ኀሩይ ወልደ ሥላሴ (ብላቴን ጌታ) ዋዜማ

ወንጌል ቅዱስ፥ ንባቡና ትርጓሜው፥ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፥ 1966 ዓ.ም.።

ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም፡ ንባቡ ከነትርጓሜው፥ ትንሣኤ አሳታሚ ድርጅት፥ አዲስ አበባ፥ 1983 ዓ.ም.

ዓሥራት ገብረ ማርያም፥ ትምህርተ መለኮት፥ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ፥ 1983 ዓ.ም.።

ዓሥራት ገብረ ማርያም፡ ፍኖተ ብርሃን፥ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ፥ 1986 ዓ.ም.

ዓሥራት ገብረማርያምና ገብረ ሕይወት መሐሪ የዘመን አቈጣጠር፥ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበበ፥ 1987 ዓ.ም.

የቤተ ክርስቲያን ጸሎት፥ (በስደት አገር በነበረች ጊዜ) ብርሃንና ሰላም ማተሚየ ቤት፥ አዲስ አበበ፥ 1936 ዓ.ም.።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፥ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፥ አዲስ አበባ፥ 1972 ዓ.ም.።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መጀመሪያው ፓትርያርክ፥ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ 1956 ዓ.ም.።

ገድለ ተክለ ሃይማኖት

ገድለ አረጋዊ

ገድለ ገሪማ

ጎርጎርዮስ (አቡነ)፡- የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፥ አዲስ አበባ፥ 1974 ዓ.ም.።

ጎርጎርዮስ (አቡነ)፥ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፥ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ፥ 1978 ዓ.ም.


## በዐረብኛ የተነበቡ


ሐቢብ ጊርጊስ፥ የኦርቶዶክስ አለት፥ ካይሮ እ.ኤ.አ 1948 ዓ.ም።

ሐፍዝ ዳውድ፥ ዲድስቅልያ፥ የሐዋርያት ትምህርት፥ ካይሮ እ.ኤ.አ. 1940 ዓ.ም.።

ሙሪስ ቴዎድሮስ (ዶክተር) ትምህርተ መለኮት፥ (1ኛ፥ 2ኛ፥ 3ኛ መጻሕፍት) ካይሮ፥ እ.ኤ.አ 1991 ዓ.ም.።

ሙሳ (አቡነ) የዮሐንስ ራእይ ትርጓሜ፥ ካይሮ፥ እ.ኤ.አ. 1993 ዓ.ም።

ሚና ዮሐና (ቄስ)፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች መልስ፥ ካይሮ፥ እ.ኤ.አ. 1940 ዓ.ም.።

ሚካኤል ሚና (ቆሞስ)፡ የግብጽ አርቶዶክስ ቤ/ክ ትምህርተ መለኮት፥ (1ኛ 2ኛ እና 3ኛ መጻሕፍት)

ቄርሎስ፥ (ዘገዳመ፡ እንጦንስ)፥ የሲኖዶሶች ዘመን፡ ካሮ፥ እ.ኤ.አ፥ 1952 ዓ.ም።

የሃይማኖት መማሪያ (ለ9ኛ፥ ለ10ኛ፥ ለ11ኛና ለ12ኛ ክፍሎች፥ እ.ኤ.አ. 1994 ዓ.ም.

የወንጌል ትርጓሜ፥ (አራቱ ወንጌሎች ካይሮ፥ እ.ኤ.አ. 1989 ዓ.ም።

የጽዮን መጽሔት ባለቤት፥ በማስረጃዎች የጎሊና ብርሃን፥ ካይሮ፥ እ.ኤ.አ 1935 ዓ.ም።

ዮስጦስ ኤልድዌይሪ፥ አጭር የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፡ ካይሮ፥ እ.ኤ.አ. 1949 ዓ.ም.።

ጂብራኤል ሪፉኤሊና ዐብዱልፋዲ አልቃሕራኒ፥ ሐዋርያዊው አትናቴዎስ፥ ካይሮ፥ 1949 ዓ.ም.።

ፍትሐ ነገሥት፥ የዓሳል ልጅ እንዳሰባሰበው፥ ካይር፡ እ.ኤ.አ በ1990 የታተመ።


## በእንግሊዝኛ የተነበቡ


(The) Bethany Parallel Commentary on the Old Testament, Bethany House Publishers, 1985. U.S.A.

(The) Bethany Parallel Commentary on the New Testament, Bethany House Publishers, 1983. U.S.A.

Bible Readings for the Home, Review and Herald Publishing Assn, Washington, D.C. 1951.

Clow W.M (D.D.) Rev. The Bible Readers Encyclopedia and Concordance, Collins' Clear - Type Press, U.K.

Concordia Self- Study Bible, New International erasion, Concordia Publishing House, U.S.A, 1986

Davidson (Prof) The New Bible Commentary EERD- MANS Publishing Co., Micluigan, 1963.

Development of the Christian Church, Pacific Press Publishing Association, U.S.A., 1952

Donald Attwater, A dictionary of Saints, 1965, Great Britan.

(The) EERDMANS Bible Dictionary, EERDMANS Publishing Company, Michigan, 1987

Harper's Bible Dictionary, Harper & Row Publishers, U.S.A., 1985.

(The) Harper Collins Study Bible, New Revised Standard Version, Harper Collins Publishers, U.S.A., 1985.

(The) Oriental Orthodox Churches Addis Ababa Conference, Artistic Printers, Addis Ababa, 1965.

Reasoning from the Scriptures, International Bible Students Association, U.S.A, 1985.

Schuster (Dr.) Illustrated Bible History, U.S.A., 1889.

Shenouda III (H.H.Pope) Comparative Theology, Coptic Orthodox Publishers Association, London, 1988.

Yolande Mara, The Church of Ethiopia, Asmara Publisher It Palaeographic, 1972.




www.ethiopianorthodox.org